አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀግብር

የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ውጤትን ለማጎልበት እና ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ያለው አስተዋፆ፤ በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ 9ኛ ክፍል ሶማልኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች ተተኳሪነት

በእሱባለው ወልደገብርኤል

አዲስ አበባ

ሰኔ 2010 ዓ.ም

የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ውጤትን ለማጎልበት እና ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ያለው አስተዋፆ፤ በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ 9ኛ ክፍል ሶማልኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች ተተኳሪነት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀግብር

በእሱባለው ወልደገብርኤል

አማካሪ

ዶ/ር ግርማ ወሰኔ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)

ተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን በማስተማር ለተባለው የ “PhD” ትምህርት መርሀግብር ማሟያነት የቀረበ ዋና ጥናት

አዲስ አበባ

ሰኔ 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀግብር

የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ውጤትን ለማጎልበት እና ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ያለው አስተዋፆ፤ በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ 9ኛ ክፍል ሶማልኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የፍልስፍና ዶክትሬት ድግሪ ማሟያ በእሱባለው ወልደገብርኤል ባንጫሬ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል።

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ_____ ፊርማ_____ ቀን_____

የውጭ ፈታኝ_____ ፊርማ_____ ቀን_____

የውስጥ ፈታኝ_____ ፊርማ_____ ቀን_____

ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀግብር ተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን በማስተማር ለተባለው የ “PhD” ትምህርት መርሀግብር የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር (Explicit reading strategy instruction) አንብቦ የመረዳት ውጤትን ለማጎልበት እና ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ያለው አስተዋፆ፤ በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ 9ኛ ክፍል ሶማልኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች ተተኳሪነት በሚል ርዕስ ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ዋና ጥናት ነው።

እኔ አቶ እሱባለው ወልደገብርኤል ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ ራሴ የሰራሁት፣ ከዚህ ቀደም በማንም አካል ያልተሰራ ወጥ ስራ መሆኑ ፍፁም እውነት ነው። ጥናታዊ ፅሁፉን በምሰራበት ወቅት ሀሳቤን ለማጠናከር የተለያዩ ፅሁፎች አንብቤያለሁ። ሀሳብ ለማጎልበት የተጠቀምኩባቸውን ፅሁፎች ምንጫቸውን በመጥቀስም በፈቃዴ ተገቢ ክብር ሰጥቻለሁ። ይህ የማረጋገጫ ቃሌ እውነት ስለመሆኑ በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ የመብት ባለቤት ነው።

የአቅራቢው ሙሉ ስም _____

ፊርማ_____

ቀን_____

አዲስ አበባ

ሰኔ 2010 ዓ.ም

ምስጋና

የዚህን ጥናታዊ ፅሁፍ ርዕስ በማስፀደቅ እና ትልመጥናት በማዘጋጀት እስከአቅርቦት ባለ ሂደት አብረውኝ የነበሩት፣ እንደአባት እና ልጅ በመስማማት በተገኘው ሰዓት እና ቦታ ሁሉ በትጋት በመነጋገር፣ በነፃነት በመከራከር እና በመግባባት (ልዩነት ቢኖርም) ብዙ ሀሳብ እንዳጠራቅም የረዱኝ አሁን ከዚህ አለም እና ከአካዳሚ አምድ የተለዩት የመጀመሪያ አማካሪዬ ዶ/ር ገሰሰ ታደሰ ስለጥልቅ እውቀታቸው፣ አስተዋይነታቸው እና በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ልቦና ስለማይጠፋው ገፅታቸው ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ መታሰቢያ ይሁንልኝ።

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከተጀመረ በኋላ በትምህርት ክፍሉ ትጋት እና በእሳቸው ሙሉ ፈቃደኝነት ዋና አማካሪ ሆነው ከተመደቡበት ጊዜ ጀምሮ በመወያየት፣ በመመካከር እና በመግባባት ጥናታዊ ፅሁፉ ለዚህ ደረጃ አንዲበቃ ሙያዊ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለአማካሪዬ ዶ/ር ግርማ ወሰኔ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን እና አክብሮቴን አቀርባለሁ።

በ “PhD” የትምህርት መርሀግብር ያስተማራችሁኝ፣ በምርምር ስራ ወቅት በየምእራፉ የፈተናችሁኝ፣ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በርታ በማለት ያበረታታችሁኝ መምህራን ሁሉ እኔ የደረስኩበት ይህ ደረጃ የእናንተ ሙያዊ ክብር መገለጫ ነውና በትክክል ክብር ይገባችኋል። በዚህ የትምህርት ቆይታዬ በተለይ ስም ጠርቼ ማመስገን የሚገባኝ መምህራን አሉ። እነሱም ፕሮፌሰር ባዬ ይማም፣ ዶ/ር ጌታቸው እንዳላማው፣ ዶ/ር ጌታሁን አማረ፣ ዶ/ር ብርሃኑ ቦጋለ፣ ዶ/ር ኑሩ መሀመድ፣ ዶ/ር ታምሬ አንዱአለም፣ ዶ/ር መኮንን ዲሳሳ፣ ዶ/ር ሙሉሰው አስራቴ፣ ጋሼ ደረጀ ገብሬ፣ አቶ አክሊሉ ለማ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)፣ አቶ ዘሪሁን አስፋው (ተባባሪ ፕሮፌሰር) እና አቶ ሞላ ማሩ ለእናንተ አድናቆት የታከለበት ምስጋና አቀርባለሁ። በተለይ ፕሮፌሰር ባዬ ይማም፣ ዶ/ር ጌታቸው እንዳላማው፣ ዶ/ር ጌታሁን አማረ እና ዶ/ር ብርሃኑ ቦጋለ ወደፊት በስራ ስምሪቴም ሞዴሎቼ ናቸው። እንዲሁም ወ/ሮ ሰብለ በቀለ (ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሪጅስትራር ቢሮ)፣ ዶ/ር አብነት ዮሀንስ፣ ዶ/ር አበበ መርድ፣ አቶ ትንግርቱ ገብረፃድቅ፣ አቶ ለታሪክ ተሾመ እና አቶ ደርብ ጌታቸው (ከጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ)፣ መምህርት ታጋይ ወጋየሁ (በጥናታዊ ፅሁፉ ሂደት የተሳተፉ መምህርት) እንዲሁም የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ የስራ ባልደረቦቼ በሙሉ ለሰጣችሁኝ ድጋፍ እና ማበረታቻ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ ።

በትምህርት ቆይታችን አብረን የተጋን የክፍል ጓደኞቼ እና ሌሎችም የትምህርት አጋሮቼ ብዙ ለፍተን ለዚህ ክብር የበቃነው በፍፁም መከባበር እና ፍቅር በመሆኑ ከልብ አመሰግናለሁ። በተለይ ለልብ ጓደኛዬ ዶ/ር ዘላለም ጌታቸው ልዩ አክብሮት አለኝ።

በትምህርት ሂደት እና በምርምር ስራ ወቅት የተለያዩ ብዛት ያላቸውን ፅሁፎች ማንበብ ግዴታ ነው። እኛም ደረቅ እና እርጥቡን ቅጂ በማንበብ ሀሳብ ለማግኘት ብዙ ጥረናል። በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ ሀሳብ ለማዳበር የተጠቀምኩባቸውን ፅሁፎች የፃፋችሁ

እውቀትን ለማስተላለፍ፣ ለምርምር ስራ እና ለማንበብ ተግባር በተለያየ መንገድ ፅሁፍ ያዘጋጃችሁ በሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ ያላችሁ ምሁራን ሁሉ ከልብ የመነጨ አክብሮቴን እና አድናቆቴን እገልፃለሁ። እንዲህ ለውን መልካም ስራ እኔም መስራት እመኛለሁ።

ራሴን በትምህርት ለማጎልበት ያለኝን ፍላጎት በማስተዋል እና የትምህርት እድል በመስጠት እንድማር የፈቀደልኝን ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ አመሰግናለሁ። በትምህርት የሚገኝ እውቀት ዘላቂ አእምሯዊ ሀብት በመሆኑ መጪውን ዘመን በቅንነት በማገልገል ውለታዬን እከፍላለሁ። የመጀመሪያ፣ ሁለተኛ ዲግሪዬን እና አሁን በ "ዶክትሬት" ማእረግ ኮትኩተሽ፣ አሳድገሽ ለክብር ያበቃሽኝ አንጋፋዋ የእውቀት ምንጭ **አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ** ከልብ ከልብ ከልብ በመነጨ አክብሮት አመሰግንሻለሁ። ለውለታሽ የሚመጥን ምን አደርግ ይሆን? ወደፊት በአለም ስምሽ የተጠራ የአካዳሚ እና የምርምር የልህቀት ማእከል እንድትሆኚ የዘወትር ምኞቴ ነው። በተጨማሪ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ በምርምር ስራዬ ወቅት የገንዘብ ድጋፍ ያደረጉልኝ ተጠቃሽ የትምህርት ተቋማት በመሆናቸው ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

በምርምር ስራው ወቅት መረጃ እንዳሰባስብ የፈቀዱልኝ በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ ጅግጅጋ መሰናዶ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ጅግጅጋ ሼክ አብዱሰላም መሰናዶ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን፣ ዩኒት መሪዎች፣ መምህራን እና ተማሪዎች ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በተጨማሪ የሶማሌ ክልል ኮሚኒኬሽን ኤጀንሲን አመሰግናለሁ።

ትምህርቴን በምከታተልበት ወቅት ብዙ ድጋፍ ያደረግሽልኝ፣ አይዞህ በርታ በማለት ያበረታታሽኝ ውድ ባለቤቴ ወ/ሮ ገነት አየለ መልካም ሰው በመሆንሽ እጅግ አድርጌ ከልቤ አመሰግንሻለሁ። ልጆቼ አንዱአምላክ፣ ሙሉቀን እና ቃልኪዳን እሱባለው እናቴ ወ/ሮ ድንበሬ ጥሩነህ፣ ወንድሜ አቶ በለጠ ከተማ፣ ወንድወሰን ሙላት፣ እህቶቼ ኮሎኔል ዘውዲቱ ከተማ፣ ወ/ሮ ትእግስት ከተማ እና ወ/ሮ የውብዳር ከተማ ከልጆቻቸው እና ከባለቤቶቻቸው ጋር፣ በአባቴ በኩል ያገኘሁኋችሁ ወንድሞቼ እና እህቶቼ እንዲሁም መላው ቤተሰቦቼ ለሰጣችሁኝ ፍቅር እና የማበረታቻ ሀሳብ ከልብ አመሰግናለሁ። ።

ከተወሰነ አመት በፊት ከህይወት ያለፍሽው የቀድሞ ባለቤቴ እና የልጆቼ እናት ወ/ሮ በልዩ መለሰ ከውስጤ ያልጠፋው አይዞህ ባይነትሽ በሀዘን ምክንያት ተስፋ እንዳልቆርጥ ረድቶኛል እና አምላክ ነፍስሽን በገነት ያኑረው።

በጥናቱ የተለያዩ ምእራፎች የጥናቱን የተወሰነ ክፍል በመፃፍ እና በጥንቃቄ አትሞ በማውጣት የተባበሩኝ የፅሀፊት ባለሙያዎች ወ/ሮ ወይንሽት ከበደ፣ሔለን ተስፋዬ እና አይናለም መንገሻ ለጥሩ ችሎታቸው እና ትእግስታቸው ከልብ አመሰግናለሁ።

አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ውጤትን ለማጎልበት እና ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ያለው አስተዋፆ ምን እንደሚመስል በጥልቀት መመርመር ላይ ያነጣጠረ ነው። ጥናቱ በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ 9ኛ ክፍል ሶማልኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎችን ተተኳሪ አድርጓል።

ጥናቱ የተነሳበትን አላማ ለማሳካት ቅድመ እና ድህረልምምድ ፈተና በመስጠት በተገኘው አሀዛዊ መረጃ ላይ ተመስርቶ ሰፊ ትንታኔ ለማቅረብ ያስቻለውን ከፊል ፍትነታዊ (Quasi Experiment) የምርምር ንድፍ ተከትሏል። በጥናቱ ሁለት የሙከራ ቡድኖች (ሙከራ ቡድን አንድ 73 ተማሪዎች፣ ሙከራ ቡድን ሁለት 69 ተማሪዎች) እና አንድ ጥብቅ ቡድን (66 ተማሪዎች) በአጠቃላይ 208 ተማሪዎች ተሳትፈዋል። ለሙከራ ቡድን አንድ በአማርኛ ለሙከራ ቡድን ሁለት ደግሞ በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት ትምህርት በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ ለአስራሁለት ሳምንት (ለ16 ሰዓት) ተሰጥቷል (የአንድ ክፍለጊዜ ርዝማኔ 40 ደቂቃ)። ጥብቅ ቡድኑ የማንበብ ብልሃትን የተመለከተ ፍንጭ እንዳያገኝ በማሰብ በተለመደው የትምህርት አሰጣጥ ትምህርቱን ተከታትሏል። በጥናቱ መረጃ ለማሰባሰብ አገልግሎት ላይ የዋለው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳርያ አንብቦ የመረዳት ብቃት መለክያ ፈተና፣ የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ እና በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ የመናገር ቃለመጠይቅ ናቸው። የጥናቱ አቅራቢ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን ለተማሪዎች ለማቅረብ መምህር በነፃ ማሰብ (እየተገበሩ ማሰብ)፣ አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ እና ትግግዝ ሞዴሎችን አቀናጅቶ ተጠቅሟል።

በጥናቱ ግኝት የተንፀባረቀው የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር ተለምዷዊ ከሆነው የትምህርት አቀራረብ በተሻለ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ከቅድመልምምድ ጉልህ በሆነ መልኩ (<0.05) ድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀማቸው ጎልብቷል። በጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን በመከታተላቸው በተለይ መተንበይ፣ የምንባቡን ዋና ሀሳብ በፍጥነት ማግኘት፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ደግሞ (ደጋግሞ) ማንበብ፣ አውዳዊ ፍቺ መጠቀም፣ ጭምቀሀሳብ መፃፍ፣ ብልሃቶችን ከሶማልኛ ወደአማርኛ/ከአማርኛ ወደሶማልኛ እያሸጋገሩ መጠቀም፣ አንብቦ መረዳትን እና ራስን መቆጣጠር፣ መገምገም፣ የቀደመ እውቀትን መጠቀም፣ ጥያቄ መጠየቅ እና ከተማሪዎች ጋር መተባበር ብልሃቶችን የበለጠ አጎልብተዋል። የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ፅሁፍን ለማንበብ ማቀድ፣ የቃላትን ፍቺ መገመት፣ ከምንባቡ ውስጥ መረጃ ፈልፍሎ በማውጣት ምክንያት ላይ የተመሰረተ ድምዳሜ ላይ መድረስ እና በአእምሮ ምስል መፍጠር ላይ ኢ-ጉልህ የሆነ ውጤት (>0.05) እንዳስመዘገቡ ግኝቱ አመላክቷል። ይህ ውጤት ከአምስቱ ንኡሳን የማንበብ ብልሃት አይነቶች አንፃር ሲታይ በአማርኛ አእምሮታዊ እና ልእለአእምሮታዊ በሶማልኛ ደግሞ አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃቶችን የበለጠ እንዳጎለበቱ

የጥናቱ ግኝት አንፀባርቋል። በጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት አጠቃቀማቸው በመጎልበቱ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው ተሻሽሏል። ተማሪዎቹ በተለይ ከአማርኛ ቋንቋ በተሻለ በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው ጎልብቶ ታይቷል። በዚህ መሰረት የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና አንብቦ የመረዳት ብቃት መካከል ጉልህ አዎንታዊ ዝምድና መኖሩን ግኝቱ አመላክቷል። የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ በመማራቸው ከሶማልኛ ወደአማርኛ ቋንቋ አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃቶችን፣ ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ደግሞ አእምሮታዊ እና ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃቶችን የበለጠ እያሸጋገሩ በመጠቀማቸው በየቋንቋው አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው እንደተሻሻለ ጥናቱ አመላክቷል። በጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎቹ የማንበብ ብልሃቶችን ከአማርኛ ወደሶማልኛ እያሸጋገሩ ከመጠቀም ይልቅ ከሶማልኛ ወደአማርኛ ቋንቋ እያሸጋገሩ የመጠቀም ሁኔታቸው የበለጠ ጎልቶ ታይቷል። በአጠቃላይ በጥናቱ ግኝት የተንፀባረቀው የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር የማንበብ ብልሃት አጠቃቀምን፣ አንብቦ የመረዳት ብቃትን፣ ከአንድ አዲስ ሁኔታ ወደሌላ አዲስ ሁኔታ ወይም ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ የማንበብ ብልሃትን ውጤታማ በሆነ መንገድ በማሸጋገር መጠቀም እንዲሁም ሽግግሮሹ አንብቦ የመረዳት ብቃት እንዲያጎለብት አስተዋፆ እንዳለው የጥናቱ ግኝት አንፀባርቋል።

ማውጫ

ዝርዝር ገጽ

ምስጋና i

አጠቃሎ iii

ማውጫ v

የሰንጠረዥ ማውጫ ix

የምስል ማውጫ xii

ምእራፍ አንድ 1

መግቢያ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች 9

1.3 የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች 12

1.4 የጥናቱ መላምቶች 13

1.5 የጥናቱ አላማ 14

1.6 የጥናቱ ጠቀሜታ 15

1.7 የጥናቱ ገደብ 16

1.8 የጥናቱ አውድ 18

1.9 የጥናቱ ውስንነት (ችግር) 20

1.10 የቁልፍ ፅንሰሀሳቦች ብያኔዎች 22

ምዕራፍ ሁለት 23

የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት 23

2.1. ማንበብ እና አንብቦ መረዳት 23

2.1.1 ማንበብ 23

2.1.2 አንብቦ መረዳት 26

2.2 የማንበብ ሒደት ሞዴሎች 28

2.2.1 የታች ላይ ማንበብ ሒደት ሞዴል 28

2.2.2 የላይ ታች ማንበብ ሒደት ሞዴል 30

2.2.3 መስተጋብራዊ የማንበብ ሒደት ሞዴል 31

2.3. የመጀመሪያ ቋንቋ (ቋ1) እና ሁለተኛ ቋንቋ (ቋ2) ማንበብ ግንኙነት 32

2.4 የማንበብ ብልሃት ምንነት እና መገለጫዎቹ 39
2.4.1 የማንበብ ብልሃት ምንነት 39
2.4.2 በማንበብ ብልሃት እና በማንበብ ክሂል መካከል ያለ ተመሳስሎ እና ልዩነት 42
2.4.3 የማንበብ ብልሃት ጠቀሜታ 44
2.4.4 የማንበብ ብልሃት አከፋፈል 45
2.4.4.1 አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት 49
2.4.4.2 ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት 50
2.4.4.3 ትውስታ የማንበብ ብልሃት 53
2.4.4.4 ማካካስ የማንበብ ብልሃት 54
2.4.4.5 ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት 54
2.5 ጠንካራና ደካማ አንባቢዎች 54
2.6 የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ 56
2.6.1 የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ምንነት እና መገለጫዎች 56
2.6.2 ሽግግር የሚያደርጉ ጉዳዮች እና መገለጫዎች 58
2.7 የማንበብ ብልሃትን መርጦ በመጠቀም ወቅት ያሉ እንቅፋቶች 65
2.8 የማንበብ ብልሃትን ማስተማር 67
2.8.1 ብልሃቶችን ከአውድ ነጥሎ ማስተማር በተቃርኖ አቀናጅቶ ማስተማር 68
2.8.2 በቀጥታ (በግልፅ) ማስተማር በተቃርኖ ግልፅ ባልሆነ መንገድ ማስተማር 69
2.9 የጥናቱ ትውረታዊ ማዕቀፍ 74
2.9.1 ግንባታዊነት 75
2.9.1.1 አእምሮታዊ ግንባታዊነት 78
2.9.1.2 ማህበራዊ ግንባታዊነት 84
2.10 የጥናቱ ሞዴል 88
2.10.1 መምህር በነፃ ማሰብ (እየተገበሩ ማሰብ) ሞዴል 88
2.10.2 አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ ሞዴል 89
2.10.3 ትግግዝ ሞዴል (Scaffolding) 93

ምዕራፍ ሶስት 99
የጥናቱ ስነዘዴ.....99
3.1 የጥናቱ ንድፍ.....99
3.2 የጥናቱ ዘዴ 100
3.2.1 የጥናቱ የመረጃ ምንጭ 100
3.2.2 የናሙና አወሳሰድ.....101
3.2.3 የጥናቱ የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች.....105
3.2.3.1 አንብቦ የመረዳት ብቃት መለክያ ፈተና.....105
3.2.3.2 የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ.....107
3.2.3.3 በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ የመናገር ቃለ መጠይቅ.....109
3.2.4 የመረጃ መሰብሰብያ መሳርያዎች ትክክለኛነት እና አስተማማኝት 110
3.2.4.1. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ትክክለኛነት 110
3.2.4.2. የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች አስተማማኝነት 112
3.2.5 የፈተናዎች የውጤት ስርጭት ወጥነት (ጤናማነት).....117
3.2.5.1 አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች ውጤት የውጤት ስርጭት ወጥነት ...117
3.2.5.2 የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቆች የውጤት ስርጭት ወጥነት 119
3.2.6 በጥናቱ ለትምህርት የቀረቡ የማንበብ ብልሃቶች አመራረጥ 120
3.2.7 በጥናቱ የማስተማሪያ ፅሁፎች አዘገጃጀት 121
3.2.8 የማንበብ ብልሃት ትምህርት አሰጣጥ.....123
3.2.9 የጥናቱ አሰራር እና የመረጃ አሰባሰብ ቅደም ተከተል 126
3.2.10 የመረጃ አተናተን.....128
ምዕራፍአራት 131
የናሙና ጥናት (Pilot Study).....131
4.1 የናሙና ጥናቱ አካሄድ.....131
4.2 በናሙና ጥናቱ የተገኙ ተሞክሮዎች 132
ምእራፍ አምስት.....135
ዋናው ጥናት (Main Study) 135
5.1 የጥናቱ መረጃ ትንተና (የተገኘ ውጤት).....135

5.1.1 በፈተና እና በፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና 135
5.1.2 በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ጊዜ አስታውሶ መናገር ቃለመጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና 173
5.2 የውጤት ማብራርያ (ትርጓሜ) 186
ምእራፍ ስድስት 199
ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳብ 199
6.1 ማጠቃለያ 199
6.2 የመፍትሄ ሀሳብ 201
ዋቢ ፅሁፎች 205
አባሪዎች (Appendix) 225

የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ አንድ፡- በጥናቱ ትኩረት የተሰጠባቸው የማንበብ ብልሃቶች ዝርዝር 17

ሰንጠረዥ ሁለት፡- በአዕምሯዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ ሞዴል የማንበብ ብልሃት ትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተልን የሚያሳ 92

ሰንጠረዥ *ሶስት*፡-ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ቅድመልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም 136

ሰንጠረዝ አራት፡-ሙከራ ቡድን አንድ ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤን በዝርዝ የሚያሳይ..138

ሰንጠረዝ አምስት፡-ሙከራ ቡድን ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት ግንዛቤ እና አጠቃቀማቸውን በዝርዝር የሚያሳይ 139

ሰንጠረዥ *ስድስት*፡-ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም.....142

ሰንጠረዥ *ሰባት*፡- ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም የሚያሳይ.....144

ሰንጠረዥ *ስምንት*፡- ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ትውስታ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም የሚያሳይ 146

ሰንጠረዥ *ዘጠኝ*፡- ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ማካካስ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም.....148

ሰንጠረዥ *አስር*፡- ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም.....150

ሰንጠረዥ *አስራአንድ*፡- ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ሁሉንም የማንበብ ብልሃቶች አጠቃቀም የሚያሳይ 152

ሰንጠረዥ አስራሁለት፡- ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ድህረልምምድ በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀማቸው ንፅፅር.....153

ሰንጠረዥ አስራሶስት ፡- ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ድህረልምምድ በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀማቸው ንፅፅር 154

ሰንጠረዥ አስራአራት፡- ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ ቋንቋ ቅድመ እና ድህረልምምድ የቀረበውን ምንባብ አንብበው ለመረዳት የተጠቀሙበትን የማንበብ ብልሃት የሚያሳይ 156

ሰንጠረዥ አስራአምስት፡- ሙከራ ቡድን አንድ፣ ሙከራ ቡድን ሁለት እና ጥብቅ ቡድን ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸውን የሚያሳይ.....159

ሰንጠረዥ አስራስድስት፡- ሙከራ ቡድን አንድ፣ ሙከራ ቡድን ሁለት እና ጥብቅ ቡድን ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸውን በንፅፅር የሚያሳይ 161

ሰንጠረዥ አስራሰባት፡- ሙከራ ቡድን አንድ፣ሙከራ ቡድን ሁለት እና ጥብቅ ቡድን ድህረልምምድ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃት ልዩነትን የሚያሳይ 163

ሰንጠረዥ አስራስምንት፡- ሙከራ ቡድን አንድ፣ሙከራ ቡድን ሁለት እና ጥብቅ ቡድን ድህረልምምድ በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃት ልዩነትን የሚያሳይ 164

ሰንጠረዥ አስራዘጠኝ፡- ሙከራ ቡድን አንድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር ያለውን ዝምድና የሚያሳይ 166

ሰንጠረዥ ሃያ ፡- ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር ያለውን ዝምድና የሚያሳይ 169

ሰኝጠረዥ ሃያ አንድ፡- ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት የማንበብ ብልሃቶችን ከአማርኛ ወደሶማልኛ እና ከሶማልኛ ወደአማርኛ ቋንቋ እያሸጋገሩ የመጠቀም ሁኔታቸውን የሚያሳይ 172

ሰንጠረዥ ሃይ ሁለት፡- በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ የመናገር ቃለመጠይቅ ሙከራ ቡድን አንድ በሶማልኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ አንብበው የሰጡት ምላሽ.....174

ሰንጠረዥ ሃያ ሶስት ፡- በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ የመናገር ቃለመጠይቅ ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ አንብበው የሰጡት ምላሽ.....174

ሰንጠረዥ ሃያ አራት፡- ሙከራ ቡድን አንድ በሶማልኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ አንብበው በመረዳት ሂደት ያጋጠማቸውን ችግር ለማስወገድ ያደረጉትን ጥረት የሚሳይ.....175

ሰንጠረዥ ሃያ አምስት፡- ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ አንብበው በመረዳት ሂደት ያጋጠማቸውን ችግር ለማስወገድ ያደረጉትን ጥረት የሚሳይ.....176

ሰንጠረዥ ሃያ ስድስት-፡- ሙከራ ቡድን አንድ የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ የመጠቀም ግንዛቤያቸውን የሚያሳይ.....178

ሰንጠረዥ ሃያ ሰባት-፡- ሙከራ ቡድን ሁለት የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ የመጠቀም ግንዛቤያቸውን የሚያሳይ.....178

ሰንጠረዥ ሃያ ስምንት፡- ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ድህረልምምድ ለማንበብ ተግባር የቀረቡ ምንባቦችን አንብቦ ለመረዳት ከአንዱ ቋንቋ ወደሌላው ቋንቋ እያሸጋገሩ የተጠቀሙባቸውን የማንበብ ብልሃቶችን የሚያሳይ 181

ሰንጠረዥ ሃያ ዘጠኝ፡- ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ድግግሞሽን የሚያሳይ.....183

ሰንጠረዥ ሰላሳ ፡- ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳታቸው መጎልበት አለመጎልበቱን የሚያሳይ. 185

የምስል ማውጫ

ምስል አንድ፡- የማንበብ ብልሃትን ቅንጅት የሚያሳይ 48

ምስል ሁለት ፡-ንጥጥል ውስጠ ብቃት 61

ምስል ሶስት፡-የጋራ ውስጠ ብቃት ሞዴል (ባለአንድ ስልት).....61

ምስል አራት፡- የቋንቋ ርስበርስ ግንኙነትን የሚያሳይ የጋራ ውስጠ ብቃት ሞድል (ባለሁለት ተያያዥ የበረዶ ክምር) 63

ምስል አምስት፡- አእምሯዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ ሞዴል 91

ምስል ስድስት፡- መምህር በነፃ ማሰብ፣ አእምሯዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ እና ትግግዝ ሞዴሎችን በማቀናጀት የቀረበ.....95

ምስል ሰባት፡- ለትምህርት የተመረጡ የማንበብ ብልሃቶችን በማስተማር መነሻ እና መድረሻውን (ለውጡን) የሚያመላክት 97

ምእራፍ አንድ

መግቢያ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ውጤትን ለማጎልበት እና ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ያለው አስተዋፆ ምን እንደሚመስል በጥልቀት መመርመር ላይ ያተኮረ ነው። ጥናቱ በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ 9ኛ ክፍል ሶማልኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎችን ተተኳሪ አድርጓል። በጥናቱ የተነሳውን ይህን ምርምራዊ ሀሳብ ከግብ ለማድረስ እንዲያስችል ጥናታዊ ፅሁፉ በዚህ ምእራፍ ስር ያካተታቸው ጉዳዮች የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ፣ የጥናቱ መላምት፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ገደብ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ አውድ እና የቃላት እና የሀረጋት (ስያሜዎች) ተግባራዊ ግላዌ ናቸው።

1.1 የጥናቱ ዳራ

ቋንቋን መማር ማስተማር ባለፉት ዘመናት ከፍተኛ ለውጥ የተካሄደበት እና አዳዲስ አስተሳሰቦች የተንፀባረቀበት በየጊዜው የሚለዋወጥ፣ የሚያድግ እና እየዳበረ የሚመጣ የተግባራዊ ስነልሳን አንድ ክፍል ነው። ቋንቋን መማር ማስተማር እድገት እየዳበረ መምጣት ዋነኛ ምክንያቶች ሰዎች አለምን ለመገንዘብ፣ ራሳቸውን እና አስተሳሰባቸውን ለመግለፅ፣ ተግባቦታዊ መስተጋብራቸውን በቀላሉ ለማቀላጠፍ እና ከሌሎች ወገኖች ጋር ለመተባበር ካላቸው ፅኑ ፍላጎት የመነጨ እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

የቋንቋ ትምህርት በቋንቋ መዋቅር ላይ ከማተኮር ይልቅ (የቋንቋ መዋቅር ሙሉ ለሙሉ ሳይዘነጋ) ተማሪዎች በቋንቋ አገልግሎት ላይ እንዲያተኩሩ በማድረግ በታላሚው ቋንቋ ተግባቦታዊ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ እና መስተጋብራዊ ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ በቋንቋ የመገልገል አቅማቸው እንዲጨምር ያስችላል የሚለው አመለካከት በሒደት የተከሰተ እና ከ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ወዲህ ጎልቶ የተንፀባረቀ ሀሳብ ነው (Richards 2006፣ Tracey & Morrow 2006፣ Cook 2004)። ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ ተግባቦታዊ ብቃት ላይ በማተኮር በታላሚው ቋንቋ አድምጠው የሚገነዘቡ፣ ራሳቸውን በሚገባ መግለፅ የሚችሉ፣ ያነበቡትን የሚረዱ እና የተረዱትን የሚያንፀባርቁ፣ አዳዲስ መረጃዎችን ከቀደመ እውቀታቸው ጋር በማስተሳሰር

የራሳቸውን አዳዲስ ሀሳብ በማፍለቅ የተደራጀ ፅሁፍ የሚፅፉ እንዲሁም ከፍ ያለ የቃላት እና የሰዋስው እውቀት ያላቸው ጠንካራ የቋንቋ ተማሪዎች እንዲሆኑ መሠረታዊ የቋንቋ ክሂሎች ላይ ማተኮር ተገቢ ነው (Tracey & Morrow 2006) ።

በቋንቋ ትምህርት መሰረታዊ ከሚባሉት ክሂሎች አንዱ ማንበብ ነው። ማንበብ አካላዊ እና ውስብስብ አእምሯዊ ተግባራት የሚንፀባረቅበት፣ የመመርመር፣ የማብላላት፣ የመተርጎም፣ የመተንተን፣ የመጠየቅ ሂደት የሚከናወንበት፣ አንባቢ፣ ውህድአሀድ፣ ብልሃት እና ግብ መስተጋብር የሚፈጥሩበት፣ የስነአእምሯዊ ስነልሳን ግምት ጨዋታ የሚስተዋልበት የቋንቋ ምስጢራዊ ክሂል ነው (Block & Pressley 2002፣ 2008፣ Goodman 1984፣ Alderson 1984፣ Nuttal 1982)።

ማንበብ በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ የቋንቋ ትምህርትንም ሆነ ሌሎች ትምህርቶችን በብቃት ለመከታተል እና የህይወት አቅጣጫን ውጤታማ ለማድረግ (ራስን ብርቱ የህይወት ዘመን ተማሪ ለማድረግ) ወሳኝ ክሂል ነው። በተለይ ለመጀመሪያ እና ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ማንበብ ጠንክሮ የመማር መስመራቸውን የሚያበጁበት፣ የታላሚውን ቋንቋ ብቃት ለማጎልበት የሚችሉበት፣ የቃላት እውቀታቸውን የሚያሰፉበት፣ ለማንበብ ተግባር የሚቀርቡ ውህድአሀዶችን አንብበው በመረዳት አዳዲስ መረጃዎችን የሚገነዘቡበት፣ የመረዳት አቅማቸው በጎለበተ መጠን የህሊና እርካታ የሚያገኙበት እና በራስ መተማመናቸውን የሚሳድጉበት ወሳኝ ክሂል ነው።

Phakiti (2006፡22) እንደገለፁት በሁለተኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት በማንበብ ትምህርት ላይ ትኩረት ማድረግ ተማሪዎች አካዳሚያዊ ክሂላቸው፣ የማንበብ እና የመፃፍ ችሎታቸው፣ የፅንሰ ሀሳብ አወቃቀር ብቃታቸው፣ የሚማሩት ትምህርት ይዘት ግንዛቤያቸው እና የማንበብ ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ የመተግበር አቅማቸው ከፍ እንዲል ትልቅ አስተዋፆ አለው።

ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት እንደሌሎች ክሂሎች ሁሉ የማንበብ ክሂልን ለማስተማርም ሆነ ለመመዘን ጥንቃቄ እና ትጋት ይፈልጋል። ይህን ጠቃሚ ክሂል ማስተማር የተጀመረው ከ1840-1940 ሁለተኛ ቋንቋን ለማስተማር ታስቦ አገልግሎት ላይ በዋለው ሰዋስው ወትርጉም ዘዴ (Grammar Translation Method) ነው (Tracey & Morrow 2006፣ Cook 2004፣ Celce- Murcia 1991፣ Richards & Rodgers

1986፣ Larsen-Freeman 1986)። ሰዋስው ወትርጉም ዘዴ በተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን ማቅረብ፣ ለተወሰኑ አላማዎች ብቻ ታላሚውን ቋንቋ መገልገል፣ የሰዋስው መዋቅራዊ ሕግጋት እና ቃላትን አጥብቆ ማስተማር፣ ስር የሰደደ ሽምደዳ ላይ ማተኮር፣ መተርጉም እና የተለያዩ ውህድአሀዶችን ተማሪዎች እንዲያነቡ ማድረግ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነበር ።

ቋንቋን የማስተማር ሂደት ብዙ ውጣ ውረዶች አልፎ አሁን እስካለበት ተግባቦታዊ አቀራረብ ወይም ብቃት ተኮር አቀራረብ ደረጃ እስኪደርስ ድረስ የማንበብ ክሂል ትምህርት ተሰጥቷል፤ አሁንም እየተሰጠ ይገኛል (ክሂሉን ለማስተማር የትኩረት መጠን እንደየዘመኑ የተለያየ ቢሆንም)። ተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ የሰዋስው ብቃት (የቃላት፣ የስርአተድምፅ እና የቋንቋ ህግጋት እውቀት)፣ የዲስኮርስ ብቃት (ንግግርን/ፅሁፍን/ ከትርጉም ጋር የማገናኘት ችሎታ)፣ የማህበራዊ ቋንቋ አጠቃቀም ብቃት (ታላሚውን ቋንቋ በሚገባ የመጠቀም ችሎታ)፣ የብልሃት አጠቃቀም ብቃት (ትክክል ያልሆነን እውቀት ወይም እጥረትን ለማስወገድ ብልሃቶችን ተግባራዊ የማድረግ ችሎታ) ላይ ያተኩራል። በመሆኑም አቀራረቡ ተማሪዎች መሰረታዊ የቋንቋ ክሂል፣ ሰዋስው እና ቃላት፣ ዲስኮርስ፣ ብልሃት አጠቃቀም ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ የሚያበረታታ አቀራረብ ነው (Griffiths 2004፣ Brown 2001)።

ይህም ሆኖ በቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ አሁን ድረስ በተማሪዎች ላይ የሚስተዋሉ ተጠቃሽ ችግሮች አሉ። ዋና ዋና ተብለው ከሚታወቁት ችግሮች አንዱ የማንበብ እና የመረዳት ችግር ነው (Ballou 2012፣ Anderson 2005፣ Pressley 2000፣ National Reading Panel 2000)። በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ቁልፍ ጉዳይ የሆነው ማንበብ እጅግ የለውጥ አብዮት ከሚያስፈልጋቸው ትምህርታዊ ጉዳዮች አንዱ እና ዋነኛው ነው (Tracey & Morrow 2006፣ National Reading Panel 2000)። ተማሪዎች በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸውም ሆነ በሌሎች የትምህርት አይነቶች ውጤታማ ለመሆን ወይም ላለመሆን መሰረታዊ ተብለው ከሚጠቀሱ ምክንያቶች ዋነኛው የማንበብ ክሂላቸው ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረስ ነው።

አንድ አንባቢ ጥሩ አንባቢ ነው የሚባለው በዋነኛነት የማንበብ አላማ ሲኖረው፣ የማንበብ ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ሲጠቀም፣ የቀደመ እውቀቱን ከአዲሱ

ሀሳብ ጋር በማቀናጀት ትርጉምን ለማዋቀር ጥረት ሲያደርግ፣ ያነበበውን በሚገባ ሲገነዘብ፣ የተገነዘበውን ማንፀባረቅ ሲችል ወዘተ ነው። መምህራንም ተማሪዎቻቸው በአላማ የሚያነቡ ጥሩ አንባቢዎች እንዲሆኑ ጠቃሚ የማስማሪያ መንገድ በመምረጥ (በመከተል) ብልሃቶችን ማስተማር ይጠበቅባቸዋል። Krashen (2013)፣ McNamara (2007)፣ Carrell (2006)፣ Kong (2006)፣ Cohen & Chi (2005)፣ McNamara (2004)፣ Pressley (2000)፣ Dole et al. (1998)፣ Oxford (1990)፣ O`Mallye & Chamot (1990) እንዳመላከቱት አንባቢዎች የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ በመጠቀም ብቃታቸውን ሲያጎለብቱ የሚታይ ጉልህ ጠቀሜታ ያገኛሉ።

የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳትን መሰረት በማድረግ በሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ የተሰሩ የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት ተማሪዎች (ከ4-12) ለመማር ማስተማር የሚያገለግሉ ውህድአሀዶችንም ሆነ ሌሎች ለትምህርት አጋዥ የሆኑ ፅሁፎችን አንብበው ለመረዳት ሲችገሩ ይስተዋላሉ (Snow 2002፣ National Reading Panel 2000፣ Anderson 1999፣ Cohen 1999፣ Bossers 1991፣ Celce- Murcia 1991፣ Alderson 1984)። በተለይ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ በሚዘጋጁ ውህድአሀዶች ውስጥ ያሉትን ቃላት በሚገባ በመጥራት (ቅላፄውን በመጠበቅ) ቢያነቡም ወይም በፍጥነት እና ፍሰቱን (ግላፄውን) ጠብቆ በማንበብ ጥሩ ቢሆኑም ያነበቡትን ከመረዳት አንፃር ምን እንዳነበቡ በሚጠየቁበት ወቅት መልስ ለመስጠት እንደሚቸገሩ ጥናታዊ ፅሁፍ አቅራቢዎቹ ያስረዳሉ። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች ቢጠቀሱም በተለይ ብዙ የቋንቋ መምህራን ተማሪዎቻቸው ለምን በሁለተኛ ቋንቋ በብቃት እንደማያነቡ ሲጠየቁ የሚያቀርቡት ዋነኛ ምክንያት ተማሪዎች በመጀመሪያ ቋንቋ በብቃት ስለማያነቡ ነው የሚል ሀሳብ ያንፀባርቃሉ (Cohen 1999፣ Bossers 1991፣ Celce-Murcia 1991፣ Aldersen 1984)።

በሀገራችን ኢትዮጵያ የቋንቋ ትምህርት አውድ ተማሪዎች በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ቋንቋ የማንበብ እና አንብቦ የመረዳት ችግር እንደሚስተዋልባቸው የተለያዩ ጥናቶች (መኮንን 2000፣ ተክላይ 2000፣ ዘውዱ 1998፣ ጌትነት 1998፣ እንግዳ 1992፣ የኔሰው 1990) ያመላክታሉ። ይህ ሁኔታ እንግሊዝኛን እንደሁለተኛ (የውጭ) ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ላይም እንደሚስተዋል ጥናት ያቀረቡ ወገኖች (Seid 2012፣ Dawit 2014፣ Abebe 2000፣ Solomon 2000 Gessesse 1999፣ Taye 1999)

አመላክተዋል። ተማሪዎች (በተለይ በሁለተኛ፣ በመሰናዶ እና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ) አንብቦ የመረዳት ብቃት ማነስ የተለያዩ ምክንያቶች የተጠቀሱ ሲሆን በዋነኛነት ተገቢ የማስተማር ዘዴ ተግባራዊ ያለመሆን፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች (ለምሳሌ የመማሪያ ማስተማሪያ መፅሀፍት) በበቂ ሁኔታ አለመዘጋጀት፣ አስፈላጊ የሆነ በቂ እውቀት ወይም የቀደመ እውቀት ማነስ፣ ለትምህርት ያላቸው ትጋት እና መነሳሳት ዝቅተኛ መሆን ተጠቃሽ ናቸው። በተማሪዎች ላይ የሚታየው ችግር ሲጠቃለል የይዘት እና የመደበኛ አእምሯዊ የእውቀት መዋቅር (Schema) ወይም አእምሯዊ የእውቀት መዋቅር እና ስልታዊ እውቀት ችግር ነው። ይህንን የእውቀት መዋቅር ማጎልበት ለመጀመሪያ እና ሁለተኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ወሳኝ ነው።

በሀገራችን የቋንቋ ትምህርት አውድ በተማሪዎች ላይ ከሚታዩ ችግሮች አንዱ ተማሪዎች እንዴት እንደሚያነቡ አለማወቅ እንደሆነም ይጠቀሳል። ተማሪዎች እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ባለመማራቸው አንብቦ የመረዳት ችግራቸው የጎላ ነው። የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችግር ለማስወገድ ምን መደረግ አለበት የሚል ጥያቄ ሲነሳ ችግሩን ለማስወገድ ከሚያስችሉ መንገዶች አንዱ የማንበብ ብልሃቶችን ማስተማር ይገባል የሚሉ ወገኖች አሉ (Tesfu 2015፣ Belilew 2015፣ Solomon 2000፣ Dawit 2014)።

ከማንበብ ብልሃት ጋር በተገናኘ በአለም አቀፍ ደረጃ የተለያዩ ሀገሮች ተማሪዎችን ተተኳሪ በማድረግ ቀደም ሲል ይሰሩ የነበሩ ጥናቶች የማንበብ ብልሃት አከፋፈል እና ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው የማንበብ ብልሃት አይነቶችን መለየት ላይ ያተኮረ ነበር (Oyetunji 2013፣ Zhang 2012 ፣ Phakiti 2006)። በአሁኑ ወቅት እየተሰሩ ያሉ ጥናቶች ጥቂት ቢሆኑም ዋነኛ ትኩረታቸው የማንበብ ብልሃቶች አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለማጎልበት ምን አይነት አስተዋፆ አላቸው? ተማሪዎች የቀረቡ ፅሁፎችን አንብበው ለመረዳት የማንበብ ብልሃቶችን እንዴት ይጠቀማሉ? የተለያዩ ፅሁፎችን በማንበብ ሂደት የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ ልምዳቸውን እንዴት ተግባራዊ ያደርጋሉ፣ የማንበብ ብልሃቶችን እንዴት ከአንድ ሁኔታ ወደሌላ አዲስ ሁኔታ ወይም ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ ሽግግር በማድረግ በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ አንብበው ለመረዳት ጥረት ያደርጋሉ ወዘተ የሚሉ ናቸው (Zhang 2012፣ Ling 2011፣ Bimmel et al. 2001)።

በአሁኑ ወቅት የቋንቋ መሰረታዊ ክሂሎችን በክፍል ውስጥ በማስተማር ሂደት ተግባራዊ ይደረጋል ተብሎ በሚታሰበው ተግባቦታዊ (ብቃት ተኮር) የትምህርት አቀራረብ የቋንቋ ትምህርት ከመምህር ተኮር ወደተማሪ ተኮር የተሸጋገረ በመሆኑ የተማሪዎች ፍላጎት፣ ችሎታ፣ ክሂል፣ አእምሯዊ ብቃት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል (ቢያንስ ቢያንስ በመርህ ደረጃ)። ተማሪዎችም ያላቸውን አእምሯዊ ብቃት አውጥተው እንዲጠቀሙ እድል አግኝተዋል። በዚህ የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎችም አእምሯዊ ብቃታቸውን ተጠቅመው በመማር ማስተማር ሂደቱ በንቃት በመሳተፍ እውቀት እና ክሂሎቻቸውን ማጎልበት ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ዘመን አስተሳሰብ የተማሪዎች የማንበብ ክሂል ከፊል እውቅያ አእምሯዊ ክንውን በመሆኑ ተማሪዎች ይህን ክሂል ውጤታማ በሆነ መንገድ ራሳቸው ማጎልበት እንዲችሉ እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው መገንዘብ አለባቸው (Khaokaew 2013፣ McNamara 2007፣ Pressley 2000)። ተማሪዎች እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው በመረዳት የማንበብ ክሂላቸውን በራሳቸው ጊዜ ማጎልበት የሚችሉት የማንበብ ብልሃቶችን በመማር ሆንብለው በሙሉ አእምሯዊ እውቅያ ሲጠቀሙ ነው (Ling 2011፣ McNamara 2007፣ Alderson 1984)።

የማንበብ ብልሃት ተማሪዎች የተለያዩ ፅሁፎችን እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው የሚረዱበት፣ ሆንተብሎ የሚተገበር ስልታዊ እቅድ ሲሆን አንባቢዎች (ተማሪዎች) ከሚነበበው ውህድአሀድ በመነሳት ዘዴዎችን፣ የተግባራት ቅደም ተከተሎችን፣ ወይም የአእምሮ ተልዕኳዊ አሰራሮችን (Mental Operations) በመረዳት እና ተግባራዊ በማድረግ ያነበቡትን መገንዘብ አልያም ባልገባቸው ጊዜ (ችግር በገጠማቸው ጊዜ) ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚወስኑበት ሁነኛ መንገድ ነው (Bimmel et al. 2012፣ Ling 2011፣ Yamashita 2006፣ Alderson 1984)።

በማንበብ አውድ ጠንካራ ተማሪዎች ከደካማ ተማሪዎች በበለጠ በተደጋጋሚ የማንበብ ብልሃቶችን እያቀናጁ ይጠቀማሉ። ደካማ ተማሪዎችም ብልሃቶችን ፍፁም አይጠቀሙም ማለት አይቻልም። ውጤታማ ያልሆኑ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የተወሰኑ የማንበብ ብልሃቶችን በግምት፣ ኢላማ ቢስ፣ ኢ-አጥጋቢ፣ ውጤት አልባ በሆነ መልኩ እና በዘፈቀደ ሊጠቀሙ ይችላሉ (ይጠቀማሉ) (Phakiti 2006)። ተማሪዎች ውጤታማ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀምን መለየት እንዲችሉ እገዛ ማድረግ ያስፈልጋል። ይኸውም ብልሃቶችን እንዴት በብቃት መምረጥ፣ ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም እና

መረዳትን መቆጣጠር እንዳለባቸው መማር ይገባቸዋል። የተለያየ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ በብቃት ማስተማተር የሚቻለው ፅንሰ ሀሳባዊ (ይዘታዊ) እና የብልሃት አጠቃቀምን ማስተማር እንዲሁም መመዘንን ባመጣጠነ መልኩ ማቅረብ ሲቻል ነው (Mokhtari & Reichard 2002፡250)።

በርግጥ ቋንቋዎች የየራሳቸው የድምፅ አወጣጥ፣ የቃላት አመሰራረት፣ ቅጥያዎች በቃላት ላይ የሚጨመሩበት ምዕላዳዊ ስርአት፣ የዐረፍተነገር አወቃቀር፣ የቃላት አደራደር፣ የፅህፈት ስርአት ወዘተ ያላቸው በመሆኑ ሊመሳሰሉ ወይም ሊለያዩ ይችላሉ። የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብም ከሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ልዩነት አለው። ይሁን እንጂ የመጀመሪያ ቋንቋ እና ለትምህርት የታሰበው ሁለተኛ ቋንቋ በአካዳሚያዊ ክህሎት፣ መፃፍ እና ማንበብን በማጎልበት ሂደት፣ የፅንሰ ሀሳብ ምስረታ፣ የይዘት እውቀት፣ ብልሃቶችን ከማጎልበት አንፃር የሚጋሯቸው ብዙ ጠቃሚ ጉዳዮች በመኖራቸው ይደጋገፋሉ። ከማንበብ ብልሃት አጠቃቀም አንፃር የተለያዩ የጥናት ወረቀቶች እንደሚያመላክቱትም በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ መካከል ጠንካራ ግንኙነት አለ (Grabe 2012፣ Carrell 2006፣ Lee & Schallert 1997) ።

Talebi (2015:35) የተባሉት ፀሀፊ Cummins (1989)፣ Alderson (1984) እና Yorio (1971) ን ጠቅሰው እንደገለፁት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ግንኙነት አለው ። ይሁን እንጂ በመጀመሪያም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ እና የሁለተኛ ቋንቋ ብቃት አስፈላጊ ነው ይላሉ። ፀሀፊዎቹ በተለይ በተማሪዎች ላይ የሚስተዋለው የሁለተኛ ቋንቋ የማንበብ ብቃት ማነስ የቋንቋ ችግር ነው ወይስ የማንበብ ችግር? በመጀመሪያ ቋንቋ ጎበዝ አንባቢዎች በሁለተኛ ቋንቋ ጎበዝ አንባቢዎች ናቸው? በመጀመሪያ ቋንቋ ደካማ አንባቢዎችስ በሁለተኛ ቋንቋ ደካማ ናቸው? በሚል ምርምራዊ ጥያቄ ተነስተው መላምቶችን ቀምረዋል (አስተዋውቀዋል)። መላምቶቹም የቋንቋ ርስበርስ ግንኙነት ወይም አእምሯዊ የጋራ ውስጠ ብቃት መላምት (ሞዴል) (Linguistic Interdependency Hypotheses / Common Underlying Proficiency Hypotheses / Model) እና የቋንቋ ጅመራ ደረጃ ወይም መጠነኛ ችሎታ መላምት (ሞዴል) (Linguistic Threshold Hypotheses /Short-Circuit Hypotheses /Model) ናቸው።

የቋንቋ ርስበርስ ግንኙነት መላምት የሚያንፀባርቀው ሀሳብ በመጀመሪያ ቋንቋ እና በሁለተኛ ቋንቋ መካከል ልዩነት ቢኖርም የጋራ አእምሯዊ ውስጠ ብቃት ወይም የጋራ ግንዛቤያዊ ችሎታ ያለ በመሆኑ ከመጀመሪያ ቋንቋ ወደሁለተኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት ሽግግር ያደርጋል። ይህ ማለት ተማሪዎች በመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ ጠንካራ ከሆኑ በመጀመሪያ ቋንቋ የተማሯቸው ጉዳዮች ወደሁለተኛ ቋንቋ በቅልጣፌ (Automatic) ሽግግር ያደርጋል። በአንፃሩ የቋንቋ ጅመራ ደረጃ (መጠነኛ ችሎታ) መላምት ከመጀመሪያ ቋንቋ ወደሁለተኛ ቋንቋ ወይም በተቃራኒው የማንበብ ብልሃት ሽግግር እንዲፈጠር በሁለተኛ ቋንቋ ቢያንስ ቢያንስ ጅመራ (መጠነኛ) የቋንቋ ችሎታ (Linguistic Threshold) ወሳኝ ነው የሚል ሀሳብ ያራምዳል። እነዚህን ሁለት ሀሳቦች በማጣመር አስታራቂ ሀሳብ የሚያቀርቡ ወገኖች ደግሞ ከመጀመሪያ ቋንቋ ወደሁለተኛ ቋንቋ ወይም በተቃራኒው የማንበብ ብልሃት ሽግግር እንዲፈጠር የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ ብቃት እና የሁለተኛ ቋንቋ የቋንቋ ችሎታ (ብቃት) እጅግ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው ይላሉ (Talebi 2015) ።

የማንበብ ብልሃት ሽግግር አንባቢዎች በታላሚው ቋንቋ የቀረበን ፅሁፍ ለመረዳት በተቸገሩ ጊዜ በራሳቸው ቋንቋ አስቀድመው የሚያውቁትን መጠቀም ወይም በተቃራኒው በሁለተኛ ቋንቋ የተማሩትን ወደመጀመሪያ ቋንቋ በመውሰድ የማንበብ ችግራቸውን የሚያስወግዱበት መንገድ ነው። የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ በሁለት ቋንቋዎች መመሳሰል እና ልዩነት ላይ ተመስርቶ የሚከሰት የስነልቦናዊ ስነልሳን ፅንሰሀሳብ ነው። ቋንቋዎቹ ሲመሳሰሉ ቋንቋዊ ጉዳዮች (ድምፅ፣ ምዕላድ፣ ቃል፣ ወዘተ) እና ኢ-ቋንቋዊ ጉዳዮች (እውቀት፣ ፅንሰሀሳብ፣ ሀይል፣ ብልሃት ወዘተ) ሽግግር ያደርጋሉ። ቋንቋዎቹ ሳይመሳሰሉ ደግሞ ቋንቋዊ ጉዳዮች ይቀሩና ኢ-ቋንቋዊ ጉዳዮች ሽግግር ያደርጋሉ። ኢ-ቋንቋዊ ጉዳዮች ከሚባሉት ውስጥ አንዱ ብልሃት ነው። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍም የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር በተለያየ መንገድ ተግባራዊ የሚደረግ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም፣ የብልሃት አጠቃቀሙ አንብቦ መረዳትን ለማጎልበት ያለው አስተዋፆ እንዲሁም የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ለአንብቦ መረዳት ያለው ድርሻ ምን እንደሚመስል መመርመር ዋነኛ ጉዳዩ ነው።

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

የሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ከመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ በበለጠ ውስብስብ ነው (Phakiti 2006፣ Celcie-Murcia 1991)። በዚህም ምክንያት ከመጀመሪያ ቋንቋ በበለጠ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ አንብቦ የመረዳት ችግር ይስተዋላል። በተማሪዎች ዘንድ በታላሚው ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችግር መኖሩን ከዚህ በፊት የተሰሩ ጥናቶች ያረጋገጡ ከመሆናቸው በተጨማሪ የዚህ ጥናት አቅራቢ በሁለተኛ ደረጃ፣ በመሰናዶ ትምህርት ቤት እና በዩኒቨርሲቲ ባስተማረባቸው ጊዜያት በተማሪዎች ላይ አንብቦ የመረዳት ችግር መኖሩን አስተውሏል። በተጨማሪ የጥናቱ አቅራቢ በተለያየ አጋጣሚ ከሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት መምህራን ጋር በነበረው ውይይት (ለመምህራን አጫጭር ስልጠና በመስጠት ወቅት፣ መምህራንን የክረምት ትምህርት በማስተማር አጋጣሚ፣ ለጥናቱ መረጃ በማሰባሰብ ጊዜ) እና ጥናቱ ከመጀመሩ በፊት የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማየት በነበረ የተወሰ ጊዜ የክፍል ውስጥ ምልከታ በተጨባጭ ችግሩ መኖሩን ተገንዝቧል። ይህ በተማሪዎች ላይ የሚታየው አንብቦ የመረዳት ችግር እንዴት ሊቀረፍ ይችላል የሚለው ጥያቄያዊ ሀሳብ የዚህ ጥናት የመጀመሪያ አነሳሽ ምክንያት ነው።

በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ የሚታየው የማንበብ ችግር ምክንያት ታላሚውን ቋንቋ በሚገባ የመጠቀም ችግር፣ በታላሚው ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችግር፣ የቋንቋ እና የማንበብ ችግር ወይስ ሌላ ተጠቃሽ ምክንያት አለ የሚለው ሀሳብ በመስኩ የተሰማሩ የምርምር ባለሙያዎችን እለት እለት ለምርምር የሚጋብዝ እና የሚያነጋግር ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጠቃሚ ጥያቄ በመጀመሪያ ቋንቋ ጎበዝ አንባቢዎች በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ጎበዝ ናቸው? በመጀመሪያ ቋንቋ ደከም ያሉ አንባቢዎችስ በሁለተኛ ቋንቋ ደካማ ናቸው የሚለው ነው። በምሁራን የሚብላላው የሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ችግር አከራካሪ እና ከብዙ አቅጣጫ ሊታይ የሚችል መሆኑ በዚህ ላይ ሰፊ ምርምር ማድረግ እንደሚያስፈልግ አመላካች ነው። የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አቅራቢም በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ እና የመረዳት ችግር የራሱ የሁለተኛ ቋንቋ (አማርኛ ቋንቋ) ማንበብ ችግር ነው ወይስ የማንበብ እና የቋንቋ ችግር ነው በማለት በተነሳበት ርዕስ ላይ እንዲያተኩር ምክንያት ሆኖታል ።

የማንበብ ብልሃት በሁለተኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳትን ከማጎልበት አንፃር ያለውን ሚና በተመለከተ በአለም አቀፍ ደረጃ ጥናቶች ተካሂደዋል። በሀገር ውስጥ የተሰሩት ውስን ጥናቶች የተማሪዎችን የማንበብ ብልሃት መፈተሽ ላይ ያተኮሩ ናቸው። የማንበብ ብልሃቶችን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ብቃት ለማጎልበት አስተዋፆ ይኖረው ይሆን (በተለይ በታላሚው ቋንቋ) በሚል ጥያቄያዊ ሀሳብ ተነሳስቶ የሙከራ ጥናት ያካሄደ ወገን ባለመኖሩ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በታላሚው ቋንቋ ብልሃቶችን በግልፅ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ብቃት ለማጎልበት ሚና ይኖረው ይሆን የሚለውን ሀሳብ መፈተሽ ሌላው የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ነው።

ሌላው በአለም አቀፍ ደረጃ የማንበብ ብልሃት ላይ ትኩረት አድርገው የሚሰሩት ጥናቶች በአብዛኛው ትኩረታቸው አእምሮታዊ እና ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት ላይ የተመሰረተ ነው። ሌሎች የማንበብ ብልሃቶችን አካተው ጥናት ያደረጉቱ በጣም ውሱን ናቸው። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ፣ ትውስታ፣ ማካካስ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃቶችን አቀናጅቶ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ውጤትን ለማጎልበት ያላቸው ሚና ምን ይመስላል የሚለው ሀሳብ የዚህ ጥናት መነሻ ምክንያት ነው።

የሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ የልሳነ ዋህድ ክስተት አይደለም። በመሆኑም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ የቀረቡ ውህድአሀዶችን አንብበው ለመረዳት የመጀመሪያ ቋንቋቸውን እንደሀብት (Resource) ይጠቀሙበታል (Grabe1991)። ከዚህ በመነሳት የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ በሁለተኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ላይ ያለው አስተዋፆ ምን እንደሚመስል በጥልቀት ማየት በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ የሚታየውን የማንበብ ችግር ይፈታው ይሆን የሚለው ጥያቄያዊ ሀሳብ ሌላው የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ መነሻ ምክንያት ነው።

ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የሚቀርቡ የተለያዩ ፅሁፎችን በሚያነቡበት ወቅት የማንበብ ብልሃቶችን እንዴት ይጠቀማሉ? በተለይ የማንበብ ብልሃቶችን ከአንድ አዲስ ሁኔታ ወደሌላ አዲስ ሁኔታ ወይም ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ እያሸጋገሩ (ከመጀመሪያ ወደሁለተኛ ወይም ከሁለተኛ ወደመጀመሪያ ቋንቋ ወዘተ) ሲጠቀሙ አንብቦ መረዳታቸው ይጎለብታል ወይስ የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ አንብቦ የመረዳት ውጤት እንዲጎለብት ምንም አስተዋፆ የለውም በሚለው ሀሳብ ዙሪያ ከዚህ ቀደም በሀገር ውስጥ

የተሰራ ጥናት ባለመኖሩ **(አዲስ ሀሳብ በመሆኑ)** ጉዳዩን በጥልቀት መመርመር ሌላው የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት ነው።

አለም አቀፍ ተሞክሮም በአብዛኛው እንግሊዝኛን እንደሁለተኛ ወይም የውጪ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ከመጀመሪያ ቋንቋቸው ጋር በማነፃፀር ለምሳሌ በቻይንኛ (ቋ1) እና እንግሊዝኛ (ቋ2)፣ በአረብኛ (ቋ1) እና እንግሊዝኛ (ቋ2)፣ በፐርሺያ (ቋ1) እና እንግሊዝኛ (ቋ2) በሂብሩ (ቋ1) እና እንግሊዝኛ (ቋ2) ወዘተ ላይ ያተኮረ ነው። ይህ ጥናት በሀገር ውስጥ መቼት እና አውድ ቋንቋዎች ርስበርስ ያላቸውን መደጋገፍ በጥልቀት በማየት ሶማልኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች በሶማልኛ እና በአማርኛ ቋንቋ ሲያነቡ ያለባቸውን አንብቦ የመረዳት ችግር መመርመር እና የመፍትሄ አቅጣጫ ማመላከት ሌላው የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ነው።

በየትኛውም መስክ ያለ የማስተማር መንገድ (የትምህርት አቀራረብ) ተማሪዎችን ለውጤት የሚያበቃ አልያም ከችግር የማይታደግ ሊሆን ይችላል። እስከአሁን ድረስ ተዕእኖ ፈጥሮ በማገልገል ላይ ያለው የማስተማር መንገድ ተማሪዎችን በንቃት በማሳተፍ ራስ መር አንባቢዎች እንዲሆኑ፣ በማንበብ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን አምነው የሚቀበሉ እና ለችግሮች ራሳቸው መፍትሄ የመፈለግ ወሳኝ ሚና እንዲኖራቸው ማብቃት የሚፈለግ ቢሆንም በተፈለገው ልክ ተግባራዊ ከማድረግ ይልቅ ባህላዊ መንገድ የተከተለ (መምህር መጠየቅ - ተማሪ መመለስ - መምህር መመዘን) በመሆኑ አዲስ የማስተማር መንገድ ማስተዋወቅ እና ማበረታታት አስፈላጊ ነው። በዚህ መሰረት የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር (Explicit Instruction) የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና አንብቦ የመረዳት ብቃት አንዲጎለብት ያለውን አስተዋፆ መፈተሽ እና ጠቃሚነቱን ማስተዋወቅ ሌላው ተጠቃሽ የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አነሳሽ ምክንያት ነው።

1.3 የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች

- የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከቅድመ ልምምድ በጎላ መልኩ በድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እንዲጎለብት ምን ያህል አስችሏል?

- የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከቅድመ ልምምድ በተሻለ በድህረልምምድ አንብቦ የመረዳት ውጤት እንዲጎለብት ምን ያህል አስተዋፆ አለው?

- የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከቅድመ ልምምድ በተሻለ በድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር አዎንታዊ ዝምድና እንዲኖር ምን ያህል አስችሏል ?

- የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ያለ የማንበብ ብልሃት ሽግግር እንዲጎለብት ምን ያህል አስተዋፆ አድርጓል?

- ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ያለ የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ውጤት እንዲጎለብት ምን ያህል አዎንታዊ ድርሻ አለው?

1.4 የጥናቱ መላምቶች

አማራጭ መላምት (H1)

የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ተማሪዎች በራሳቸው መንገድ የማንበብ ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገብ በመጠቀም አንብቦ መረዳታቸውን እንዲያጎለብቱ አስተዋፆ አለው፡፡

አልቦ መላምት (H0)

የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ተማሪዎች በራሳቸው መንገድ የማንበብ ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲጠቀሙ ማድረግ የማያስችል በመሆኑ አንብቦ መረዳታቸውን አያጎለብትም፡፡

አማራጭ መላምት (H1)

የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከቅድመልምምድ በተሻለ መልኩ በድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ የመረዳት ውጤት ጋር አዎንታዊ ዝምድና አለው፡፡

አልቦ መላምት (H0)

የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከቅድመልምምድ በተሻለ መልኩ በድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ የመረዳት ውጤት ጋር አዎንታዊ ዝምድና የለውም፡፡

አማራጭ መላምት (H1)

የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ያለ የማንበብ ብልሃት ሽግግር እንዲጎለብት በማድረግ በየቋንቋው ላለ አንብቦ የመረዳት እድገት አስተዋፆ አለው፡፡

አልቦ መላምት (H0)

የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ያለ የማንበብ ብልሃት ሽግግር እንዲጎለብት አስተዋፆ የሌለው በመሆኑ በየቋንቋው ላለ አንብቦ የመረዳት እድገትም አስተዋፆ የለውም፡፡

1.5 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋነኛ አላማ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ውጤትን ለማጎልበት እና ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ያለው አስተዋፆ ምን እንደሚመስል በጥልቀት መመርመር ነው፡፡ በጥናቱ ይህንን ዋና አላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ንዑሳን አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር በጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም መጎልበት ላይ አስተዋፆ ያለው መሆን አለመሆኑን መመርመር፣

- የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ውጤትን ለማጎልበት አስተዋፆ ያለው መሆን አለመሆኑን መመርመር፣

- በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር አዎንታዊ ዝምድና ያለው መሆን አለመሆኑን መመርመር፣

- የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር የማንበብ ብልሃት ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ያለን ሽግግር ማጎልበት አለማጎልበቱን መመርመር፣

- ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ያለ የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ውጤት መጎልበት ላይ ያለውን አስተዋፆ መመርመር ናቸው፡፡

1.6 የጥናቱ ጠቀሜታ

የማንበብ ብልሃትን በተመለከተ በዚህ ወቅት እየተሰሩ ያሉ ጥናቶች ትኩረታቸው አንብቦ መረዳትን ለማጎልበት የበለጠ ጠቀሜታ ያላቸውን የማንበብ ብልሃቶች መለየት፣ ጠንካራ እና ደካማ አንባቢዎች የሚጠቀሙበትን የማንበብ ብልሃት መለየት፣ የማንበብ ብልሃትን ማስተማር አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለማጎልበት ያለውን አስተዋፆ መፈተሽ ወዘተ የሚሉ ናቸው። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍም የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ በማስተማር የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም አለመጠቀማቸው፣ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ከመጀመሪያ ቋንቋ ወደሁለተኛ ቋንቋ ወይም በተቃራኒው እያሸጋገሩ መጠቀም አለመጠቀማቸው፣ በዚህም ምክንያት አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው መጎልበት አለመጎልበቱን የመመርመር ጠቀሜታ አለው። ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት።

- የማንበብ ብልሃቶችን በማቀናጀት ግልፅ በሆነ የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ማስተማር ያለውን ጠቀሜታ ማመላከት፣
- ጥናቱ ትኩረት ባደረገበት ክልል እና በሌሎች አካባቢዎች ያሉ ተማሪዎችን በመጀመሪያ ቋንቋም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል በክፍል ውስጥ በማስተማር ወቅት የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው በማስገንዘብ የማንበብ ክሂላቸውን ራሳቸው እንዲያጎለብቱ እድል መስጠትን ማበረታታት፣
- መምህራን የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው ግንዛቤ ማስጨበጥ፤መምህራኑም የተገነዘቡትን ወደተግባር ለውጠው በተማሪዎቻቸው ላይ የሚታየውን አንብቦ የመረዳት ብቃት ማነስ ለመቅረፍ እንዲችሉ ማነሳሳት፣
- የትምህርት ፖሊሲ አውጪዎች፣ ስርአተትምህርት፣ መማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያ እና ጠቃሚ የትምህርት ግብአቶችን የሚያዘጋጁ ወገኖች ለመማር ማስተማር የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን በሚያዘጋጁበት (በሚያሻሽሉበት) ወቅት የማንበብ ብልሃቶችን ሆን ብሎ በግልፅ ለማስተማር እንዲያስችል የማንበብ ብልሃቶችን እንዲያካትቱ ሀሳብ መስጠት፣
- እንዲሁም በርዕሰ ጉዳዩ እና ተያያዥ ጠቃሚ ሀሳቦች ዙርያ ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ ወገኖች መነሻ ሀሳብ ለመስጠት ያስችላል።

1.7 የጥናቱ ገደብ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ 9ኛ ክፍል ሶማልኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች ላይ ያተኮረ ነው። ጥናቱ ከማንበብ ሒደት መሰረታዊ ነገሮች (ፊደልን እና ቃላትን መለየት፣ ቅላፄ፣ የሀሳብ ፍሰትን ወይም ግላፄን ጠብቆ ማንበብ እና አንብቦ መረዳት) ውስጥ አንብቦ መረዳት ላይ ሙሉ ትኩረት አድርጓል። ጥናቱ ማንበብ እና አንብቦ መረዳት ብቃት ላይ ያተኮረው ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርትም ሆነ በሌሎች የትምህርት መስኮች አካዳሚያዊ ግባቸውን ለማሳካት ወሳኝ በመሆኑ ነው።

በማንበብ ሂደት አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመጎናፀፍ የሚያስችሉ የተለያዩ ግብአቶች ያስፈልጋሉ። አንብቦ መረዳትን ለማጎልበት ከሚያስችሉ መሰረታዊ ነገሮች አንዱ የማንበብ ብልሃትን ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም ነው። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የተመረጡ የማንበብ ብልሃቶችን አቀናጅቶ በግልፅ ማስተማር አንብቦ መረዳትን ለማጎልበት ያለው አስተዋፆ ምን እንደሚመስል በጥልቀት መመርመር ላይ የተገደበ ነው። የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ ወይም ግልፅ ባልሆነ መንገድ ማስተማር ይቻላል። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ብልሃቶችን ግልፅ በሆነ መንገብ አቀናጅቶ ማስተማር ላይ የተመሰረተ ነው።

በጥናታዊ ፅሁፉ ለትምህርት የተመረጡት የማንበብ ብልሃት አይነቶች የ Oxford (1990) አከፋፈልን መሰረት ያደረጉ ናቸው (በምእራፍ ሁለት የማንበብ ብልሃት አከፋፈልን ይመለከቱዋል)። ጥናቱ የ Oxford (1990) አከፋፈል ላይ የተመሰረተበት ምክንያት ሌሎች ምሁራን (Rubin 1975፣ Stern 1975፣ O`Malley & Chamot 1990) ካቀረቡት በተሻለ አከፋፈሉ ግልፅ በመሆኑ፣ ማንበብን ከማስተማር ጋር በቀጥታ የተዛመደ እና ለማስተማር የሚመች በመሆኑ ነው። Oxford (1990) የማንበብ ብልሃቶችን ቀጥተኛ እና ኢ-ቀጥተኛ የማንበብ ብልሃት በማለት ይከፍላሉ። በቀጥተኛ የማንበብ ብልሃት ስር ትውስታ፣ አእምሮታዊ እና ማካካስ በኢ-ቀጥተኛ የማንበብ ብልሃት ስር ደግሞ ልእለአእምሮታዊ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ ብልሃቶች እንደሚካተቱ አመላክተዋል። በነዚህ በተጠቀሱት ስር ብዛት ያላቸው የማንበብ ብልሃቶች ይገኛሉ። በጥናቱ ትኩረት የተሰጠባቸው የማንበብ ብልሃቶች በአእምሮታዊ፣ ማካካስ፣ ትውስታ፣ ልእለአእምሮታዊ እና ማህበራዊ ብልሃት ስር የሚካተቱ አስራስድስት የማንበብ

ብልሃቶች ናቸው። እንደ Oxford (1990) አገላለፅ ስሜታዊ የማንበብ ብልሃቶች ይበልጡኑ በተግባቦታዊ መስተጋብር ለንግግር የሚያገለግሉ በመሆናቸው በዚህ ጥናት ውስጥ አልተካተቱም። በጥናቱ ለትምህርት የተመረጡት የማንበብ ብልሃቶች የሚከተሉት ናቸው።

ሰንጠረዥ አንድ፡- በጥናቱ ትኩረት የተሰጠባቸው የማንበብ ብልሃቶች ዝርዝር

የማንበብ ብልሃቶች ዝርዝር				
ቀጥተኛ የማንበብ ብልሃቶች			**ኢ-ቀጥተኛ የማንበብ ብልሃቶች**	
አእምሮታዊ	**ትውስታ**	**ማካካስ**	**ልእለአእምሮታዊ**	**ማህበራዊ**
መተንበይ፣ ዋናውን ሀሳብ በፍጥነት ማግኘት፣ መረጃን ፈልፍሎ ማውጣት፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ደግሞ (ደጋግሞ) ማንበብ፣ ሀሳብን በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ፣ አዳዲስ ቃላትን ለመረዳት አውዳዊ ፍቺ መመጠቀም፣ከሶማልኛ ወደአማርኛ/ ከአማርኛ ወደሶማልኛ ማሸጋገር፣	የቀደመ እውቀትን መጠቀም፣ በአእምሮ ምስል መፍጠር	ዘዴ በተሞላበት መንገድ መገመት	ዕሁፍን ለማንበብ ማቀድ፣ ራስን እና አንብቦ መረዳትን መቆጣጠር፣ ራስን መገምገም	ጥያቄ መጠየቅ፣ ከሌሎች ጋር መተባበር

ሌላው ጥናቱ የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ ማስተማር የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ (ከሶማልኛ ወደ አማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ) እንዲጎለብት አስተዋፆው ምን እንደሚመስል እንዲሁም የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሹ በየቋንቋው አንብቦ መረዳት ላይ ያለውን አስተዋፆ በጥልቀት መመርመር ነው። የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ የቋንቋዎች መመሳሰል እና ልዩነት ላይ ተመስርቶ የሚከሰት ነው። ሽግግሮሹ ቋንቋ ነክ ወይም ኢ-ቋንቋ ነክ ሊሆን ይችላል። ለጥናት የታሰቡት ቋንቋዎች ከተመሳሰሉ ቋንቋ ነክ እና ኢ-ቋንቋ ነክ ጉዳዮች ሽግግር የሚያደርጉ ሲሆን፤ ቋንቋዎቹ ካልተመሳሰሉ ቋንቋ ነክ ጉዳዮች ይቀሩና ኢ-ቋንቋ ነክ ጉዳዮች ብቻ ሽግግር ያደርጋሉ። ጥናታዊ ዕሁፉ ትኩረት ያደረገባቸው ሶማልኛ እና አማርኛ ቋንቋዎች ተመሳሳይ ባለመሆናቸው (በመዋቅር፣ በዕህፈት ስርአት ወዘተ) ጥናታዊ ዕሁፉ ኢ-ቋንቋ ነክ ጉዳይ ከሚባሉት ውስጥ ብልሃት ላይ ያተኮረ እና የተገደበ ነው። በዚህ ጥናት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ሙሉ ትኩረት

ለማድረግ በማሰብ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች ፆታ፣ እድሜ እና ዝርያ (ጎሳ) የተባሉ ተላዎጦዎች (Moderator Variabels) ላይ ትኩረት አልተደረገም።

1.8 የጥናቱ አውድ

ሶማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በኢትዮጵያ ከሚገኙ ዘጠኝ ክልሎች እና ሁለት መስተዳድራዊ ከተሞች ውስጥ ክልል አምስት በመባል የሚታወቅ የሀገሪቱ ክፍል ነው። ክልሉ በሀገሪቱ ደቡብ ምስራቅ አካባቢ 4/11 ላቲቲውድ እና 40/48 ዲግሪ ምስራቃዊ ሎንግቲውድ ይገኛል። ሶማሌ ክልል 350,000 ኪሎ ሜትር ስኩዬር የቆዳ ስፋት ያለው በሀገሪቱ ሁለተኛ ሰፊ ክልል የሚባል ነው። ሶማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስትን የሚያዋስኑ ጎረቤት ሀገሮች በምስራቅ እና በደቡብ ምስራቅ ሶማልያ፣ በደቡብ በኩል ኬንያ፣ በሰሜን ጅቡቲ ናቸው። በሀገር ውስጥ ደግሞ በሰሜን ምእራብ አፋር፣ በደቡብ ምእራብ ኦሮሚያ ያዋስኑታል።

የሶማሌ ክልል ኮሚዩኒኬሽን ኤጀንሲ መረጃ እንዳመላከተው ክልሉ 9 ዞኖች 93 ወረዳዎች እና 6 የከተማ አስተዳደሮች አሉት። የክልሉ የህዝብ ብዛት 5,318,000 ሲሆን 56% ወንዶች እና 44% ሴቶች እንደሆኑ ይገመታል። የክልሉ ነዋሪዎች በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች ይኖራሉ። 86% ከከተማ ውጭ ባሉ ገጠራማ ዞኖች እና ወረዳዎች የሚኖሩ ሲሆን 14% በከተማ ይኖራሉ። የክልሉ ህዝብ የኢኮኖሚ ምንጭ 40% ከብቶችን በማርባት (ግመል እና የቀንድ ከብቶች) 26% ግብርና፣ 14% ንግድ እና የተለያየ ስራ ፣7% ቋሚ ስራ የሌለው ወይም ተቀጣሪ ያልሆነ የህብረተሰብ ክፍል ይኖራል። የክልሉ ዋና ከተማ ጅግጅጋ ሲሆን 500,000 ህዝብ በላይ ይኖርበታል ተብሎ ይታሰባል።

በኢትዮያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት (1987፡42) አንቀፅ 39 ንኡስ አንቀፅ 2 መሰረት የክልሉ ኦፊሴልዊ የስራ ቋንቋ ሶማልኛ ሲሆን ተማሪዎች በዚሁ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እስከ 8ኛ ክፍል የተለያዩ የትምህርት አይነቶችን ይማሩበታል። በክልሉ ሶማልኛ ቋንቋ ከ 1ኛ ክፍል ጀምሮ እንደአንድ የትምህርት አይነት የሚሰጥ ሲሆን አማርኛ እና እንግሊዝኛ ቋንቋ ከ 3ኛ ክፍል ጀምሮ እንደአንድ የትምህርት አይነትነት ይሰጣሉ። እንግሊዝኛ እንደአንድ የትምህርት አይነት ከመሰጠቱ በተጨማሪ ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ የትምህርት ቋንቋ ሆኖ ያገለግላል። ቋንቋዎቹን ለማስተማር

የተመደበው የክፍለ ጊዜ ስርጭት ሲታይ አማርኛ እና ሶማልኛ እስከ 8ኛ ክፍል በሳምንት 3 ክፍለጊዜ ይሰጣል። እንግሊዝኛ እስከ 6ኛ ክፍል በሳምንት 3 ክፍለጊዜ የሚሰጥ ሲሆን 7ኛ እና 8ኛ ክፍል ወደ 4 ክፍለጊዜ ያድጋል። የክፍል ደረጃው አድጎ ሁለተኛ እና መሰናዶ ደረጃ ሲደርስ አማርኛ እና ሶማልኛ ቋንቋ በሳምንት 2 ክፍለ ጊዜ የሚሰጥ ሲሆን እንግሊዝኛ በሳምንት ውስጥ ባሉት ቀናት በሙሉ (5 ክፍለጊዜ) ይሰጣል።

በክልሉ ለማንበብ እና አንብቦ መረዳት ክሂል የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑን የተለያዩ ሁኔታዎች ያመላክታሉ። አንደኛው ዘመኑ ከሚፈቅደው ብቃት ተኮር የትምህርት አሰጣጥ (Competency Based Approch) ይልቅ ምክንያቱ የተለያየ ቢሆንም (በአንድ ክፍል የተማሪ ቁጥር ከልክ በላይ መብዛት፣ የመማሪያ ማስተማሪያ ክፍሎች አለመመቸት፣ የመምህራን ቅድመ ስራ እና በስራ ጊዜ ስልጠና እና የትምህርት ዝግጅት ማነስ፣ የመማሪያ ማስተማሪያ መፅሀፉት በብቃት አለመዳረስ ወዘተ) ተለምዷዊ የትምህርት አሰጣጥ መከተል (በምልከታ የተረጋገጠ)፣ በጅግጅጋ ከተማ በሚገኙ ሁሉም ትምህርት ቤቶች የተደራጀ ቤተመፅሀፍት እና ለንባብ የሚሆኑ መፅሀፍት አለመኖር፣ በከተማው ውስጥ ለህዝብ አገልግሎት የሚሆን ምንም አይነት የተደራጀ ቤተመፅሀፍት አለመኖር፣ ተማሪዎችን የሚሳትፉ ክበባት በተለይ ከማንበብ ጋር የተያያዙ ለምሳሌ የሚኒ-ሚዲያ፣ የጋዜጠኝነት፣ የስነፅሁፍ፣ የጥናትና ምርምር ክበብ ወዘተ አለመኖር፣ በተማሪዎች እና በአካባቢው ማህበረሰብ የንባብ ባህል አለመኖር እና አለመዳበር በዋናነት ይጠቀሳሉ። ከዚህ በተጨማሪ ሁሉም የመንግስት ትምህርት ቤቶች የትምህርት አቅርቦት በፈረቃ የተከፋፈ በመሆኑ ተማሪዎች በትምርት ቤት የሚያጠፉት ጊዜ አነስተኛ በመሆኑ ለማንበብ በአጠቃላይ ለትምህርት ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ እንደሆነ ይታያል።

ሌላው ሶማልኛ ቋንቋ ለክልሉ ተወላጆች የአፍመፍቻ ቋንቋ፣ የትምህርት ቋንቋ እና የክልሉ የስራ ቋንቋ ቢሆንም እስከአሁን ድረስ በመሰናዶ ትምህርት መርሀግብር ለ11ኛ እና 12ኛ ክፍል ተማሪዎች እንደአንድ የትምህርት አይነት መሰጠት ሲገባው እየተሰጠ አይደለም። ይህም ተማሪዎች በቋንቋቸው ማዳበር የሚገባቸውን የማንበብ ክሂል በሚገባ ማዳበር እንዳይችሉ እድል የነፈገ ነው።

1.9 የጥናቱ ውስንነት (ችግር)

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ተተኳሪ ተማሪዎች ለ 12 ሳምንት (16 ሰዓት) የተመረጡ የማንበብ ብልሃቶችን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ግልፅ በሆነ የማስተማር አቀራረብ እንዲማሩ ተደርጓል። ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ በመማራቸው ከቅድመልምምድ በተሻለ በድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤያቸው ጨምሯል። ለማንበብ ተግባር የቀረቡ የተለያዩ ውህድአሀዶችን አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው አዎንታዊ እና ጉልህ በሆነ መልኩ መጎልበቱ የጥናቱ ግኝት አመላክቷል። ከዚህ በተጨማሪ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ እያሸጋገሩ በመጠቀማቸው በየቋንቋው አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው እንዲጎለብት ከፍተኛ አስተዋፆ እንዳለው መረዳት ተችሏል።

ይሁን እንጂ በጥናቱ ተግባር ላይ ከዋለው የትምህርት መርሀግብር በበለጠ ለረጅም ጊዜ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ ቢሰጥ በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከተመዘገበው ውጤት በበለጠ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እውቀታቸው ከፍ እንዲል ሊያደርግ ይችላል። የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው በላቀ ደረጃ እንዲጎለብት አስተዋፆ ይኖረዋል። ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ጥናት ከታየው በጎላ መልኩ ተተኳሪ ተማሪዎች ከአንድ አዲስ ሁኔታ ወደሌላ አዲስ ሁኔታ ወይም ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ በመጠቀም አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው የበለጠ እንዲጎለብት ያስችላል። በመሆኑም ጊዜ የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አንድ ችግር ነው።

ተተኳሪ ተማሪዎች ለትምህርት የቀረቡትን የማንበብ ብልሃቶች በመማር ወቅት ለማንበብ ተግባር የቀረቡ ፅሁፎችን አንብበው የመረዳት ፍላጎታቸው መጨመር እና ከፍተኛ መነቃቃት እንዳሳዩ የጥናቱ ሂደት አመላክቷል። ይሁን እንጂ ለማንበብ ተግባር የቀረበን ፅሁፍ አንብቦ መረዳት ግላዊ እና ማህበራዊ ክንውን በመሆኑ ተተኳሪ ተማሪዎች የተረዱትን ለመምህራቸው እና ለክፍል ጓደኞቻቸው በአማርኛ ቋንቋ ለመግለፅ ሲቸገሩ ታይቷል። ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በሚገባ መጠቀም አለመቻላቸው በተማሪዎች ውጤት እና በጥናቱ ግኝት ላይ ተፅእኖ ሊኖረው ይችል ይሆናል።

ተማሪ ተኮር የትምህርት አቀራረብን በቋንቋ ክፍል ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ከሚያስፈልጉ ቅድመሁኔታዎች አንዱ በክፍል ውስጥ መደበኛ የተማሪዎች ቁጥር መጠን ነው፡፡ በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር ከሚገመተው መጠን በላይ ሲበዛ (Large Class Size) የመማር ማስተማር ሂደቱ ውጤታማ እንዳይሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡ በተለይ መምህራን በክፍል ውስጥ እንደልብ ተዘዋውረው ለማስተማር መቸገር፣ ተማሪ ተኮር የትምህርት አቀራረብን ተግባራዊ በማድረግ አብዛኛውን የክፍል ውስጥ ክንውን ተማሪዎች እንዲያከናውኑ ማድረግ አለመቻል፣ ማንበብ ግላዊ እና ማህበራዊ ክንውን እንደመሆኑ ተማሪዎች የተለያዩ ቡድኖችን በመመስረት ርስበርስ እንዲወያዩ፣ እንዲጠያየቁ፣ ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ (ፅብረቃ) በማድረግ ጠንካራ መስተጋብር እንዲፈጥሩ የማድረግ ሁኔታን ሊያውክ ይችላል፡፡ በክፍል ውስጥ የተማሪ ቁጥር በበዛ መጠን መተፋፈግ እና ከፍተኛ ሙቀት ሊፈጠር የሚችል በመሆኑ የተማሪዎችን እና የመምህሩን ምቾት ይነሳል፡፡ በጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ባሉ የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ያጋጠመው የተማሪ ቁጥር መብዛት በጥናቱ ግኝት ላይ አሉታዊ አስተዋፆ ሊኖረው ይችላል፡፡

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አላማ እንደተንፀባረቀው የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ ለተተኳሪ ተማሪዎች በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ቀርቧል፡፡ የቀረበው የማንበብ ብልሃት ትምህርት በተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም፣ አንብቦ የመረዳት ውጤት ላይ፣ ከሶማልኛ ወደአማርኛ/ ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ በመጠቀማቸው አንብቦ የመረዳታቸው ውጤት መጎልበት አለመጎልበቱን ጥናቱ መርምሯል፡፡ በጥናቱ ይህን አላማ ለማሳካት የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ እና ምዘናው በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ተሰጥቷል፡፡ በዚህ ሂደት የጥናቱ አቅራቢ ሶማልኛ ቋንቋን በሚገባ መጠቀም አለመቻሉ ብዙ ተቸግሯል፡፡ ይህም በጥናቱ ግኝት ላይ ተፅእኖ ሊኖረው ይችላል፡፡

1.10 የቁልፍ ፅንሰሀሳቦች ብያኔዎች

የማንበብ ብልሃት፡- በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ የማንበብ ብልሃት ማለት ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የተሰጠን ውህድአሀድ አንብበው ለመረዳት በንቃተህሊና ሆንብለው የሚጠቀሙበት ዘዴ፣ እቅድ፣ የአእምሮ ተልኳዊ አሰራር ወይም ቅደምተከተል ነው። የማንበብ ብልሃት ተማሪዎች የቀረበላቸውን ፅሁፍ አንብበው ለመረዳት ብቻ ሳይሆን የፅሁፉ ሀሳብ ባልገባቸው ጊዜ (ችግር በገጠማቸው ጊዜ) ምን ማድረግ እንዳለባቸው በመገንዘብ እርምጃ የሚወስዱበት መንገድ ነው።

አንብቦ መረዳት፡- በዚህ ጥናት አንብቦ መረዳት የሚለው ሙያዊ ቃል የሚገልፀው ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር ከቀረበላቸው ፅሁፍ ጋር መስተጋብር በመፍጠር የፅሁፉን ፍቺ መለየት እና በአእምሯቸው ውስጥ መልሰው በማዋቀር እንዲሁም ከቀደመ እውቀታቸው ጋር በማገናኘት ትርጉም ያለው ሀሳብ የሚያዋቅሩበት ውስብስብ አእምሯዊ ሂደት ነው።

የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ፡- የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ለማንበብ ተግባር የቀረበላቸውን ፅሁፍ አንብበው ለመረዳት ሲቸገሩ ወይም ይበልጥ ለመረዳት ባሰቡ ጊዜ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው (ሶማልኛ) ወደሁለተኛ ቋንቋ (አማርኛ) ወይም በተቃራኒው የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ መጠቀምን ይገልፃል።

የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር ፡- በዚህ ጥናት የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር (Explicit Instruction) ማለት ለተማሪዎች የትምህርቱ አላማ የሚነገርበት፣ የማንበብ ብልሃቶችን ምንነት (ብያኔ)፣ ጠቀሜታ፣ አይነት እና ተግባራዊ አገልግሎት በዝርዝር የሚቀርብበት ነው። የትምህርት አቀራረቡ ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን መቼ፤ የት፣ ለምን እና እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው በማስገንዘብ ብልሃቶችን በተግባር እንዲጠቀሙባቸው የማድረግ ክንውኖችን ያካተተ ነው። በትምህርት አቀራረቡ ተማሪዎችን በንቃት በማሳተፍ በጥንድ እና በቡድን በመሆን በትግግዝ የተለያዩ ትምህርታዊ ተግባራትን በማከናወን የተረዱትን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ነው።

ምዕራፍ ሁለት

የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት

አንብቦ መረዳት ከፅሁፍ ቋንቋ ጋር መስተጋብር በመፍጠር በአእምሮ ውስጥ በአንድ ጊዜ ትርጉምን ፈልጎ ማውጣት እና መልሶ መገንባት ነው (Reading Study Group /RAND/ 2002)። ይህን ለማከናወን አንባቢ፣ ውህድአሀድ፣ የማንበብ አላማ (ግብ) እና የማንበብ ብልሃት መስተጋብር ይፈጥራሉ። ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማንበብ እና አንብቦ ለመረዳት ምን ማድረግ ያስፈልጋል የሚለው ጥያቄያዊ ሀሳብ የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ቁልፍ ጉዳይ ወይም ዋነኛ ትኩረት ነው። ይህ ምዕራፍም ጥናቱ የተነሳበትን አላማ ለማሳካት በሚያስችል መልኩ ትኩረት የተደረገባቸውን ንድፈሀሳባዊ እና ተዛማጅ ፅሁፎች በዝርዝር አካቷል። ምዕራፉ በውስጡ የያዛቸው ዋና ዋና ንድፈሀሳባዊ ጉዳዮች ማንበብ እና አንብቦ መረዳት፣ ጥናቱ የሚከተለው ትውረታዊ ማእቀፍ፣ የመጀመሪያ ቋንቋ እና ሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ግንኙነት፣ የማንበብ ብልሃት ምንነት እና መገለጫዎች፣ የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ምንነት እና መገለጫዎች፣ የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ ማስተማር ምንነት እና የማስተማር ሂደቱን የሚያመላክቱ ቅደም ተከተሎች ናቸው።

2.1. ማንበብ እና አንብቦ መረዳት

2.1.1 ማንበብ

ማንበብ በክፍል ውስጥ አካዳሚያዊ ለሆነ ተግባር እንዲሁም ከክፍል ውጪ የህይወት አቅጣጫን መስመር ለማስያዝ እና ውጤትን ለማስመዝገብ የሚያገለግል ወሳኝ ክሂል ነው። እንደ Grabe (2009)፣ Carrell (1998) አገላለፅ ቀደም ሲል ማንበብ ፊደላትን እና ቃላትን መለየት ብቻ ያለበት ፍዝ ሒደት ተደርጎ ይወሰድ ነበር። ይህ በተለይ በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ትምህርት አሰጣጥ ላይ ጎልቶ የሚታይ አስተሳብ ነበር። አስተሳሰቡ በተለያየ ዘመን ማንበብ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ካንፀባረቁት አመለካከት ጋር የተያያዘ ነው።

Tracey and Morrow (2006:22) እንዳስረዱት ማንበብን ማጥናት የተጀመረው በቀደምት መዋቅራውያን ስነልቦና ሲሆን ጥናቱም የመዋቅራዊነት ትውረታዊ ማእቀፍ ከመሞከር ጋር

የተገናኘ ነበር። መዋቅራዊነት በስነልቦና ትምህርት ቤት የመጀመሪያው አስተምህሮ የነበረ ሲሆን አመለካከትን (Perception) በማጥናት የአእምሮን መዋቅር ለማስረዳት ጥረት ያደርጋል። በወቅቱ ማንበብ የሚጠናው ከአመለካከት የጥናት ንድፍ ጋር ተያይዞ ሲሆን የሚያንፀባርቀው ራሱን ማንበብን እና ሂደቱን ሳይሆን አጠቃላይ ስነልቦናዊ ተግባሩን ነበር። Tracey and Morrow (2006:23) Venezky (1984)ን ጠቅሰው እንደገለፁት ቀደም ሲል (ከ19ኛው ክፍለ ዘመን በፊት) ማንበብ ላይ ጥናት ያደርጉ የነበሩ ወገኖች ትኩረታቸው ተማሪዎች ፊደል እና ቃላትን የመለየት ችሎታ፣ የቀረበው ፅሁፍ ተነባቢነት እና ፅሁፉን ለማንበብ ትኩረት የማድረግ ቆይታ ወዘተ ነበር። ቀስበቀስ ተማሪዎች ትርጉም ያለው ቃላት ውስጥ ያሉትን ፊደላት የማንበብ ፍጥነት ትርጉም በሌላቸው ቃላት ውስጥ ካሉት ፊደላት የማንበብ ፍጥነት፣ በአረፍተነገር ውስጥ ያሉትን ቃላት የማንበብ ፍጥነት አረፍተነገር ውስጥ ያልተካተቱትን ቃላት ከማንበብ ፍጥነት ጋር በማነፃፀር ማጥናት ታይቷል። በ19ኛው ክፍለ ዘመን በተለይ በ1950ዎቹ አካባቢ አእምሮታዊ የማብላላት ትውረታዊ አተያይ (Cognitive Processe Theory) መጎልበት ከጀመረ በኋላ ተማሪዎች በማንበብ ሂደት የአይን እንቅስቃሴ (ትኩረትን ሊበትን የሚችል ባልተለመደ መልኩ አይንን በፍጥነት ማንቀሳቀስ / Saccade)፣ መጣቀስ (ጣትን እያመላከቱ ማንበብ)፣ የማንበብ ፍሰት እና ቀጣይነት፣ የአይን እንቅስቃሴ እና የድምፅ አብሮ የመሄድ ምጣኔ (ዝም ብሎ በማንበብ ሂደት የከንፈር እንቅስቃሴ)፣ የማንበብ ፍጥነት፣ ከፊልድምፀት፣ የትርጉም ተፈጥሮ፣ ፍጥነት እና ቅላፄ ጠብቆ ማንበብ እንዲሁም ማንበብን የማስተማር ታሪክ በመፈተሽ ያለን አመለካከት ለማነፃፀር ጥረት ተደርጓል።

ቀደም ሲል የተሰሩት እነዚህ ጥናቶች የሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ፍዝ የሆነ ፊደላትን በመጠቀም የምልክት መልዕክትን መተርጎም እና ቃላትን በመለየት ፍቺን መገንባት ወይም ፍጥነት እና ቅላፄ ያለበት ሒደት እንደሆነ አንፀባርቀዋል። ነገር ግን ማንበብ በውህድ አሀድ፣ በአንባቢው የቀድመ እውቀት፣ በማንበብ ሁኔታዎች እና በማንበብ አውድ መካከል ያለ ጠንካራ መስተጋብራዊ ሒደት ሲሆን በሒደቱ ቃላትን መለየት ብቻ ሳይሆን አንብቦ መረዳት ጭምር ያለበት ውስብስብ አእምሯዊ ሒደት ነው።

ማንበብን በተመለከተ Hittleman (1998፡7) እንደገለፁት ማንበብ ድምፅን ከመለየት አንስቶ ትርጉምን እስከማዋቀር ድረስ በመዝለቅ ቃላት የተሸከሙትን ሀሳብ፣ ስሜት፣ እውቀት እና ራእይ ማስተዋል፣ መረዳት እና መገምገም ያለበት ውስብስብ አእምሯዊ

ሂደት ነው ሲሉ Carrell (2006፡12) በበኩላቸው ማንበብ ውስብስብ አእምሯዊ ሒደት የሚንፀባረቅበት በፀሐፊ የቀረበን ፅሑፍ ሐሳብ (ስሜት) ለመለየት፣ ለመገንዘብ (ለመረዳት)፣ ለመተርጎም እና ለመተንተን አካላዊ፣ አእምሯዊ እና ስሜታዊ ጉዳዮችን ያካተተ መስተጋብራዊ ሂደት ነው ብለውታል፡፡

Kong (2006:19) የተወሰኑ ፀሀፊዎችን ብያኔ ጠቅሰው እንደገለፁት ማንበብ ከፊደል ወደድምፅ፣ ከድምፅ ወደትርጉም የሚሸጋገር አንድዬ አቅጣጫ (Unidirectional) ሂደት ያለው ክሂል ነው (Gough 1972)፣ ማንበብ ለቅልጣፌ (ለስላጤ) (Automaticity) ትኩረት በመስጠት ትውስታን ተግባራዊ የሚያደርግ መስመራዊ ሂደት ነው (Gough et al. 1974)፣ ማንበብ ከፊደል አጣጣል (ቅርፅ) እና ከድምፅ እውቀት ይልቅ የአገባብ እና የትርጉም እውቀት የሚያስፈልገው የስነልቦና ግምት ጨዋታ ያለበት ክሂል ነው(Goodman 1967)፣ ማንበብ ተጣጣፊ (ተለማጭ) ሂደት ተግባራዊ የሚሆንበት አውዳዊ ሁኔታን መሰረት ያደረገ ብዛት ያለው የመረጃ ምንጭ ነው (Rumelhart 1977) ብለውታል፡፡

Grabe (2009፡2) የማንበብን ምንነት በትክክል ለመረዳት የጥሩ አንባቢዎችን የማንበብ ባህሪ ማየት ወይም የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማንሳት ተገቢ ነው ይላሉ፡፡ ጥያቄዎቹም፡-

- ጥሩ አንባቢዎች በማንበብ ወቅት ምን ያደርጋሉ?
- ጥሩ አንባቢዎች ምን አይነት ሒደት ይከተላሉ?
- ጥሩ አንባቢዎች የማንበብ ብልሃቶችን እንዴት ይጠቀማሉ?
- በአጠቃላይ የማንበብን ፅንሰ ሐሰብ ከመረዳት አንፃር ጥሩ አንባቢዎች የሚከተሉት ሒደት ምን ጠቀሜታ አለው? ወዘተ የሚሉ ናቸው፡፡

የማንበብን ምንነት በተመለከተ ከላይ ብያኔ በሰጡት ፀሀፊዎች ዘንድ የሚንፀባረቀው ተመሳሳይ አቋም ማንበብ አንባቢ ከውህድአሀድ ጋር በተለያየ ደረጃ በሚፈጥረው መስተጋብር የውህድአሀዱ ፍቺ ስሜት እንዲሰጥ አካላዊ፣ አእምሯዊ እና ስነልቦናዊ ተግባራት የሚከናወንበት ውስብስብ ሂደት መሆኑ ነው፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ትምህርት ግብም ለማንበብ መማርን በማሳደግ ወደለመማር ማንበብ መቀየር ነው ::

2.1.2 አንብቦ መረዳት

የማንበብ ትውረት መሰረታዊ ትኩረት ተማሪዎች በውህድ አሀድ ውስጥ ላሉ ቃላት ትርጉም ከመስጠት በላይ ከፍተኛ የክህሎት ደረጃቸውን እንዲያዳብሩ በማድረግ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸውን ማሻሻል ነው። እንደ Rowell and Palmer (2007)፣ Snow/ Reading Study Group (RAND) (2002) እና Economic and Social Research Council (E.S.R.C) (2000) አገላለፅ አንብቦ መረዳት በፅሁፍ ከቀረበ ሀሳብ ጋር መስተጋብር በመፍጠር ፍቺን ፈልፍሎ ማውጣት እና መልሶ የማዋቀር ሒደትን የሚያስተናግድ ውስብስብ አእምሯዊ ሂደት ነው። ይህም ሁሉንም የማንበብ ሒደት መሰረታዊ ነገሮች **(ፊደልን እና ቃላትን መለየት፣ ቅላፄ፣ የሀሳብ ፍሰትን (ግላፄን) ጠብቆ ማንበብ እና አንብቦ መረዳት)** በጋራ በማሳተፍ አንባቢው የውህድአሀዱን አጠቃላይ ምስል (ይዘት እና ቅርፅ) እንዲገነዘብ ማድረግ ነው።

በአንብቦ መረዳት አውድ ሁለት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል። ይኸውም ላዕላይ አቀራረብ ወይም የምልክት መልእክቶችን መተርጎም ላይ ማተኮር እና ታህታይ አቀራረብ ወይም በፀሐፊው የተላለፈው ዋነኛ ጉዳይ ምን እንደሆነ መረዳት ላይ ማተኮር ናቸው። ታህታይ አቀራረብ ከላዕላይ አቀራረብ በተሻለ መልኩ የፀሐፊውን መልእክት የበለጠ ለመረዳት ይጠቅማል (Snow 2002:11)።

ውጤታማ አንብቦ መረዳት ቃላትን በሚገባ ማንበብ እና ትርጉማቸው ላይ መድረስ፣ የእያንዳንዱን ሐረግ እና ዐረፍተነገር ስሜት ማወዳደር እና መረዳት ይታይበታል። ለማንበብ ተግባር የቀረበን ውህድአሀድ ትርጉም በሚሰጥ መንገድ ለመረዳት አንባቢዎች የዐረፍተነገሮችን ትርጉም ማቀናጀት እና ከባቢያዊ የሐሳብ ቅደም ተከተል (Local Coherence) መፍጠር ይጠበቅባቸዋል። አንባቢዎች መረጃ እንዴት በአንድ ላይ ቅንጅት አንደሚፈጥርም መገንዘብ አለባቸው። መረጃ በአንድ ላይ በማቀናጀት ጠንካራ ሐሳብ የመስጠት ሁኔታ ሁለንተናዊ (አጠቃላይ) የሀሳብ ቅደም ተከተል (Global Coherence) ነው። ከባቢያዊም ሆነ አጠቃላይ የሀሳብ ቅደም ተከተል አንባቢዎች የቀደመ እውቀታቸውን እና ሐሳባቸውን ከረጅም ጊዜ ትውስታ በማንቃት፣ በማስተባበር እና በመጠቀም በእያንዳንዱ ዝርዝር ሐሳብ ስሜት ሰጪ ሁኔታን ይፈጥራሉ (Economic and Social Research Council /E.S.R.C/ 2000)። በአንብቦ መረዳት ወቅት

ተማሪዎች የውህድአሀድን ይዘት ይተነትናሉ፤ ያቀናጃሉ፤ ይገመግማሉ፤ ይሔሳሉ፤ መረጃን ፈልፍለው ያወጣሉ፤ ወይም ከቀረበው መረጃ በመነሳት ይወስናሉ፡፡ ተማሪዎች በአነበቡት ውህድአሀድ መሰረት በብዝሀ ትርጉም ላይ በራሳቸው አእምሮ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሰዎች አእምሮ ውስጥ ያለውን በማሰብ ይወያያሉ፡፡ በዚህም ሒደት ደስተኛ ይሆናሉ፡፡

አንብቦ መረዳት ተማሪዎችን የቋንቋ እና የቃላት እውቀት ከፍ በማድረግ ለአዲስ መረዳት እና ለአርቆ ማስተዋል ያዘጋጃቸዋል፡፡ ውጤታማ (ጠንካራ) አንባቢዎች የተለያዩ ውህድአሀዶችን አንብበው ለመረዳት በተደጋጋሚ የማንበብ ብልሃቶችን አቀናጅተው ይጠቀማሉ (Pressley 2002፡22)፡፡ እንደፀሀፊው ገለፃ ጠንካራ አንባቢዎች አንብቦ መረዳታቸውን ለማገዝ የተለዩ ብልሃቶችን እንዴት አቀናጅተው ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው ያውቃሉ (በተለይ ውህድአሀዱ ወይም መረጃው አስቸጋሪ ሲሆን)፡፡

እንደ Nation (2005)፣ Economic and Social Research Council /E.S.R.C/ (2000) አገላለፅ በውህድአሀድ ውስጥ ያሉትን ሁኔታዎች እና ጉዳዮች ለመግለፅ በተለይ በውህድአሀዱ ውስጥ ያለውን ታሪካዊ አካሄድ ለመገንባት በሁነቶች፣ በገፀባህርያት፣ በተፋላሚዎች፣ በግቦች እና በመረጃዎች መካከል ያለውን ምክንያታዊ ግንኙነት ለመረዳት ውጤታማ በሆነ መንገድ አንብቦ መረዳትን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህን አንብቦ የመረዳት ክህሎት የሚገልፅ ሞዴል አእምሯዊ ሞዴል ወይም ሁኔታዊ ሞዴል ነው፡፡ አእምሯዊ ሞዴል ከባቢያዊውን አለም የሚወክል፣ በከባቢ አለም የተለያየ ክፍል እና ግለሰብ ተግባራትን ለመፈፀም ባለው ማስተዋል እንዲሁም ውጤት መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ አእምሯዊ ሞዴል የተሻለ በማሰብ ለመማር፣ ችግርን ለመፍታት (እንደግለሰብ የችግር መፍቻ ቅደም ተከተል /personal algorithm) እና ተግባርን ለማከናወን የሚረዳ ባህሪ ነው (Clear 2010)::

ተማሪዎች ይህን አንብቦ የመረዳት ሞዴል በአግባቡ በተጠቀሙ ቁጥር የመገንዘብ ችሎታቸው ከፍ ይላል፡፡ ዝቅተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ውህድአሀዱን አንብበው ከመረዳት ይልቅ አብዛኛውን ጊዜ በቃላት ትክክለኛነት ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ ዝቅተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች መረጃን ፈልፍሎ ማውጣት ወይም መረጃን መሰረት በማድረግ ውሳኔ መስጠት እና

ከውሀድአሀዱ የተገኘውን መረጃ የማቀናጀት ድክመት ያለባቸው በመሆኑ ደካማ ልዕለአዕምሯዊ ክሂል (Weak Metacognition skill) ይታይባቸዋል (Zhang 2008)።

አንብቦ ለመረዳት የአንባቢው መገንዘብ፣ አንባቢው የሚገነዘበው ውህድ አሀድ፣ አንብቦ ለመረዳት ያለው ክንውን እና አንባቢው አንብቦ ለመረዳት የሚጠቀምበት ብልሃት ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው (Karami 2008:2)። አንብቦ ለመረዳት የአንባቢው የማንበብ ክንውን፣ አላማ፣ ሒደት እና ቅደም ተከተልም ግምት ውስጥ ይገባሉ። እነዚህ መሰረታዊ ጉዳዮች የሚከሰቱት በትልቅ ማህበረባህላዊ አውድ ውስጥ ነው። አንባቢው ከነዚህ መሰረታዊ ነገሮች ጋር በሚፈጥረው መስተጋብር የማንበብ ሒደቱ ቅርፅ ይይዛል። አንባቢን ከማንዛቤ በምናስገባበት ወቅት አብሮ የሚነሳው ሌላው ጉዳይ የአንባቢው ብቃት፣ ችሎታ፣ እውቀት እና ልምድ ነው።

አንብቦ መረዳት ቅድመማንበብ፣ የማንበብ ጊዜ እና ድህረማንበብ ክንውኖችን ያስተናግዳል። እነዚህ አነስተኛ የማንበብ ጊዜያት ለአንብቦ መረዳት ወሳኝ ቅደም ተከተላዊ ክንውኖች ናቸው። ምክንያቱም አንባቢው በማንበብ ወቅት ያመጣውን ወይም የተጠቀመበትን የቀደመ እውቀት እና በአነበበው ፅሁፍ ውስጥ ባገኘው አዲስ እውቀት መካከል ያለውን ልዩነት ለማየት ይጠቅማል። እያንዳንዱ የማንበብ ክንውን የራሱ የሆነ አነስተኛ የእድገት ሒደት አለው። በሒደቱ አንባቢው አእምሯዊ (ግንዛቤያዊ) ብቃቱ ሲያጎለብት እና ተጨማሪ ልምድ ሲያገኝ እንዲሁም የበለጠ አስቸጋሪ ውህድአሀድ ሲገጥመው እና ሲታገል ከትምህርቱ ይጠቀማል (Snow 2002)።

2.2 የማንበብ ሒደት ሞዴሎች

አንድን የቀረበ ውህድአሀድ በአእምሮ ውስጥ በማብላላት አንብቦ ለመረዳት የተለያየ የማንበብ ሒደት ሞዴሎች ተግባራዊ ይሆናሉ። የማንበብ ሒደት ሞዴል ተብለው በዋናነት የሚጠቀሱት የታች ላይ (Bottom-up)፣ ላይ ታች (Top-down) እና መስተጋብራዊ (Interactive) ሞዴሎች ናቸው (Urquhart & Weir 1998፣Cellce- Murcia 1991)።

2.2.1 የታች ላይ ማንበብ ሒደት ሞዴል

ባህላዊ የታች ላይ ማንበብ ሒደት ሞዴል በ1950ዎቹ አካባቢ በባህርያውያን ስነአእምሯዊ ትውረት ተፅእኖ የተፈጠረ የማንበብ ሂደት ሞዴል ነው። በባህርያውያን ትውረታዊ አተያይ

መማር የባህሪ ምስረታ ሲሆን ድግግሞሽ፣ ማነቃቃት እና ምላሽ መስጠት (የሚታይ ተግባር) ለቋንቋ መማር (መልመድ) ወሳኝ ተግባራት እንደሆኑ ያስረዳል (Ertmer & Newby 2013:48፣ Omaggion 1993:45)።

በባህርያውን አተያይ የማንበብ ሂደት ከእይታ መረጃ (ከተሰጠ ምንባብ ፊደል እና ቃላትን መለየት) አንባቢን በማነቃቃት ፍቺን መልሶ ማዋቀር እና መገንዘብ ያስችላል የሚል ነው። በታች ላይ ማንበብ ሒደት ሞዴል ውህድአሀድ ውስጥ የቀረበውን ፅሁፋዊ ምስል ለማንበብ እና ለመተርጎም ከመስመራዊ እድገት የሚጀምር እና በስነትርጉም ውክልና የሚጨርስ ተደርጎ ይወሰዳል። Ling (2011፡9) ሞዴሉ መስምራዊ ሒደት እድገት የሚታይበት ሲሆን እድገቱም ከቅንጣት ስነድምፃዊ ደረጃ (Morphophonemic Level) እስከ ስነአገባብ ከዛም ቀስበቀስ ወደ ስነትርጉም ደረጃ የሚያድግ እንደሆነ ያስረዳሉ። በዚህ ሞዴል አንባቢው የትርጉም አሻሚነትን የሚያሻሽለው ወደቅንጣት ስነድምፅ እና ስነአገባብ ደረጃ የመመለስ ውሳኔ ላይ በመድረስ ነው።

የታች ላይ ማንበብ ሒደት ዝቅተኛ ደረጃ የማንበብ ሒደት (Lower Level Reading Process /Data Driven) በመባል የሚገለፅ ሲሆን ውህድአሀድ ተኮር ነው (Zainal 2011፣ Celce-Murcia 1991)። በዚህ ሞዴል አንባቢዎች ከቀኝ ወደግራ ፊደል በፊደል ይቆጥራሉ (ይለያሉ)፣ በመቀጠል ፊደላቱን በመገጣጠም የቃላትን ትርጉም በአጭር ጊዜ ትውስታቸው ውስጥ ያጠራቅማሉ። የቀረበው ውህድአሀድ የተሟላ ትርጉም እንዲሰጥ እና ከፀሐፊው ጋር መስተጋብር ለመፍጠር እንዳያስቸግራቸው አንባቢዎች ውህድአሀዱን በተለያዩ ክፍሎች ይከፋፍላሉ።

እንደ Ling (2011፡9-10) ገለፃ Kintsch (1988) አንብቦ የመረዳት መዋቅራዊ ቅንጅት ሞዴልን (Construction Integration Model of Reading Comprehension) ያስተዋወቁ ናቸው። ሞዴሉ የማንበብ ሒደትን በሁለት መንገድ ያየዋል። ይኸውም የትርጉም ውክልናዎች ከቋንቋ ግብአት ይዋቀራሉ፤ ይህም የታች ላይ ወይም ከባቢያዊ ክፍሎችን ከአንባቢ የቀደመ እውቀት ጋር ማስተሳሰር እና ከውህድአሀዱ ውክልና ጋር ቅደም ተከተላዊ ቅንብር መፍጠር ነው። የማንበብ መነሻ ሒደት የታች ላይ ሞዴል መሆን እንዳለበትም ያምናሉ። የታች ላይ መስመራዊ ሒደት ትውረት ተቀባይነት ያጣው የማንበብ ማንኛውም ከፍተኛ ደረጃ ሒደት መሰረታዊ ነገሮችን ከፊደላት ጋር መስተጋብር በመፍጠር መረጃ

ይገኛል የሚል ሐሳብ ላይ በማተኮሩ ነው። የታች ላይ ማንበብ ሒደት ሞዴል ትችት በገጠመው ወቅት የላይ ታች ሞዴል ተክቶታል።

2.2.2 የላይ ታች ማንበብ ሒደት ሞዴል

የላይ ታች ሞዴል ከታች ላይ ሞዴል ክፍተት በመነሳት የተፈጠረ ሲሆን የስነአእምሯዊ ስነልሳን ሞዴል ላይ ተመስርቶ የተፈጠረ ነው (Ling 2011፣ Urquhart & Weir 1998፣ Cellce- Murcia 1991)።

Ling (2011:9) እንደገለፁት የዚህ ትውረት ምንጭ Goodman (1988) ለማንበብ ከሰጡት ብያኔ "ማንበብ የስነአምሯዊ ስነልሳን ግምት ጨዋታ ነው" የተቀዳ ነው። ሞዴሉ የሚያንፀባርቀው አንባቢ የቀደመ እውቀቱን ወይም ልምዱን መሰረት በማድረግ ስለውህድ አሀዱ መገመት የሚችልበት ሒደትን ነው። የላይ ታች ማንበብ ሒደት ሞዴል ፅንሰ ሐሳብ ተኮር ማንበብ ሞዴል (Concept Driven Reading Model) በመባል የሚታወቅ ሲሆን በአንብቦ መረዳት የአንባቢ የቀደመ እውቀት ያለው ጠቀሜታ ላይ ትኩረት ያደርጋል።

የላይ ታች ሞዴል አንባቢዎች የስነአገባብ እና የስነትርጉም እውቀታቸውን በመጠቀም በውህድአሀዱ ፅሁፋዊ ፊደሎች ላይ ጥገኛ መሆንን ለመቀነስ ያስችላል። አንባቢዎች የማንበብ ብልሃታቸውን እና የማንበብ ክሂላቸውን በመጠቀም ፀሐፊው ምን እንዳለ እና መረጃዎቹ ምን እንደሚያስተላልፉ ፈልፍሎ ለማውጣት ይጠቅማል። በዚህ ሞዴል አንባቢዎች በውህድአሀድ ውስጥ ያሉትን እያንዳንዱን ፊደላት እና ቃላትን መለየት እና ማስረዳት (መተንተን) አይጠበቅባቸውም። ይልቁንም የቀደመ እውቀታቸውን መሰረት በማድረግ ትርጉምን ይገምታሉ። ሞዴሉ በግልፅ ትኩረት የሚያደርገው ትርጉምን በመገንባት እንጂ በውህድአሀዱ ውስጥ የሚገኙ ነጠላ ቃላትን ወይም በቃላት የተገነቡ ሐረጎችን መለየት አይደለም (Khaokaew 2013)።

Ling (2011፡10) Smith (1973)ን ጠቅሰው እንደገለፁት ማንበብ ከስነልቦናዊ ስነልሳን እይታ አንፃር ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ይንፀባረቅበታል። አንደኛው በእይታ ወይም በፅሁፋዊ ግብአት (ታች ደረጃ) እና እይታ አልባ ወይም እንደ Smith አጠራር ከአይን ብሌን በስተጀርባ (Behind the Eyeball) ወይም የቀደመ እውቀት (ከፍተኛ ደረጃ) ግብአት መካከል ግንኙነት የለም የሚል ነው። Ling (2011፡11) አያይዘው እንደገለፁት ከእይታ አልባ ይልቅ በእይታ ግብአት ላይ ብዙ መተማመን በእይታ ስልት ላይ ጫና መፍጠር ብቻ ሳይሆን ትርጉምን

የማጣት ምክንያት ነው። በማመጣጠን መላምት ፅንሰ ሀሳባዊ ትውረት (Concept of the Compensatory Hypothesis) መሰረት በታች ላይ እና በላይ ታች ማንበብ ሂደት ሞዴል መካከል ሚዛናዊ የሆነ ተመጣጣኝነት ቢፈጠር ጠቃሚ ነው። በእይታዊ ግብአት ከልክ በላይ ባለ ጫና ምክንያት በአደገኛ ሁኔታ የተለጠጠ የማገናዘቢያ (የመስሪያ ማስታወሻ) እና ስልት ትኩረት የተደረገባቸው ነጥቦች ናቸው። የቀደመ እውቀት በእይታዊ ግብአት አንብቦ ለመረዳት ቅድመ ሁኔታ እና ወሳኝ ነው።

የላይ ታች ማንበብ ሒደት ሞዴል ጠቀሜታው ከፍተኛ ቢሆንም የዝቅተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ ሒደት ሁለትዮሻዊ መስተጋብርን በአንድነት ማስኬድ ላይ ትኩረት አለማድረጉ በዋናነት የሚጠቀስ ክፍተት ነው። የሁለተኛ ቋንቋ አንባቢዎች በሞዴሉ በመጠቀም በውህድአሀዱ ውስጥ ያሉት ቃላት እና ዐረፍተነገሮች ላይ የበለጠ ትኩረት ማድረግ ባለመቻላቸው አንብበው ለመረዳት ይቸገራሉ። ከዚህ በተጨማሪ አንባቢዎች በውህድአሀድ ውስጥ ያሉት ፊደላት እና ቃላት ላይ ትኩረት መስጠት ከተቸገሩ አንብቦ መረዳታቸው ግምታዊ ጨዋታ ብቻ ይሆናል (Zainal 2011:10)። ይህን እጥረት በመገንዘብ የታች ላይ እና የላይ ታች ማንበብ ሒደት ሞዴልን በማቀናጀት መስተጋብራዊ የማበብ ሞዴል ተከሰተ።

2.2.3 መስተጋብራዊ የማንበብ ሒደት ሞዴል

የታች ላይ እና የላይ ታች ማንበብ ሒደት ሞዴሎች የገጠማቸውን ክፍተቶች ለመሙላት መስተጋብራዊ ሞዴል መከሰት ችሏል። የሞዴሉ ስያሜ እንደሚያመለክተው በዋናነት የማንበብ ሒደት የታች ላይ እና የላይ ታች ሞዴሎችን በማጣመር እና መስተጋብር በመፍጠር የተመሰረተ ነው። ሞዴሉ ከሌሎች በተሻለ መልኩ ሚዛናዊ የማንበብ ሒደትን የሚያንፀባርቅ ነው (Ling 2011፣ Zainal 2011)።

Carrell (1998:27) እና Rumelhart (1994፡588) በየተነሱበት ዘመን እንዳንፀባረቁት መስተጋብራዊ የማንበብ ሒደት ሞዴል የተለያዩ እውቀቶች መስተጋብር እንዲፈጥሩ የሚፈቅድ ውህደሞዴል ነው። ሞዴሉ የተለያየ ምንጭ ያላቸውን እውቀቶች በአንድ ቦታ ላይ በአንድነት በማምጣት እና በተመሳሳይ ሁኔታ ሁሉንም የእውቀት ምንጮች ተግባራዊ በማድረግ የማንበብ ሒደቱን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ነው። ይህ ሞዴል የታች ላይ እና የላይ ታች ማንበብ ሒደት ሞዴሎችን አንፃራዊ በሆነ መልኩ ርስበርሳዊ ትስስር እንዲኖራቸው ያደረገ ነው። ሞዴሉን በሚያራምዱ ወገኖች እይታ በናሙናነት የተመረጠው

ውህድአሀድ ትርጉም የሚከሰተው በአንባቢ የቀደመ እውቀት (በአንባቢው አእምሮ ውስጥ በተጠራቀመ እውቀት) እና በፅሁፍ ቋንቋ መረጃ መካከል በሚፈጠር መስተጋብር ነው። በዚህ ሞዴል አንባቢ ፍዝ በሆነ መንገድ መረጃ የሚቀበል ሳይሆን ንቁ፣ መረጃ አሳሽ እና መረጃውን እንደገና በራሱ አእምሮ የሚያዋቅር ነው ።

በዚህ ሞዴል የማንበብ ሂደት ከታች ላይ እና ከላይ ታች ደረጃዎች የተገናኘውን ብዛት ያለውን የእውቀት ምንጭ በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲዋሀድ ያደርጋል። ሞዴሉ በማመጣጠን መላምት አንባቢ በአንድ የማንበብ ሒደት ደከም ያለ ቢሆን ለምሳሌ ቃላትን በመለየት (በዝቅተኛ ደረጃ ሒደት) የቀደመ እውቀት (የከፍተኛ ደረጃ ሒደት) በመጠቀም ድክመትን ለማስወገድ እና ለማንሰራራት እድል ይሰጣል። በሞዴሉ የሁለተኛ ቋንቋ አንባቢዎች ቃላትን፣ ስነአገባብን፣ ስነትርጉምን እና የጋራ እውቀትን በሚገባ መጠቀም ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የማንበብ ተግባራትን ለመጨረስ ወይም የተለያዩ የማንበብ አላማዎችን ለማከናወን የማንበብ ብልሃትን በአግባቡ በመጠቀም የማንበብ ክሂላቸውን ራሳቸው ማጎልበት እንዳለባቸው ያበረታታል (Carrell 1998)። በዚህ ጥንታዊ ፅሁፍ የማንበብ ብልሃት ትምህርት በሚቀርብበት ወቅት ተማሪዎች በንቃት በመሳተፍ ጠንካራ መስተጋብር እንዲፈጥሩ የማድረግ አላማ ያለው ነው። በመሆኑም ለዚህ ሞዴል የተሰጠው ብያኔ እና ተጠቃሽ ባህርያቶች ከጥናቱ አላማ ጋር የሚጣጣም በመሆኑ ጥናቱ ይህን ሞዴል ግምት ውስጥ ያስገባል።

2.3. የመጀመሪያ ቋንቋ (ቋ1) እና ሁለተኛ ቋንቋ (ቋ2) ማንበብ ግንኙነት

የሁለተኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት በጣም ውስብስብ፣ ተለዋዋጭ፣ ብዙ ክፍሎች (አካሎች) ያለው ፈርጀብዙ ነው (Phakiti 2006፡19)። ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ብዛት ያላቸው መስተጋብሮች የሚሳተፉበት በመሆኑ ነው። ከአንባቢ ሁኔታዎች አንፃር ያሉ መስተጋብሮች ለምሳሌ የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ እና መፃፍ፣ የቀደመ እውቀት፣ የሁለተኛ ቋንቋ ብቃት፣ የፅሁፍ ዘውግ እና የቋንቋ አጠቃቀም (Pragmatics)፣ የቋንቋ እና ባህል እውቀት (Knowladge of Metalinguistics)፣ መነሳሳት፣ የብልሃት አጠቃቀም እውቀት ወዘተ ይጠቀሳሉ። ሌላው የሁለተኛ ቋንቋ ማንበብን ውስብስብ የሚያደርገው አውዳዊ ጉዳይ ነው። ይኸውም የውህድአሀድ ርዕስ እና ይዘት፣

የውህድአሀድ አይነት እና ዘውግ፣ የውህድአሀድ ተነባቢነት፣ ቃላዊ እና ቃልአልባ ተግባር በዋናነት ይጠቀሳሉ (Phakiti 2006)።

ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ የማንበብ ብቃታቸውን ከፍ ለማድረግ ትልቅ ትኩረት ቢኖራቸውም (ለምሳሌ እንግሊዝኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች) የሚያነቡት ግን በዝግታ ከደካማ አንብቦ የመረዳት ችግር ጋር ነው (Anderson 1999፣ Celce-Murcia 1991፣ Cohen 1999፣ Alderson 1984)።

Bossers (1991፡145) Coady (1979)ን በመጥቀስ እንዳስረዱት በሁለተኛ ቋንቋ ከፍተኛ የማንበብ ፍላጎት ቢኖርም የብቃት ማነስ በመኖሩ ግልፅ የሆነ የፍላጎት እና የችሎታ ተቃርኖ (Paradox) መኖሩን መረዳት ይቻላል። የማንበብ ችሎታ በየትኛውም ደረጃ በብቃት ለመሳተፍ ከፍተኛ ሚና አለው። ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ የሚፈለገው የብቃት ደረጃ ላይ የማይደርሱበት ምክንያት ምን ሊሆን እንደሚችል በተዋሪዎች መካከል ብዙ አነጋጋሪ ሐሳቦች ይሰነዘራሉ። Bossers (1991፡145) የተለያዩ ፀሀፊዎችን ጠቅሰው እንደሚከተለው አመላክተዋል። ይኸውም ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ሂደት እንደመጀመሪያ ቋንቋ ለማንበብ የሚቸገሩት "የማንበብ ችግር ወይስ የቋንቋ ችግር" (Alderson 1984)፣ "የቋንቋ ብቃት ማነስ ወይስ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ችግር" (Cziko 1984)፣ "የማንበብ ችሎታ ወይስ የቋንቋ ብቃት ማነስ" (Carrell 1991) "ስነልቦናዊ (ስነአእምሯዊ) ወይስ የቋንቋ ችግር" (Clark 1988) ወዘተ በማለት የችግሩን መንስኤ በተለያየ አቅጣጫ ለመለየት ተግተው እንደሚጠይቁ አመላክተዋል። መጠይቆቹ ሲጠቃለሉ በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ያለው ችግር የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ ብቃት ማነስ፣ የሁለተኛ ቋንቋ የቋንቋ ችሎታ ማነስ ወይስ የነዚህ መሰረታዊ ጉዳዮች ድምር ነው? በሚል ሊቀመጡ ይችላሉ።

ከዚህ በመነሳት Alderson (1984:4) በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ የሚታየውን አንብቦ የመረዳት ችግር በተመለከተ መላምቶችን በሚከተለው መልኩ አስቀምጠዋል።

1. በሁለተኛ ቋንቋ የማንበብ ድክመት በመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ ደካማ የመሆን ውጤት ነው፤ በመጀመሪያ ቋንቋ ደካማ አንባቢዎች በሁለተኛ ቋንቋም ደካማ ናቸው፤ እንዲሁም በመጀመሪያ ቋንቋ ጥሩ አንባቢዎች በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብም ጥሩ ይሆናሉ።

2. በሁለተኛ ቋንቋ ደካማ አንባቢዎች ብቁ የሆነ የታላሚው ቋንቋ እውቀት የላቸውም፡፡

Alderson (1984:4) ከላይ በሚነበበው መልክ ያቀረቡዋቸውን መላምቶች አሻሽለው (እንደፀሀፊው አገላለፅ) እንደሚከተለው አቅርበዋቸዋል፡፡

1. በሁለተኛ ቋንቋ የማንበብ ድክመት በዚሁ በሁለተኛ ቋንቋ የተሳሳተ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ውጤት ነው፡፡
2. በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ድክመት በመጀመሪያ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና ብቁ ያልሆነ የሁለተኛ ቋንቋ እውቀት ውጤት እንጂ የሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ብልሃት አጠቃቀም አይደለም፡፡ ጥሩ የመጀመሪያ ቋንቋ አንባቢዎች አንድ ጊዜ የሁለተኛ ቋንቋ ችሎታ ጅመራ ደረጃን ካለፉ በሁለተኛ ቋንቋም ጥሩ አንባቢዎች ይሆናሉ፡፡

መላምቶቹ በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ መካከል ግንኙነት መኖሩን ፣ የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ ችሎታ ለሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ አስፈላጊ መሆኑን እና የሁለተኛ ቋንቋ የቋንቋ እውቀት (ቢያንስ ቢያንስ ጅመራ የቋንቋ እውቀት ደረጃ መኖር እና ማለፍ) አስፈላጊ መሆናቸውን ያመላክታሉ፡፡

በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ሒደት አንባቢ የመጀመሪያ ቋንቋውን እንደሀብት (Resource) ወይም እንደማንበብ ብልሃት የመጠቀም እድል አለው (Jiang 2011፣ Grabe 1991)፡፡ ለአካለ መጠን የደረሱ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በመጀመሪያ ቋንቋ ከነበራቸው የማንበብ እና የመፃፍ የቀደመ እውቀት በመነሳት በተወሰነ ደረጃ የማንበብ ክሂል እና የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ልእለአእምሮታዊ እውቀት አላቸው፡፡ ነገር ግን ብዙ ጊዜ የሁለተኛ ቋንቋ እውቀት እጥረት ይታይባቸዋል፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ አንባቢዎች በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ሒደት ምን አይነት የማንበብ ብልሃት ይጠቀማሉ? የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ ብልሃታቸውን ወደሁለተኛ ቋንቋ ወይም በተቃራኒው እያሸጋገሩ ይጠቀማሉ? የሚሉ ጥያቄዎችን ምሁራን ያነሳሉ (Cummins 1991፣ Alderson 1984)፡፡

የቋንቋ ባህሪያት ብቻቸውን የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ቋንቋ ማንበብን እና የማንበብ ብልሃት አጠቃቀምን ከባድ እና ውስብስብ ያደርጉታል ማለት አይደለም፡፡ በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ሂደት አንባቢ ታላሚን ቋንቋ በሚገባ የመጠቀም ሁኔታ፣ የቀደመ

እውቀት፣ ባህል ተኮር አእምሯዊ የእውቀት መዋቅር፣ የአንባቢው የማንበብ አላማ፣ በመጀመሪያ ቋንቋ ያለ የማንበብ ችሎታ ወዘተ ትልቅ ሚና አላቸው። ከአንብቦ መረዳት ሂደት አንፃር የመጀመሪያ ቋንቋ እና ሁለተኛ ቋንቋ በሶስት ጉዳዮች ይለያያሉ። የልዩነታቸው መነሻ የሚሆኑት ሶስቱ አውዳዊ ጉዳዮች የቋንቋ እና የማብላላት ሒደት ልዩነቶች (Linguistic and Processing Differences)፣ የግል እና የልምድ ልዩነት (Individual and Experiential Differences)እና ማህበረባህላዊ እና ተቋማዊ ልዩነቶች (Socio-Cultural and Institiutional Differences) ናቸው (Phakiti 2006)።

የቋንቋ እና የማብላላት ሒደት ልዩነት ማለት የመጀመሪያ ቋንቋ ከሁለተኛ ቋንቋ ጋር ያለው መመሳሰል እና ልዩነት (መዋቅራዊ፣ ፅህፈታዊ/ ለምሳሌ ፊደላዊ /Ortographic/ ልዩነት ወዘተ) እና አእምሮታዊ ሂደትን ያመላክታል። በዚህ ስር የሚካተቱት ዋና ዋና ጉዳዮች ቃላት፣ ሰዋስው፣ ዲስኮርስ፣ ስርአተፅህፈት፣ የቋንቋ እና ባህል እውቀት፣ ልእለአእምሮታዊ የማብላላት ሒደት ናቸው። እነዚህ መሰረታዊ ጉዳዮች በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብን በማጎልበት ሒደት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥባቸው እና ሰፊ የጥናት አቅጣጫዎች ናቸው። ሁለተኛው ነጥብ በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ቋንቋ አንባቢዎች መካከል ያለ የግል እና የልምድ ልዩነት ነው። በዚህ መሰረታዊ ጉዳይ ስር የሚካተቱት የሁለተኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት፣ የተማሪዎች በመጀመሪያ ቋንቋ የማንበብ እና የመፃፍ ክሂል ብቃት ደረጃ፣ የሁለተኛ ቋንቋ የቀደመ የማንበብ ልምድ፣ በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ መነሳሳት፣ የግል ልምድ ልዩነት፣ እውናዊ ለሆነ ውህድአሀድ ያላቸው አመለካከት እና የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ፅሁፎች አጠቃቀም ስልጠናን ያካትታል። በሶስተኛ ደረጃ የሚነሳው የተማሪዎች ማህበረባህላዊ እና ተቋማዊ ልዩነት ነው። በዚህ ስር የሚካተተው የተለየ ግለ ልዩነት የቋንቋ አጠቃቀም ወዘተ ስፋት ያለው ባህላዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ሆነው በአብዛኛው ከክፍል ውጪ ተግባራዊ የሚሆኑ ናቸው። የማንበብ እድገትም ሆነ ማንበብን የማስተማር ሒደት በሰፊው የግል እና የማህበረሰብ ፍላጎት (አቋም) ተፅእኖ ሊያርፍበት ይችላል። ነገር ግን ይህ ጉዳይ ሁልጊዜ በተመሳሳይ ሁኔታ ተግባራዊ አይሆንም (Grabe & Stoller 2002)።

Phakiti (2006:20) በበኩላቸው እንደገለፁት በመጀመሪያ ቋንቋ እና በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ መካከል ያለው ልዩነት የመጀመሪያ ቋንቋ እና የሁለተኛ ቋንቋ ቃላት እውቀት ስፋት እና ጥልቀት፣የመጀመሪያ ቋንቋ አንባቢዎች ከባድ እና እውናዊ ለሆነ ውህድአሀድ

ያላቸው የምላሽ አይነት፣ የቋንቋ ግንዛቤ ደረጃ፣ የማንበብ ፍጥነት እና የሐሳብ ፍሰቱን ጠብቆ የማንበብ ሁኔታ፣ አንብቦ መረዳት፣ የሁለተኛ ቋንቋ ባህል እውቀት እና ከባህል አንፃር ከመጀመሪያ ቋንቋ ጋር ያላቸው ልዩነትና ስፋት (መጠን)፣ የሁለተኛ ቋንቋ የቋንቋ ጅመራ ደረጃ ለማንበብ ያለው ሚና በዋናነት ይጠቀሳሉ ብለዋል። እነዚህ ነጥቦች የሁለተኛ ቋንቋ ማንበብን በማስተማር ሒደት የማንበብን ባህሪ እና የማስተማር ዘይን ብቻ ሳይሆን የተማሪዎችን ባህሪ እና አውድ ያመላክታሉ። ይህም ሆኖ በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ቋንቋ መካከል ጠንካራ ግንኙነት እና መደጋገፍ አለ። በተለይ የመጀመሪያ ቋንቋ የማንበብ ብቃት (ተክህኖ)፣ የሁለተኛ ቋንቋ የቋንቋ እውቀት፣ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ብልሃት ግንኙነት እና ሽግግር ከሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ እና አንብቦ መረዳት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው።

Alderson (1984)፣ Cummins (1979)፣ Yorio (1971) የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ያላቸውን ግንኙነት በማጤን በተለይ የሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ችግር የቋንቋ፣ የእውቀት ወይስ የማንበብ ችግር ነው በማለት በአእምሯቸው ውስጥ የሚመላለሰውን ምርምራዊ ጥያቄ ለመመለስ የተለያዩ መላምቶችን ቀምረዋል (አስተዋውቀዋል)። መላምቶቹ የቋንቋ ርስበርስ ግንኙነት መላምት ወይም አእምሯዊ የጋራ ውስጠ ብቃት (Linguistic Interdependency Hypotheses/ Common Underlying Proficiency Hypotheses) እና የቋንቋ ጅመራ ደረጃ መላምት ወይም ውስን ችሎታ (Linguistic Threshold Hypotheses / Short-Circuit Hypotheses) ናቸው። መላምቶቹን የሚያራምዱ ወገኖች በዋናነት ከአንድ ሁኔታ ወደሌላ አዲስ ሁኔታ ወይም ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ ለሚፈጠር የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ወሳኙ ነገር የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ ብቃት ነው ወይስ የሁለተኛ ቋንቋ ችሎታ የሚል ሀሳብ ይዘው ይከራከራሉ (Talibi 2015:35) ።

ሀ. የቋንቋ ርስበርስ ግንኙነት መላምት

የቋንቋ እርስ በርስ ግንኙነት መላምት በ Cummins (1979) የተነደፈ መላምት ሲሆን አእምሯዊ የጋራ ውስጠ ብቃት መላምት ተብሎ እንደሚጠራ (Talibi 2015፣ Lee 1997፣ Bernhardt & Kamil 1995፡ Hulstun & Matter 1991) ይገልፃሉ። መላምቱ የሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ተግባር ከመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ ልምድ ጋር በትልቁ የሚጋራው መሰረታዊ ጉዳይ አለ የሚል ሐሳብ ያራምዳል። በሌላ አገላለፅ መላምቱ

ክሂል፣ ብልሃት፣ እውቀት፣ ባህል፣ ዕንስ ሐሳብ፣ ግንዛቤያዊ ችሎታ ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ ሽግግር የሚያርግ መሆኑን፣ የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ ብልሃት ወደሁለተኛ ቋንቋ ሽግግር የሚያደርግ መሆኑን፣ የመጀመሪያ ቋንቋ እና የሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ብልሃት በተወሰኑ መሰረታዊ ጉዳዮች ተመሳሳይ መሆናቸውን እና አንድ ጊዜ የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ ችሎታ ከተለመደ (ከተገኘ) በሁለተኛ ቋንቋ ተመሳሳይ አእምሯዊ ተልዕኮ የሚጎለብት በመሆኑ የማንበብ ብልሃት ከመጀመሪያ ቋንቋ ወደ ሁለተኛ ቋንቋ ሽግግር ያደርጋል የሚል ሃሳብ ያንፀባርቃል (Bernhardt & Kamil 1995:17)። ይህ አመለካከት ሁለንተናዊ ማንበብ መላምት (Universal Reading Hypotheses) እንደሚባል Talibi (2015:35፣2007፡3) ገልፀዋል።

አእምሯዊ የጋራ ውስጠ ብቃት መላምት እንደሚያመለክተው የሁለተኛ ቋንቋ አንባቢዎች በመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ እና መፃፍ የተማሩ በመሆናቸው የሁለተኛ ቋንቋ ማንበብን ለማጎልበት ሁለት መንገዶች (Chanels) አሉዋቸው። የመጀመሪያው በራሳቸው ቋንቋ ማንበብ የቀደመ እውቀት ሲሆን ሁለተኛው ከሁለተኛ ቋንቋ ግብአት በማግኘት የሚያጎለብቱት ይሆናል Talibi (2007)፣Cummins (2005)። ሁሉም የፅሁፍ ቋንቋዎች በተለያየ ሁኔታ ቢመሳሰሉም ባይመሳሰሉም (ቋንቋዎቹ ቢመሳሰሉ የበለጠ ምቹ ሁኔታ ይኖራል) አእምሯዊ የአካዳሚ ብቃትን ይጋራሉ ወይም ርስበርስ የመረዳዳት ግንኙነት አላቸው። በመሆኑም በትውረቱ አተያይ ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂላቸውን ለማጎልበት የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ እውቀት እና ልምድ እንደግብአት ያገለግላል (ወሳኝ ነው)።

ለ. የቋንቋ ጅመራ ደረጃ መላምት

ከቋንቋ ርስበርስ ግንኙነት መላምት በተቃራኒው በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ሒደት የቀረበውን ውህድአሀድ አንብቦ ለመረዳት የሁለኛ ቋንቋ እውቀት ወሳኝ እና ቁልፍ ሚና አለው የሚሉ ወገኖች አሉ። እንደ Grenfell and Razi (2012)፣ Talibi (2015፣2012፣2007)፣ Hulstun and Matter (1991)፣ Yorio (1971) አገላለፅ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ የቀረበውን ውህድአሀድ አንብበው ለመረዳት የተወሰነ የሁለተኛ ቋንቋ ተክህኖ ደረጃ ያስፈልጋቸዋል። ይህም የቋንቋ ጀማሪ ደረጃ (ጅመራ) መላምት ወይም ውስን የሁለተኛ ቋንቋ ችሎታ አመላካች ይባላል። የዚህ ሞዴል አራማጅ Yorio (1971) የተባሉት ምሁር ናቸው። Talibi (2015፡35) Yorio (1971)ን

ጠቅሰው እንደገለፁት ዋነኛው የሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ችግር የራሱ የሁለተኛ ቋንቋ ብቃት ማነስ እና የመጀመሪያ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት ነው።

የቋንቋ ጅመራ ደረጃ መላምት የሁለተኛ ቋንቋ መቆጣጠር ውስንነትን የሚያመለክት በመሆኑ አንባቢዎች በሁለተኛ ቋንቋ ጠንካራ (አስቸጋሪ እና ውስብስብ) የማንበብ ተግባር ሲገጥማቸው ደካማ የሁለተኛ ቋንቋ ብቃት ያላቸው ከሆነ ደካማ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና ደካማ የአንብቦ መረዳት ብቃት ይኖራቸዋል። እንደ Zainal (2011:113)፣ Carrell et al. (1998፡120) ይህ መላምት ሶስት ነገሮችን ያመላክታል። አንደኛው አንባቢዎች በሁለተኛ ቋንቋ ለማንበብ የተወሰነ ደረጃ የሁለተኛ ቋንቋ የቋንቋ ችሎታ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን፣ ሁለተኛው አንባቢዎች በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ከተወሰነ የቋንቋ ጅመራ ደረጃ በታች ከሆኑ የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ ብልሃታቸውን ተጠቅመው በታላሚው ቋንቋ የቀረበውን ውህድአሀድ አንብበው ለመረዳት የሚቸገሩ መሆኑን እና ሶስተኛው የመጀመሪያ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት ከአንዱ ቋንቋ ወደሌላው ቋንቋ ሽግግር የሚያደርግ መሆኑን ያመለክታል።

Carrell et al.(1998:120) አገላለፅ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ብቁ ያልሆነ ተክህኖ ምክንያት በመጀመሪያ ቋንቋ የላይ ታች (Top down) ማንበብ ሒደት ወደ ሁለተኛ ቋንቋ ታች ላይ (Bottm up) የማንበብ ሒደት ይለወጣል። እንደመላምቱ አተያይ በሁለተኛ ቋንቋ የተወሰነ የቋንቋ ጅመራ ደረጃ ብቃት ለጥሩ አንባቢዎች የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ ብልሃት ወደሁለተኛ ቋንቋ ሽግግር እንዲያደርግ ይጠቅማቸዋል።

ከላይ ከቀረበው ክርክር የተለየ አቋም የሚያራምዱት Alderson (1984፡1-20) ናቸው። እንደምሁሩ ገለፃ የሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ችግር የቋንቋ እውቀት ማነስ (የቋንቋ ክፍሎችን የማብላላት ድክመት ለምሳሌ የዕህፈት፣ የድምፅ፣ ቃላት፣ አገባብ፣ ትርጉም፣ ዲስኮርሳዊ እውቀት በተለይ በሁለተኛ ቋንቋ) እና የማንበብ ችግር (ከፍተኛ ደረጃ የአእምሮ ክንውን ድክመት ለምሳሌ መተንበይ፣ መተንተን፣ ማዋሃድ፣ መረጃን ፈልፍሎ ማውጣት እና መልሶ መጠቀም፣ጠቃሚ የቀደመ እውቀትን መጠቀም ይህ በሁሉም ቋንቋ) ናቸው በማለት የሁለቱንም ወገኖች ሀሳብ አጣምረው ይመለከታሉ።

እንደ Alderson (1984፡1-6) እምነት የሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ችግር የቋንቋ ብቃት ማነስ እና የማንበብ ችግር ቢሆንም (ሁለቱም የሚያስፈልጉ ናቸው) በተለይ የሁለተኛ

ቋንቋ ዝቅተኛ ብቃት ያላቸው ዋናው ችግር የቋንቋ ችግር ሲሆን የሁለተኛ ቋንቋ ጅመራ ደረጃ ላይ ከደረሱ የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ ችሎታ (የማንበብ ብልሃት) ወደሁለተኛ ቋንቋ ሽግግር ያደርጋል። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍም ይህንን የ Alderson (1984) ሀሳብ ይጋራል።

2.4 የማንበብ ብልሃት ምንነት እና መገለጫዎቹ

2.4.1 የማንበብ ብልሃት ምንነት

ቋንቋ የመማር ብልሃት አካል የሆነው የማንበብ ብልሃት መሰረታዊ መነሻው የመማር ብልሃት ነው (Mehrpour et al. 2011፣ Ling 2011፣ Griffiths 2004)። ብልሃት የሚለው ፅንሰሀሳባዊ ቃል የመማር ባህሪ፣ እቅድ፣ ዘዴ ወዘተ ነው በሚሉ ተቀራራቢ ትርጉም ባላቸው ቃላት ይገለፃል። እንደ Cubukcu (2007:95) አገላለፅ ብልሃት ግለሰቦች ተግባራትን ለመረዳት እና ለማከናወን የሚነድፉት እቅድ ነው። ብልሃት ግለሰበቦች የመማር ባህሪያቸውን በሚያቅዱበት እና በሚገመግሙበት ወቅት እንዴት እንደሚያስቡ እና እንደሚተገብሩ ጠልቀው ለማሰብ ያስችላቸዋል። ቋንቋ የመማር ብልሃት ፅንሰሀሳብን በተመለከተ ከ1970ዎቹ በፊት በመስኩ በተሰማሩ ፀሀፊዎች እና ጥናት አቅራቢዎች ዘንድ ግልፅ የሆነ መግባባት ያልነበረበት የሚያወዛግብ እና የተድበሰበሰ (Fuzzy) ነበር (Ellis 1994:529)። በ1970ዎቹ አጋማሽ የተለያዩ ወገኖች Rubin (1975)፣ Stern (1975) በመስኩ ጥናት በማድረግ ቋንቋን በመማር ሂደት ብልሃትን መጠቀም ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ እንደሆነ ግንዛቤ ፈጥረዋል (Griffiths 2004)። Griffiths (2004፡2) Skehan (1989)ን ጠቅሰው እንደገለፁት ይህም ሆኖ ቋንቋ የመማር ብልሃት ብያኔ መስጠት እና አከፋፈሉን ማሳየት ቀላል ስራ እንዳልሆነ አስረድተዋል።

ቋንቋ የመማር ብልሃት የጥናት መስክ ላይ ትኩረት በማድረግ ተቀዳሚ የሚባሉት Rubin (1975፡45) ፅንሰሀሳባዊ ቃሉን ሲበይኑ ተማሪዎች እውቀትን ለማግኘት የሚጠቀሙበት ዘዴ ወይም መሳርያ ነው ሲሉ Stern (1975፡311) በበኩላቸው ሆን ብሎ በሰፊው ለመረዳት የሚያስችል መንገድ ብለውታል። O`Malley et al. (1985:23) እንደገለፁት ቋንቋ የመማር ብልሃት ተማሪዎች መረጃን ለማግኘት፣ ለማጠራቀም እና መልሶ ለመጠቀም የሚያስችል አእምሯዊ ተልእኮ፣ ቅደም ተከተል ነው ሲሉ Oxford

(1990:8) ከ O`Malley et al.(1985) ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ተማሪዎች መረጃን ለማግኘት፣ ለማጠራቀም እና መልሶ ለመጠቀም በተማሪዎች ተግባራዊ የሚሆን የአእምሮ ተልእኳዊ አሰራር እንደሆነ አስረድተዋል።

ማንበብን በማስተማር ሂደት የብልሃት ፅንሰሀሳብ አገልግሎት ላይ የዋለው በ1945 Robinson " Effective Study" በተባለ መፅሀፋቸው ነው (Oyetunji 2013:35)። እንደ Oyetunji (2013) አገላለፅ Robinson በመፅሀፋቸው ውስጥ ከሌሎች ብልሃቶች በተለየ ማሰስ፣ መጠየቅ፣ መድገም ወይም ድምፅን ከፍ አድርጎ ማንበብ እና ማስጣጣት (Survey,Question,Read,Recite and Review / SQ3R) የመማር (የማጥናት) ዘዴ የቀደመ እውቀትን በሂደት ለማጎልበት እና ዋናውን ሀሳብ ለመለየት ያለውን ጠቀሜታ ገልፀዋል። እንደ Oyetunji 2013:35) ገለፃ በመቀጠል 1970 ዎቹ Hereber (1970) "Teaching Reading in Context Areas" የተባለውን መፅሀፋቸውን ሲያሳትሙ የመጀመሪያ (ቀዳሚ) የሆኑትን የመማር ብልሃቶች አስተዋውቀዋል። በ1970 ዎቹ አጋማሽ አእምሮታዊ ስነልቦና የቀደመ እውቀት ለአንብቦ መረዳት ያለውን ጉልህ ሚና አጉልቶ ያሳየበት ወቅት ነው (Oyetunji 2013)። በወቅቱ በብልሃት አጠቃቀም ዙርያ ቀደምት ተመራማሪዋ Rubin (1975) ውጤታማ እና ደካማ (ውጤት አልባ) የቋንቋ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና ደካማ ተማሪዎች ብልሃቶችን በተሻለ መንገድ እዲጠቀሙ የሚረዱበት መንገድ ላይ ጥናት አድርገዋል። የማንበብ ብልሃትን ማስተማር መሰረት የተጣለውም በ Rubin (1975) እና Flavell (1976) ስራ ላይ በመመስረት ነው። የማንበብ ብልሃት ትምህርት አላማም ተማሪዎች አንብቦ መረዳትን እንዲያሻሽሉ ማድረግ ነው (Oyetunji 2013፣ Griffths 2004፣ Duffy 2002)።

ቋንቋ የመማር ብልሃትን የተመለከተ ወጥ ብያኔ መስጠት አስቸጋሪ እንደሆነ ሁሉ የማንበብ ብልሃትን በተመለከተ የምርምር ባለሙያዎች አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ ሲጠቀሙ አይስተዋልም። ለዚህም አራት መሰረታዊ ምክንያቶች እንዳሉ Paris et al. (1991) አመላክተዋል። እነሱም የማንበብ ብልሃትን ከሌሎች አእምሮታዊ ሒደት ካላቸው ማለትም ከማሰብ፣ ከምክንያታዊነት፣ ከማጥናት እና ከመነሳሳት ብልሃት ጋር ማመሳሰል ወይም ከተዘረዘሩት መለየት አለመቻል፣ የማንበብ ብልሃት መጠነርዕይ ሰፊ መሆን፣ ሆን ብሎ መተግበር እና ንቃተ ህሊናን የሚፈለግ መሆን፣ ብልሃት እና ክሂል አንዳንድ ጊዜ በተለዋዋጭነት ማገልገላቸው በዋናነት ይጠቀሳሉ።

የማንበብ ብልሃትን የተመለከተ ወጥ የሆነ ብያኔ ባይኖርም ፀሀፊዎች ፅንሰሃሳባዊ ቃሉን በየራሳቸው መንገድ ገልፀውታል። Block (1986፡465) እንዳስረዱት የማንበብ ብልሃት ተማሪዎች የተሰጠን የማንበብ ተግባር ለመረዳት በንቃተህሊና ሆንብለው የሚጠቀሙበት ዘዴ፣ የአእምሮ ተልዕኳዊ አሰራር ወይም ቅደም ተከተል ሆኖ ተማሪዎች ውህድአሀዱን ለመረዳት ምን አይነት ምልክት (ፍንጭ) እንደሚጠቀሙ፣ ያነበቡት እንዴት ስሜት እንደሚሰጥ፣ ባልገባቸው ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለባቸው በመገንዘብ እርምጃ የሚወስዱበት መሳሪያ (መንገድ) የማንበብ ብልሃት ነው። Anderson (1991፡460) እንዳስረዱት የማንበብ ብልሃት አዲስ መረጃን ለማግኘት፣ ለማጠራቀም እና መረጃን አሻሽሎ ለመጠቀም (ወደራስ ተርጉሞ ለመጠቀም) ተማሪዎች በጥንቃቄ እና በአእምሯዊ ልኬት የሚተገብሩት ድርጊት ነው። የማንበብ ብልሃት አንባቢ ከውህድአሀዱ ጋር የሚያደርገውን መስተጋብር እንዴት መቆጣጠር እንዳለበት ለማወቅ የሚያስችል ብቻ ሳይሆን ብልሃቶችን በመጠቀም እንዴት ውጤታማ አንብቦ መረዳትን ማጎልበት ይቻላል የሚለውን ፍላጎት የሚያንፀባርቅ ነው (Carrell 2006:1)። Phakiti (2006:23) በበኩላቸው እንደገለፁት የማንበብ ብልሃት አንባቢዎች በማንበብ ሂደት የቀረበላቸውን ፅሁፍ አንብበው ለመረዳት በንቃተህሊና ሆን ብለው እና አስበውበት የሚተገብሩት ግብ ተኮር እቅድ ነው።

የማንበብ ብልሃት ሆን ተብሎ የሚተገበር፣ ቅደምተከተላዊ፣ አላማ ተኮር፣ ትጋት የሚፈልግ፣ ፈቃደኝነትን የሚሻ፣ በጣም አስፈላጊ እና የማንበብ ሂደትን አመቻች ነው። ከላይ የተጠቀሱት የምርምር ባለሙያዎች የማንበብ ብልሃትን በተለያየ መንገድ ቢገልፁትም ተማሪዎች የማንበብ ሂደታቸውን በማመቻቸት አንብቦ መረዳታቸውን ለማጎልበት እንዲሁም የሚያጋጥሙ ችግሮችን በማስወገድ የተለየ የማንበብ ግባቸውን ለማሳካት ሆንብለው የሚተገብሩት አእምሯዊ ክንውን ነው የሚለውን ሀሳብ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የሚጋራው ሀሳብ ነው።

2.4.2 በማንበብ ብልሃት እና በማንበብ ክሂል መካከል ያለ ተመሳስሎ እና ልዩነት

የማንበብ ክሂልን እና የማንበብ ብልሃትን እያምታቱ የመጠቀም ሁኔታ አለ። አንዳንዶች ሙያዊ ቃሉን አንድ አድርገው ይጠቀማሉ። አንዱ የአንዱ ማሚያ (ለምሳሌ ብልሃት ክሂልን የሚደግፍ) አድርገው የሚያስቡም አሉ። ሌሎች ደግሞ የማንበብ እድገት እቅድ ፅንሰሀሳባዊ ቃል (ለምሳሌ ከድምፅ ስርአት እድገት ቀጥሎ የመረዳት ብልሃት) አድርገው ይወስዳሉ። ፖሊሲ አውጪዎች፣ ስርአተትምህርት የሚያጎለብቱ ወገኖች፣ ፈተና አውጪዎች ሙያዊ ቃላቱን በትክክል ለመለየት ሲቸገሩ ይስተዋላል (Afflerbach et al. 2003)።

እንደ Afflerbach et al. (2003፡364) አገላለፅ ሙያዊ ቃላቱ ላይ መምታታት የተፈጠረበት ሶስት መሰረታዊ ምክንያቶች አሉ። እነሱም ፅንሰ ሐሳቡን ለመግለፅ የተለያየ ተራ የቋንቋ አጠቃቀም መጠቀም፣ ተገቢ (ብቁ) ያልሆነ ብያኔ መስጠት እና ጠቃሚ መረጃ በማስቀመጥ ወጥ የሆነ አካሄድ (አጠቃቀም) አለመኖር ናቸው። ፀሐፊዎቹ እንዳስረዱት በሁለቱ ፅንሰሀሳባዊ ቃላት መካከል ያለውን ግንዛቤ ለመረዳት (በተለይ የፕሮፌሽናል ባለሙያዎችን ሐሳብ ለማግኘት) በአንድ ተቋም ፈቃደኛ የሆኑ የቅድመ እና ድህረምረቃ መምህራን እና በትምህርት መስክ ያሉትን የከፍተኛ ተቋማት መምህራንን በመጠየቅ የተሰበሰበው መረጃ ያሳየው የተለያየ አመለካከት መኖሩን ነው። በሙያ ቃላቱ ዙሪያ መምህራን እና የትምህርት ባለሙያዎች የሰጡት አስተያየት የሚከተለው ገፅታ አለው።

- ክሂል ብልሃትን ይፈጥራል
- ብልሃት ወደክሂል ያመራል
- ክሂል መዳረሻ ነው፣ ብልሃት ግን ማድረሻ (ማጓጓዣ) ነው
- ክሂልን ተግባራዊ ለማድረግ ብልሃትን እንማራለን
- ክሂል ቅፅበታዊ ሲሆን ብልሃት አቅምን የሚፈልግ እና አማካይ ነው።
- ብልሃትን እንደ መሳሪያ (tool) እንጠቀምበታለን
- ብልሃት ክሂልን ለማግኘት የሚያገለግል ነው
- በመማር ሒደት ክሂል ላይ ትኩረት እናደርጋለን ነገር ግን በሒደት ሁለቱንም በአንድ ጊዜ (automatically) እንጠቀማለን

- ስለክሂል አናስብም ነገር ግን ስለ ብልሃት እናስባለን ወዘተ በማለት ሐሳባቸውን አንፀባርቀዋል።

Harris and Hodges (1995:235) እንደገለፁት ክሂል አንድን ነገር ለመተግበር (ማንበብ) የሚለመድ ችሎታ ወይም ብቃት ነው። ክሂል ድግግም በሆነው መማር ውስብስብ ሞተራዊ ክንውንን ማስተባበር እንዲሁም ለማሰብ ወይም ለመረዳት እውቀትን ተግባራዊ የሚያደርግ ክንውን ነው ሲሉ ብልሃት ደግሞ በትምህርት ዘርፍ መማርን (ማንበብን) ለማሻሻል ሆን ተብሎ የሚተገበር ስልታዊ እቅድ ነው። Hudson (2007:78) በበኩላቸው ክሂል አንድን ነገር በሚገባ መተግበር ነው ሲሉት ብልሃት ደግሞ አእምሯዊ መሳሪያ (Device)፣ ዘዴ፣ የአእምሮ ተልእኳዊ አሰራር፣ ቅደም ተከተል ወይም አቅጣጫ ነው በማለት ይገልፁታል።

Celce-Murcia (1991:185) እንዳስረዱት ማንበብ እና መፃፍን ለማስተማር ሁለት አቀራረቦች አሉ። አንደኛው ክሂል ተኮር ሞዴል ሲሆን ሌላው ብልሃት ተኮር ሞዴል ነው። አብዛኛው የማንበብ ትምህርት አቀራረብ ትኩረቱ የማንበብ ክሂል ላይ ነው። በዚህም ለምሳሌ የመረዳት ክሂል፣ ቅላፄ ላይ ትኩረት ማድረግ እና ቃላትን መለየት ላይ ያተኩራል። በተቃራኒው ስነአእምሯዊ ስነልሳን ብልሃትን ከማጎልበት አንፃር ትኩረት የሚያደርገው ከውህድአሀዱ ትርጉም ለማግኘት መጣር የሚል ሀሳብ ላይ ነው።

Celce-Murcia (1991:185) Holdaway (1985) እና Smith (1983)ን ጠቅሰው እንደገለፁት ክሂል ተኮር ሞዴል አነስተኛ የቋንቋ ክሂል እየጎለበተ መምጣት ማለትም ከድምፅ እስከ ቃላት እና ሀረጎች ወይም ከቋንቋ ከፍተኛ አሃል ወደ አነስተኛ ነጠላ ክፍል እየበታተነ ማየት ላይ ትኩረት ያደርጋል። ብልሃት ተኮር ሞዴል ማንበብን ሲበይን "ትርጉም፣ አገባብ፣ ፊደል (Graphophonics) መካከል ያለ ግንኙነት የሚሳተፍበት ቋንቋ የማሰብ ሂደት ነው" ይላል። ከብልሃት ተኮር ሞዴል አንፃር ማንበብ ፅንሰ ሀሳባዊ ልምድ፣ የቀደመ እውቀት እና የማብላላት ውጤት መስተጋብር ነው። በዚህም ማንበብ ትኩረቱ መረዳት ነው እንጂ ምልክትን መተርጎም አይደለም። በሌላ በኩል በክሂል ተኮር ሞዴል ቃላት፣ የድምፅ እና የምልክት ግንኙነት፣ ሰዋስው እና መረዳትን ለይቶ ያስቀምጣል። የበለጠ ትኩረቱም በድምፅ እና በምልክት መካከል ያለን ግንኙነት ጠንቅቆ ማወቅ ትርጉምን ለማግኘት ያስችላል የሚል አመለካከት ይራመዳል። ተማሪዎች ቅንጣት ድምፃዊ ስርአት እና የቃላት ፊደሎችን መለየት ከተፃፈው ውህድአሀድ ትርጉም

ማግኘት ያስችላቸዋል የሚል ነው። ክሂል አንድን ነገር ውጤታማ በሆነ መንገድ መተግበር ሲሆን ብልሃት ደግሞ ድርጊቱ እንዴት እንደሚተገበር ማወቅ ነው። እንደ Carrell (2006:2) አገላለፅ በእርግጥ ክሂል ሆን ተብሎ ከተተገበረ ብልሃት ይሆናል በተመሳሳይ ብልሃት በፍጥነት ከተተገበረ ክሂል ይሆናል።

2.4.3 የማንበብ ብልሃት ጠቀሜታ

በማንበብ ሂደት ተማሪዎች የተለያዩ ችግሮች ይገጥሟቸዋል። ከሚገጥሟቸው ችግሮች የተወሰኑቱ በአረፍተ ነገር ውስጥ ያሉ ቃላት በአንድነት ሆነው እንዴት ትርጉም እንደሚሰጡ የመረዳት ችግር፣ እያንዳንዱን ቃላት ወይም አረፍተነገር በነጠላ ቢረዱም በአረፍተነገሮቹ መካከል ያለውን ግንኙነት ወይም በአጠቃላይ የውህድአሀዱን ፍቺ አለመረዳት፣ የፅሁፉን ዘውግ አለመረዳት፣ እውቀት የሚጠይቁ ውህዶችን የመረዳት ብቃት ማነስ ወዘተ ይጠቀሳሉ። እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ ከሚያስችሉ መንገዶች አንዱ የማንበብ ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም ነው (McNamara 2007:34)።

የማንበብ ብልሃት በጣም ጠቃሚ ነው የሚባለው ውጤታማ ለሆነ አንብቦ መረዳት ብቻ ሳይሆን በማንበብ ወቅት የሚያጋጥምን ችግር በመፍታት የተሻለ አንባቢ መሆን የሚያስችል በመሆኑ ነው። እንደ Cubukcu 2007፡95) አገላለፅ የማንበብ ብልሃት አጠቃላይ እውቀት እና የተለየ ጥልቅ (ዝርዝር) መረጃ ለማግኘት ዋናውን ሀሳብ (ጭብጥ) ለይቶ ለማውጣት፣ ለመማር፣ለማስታወስ፣ ደስታን ለመፍጠር፣ ጭምቀሀሳብ ለመፃፍ እና ምርምር ለመስራት ያገለግላል ።

Moktari and Reichard (2002)፣ Pressley (2002) የማንበብ ብልሃት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች እንዳሉት ዘርዝረዋል። እነሱም ተማሪዎች የበለጠ ራሳቸውን የቻሉ ራስ መር (Self-regulated)፣ ነፃ (Autonomous) እና ግለ ብቃታቸው ከፍ ያለ እንደሆነ እምነት ያላቸው (Self-efficacy) ለትምህርት ኃላፊነት የሚወስዱ ጠንካራ አንባቢዎች እንዲሆኑ፣ የማንበብ ብልሃቶችን በሚገባ በመጠቀም አንብቦ የመረዳት ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ፣ የሚያነቡትን የሚገነዘቡ (የሚረዱ) በመሆናቸው ሁል ጊዜ ለመማር የተነሳሱ ንቁ እንዲሆኑ ያደርጋል። ተማሪዎች በንቃት የመማር ማስተማር ሒደቱን

የሚከታተሉ በመሆናቸው ተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን ተግባራዊ ለማድረግ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል።

የተለያዩ የምርምር ስራዎች (Krashen 2013፣ Karami 2008፣ Carrell 2006፣ Phakiti 2006፣ Hass & Flower 2006፣ Dole et al. 1996) እንዳመለከቱት ተማሪዎች ተገቢውን የማንበብ ብልሃት ትምህርት በሚገባ ሲያገኙ እና የማንበብ ብልሃቶች ሆን ብለው ውጤታማ በሆነ መንገድ ሲጠቀሙ የመረዳት ብቃታቸው ብቻ ሳይሆን የሚጨምረው ብዙ ቃላትን የማወቅ እና የመጠቀም፣ በቃላት ውስጥ ያሉትን ምልክቶች የመተርጎም፣ በማበብ ሒደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል አቅም ይፈጥራሉ።

2.4.4 የማንበብ ብልሃት አከፋፈል

የማንበብ ብልሃት በቋንቋ መማር ብልሃት ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ አከፋፈሉም እንዲሁ በቋንቋ መማር ብልሃት ላይ የተመሰረተ ነው። የተለያዩ ፀሐፊዎች ቋንቋ የመማር ብልሃቶችን በተለያየ መንገድ ይከፍሉታል። የብልሃቶቹ አከፋፈል ወጥ አለመሆንም ከብልሃቶቹ አገልግሎት ጋር የተገናኘ ሊሆን እንደሚችል Cohen (1996:7) ያስረዳሉ። አንዳንድ ብልሃቶች መማርን በቀጥታ የሚያግዙ ናቸው። ለምሳሌ ቃላትን፣ ሰዋስዋዊ መዋቅርን ለመማር፣ ብልሃቶችን ለማስታወስ ወዘተ የሚያገለግሉ ናቸው። ሌሎች ብልሃቶች ደግሞ በግልፅ የሚታዩ ናቸው። ለምሳሌ ሐሳብ ግልፅ እንዲሆን በማሰብ ጥያቄ መጠየቅ፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ዋናውን ሀሳብ በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ ይሆናል። ሌሎች ተጠቃሽ ብልሃቶች አእምሯዊ እና በቀላሉ የማይታዩ ናቸው። ለምሳሌ በማንበብ ጊዜ ሀሳብ ግልፅ እንዲሆን በማሰብ አእምሯዊ ትርጉም መፍጠር፣ መገመት፣ መተንበይ የውህድአሀድን ይዘትና ቅርፅ ለመረዳት አእምሯዊ ምስል መፍጠር፣ ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ ማሸጋገር ወዘተ ናቸው።

የተለያዩ ፀሀፊዎች እና የምርምር አቅራቢዎች ቋንቋ የመማር ብልሃትን በተለያየ መንገድ ከፍለው አሳይተዋል። ቋንቋ የመማር ብልሃት አይነቶችን ከፍለው በማሳየት ቀዳሚ የሆኑት Rubin (1975) ብልሃቶችን በሁለት ከፍለው አሳይተዋል። እነሱም መማርን በቀጥታ የሚያግዙ እና መማርን ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የሚያግዙ ናቸው። ቀጥተኛ ቋንቋ የመማር ብልሃት ስር ግልፅ ማድረግ (ማጣራት)፣ መቆጣጠር፣

ማስታወስ፣ መገመት (ምልከታ ላይ የተመሰረተ ድምዳሜ ላይ መድረስ)፣ ተጠየቅ (ምክንያት ላይ የተመሰረተ ድምዳሜ ላይ መድረስ) እና ልምምድ ናቸው። ቀጥተኛ ያልሆኑ ብልሃቶች ደግሞ በሁለት ከፍለዋቸዋል። እነሱም ለልምምድ እድል መፍጠር እና ብልጠት (ቅልጣፊ) (Trick) ናቸው። ብልጠት (ቅልጣፊ) መፍጠር በሚለው ብልሃት ስር የተግባቦት ብልሃትን አካተዋል። ከቋንቋ መማር ባህሪ አንፃር የመማር ብልሃትን እና ተግባቦታዊ ብልሃትን በአንድ ጎራ ማየት ሁለት የተለያዩ ባህርያትን በአንድ ላይ ማየት በመሆኑ ማምታታትን ይፈጥራል በማለት (Griffiths 2004፡2) ያስረዳሉ። Brown (1980:87) ተግባቦት የውዕአት ቅርፅ ሲሆን መማር ደግሞ የግብአት ቅርፅ ነው በማለት በመማር ብልሃት እና በተግባቦት ብልሃት መካከል ልዩነት መኖሩን ለማሳየት ሞክረዋል። Ellis (1994:165) ብልሃትን ለመማር እና ለተግባቦት (እንዲሁም የችሎታ እጥረት ባጋጠመ ጊዜ ማካካስን የሚያካትት) የሚያገለግል በማለት በሁለት ከፍለው አመላክተዋል። Ellis (1994) በቋንቋ መማር ሂደት ተማሪዎች የቋንቋ እውቀት እጥረት በገጠማቸው ጊዜ እጥረቱን ለማስወገድ ወይም ለመከላከል ውጤታማ የተግባቦት ብልሃት አጠቃቀም ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው የሚል አቋም ያራምዳሉ። Tarone (1980:419) በበኩላቸው እንዳስረዱት ተግባቦታዊ ብልሃት ተማሪዎች ምን እንደሚፈልጉ ወይም ምን ማለት እንደሚፈልጉ ለማስረዳት የሚያገለግል በመሆኑ ጠቀሜታ አለው። በቋንቋ ትምህርት እና በተግባቦት ሂደት የተማሪዎች መነሳሳት ምን እንደሆነ መለያ የለም። ምናልባትም ተማሪዎች የመማርም የመግባባትም ሁለትዮሽ ተነሳስቶ ሊኖራቸው ይችላል። በመሆንም ቋንቋ የመማር እና የተግባቦት ብልሃትን በቀላሉ መለየት አይቻልም ይላሉ።

ብልሃት እና የብልሃት አከፋፈልን በተመለከተ እንደ Rubin (1970) ታዋቂ የሆኑት Stern (1992) በበኩላቸው ብልሃቶችን በአምስት ከፍለው ያሳያሉ። እነሱም አስተዳደራዊ እና የእቀዳ ብልሃት፣ አእምሮታዊ፣ ተግባቦታዊ- ልምዳዊ፣ ሁለትዮሻዊ (በሁለት ወገኖች መካከል የሚተገበር) እና ስሜታዊ ናቸው። O`Malley et al. (1985፡ 23)፣ O`Malley and Chamot (1990፡43) የማንበብ ብልሃትን ልእለአእምሮታዊ፣ አእምሮታዊ እና ማህበራዊ ብልሃት በማለት በሶስት በመክፈል 26 ንኡሳን ብልሃቶች በውስጣቸው አካተው አስተዋውቀዋል። ልእለአእምሮታዊ እና አእምሮታዊ ብልሃቶች Rubin (1975) ቀጥተኛ እና ኢ-ቀጥተኛ ብለው ካስቀመጡት ጋር ተመሳሳይ ነው።

O`Malley et al.(1985) ማህበራዊ ቋንቋ የመማር ብልሃትን መጨመራቸው ለመስተጋብራዊ ብልሃት እውቅና የመስጠት መነሳሳትን የፈጠረ ጠቃሚ እርምጃ ነው።

ከላይ የቀረበው አከፋፈል በአብዛኛው ለአእምሮታዊ እና ልእለአእምሮታዊ ብልሃት ብዙ ትኩረት የሰጠ ነው። Oxford (1990፡8) አከፋፈሉን ምቹ በማድረግ እና ከተጠቀሱት በተጨማሪ ሌሎች ብልሃቶችን በማከል በስድስት ከፍለው አስተዋውቀዋል። እነሱም ትውስታ፣ አእምሮታዊ፣ ማካካስ፣ ልእለአእምሮታዊ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ ብልሃቶች ናቸው። ከተዘረዘሩት የመጀመሪያዎቹ ሶስቱ በቀጥተኛ ብልሃት ስር የተቀሩት ደግሞ በኢ-ቀጥተኛ ብልሃት ስር የሚካተቱ ናቸው። እንደ Oxford (1990) አገላለፅ ቀጥተኛ የሚባሉት ብልሃቶች ታላሚውን ቋንቋ ለመማር በቀጥታ የሚያገለግሉ ለምሳሌ መገምገም (ማስጣጣት)፣ መለማመድ ሲሆኑ ኢ-ቀጥተኛ በመባል የሚታወቁት ቋንቋ የመማር ሂደቱን ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የሚደግፉ ለምሳሌ ማቀድ፣ መተግበር፣ በጣም ግልፅ ያልሆኑትን ሀሳቦች መዝለል ወዘተ ናቸው። እነዚህ ብልሃቶች በምርምር ስራ ወቅት ተማሪዎች ምን ያህል እንደተጠቀሙባቸው ለመፈተሽ ቋንቋ የመማር ብልሃት ቆጠራ (አሰሳ) (Strategy Inventory for Language Learning/SILL) በተባለ ዘዴ ሊፈተሽ እንደሚችል አመላክተዋል።

የ Oxford (1990) አከፋፈል ከቋንቋ መማር ጋር በቀጥታ የሚገናኝ፣ በጣም ግልፅ የሆነ፣ ቀለል ባለ እና በሚገባ መንገድ ተደራጅቶ የቀረበ ለማስተማር የሚመች እንደሆነ (Ling 2011፣ Medina 2011፣Griffiths 2004፣ Ellis 1994) ይገልፃሉ። የ Oxford (1990) አከፋፈል ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አላማ ጋር የሚጣጣም በመሆኑ ጥናቱ የምሁራኑን ሀሳብ ይጋራል። Oxford (1990) የማንበብ ብልሃቶች አከፋፈል ከላይ እንደተጠቀሰው ቢሆንም ብልሃቶቹ ያላቸውን የርስበርስ ትስስር ለማመላከት በምስል መልክ እንደሚከተለው አስቀምጠውታል (Oxford 1990፡15)።

ምስል አንድ፡- የማንበብ ብልሃትን ቅንጅት የሚያሳይ



የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም የተነጣጠለ ተግባር ሳይሆን የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ቋንቋ ተግባራትን ለማከናወን የተቀናበረ ሂደት ነው፡፡ የማንበብ ብልሃቶችን አቀናጅቶ መጠቀምን እንደትልቅ የሙዚቃ ቡድን (እንደኦኬስትራ) ማየት ጠቃሚ ነው (Anderson 2005:757)፡፡ አንዳንድ ጊዜ አንድ የሙዚቃ መሳሪያ ጥሩ ድምፅ ሊሰጥ ይችላል፣ የሙዚቃ መሳሪያው ከሌሎች የሙዚቃ መሳሪያዎች ጋር ሲጣመር ደግሞ ውጤቱ በጣም ያማረ ሙዚቃ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ አንድ ብልሃትን መማር ወይም ማወቅ ጥሩ ነው፤ ነገር ግን በዛ ያሉ ብልሃቶችን ማወቅ እና መጠቀም ደግሞ የማንበብ ሂደትን ለመቆጣጠር እና አንብቦ መረዳትን ለማረጋገጥ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍም ብልሃቶች ያላቸውን ርስበርሳዊ ትስስር ከግምት ውስጥ በማስገባት አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ፣ ማካካስ፣ ትውስታ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃቶች ላይ ያተኩራል፡፡ ጥናቱ ስሜታዊ ብልሃትን ያላካተተበት ምክንያት ብልሃቱ ከማንበብ ይልቅ ብዙ ጊዜ ለተግባቦት አገልግሎት በተለይ የንግግር ክሂልን ለማጎልበት የሚውል በመሆኑ (Oxford 1990) ጥናቱ ይህንን ብልሃት አላካተተም፡፡

የማንበብ ብልሃት መጠነ ስፋት በማንበብ ተግባር የገጠመን ችግር ለማቃለል ከሚያስችሉ ቀላል የማስተካከያ ብልሃቶች ለምሳሌ ደግሞ ማንበብ፣ መተንበይ፣ አዳዲስ የሆኑ ቃላትን ለመረዳት በአውድ መገመት እሰከ ይበልጥ ሰፊ ወይም አጠቃላይ

ብልሃቶች ለምሳሌ ጭምቀሀሳብ መፃፍ፣ መረጃን ፈልፍሎ ማውጣት፣ ዋናውን ሀሳብ መለየት እና ሌሎች ከአንባቢዎች የቀደመ እውቀት ጋር የሚገናኙ ብልሃቶች ድረስ የሚዘልቅ ነው (Mehrpour et al. 2012:109)::

2.4.4.1 አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት

አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት ተማሪዎች የቀረበውን ፅሁፍ በራሳቸው ለማከናወን፣ ተግባራትን ለመጨረስ እና ወደፊት ለመገስገስ፣ የሚማሩት ትምህርት እንዲሰማቸው ወይም አንዲገባቸው፣ በማንበብ ወቅት የሚገጥማቸውን ችግር ለመፍታት፣ ተግባራትን ለማጠናቀቅ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ነው። አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት በማንበብ ሂደት ከእያንዳንዱ (ከተለየ) የማንበብ ተግባር ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ፅሁፍን ለማብላላት፣ ለመረዳት፣ ለመተንተን በቀጥታ (ወዲያው) ሆን ተብሎ የሚተገበር ነው። አእምሮታዊ ብልሃት የማንበብ ቅደም ተከተልን የሚያመቻች (የሚያፋጥን) ወይም የሚደግፍ ነው (Phakiti 2006:24፣ Griffiths 2004፡4፣O`Malley and Chamot 1990:44)::

አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት በስሩ በርካታ ንዑሳን ብልሃቶችን ያካትታል። እነዚህ ብልሃቶች ገለፃን ለማብላላት ከመድገም እስከ ሐሳብን በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ ድረስ መጠነ ሰፊ ናቸው (Oxford 1990:43)። አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት ውስጥ ከሚካተቱት የተወሰኑቱ የቀደመ እውቀትን መሰረት በማድረግ መገመት፣መተንበይ፣ የተነጠሉ ክፍሎችን በማስተዋል የውህድአሀዱን አደረጃጀት መተንተን፣ ጭምቀ ሐሳብ መፃፍ፣ ማስታወሻ መያዝ፣ መተርጎም፣ መረጃን ፈልፍሎ ማውጣት እና ማሸጋገር ይጠቀሳሉ (O'Malley and Chamot 1990፣ Oxford 1990)። እነዚህ ብልሃቶች በክፍል ውስጥ ካለው አካዳሚያዊ ብቃት ጋር ይገናኛሉ። ምክንያቱም ተማሪዎች ተግባራዊ የሚያደርጉት ቀላል የትውስታ ተግባራትን (ለምሳሌ መረጃን ማስታወስ) ወይም መረጃን መረዳት የሚያስችል በጣም ውስብስብ የሆነ ተግባር ለማከናወን (ለምሳሌ የውህድአሀዱን ክፍሎች ለመረዳት) ያስችላል።

Pressley and Affelerbach (1995) ለተለያየ ተግባር የሚያገለግሉ አእምሮታዊ ብልሃቶችን በተለያዩ መጠነርዕዮች ገልፀዋቸዋል። ለምሳሌ ችግሮችን ለመፍታት እና ለመተንተን የሚያስችሉ (ሁለንተናዊ ብልሃቶች)፣ ወሳኝ የሆኑ ሁነቶች ወይም የፈተና

ፕሮግራሞችን ለማስታወስ (የማጥናት ብልሃት)፣ ማቀድ፣ መንደፍ፣ በሳል ፅሁፍ መፃፍ፣ መከለስ እና መገምገም (የመፃፍ ብልሃት) እና ራስን መጠየቅ፣ አእምሯዊ ምስል ውክልናን ማዋቀር፣ የቀደመ እውቀትን ማነቃቃት፣ ከውህድአሀዱ ለመረዳት አስቸጋሪ የሆነውን ክፍል ማንበብ፣ ውህድአሀዱን መተንበይ እና አሳጥሮ መፃፍ (የማንበብ ብልሃት) ብለው ገልፀውታል።

O`Malley and Chamot (1990:44) Weinstein and Mayer (1986)ን ጠቅሰው አእምሮታዊ ብልሃትን በሶስት ባህሪ ከፍለው ያሳያሉ። እነሱም የመለማመድ፣ የማደራጀት እና የመዘርዘር ወይም የማብራራት ብልሃቶች ናቸው። የመለማመድ ብልሃት ውህድአሀዱን ማስመር፣ ቃላትን ወይም ዐረፍተነገሮችን ድምፅ ከፍ አድርጎ ማንበብ ወይም ለማስታወስ የሚረዳ ምልክት መጠቀም (Mnemonic) የሚፈልጉ ናቸው። እነዚህ ብልሃቶች ለመሳተፍ፣ ጠቃሚ መረጃ ከውህድአሀድ እና ከአእምሮ ውስጥ ወይም ከትውስታ ለመምረጥ የሚያገለግሉ ናቸው። የማደራጀት ብልሃቶች ደግሞ ከውህድአሀድ ውስጥ ዋናውን ሐሳብ መለየት፣ ቢጋር መስራት፣ በፅሁፉ ውስጥ ያለውን ሐሳብ ለመለየት እና ለማደራጀት የተለያየ እና የተለየ ዘዴ መጠቀም ይጠቀሳሉ። የመዘርዝር ወይም የማብራራት ግንዛቤያዊ ብልሃቶች የሚያካትቱት ሐሳብን በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ ወይም ጭምቀሀሳብ መፃፍ፣ ምክንያታዊነትን መፍጠር፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ማነቃቃት፣ ሐሳብን ለሌላ ወገን መግለፅ፣ ውህድአሀዱን መሰረት በማድረግ ጥያቄ መጠየቅ እና መልስ መፍጠር ናቸው።

2.4.4.2 ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት

በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ንድፈሀሳብ አንብቦ መረዳትን ለማጎልበት የማንበብ ብልሃትን መጠቀም ወሳኝ ጉዳይ ነው። Block (1992:320) እንደገለፁት የሁለተኛ ቋንቋ አንባቢዎች በማንበብ ሂደት ቆም ማለት እና ራሳቸውን ማስተዋል ይገባቸዋል። ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት በማንበብ ሂደት እቅድን ተግባራዊ ለማድረግ፣ ራስን እና አንብቦ መረዳትን ለመቆጣጠር እንዲሁም የመማርን ክንውን ውጤታማነት ለመገምገም የሚያስችል ከፍተኛ ደረጃ የማስተዳደር ክሂል ነው (O`Malley & Chamot 1990፣ O`Malley et al. 1985)። እንደ Phakiti (2006:25)፣ Carrell (2006:4)፣ Oxford (1990:136)፣ O`Malley and Chamot (1990:47) አገላለፅ ልእለአእምሮታዊ ብልሃት ተማሪዎች የራሳቸውን የማንበብ ሂደት እና አእምሯቸውን ለመቆጣጠር

ሆንብለው የሚተገብሩት በግልፅ የማይታይ ባህሪ ነው፡፡ ልእለአእምሮታዊነት ስለማሰብ ማሰብ (Thinking about Thinking) ነው ፡፡

በማንበብ ሂደት ተማሪዎች አእምሮታዊ ብልሃቶችን እና ሌሎች ሂደቶችን በመቆጣጠር የተሰጣቸውን ተግባር ለማከናወን እንዲችሉ ልእለአእምሮታዊ ብቃታቸው ላይ ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች ልእለአእምሮታዊ በልሃት አጠቃቀም ብቃታቸው ከፍ ሲል በማንበብ ሂደት ውጤታማ ለመሆን አይቸገሩም፡፡ ውጤታማነት ራስን የመቆጣጠር ችሎታ (ልእለአእምሮታዊነት) ያላቸው አንባቢዎችን እና ታግለው የሚያነቡ ወገኖችን ለመለየት ያስችላል፡፡ አንባቢዎች አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው ዝቅተኛ የሚሆነው አእምሮታዊ እና ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃቶችን የመገንዘብ እና የመጠቀም ችሎታቸው ዝቅተኛ ሲሆን ነው (Oxford 1990፣ O`Mally & Chamot 1990)፡፡

እንደአእምሮታዊ እድገት ትውረት ተማሪዎች በመደበኛ አእምሯዊ አሰራር ደረጃ እድገት ውጤታማ እንዲሆኑ ከልጅነታቸው ጀምሮ ጎልማሳ እስኪሆኑ ድረስ ልእለአእምሮታዊ ችሎታቸውን ማግኘት አለባቸው (Zhang 2012)፡፡ እንደ Zhang (2012፡1063) ገለፃ ግለሰቦች ከአስራሁለት አመታቸው ቀደም ባሉት አመታት ልእለአእምሮታዊ እድገታቸው ከንቱ ከሆነ (ካላደገ) ለአካለ መጠን በደረሱ እና ጎልማሳ በሆኑ ጊዜ የእለት ክንውናቸው እና አካዳሚያዊ ብቃታቸው ጥያቄ ውስጥ ይገባል፡፡ ፀሀፊው በተጨማሪ እንዳስረዱት ማንበብ ንቁ፣ የተገነባ እና ትርጉም የመስራት ሒደት የሚሆነው ተማሪዎች አንድ ጊዜ አእምሮታዊ ሒደታቸውን በልእለአእምሮታዊ ችሎታቸው ከተገነዘቡ እና ከተቆጣጠሩ እንዲሁም ልእለአእምሮታዊ ብልሃታቸውን ለውጤታማ ማንበብ ወሳኝ መሳሪያ ካደረጉ ነው፡፡ በማንበብ ሒደት ልእለአእምሮታዊ ብልሃትን መጠቀም በአጠቃላይ ግንዛቤያዊ፣ ማህበራዊ እና ቋንቋዊ ጉዳዮች ዋጋ እንዲኖራቸው ያግዛል፡፡

Phakiti (2006:25-26) እንደገለፁት ልእለአእምሮታዊነትን ለማጎልበት ሶስት ተላውጦዎች ግምት ውስጥ ይገባሉ፡፡ እነሱም **ግለሰብ**፣ **ተግባር** እና **ብልሃት** ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ተላውጦ የሚያመለክተው የግለሰብን የመረዳት ችሎታ ሲሆን ሁለተኛው ከባድ ተግባርን የመመዘን ሁኔታን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ ግለሰቦች ብልሃትን የመጠቀም ችሎታ ወይም የተሰጠን ተግባር ለማከናወን ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀምን ያመለክታል፡፡ በሌላ አገላለፅ ተግባርን ለማከናወን ከመጀመር አስቀድሞ ግለሰቦች የራሳቸውን ችሎታ እና የተግባሩን ክብደት መመዘን

አለባቸው። በተጨማሪ የተሰጠውን ተግባር በብቃት ለማከናወን ምን አይነት ብልሃት ልጠቀም ማለት ይጠበቅባቸዋል።

እንደ Phakiti (2006፣26) አገላለፅ ሁለት አይነት ልእለአእምሮታዊ እውቀቶች አሉ። እነሱም የመረዳት እውቀት (Knowledge of Cognition) እና መረዳትን የመቆጣጠር እውቀት (Regultion of Cognition/ Knowledge of Regultion) ናቸው። የመረዳት እውቀት በስሩ ሶስት ክፍሎችን ያካተተ ነው። እነሱም ገላጭ (ተጨባጭ) (Declarative)፣ ሂደታዊ (Procedural) እና ሁኔታዊ (Conditional) እውቀቶች ናቸው። ገላጭ እውቀት ግለሰቦች የተነጠሉ ብልሃቶች ላይ ያላቸውን መረዳት የሚያንፀባርቁበት ወይም ብልሃት ምንድን ነው ለሚለው ጥያቄያዊ ሐሳብ መልስ የሚሰጡበት ነው። ሂደታዊ እውቀት ብልሃቶችን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል የሚያስገነዝብ እውቀት ሲሆን ሁኔታዊ እውቀት ደግሞ ጥሩ አንባቢዎች የማንበብ ብልሃቶችን መቼ፣ የት እና ለምን መጠቀም እንዳለባቸው የሚረዱበት እውቀት ነው። መረዳትን የመቆጣጠር እውቀት ደግሞ አጠቃላይ የመገንዘብ ሂደቱን መቆጣጠር የሚያስችል፣ በማንበብ ሂደት ችግር ባጋጠመ ጊዜ ችግሩ የሚፈታበትን መንገድ ለማፈላለግ የሚያስችል ልእለአእምሮታዊ እውቀት ነው።

Lee (2007) በጥናታቸው እንዳመላከቱት ተማሪዎች ሂደታዊ እና ሁኔታዊ እውቀቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ይቸገራሉ። መምህራን ተማሪዎቻቸው ሁኔታዊ እና ሂደታዊ እውቀቶችን እንዲያጎለብቱ በተናጠል ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ በማስረዳት ከረዷቸው ተማሪዎች ወዲያው የተነጠሉ ብልሃቶች ጥቅማቸውን እና እንዴት እንደሚጠቀሙባቸው ይገነዘባሉ። ሌላው መረዳትን የመቆጣጠር እውቀት (የመቆጣጠር እውቀት) ነው። መረዳትን መቆጣጠር የሚያያዘው ከግለሰቦች ቀጥተኛ የማብላላት ደረጃ ጋር ነው። ይህ ፅንሰሀሳብ ስሙ እንደሚያመለክተው በልእለአእምሮታዊ ልምድ ሳቢያ ግለሰቦች በውስጥ መቆጣጠርያ ዘዴ የራሳቸውን መረዳት መቆጣጠር ነው። ለምሳሌ ተማሪዎች አንድን ፅሁፍ ሲያነቡ ፅሁፉን ባለመረዳታቸው ሊደናገጡ ይችላሉ፣ ነገር ግን መረዳት ይፈልጋሉ። በመሆኑም ራሳቸውን ተቆጣጥረው ለመረዳት መጣር የልእለአእምሮታዊነት ልምድ ምሳሌ ነው።

ልእለአዕምሮታዊነት እና የማንበብ ብልሃት ትምህርት አብረው የሚሄዱ ናቸው። Phakiti (2006፡25) ባቀረቡት ጥናት እንደገለፁት የማንበብ ብልሃት ትምህርት

ተማሪዎች ስለአእምሯዊ ሒደታቸው እንዲያስቡ እና ከቀረበው ፅሁፍ ጋር መስተጋብር በመፍጠር ብልሃቶችን ማስተዳደር እንዲችሉ ያበረታታል። መምህራን ይህንን አእምሯዊ ሒደት ሞዴል በማድረግ ማስተማር እና የተማሪዎችን አእምሯዊ ሒደት መቆጣጠር እንዲችሉ ረቂቅ የሆኑ ሁነቶችን ወደ ተጨባጭ ሁነት መቀየር አለባቸው (Oxford 1990፣ O`Mally & Chamot 1990)።

2.4.4.3 ትውስታ የማንበብ ብልሃት

ትውስታ የማንበብ ብልሃት አንዳንድ ጊዜ ለትውስታ የሚረዳ (Mnemonics) ተብሎ ይጠራል (Oxford 1990)። በትውስታ ብልሃት አጠቃቀም መረጃን ማጠራቀም እና ያጠራቀሙትን (ያስቀመጡትን) መረጃ እንደገና መጠቀም ወሳኝ ጉዳይ ነው። የብልሃቱ ዋነኛ መርህ ተማሪዎች እውቀታቸውን ለማዳበር ያነበቡትን ጠቃሚ ሀሳብ ማስቀመጥ እና አስታውሶ እንደገና መጠቀም ነው። እንደ Oxford (1990፡136) አገላለፅ አእምሮ ከመቶ ትሪሊዮን በላይ መረጃዎችን ማስቀመጥ ይችላል። ነገር ግን መረጃው ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የነቃ ትውስታ ሲኖር ነው። ተማሪዎች የትውስታ ብልሃቶችን ሆን ብለው ሲጠቀሙ የቀደመ እውቀታቸውን በማነቃቃት እና ከአዲሱ መረጃ ጋር በማጣመር መረዳታቸውን ያጎለብታሉ።

በማንበብ ሂደት የቀረበን ፅሁፍ ለመረዳት አእምሯዊ ትስስር መፍጠር፣ ምስል እና ድምፅን ተግባራዊ ማድረግ፣ በሚገባ መከለስ (መገምገም) እና ተግባርን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። ተማሪዎች የትውስታ ብልሃቶችን ከልእለአእምሮታዊ ብልሃት (ለምሳሌ ትኩረት መስጠት)፣ ከስሜታዊ ብልሃት (ለምሳሌ ጥልቅ በሆነ አተነፋፈስ ፍርሀትን ማስወገድ) ጋር አጣምረው ሲጠቀሙ የበለጠ ተጠቃሚ ይሆናሉ (Oxford 1990፣ O`Mally & Chamot 1990)።

2.4.4.4 ማካካስ የማንበብ ብልሃት

ማካካስ የማንበብ ብልሃት ተማሪዎች አነስተኛ እውቀት ቢኖራቸውም አዲስ ቋንቋን ለመረዳት ወይም ለማፍለቅ ይረዳቸዋል። ማካካስ የማንበብ ብልሃት በታላሚው ቋንቋ የሰዋስው እና የቃላት እውቀት ማነስን የማስተካከል እቅድን ለማሳካት የሚያገለግል ብልሃት ነው (Lee 2007፣ Oxford 1990፣ O`Mally & Chamot 1990)። እንደ Oxford (1990) ገለፃ ማካካስ የማንበብ ብልሃት ተማሪዎች የገጠማቸውን የእውቀት

ማነስ ለማስተካከል የሚያስችል በተለይ ለጀማሪ እና መካከለኛ ደረጃ ቋንቋ ተማሪዎች እጅግ ጠቃሚ ነው። ብልሃቱ ቋንቋን በሚገባ ለሚጠቀሙበት ወገኖችም ያገለግላል። በተለይ አንዳንድ ጊዜ ያልገባቸው ገለፃ ሲገጥማቸው ለመረዳት ያስችላል።

2.4.4.5 ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት

ማንበብ ግለሰባዊ ቢሆንም የተነበበውን የበለጠ ለመረዳት የሰዎችን ተግባቦታዊ ተሳትፎ ይፈልጋል። ተግባቦትም በሰዎች መካከል የሚፈጠር መስተጋብር ነው። በማንበብ ሂደት የሰዎች ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ ተገቢ ማህበራዊ ብልሃት መጠቀም ጠቃሚ ነው (Oxford 1990፣ O`Mally & Chamot 1990)። በማህበራዊ ብልሃት ስር የሚካተቱት ንኡሳን ብልሃቶች ጥያቄ መጠየቅ፣ ከሌሎች ጋር መተባበር እና ሌሎችን ማዳመጥ ናቸው።

ከላይ የተብራሩት የማንበብ ብልሃት አይነቶች በስራቸው በርካታ ንኡሳን የማንበብ ብልሃት አይነቶች አሉዋቸው። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከላይ ከቀረቡት የማንበብ ብልሃት አይነቶች ውስጥ መርጦ የተጠቀመባቸውን አስራስድስት የማንበብ ብልሃቶች ማብራሪያ በአባሪ ሶስት ላይ ይመለከቱዋል)። ጥናቱ የማንበብ ብልሃቶችን የመረጠበት መነሻ ምክንያት በምእራፍ ሶስት ይመለከታል።

2.5 ጠንካራና ደካማ አንባቢዎች

የተለያዩ የምርምር ስራዎች እንደሚያመለክቱት ከ1970ዎቹ አካባቢ ጀምሮ በጎበዝ እና ሰነፍ (ጠንካራ እና ደካማ) አንባቢዎች የማንበብ ባህሪን መሰረት በማድረግ የሚሰሩ ጥናቶች ትኩረታቸው የአንባቢዎች የአይን እንቅስቃሴ፣ በማንበብ ወቅት የሚፈጠሩ ስህተቶች፣ የዝቅተኛ እና የከፍተኛ ደረጃ ማንበብ ሒደትን መቆጣጠር ላይ ነበር። አንባቢዎች በማንበብ ሒደት የሚጠቀሙበትን የማንበብ ብልሃት፣ ያላቸውን የቀደመ እውቀት እና እውቀታቸው በማንበብ ሒደቱ ላይ እንዴት ተፅእኖ እንደሚፈጥር ጥናት ማድረግ የቅርብ ጊዜ ተሞክሮ ነው(Cohen1998፣Anderson 1991)።

እንደ Pang(2008፡2) አገላለፅ ጥሩ አንባቢዎች ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የማንበብ ሒደት ደረጃን የተካኑ ሲሆን አስፈላጊ መረጃዎችን መልሶ ለማስታወስና ለመጠቀም የተለያዩ ብልሃቶች የሚጠቀሙ መሆኑን ያመለክታሉ። ለምሳሌ ጭምቀ ሐሳብ፣ዋና ዋና ሐሳቦች

ላይ ማስመር፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ያነበቡትን መገምገም እና ውሳኔ ላይ መድረስ የውህድአሀዱን ችግር ፈልፍሎ ማውጣት፣ የትኛውን የማንበብ ብልሃት መቼ መጠቀም እንዳለባቸው ማወቅ፣ የቀደመ እውቀታቸውን መጠቀም፣ በቂ የሆነ የቃላት እውቀት እና የተለያየ የውህድአሀድ መዋቅርን ማወቅ፣ የመጀመሪያ ቋንቋ እውቀታቸውን ለሁለተኛ ቋንቋ መጠቀም ላይ ጠንካራ እንደሆኑ አመላክተዋል።

Anastasiou and Griva (2009:284) እንደገለፁት ጎበዝ አንባቢዎች ከደካሞቹ አንባቢዎች በብዙ መንገድ ይለያሉ። ጎበዞች ከሚታወቁበት መገለጫዎች የተወሰኑት በሚከተለው መንገድ ቀርቧል።

- የማንበብ ብልሃቶችን በእቅድ ለታለመ አላማ ውጤታማ በሆነ መንገድ በተደጋጋሚ ይጠቀማሉ።
- የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን አቀናጅተው በተደጋጋሚ ይጠቀማሉ።
- መረዳታቸውን ከደካሞቹ በበለጠ ይቆጣጠራሉ።
- ስለሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ግንዛቤ አላቸው።
- ተለዋዋጭ(ተለማጭ) በሆነ መንገድ ብልሃቶችን እያቀያየሩ ይጠቀማሉ።
- እንደውህድአሀዱ አይነት እና እንደማንበብ አላማቸው የማንበብ ብልሃቶቻቸውን ያስተካክላሉ።
- በሚያነቡበት ጊዜ ጠቃሚ እና ዝርዝር መረጃዎችን ለይተው ያውቃሉ።
- አውዶችን የበለጠ ውጤታማ በሆነ መንገድ ይጠቀማሉ።
- አዲስ መረጃ እና አስቀድሞ የሚታወቅን መረጃ ለይተው ያውቃሉ።
- በውህድአሀዱ ውስጥ ያለን የወጥነት ችግር ይረዳሉ፤በዚህም ብልሃቶችን በመጠቀም የተፈጠረውን የወጥነት ችግር ግንዛቤ ውስጥ ያስገባሉ።

ጠንካራ አንባቢዎች የታች ላይ(Bottom-up) እና የላይ ታች(Top-down) ማንበብ ሒደት ሞዴሎችን አቀናጅተው በመጠቀም ውጤታማ ናቸው። ነገር ግን ደከም ያሉ አንባቢዎች ከማንበብ ሒደት ሞዴሎች አንዱን ብቻ ይጠቀማሉ። ደካማ አንባቢዎች የታች ላይ ማንበብ ሂደትን ተግባራዊ የሚያደርጉ በመሆናቸው የማንበብ ብልሃቶችን ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ ለማሸጋገር ይቸገራሉ። ተማሪዎች ውጤታማ የሆኑ የማንበብ ብልሃቶችን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ለማድረግ መምህራን የማንበብ ሒደቱን መሰረት ያደረጉ መርሆዎችን መመሪያዎችን እና የአጠቃቀም ተግባራትን ማስተማር አለባቸው።

2.6 የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ በማስተማር የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና አንብቦ የመረዳት ውጤት መጎልበት አለመጎልበቱን መመርመር ላይ ብቻ አላቆመም። ይልቁንም የማንበብ ብልሃቶችን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ በማስተማር የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃትችን እያሸጋገሩ መጠቀማቸው በየቋንቋው አንብቦ የመረዳት ብቃት መጎልበት አለመጎልበቱን መርምሯል።

2.6.1 የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ምንነት እና መገለጫዎች

በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ሂደት ወሳኝ ከሚባሉ ጉዳዮች አንዱ የማንበብ ብልሃት ሽግግር ነው። ሽግግር የሚለው ቃል ትርጓሜውም መሸከም (to carry)፣ መጫን(መሸከም) (to bear) ወይም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማስተላለፍ ወይም መቅዳት (እንደ ስዕል ወይም በድንጋይ ላይ እንደተቀረፀ ምስል መቅረፅ፣ ማተም እንደሆነ (Webster Third New World International Dictionery 1989) ያስረዳል።

በዚህ ዘመን ብዙ ነገሮች ከአንድ ሁኔታ መደሌላ ሁኔታ ሽግግር ያደርጋሉ። ለምሳሌ ብዙ ጊዜ የሚነገረው "የቴክኖሎጂ ሽግግር" እንደምሳሌ ቢወሰድ የሚያስረዳው የቴክኖሎጂ ሀሳቦችን እና ውጤቶችን ከአንዱ ወደ ሌላው (የቴክኖሎጂ አቅም ካለው ወደሌለው) ማሸጋገር (ማስተላለፍ) ነው። ሽግግሮሹ በአእምሮ ውስጥ ያለው የቴክኖሎጂ ሐሳብ ሲሆን ውጤቱ በድርጊት ይገለፃል። የማንበብ ክሂልን በማስተማር ወቅት ተማሪዎች ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ ወይም ከአንድ ሁኔታ ወደሌላ አዲስ ሁኔታ ቋንቋ ነክ እና ኢ-ቋንቋ ነክ ጉዳዮችን ማለትም ድምፅ፣ ምእላድ፣ ቃል፣ እውቀት፣ ክህሎት፣ ሐይል፣ ችሎታ፣ ብልሃት ወዘተ ሽግግር ያደርጋሉ።

ሽግግር የስነልቦናዊ ስነልሳን ፅንሰ ሀሳብ ሲሆን ተማሪዎች ታላሚን ሁለተኛ ቋንቋ ለመማር እንዲረዳቸው ከመጀመሪያ ቋንቋ ወደሁለተኛ ቋንቋ ወይም በተቃራኒው ከሁለተኛ ቋንቋ ወደመጀመሪያ ቋንቋ የተለያዩ ቋንቋ ነክ ጉዳዮች (ድምፅ፣ ምእላድ፣ ቃል... ዲስኮርስ) እና ኢ-ቋንቋ ነክ ጉዳዮችን (ብልሃት፣ ክሂል፣ እውቀት፣ ሀይል፣

ባህል፣ አመለካከት...) ማስተላለፍ ወይም ማጠቃለል የሚችሉበት አእምሯዊ ሂደት ነው (Bimmel et al. 2001:512)። O`Malley & Chamot (1990፡120) እና Liu (2001:1) አንደገለፀት ሽግግር ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር እንዲረዳቸው የቅርብ ጊዜ የመጀመሪያ ቋንቋ እውቀትን ወይም የቅርብ ጊዜ ክህሎታቸውን ወደሁለተኛ ቋንቋ ማስተላለፍ ወይም ማሸጋገር ነው።

የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ሁለት ወይም ከዛ በላይ ቋንቋዎች መመሳሰላቸውን ወይም ልዩነታቸውን መሰረት አድርጎ የሚታይ ክስተት ነው (Talebi 2014:1064፣ Masoud 2011፡208፣ Bimmel et al. 2001:512) ። የሁለት ቋንቋዎች ጠቃሚ ክፍሎቻቸው ወይም መዋቅራቸው ተመሳሳይ ከሆነ ትክክለኛ የቋንቋ ውጤት ወይም አዎንታዊ ሽግግር ይፈጠራል። ትክክለኛ ማለት በአብዛኛው የመጀመሪያ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚቀበሉት ነው። ለምሳሌ የተመሳሳይ ቋንቋዎች አጠቃቀም (the use of cognates) ሊጠቀስ ይችላል። በሌላ በኩል የቋንቋ ተፅዕኖው ስህተት የበዛበት ከሆነ አሉታዊ ሽግግር ይሆናል። አሉታዊ ሽግግር የሚፈጠረው ተናጋሪዎች ወይም ፀሐፊዎች በሁለቱ ቋንቋዎች መካከል ተመሳሳይ ያልሆኑ ክፍሎች እና መዋቅሮች ሽግግር ሲያደርጉ ነው። በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል አዎንታዊ ሽግግር የሚደገፍ ነው Masoud 2011፣ Karim 2011፣ Yamashita 2012፣ Zhang 2012፣ Liu 2001)። እንደ Talebi (2014፣2012) አገላለፅ ቋንቋዎቹ ቢመሳሰሉም ባይመሳሰሉም የጋራ አእምሯዊ ውስጠብቃት በመኖሩ ቋንቋ ነክ እና ኢ-ቋንቋ ነክ ጉዳዮች ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ ሽግግር ደርጋሉ።

Liu (2001:2) Odlin(1989)ን ጠቅሰው የሽግግር ምንነትን እንዲሁም በሽግግር እና በተፅእኖ መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት ጥረት አድርገዋል። ፀሐፊው እንዳስረዱት ሽግግር ከቋንቋ ዘለል ተፅእኖ (Cross Language Influence) ጋር ተመሳሳይነት የለውም። ሽግግር የሚያንፀባርቀው ያለ ሌላ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት የተለያዩ የቋንቋ ባህርያት ከመጀመሪያ ቋንቋ ወደ ሁለተኛ ቋንቋ ወይም በተቃራኒው መካተት ነው። ቋንቋ ዘለል ተፅእኖ ግን የመጀመሪያ ቋንቋ ተፅእኖ ውጤት ሲሆን በሁለተኛ ቋንቋ መማር እና ብቃት ላይ የመጀመሪያ ቋንቋ አስገዳጅ ሁኔታዎች እና በቋንቋ መካከል ያለ የተለያየ አቅጣጫዊ ተፅእኖ ጭምር ነው። ሽግግር በየትኛውም ደረጃ ማለትም

በብልሃት፣ በቋንቋ፣ በዲስኮርስ፣ በቋንቋ አጠቃቀም (ፕራግማቲክስ) ደረጃ ይከሰታል (Talebi 2012፣2013፣ Liu 2001)።

2.6.2 ሽግግር የሚያደርጉ ጉዳዮች እና መገለጫዎች

ሽግግር በተተኳሪው ቋንቋ እና በሌላ በማንኛውም ቋንቋ መካከል ያለ ተመሳሳይነት እና ልዩነት ላይ ተመስርቶ የሚፈጠር የቋንቋ መስተጋብራዊ ውጤት ነው። ተማሪዎች በሁለተኛ (ተተኳሪ) ቋንቋ የተለያዩ ውህድአሀዶችን በማንበብ ሂደት አንዳች የመረዳት ችግር ሲገጥማቸው የመጀመሪያ ቋንቋ እውቀታቸውን፣ ብልሃታቸውን ወይም ክሂላቸውን (በመጀመሪያ ቋንቋ የተማሩትን) ወደሁለተኛ ቋንቋ አምጥተው መጠቀም ቀጥተኛ ሽግግር (Substratum/Overt Transfer) በመባል ይታወቃል። ሌላው የውሰት ሽግግር ወይም ግልብጥ ሽግግር (Borrowing Transfer / Reverse or Backward Transfer) ሲሆን የሚከሰተው የሽግግር አቅጣጫው ከሁለተኛ ቋንቋ ወደመጀመሪያ ቋንቋ ሲሆን ነው። ቀጥተኛ ወይም ግልብጥ ሽግግሩ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይችላል። በሁለቱም የሽግግር አቅጣጫዎች የተለያዩ ቋንቋ ነክ ጉዳዮች (ድምፅ፣ ምዕላድ፣ ቃላት፣ ትርጉም፣ አገባብ፣ ዲስኮርስ ወዘተ) እና ኢ-ቋንቋ ነክ ጉዳዮች (ሀይል፣ እውቀት፣ ፅንሰሀሳብ፣ ብልሃት፣ ክሂል ወዘተ) ሽግግር ያደርጋሉ (Talebi 2012፣ 2013፣Masoud 2011፣ Liu 2001፣ Bimmel 1999)። እንደ Talibi (2012:217) ገለፃ ቋንቋዎቹ በተለያዩ ጉዳዮች ሲመሳሰሉ (በመዋቅር፣ በፅሀፈት ወዘተ) ቋንቋዊም ሆነ ኢ-ቋንቋዊ ጉዳዮች ሽግግር ያደርጋሉ (ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል)። ነገር ግን ቋንቋዎቹ የማይመሳሰሉ ከሆነ የሚከሰተው ሽግግር ኢ-ቋንቋዊ ጉዳዮች ብቻ ነው።

እንደ Cummins (2005:5) አገላለፅ ከማህበራዊ ስነልሳን ሁኔታዎች አንፃር አምስት አይነት ሽግግሮሽ ይከሰታል። እነርሱም 1. የፅንሰ ሐሳባዊ ጉዳዮች ሽግግር (ለምሳሌ የደም ዝውውርን ወይም የካንሰርን ፅንሰ ሐሳብ መረዳት) 2. የቋንቋ እና ባህል እውቀት እና የልእለአእምሮታዊ ብልሃት ሽግግሮሽ (ለምሳሌ እይታዊ ብልሃት፣ ግራፍን ለማቀናጀት የሚያለግል፣ ለማስታወስ የሚረዳ (mnemonic devices)፣ ቃላትን ለመልመድ የሚያገለግሉ ብልሃቶች ወዘተ 3. በቋንቋ አጠቃቀም ያሉ የፕራግማቲክ ጉዳዮች ችግርን ተጋፍጦ ለመግባባት ያለ ፍቃደኝነት፣ የፕራግማቲክ ጉዳዮችን የመጠቀም ችሎታ (ለምሳሌ ተግባቦትን ለማገዝ የሚያገለግሉ አካላዊ እንቅስቃሴዎች ወዘተ) 4. የተለዩ (የተነጠሉ) የቋንቋ ጉዳዮች ሽግግር (የትርጉም እውቀት ለምሳሌ በፎቶ

እና በፎቶሲንተሲስ ውስጥ ያለን ፅንስ ሐሳብ መተርጎም) 5. የስነድምፅ እውቀት ሽግግር በተለያዩ ድምፆች ቅንብር የተዋቀሩ ቃላት እውቀት ናቸው።

Talibi (2013:232)፣ Pavlenko and Travis (2001:191) እንዳንፀባረቁት ሁለትዮሽ አቅጣጫ ሽግግሮሽ (Bidirectional Transfer) ማለት በሁለት ቋንቋዎች ስልት መካከል ያለ ሁለትዮሽ መስተጋብር ነው። ከሁለትዮሽ አቅጣጫ ሽግግር አንፃር ሁለት ቋንቋ ማለት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚያፈልቁት ሁለት (ከዛ በላይ) ቋንቋዎች ጥምረት እንደአማራጭ መጠቀም ነው። ሁለት ቋንቋዎችን በማቻቻል መጠቀም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቋንቋ እንደመጀመሪያ ቋንቋ ዋና ተናጋሪ ስልት አይነት የተጠጋ ነው። Coock (2003:1) ይህን ሀሳብ ሰፋ ባለ መልክ ብዝሀተክህኖ (Multicompetence) የሚል ሙያዊ ቃል በመጠቀም አስተዋውቀዋል። ብዝሀ ተክህኖ ማለት በአንድ አእምሮ ውስጥ ሁለት ወይም ከዛ በላይ ቋንቋ እውቀት ማለት ነው። Coock (2003) እንዳስረዱት በአንድ አእምሮ ውስጥ ያሉ ቋንቋዎች ወይም የመጀመሪያ እና ሌሎች ቋንቋዎች በአጠቃላይ የተነጣጠለ ስልት ከመጠቀም ይልቅ በተወሰነ ደረጃ አንድ የቋንቋ ልዩ ስልት የግድ ይፈጥራሉ። ልሳነ ክልኤነትም ሁለት ያልተሟሉ ወይም የተሟሉ ቋንቋዎች በድምር በአንድ አካል ማለት ሳይሆን አንድ የተለየ ተናጋሪ ከተለየ የቋንቋ ስልት ጋር (a speaker with a unique linguistic system) ማለት ነው (Talibi 2012:217)::

Talibi (2013፣2012)፣ Yamashita (2012)፣ Bimmel (1999)፣ Cummins (1991)፣ Cohen(1991)፣ Alderson (1984)፣ Yorio (1971) እንደገለፁት በሁለተኛ ቋንቋ የማንበብ ሂደት የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ ብቃት ወይም የሁለተኛ ቋንቋ የቋንቋ እውቀት አልያም ሁለቱም በጋራ ተዳምረው ከመጀመሪያ ቋንቋ ወደሁለተኛ ቋንቋ ወይም በተቃራኒው የማንበብ ችሎታም ይሁን የማንበብ ብልሃት ሽግግር እንዲከሰት ወይም እንዳይከሰት የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው።

በመጀመሪያ ቋንቋ እና በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ መካከል ያለን ግንኙነት አስመልክቶ እውቅና ያለው የቋንቋ ርስበርስ ግንኙነት መላምት የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ እንዲከሰት የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ ብቃት ወሳኝ ነው ይላል። እንደ መላምቱ አራማጆች (Carrell 2006፣Cummins 1991) እምነት በመጀመሪያ ቋንቋ እና በሁለተኛ ቋንቋ መካከል የጋራ አእምሮታዊ ችሎታ (Common Underlying Cognitive Ability)

በመኖሩ ሁለቱ ቋንቋዎች በጋራ የሚሳፉበት እና የሚጋሩት የሚታወቅ የአእምሮ ተልኳዊ አሰራር ስልት እንዳለ ያመላክታሉ። ሁለት ቋንቋዎች የተለያዩ ቢሆኑም ርስበርስ ይደጋገፋሉ። በዚህም ተማሪዎች ከሚሰጠው ትምህርት ፅንሰሀሳብ እና እውቀት፣ ልምድ፣ ግንዛቤ በመነሳት የማንበብ ክሂል እና ብልሃት የመጠቀም ችሎታን ይጋራሉ፤ ይደጋገፋሉ። ተማሪዎች ከመነሻው ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ እድገት ካላቸው በተመሳሳይ ደረጃ በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ብቃት ሊኖራቸው እንደሚችል ይታመናል (Talibi 2013፣ Carrell 2006፣ Cummins 1991)።

ከዚህ በተቃራኒው የቋንቋ ጅመራ ደረጃ መላምት የማንበብ ብልሃት ሽግግር እንዲከሰት የሁለተኛ ቋንቋ የቋንቋ እውቀት ቢያንስ ቢያንስ ጅመራ ደረጃ ወሳኝ ነው የሚል አቋም ያራምዳል (Yamashita 1999፣Carrell 1991፣ Yorio 1971)። ሌሎች ወገኖች ደግሞ ተማሪዎች ከመጀመሪያ ቋንቋ ወደ ሁለተኛ ቋንቋ ወይም በተቃራኒው የማንበብ ብልሃት ሽግግር እንዲያደርጉ የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ ብቃት እና የሁለተኛ ቋንቋ የቋንቋ ብቃት ትልቅ ሚና ይጫወታሉ በማለት የሁለቱንም ወገኖች ሀሳብ ይቀበላሉ (Alderson 1984)።

ከፍተኛ ደረጃ አንባቢዎች ከዝቅተኛ ደረጃ አንባቢዎች በተሻለ መልኩ የማንበብ ብልሃቶችን ከአንድ ሁኔታ ወደሌላ አዲስ ሁኔታ ወይም ተግባር ሽግግር የሚያደርጉ መሆናቸውን እንዲሁም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ የማንበብ ብልሃት ሽግግር ማድረጋቸው የማይለይ (የማይታወቅ) መሆኑን አንፀባርቀዋል (Alderson 1984:1-27)። እንደ Alderson (1984) አገላለፅ የሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ችግር የቋንቋ እና የማንበብ ችግር ነው። በተለይ ዝቅተኛ የቋንቋ ብቃት ደረጃ ያላቸው ተማሪዎች የማንበብ ችግራቸው መንስኤ የቋንቋ ችግር ሲሆን ጀማሪ ደረጃ የቋንቋ ብቃት ላይ ከደረሱ ግን ከመጀመሪያ ቋንቋ ወደሁለተኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃትም ሆነ የማንበብ ልምድ ሽግግር ያደርጋል።

Cummins (2005፡5) Baker(2007)ን ጠቅሰው እንደገለፁት የግለሰቦች አእምሮታዊ መሳርያ ወይም የማከናወኛ ስልት አንድ ጊዜ ከተከሰተ ቋንቋ ዘለል ሽግግሮሽ ይፈጠራል። የቋንቋ ርስበርስ ግንኙነት መላምት በግለሰቦች አእምሮ ውስጥ ያለውን ሽግግር በሶስት ምስሎች አስደግፈው አብራርተዋል።

ከታች በምስል ሁለት ንጥል አእምሯዊ ውስጠ ብቃት ሞዴልን (The Separate Underlying Proficiency/SUP Model) የሚያመላክት ሲሆን ከቋንቋ ርስበርስ ግንኙነት መላምት የተለየ አማራጭ ትልምን የሚያሳይ ነው። ይኸውም በአንድ አእምሮ ውስጥ ያሉ ሁለት ወይም ከዛ በላይ ቋንቋዎች ተነጣጥለው አለመገናኘታቸውን በዚህም ምክንያት ምንም አይነት የእውቀት፣ የልምድ፣ የብልሃት ልውውጥ የማይካሄድ መሆኑን ያመላክታል (በዚህ ሁኔታ ሽግግሮሽ የለም)።

ምስል ሁለትት፡-ንጥጥል ውስጠ ብቃት

ምስል ሶስት፡-የጋራ ውስጠ ብቃት ሞዴል



Cummins (2005፡5)

Cummins (2005) እንዳስረዱት በቋንቋ ዘለል ምንም ሽግግር ከሌለ ወይም የመጀመሪያ ቋንቋ እና ሁለተኛ ቋንቋን የሚያገናኝ አእምሯዊ ውስጠ ብቃት ከሌለ በግለሰቦች አእምሮታዊ የመከወኛ ስልት ውስጥ መረጃ የሚከማችው ተነጣጥሎ ነው። ንጥል ውስጠ ብቃት ሞዴል የሚያመለክተው አንደኛ ጉዳይ የሁለተኛ ቋንቋ ብቃት ከመጀመሪያ ቋንቋ የተለያየ መሆኑን እንዲሁም በቋንቋ መጋለጥ (በቤት ወይም በትምህርት ቤት) እና በታላሚው ቋንቋ ውጤት መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት መኖሩን ሲሆን ሁለተኛው ጉዳይ የሁለተኛ ቋንቋ እና የመጀመሪያ ቋንቋ ብቃት የተለያየ ከሆነ አንባቢዎች በሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩት የማንበብ ብልሃት ወደ መጀመሪያ ቋንቋ ወይም በተቃራኒው ከመጀመሪያ ቋንቋ ወደ ሁለተኛ ቋንቋ ሽግግር የማያደርግ መሆኑን ነው።

ሌላው በምስል ሶስት የተንፀባረቀው በባለ አንድ ፊኛ የተወከለ አእምሯዊ የጋራ ውስጠ ብቃት ሞዴል (Common Underlying Proficiency/CUP Model) ነው። ይህ ሞዴል የሚያመለክተው በመጀመሪያ ቋንቋ እና በሁለተኛ ቋንቋ መካከል ያለ የልሳነ ክልኤ ብቃት በቋንቋ ዘለል ግንኙነት የጋራ ወይም ርስበርስ ግንኙነት ብቃት ተደርጎ የሚወሰድ መሆኑ ነው Cummins (2005)። በሌላ አገላለፅ በልሳነ ክልኤ ትምህርት አውድ የጋራ አእምሯዊ ውስጠ ብቃትን ተግባራዊ ማድረግ የሚያመለክተው አእምሮታዊ ወይም አካዳሚያዊ እውቀት እና ችሎታ በሁለቱም ቋንቋ ውስጥ አካዳሚያዊ ትግበራ ላይ ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ነው። ምስሉ እንደሚያመላክተው ከሁለት በአንዱ ቋንቋ ያለው ልምድ ወይም ብልሃት ወደሌላው ቋንቋ የሚሻገር እና ተገቢ (ተመጣጣኝ) የሆነ መነሳሳት እና በትምህርት ቤትም ሆነ በሰፊው ከባቢ የመጋለጥ እድል በመስጠት በሁለቱም ቋንቋ ያለ ልምድ እና ውስጠ ብቃት በጋራ የሚጎለብት መሆኑን ነው። ይህ ሞዴል ከንጥጥሎሽ ሞዴል ተቃራኒ ሲሆን ትኩረት የሚያርገው በአእምሮ ውስጥ ያሉ ቋንቋዎች አንድ ስልት(One System/ Unitary System) ይጠቀማሉ የሚል ነው። በዚህ ሞዴል አተያይ በአእምሮ ውስጥ ቋንቋዎቹ ተመጣጣኝነት ያላቸው በመሆኑ የመጀመሪያ ሁለተኛ እያሉ ቋንቋዎቹን ለይቶ ማየት አይቻልም Cummins (2005) ።

ከታች የቀረበው ምስል አራት ደግሞ ከታች የተገናኘ መዋቅር ያለው እና ከላይ የተለያየ ጥንድ ተራራ የተመሰለ ሲሆን የቋንቋ ርስበርስ ግንኙነት ሞድልን (አእምሯዊ የጋራ ውስጠ ብቃት) ይወክላል። እንደ Talibi (2015፡35) አገላለፅ ይህ ሞዴል የሚያንፀባርቀው ቋንቋዎች በተለያየ ሁኔታ የተለያዩ ቢሆንም አእምሯዊ የጋራ ውስጠ ብቃት ያላቸው በመሆኑ ይደጋገፋሉ። በዚህ ሁኔታ ድምፅ ምእላድ፣ ቃል፣ እውቀት፣ ችሎታ፣ አመለካከት፣ ሀይል፣ ክሂል፣ ብልሃት ወዘተ ከአንዱ ቋንቋ መደሌላው ቋንቋ ሽግግር እንደሚያደርግ ያመላክታል።

ምስል አራት፡- የቋንቋ ርስበርስ ግንኙነትን የሚያሳይ ሞድል



Cummins (2005:6)

በተግባር ላይ የዋለ የምርምር ስራ እንዳመለከተው ለምሳሌ የእንግሊዝኛ እና የጃፓንኛ ቋንቋዎች የሰዋስው እውቀትን በተመለከተ አነስተኛ ግንኙነት ያላቸው ቢሆንም በማንበብ እና መፃፍ እውቀት ጉልህ ግንኙነት እንዳላቸው (አንብቦ መረዳት፣ ቃላት) እንዲሁም በቃላዊ ቋንቋ የፕራግማቲክስ ጉዳይ (የተግባቦት ስልት) ሽግግር መኖርን አመላክቷል (Cummins 2005) ።

እንደ Talibi (2013፡432-436) ገለፃ ቋንቋዎች ቢመሳሰሉም ባይመሳሰሉም አእምሯዊ የጋራ ውስጠ ብቃት ያለ በመሆኑ የማንበብ ብልሃት ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ ሽግግር ያደርጋል። የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችም በራሳቸው ቋንቋ ጥሩ የማንበብ ብልሃት አዳብረው ቢመጡም ተገቢውን የማንበብ ብልሃት መጠቀም እና አዎንታዊ ሽግግር እንዲኖር ጥረት ማድረግ ካልቻሉ በሁለተኛ ቋንቋ ያለውን አዲስ ስልት ለማጎልበት ይቸገራሉ። ቋንቋዎች አንዱ ከአንዱ በብዙ ጉዳይ ይለያያሉ። ይሁን እንጂ የመጀመሪያ ቋንቋ እና ለትምህርት የሚቀርበው ሁለተኛ ቋንቋ በአካዳሚያዊ ክህሎት፣ ማንበብ እና መፃፍን በማጎልበት ሒደት፣ የፅንሰ ሐሳብ ምስረታ፣ የይዘት እውቀት፣ ብልሃትን ከማጎልበት አንፃር የሚጋሯቸው ብዙ ጠቃሚ ጉዳዮች በመኖራቸው ይደጋገፋሉ (Yamashita 2007፣ Cummins 1991፣ Alderson 1984)::

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ጋር በመዋቅር፣ በስርአተ ፅህፈት ወዘተ ባይመሳሰል ምን ማድረግ እንዳለባቸው ማወቅ ተገቢ

ነው። አንዳንድ ተማሪዎች የመጀመሪያ ቋንቋ እና የሁለተኛ ቋንቋ ስርአተዕህፈት የተለያየ ቢሆንም ራሳቸውን በማዘጋጀት እና በማስተካከል እንዲሁም የማንበብ ብልሃታቸውን በመጠቀም ይለማመዳሉ። ሌሎች ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ ፍፁም የሚቸገሩ አሉ። የተለያዩ የምርምር ስራዎች (Romance & Vital 2009፣ Talebi 2013፣ 2011፣ Akamatsu 2003) እንደሚያመለክቱት ስርአተዕህፈት የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ላይ ተፅእኖ ሊፈጥር የሚችል ሚና እንዳለው አስረድተዋል። ተማሪዎች በራሳቸው ቋንቋ የድምፅ ወካይ ፊደል ስርአት (Grapheme Phoneme) ወይም እይታዊ ፍንጭ (Visual Cues) ላይ ብቻ ከተወሰኑ እና ቋንቋው ኢ-አልፋቤታዊ ቢሆን ሁለተኛ ቋንቋን በሚማሩበት ጊዜ ራሳቸውን ካላዘጋጁ የማንበብ ክሂላቸውን ለማጎልበት ይቸገራሉ።

የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ በአንብቦ መረዳት ላይ ያለው አስተዋፆ ምን እንደሚመስል በአለም አቀፍ ደረጃ ውስን ጥናቶች ተካሂደዋል። ለአብነት Talebi (2013) ያቀረቡት "Cross-Linguistic Transfer (from L1 to L2, L2 to L1 and L2 to L3) of reading Strategies in a Multi-competent Mind" ተጠቃሽ ነው። በጥናቱ Talebi (2013፡232) የብዝሀ ብቃት አተያይን ሲጠቅሱ የመጀመያ፣ ሁለተኛ እና ተጨማሪ ሌሎች ቋንቋዎች በአእምሮ ውስጥ የሚስተናገዱበት ልዩ ስልት አለ። ይህ ስልት ፍፁም የተለያየ አይደለም። በጥቅል አገላለፅ አንድ ቋንቋ በሌላ ቋንቋ ላይ ተፅእኖ አለው። በዚህ ሀሳብ ላይ ተመስርቶ የቀረበው ይህ ጥናት አላማ ያደረገው የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤ እና አንብቦ የመረዳት ውጤት መጎልበት አለመጎልበቱን መመርመር ነው። በዚህ ጥናት ሶስት ንኡሳን ጥናቶች ተካተዋል። እነሱም ቋ1 (ፐርሺያ) በ ቋ2 (እንግልዚኛ)፣ ቋ2 (እንግሊዝኛ) በ ቋ3 (አረብኛ) እና ቋ2 (እንግሊዝኛ) በ ቋ1 (ፐርሺያ) ከማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ አንፃር ያላቸው ተፅእኖ ምን እንደሚመስል መመርመር ነው።

በዚህ ጥናት ንኡስ አንድ የጥናት ክፍል የተነሳው የምርምር ጥያቄ 1. በመጀመሪያ ቋንቋ (ፐርሺያ) የማንበብ ብልሃትን ማስተማር በመጀመሪያ ቋንቋ (ፐርሺያ) እንዲሁም በሁለተኛ ቋንቋ (እንግሊዝኛ) የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤ ላይ ተፅእኖ (አስተዋፆ) አለው? 2. በመጀመሪያ ቋንቋ (ፐርሺያ) የተሰጠው የማንበብ ብልሃት ትምህርት በመጀመሪያ ቋንቋ (ፐርሺያ) እንዲሁም በሁለተኛ ቋንቋ (እንግሊዝኛ) አንብቦ የመረዳት ውጤት እንዲጎለብት አስተዋፆ አለው? የሚል ነው። በሁለተኛው ንኡስ

ጥናት የተነሳው ጥያቄ በሁለተኛ ቋንቋ (እንግሊዝኛ) የማንበብ ብልሃትን ማስተማር በሁለተኛ ቋንቋ (እንግሊዝኛ) እና በሌላ ሁለተኛ ቋንቋ (አረብኛ) አንብቦ የመረዳት ብቃት እንዲጎለብት አስተዋፆ አለው ? የሚል ነው፡፡ በሶስተኛው ንኡስ ክፍል የተነሳው ጥያቄ በሁለተኛ ቋንቋ (እንግሊዝኛ) የማንበብ ብልሃትን ማስተማር በሁለተኛ ቋንቋ (እንግሊዝኛ) እና በመጀመሪያ ቋንቋ (ፐርሺያ) የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤ እና አንብቦ የመረዳት ውጤት እንዲጎለብት አስተዋፆ አለው ? የሚል ነው፡፡

በዚህ በተጠቀሰው ጥናት የተንፀባረቀው የጋራ ግኝት (በሶስቱም ንኡሳን ጥናቶች) በአንደኛው ተተኳሪ ቋንቋ የማንበብ ሂደት የታየው መሻሻል በሌላኛው ቋንቋ የማንበብ ሂደት እንዲሻሻል አስተዋፆ አድርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሹ በሶስቱም ጥናቶች ላይ የታየ ቢሆንም በማንበብ ውጤት ላይ ያሳየው አስተዋፆ የተለያየ ነው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የሽግግሮሹ አቅጣጫ እና በዚህ ሂደት የነበረ የቋንቋ ብቃት ጣልቃ ገብነት ነው በማለት ጥናቱ አስረድቷል፡፡ ይህ የሚያመላክተው የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ አንብቦ የመረዳት ውጤት እንዲሻሻል አስተዋፆ ያለው መሆኑን ነው፡፡

2.7 የማንበብ ብልሃትን መርጦ በመጠቀም ወቅት ያሉ እንቅፋቶች

በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ሂደት በተማሪዎች ላይ የሚታይ የቋንቋ ብቃት ማነስ (የቃላት ቅርፅ እና ፍቺ፣ ምእላዳዊ ስርአት፣ አገባብ፣ ትርጉም ፣ዲስኮርስ፣ የፅህፈት ስርአት)፣ የማንበብ ብቃት ማነስ (አንብቦ የመረዳት ችግር፣ የማንበብ አላማ አለመኖር፣ ራስን እና አንብቦ መረዳትን መቆጣጠር አለመቻል)፣ የእውቀት ማነስ (ለማንበብ ተግር የቀረበን ውህድአሀድ በመረዳት ሂደት ያለባቸውን ቋንቋዊ ክፍተት ለመሙላት እና አንብቦ ለመረዳት አንባቢዎች የሚያብላሉት የቀደመ እውቀት)፣ ባህላዊ እውቀት፣ መነሳሳት እና ስነልቦና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው (Bernhardt 1991:32)

በማንበብ ሂደት አንብቦ መረዳትን ለመቆጣጠር የማንበብ ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን መርጠው በመጠቀም ሂደትም ከላይ የተጠቀሱት (የቋንቋ ብቃት፣ የማንበብ እና የእውቀት ማነስ ወዘተ) ችግሮች እውክታ ወይም እንቅፋት ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተማሪዎች ፆታ፣

የስነልቦና አይነት፣ በብልሃት አጠቃቀም ላይ ያለ አመለካከት እና መነሳሳት ፣ ዜግነት፣ የመማር ስልት ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው (Griffiths 2004፡14)፡፡

የማንበብ ብልሃትን መርጦ በመጠቀም ሂደት ልዩነት ከሚፈጥሩ ጉዳዮች የተማሪዎች የፆታ ልዩነት አንዱ ተጠቃሽ ምክንያት ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት የፆታ ልዩነት ላይ የተደባለቀ አቋም አለ፡፡ Ehrman and Oxford 1989፣ Ehrman and Oxford (1989)፣ Oxford and Nyikos (1989)፣ Green and Oxford (1995) የፆታ ልዩነት የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ልዩነትን ያስከትላል የሚል ግኝት አንፀባርቀዋል፡፡ Ehrman and Oxford (1990) ደግሞ የብልሃት አጠቃቀም ከፆታ ልዩነት ጋር የሚያዛምደው ነገር የለም በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከጥናቶቹ ድምዳሜ መረዳት የተቻለው የፆታ ልዩነት ከብልሃት አጠቃቀም ጋር ጎልቶ የታየ ልዩነት ባይኖርም ሴት ተማሪዎች ከወንዶች በበለጠ የማንበብ ብልሃት የመጠቀም ፍላጎት እንዳላቸው አሳይቷል፡፡

የተማሪዎች የስነልቦና አይነት በብልሃት አጠቃቀም ላይ ተፅእኖ አለው (Griffiths 2004፡14)፡፡ Ehrman and Oxford (1990) የቋንቋ መማር ብልሃት እና የስብእና አይነት መካከል ያለውን ዝምድና በማጥናት ያንፀባረቁት ግኝት እንዳመላከተው የተማሪዎች የስብእና አይነት በብልሃት አጠቃቀም ላይ ጠንካራ የሆነ ተፅእኖ አለው፡፡ የጥናቱ ግኝት እንዳመላከተው ጠንካራ በራስ መተማመን ያላቸው ተማሪዎች፣ በንቃት ከማይሳተፉ እና አነስተኛ ትጋት ካላቸው ተማሪዎች በተሸለ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀማቸው እና አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው ከፍተኛ ነው፡፡

ሌላው በቋንቋ የመማር ብልሃት አጠቃቀም ላይ ያለ አመለካከት እና መነሳሳት ያለውን አዎንታዊ እና አሉታዊ ተፅኖን በተመለከተ Oxford and Nyikos (1989)፣ Ehrman and Oxford (1990) ጥናት አድርገዋል፡፡ ጥናት አቅራቢዎቹ በአሜሪካን 1,200 ተማሪዎች ላይ ባካሄዱት ጥናት በተማሪዎች የማንበብ ብልሃት ምርጫ ላይ ያለ አመለካከት እና መነሳሳት ዋነኛ ተፅእኖ ፈጣሪ ተላውጦዎች መሆናቸውን በግኝታቸው አመላክተዋል፡፡ ይኸውም ለማንበብ እና አንብቦ ለመረዳት አዎንታዊ አመለካከት እና ከፍተኛ መነሳሳ ያላቸው ተማሪዎች ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ይጠቀማሉ የሚል ድምዳሜ በጥናታቸው አመላክተዋል፡፡

ዜግነት በተማሪዎች የማንበብ ብልሃት አመራረጥ እና አጠቃቀም ልዩነት እንዲፈጠር አንድ ምክንያት እንደሆነ የተለያዩ ጥናት አቅራቢዎች ያመላክታሉ። Griffiths and Parr (2000) በጥናታቸው እንዳንፀባረቁት የአውሮፓ ተማሪዎች በሌላ ሀገር ካሉ ተማሪዎች በተሻለ ቋንቋ የመማር ብልሃቶችን በተለይ ቃላትን ለመምረጥ፣ ለማንበብ፣ መስተጋብር ለመፍጠር፣ አሻሚነትን ለመታገስ ወዘተ ጉልህ በሆነ መልኩ በድግግሞሽ ይጠቀማሉ። Yang (1998) በታይዋን ባደረጉት ጥናት ዜግነታቸው ከአውሮፓ የሆኑ ተማሪዎች መዝገበ ቃላትን መጠቀም ጨምሮ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ጠንካራ መሆናቸውን በግኝታቸው አመላክተዋል።

ሌላው እና ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው የተማሪዎች የመማር ስልት ነው። Willing (1998) በአውስትራልያ ብዛት ያላቸው ወጣት ስደተኞች (በአውስትራልያ እየኖሩ የሌሎች ሀገሮች ቋንቋዎችን የሚጠቀሙ) ስደተኞች ላይ ጥናት አድርገዋል። ጥናታቸው የተማሪዎች የመማር ስልት (አተገባበር) እና የብልሃት አጠቃቀም ከተለያየ ግለታሪካዊ ተላውጦዎች (ዝርያ፣ እድሜ፣ ፆታ፣ ብቃት እና በአውስራልያ የቆይታ ጊዜ) በማነፃፀር ለማየት ሞክረዋል። የጥናታቸው ግኝት እንዳመላከተው እንደሌሎች ከላይ እንደተገለፁት ተላውጦዎች የተማሪዎች የመማር ስልት የማንበብ ብልሃት ምርጫ ላይ ተፅእኖ ሊፈጥር እንደሚችል አመላክተዋል። የተማሪዎች የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ብቃት ልዩነትም ወሳኝ ጉዳይ ነው(Griffiths 2004፡15)።

ከላይ የተዘረዘሩትን የልዩነት ምክንያቶችን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ባይቻልም የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀም ብቃት ከፍ በማድረግ ተማሪዎች ጠቃሚ የሆኑ ብልሃቶችን በመምረጥ በተደጋጋሚ እንዲጠቀሙ ማድረግ ተገቢ ነው። ለዚህ ደግሞ ዋነኛው መንገድ የማንበብ ብልሃትን ማስተማር ነው።

2.8 የማንበብ ብልሃትን ማስተማር

የማንበብ ብልሃት የቋንቋ መማር ብልሃት ትውረትን መሰረት ያደረገ እንደመሆኑ ማስተማርያ ዘዴዎቹም ቋንቋ መማር ብልሃት ላይ የተሞከሩ ናቸው። ብልሃትን ማስተማር በተለያየ ስያሜ እንደሚጠራ Oxford (1990:202) ይገልፃሉ። ይኸውም “የብልሃት ስልጠና”፣ “የመማር ስልጠና”፣ “ለመማር መማር ስልጠና”፣ “የመማር ዘዴ ስልጠና” እና “ለተማሪዎች የዘዴ መነሳሳት” ናቸው። በተለያዩ ጥናቶች ውስጥ በሰፊው

የሚያገለግለው “የብልሃት ትምህርት (ስልጠና)” ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የሚጠቀምበት ነው።

ተማሪዎች እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው መማር ይፈልጋሉ። መምህራንም እንዴት የማንበብ ሒደትን ማስተማር ወይም ማመቻቸት እንዳለባቸው መማር ይፈልጋሉ። መማር የሰው ልጅ ከፊል ሁኔታዊ እና የታሰበ ክሂል አካል ሲሆን የመማር ሒደቱ በራስ መር መማር እና ብልሃትን በመጠቀም ሒደት የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን በትምህርት መታገዝ አለበት። የብልሃት ትምህርት በተለይ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በጣም ወሳኝ ነው (Oxford 1990፣ O`Malley & Chamot 1990)።

ቋንቋን መማር በንቃት ራስን መምራት ይፈልጋል። በተለይ ተማሪዎችን በንቃት በማሳተፍ ተግባቦታዊ ብቃታቸውን ለማጎልበት እና ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ መምህር ብቻ የሚመራው የማስተማር ዘዴ አዋጭ አይደለም። የማንበብ ብልሃትን በማስተማር ሂደት ተማሪዎች በጥንድ እና በቡድን እየሆኑ በንቃት ሊሳተፉ ይገባል። የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ ማስተማር ተማሪዎችን በንቃት በማሳተፍ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል በጣም ጠቃሚ አቀራረብ እንደሆነ (Oxford 1990:201) ያስረዳሉ።

O’Malley and Chamot (1990:152) የመማር ብልሃቶችን ለማስተማር የሚያስችሉ አቀራረቦች እንዳሉ ዘግበዋል። እነሱም ብልሃቶችን ከአውድ ነጥሎ ማስተማር በተቃርኖ ብልሃቶችን አቀናጅቶ ማስተማር፣ በግልፅ ወይም በቀጥታ ማስተማር በተቃርኖ ግልፅ ባልሆነ መንገድ ማስተማር ናቸው።

2.8.1 ብልሃቶችን ከአውድ ነጥሎ ማስተማር በተቃርኖ አቀናጅቶ ማስተማር

የመማር ብልሃት ላይ መሰረት አድርጎ የሚሰጥ ትምህርት በአብዛኛው ትኩረት የሚያደርገው የመማር ብልሃቶቹ ላይ ወይም በክፍል ውስጥ ከሚያገለግለው ቋንቋ ጋር ወይም ከትምህርቱ ይዘት ጋር ተቀናጅቶ እንዲቀርብ ማድረግ ነው።

O’Malley and Chamot (1990:152) Jones et al. (1987)ን ጠቅሰው እንደገለፁት ተማሪዎች ይዘት እና ብልሃት ላይ ከማተኮር ይልቅ ብልሃትን የማብላላት ክሂል እድገት ላይ ሙሉ በሙሉ ትኩረት ካደረጉ ብልሃቶችን በሚገባ ይማራሉ በማለት ብልሃቶችን

ከአውድ ነጥሎ ማስተማር ጠቀሜታ አለው የሚሉ ወገኖች እንዳሉ ይገልፃሉ። ምሁራኑ Wenden (1987)ን ጠቅሰው እንደገለፁት ከዚህ በተቃራኒው ብልሃቶችን ከአውድ ነጥሎ ከማስተማር ይልቅ ከአውድ ጋር አጣምሮ ማስተማር የበለጠ ውጤታማ ነው የሚሉ ወገኖችም አሉ። ምክንያቱም ብልሃቶችን ከአውድ ጋር አቀናጅቶ ማስተማር እውናዊ አካዳሚያዊ እና ቋንቋ ነክ ተግባራትን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመተግበር እንዲሁም ብልሃቶችን ከተሰጠው ተግባር ጋር በተመሳሳይ ወደሌላ ተግባር ሽግግር ለማድረግ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ብለው ስለሚያምኑ ነው። O'Malley and Chamot (1990፡152) Danseveau(1985) የተባሉ የምርምር ባለሙያ ያደረጉትን ጥናት በምሳሌነት ጠቅሰዋል። ይኸውም ተማሪዎች ብልሃቶችን ሳይንሳዊ ይዘት ካላቸው ፅሁፎች ጋር አቀናጅተው ለማስተማር ጥረት ያደረጉበት ነው። በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገባቸው የኮሌጅ ተማሪዎች ሳይንስ ተኮር የሆነውን ፅሁፍ በማንበብ በቀላሉ ይዘቱን ለማስታወስ እንደረዳቸው አስረድተዋል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ብልሃቶችን ከአውድ ጋር አቀናጅቶ ማስተማር ጠቃሚ መሆኑን ነው። የማንበብ ብልሃቶችን ከአውድ ጋር አቀናጅቶ ማስተማር ጠቃሚ በመሆኑ በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍም ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል።

2.8.2 በቀጥታ (በግልፅ) ማስተማር በተቃርኖ ግልፅ ባልሆነ መንገድ ማስተማር

የማንበብ ብልሃቶችን በማስተማር መርሀግብር ብልሃቶችን ነጥሎ በማስተማር እና አቀናጅቶ በማስተማር ሒደት የሚነሳው ተመሳሳይ ክርክር ብልሃቶችን በቀጥታ (በግልፅ) ማስተማር ወይስ ግልፅ ባልሆነ መንገድ ማስተማር ይጠቅማል የሚል ነው።

O'Malley and Chamot (1990፡153) እንዳስረዱት ብልሃቶችን በቀጥታ በማስተማር ሒደት ተማሪዎች የትምህርቱ አላማ እና ግብ በግልፅ ይነገራቸዋል። በአንፃሩ ግልፅ ባልሆነ መንገድ ብልሃቶችን ተማሪዎች ሲማሩ ከትምህርት ክንውን እና ከቀረበ ፅሁፍ መዋቅር ጋር ይቀርባሉ። በሒደቱም ግልፅ ባልሆነ መንገድ በተማሩት መሰረት የብልሃቶችን ጠቀሜታ ለማውጣት ጥረት ያደርጋሉ። ነገር ግን በዚህ ሒደት ተማሪዎች ይህንን ለምን እንደሚያደርጉ ምንም ምክንያት በግልፅ አይነገራቸውም። ግልፅ ባልሆነ መንገድ የማንበብ ብልሃትን ማስተማር የብልሃቶችን ምንነት በተመለከተ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ጠቃሚ ነው። ነገር ግን ዝርዝር ትግበራን ለማስተማር ውስንነት ይስተዋልበታል።

ቀደም ሲል ግልፅ ባልሆነ መንገድ ብልሃቶችን ማስተማር ላይ መሰረት ያደረጉ ጥናቶች ይሰሩ ነበር። ጥናቶቹ በግኝታቸው ላይ ተመስርተው ያቀረቡት ሐሳብ የስልጠናው ዘዴ መሻሻል እንዳለበት ነው። O'Malley and Chamot (1990:154) እንደገለፁት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተሰሩ ያሉ ጥናቶች እንዳመላከቱት በስልጠናው ልእለአእምሮታዊ ክፍሎችን በማከል፣ የብልሃቶችን አላማ እና ጠቀሜታ በግልፅ በማስረዳት እንዲሁም ስልጠናውን በማሻሻል ተማሪዎች ብልሃቶችን እንዲያስተዳድሩ እና እንዲቆጣጠሩ ማድረግ አስችሏል። በዚህም የልእለአእምሮታዊ ክፍሎች በስልጠናው ውስጥ መካተት ተማሪዎች የበለጠ ብልሃቶችን እንዲጠቀሙባቸው እና ከአንድ ተግባር ወደ ሌላ አዲስ ተግባር ለማሸጋገር እንዲችሉ ረድቷቸዋል።

O'Malley and Chamot (1990:191) እንደገለፁት የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ ማስተማር ስልታዊ በሆነ መንገድ ለውጥ በማድረግ "አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋን መማር አቀራረብ" (Cognitive Academic Language Learning Approach /CALLA) በመባል ይታወቃል። አቀራረቡ በውስጡ ያካተታቸው ቁምነገሮች የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የመማር ልምድ ማግኘት፣ ይዘትን ማስተማር፣ አካዳሚያዊ ቋንቋን ማጎልበት እና ብልሃትን ማስተማር ናቸው። አእምሮታዊ አካዳሚዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ እንደመርህ የሚከተለው መጀመሪያ ማስተማር፣ ጥያቄ መጠየቅ፣ ተማሪዎችን ማቀናጀት (በቡድን ማደራጀት)፣ ለመሳተፍ ፍቃደኛ ያልሆኑ ተማሪዎችን መለየት፣ እንዲሳተፉ እድል በመስጠት ምላሻቸውን ማዳመጥ እና ምጋቤ ምላሽ መስጠት ናቸው። በዚህ አቀራረብ ተማሪዎች ብልሃቶችን ቢማሩ አካዳሚያዊ እድገታቸው እንደሚያጎለብቱ አስረድተዋል (O'Malley and Chamot (1990)።

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ለትምህርት አላማ የቀረቡትን ብልሃቶች ለተተኳሪ ተማሪዎች ለማስተማር የተከተለው አቀራረብ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር ነው። በትምህርት ባለሙያዎች ዘንድ ያለው የጋራ እምነት የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ ማስተማር (Explicit Reading Strategy Instruction) በማንበብ ሒደት ተገቢ የማንበብ ብልሃቶችን በመጠቀም አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለማጎልበት አወንታዊ አስተዋፆ ያለው መሆኑን ነው (Lencioni 2013፣ Ballou 2012፣ Medina 2011፣ McNamara 2007፣ National Reading Panal 2000፣Cohen et al. (1998)። ምሁራኑ እንደገለፁት ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን እንዴት መጠቀም እንዳባቸው

ሲገነዘቡ አንብበው በመረዳት ትርጉምን በንቃት በአእምሯቸው ያዋቅራሉ፡፡ የማንበብ ብልሃት ቅደም ተከተላዊ፣ ምክንያታዊ፣ ፍላጎት እና ጥረት የሚፈልግ በመሆኑ ተማሪዎችን በግልፅ ማስተማር ያስፈልጋል፡፡ የማንበብ ብልሃት ትምህርት በጭፍን የሚመራ ሳይሆን በትውረት እና በምርምር የታገዘ ነው፡፡

የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር የማንበብ ብልሃቶችን ምንነት፣ አላማ እና ተግባራዊ አገልግሎታቸውን ከአውድ ጋር በማስተሳሰር በተደራጀ ቅደም ተከተል ለማስተማር የሚያስችል ነው፡፡ እንደ Hollingsworth and Ybarra (2009) አገላለፅ በግልፅ ማስተማር ብልሃቶችን በብዛት እና በማቀናጀት ማስተማር ያስችላል፡፡ ይዘትንም ከብልሃት ጋር አዋህዶ በግልፅ ለማስተማር የተደገፈ እና በሚገባ የተዋቀረ የማስተማር ሂደት ነው፡፡ በግልፅ ወይም በቀጥታ ማስተማር አንብቦ መረዳትን ብቻ ሳይሆን ማንኛውንም ርዕሰ ጉዳይ ለማስተማር የሚያገለግል ምርምር መሰረት ያለው እና አዎንታዊ ተሞክሮ (ግኝት) የተንፀባረቀበት ነው (Lencioni 2013)::

Oyetunji (2013)፣ Lencioni (2013)፣ Mehrpour et al. (2012)፣ Zhang (2012)፣ Ballou (2012)፣ Medina (2011)፣ Zhang (2008)፣ Steinagel (2005)፣ Keer & Verhaeghe (2005)፣ Cohen et al. (2005)፣ Bimmel et al. (2001)፣ Oxford (1990)፣ O`Mallye and Chamot (1990) እና ሌሎች የማንበብ ብልሃቶችን በተለይ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በግልፅ ማስተማር ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ ትልቅ አስተዋፆ አለው በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በተቃራኒ Kellerman (1991) ተማሪዎች አስቀድመው የማንበብ ብልሃቶችን በመጀመሪያ ቋንቋ ያጎለበቱ (ሊያጎለብቱ የሚችሉ በመሆናቸው) እና ወደሁለተኛ ቋንቋ የሚያሸጋግሩ በመሆናቸው የማንበብ ብልሃትን በሁለተኛ ቋንቋ ማስተማር አስፈላጊ አይደለም በማለት ይከራከራሉ፡፡

Hollingsworth and Ybarra (2009) የ Kellerman (1991)ንን ሀሳብ አጥብቀው በመቃወም የማንበብ ብልሃትን ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ማስተማር ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው ይላሉ፡፡ ለዚህም ያስቀመጡት ምክንያት በግልፅ ማስተማር በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ መረዳትን፣ የተቀመጠ አላማን፣ የቀደመ እውቀት መነቃቃትን፣ በገለፃ ሂደት የተማሪዎችን ክሂል ማጎልበትን፣ ሞዴል ማድረግን፣ ይዘት ማቅረብ እና ራስ መር የሆነ ተግባርን ለማከናወን የሚያስችል የተለየ ቅርፅ ያለው መሆኑ ነው፡፡ የትምህርት አቀራረቡ በተለይ ዝቅተኛ ብቃት ያላቸው ተማሪዎች

ብልሃቶችን ሲማሩ የማንበብ ፍላጎታቸው እንዲጨምር እና ብልሃቶችን ሆን ብለው ወደ መጠቀም በመሸጋገር የአንብቦ መረዳት ብቃታቸው እንዲጎለብት ያደርጋል (Snow 2002)።

የማንበብ ብልሃትን የማስተማር ግብ ተማሪዎች ነፃ፣ ራስ መር፣ ውጤታማ እና ለትምህርት ተነሳስቶ ያላቸው እንዲሆኑ ማድረግ ነው። Byrd et al. (2001) እና Zhang (2012) እንዳመለከቱት ተማሪዎች ራስ መር ሲሆኑ **ራስን የማወቅ** (የመቆጣጠር)፣ **ብልሃቶችን የማወቅ** (በሚገባ መጠቀም) እና **ተግባርን የማወቅ** ግንዛቤያቸው ይጎለብታል። የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ የማይማሩ ተማሪዎች መማራቸውን፣ እድገታቸውን እና የማንበብ ብልሃት የመጠቀም ብቃታቸውን ይጠራጠራሉ።

እንደ Carrell (2006) አገላለፅ የማንበብ ብልሃቶችን ለተማሪዎች ማስተማር ጠቃሚ ነው። ነገር ግን ብልሃቶችን ማስተማር ከመጀመሩ በፊት ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው። እነሱም ተተኳሪ ተማሪዎች ባሉበት የትምህርት ደረጃ የትኞቹን ብልሃቶች መርጦ ማስተማር እንደሚያስፈልግ መወሰን (የፍላጎት አሰሳ ማድረግ)፣ የተመረጡትን የማንበብ ብልሃቶች እንዴት አቀናጅቶ ማስተማር እንደሚያስፈልግ ማቀድ፣ የማስተማሪያ ዘዴ መምረጥ፣ ብልሃት ተኮር ትምህርት አቀራረቡ ከተቀረፀው መርሀትምህርት ጋር በማቀናጀት ማስተማር ወይስ ነጥል ማስተማር የተሻለ ነው ብሎ መመርመር (ብልሃቶችን ከአውድ ጋር አጣምሮ ማስተማር ጠቃሚ እንደሆነ Carrell (2006) ይገለልፃሉ)፣ ተማሪዎች ለትምህርቱ ትኩረት በመስጠት አዲስ እውቀት እንዲገበዩ በማነሳሳት ትምህርቱን መጀመር ናቸው።

ውጤታማ በሆነ መንገድ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ለማስተማር በክፍል ውስጥ ተግባራዊ መደረግ ያለባቸው ቅደም ተከተሎች ዝግጅት፣ ሞዴል በመሆን አቅርቦት፣ ልምምድ (በተግባር መሞከር)፣ ተማሪዎች ራሳቸውን እንዲገመግሙ ማድረግ፣ ማስፋፋት ወይም ከአንድ ሁኔታ ወደሌላ ሁኔታ ማሸጋገር እና ግምገማ ናቸው (Zhang 2012:1070)። እነዚህ ሂደቶች በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በሚሆኑበት ጊዜ ትኩረት የሚሹ ክንውኖች የሚከተሉት ናቸው (Medina 2011፣ Zhang 2012፣ Bimmle et al. 2001፣ Carrell 2006)።

- የማንበብ ብልሃት ምንነትን እና አይነታቸውን ግልፅ በሆነ አቀራረብ ማስረዳት፣
- የተለያዩ ፅሁፎችን በማንበብ ሂደት የማንበብ ብልሃቶችን መጠቀም ምን ያህል ጠቀሜታ እንዳለው ማስረዳት፣
- ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን እንዴት በተግባር መጠቀም እንደሚችሉ መምህር ሞዴል በመሆን (እየተገበሩ) ማሳየት፣
- ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን መቼ እና የት መጠቀም እንዳለባቸው ማሳየት፣ መምራት፣ ማገዝ እና በግባር እንዲለማመዱ ማድረግ
- ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በትክክል መጠቀም አለመጠቀማቸውን መከታተል፣ ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም አለመጠቀማቸውን ለማረጋገጥ ራሳቸውን እንዲገመግሙ ማበረታታት፣
- ተማሪዎች በተማሩት መሰረት የማንበብ ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም አለመጠቀማቸውን መመዘን ናቸው።

የማንበብ ብልሃትን በግልፅ በማስተማር ሒደት ተግባራትን ለመፍጠር፣ ተማሪዎች ሙሉ ትኩረት እንዲያደርጉ ለማነሳሳት፣ የቀደመ እውቀታቸውን ለማነቃቃት ተግባራትን በንዑሳን ደረጃዎች ከፋፍሎ ለማቅረብ፣ በእያንዳንዱ ደረጃ በቂ የሆነ ዝግጅት፣ ልምምድ እና የመምህር ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት ያስችላል (Snow 2002):: የማንበብ ብልሃት ትምህርት ንድፈ ሐሳብ ላይ ከማተኮር ይልቅ ተማሪዎች ብልሃቶችን እንዴት፣ መቼ እና የት መጠቀም እንዳለባቸው ማስተማር ላይ ማተኮር አለበት። በአጠቃላይ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር ተማሪዎች የትምህርቱን ይዘታዊ መዋቅር ለመለየት እና ለመገምገም ፣ የቀረበን ፅሁፍ ለመረዳት እና በፅሁፍ ውስጥ ያሉ አዳዲስ ቃላትን ለመለየት፣ በፍጥነት የማንበብ ብልሃቶችን እንዲጠቀሙ ማድረግ ያስችላል። ብልሃትን በግልፅ ማስተማር በክፍል ውስጥ የታሰበውን ትምህርት ለማቅረብ የሚመች ቅደም ተከተል ያለው ከፍተኛ መካከለኛ እና ዝቅተኛ የትምህርት ብቃት ያላቸው ተማሪዎችን ሁሉ ለማገዝ አመቺ የሆነ ዘዴ ነው።

2.9 የጥናቱ ትውረታዊ ማዕቀፍ

ማንበብ ለመማር (አካዳሚያዊ ግብን ለማሳካት)፣ ለምርምር፣ ሙያዊ ብቃትን ለማሻሻል፣ ግለሰባዊ እድገት ለማጎልበት የሚያስችል ክሂል ነው (McDonough & Shaw 1993)። በማንበብ ሂደት ለማንበብ ተግባር የቀረበን ውህድአሀድ አንብቦ ለመረዳት ተማሪዎች የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን ሆን ብለው በንቃት ቢጠቀሙ ውጤታማ ይሆናሉ (Affelrbach et al. 2003፣ Williams 2002፣ Dole et al. 1996)። የማንበብ ብልሃት የተለየ፣ ሆንተብሎ የሚተገበር፣ ግብ ያለው አእምሯዊ ሂደት ወይም ባህሪ ሲሆን ተማሪዎች አንብበው መረዳታቸውን ለመቆጣጠር፣ በውህድአሀድ ውስጥ ያለውን መረጃ ለመተርጎም፣ ቃላትን በመረዳት የውህድ አሀዱን ትርጉም ለማዋቀር የሚያገለግል መሳርያ ነው (Phakiti 2006፣ Griffiths 2004)።

በተለያዩ ጥናቶች ውስጥ (Zhang 2008፣ Rubin et al. 2007፣ Phakiti 2006፣ Cohen & Chi 2005፣ Anderson 1991፣ Chamot and O`Malley 1994፣ Oxford 1990፣ O`Malley and Chamot 1990) እንደተመላከተው ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲጠቀሙባቸው ማስተማር ቅድምያ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው። የማንበብ ብልሃት ትምህርት መሰረታዊ አላማ ተማሪዎች በማንበብ ሂደት ማንኛውም አስቸጋሪ ሁኔታ ሲገጥማቸው ብልሃቶችን ተግባራዊ በማድረግ ችግር የመፍታት ችሎታ እንዲኖራቸው ያደርጋል፤ የተማሪዎችን የመማር ነፃነት ያጎለብታል፤ ተማሪዎች መደበኛ የመማርያ ክፍል ውስጥ ባይሆኑ እንኳን ስለትምህርታቸው ሀላፊነት እንዲሰማቸው በማድረግ ራስ መር ተማሪ እንዲሆኑ ያስችላል።

በፍጥነት በሚለዋወጥ በዚህ ዘመን እና በአለማቀፋዊ የህይወት ስልት የትምህርት አሰጣጥ በቀደመው ዘዴ ላይ ተወስኖ የሚቀርበት ምንም ምክንያት የለም። በፍጥነት በሚለዋወጥ አለም ከሚመጡ አዳዲስ አስተሳሰቦች ጋር የማስተማር ትውረቶች እና ሞዴሎች አብረው መራመድ አለባቸው። አዲስ ነገር መከተል አዲስ የመሆን ስሜትን ለማምጣት ብቻ ሳይሆን በመማር ማስተማር ሂደት የተሻለ መፍትሄ የሚሆን አካዳሚያዊ አቅጣጫ በመከተል ውጤት ማስመዝገብ ጠንካራ ምክንያት ነው። በዚህ መሰረት ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ **ግንባታዊነት** (Constructivism) የመማር ትውረት ላይ

የተመሰረተ ነው። ጥናቱ በዚህ የመማር ትውረት ላይ የተመሰረተበት ዋነኛ ምክንያት ትውረቱ መማርን መገንባት እና መገንዘብ ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ ነው። የማንበብ ብልሃት የማስተማር አላማም ተማሪዎች ብልሃቶችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው በመገንዘብ እውቀትን ፣ ፍቺን በአእምሯቸው መገንባት እና መልሶ መጠቀም እንዲችሉ ማድረግ ነው።

2.9.1 ግንባታዊነት

ግንባታዊነት የመማር ትውረት ሲሆን የሚያንፀባርቀው ግለሰቦች (ተማሪዎች) በመማር ማስተማር ሂደት በንቃት ተሳታፊ በመሆን ትርጉምን የሚያዋቅሩ (የሚገነቡ) መሆናቸውን ነው። ግንባታዊነት የእውቀት ምንነትን እና አንድ ግለሰብ እንዴት ይማራል፣ እንዴት ያውቃል የሚለውን ፅንሰሀሳብ በማጤን የግለሰቦች የመማር እና የእውቀት ግንባታ ላይ ያተኩራል። በግንባታዊነት ትውረት አተያይ ማንበብ ግለሰባዊ እና ማህበራዊ ክንውን ነው። ማንበብን በመማር ማስተማር ሂደት አንባቢው የሚያከናውነው ንቁ የፍቺ ግንባታ የትውረቱ የትኩረት አቅጣጫ ነው (Rowell & Palmer 2007፣ Zhang 2008፣ Tracey and Morrow 2006፣ Derry 1996) ።

ግንባታዊነት ከፍልስፍና፣ ከስነልቦና፣ ከትምህርት እና ከማህበራዊ ጥናት ዘርፍ ጋር የሚዛመድ ትውረት ሲሆን አዲስ ሀሳብ ማፍለቅ፣ ሳይንስ እና ቋንቋ ለማስተማር የሚያስችሉ ብልሃቶችን መጠቀምን፣ አውዳዊነትን፣ ችግር መፍታትን፣ ትብብርን ወዘተ የሚያበረታታ ነው (Zhang 2008፣ Derry 1996)። በግንባታዊነት ትውረት አተያይ መማር የሚከሰተው ግለሰቦች (ተማሪዎች) የገጠማቸው አዲስ እውቀት አስቀድሞ ከነበራቸው የቀደመ (ዳራዊ) እውቀት ጋር ሲገናኝ ነው። ተማሪዎች የነበራቸውን ዳራዊ እውቀት ከአዲሱ መረጃ ጋር ማቀናጀት የሚችሉት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በንቃት ሲሳተፉ ነው። መማር የነቃ አእምሮ ተሳትፏዊ ውጤት የሚሆነው ተፈጥሯዊ (ጤናማ) እና ትጉህ አእምሯዊ ሁኔታ ሲኖር ነው (Woolfolk 1998)።

እንደ Zhang (2008:91)፣ Evangelisto (2002:1)፣ Derry (1996:165) በግንባታዊነት እውቀት እውነትን የሚገልፅ (የሚያስረዳ) ሲሆን ሁሉም እውቀት የሚገነባው ደግሞ የቀደመ እውቀት ላይ ተመስርቶ ነው። ተማሪዎች እንደባዶ ማስቀመጫ አይነት አይደሉም። ይልቁንም የቀደመ እውቀታቸውን በማነቃቃት እና መስተጋብር በመፍጠር

የቀረበው ትምህርት አካል በመሆን ትምህርቱ ስሜት እንዲሰጣቸው በንቃት የሚሳተፉ (የራሳቸውን ትርጉም የሚያዋቅሩ) ንቁ የጉዳዩ ባለቤት ናቸው። ትውረቱ ግንባታዊ መምህራን የመማር ልምድ በመፍጠር ተማሪዎች አንዱ ከአንዱ (ርስበርስ) በተለየ መንገድ እንዲሁም ከመምህራኑ ግምት በተለየ አቅጣጫ እንዲማሩ ያደርጋል (ያበረታታል)።

Tracey and Morrow (2006፡47) የግንባታዊነት ትውረት አቀንቃኝ የሆኑትን Smith (1971)ን በመጥቀስ እንደገለፁት መማር የገጠመኝ ሁነት አይደለም። ይልቁኑም መማር ሁኔታዊ (Situationalized) ሲሆን በሂደቱ አእምሮ ተፈጥሯዊ እና ቀጣይ በሆነ መንገድ ሆንብሎ የሚያከናውነው አነቃቂ፣ አነሳሽ ወይም ሀይል ሰጪ ድርጊት አለ። በመሆኑም መማር በሁኔታዎች ላይ የተገነባ ተተግባሪ፣ ትርጉም አዘል እና እውናዊ አውድ ነው። በግንባታዊነት ትውረት አተያይ እውቀትን እና ክሂልን ወይም ብልሃትን ነጥሎ ማስተማር አይቻልም። እውቀት እና ብልሃት በአውዳዊ መረጃ የተጋመዱ ናቸው። ይህ መርህ የሚፈልገው መምህራን የመማር ማስተማር ሂደቱን ማደራጀት፣ ተማሪዎችን በማወያየት፣ በማድነቅ እና የተረዱትን እንዲያንፀባርቁ በማድረግ የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ማዘጋጀት፣ ብልሃት እና እውቀታቸውን ከተግባር ጋር በማቀናጀት ውጤታማ በሆነ መንገድ በተግባር እንዲጠቀሙ መምራት ነው።

Tracey and Morrow (2006:46) የግንባታዊነት መለያ ባህርያት በማለት ሶስት ጠቃሚ ነጥቦችን አንፀባርቀዋል። የመጀመሪያው ግንባታዊነት ከባህሪያውያን በተለየ መልኩ መማር ለውጭ ተመልካች ምንም አይነት የሚታይ ምልክት የሌለው ውስጣዊ የአሰራር ዘዴ ነው (ባህርያውያን መማር ድግግሞሽ፣ ማነቃቅያ እና አዎንታዊ ምላሽ መስጠት የሚፈልግ የሚታይ ባህሪ ነው ይላሉ)። ሁለተኛው ጉዳይ መማር የግለሰቦች መላምታዊ ፈተና ልምድ ውጤት ነው። ለምሳሌ በማንበብ ሂደት አንድ ተማሪ በሚያነበው ፅሁፍ ውስጥ የማያውቀው አንድ ቃል ቢያጋጥመው ቃሉን ለመረዳት ይገምታል። በገመተው መሰረት ዐረፍተነገሩ ትክክል (ስሜት ሰጪ) መሆኑን ያረጋግጣል። ዐረፍተነገሩ ስሜት ካልሰጠው እንደገና ይገምታል። በዚህ ሂደት ተማሪው ዐረፍተነገሩ ስሜት እስኪሰጠው ድረስ ጥረት ያደርጋል። ግንባታዊነት በመማር ላይ ያንፀባረቀው ሶስተኛው ጉዳይ መማር መረጃን ፈልፍሎ የማውጣት ወይም ምልክት ላይ ተመስርቶ ድምዳሜ ላይ የመድረስ ሂደት ውጤት ነው። ምክንያት ላይ የተመሰረተ

ድምዳሜ ላይ መድረስ ትርጉምን በመገንባት ሂደት ያለን ክፍተት የመሙላት ሂደት ነው (Zhang 2008፡ Tracey & Morrow 2006፡ Derry 1996)።

እንደ Wikipedia (2016:1-20) አገላለፅ ግንባታዊነት ትውረት ላይ የተመሰረተ የትምህርት አቀራረብ የክፍል ገፅታ ተማሪዎችን በንቃት የሚያሳትፍ ነው፣ የመማር ማስተማር ከባቢያዊ ሁኔታው ዲሞክራሲያዊ ነው፤ ክንውኖቹ መስተጋብራዊ እና ተማሪ ተኮር ናቸው፤ መምህራን መማር ማስተማሩን ምቹ በማድረግ ተማሪዎች ሀላፊነት የሚወስዱ እና ነፃ እንዲሆኑ የሚያደርጉበት ነው። ትውረቱ ራስመር መማር፣ የተማሪዎች የቀደመ እውቀት፣ አውዳዊ መማር፣ ትብብራዊ መማር፣ እውናዊ የመማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያዎች መጠቀም፣ ማህበረ አእምሮታዊ የመማር ማስተማር ሁነት ላይ የበለጠ ትኩረት ያደርጋል።

ግንባታዊነት ሁለት አይነት ክፍሎች አሉት (Rowell and Palmer 2007:4) እነሱም አእምሮታዊ ግንባታዊነት (Cognitive Constructivism) እና ማህበራዊ ግንባታዊነት (Social Constructivism) ናቸው። እንደ ፀሀፊዎቹ ገለፃ ሁለቱ የግንባታዊነት አይነቶች ወሳኝ እና የተሟሉ መሆናቸውን በመጥቀስ በፅንሰ ሐሳቦቹ መካከል ያለውን ግንኙነት በሚከተለው መንገድ ገልፀውታል። አእምሮታዊ እና ማህበራዊ ግንባታዊነት በብዙ ሐሳቦች ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም በአንድ ወሳኝ ጉዳይ ልዩነት አላቸው። ይህም በተማሪዎች እና በመምህራን የተሳትፎ አይነት፣ ስፋት እና መጠን ነው። እያንዳንዱ ሞዴል የየራሱ ጥረትና ሀላፊነት ይፈልጋል። ማህበራዊ ግንባታዊነት የበለጠ ትኩረት የሚያደርገው በትምህርት ሒደት የበለጠ ችሎታ ያላቸው ወጣቶች ወይም አቻዎች ያነሰ ክህሎት ያላቸው ተማሪዎችን በመርዳት ላይ የተመሰረተ ማህበራዊነትን ማደራጀት ነው። አእምሯዊ ግንባታዊነት ደግሞ ትኩረት የሚያደርገው በተማሪ ተኮር ከባቢ እውቀትን ለመመስረት የሚቻለው ግለሰብ (እያንዳንዱ) ተማሪ ፍላጎቱን እና ምኞቱን ለመደገፍ በሚያደርገው ጥረት ነው። በአእምሯዊ ግንባታዊነት መማር በዋናነት በግለሰባዊነት ሙከራ ላይ ያነጣጠረ ነው።

ግንባታዊነት ትውረት ከሚያንፀባርቃቸው ፅንሰሀሳቦች አንዱ ማንበብ ግለሰባዊ እና ማህበራዊ ክንውን መሆኑ ከላይ ተገልጿል። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍም የግንባታዊነት አካል የሆኑትን **አእምሮታዊ ግንባታዊነት** (Cognitive Constructivism) እና **ማህበራዊ ግንባታዊነት** (Social Constructivism) ትውረታዊ አተያዮች ይከተላል።

2.9.1.1 አእምሮታዊ ግንባታዊነት

በአእምሮታዊ ግንባታዊነት ትውረት አተያይ መማር አለምን ለመገንዘብ የሚያገለግል ጥረት ውጤት ነው። ተማሪዎች መገንዘባቸውን ውጤታማ ለማድረግ ሁሉንም አእምሯዊ መሳሪያዎች (Mental Tools) ይጠቀማሉ። በአእምሮታዊ ግንባታዊነት ትውረት አተያይ ሰዎች ልምድ የመጋራት ተነሳሽነት ያላቸው፣ ችግሮችን ለመፍታት መረጃዎችን የሚያፈላልጉ፣ ውጤታማ በሆነ መንገድ አዲስ ሀሳብ ለማግኘት እውቀታቸው እምን ድረስ እንደሆነ የሚያውቁ ንቁ ተማሪዎች ናቸው (Woolfolk 1998:247)።

የአእምሮታዊ ግንባታዊነት ትውረት ከቋንቋ መማር ብልሃት ትምህርት ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው ነው። በትውረቱ አተያይ ተማሪዎች ቋንቋ የመማር ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የግለሰቦች አእምሯዊ ብቃት ወይም አእምሯዊ ችሎታን ማጎልበት ያስፈልጋል። ለዚህ ወሳኙ ነገር ደግሞ ብልሃቶችን በግልፅ በማስተማር ግንዛቤያቸውን እና የአጠቃቀም እውቀታቸውን ማጎልበት እንደሆነ በትውረቱ ይንፀባረቃል (Ertmer & Newby 2013፣ Rowell & Palmer 2007፣ Derry 1996) ። እንደአእምሮታዊ ግንባታዊነት አተያይ በየትኛውም የክፍል ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች መረጃን በማሰባሰብ እና የራሳቸውን እውቀት በማዋቀር ሂደት በንቃት ይሳተፋሉ። እውቀት በአንድ ቦታ ቋሚ አይደለም ። ተማሪዎች አዲስ ልምድ ባካበቱ (በተማሩ) ቁጥር እውቀታቸው ቀስበቀስ እያደገ እና እየተለወጠ እንዲሄድ በማድረግ የቀደመ እውቀታቸውን ያጎለብታሉ።

በአእምሮታዊ ግንባታዊነት ትውረት አተያይ ማንበብ አንባቢዎች በአእምሯዊ እውቀት መዋቅራቸው ከተጠራቀመው እውቀት በመነሳት እና በቀረበው ፅሁፍ ከተገኘው አዲስ ሀሳብ ጋር በማጣመር ትርጉምን የመገንባት ተግባር ነው። በዚህም ሂደት አንባቢዎች ከሚነበበው ፅሁፍ እና ከማንበቡ ግብ ጋር መስተጋብር በመፍጠር ፅሁፉን ለመገንዘብ ጥረት ደርጋሉ።

በአእምሮታዊ ግንባታዊነት ስር የሚጠቀሰው አእምሯዊ የእውቀት መዋቅር ትውረት (Schema Theory) በዚህ ጥናት በተለይ ትኩረት የተሰጠው አንደኛው ትውረት ነው። አእምሮታዊ ግንባታዊነት ትውረት መማር ሁልጊዜ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ነው፤

ይህ የቀደመ እውቀት አእምሯዊ የእውቀት መዋቅር (Schema) ነው Rowell & Palmer 2007:3)። አእምሯዊ የእውቀት መዋቅር አእምሯዊ ንድፍ (Mental Pattern) ወይም የእውቀት መዋቅር (Knowledge Stracture) በመባልም ይታወቃል (Tracey & Morrow 2006)። በአእምሯዊ የእውቀት መዋቅር ትውረት አተያይ በአእምሮ ውስጥ ባለ ትውስታ መረጃ በመልክ በመልክ (ቅርፅ ባለው ሁኔታ) ተደራጅቶ ይቀመጣል። በሌላ አገላለፅ አእምሯዊ የእውቀት መዋቅር ስለእውቀት እና ያ የእውቀት ውክልና እንዴት በእውቀት አጠቃቀም ላይ ውጤት እንዳለው የሚያሳይ ሲሆን ሁሉም የእውቀት መዋቅሮች በፅንሰሀሳባዊ ክፍል ያላቸው ቦታ አእምሯዊ የእውቀት መዋቅር ነው (Tracey & Morrow 2006፣ Phakiti 2006፣ Rumelhart 1994፣ Anderson & Pearson 1984)።

በአእምሯዊ የእውቀት መዋቅር ትውረት አተያይ ሰዎች ማንኛውንም ነገር የሚያዋቅሩት በአእምሯዊ የእውቀት መዋቅራቸው ነው። ለምሳሌ ሰዎች ስለሰዎች፣ ስለቦታ፣ ስለቋንቋ፣ ስለሂደት፣ ስለክህሎት፣ ስለብልሃት የእውቀት መዋቅር አላቸው። እንደ Tracey & Morrow (2006:52) አገላለፅ አእምሯዊ የእውቀት መዋቅር ትውረት የራሱ መገለጫ ባህሪ አለው። የትውረቱ አንደኛ መገለጫ ባህሪ የእውቀት መዋቅር ግለሰባዊ መሆኑን ማንፀባረቁ ነው። በእያንዳንዱ ተማሪ መካከል ያለ የእውቀት መዋቅር ልዩነት በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ አለው። ትውረቱ እንደሚያንፀባርቀው አንድ ሰው ስለአንድ ጉዳይ አስቀድሞ የሚያውቀው ነገር አለ ማለት ግለሰቡ ስለጉዳዩ አዲስ መረጃ ሲቀርብለት መማር ይችላል ማለት ነው። ሌላው የአእምሯዊ የእውቀት መዋቅር ትውረት መገለጫ ባህሪ የእውቀት መዋቅር የሚተጣጠፍ (Pliant) እና የሚስፋፋ (Expandeble) መሆኑን ማንፀባረቁ ነው። ለምሳሌ ተማሪዎች በአንድ ርእሰ ጉዳይ ላይ የቀረበን ፅሁፍ ከአነበቡ በኋላ ከርእሰነገሩ ሀሳብ ጋር የተያያዘ ሌላ ፅሁፍ ቢያጋጥማቸው የእውቀት መዋቅራቸውን በማስፋፋት ይጠቀማሉ። የማንበብ ብልሃቶችን ከአንድ ሁኔታ ወደሌላ አዲስ ሁኔታ እያስፋፉ መጠቀም በምሳሌነት ሊጠቀስ ይችላል። በአእምሯዊ የእውቀት መዋቅር ትውረት አተያይ አሁን ያለ የእውቀት መዋቅር በቋሚነት ይቀያየራል ።

Anderson and Pearson (1984:257) እንደገለፁት በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች የተለያየ አእምሯዊ የእውቀት መዋቅር አላቸው። ይኸውም አንባቢዎች

በይዘት ላይ ያላቸው አእምሯዊ የእውቀት መዋቅር (ለምሳሌ ስለሰዎች፣ ስለነገሮች)፣ በማንበብ ሂደት ያላቸው አእምሯዊ የእውቀት መዋቅር (ፊደልን መለየት፣ የገረፍታ ንባብ ማድረግ፣ ምክንያት ላይ የተመሰረተ ድምዳሜ ላይ መድረስ፣ ጭምቀሀሳብ መፃፍ ወዘተ)፣ በተለያየ ውህድአሀድ መዋቅር ላይ ያለ የእውቀት መዋቅር (ለምሳሌ ተራኪ፣ ገላጭ ወዘተ) ይጠቀሳል። እንደ Anderson and Pearson (1984) አገላለፅ የአንባቢዎች የእውቀት መዋቅር ብቃት ከመረዳት ብቃት ጋር የተያያዘ ነው። ለምሳሌ አንድ ተማሪ ስለስደት ያለው የእውቀት መዋቅር ከሌላኛው ተማሪ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ቢሆን በስደት ዙሪያ ፅሁፍ ሲቀርብ ስለስደት አስቀድሞ እውቀት ያለው የመረዳት ብቃቱ ይጨምራል።

Zhang (2008፡91) እንደገለፁት የእውቀት መዋቅር በላይ ታች ማንበብ ሂደት (Top-Down Process) ተማሪዎች በቀደመ እውቀታቸው ስለአለም እና በእነርሱ ዙሪያ ስላስተዋሉት ሀቅ ያላቸውን ግንዛቤ የሚያንፀባርቅ ነው። በትውረቱ አተያይ ለማንበብ ተግባር የሚቀርብ ውህድአሀድ በራሱ የያዘው ትርጉም የለም። አንባቢዎች የራሳቸውን ልምድ፣ ስሜት እና ባህላዊ እውቀት ወደውህድአሀዱ በማምጣት እና በማጣመር ውህድአሀዱ ስሜት እንዲሰጥ ያደርጋሉ።

Celce-Murcia (1991፡176) የእውቀት መዋቅርን የግንዛቤ ደረጃን ማጎልበቻ (Building Blocks of Cognition) በማለት የሚጠሩት ሲሆን የተጣራን መረጃ በመተርጎም፣ ከትውስታ ውስጥ መረጃ በመመለስ፣ ድርጊትን በማቀናበር ዋና እና ንኡሳን ግቦችን በመወሰን፣ ምንጭን በማመላከት በአጠቃላይ በማንበብ ብልሃት ውስጥ ያለውን የሂደቱን ፍሰት በመምራት ይጠቀሙበታል። እንደ Celce-Murcia (1991፡177) አገላለፅ ሁለት አይነት አእምሯዊ የእውቀት መዋቅር አለ። አንደኛው መደበኛ አእምሯዊ የእውቀት መዋቅር ሲሆን የሚያንፀባርቀው የውህድአሀዳዊ የመተረክ እና የአደረጃጀት መዋቅር እውቀት (Knowledge of the rhetorical and organizational stracture of the text) ነው። ሁለተኛው ይዘታዊ የእውቀት መዋቅር ነው። ይህም የሚገልፀው በተለየው ትምህርታዊ ይዘት ላይ ያለውን እውቀት (Knoweldge of the subject matter of a particular topic) ነው። ፀሀፊዋ እንዳስረዱት አንባቢዎች በቂ የይዘት እውቀት መዋቅር ከሌላቸው፣ ያላቸውን የእውቀት መዋቅር ወደዝግ የእውቀት መዋቅር ይለውጡና

የመጣውን መረጃ ከእውቀት መዋቅሩ ጋር ለማገናኘት ይሞክራሉ። ውጤቱም የእውቀት መዋቅር ጣልቃገብነት ይሆናል።

Tracey and Morrow (2006:51) ከአእምሯዊ የእውቀት መዋቅር አንፃር የእውቀት መዋቅር የሚቀየርባቸውን (በማንበብ ሂደት) ሶስት ሂደቶች አንፀባርቀዋል። እነሱም እውቅና የመስጠት፣ የማስተካከል እና መልሶ የማዋቀር ሂደቶች ናቸው። እውቅና በመስጠት ሂደት ተማሪዎች አዲስ መረጃ ማግኘት (መያዝ) እንጂ በአእምሯዊ የእውቀት መዋቅር መረጃውን የመቀየር ፍላጎት የላቸውም። በመቀጠል የተገኘውን አዲስ መረጃ በአእምሯዊ የእውቀት መዋቅር የማስተካከል ሂደት ይከናወናል። መልሶ በማዋቀር ደረጃ አዲስ የእውቀት መዋቅር የግድ ይፈጠራል። ምክንያቱም የቀደመው (አሮጌው) የእውቀት መዋቅር ለረጅም ጊዜ በብቃት ለመቆየት እድሳት ወይም ለውጥ የሚፈልግ በመሆኑ ነው።

ማንበብን በማስተማር ሂደት ተማሪዎች የእውቀት መዋቅራቸውን እንዲያጎለብቱ የተለያዩ ብልሃቶችን አቀናጅቶ ማስተማር፣ ቃላትን፣ አያያገሮችን፣ ሀሳብ ማስተሳሰርን (ማያያዝን) ማስተማር እና ለተማሪዎች የቀደመ እውቀት ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል። በዚህ ሂደት የመምህራን ድርሻ ከፍተኛ ነው።

የአእምሮታዊ ግንባታዊነት አካል የሆነው መረጃን የማብላላት ሂደት ትውረት (Information Process Theory) በዚህ ጥናት ልዩ ትኩረት የተሰጠው ሌላው ትውረት ነው። መረጃን የማብላላት ሂደት ትውረት የሚያንፀባርቀው እንዴት የቀደመ እውቀት እንደሚጠራቀም፣ ከተፃፈ ፅሁፍ አዲስ እውቀት እንዴት እንደሚፈጠር እና ምን አይነት ሂደት እንደሚፈልግ ነው (Slavin 1997:185)።

መረጃን በማብላላት ሂደት ትውረት አተያይ መረጃ በአእምሮ ውስጥ በተለያየ ደረጃ (ቅደም ተከተል) የመጓዝ፣ የመጠራቀም፣ የመብላላት፣ የመንፀባረቅ፣ ትምህርት የመሆን (አዲስ ሀሳብ የመስጠት) የመቀመጥ እና መልሶ የመጠቀም ሂደት እና ስልት ያለው ነው። ትውረቱ የአጨር ጊዜ ትውስታ ወይም በመስራት ላይ ያለ ትውስታ ያለውን ውስን አቅም የሚያመለክት አንዲሁም ይህን ውስን አቅም ለመቅረፍ መረጃ በተከፋፈለ መንገድ እንዴት እንደሚብላላ የሚያመለክት አተያይን መሰረት ያደርጋል።

የሰው ልጅ አዕምሮ መረጃን የሚያብላላው ከኮምፒውተር ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ እንደሆነ፣ የተፃፈ ፅሁፍ እውቅና የሚያገኘው በአእምሮ ውስጥ ባለ የስሜት መመዝገቢያ (ማጣርያ) እንደሆነ፣ አንባቢ የተገነዘበው መረጃ በአአምሮ ውስጥ የሚቀመጠው በጊዜያዊነት በአጭር ጊዜ ትውስታ ወይም በመስራት ላይ ያለ ትውስታ እንደሆነ እና ይህ በሒደት ወደ ረጅም ጊዜ ትውስታ አንደሚሸጋገር ትውረቱ ያንፀባርቃል (Ali-Hossan 2005፣ Huitt 2003)።

በአእምሮታዊ ግንባታዊነት አተያይ ለብልሃት የሚሰጠው ብያኔ የተለየ ተግባር ላይ መሰረት ያደረገ እቅድ ወይም ዘዴ፣ የሚታይ ወይም የማይታይ፣ ለማንበብ ተግባር የቀረበ ፅሁፍን ለመረዳት፣ መረጃን ለማጠራቀም እና መልሶ ለመጠቀም እንዲሁም ማንበብን ለማቀድ፣ ለመቆጣጠር ግለሰቦች የሚጠቀሙበት መሳርያ ነው (Carrell 1998፣ O`Malley & Chamot 1990):: በማንበብ ሂደት ብልሃት በጣም ጠቃሚ የሚሆንበት ምክንያት የአጭር ጊዜ ትውስታ ውስንነትን ለመቅረፍ፣ መረጃን ከአጭር ጊዜ ትውስታ ወደ ረጅም ጊዜ ትውስታ ለማሸጋገር የሚያስችል በመሆኑ ነው።

መረጃን በማብላላት ሒደት ትውረታዊ አተያይ ብልሃትን በተግባር ለመጠቀም ሁለት አይነት ልእለአእምሯዊ እውቀት ያስፈልጋል። ይኸውም የመረዳት እውቀት (Knowladge of Cognition) እና መረዳትን የመቆጣጠር እውቀት (Knowledge of Regulation/ Regulation of Cognition) ናቸው። የመጀመሪያው አንባቢዎች የብልሃትን ምንነት በመለየት በማንበብ ወቅት ብልሃቶችን መቼ፣ የት እና እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተገቢ ወይም ውጤታማ ብልሃቶችን በመጠቀም ፅሁፍን ለማንበብ ማቀድ፣ ራስን እና መረዳትን መቆጣጠር እንዲሁም መገምገምን ያካተተ ነው። ተማሪዎች እነዚህን እውቀቶች ሲያጎለብቱ የማንበብ ብልሃቶችን በሚገባ እንዲጠቀሙባቸው ከማስቻሉም በላይ ብልሃቶችን ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ ወይም ከአንድ ሁኔታ ወደሌላ አዲስ ሁኔታ የማሸጋገር ብቃታቸው ይጎለብታል (Zhang 2008፣ Talibi 2015፣ Bimmel et al. 2001)።

በመማር ብልሃት ፅንሰ ሀሳብ መረጃን በማብላላት ማዕቀፍ ስር ታዋቂዎች ተብለው የሚጠቀሱት የማንበብ ብልሃቶች አእምሮታዊ እና ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃቶች ናቸው። እንደ O'Malley and Chamot (1990፡44) አገላለፅ አእምሮታዊ የማንበብ

ብልሃት የሚመጣን መረጃ ቀጥታ ተግባራዊ በማድረግ መማርን ለማጎልበት ያስችላል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ በመሆን የሚጠቀሱት መለማመድ፣ ቃላትን ማቧደን እና ቃላትን መከፋፈል፣ ሐሳብን በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ፣ መረጃን ፈልፍሎ ማውጣት፣ ልዩ ልዩ ነገሮችን መመርመር፣ ማሸጋገር እና ማስፋፋት ወዘተ ናቸው። ልእለዕምሯዊ የማንበብ ብልሃት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ ማሰብ ሲሆን መማርን የራስ ለማድረግ ማቀድ፣ ማደራጀት እና መገምገምን የሚያካትት ነው።

የማንበብ ብልሃት አንደኛው ባህሪ የሚያስተምሩት (ለማስተማር የተመቸ) መሆኑ ነው (Karami 2008፣ Carrell 2006)። እንደመረጃን የማብላላት ትውረት አእምሯዊ (ግንዛቤያዊ) እድገት የሚወሰነው አእምሮታዊ ብልሃቶችን መጠቀም በማጎልበት እና በማሳደግ ነው። ለተማሪዎች ብልሃቶችን ማስተማር ተማሪዎች የሚያውቋቸውን (ያልደረሱባቸውን) እና በራሳቸው የማይጠቀሙባቸውን ብልሃቶች እንዲያውቁ በማድረግ የማሰብ እና የመማር ብቃታቸው እንዲጎለብት ማድረግ ያስችላል። መምህራንም የቀረበውን ትምህርት ብቻ ሳይሆን የማንበብ ብልሃቶችን በማስተማር ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት በደንብ እንዲያውቁ ማድረግ ያስፈልጋል። ብልሃትን የማስተማሩ ወሳኝ ጉዳይ ተማሪዎች የተለያዩ ብልሃቶችን አቀናጅተው በመጠቀም ሒደታዊ እውቀት ሞዴልን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማስቻል ነው። አብዛኛዎቹ የምርምር ስራዎች እንዳመላከቱት ተማሪዎች ብልሃቶችን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ በግልፅ ማስተማር ተማሪዎች ተገቢ በሆነ መንገድ ብልሃቶችን እንዲጠቀሙ ማድረግ ያስችላል (Anderson 2005፣ Cohen 1999)።

ተማሪዎች ስለብልሃቶች ምንም ሳይማሩ በፊት የተወሰኑ ብልሃቶችን በግምት ቢጠቀሙም ሆን ብለው በተከታታይ ለመጠቀም የሚቸገሩበትን ሁኔታ በተመለከተ ሁለት ችግሮች እንዳሉባቸው ተስተውሏል። ይኸውም አንድ ጊዜ የተጠቀሙባቸውን ብልሃቶች ወጥ በሆነ መንገድ አቀናጅተው የመጠቀም ችግር እና ብልሃቶችን ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ ወይም ከአንድ ሁኔታ ወደሌላ አዲስ ሁኔታ (ወደአዲስ ተግባር) የማሸጋገር ችግሮች ናቸው። በአንብቦ መረዳት ትምህርት ተማሪዎች የትኛውን የተለየ ብልሃት መጠቀም እንዳለባቸው ማስተማር ብቻ ሳይሆን ለምን፣ መቼ እና የት መጠቀም እንዳለባቸው ማስተማር ያስፈልጋል። በተለያየ አውድ የተለዩ የማንበብ ብልሃቶችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ግን ራሳቸው ማጎልበት ይጠበቅባቸዋል።

2.9.1.2 ማህበራዊ ግንባታዊነት

የግንባታዊነት ትውረት አካል የሆነው **ማህበራዊ ግንባታዊነት** በዚህ ጥናት ሌላው ትኩረት የተሰጠው ትውረት ነው። Lev Semionovich Vygotsky የተባሉት ሩስያዊ ምሁር በዋናነት ከሚጠቀሱ የማህበራዊ መማር ትውረት አራማጆች መካከል ተቀዳሚው ናቸው። የ Vygotsky ትውረት ቀጥተኛ ስያሜ የአእምሮታዊ እድገት ማህበረታሪካዊ ትውረት (Socio-Historical Theory of Cognitive Development) ሲሆን በስፋት የሚታወቀው ማህበራዊ ግንባታዊነት (Social Constractivism) በሚል ስያሜ ነው (Tracey & Morrow 2006፡108)።

በማህበራዊ ግንባታዊነት አተያይ ተማሪዎች ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር በሚያደርጉት መስተጋብር ይማራሉ። Woolfolk (1998:44) Vygotsky (1986) ን ጠቅሰው እንደገለፁት ተማሪዎች ብቻቸውን ሆነው አለምን በትልቁ ለመረዳት ጥረት ሲያደርጉ እንደትንሽ ሳይንቲስት ናቸው። ነገር ግን የልጆች አእምሯዊ እድገት የተመሰረተው የበለጠውን ከሌሎች ጋር በሚያደርጉት መስተጋብር በመሆኑ ከአቻዎቻቸው እና ከእነርሱ የበለጠ ክህሎት እና እውቀት ካላቸው ጓደኞቻቸው ጋር ሲተባበሩ የበለጠ ይማራሉ። የተማሪዎች እውቀት፣ ሀሳብ፣ አመለካከት እና እሴት ከሌሎች ጋር በሚያደርጉት መስተጋብር ይጎለብታል። በዚህ ሂደት ባህል ማሰብን ለማጎልበት እንደመሳሪያ ያገለግላል።

እንደ Lencioni (2013፡9) ተማሪዎች የሚኖሩበት ህብረተሰብ፣ በክፍል ውስጥ ያሉት ተማሪዎች፣ የተማሪ ወላጆች፣ መምህር ከተማሪ እና ተማሪ ከተማሪ ጋር ያለ መስተጋብር በተማሪዎች ማንበብ እና መፃፍ ትምህርት ላይ ተፅእኖ እንዳላቸው ይገልፃሉ። በማህበረ ግንባታዊነት ትውረት አእምሮታዊ እድገት ከተፈጥሯዊ ክፍሎች ይልቅ የባህል ተፅእኖ የሚያርፍበት መሆኑ ይገለፃል። ምክንያቱም የማንበብ እና የመፃፍ ትምህርት ማህበረባህላዊ እና ቋንቋዊ ጉዳዮች ተፅእኖ ያርፍበታል እና ነው። ማህበረ ግንባታዊነት ትውረት የሚያንፀባርቀው ዋና ጉዳይ ሰዎች የበለጠ የሚማሩት ከግል ተሞክሯቸው ይልቅ ሌሎችን በመመልከት ነው።

በተመሳሳይ የማህበራዊ መማር ትውረት (Social Learning Theory) ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ስያሜው የማህበረ አእምሮታዊ ትውረት (Social Cognitive Theory)

በመባል የሚታወቀውን ትውረት ያጎለበቱት Bandura (1989:24) እንዳመላከቱት ሰዎች በራሳቸው ከሚያከናውኑት ይልቅ ሌሎችን በመመልከት የበለጠ ይማራሉ። የሰው ልጅ ሁሉንም እኔ ብቻ ላከናውን ከማለት ይልቅ ሌሎችን ተመልክቶ መማር የመቻል ተሰጦ አለው። ሰዎች የሌሎችን ውጤታማነት፣ ውድቀት፣ ጥረት፣ ስልት በመመልከት ይማራሉ። በማህበረ አእምሮታዊ ትውረት ሰዎች የሚማሩባቸው ሌሎች ሰዎች "ሞዴሎች" ናቸው።

እንደ Bandura (1989፡24) ገለፃ ሰዎች በምልከታ የሚማሩባቸው አራት ደረጃዎች አሉ። እነሱም ትኩረት፣ይዞ ማቆየት (ትውስታ)፣ ማባዛት(መድገም) እና ሃይል ማግኘት ወይም መነሳሳት ናቸው። ተገቢ መማር እንዲከሰት ተማሪዎች ቁልፍ መረጃዎችን እንደሞዴል በመውሰድ እና መምህራቸው ሞዴል በሚሆኑበት ጊዜ በመመልከት ትኩረት ማድረግ አለባቸው። በመቀጠል ተማሪዎች የቀረበውን መረጃ ማስታወስ ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ሞዴል አድርገው የወሰዱትን ወደትውስታቸው ማካተት ይገባቸዋል። ሌላው ንኡስ ክፍል ሞተራዊ ድግግም ነው። በዚህ ደረጃ ተማሪዎች የተመለከቱትን የሚደግሙበት ነው። የመጨረሻው ተማሪዎች በቀጥታ፣ በውክልና ወይም በራስ አፍልቆት ባገኙት ጥቅም ወይም ያዩትን በመድገም ለበለጠ ትምህርት መነሳሳት ነው።

ተማሪዎች በምልከታ በሚማሩበት ወቅት የሞዴሉን አጠቃላይ ባህሪ ትምህርታዊ ባልሆነ መልኩ አይቀዱም። ይልቁኑም በትኩረት በመከታተል ጠቃሚ እና ትምህርታዊ በሆነ መልኩ ሞዴሉ የሚያሳየውን እየተከታተሉ በማብላላት የቀረበውን የትምህርት ይዘት ለመረዳት ጥረት ያደርጋሉ። በምልከታ መማር ወቅት በራስ መተማመን (Self-efficacy) በጣም ወሳኝ ነው። በራስ መተማመን ተማሪዎች አንዳች የተለየ ግብ ለማሳካት ችሎታ እንዳላቸው ማመንን ይገልፃል (Tracey & Morrow 2006፡112)። ተማሪዎች በራስ መተማመናቸው በጨመረ መጠን ለሌላ አዲስ መማር፣ የበለጠ ለማጠናቀቅ፣ በቀጣይነት ሌሎች ተግባራትን ከሌሎች በተሻለ ለማከናወን ይነሳሳሉ።

በምልከታ እና በሞዴልነት ማንበብን በማስተማር ወቅት መምህር ከአነበቡት አንድ መፅሀፍ ውስጥ በጣም መሳጭ የሚሉትን ሀሳብ በመንገር በእለቱ ተማሪዎች እንዲደመሙ እና ለማንበብ ያላቸው ፍላጎት እንዲነሳሳ ማድረግ ይችላሉ። በተመሳሳይ ሁሉንም በመተው የማንበብ ጊዜ (Drop Everything And Read Time/D.E.A.R)

በቋሚነት በማዘጋጀት (በሳምንት አንድ ቀን አንድ ክፍለ ጊዜ ሊሆን ይችላል) በትምህርት ቤት ወይም በክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በሙሉ እንዲያነቡ ማድረግ አንብቦ የመረዳት ብቃትን እንዲያጎለብቱ ያደርጋሉ (ማድረግ ይችላሉ) (Tracey & Morrow 2006)።

በማህበራዊ ግንባታዊነት ተፅእኖ ፈጣሪ የሚባለው ፅንሰሀሳብ **የእድገት አማካይ ክፍል** (Zone of Proximal Development) ነው። ፅንሰሀሳቡ የሚያንፀባርቀው በመማር ሂደት የተግባር ክብደት ደረጃን ለማስተካከል የሚፈለገው ቀና የሆነ የመማር መደጋገፍን ነው። Mooney (2000:83) Vygotsky (1978)ን ጠቅሰው የእድገት አማካይ ክፍልን ሲበይኑ "የተማሪዎች አሁን ባለ ትክክለኛ እድገት እና በእድገት አቅም ደረጃ መካከል ያለ ልዩነት ነው"። በቀላል አገላለፅ የእድገት አማካይ ክፍል ተማሪዎች ብቻቸውን በሚሰሩት በጣም ከባድ በሆነ ተግባር እና ከእርዳታ ጋር በሚሰሩት በጣም ከባድ ተግባር መካከል ያለ ልዩነት ነው። (ተማሪዎች ያለእርዳታ መስራት መቻል እና ተማሪዎች በእርዳታ በመስራት መቻል መካከል ያለ ልዩነት)።

የእድገት አማካይ ክፍልን ለመረዳት የስነልቦና ባለሙያዎች በመማር ሂደት የማስመሰልን ሚና እንደገና ማየት ያስፈልጋል ይላሉ (Steinagel 2005፣ Lencion 2013)። በአእምሮ እድገት ተማሪዎች ብቻቸውን ሆነው በሚሰሩት ክንውን ሂደት ክንውኖቹን የማስመሰል እድል አያገኙም። የስነልቦና ባለሙያዎች እንዳረጋገጡት ተማሪዎች የማስመሰል አቅማቸው የሚጎለብተው በነሱ የእድገት ደረጃ ከሌሎች ጋር ባላቸው መስተጋብር ነው። ተማሪዎች ከአቻዎቻቸው እና ከመምህራቸው ጋር ባለ መስተጋብር ሲመሰጡ በተለይ በመስተጋብሩ መምህራቸው እና ከአቻዎቻቸው መካከል ላቅ ያለ ችሎታ ያለው ጓደኛቸው ሲረዳቸው አዳዲስ ፅንሰሀሳብ የማፍለቅ እና የማስመሰል ብቃታቸው ይጨምራል። በመስተጋብሩ ሂደት ያለው ጠቃሚ እርዳታም ትግግዝን ይፈጥራል።

የማህበራዊ ግንባታዊነት ትውረት አካል የሆነው **ትግግዝ** (Scaffolding) ይህ ጥናት የሚያራምደው ትውረት ነው። ትግግዝ የማህበራዊ ግንባታዊነት ቁልፍ ፅንሰሀሳብ ነው። ትግግዝ የሚገለፀው በእያንዳንዱ የትምህርት ምእራፍ ተማሪዎች ያላቸውን አዎንታዊ የርስበርስ መረዳዳት ነው። እንደ Tracey and Morrow (2006:109) እና Slavin (1997:48) አገላለፅ ትግግዝ የ Vygotsky (1978) ተከታዮች ዘይቤያዊ ትርጉም ሲሆን

ትርጓሜውም መምህራን ተማሪዎችን፣ተማሪዎች አቻዎቻቸውን በውይይት፣ በመጠየቅ፣ በርስበርስ ንግግር እና ቃል አልባ ሞዴል በመጠቀም መርዳት እና የቀረበን ፅሁፍ አንብበው እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው፡፡ መተጋገዝ ፍንጭ የመስጠት፣ የማስታወስ፣ የማበረታታት፣ ችግሮችን በቅደም ተከተል የመከፋፈል እና መፍትሄ የማፈላለግ፣ ምሳሌዎችን የማቅረብ እና ሌሎች ትምህርቱን ምቹ የሚያደርጉ ተግባራትን በጋራ በማከናወን ተማሪዎች ራሳቸውን እንዲችሉ ያደርጋል፡፡

መምህራን ተማሪዎቻቸውን በማስተዋል በጥንድ እና በቡድን ሆነው ርስበርስ እንዲማማሩ እድል ሲፈጥሩ የትግግዝ መንፈስ ይዳብራል፡፡ በተለይ መምህራን ቡድን ሲመሰርቱ የፆታ፣ የእድሜ፣ የችሎታ ወዘተ ስብጥር በመፍጠር በየክንውኖቹ ውስጥ ተማሪዎች ርስበርስ እንዲማማሩ እና የትግግዝ ችሎታቸው እንዲጎለብት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህም መምህሩ ማብራራት፣ ተማሪዎችን ለተሳትፎ ማበረታታት፣ የተማሪዎችን መረዳት ግልፅ ማድረግ እና ማረጋገጥ፣ መሆን የሚገባን ባህሪ ለማሳየት ሞዴል መሆን እና በማንበብ ሂደት ችግር ወይም አዲስ ጉዳይ ሲገጥም ምክንያታዊ እንዲሆኑ ተማሪዎችን ማነቃቃት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ማህበራዊ ግንባታዊነት አእምሯዊ እድገት እንዲፈጠር የሚያስችል መመሪያ ያንፀባርቃል፡፡ ይኸውም ልጆች በማህበራዊ ሁኔታ ውስጥ ከፍተኛ አእምሯዊ አሰራርን ተግባራዊ ከማድረጋቸው አስቀድሞ ልምድ ወይም ልምምድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በተመሳሳይ ተማሪዎች በማህበራዊ ሁኔታ ውስጥ ባህላዊ ተግባቦታዊ ስልቶችን በግላቸው ከመጠቀማቸው አስቀድመው መማር አለባቸው፡፡ Tracey and Morrow (2006:109) Vygotsky (1978) ጠቅሰው እንደገለፁት መምህራን መርሀትምህርት በመንደፍ ተማሪዎችን ለመርዳት ሲያቅዱ ተማሪዎች ወደሚቀጥለው የእድገት ደረጃ እንዲደርሱ በማድረግ ብቃታቸውን ለማጎልበት ያስችላቸዋል ፡፡

በአእምሯዊ ግንባታዊነት በተማሪ ተኮር ክባቢ እውቀትን ለመመስረት የሚቻለው ግለሰብ (እያንዳንዱ)ተማሪ ፍላጎቱን እና ምኞቱን ለመደገፍ በሚያደርገው ጥረት ነው፡፡ በአእምሯዊ ግንባታዊነት መማር በዋናነት የግለሰባዊነት ሙከራ ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ ማህበራዊ ግንባታዊነት በትምህርት ሂደት የበለጠ ችሎታ ያላቸው ወጣቶች ወይም አቻዎች ያነሰ ክህሎት ያላቸው ተማሪዎችን በመርዳት ውጤታማነትን ማረጋገጥ ነው፡፡ አእምሮታዊ ግንባታዊነት እና ማህበራዊ ግንባታዊነት ትውረቶች ከ “ኢፒስቲሞሎጂያዊ”

እና “አንቶሎጂያዊ” አተያይ ልዩነት አላቸው ቢባልም እነዚህ ሁለት ትውረቶች የሚጣጣሙ እና በቀላል ማዕቀፍ ሊጣመሩ እንደሚችሉ አስረድተዋል። ይህም ማዕቀፍ ግንባታዊነት ነው (Rowell & Palmer 2007፣ Oxford and Ehrman 1995)።

2.10 የጥናቱ ሞዴል

ከላይ በ 2.4 እንደተገለፀው ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በግንባታዊነት ትውረታዊ ማእቀፍ ላይ የተመሰረተ ነው። ጥናቱ የማንበብ ብልሃቶችን ለማስተማር አቀናጅቶ ተግባራዊ ያደረገው ሞዴልም ይህንኑ ትውረታዊ ማእቀፎች እንዲያንፀባርቅ በሚያስችል መንገድ የተቀረፀ ነው። በመሆኑም በጥናቱ ተቀናጅተው አገልግሎት ላይ የዋሉት ሞዴሎች መምህር በነፃ ማሰብ (እየተገበሩ ማሰብ) (Teacher Think Aloud)፣ አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ (Cognitive Academic Language Learning Approach /CALLA) እና ትግግዝ (Scaffolding) ሞዴሎች ናቸው።

ጥናቱ እነዚህን ሞዴሎች አቀናጅቶ የተጠቀመበት ምክንያት ሞዴሎቹ ርስበርስ የተሳሰሩ በመሆናቸው፣ በሞዴሎቹ ውስጥ የትምህርት አቀራረብ ክፍተት ቢኖር ክፍተቱን ለመሙላት እንዲያስችል እና እንደተገለፀው ከትውረታዊ ማእቀፉ ጋር ለማስተሳሰር (መምህር በነፃ ማሰብ (እየተገበሩ ማሰብ) እና አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ አእምሮታዊ ግንባታዊነት ትውረት ላይ የሚመሰረቱ ሲሆን ትግግዝ ሞዴል ደግሞ ማህበራዊ ግንባታዊነት ትውረት ላይ የተመሰረተ ነው) በማሰብ ነው።

2.10.1 መምህር በነፃ ማሰብ (እየተገበሩ ማሰብ) ሞዴል

መምህር በነፃ ማሰብ (እየተገበሩ ማሰብ) ሞዴል አእምሮታዊ ግንባታዊነት ትውረት ላይ የተመሰረተ ነው። ይህ ሞዴል ተማሪዎች ውህድአሀዶችን በሚያነቡበት ወቅት የማንበብ ብልሃቶችን እንዴት እንደተጠቀሙ፣ በማንበብ ወቅት ያጋጠማቸውን ችግር ለመፍታት ምን አይነት መፍትሄ እንደወሰዱ፣ በአእምሯቸው ያለውን ሀሳብ በነፃነት አውጥተው እንዴት መግለፅ እንደሚችሉ፣ የቀረበውን ፅሁፍ ሀሳብ በተረዱት ልክ የማንፀባረቅ ክህሎታቸው እንዴት ከፍ እንደሚል ለማስተማር የሚያመች ነው (Ballou 2012፣ Griffiths 2004)።

ይህን ሞዴል ተጠቅሞ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ ለተማሪዎች በሚቀርብበት ወቅት ትምህርቱን የሚሰጠው መምህር ሞዴል በመሆን ለማስተማርያነት ከተመረጡት ምንባቦች የተወሰኑትን በተማሪዎች ፊት በማንበብ እና የማንበብ ብልሃቶችን በመጠቀም ተማሪዎች እንዴት አንብበው መረዳት እንዳለባቸው ያለማምዳል። ለምሳሌ መረዳትን ለመቆጣጠር መምህር ሞዴል በመሆን ድምፁን ከፍ አድርጎ ካነበበላቸው በኋላ "ይህን አንቀፅ ተረድቸዋለሁ፤ ስለዚህ መቀጠል እችላለሁ" ወይም "አንቀፁ ስላልገባኝ እንደገና አነበዋለሁ" እያለ ይነግራቸዋል። በዚህ መሰረት ተማሪዎችም በሚያነቡበት ወቅት "ስለርዕሱ የማውቀው ነገር አለ?" "የምንባቡ ዋና ሀሳብ ምንድን ነው?" "ያነበብኩትን ሀሳብ በራሴ መንገድ አሳጥሬ መፃፍ እችላለሁ?" እያሉ በመጠየቅ ወደተግባር እንዲሸጋገሩ የሚለማመዱበት ሞዴል ነው። በዚህ መንገድ ትምህርቱ ሲቀርብ ተማሪዎች የተረዱትን እንዲያንፅባርቁ (ፅብረቃ) እድል በመስጠት በነፃነት ትምህርቱን እንዲከታተሉ ማድረግ ያስፈልጋል።

2.10.2 አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ ሞዴል

አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ ሞዴል (Cognitive Academic Language Learning Approach/ CALLA Model) አእምሮታዊ መማር ብልሃት ትውረት ላይ ተመስርቶ የጎለበተ ሞዴል ነው (O`Malley & Chamot 1990፡190)። በዚህ ሞዴል መምህሩ የመማር ማስተማሩን ሂደት የመምራት እና ተማሪዎችን የመርዳት ሚናው ከፍተኛ ነው። በመማር ማስተማሩ ሂደት የመምህሩ እርዳታ እና መተጋገዝ ቀስ በቀስ እየቀነሰ በዛ ያሉ ሙከራዎችን ተማሪዎቹ ራሳቸው በመተግበር የማንበብ ብልሃቶችን በመለማመድ ነፃ ሆነው በራሳቸው መንገድ እንዲተገብሩ ለማድረግ ያስችላል። (ሞዴሉ የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ማእከላዊ ምሰሶ ነው)።

በዚህ ሞዴል ትምህርቱ ሲቀርብ የማንበብ ብልሃቶች ምንነት እና ጠቀሜታው በዝርዝር ይቀርባል። ተማሪዎችም የማንበብ ብልሃቶችን በሚገባ መጠቀማቸውን ለመገንዘብ ራሳቸውን ይገመግማሉ። ሌሎች ፅሁፎችን ሲያነቡም የማንበብ ብልሃቶችን በማሸጋገር እንዲጠቀሙ መምህሩ የማበረታታት ስራ ይሰራል። ተማሪዎች የቀረበላቸውን ፅሁፍ በሚያነቡበት ወቅት ትኩረት የተሰጠባቸውን ብልሃቶች በራሳቸው መንገድ በተደጋጋሚ በመለማመድ እና በመጠቀም በነፃነት የማንበብ ብቃታቸውን በማጎልበት ራስመር

ተማሪዎች እንዲሆኑ ይለማመዳሉ። ይህም የማንበብ ብልሃት ተኮር ትምህርት የመጨረሻ ግብ ነው (O`Malley & Chamot 1990)።

ሞዴሉ በውስጡ ያካተታቸው ጉዳዮች የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የመማር ልምድ ማግኘት፣ ይዘትን ማስተማር፣ ቋንቋን ማጎልበት እና ብልሃትን ማስተማር ናቸው። የሞዴሉ ዋነኛ አላማም ተማሪዎች በመማር ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ፣ ይዘታዊ መማርን ማበረታታት፣ እውናዊ በሆነ ይዘት ብልሃቶችን ማስተማር፣ ደረጃውን የጠበቀ ስርአተትምህርት መፍጠር፣ ትምህርትቤታዊ እና ባህላዊ ርዕሶች ላይ ፍላጎት መጨመር፣ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት እና ባህላዊ እውቀት ማስተሳሰር እንዲሁም በትብብራዊ መማር ተማሪዎች ተግባራትን እንዲያከናውኑ ማድረግ ነው (O`Malley & Chamot 1990)። ሞዴሉ ይህን ለመተግበር የሚከተለው መርህ "ታፕል" (TAPPLE) "Teach first, Ask a question, Pause and pair-share, Pick a nonvolunteer, Listen to the response, and Effective feedback" ይባላል። መርሁ መጀመሪያ ማስተማር፣ ጥያቄ መጠየቅ፣ ተማሪዎችን ማቀናጀት (በቡድን ማደራጀት)፣ ለመሳተፍ ፍቃደኛ ያልሆኑ ተማሪዎችን መለየት፣ እንዲሳተፉ እድል በመስጠት ምላሻቸውን ማዳመጥ እና ምጋቤ ምላሽ መስጠት ናቸው (Lencioni 2013፣ DataWorks Educational Research 2011)።

አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ ሞዴል ስድስት ቅደም ተከተሎች አሉት። እነሱም ዝግጅት፣ አቅርቦት፣ ልምምድ፣ ግምገማ፣ ማስፋፋት እና ምዘና ናቸው። O'Mallye and Chamot (1994:66) አእምሮታዊ ትውረትን መሰረት በማድረግ አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ ሞዴል በማለት ያቀረቡት ምስለሀሳብ የሚከተለውን ይመስላል።

ከታች የቀረበው ምስለሀሳብ የማንበብ ብልሃትን ለማስተማር የሚያስፈልጉ ቅደም ተከተሎችን፣ በዚህ ሂደት የመምህሩ እና የተማሪዎች ተግባር (ሚና) ምን እንደሆነ ያንፀባርቃል። የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ ሲጀመር የብልሃትን ምንነት፣ ጠቀሜታ እና አይነቶች በማስረዳት እና መምህሩ ሞዴል በመሆን ምሳሌዎች እያቀረበ የሚያሰተምር በመሆኑ ትምህርቱ ሲጀመር የተማሪዎቹ ሚና አነስተኛ የመምህሩ ሚና ግን ሰፊ መሆኑን ያሳያል። በመማር ማስተማር ሂደቱ የመምህሩ ሚና ግን ቀስበቀስ እየቀነሰ እና የተማሪዎቹ ሚና ሰፊ እየሆነ በመምጣት ተማሪዎች ብዙውን ሀላፊነት ራሳቸው

እንዲወጡ የሚያበረታታ መሆኑን ተገላብጠው የተቀመጡት ሶስት መአዘን ምስሎች ያሳያሉ፡፡ ሶስት መአዘን ምስሉ ርስበርስ መያያዙ በመማር ማስተማር ሂደቱ የመምህሩ እና የተማሪዎች ሚና መደጋገፍ እና ትግግዝ ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡ በምስሉ ላይ ምዘና በግልፅ ባይታይም ከየክንውኖቹ በኋላ መተግበር ያለበት እንደሆነ O'Mallye and Chamot (1994) አስረድተዋል፡፡ የአእምሯዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ ቅደም ተከተል የዚህ ጥናት ትምህርት አቀራረብ አምድ ነው፡፡

ምስል አምስት፡- አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ ሞዴል



O'Mallye and Chamot (1994b:66)

ከዚህ በታች የቀረበው ሰንጠረዥ ሞዴሉ የሚከተለው ቅደም ተከተላዊ የማንበብ ብልሃት ትምህርት አቀራረብን በዝርዝር ያሳያል፡፡

ሰንጠረዥ ሁለት፡- በአእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ ሞዴል የማንበብ ብልሃት ትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተልን የሚያሳይ

ተ.ቁ	ቅደምተከተል	ተግባራት
1	ዝግጅት	ተማሪዎች አሁን ያላቸው የተለያየ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤን መለየት ልየታው - በአነስተኛ ቡድን ሆኖ ያለፈን ነገር የማስታወስ መጠይቅ - በነፃ ማሰብ ሞዴል ተማሪዎች በአነስተኛ ቡድን በነፃ ማሰብ እና ያሰቡትን እንዲያንፀባርቁ ማድረግ - በነፃ ማሰብ ፣ ቃለ መጠይቅ እና ውይይት
2	አቅርቦት	የተማሪዎችን የማንበብ ብልሃት እውቀት ማጎልበት ትግበራው - የማንበብ ብልሃትን ለመጠቀም ምክንያታዊ እንዲሆኑ ማስረዳት - ብልሃቶችን በየስማቸው መጥራትና ማስረዳት - ብልሃቶችን ለማስተማር ሞዴል መሆን
3	ልምምድ	ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን የመጠቀም ክህሎታቸውን ማጎልበት ትግበራው - ትብብራዊ የመማር ተግባራትን ተግባራዊ ማድረግ - ችግሮችን ለመፍታት በነፃ ማሰብ - የአቻ መማርን መተግበር - የቡድን ውይይት - ራሳቸውን ችለው ብልሃቶችን እንዲጠቀሙ ማበረታታት
4	ግምገማ	ከልምምድ በኋላ ተማሪዎች የራሳቸውን የማንበብ ብልሃት የሚገመግሙበትን ልምድ እንዲያዳብሩ ማድረግ ትግበራው - ከተሰጠው ተግባር በኋላ የተጠቀሙበትን ብልሃቶች እንዲዕፁ ማድረግ - በተጠቀሙባቸው ብልሃቶች ዙርያ መወያየት - በብልሃት አጠቃቀም ዙርያ ከመምህር ጋር የተደረገውን ውይይት በማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ
5	ማስፋፋት	ተማሪዎች ብልሃቶችን ወደአዲስ ተግባር ማሸጋገርን እንዲያጎለብቱ ማድረግ ትግበራው - በልዕለአእምሯዊ እና ተነሳስኟዊ ብልሃቶች ላይ ውይይት ማድረግ - የቀደመ እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ ማድረግ - በተማሪዎች ባህላዊ ዳራ ላይ መሰረት በማድረግ የማንበብ ብልሃት ትግበራ ያለበት ተደጋጋሚ የክፍል እና የቤት ስራ መስጠት - በታላሚው ቋንቋ ማንበብ ሂደት ለመረዳት ሲቸገሩ በራሳቸው ቋንቋ የተማሩትን (በተቃራኒው) በማስታወስ ብልሃቶችን ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ እያሸጋገሩ እንዲጠቀሙ ማበረታታት - ብልሃቶችን አቀናጅተው እንዲጠቀሙ ማድረግ
6	ምዘና	የተማሪዎችን የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና አጠቃቀማቸው በአንብቦ መረዳታቸው ላይ የፈጠረውን ውጤት መገምገም

O'Mallye and Chamot (1990፡158)

2.10.3 ትግግዝ ሞዴል (Scaffolding)

ትግግዝ ሞዴል ማህበራዊ ግንባታዊነት ትውረትን መሰረት አድርጎ የተገነባ ነው። በዚህ ሞዴል ተማሪዎች የመማርም ሆነ የማንበብ ልምዳቸው እንዲጎለብት እና ራሳቸውን የቻሉ ውጤታማ አንባቢ እንዲሆኑ የመምህር እንዲሁም የተማሪ ከተማሪ ድጋፍ ወሳኝነት አለው። በሞዴሉ የታሰበው ትምህርት በሚቀርብበት ወቅት የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን የሚሰጠው መምህር ተማሪዎችን መርዳቱን ወይም መደገፉን የሚያመላክተው ከተማሪዎች ጋር በመነጋገር፣ በመጠየቅ፣ ድምፅ አልባ በሆነ እንቅስቃሴ በማበረታታት እና ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ተማሪዎች የተሰጣቸውን ተግባራት በብቃት እንዲተገብሩ ማድረግ ሲቻል ነው። በዚህ ሂደት ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው ጠንካራ አንባቢ እንዲሆኑ የመምህር ድጋፍ ቀስ በቀስ እየቀነሰ በሂደቱ ሙሉ በሙሉ ሀላፊነትን ለተማሪዎች መስጠት ደረጃ የሚያደርስ ነው። ሞዴሉ ተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል እና የመምህር ተማሪን አቀራረብ የሚያመጣጥን ነው ።

በዚህ ሂደት ሁለት ማእከላዊ ጉዳዮች ትኩረት ያገኛሉ። ይኸውም የእቀዳ ምእራፍ እና የትግበራ ምእራፎች ናቸው። በእቀዳ ምዕራፍ ትምህርቱን የሚሰጠው መምህር ትኩረት የሚያደርገው የተማሪዎችን ፍላጎት፣ ትኩረት፣ መሻት፣ ጥንካሬ፣ ድክመት፣ የቀደመ እውቀት ወዘተ ላይ ነው። የመማሪያ ማስተማሪያ መፅሀፍን በተመለከተ የምንባቦችን ርዕሶች እና ጭብጣቸው፣ተነባቢነታቸው ወዘተ፣የማንበብ አላማን በተመለከተ ተማሪዎች የቀረበውን ውህድአሃድ ለምን አላማ ነው የሚያነቡት የሚሉትን ግምት ያስገባል። በትግበራ ምእራፍ የማንበብ ብልሃቶችን በቅድመ ማንበብ፣ በማንበብ እና በድህረማንበብ ጊዜ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ግምት ውስጥ ማስገባት እና ተግባራዊ ማድረግ ላይ ያተኩራል ።

እንደ Talibi (2014) አገላለፅ ሶስት አይነት ትግግዝ አለ። ይኸውም የመምህር እና የአቻ ትግግዝ፣ የውህድአሀድ ትግግዝ እና የተግባር ትግግዝ ናቸው። የመጀመሪያው የመምህር እና የአቻ ትግግዝን ተግባራዊ ለማድረግ እበራ (መተባበር) የማንበብ ብልሃት ትግበራ (Collaboration)፣ ትክ ማስተማር (Reseprocal Teaching) (በተለይ በመጀመሪያ ቋንቋ የማንበብ ብልሃትን ለማስተማር ጠቃሚ ነው) እና ትብብራዊ ማስተማር (Cooperative Learning) ተግባራዊ ይሆናሉ። በዚህም የተመረጡት

የማንበብ ብልሃቶች ተማሪዎችን በአነስተኛ ቡድኖች በመከፋፈል እና በግል በተደጋጋሚ ልምምድ እንዲያደርጉ እድል ለመስጠት ያስችላል። አላማውም ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው እንዲጎለብት እና ፅንሰሀሳባዊ የመማር ብቃታቸው እንዲጨምር ማድረግ ነው።

ሁለተኛው ውህደአሀድ ትግግዝ ነው። ይህም የውህድአሀድ ምክንያታዊ የመነበብ ክብደት፣ የማንበብ ብልሃትን የመጠቀም ትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት፣ አነስተኛ ክትትል፣ የተማሪዎች ግራ መጋባት፣ የሚነበበው ፅሁፍ ጭብጥ እና ድጋፍ ሰጪ ዝርዝር ጉዳዮች እና ለግመታ የሚያመቹ የተለያዩ ፍንጭ ሰጪ አንቀፆች እና ስዕሎች እንዳሉት ግምት ማስገባት ነው።

ሶስተኛው የትግግዝ አይነት የተግባር ትግግዝ ነው። ይህም ተማሪዎች የተሰጣቸውን የማንበብ ተግባር በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያግዛቸው የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን ሽግግር ያደርጋሉ። የተግባር መመሳሰል ሽግግርን ይፈጥራል። ከአንድ ተግባር ወደሌላ ተግባር ሽግግር የመከሰት ሁኔታ እንዲጨምር የሚሰጠው አዲስ ተግባር ቀደም ሲል ከተሰጠው ተግባር ጋር መመሳሰል ሲኖር ነው። በዚህም ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው እየተገነዘቡ ይመጣሉ። ተማሪዎችም የቀረበው ውህድአሀድ እና የተሰጠው የማንበብ ተግባር በሚጠይቀው መሰረት የማንበብ ብልሃቶችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ መምህሩ ያበረታታል።

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከላይ የተጠቀሱተን ሞዴሎች በማቀናጀት ከዚህ በታች የቀረበውን ሞዴል ተግባራዊ አድርጓል።

ምስል ስድስት፡- መምህር በነፃ ማሰብ (እየተናገሩ ማሰብ)፣ አእምሯዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ እና ትግግዝ ሞዴሎችን በማቀናጀት የቀረበ፡፡



ምንጭ፡- የጥናቱ አቅራቢ

ከላይ የቀረበው ምስለሀሳብ ጥናታዊ ፅሁፉ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ለማስተማር ተግባራዊ ያደረገውን ሞዴል ያሳያል። ምስሉ እንደሚያመላክተው የማንበብ ብልሃትን በግፅ ማስተማር ዋናው ጉዳይ ነው። በጥናቱ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ለማስተማር መምህር በነፃ ማሰብ (እየተገበሩ ማሰብ)፣ አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ እና ትግግዝ ሞዴል ተቀናጅተው አገልግሎት ላይ እንደዋሉ ምስለሀሳቡ ያሳያል። በምስሉ ላይ እንደተመላከተው ሞዴሎቹ ርስበርስ የተያያዙ እና የተደጋገፉ መሆናቸውን ቀስት ያላቸው መስመሮች ያመላክታሉ። መምህር በነፃ ማሰብ ሞዴል በዋናነት መምህሩ ራሱን ሞዴል በማድረግ ተማሪዎች በአእምሯቸው ውስጥ ያለውን ሀሳብ አውጥተው እንዲናገሩ ለማስተማር የሚያመች ነው። የማንበብ ብልሃቶችን በማስተማር ወቅት መምህሩ ሞዴል በመሆን የተለያዩ ፅሁፎችን እያነበበ ተማሪዎች ብልሃቶችን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው በዝርዝር ያስረዳል። ተማሪዎችም በትምህርቱ ሂደት በተገነዘቡት ልክ ብልሃቶችን ተግባራዊ እያደረጉ ውህድአሀዶችን እንዴት እንደተረዱ የሚያንፀባርቁ መሆኑን ያሳያል። አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ ጥናታዊ ፅሁፉ የማንበብ ብልሃቶችን የመማር ማስተማር ሂደቱን ሚዛን ለመጠበቅ የተጠቀመበት ዋነኛ ሞዴል (ምሰሶ) ነው። በምስሉ ላይ እንደተንፀባረቀው ሞዴሉ ስድስት የትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተሎች አሉት። እነሱም ዝግጅት፣ አቅርቦት፣ ልምምድ፣ ግምገማ፣ ማስፋፋት እና ምዘና ናቸው። ከነዚህ ቅደም ተከተሎች ጋር ተያይዘው ያሉት ቀስቶች የሚያመላክቱት እያንዳንዱ ቅደም ተከተል ርስበርስ እና ከሌሎች ክንውኖች ጋር ጥብቅ ትስስር ያላቸው መሆኑን ነው።

በምስለሀሳቡ የተንፀባረቀው ሶስተኛው ሞዴል ትግግዝ ሞዴል ነው። የማንበብ ብልሃቶችን በማስተማር ሂደት መምህር ለተማሪዎች ሞዴል በመሆን ብልሃቶችን በተሳካ መንገድ እንዲጠቀሙ ያግዛል። ከፍተኛ ብቃት ያላቸውም ተማሪዎች ዝቅተኛ ብቃት ካላቸው ተማሪዎች ጋር በመተጋገዝ ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲተገበሩ የማድረግ አላማ አለው። በዚህ ሂደት የመምህሩ እገዛ ቀስበቀስ እየቀነሰ ተማሪዎች ሃላፊነትን ይወስዳሉ። በዚህ ወቅት የመምህሩ ድርሻ ብልሃቶችን በዝርዝር ማስረዳት ፣ሞዴል መሆን፣ ትብብራዊ መንፈስ መፍጠር፣ ክፍለትምህርቱን ምቹ ማድረግ ወዘተ ነው። ተማሪዎችም በግል እና በቡድን ሆነው በንቃት በመሳተፍ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸውን ለማጎልበት ጥረት ያደርጋሉ። በምስለሀሳቡ የመምህሩ እና

የተማሪው ሚና የመማር ማስተማር ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ መከናወን እንዳለበት ለማሳየት የአእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ ምስለሀሳብ ከታች ይታያል፡፡

በጥናቱ ተቀናጅተው የቀረቡት ሞዴሎች ሞዴል መሆንን፣ መለማመድን፣ ብልሃቶችን በተግባር መጠቀምን፣ ፅብረቃን እና መተጋገዝን ይጋራሉ፡፡ ትምህርቱ በዚህ መልክ ተቀናጅቶ ሲቀርብ የመማር ማስተማር ኡደቱን ሚዛናዊ ለማድረግ ያስችላል፡፡ በዚህም ተማሪዎች ራስመር፣ ነፃ፣ ለትምህርት መነሳሳት ያላቸው እና በራስ መተማመናቸው የዳበረ ይሆናል፡፡ ተማሪዎች እንዲህ አይነት ብቃት ሲያጎለብቱ የተለያዩ ውህድአሀዶችን በቀላሉ መረዳት እንደሚችሉ ምስለሀሳቡ ያሳያል፡፡ በጥናቱ የማንበብ ብልሃትን ለማስተማር ያስችላል በሚል ሀሳብ ከላይ የቀረበው የትምህርት አሰጣጥ ቅደም ተከተል መነሻ እና መድረሻ በሚከተለው መንገድ ቀርቧል፡፡

ምስል ሶስት፡- ለትምህርት የተመረጡ የማንበብ ብልሃቶችን በማስተማር መነሻ እና መድረሻውን (ለውጡን) የሚያመላክት

ምንጭ፡- የጥናቱ አቅራቢ

በምስሉ ውስጥ የቀረበው ቅደም ተከተል እንደሚቀርበው የትምህርት አይነት እየተሸነሸነ በእለታዊ የትምህርት እቅድ ውስጥ ተካቶ ተግባራዊ ይሆናል (ሁሉም ጉዳይ በአንድ ክፍለ ጊዜ የማከናወን ግዴታን አያሳይም)፡፡ ሌላው ቅደም ተከተላዊ ትግበራው ትምህርቱን በሚሰጠው መምህር እና ተማሪዎች ምክክር እንደአስፈላጊነቱ ሊሻሻል ወይም እንዳለ ሊተገበር ይችላል፡፡

ምዕራፍ ሶስት

የጥናቱ ስነዘዴ

ማንበብን በተመለከተ በተለያየ ጊዜ ብዙ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ቀደም ሲል ይሰሩ የነበሩ ጥናቶች አንብቦ የመረዳት ውጤት ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው፡፡ የማንበብ ውጤት ላይ መሰረት ያደረጉ ጥናቶች ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የሚቀርቡ ውህድአሀዶችን አንብቦ ለመረዳት የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶች ወይም ተማሪዎች በማንበብ ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች እንዴት እንደሚፈቱ በአጠቃላይ የተማሪዎችን የማንበብ ሂደት እና በሂደቱ ያላቸውን ንቁ ተሳትፎ የሚያቀርቡ ባለመሆናው ነቀፌታ ገጥሟቸዋል፡፡ ተማሪዎች ውህድአሀዶችን አንብበው ለመረዳት የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶች እንዲሁም በማንበብ ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች እንዴት እንደሚፈቱ በአጠቃላይ የተማሪዎችን የማንበብ ሂደት ከውጤት ጋር አስተሳስሮ መፈተሽ ተገቢ ነው፡፡

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍም የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ውጤትን ለማጎልበት እና ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ያለው አስተዋፆ ምን እንደሚመስል በጥልቀት መመርመር ዋነኛ ጉዳዩ ነው፡፡ ጥናቱ የተነሳበትን አላማ ለማሳካት እንዲያስችለው በዚህ ምእራፍ የጥናቱን ንድፍ እና የአጠናን ዘዴ አካቶ ይዟል፡፡ የጥናቱ ዘዴ በስሩ ያካተታቸው ዋና ዋና ጉዳዮች የመረጃ ምንጭ፣ የናሙና አወሳሰድ፣ የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች፣ የመረጃ አሰባሰብ ቅደም ተከተል እና የመረጃ አተናተን ናቸው፡፡ ዋናው ጥናት ከመካሄዱ በፊት በዚሁ ምዕራፍ በተንፀባረቀው ስነዘዴ መሰረት የናሙና ጥናት (Pilot Study) ተከናውኗል፡፡ ዝርዝር ሀሳቡ በምዕራፍ አራት ውስጥ ተካቶ ቀርቧል፡፡

3.1 የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ቅድመ እና ድህረልምምድ ፈተና በመስጠት በተገኘው አሃዛዊ መረጃ ላይ ተመስርቶ ሰፊ ትንታኔ የሚያቀርብ ከፊል ፍትነታዊ የምርምር ንድፍ (Pre-test Post-test With Comparison Control Group Quasi- Expermental Design) የተከተለ ነው፡፡ ጥናቱ ይህንን ንድፍ የተከተለበት ምክንያት ሶማልኛ ቋንቋ አፍፊት

የሆኑ የ 9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ በመማራቸው አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው መጎልበት አለመጎልበቱን፤ እንዲሁም የተሰጠው ትምህርት የማንበብ ብልሃት ሽግግር እንዲጎለብት አስተዋፆ በማድረጉ ምክንያት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው መሻሻል አለመሻሻሉን ለመመርመር ያስችላል የሚል እምነት በመኖሩ ነው።

3.2 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከፊል ፍትነታዊ እንደመሆኑ ቅድመ እና ድህረልምምድ ፈተና በመስጠት በተገኘው አሀዛዊ መረጃ ላይ ተመስርቶ ሰፊ ትንታኔ የቀረበበት ነው። ጥናቱ ፍትነታዊ በመሆኑ በአብዛኛው አሀዛዊ የምርምር ዘዴን (Quantitative Research Method) መሰረት ያደረገ ቢሆንም ለጥናቱ ይጠቅማሉ ተብለው የተሰበሰቡትን መረጃዎች ተንትኖ ለማቅረብ እንዲያመች ገላጭ የአቀራረብ ዘዴንም (Discriptive Method) ተጠቅሟል።

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ የተነሱትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ መረጃ ከማን እና እንዴት መገኘት እንደሚቻል፣ መረጃ እንዴትስ መሰብሰብ እንዳለበት፣ የተሰበሰበው መረጃ እንዴትስ ባለመንገድ መተንተን እንደሚገባ፣ የተተነተነው መረጃ እንዴት ትርጉም እንደሚሰጥ እና ጥናቱ ግቡን መምታት እንዲችል ለማድረግ የጥናቱ ዘዴ በስሩ የጥናቱን የመረጃ ምንጭ፣ የናሙና አወሳሰድ፣ የመረጃ መሰብሰብያ መሳርያዎች፣ የማንበብ ብልሃት ትምህርት አሰጣጥ፣ የመረጃ አሰባሰብ ቅደም ተከተል እና የመረጃ አተናተን ዘዴን አካቶ ይዟል።

3.2.1 የጥናቱ የመረጃ ምንጭ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋነኛ የመረጃ ምንጭ ሆነው ያገለገሉት በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ በሁለት የመሰናዶ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ የ9ኛ ክፍል ሶማልኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች ናቸው። ጥናቱ የተነሳበትን አላማ ለማሳካት ጅግጅጋ ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት እና ጅግጅጋ ሼክ አብዱሰላም ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤቶችን ተጠቅሟል። ለጥናቱ ከተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሁለት የሙከራ እና አንድ ጥብቅ ቡድኖች በጥናቱ መረጃ በመስጠት ተሳትፈዋል።

ለጥናቱ መረጃ በመስጠት የተሳተፉት በሶማልኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ብቻ ናቸው። ለዚህም ሁለት ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው በሶማልኛ እና በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች መካከል በአማርኛም ሆነ በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃት መበላለጥ ሊኖር ስለሚችል በአንደኛው ቋንቋ ተጠቃሚዎች ላይ ለማተኮር በማሰብ ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽን ለማየት ተማሪዎች በሁለት ቋንቋዎች መጠቀም ያለባቸው በመሆኑ ነው። በዚህ መሰረት መረጃ በመሰብሰብ ወቅት በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የጥናቱን አካሄድ ለመጠበቅ ሲባል(መረጃ እንዳይዛባ) በፈተና ወቅት መረጃ ከመስጠት ተሳትፎ እንዲገለሉ ተደርጓል።

3.2.2 የናሙና አወሳሰድ

ሀ. ጥናቱ የተካሄደበት ክልል እና ከተማ አመራረጥ

ጥናቱ ሶማሌ ክልልን በኢላማዊ ንሞና ዘዴ መርጧል። ሶማሌ ክልል የተመረጠበት ምክንያት በክልሉ የአፍ መፍቻ ቋንቋ (ሶማልኛ) እና ሁለተኛ ቋንቋ (አማርኛ) ትምህርት በተለይ ደግሞ የማንበብ ክሂል ትምህርት እንዴት እየተሰጠ እንዳለ በመመርመር የተሻለ የትምህርት አሰጣጥ አቅጣጫ ለማሳየት የተለያዩ ምርምራዊ ስራዎችን ማከናወን ተገቢ መሆኑ ስለታመነበት ነው።

ጥናታዊ ፅሁፉ በክልሉ ከሚገኙ ዘጠኝ ዞኖች (ሺነሌ፣ ጅግጅጋ፣ ዳጋሃቡር፣ ፊቅ፣ ዋርዴር፣ ቆራሄይ፣ ጎዴ፣ አፍዴር፣ ሊበን) መካከል ጅግጅጋ ከተማን በአመቺነት እና ኢላማዊ ንሞና ዘዴ ወስዷል። ይህ የሆነበት ዋነኛ ምክንያት የጥናቱ አቅራቢ በስራ ምክንያት በአካባቢው ባሉ ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች በተዘዋወረበት አጋጣሚ ተማሪዎች (በተለይ ሶማልኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች) በአማርኛ ቋንቋ በከፍተኛ ደረጃ አንብቦ የመረዳት ችግር እንዳለባቸው በማስተዋሉ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የጥናቱ አቅራቢ በዚሁ አካባቢ የሚሰራ በመሆኑ መረጃን በቀላሉ ለማግኘት በማሰብም ነው።

ለ. የትምህርት ቤቶች አመራረጥ

በጅግጅጋ ከተማ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ጅግጅጋ ሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት እና ጅግጅጋ ሼክ አብዱሰላም ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች

በኢላማዊ እና አመቺነት ንሞና ዘዴ ተመርጠዋል። እነዚህ ትምህርት ቤቶች የተመረጡበት ምክንያት በከተማው ውስጥ የሚገኙ ብቸኛ የመንግስት ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች በመሆናቸው በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ሁኔታ በማጤን ምርምራዊ ሀሳብ ለመሰንዘር፣ ትምህርት ቤቶቹ በከተማው መካከል ተቀራርበው የሚገኙ በመሆናቸው በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ላይ ጥናቱን ለማካሄድ በማሰብ እና ለምርምር ስራው ተባባሪ እና ፈቃደኛ ርዕሳነ መምህራን፣ መምህራን እና ተማሪዎች በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ በመኖራቸው መረጃን በቀላሉ ለመሰብሰብ ያስችላል የሚል እምነት በመኖሩ ነው።

ሐ. የክፍል ደረጃ አመራረጥ

ለዚህ ጥናት ዘጠነኛ ክፍል በኢላማዊ ንሞና ዘዴ ተመርጧል። ዘጠነኛ ክፍል የተመረጠበት ምክንያት የክፍል ደረጃው የሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት መነሻ በመሆኑ በዚህ ደረጃ ያለውን የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና አንብቦ የመረዳት ሁኔታ በጥልቀት ለማየት በማሰብ ነው። ከተጠቀሰው የክፍል ደረጃ ዝቅ ማለት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ብቃታቸው ሊቀንስ የሚችል በመሆኑ የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽን ለመከታተል አመቺ አለመሆኑ ታሳቢ ተደርጓል። ጥናቱ በመሰናዶ ትምህርት መርሃ ግብር የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ ያላደረገበት ምክንያት በነዚህ የክፍል ደረጃዎች በአሁኑ ሰዓት በክልሉ የሶማልኛ ቋንቋ ትምህርት እየተሰጠ ባለመሆኑ (መሰጠት ሲገባው) ነው።

መ. በጥናቱ የተሳተፉትን መምህርት አመራረጥ

በጥናቱ የሙከራ ቡድኖችን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃቶችን እንዲያስተምሩ አንድ ሴት መምህርት በኢላማዊ ንሞና ዘዴ ተመርጠዋል። ጥናቱ በተካሄደበት ጅግጅጋ ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት ዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ቁጥር አምስት ሲሆኑ ሶማልኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ደግሞ አራት ናቸው። እንዲሁም በጅግጅጋ ሼክ አብዱ ሰላም ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት በዚሁ የክፍል ደረጃ አምስት የአማርኛ እና አምስት የሶማልኛ ቋንቋ መምህራኖች አሉ። በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ሶማልኛ ቋንቋ የሚስተምሩት መምህራን የትምህርት ዝግጅታቸው ከተለያዩ ኮሌጆች በዲፕሎማ የትምህርት

መርሃግብር የተመረቁ ናቸው። በሁለቱም ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋ የሚያስምሩት መምህራንም የትምህርት ዝግጅታቸው ከተለያየ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ቋንቋ እና ስነፅሁፍ ክፍል በዲግሪ የትምህርት መርሀግብር የተመረቁ ናቸው።

ሶማልኛ ቋንቋ መምህራኑ የትምህርት ዝግጅታቸው ዲፕሎማ ደረጃ በመሆኑ እና አማርኛ ቋንቋን በሚገባ መጠቀም ባለመቻላቸው በጥናቱ እንዲሳተፉ አልተደረገም። አማርኛ ቋንቋ መምህራኑም በጥናቱ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን ለማስተማር የትምህርት ዝግጅታቸው በቂ ቢሆንም ሶማልኛ ቋንቋን በሚገባ መጠቀም ባለመቻላቸው በጥናቱ አልተሳተፉም። ለጥናቱ ከተመረጡት ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምህራን እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር በጅግጅጋ ሼክ አብዱሰላም ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት እንግሊዝኛ ቋንቋ የሚያስተምሩት ሴት መምህርት በጥናቱ አቅራቢ የማንበብ ብልሃት ትምህርት አሰጣጥ ስልጠና ተሰጥቷቸው በጥናቱ እንዲሳተፉ ተደርጓል። ትምህርቱ በአንድ መምህርት እንዲሰጥ ያስፈለገበት ምክንያት በተለያየ የሙያ ብቃት፣ የትምህርት ዝግጅት፣ የቋንቋ ችሎታ እና የትምህርት አሰጣጥ መለያየት ምክንያት ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ተላውጦ እንዳይከሰት በማሰብ ነው። በጥናቱ መምህርቷ ትምህርቱን እንዲያስተምሩ የተመረጡት መደበኛ ስራቸው ቋንቋ ማስተማር (እንግሊዝኛ) በመሆኑ፣ እንግሊዝኛ ቋንቋ ለማስተማር የሚያበቃውን የመጀመሪያ ዲግሪ ከማግኘታቸው አስቀድሞ ሶማልኛ ቋንቋ ለረጅም ጊዜ በማስተማራቸው እና በአማርኛ ቋንቋ አፍፈት በመሆናቸው ቋንቋዎቹን በሚገባ እንደሚጠቀሙባቸው የጥናቱ አቅራቢ በማረጋገጡ ነው። ከዚህ በተጨማሪ መምህርቷ በጥናቱ ለመሳተፍ ፈቃደኛ በመሆናቸውም ጭምር ነው። መምህርት ከማስተማር ሙያዊ እገዛቸው በተጨማሪ ለጥናታዊ ፅሁፉ አስፈላጊ የሆኑ ፅሁፎችን ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ በመተርጎም እና በጥናቱ በመከራ ቡድን ውስጥ ለተሳተፉ የተወሰኑ ተማሪዎች በሶማልኛ ቋንቋ ቃለመጠይቅ በማቅረብ ስራ ተሳትፈዋል።

በጥናቱ ሂደት የጥናቱ አቅራቢ ራሱ ተተኳሪ ተማሪዎችን ያላስተማረበት ምክንያት አድሏዊነት (ጥናቱ ራሱ ከሚያስገኘው ውጤት ይልቅ ወደጥናቱ አቅራቢ ፍላጎት መጎተት) እንዳይፈጠር በማሰብ፣ የጥናቱ አቅራቢ በጥናቱ ተተኳሪ የሆነውን ሶማልኛ ቋንቋን ምርምሩ በሚፈልገው ደረጃ መናገር የማይችል በመሆኑ እና ተማሪዎች

በሚያውቋቸው በራሳቸው መምህር ትምህርቱ ቢሰጥ የበለጠ ጠቃሚ ነው ብሎ በማሰብ ጭምር ነው።

ሰ. የሙከራ እና ጥብቅ ቡድኖች አመራረጥ

ለዋናው ጥናት መረጃ በተሰበሰበበት በ 2009 ዓ.ም ለጥናቱ በተመረጠው በጅግጅጋ ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት አስራአምስት ዘጠነኛ ክፍሎች (9A-9O) ያሉ ሲሆን በጅግጅጋ ሼክ አብዱሰላም ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት ደግሞ አስራአራት ዘጠነኛ ክፍሎች (9A-9N) አሉ። በጥናቱ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን እንዲያስተምሩ የተመረጡት መምህርት ዋናውን የስራ ጊዜያቸውን በማይነካ መልኩ ካሉት 9ኛ ክፍሎች ሁለት የሙከራ እና አንድ ጥብቅ ቡድን በአመቺነት ንሞና ዘዴ ተመርጠዋል። የተመረጡት ክፍሎች ሙከራ ቡድን አንድ "9H" (በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን የተከታተለ) እና ጥብቅ ቡድን "9D" ከጅግጅጋ ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት ሲሆኑ ከጅግጅጋ ሼክ አብዱሰላም ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት ሙከራ ቡድን ሁለት "9F" (በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት ትምህርት የተከታተለ) ናቸው። በጥናቱ ሁለት የሙከራ ቡድኖች ያስፈለጉበት ምክንያት በእያንዳንዱ ሙከራ ቡድን ውስጥ የተሳተፉ ተማሪዎች በተማሩበት ቋንቋ የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ በመማራቸው በዛው በተማሩበት ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እውቀታቸው እና አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው መጎልበት አለመጎልበቱን ለማየት እና ተማሪዎቹ የማንበብ ብልሃቶችን ከተማሩበት ቋንቋ ወደአልተማሩበት ቋንቋ እያሸጋገሩ በመጠቀማቸው አንብቦ መረዳታቸው መጎልበት አለመጎልበቱን ለመመርመር በማሰብ ነው።

ረ. የተማሪዎች አመራረጥ

ለዋናው ጥናት መረጃ በተሰበሰበበት ወቅት በጅግጅጋ ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት ውስጥ 762 ወንድ 508 ሴት በድምሩ 1270 የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ያሉ ሲሆን በጅግጅጋ ሼክ አብዱ ሰላም ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት ደግሞ 665 ወንድ 408 ሴት በድምሩ 1073 9ኛ ክፍል ተማሪዎች አሉ። ለጥናቱ በተመረጠው በእያንዳንዱ ክፍል ማለትም በሙከራ ቡድን አንድ "9H" 52 ወንድ እና 45 ሴት በድምሩ 97 በስም መዝገብ ላይ የተመዘገቡ ሲሆን በጥናቱ የተሳተፉት 73 ተማሪዎች

ናቸው። በመካራ ቡድን ሁለት “9F” 44 ወንድ እና 51 ሴት በድምሩ 95 ተማሪዎች በስም መዝገብ ላይ የተመዘገቡ ሲሆን 69 ተማሪዎች በጥናቱ ተሳትፈዋል። እንዲሁም በጥናቱ ጥብቅ ቡድን “9D” ክፍል ውስጥ 52 ወንድ እና 34 ሴት በድምሩ 86 ተማሪዎች በስም መዝገብ ላይ የተመዘገቡ ሲሆን 66 ተማሪዎች በጥቅሉ 208 ተማሪዎች ተሳትፈዋል። በጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎች እና በስም መዝገብ ላይ የሰፈረው ቁጥር የተለያየበት ምክንያት የተወሰኑቱ ተማሪዎች ፈተና በተሰጠበት ወቅት ባለመኖራቸው፣ የተወሰኑቱ ተማሪዎች ከትምህርት በማቋረጣቸው ሌሎች በአማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች መረጃ እንዳይሰጡ በመደረጋቸው ነው። በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዘፈቀዳዊ (ብድግብድግ) ንሞና ዘዴ ተግባር ላይ አልዋለም።

በጥናቱ በመካራ ቡድኖቹ እና በጥብቅ ቡድኑ ውስጥ የተሳተፉት ተማሪዎች በሙሉ አንብቦ የመረዳት ብቃት መለክያ ፈተናውን ወስደዋል። የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቁ ላይ የተሳተፉት በመካራ ቡድን ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ብቻ ናቸው። ምክንያቱም የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን የተከታተሉት መካራ ቡድኖቹ ብቻ በመሆናቸው ነው። ከዚህ በተጨማሪ በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ መናገር ቃለመጠይቅ ከእያንዳንዱ መካራ ቡድን ስድስት ስድስት ፈቃደኛ የሆኑ ተማሪዎች እንዲሳተፉ ተደርጓል።

3.2.3 የጥናቱ የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ሶስት አይነት የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች ተጠቅሟል። እነሱም አንብቦ የመረዳት ውጤት መለክያ ፈተና (Reading Comprehension Achievement Test) ፣ የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ (Survey of Reading Strategy Questionaire / SORSQ) እና በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ የመናገር ቃለመጠይቅ (Think Aloud Protocol and Retrospective Interview) ናቸው።

3.2.3.1 አንብቦ የመረዳት ብቃት መለክያ ፈተና

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ (በየቋንቋው) የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ብቃት ለመለካት የሚያስችል ፈተና ተጠቅሟል ።

በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መርሀግብር በቋንቋ ክፍል የሚደረግ የማንበብ ሂደት ዋነኛ አላማ የቀረበን ውህድአሀድ አንብቦ መዳት ነው። በዚህ ጥናት ሒደት የተማሪዎች በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ዋነኛ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው። በዚህ መሰረት ተማሪዎች በሶማልኛ እና በአማርኛ ቋንቋ ያላቸውን አንብቦ የመረዳት ብቃት ለመለካት ለሙከራ እና ጥብቅ ቡድኖች ቅድመልምምድ ፈተና (Pre-Test) ተሰጥቷል። በዚህ ጥናት በተነደፈው የትምህርት መርሀግብር መሰረት ለሙከራ ቡድኖቹ የማንበብ ብልሃት ትምህርት በሁለቱም ቋንቋዎች ከተሰጠ በኋላም ድህረልምምድ አንብቦ የመረዳት ብቃት መለኪያ ፈተና (Post-test) ተሰጥቷል። ቅድመልምምድ ፈተና የተሰጠበት ምክንያት በጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎች በሶማልኛም ሆነ በአማርኛ ቋንቋ (በየቋንቋው) አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው እኩል ደረጃ ላይ መሆን አለመሆኑን (የችሎታ መበላለጥ መኖር አለመኖሩን) ለማረጋገጥ ነው። ድህረልምምድ ፈተና የተሰጠበት ምክንያት የማንበብ ብልሃትን ለማስተማር በተነደፈው የትምህርት በመርሀግብር መሰረት ለሙከራ ቡድኖቹ ትምህርቱ ከተሰጠ በኋላ ሙከራ ቡድኖቹ እና ጥብቅ ቡድኑ ከቅድመልምምድ በተሻለ መልኩ ድህረልምምድ የባህሪ ለውጥ ማምጣት አለማምጣታቸውን ለመመርመር ነው።

በሁለቱም ቋንቋዎች አንብቦ መረዳትን ለመፈተሽ የቀረቡት ፈተናዎች እያንዳንዳቸው አንድ ምንባብ እና አስራአምስት የምርጫ ጥያቄዎችን ያካተቱ ናቸው። ቅድመ እና ድህረልምምድ የቀረቡት ፈተናዎች ከይዘት አንፃር የተለያዩ ቢሆኑም ከመጠን ከርዝመት፣ ከይዘት ክብደት፣ ከቋንቋ አጠቃቀም አንፃር ተመሳሳይ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል። ቅድመ እና ድህረልምምድ አንብቦ የመረዳት ውጤትን ለመለካት የቀረቡት ምንባቦች እና የምርጫ ጥያቄዎች ከይዘት አንፃር ተመሳሳይ ያልተደረጉበት ምክንያት ተማሪዎች የጥያቄዎቹን መልሶች እያስታወሱ ሊሰሩ ይችሉ ይሆናል የሚል ስጋት በመኖሩ ነው።

የፈተናዎቹ ትኩረት የምንባቡን ዋና ሀሳብ መለየት፣ ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት፣ ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ መስጠት፣ ዋና ሀሳብን አሳጥሮ ማቅረብ፣ የተለዩ ዝርዝር ጉዳዮችን ወይም የተለየ መረጃን መለየት፣ በውህድአሀዱ ውስጥ ያለውን መልእክት መለየት ወዘተ ናቸው። በሁለቱም ቋንቋ ለቅድመ እና ድህረልምምድ ፈተና የተዘጋጁት ምንባቦች እና አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች በ9ኛ ክፍል ደረጃ በሀገር ውስጥ ወጥ ሆኖ የተዘጋጀ

(Standard) ፈተና ባለመኖሩ የተለያዩ ወገኖች ያደረጉትን ጥናት በማስተዋል (Nation 2006፣ Cain & Oakhill 2006፣ Alderson 2005፣ Weir 1990) የጥናቱ አቅራቢ በራሱ መንገድ አዘጋጅቷል።

አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመለካት የቀረቡት ፈተናዎች ምንባቦችን እና የምርጫ ጥያቄዎችን ያካተቱበት ምክንያት ተማሪዎች ምንባቦቹን በማንበብ ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለመፈተሽ የሚያስችሉ ሁነኛ መሳርያዎች በመሆናቸው ነው (Alderson 2005፣ Weir 1990፣ ።። የምርጫ ጥያቄ በራሱ መጠነኛ ድክመት ቢኖርበትም (ለማምት የተጋለጠ መሆን) መረጃ ሰጪ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ በተለያዩ ወገኖች ቢታረም የግል አተያይ ሳይታከልበት ትክክለኛ ውጤት መመዝገብ የሚያስችል በመሆኑ ጥናቱ ተጠቅሞበታል። ከዚህ በተጨማሪ የምርጫ ጥያቄ የጥናቱ ተሳታፊዎች የሰጡትን ምላሽ በቀላሉ ለማረም አመቺ በመሆኑ ጭምር አገልግሎት ላይ ውሏል።

3.2.3.2 የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ

የተማሪዎችን የማንበብ ብልሃት ለመፈተሽ የሚያስችሉ የተለያዩ አማራጮች አሉ። አማራጮቹም የማንበብ ብልሃት የአጠቃቀም ግንዛቤን ለመፈተሽ የሚያገለግል የፅሁፍ መጠይቅ፣ በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ የመናገር ቃለመጠይቅ፣ ትውስታን የማነቃቅያ ቃለመጠይቅ፣ ምልከታ፣ የብልሃት ማረጋገጫ (መከታተያ) ዝርዝር፣ የእለት ገጠመኝ መመዝገብያ እና የጉዞ ማስታወሻ በዋናነት ይጠቀሳሉ (Mokhtari & Sheory 2002)። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከነዚህ ዘዴዎች ውስጥ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤን ለመለየት የሚያስችል አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅን ዋነኛ የመረጃ መሰብሰብያ አድርጎ ተጠቅሟል። ጥናቱ የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ የተጠቀመበት ምክንያት የተማሪዎችን የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ለመፈተሽ የበለጠ ተመራጭ እና ታዋቂ ዘዴ በመሆኑ ነው (Mokhtari & Sheory 2002፣ Mokhtari & Reichard 2002)።

ጥናታዊ ፅሁፉ ለሙከራ ቡድኖች በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ቅድመ እና ድህረ ልምምድ አንድ አይነት ይዘት እና ቁጥር ያለው የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ አቅርቧል። በዚህ የምርምር ስራ የጥናቱ ተሳታፊዎችን የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ለመፈተሽ አገልግሎት ላይ የዋለው መጠይቅ ሁለት ክፍሎች አሉት።

የመጀመሪያው አጠቃላይ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀማቸውን ለመፈተሽ የቀረበ ሚዛናዊ የደረጃ ልኬት (Likert Scale) ነው።

ሚዛናዊ የደረጃ ልኬት ጥያቄዎችን በአረፍተነገር በዝርዝር በማቅረብ ተተኳሪ ተማሪዎች ምላሻቸውን በቁጥር አማካኝነት (ከ 0-5 ወይም ከ1-5) የሚገልፁበት ነው (Mokhtari 2001)። የመጠይቁ ጠቀሜታ ብዛት ያላቸው መላሾች በቀረበው ጥያቄ መሰረት የፈለጉትን ጥያቄ መስማማት አለመስማማታቸውን ለማመላከት (አቋም ለመያዝ) የሚችሉበት መሆኑ ነው። ምርምር አቅራቢውም ብዙ ሰዎች የሰጡትን ምላሽ አንፃራዊ በሆነ መልኩ በቀላሉ (በተመቸ ሁኔታ) ለመተንተን ያስችለዋል። የመጠይቁ ድክመት በግምት ወይም በግዴለሽነት መልስ መስጠት፣ አማካይ ላይ ያለውን ቁጥር (3 ለመወሰን እቸገራለሁ) የመረጡ ተተኳሪዎች የሰጡትን ሀሳብ ተረድቶ መተርጎም መቸገር ነው። ምክንያቱም መላሾች ይህን ቁጥር የሚመርጡት ጥያቄው ጠቃሚ ባለመሆኑ ወይም ፍላጎት የሌላቸው በመሆኑ ወዘተ ነው (McDonough 1997)። በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ይህን ችግር ለመፍታት በአማካይ ላይ ያለውን ቁጥር (3) ትርጉም ያለው ሀሳብ እንዲወክል በማድረግ ችግሩን ለማስወገድ ጥረት ተደርጓል።

በዚህ ጥናት ሚዛናዊ የደረጃ ልኬት የፅሁፍ መጠይቁ አምስት አማራጮች አሉት። እነሱም **(1 በጭራሽ አልጠቀምም፣ 2 አልፎ አልፎ (ውስን ጊዜ) እጠቀማለሁ፣ 3 አንድ አንድ ጊዜ እጠቀማለሁ (50% ያህል)፣ 4 አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ እና 5 ሁልጊዜ እጠቀማለሁ)** ናቸው። በዚህ ጥናት 3. አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ (50% ያህል) በሚል ትርጉም እንዲይዝ የተደረገበት ምክንያት በአማራጭ 2.አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ የሚል አማራጭ ከመጣ በኋላ 3.ለመወሰን እቸገራለሁ ማለት በ 2 ቁጥር የተቀመጠውን ሀሳብ የሚያፋልስ በመሆኑ ነው።

በመጠይቁ ሚዛናዊ የደረጃ ልኬት አቀራረብ እያንዳንዱ ብልሃት በሁለት ጥያቄዎች (Items) እንዲለካ የተደረገ በመሆኑ የፅሁፍ መጠይቁ በየቋንቋው 32 አሳሽ የፅሁፍ ጥያቄዎችን ያካተተ ነው። ትኩረት የተሰጠባቸው የማንበብ ብልሃቶች አስራስድስት ሲሆኑ በሁለት ጥያቄዎች ሲሰሉ ከአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት 16፣ ከልእለአእምሮታዊ 6፣ ከትውስታ 4፣ ከማካካስ 2 እና ከማህበራዊ የማንበብ ብልሃት 4 ጥያቄዎች ተካተዋል። በመጠይቁ ተራ ቁጥር 1፣3፣4፣5፣ 6፣7፣11፣ 14፣ 17፣19፣20፣21፣22፣23፣2፣30 አእምሮታዊ፣ ተራ ቁጥር 2፣10፣13፣18፣26፣29

ልእለአእምሮታዊ፣ ተራ ቁጥር 9፣16፣25፣32 ትውስታ፣ ተራ ቁጥር 12፣28 ማካካስ፣ ተራ ቁጥር 8፣15፣24፣31 ማህበራዊ የማንበብ ብልሃቶችን ያካተተ ነው (አባሪ ስምንትን ይመለከቷል)። የጥያቄዎቹ ቁጥር የተበላለጠበት ምክንያት ከተመረጡት የማንበብ ብልሃት አይነቶች ጋር የተያያዘ ነው።

የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ ሚዛናዊ የደረጃ ልኬት አማካይ ውጤት 3.5 እና ከዛ በላይ ከሆነ ከፍተኛ፣ ከ 2..5 — 3.4 ከሆነ መካከለኛ እንዲሁም 2.4 እና ከዛ በታች ከሆነ ዝቅተኛ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ውጤት የሚል ትርጉም እንዳለው ፀሀፊዎች ያስረዳሉ (Mokhtari & Sheorey 2002፣ Oxford 1990)። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ይህን ሀሳብ ይጋራል።

የመጠይቁ ሁለተኛ ክፍል ለማንበብ ተግባር የተመረጠ አጭር ምንባብ (Specific Passage) አንብቦ ለመረዳት የተጠቀሙበትን የማንበብ ብልሃት ራሳቸው በስም እየጠቀሱ እንዲዘረዝሩ በማድረግ አጠቃቀማቸውን ለመፈተሽ ታስቦ የቀረበ ነው። ይህ የመጠይቅ ክፍል ጠቀሜታው ግምት እና ግዴለሽነትን ማስወገድ ነው።

3.2.3.3 በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ የመናገር ቃለ መጠይቅ

በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ የመናገር ቃለመጠይቅ ሌላው የዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያ ነው። ጥናቱ ይህን ቃለመጠይቅ የተጠቀመበት ምክንያት ከላይ በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰብያ መሳርያዎች ከተሰበሰበው መረጃ በተጨማሪ ጠቃሚ መረጃ ለማግኘት በማሰብ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ቃለ መጠይቁ በማንበብ ሂደት በአይን የማይታይን አእምሯዊ ሂደት ለመሰብሰብ ወይም ድብቅ በሆነው አእምሮ ውስጥ ያለውን ሂደት ለማግኘት ልክ እንደመስኮት የሚያገለግል በመሆኑ በተለይ ደግሞ የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽን የተመለከተ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ውጤታማ መሳሪያ በመሆኑ ነው (Yoshida 2008፣ Kyems 2005)።

በጥናቱ የቀረበው ይህ ቃለመጠይቅ ክፍት እንዲሁም የማንበብ ብልሃቶችን በዝርዝር ያካተተ ሲሆን ዋነኛ አላማው ተማሪዎች የቀረበውን ውህድአሀድ አንብበው ለመረዳት ምን እንዳደረጉ፣ የማንበብ ብልሃቶችን እንዴት እንደተጠቀሙ፣ የቀደመ እውቀታቸውን ከአዲሱ ሐሳብ ጋር እንዴት እንዳቀናጁ፣ የቀረበውን ውህድአሀድ አንብቦ ለመረዳት ምን

አይነት ችግር እንደገጠማቸው፣ የገጠማቸውን ችግር ለማስወገድ ምን እርምጃ እንደወሰዱ ወዘተ በመግለፅ መረጃ እንዲሰጡ ማድረግ ነው።

በዚህ ዘዴ ተማሪዎች መረጃ ሲሰጡ ፍፁም ነፃነት እንዲሰማቸው በማድረግ በአንድ ክፍል ውስጥ ብቻቸውን ሆነው ከራሳቸው ጋር እንደሚነጋገሩ አይነት በተናጠል እንዲተገብሩ ተደርጓል። በዚህ መረጃ መሰብሰብያ ዘዴ መረጃ የሰጡት ተማሪዎች በፍትነታዊ (በመከራ) ቡድኖች ውስጥ ከተሳተፉት የተወሰኑትን (ከእያንዳንዱ መከራ ቡድን ስድስት ስድስት ተማሪዎች) በመውሰድ ተከናውኗል። ጥናቱ የተለያዩ ፀሀፊዎች (Yoshida 2008፣ Kyems 2005፣ Mokhtari & Reichard 2002) የተጠቀሙበትን በመውሰድ እና ለጥናቱ በሚያመች መንገድ ተዘጋጅቶ (ትኩረት የተደረገባቸው ብልሃቶች አይነት ላይ በማነጣጠር) ቀርቧል።

በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ የመናገር ቃለመጠይቁን ለጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ያቀረቡት የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን ያስተማሩት መምህርት ናቸው። ቃለመጠይቁ በተማሪዎች ፍላጎት በሶማልኛ ቋንቋ ቀርቧል። ቃለመጠይቁ በመቅረፀ ድምፅ ተቀርፆ ወደፅሁፍ ከተገለበጠ እና ከተተረጎመ በኋላ አስፈላጊው መረጃ ተለይቶ በጥናቱ የመረጃ ትንተና ክፍል አገልግሎት ላይ እንዲውል ተደርጓል።

3.2.4 የመረጃ መሰብሰብያ መሳርያዎች ትክክለኛነት እና አስተማማኝነት

3.2.4.1. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ትክክለኛነት

ለአንድ የምርምር ስራ አገልግሎት እንዲውል የተነደፈ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ (መለኪያ) ለመሰብሰብ የታቀደውን መረጃ በታሰበው መንገድ በተቃና፣ በተሟላ እና በተገቢ ሁኔታ ለመሰብሰብ እንዳስቻለ የሚያመለክት ከሆነ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያውን ትክክለኛነት ያሳያል (ያለው 2006፣ Perry 2005፣ Muijs 2004)። በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ መረጃ ለማሰባሰብ ያገለገሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ትክክለኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የጥናቱ አቅራቢ የተለያዩ አማራጮችን ተጠቅሟል።

የጥናቱ አቅራቢ በጥናቱ ሒደት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የተጠቀመበት አንደኛው መንገድ ለአማካሪ ደጋግሞ ማሳየት ነው። በጥናቱ

ሒደት የጥናቱ አቅራቢ ከአማካሪው ጋር በተደጋጋሚ ጊዜ በመወያየት እና የተገኘውን ግብአት በመጠቀም የተፈለገው የጥናት ግብ እውን እንዲሆን በሚያስችል መልኩ የመረጀ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ለማስተካከል ጥረት አድርጓል። በተለይ በናሙና ጥናቱ የቀረቡት 24 ዝርዝር የማንበብ ብልሃት አይነቶች ከተማሪዎች የክፍል ደረጃ እና እድሜ አንፃር የበዙ በመሆናቸው ቢቀነሱ፤ ከይዘት አንፃር ድግግሞሽ የሚታይባቸው ጥያቄዎችን ስርጭት ማመጣጠን ያስፈልጋል (ሁሉም የማንበብ ብልሃቶች በተመጣጣኝ ቁጥር ለምሳሌ አንድ ብልሃት በሁለት ጥያቄዎች) የሚል አስተያየት ከአማካሪዬ የተሰነዘሩ በመሆናቸው በዋናው ጥናት የማንበብ ብልሃቶች ከ24 ወደ 16 ተቀንሰዋል።

አስቀድሞ የተቀረፀው አሳሽ የማንበብ ብልሃት የፅሁፍ መጠይቅ ውስጥ አንዳንድ ብልሃቶች በሁለት ጥያቄዎች የቀረቡ በመሆናቸው ለትምህርት የቀረቡት ብልሃቶች እና በፈተናው ወቅት የቀረቡት ጥያቄዎች ቁጥር አለመጣጣም ታይቶ ነበር (24 ብልሃቶች 34 ጥያቄዎች)። ይህ ማለት የተወሰኑቱ የማንበብ ብልሃቶች ከአንድ በላይ ጥያቄዎች የተጠየቁ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በአንድ ጥያቄ ተጠይቀው ነበር። በዋናው ጥናት እያንዳንዱ ብልሃት በሁለት ጥያቄዎች እንዲፈተሽ ተደርጎ ሁሉም ብልሃቶች ተመጣጣኝ በሆኑ የጥያቄዎች ቁጥር እንዲፈተሽ ተደርጓል። በተጨማሪ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቁን በግምት እንዳይመልሱ አጭር ምንባብ ቀርቦላቸው እያነበቡ የተጠቀሙበትን የማንበብ ብልሃት ራሳቸው ቢገልፁ የሚል ጠቃሚ አስተያየት የተሰነዘረ በመሆኑ ይህም በዋናው ጥናት ተግባራዊ ተደርጓል።

ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል መምህራን፣ ለውጭ ቋንቋዎች እና ስነፅሁፍ መምህራን፣ ለስነልቦና መምህራን፣ በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ለሚያስተምሩ የምጣኔ ሀብት ጥናት መምህር በማሳየት እና የተገኙ ጠቃሚ ሀሳቦችን (አስተያየት) በማከል የመረጃ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት ለመጠበቅ ጥረት ተደርጓል። በዚህ ሂደት አብዛኛው አስተያየት የማንበብ ብልሃት ግንዛቤ እና አጠቃቀምን ለመፈተሽ የቀረበው ፈተና የአቀራረብ ልዩነት ካልሆነ በስተቀር (ምርጫ እና ሚዛናዊ የደረጃ ልኬት) ተመሳሳይ በመሆኑ ግንዛቤን ለመፈተሽ የቀረበው ቢቀር፣ የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቁ ተመሳሳይ ወይም ድግግሞሽ የሚመስሉ ጥያቄዎች ቢስተካከሉ፣ ግልፅ በሆነ (በሚገባ)

መንገድ ቢቀርቡ የሚል እና እንዳንዱ የማንበብ ብልሃት ወጥ በሆነ ቁጥር ይለካ የሚሉ ጠቃሚ ሀሳቦች ይገኙበታል። አንብቦ መረዳትን ለመለካት የቀረበው ፈተና የምርጫ ጥያቄዎች መጠነኛ ጭማሪ ቢደረግባቸው የሚል አስተያየትም ተሰንዝሯል። ሌላው በናሙና ጥናቱ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳትን ለመፈተሽ የቀረቡት ፈተናዎች የምርጫ ጥያቄዎች መጠን የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ እና እድሜ ግምት ውስጥ ቢያስገባ የሚል ሀሳብም ተሰንዝሯል። የጥናቱ አቅራቢ የተሰጡትን ጠቃሚ ምክረሀሳቦች በመቀበል እና የተተኳሪ ተማሪዎችን የክፍል ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በተለይ አንብቦ መረዳትን ለመፈተሽ የቀረቡትን ፈተናዎች የጥያቄ ቁጥር ወደአስራአምስት ለማስተካከል ሞክሯል።

የጥናቱ አቅራቢ በጥናቱ ሂደት የምርምር ስራውን ለማካሄድ በመረጣቸው ትምህርት ቤቶች ላሉ የአማርኛ እና የሶማልኛ ቋንቋ መምህራን በማሳየትም የማሻሻል ስራ ተሰርቷል። በአማርኛ ቋንቋ ቅድመ እና ድህረልምምድ አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመለካት የተዘጋጁት ሁለት ሁለት ምንባቦች ሃያ ሃያ ጥያቄዎችን ያካተቱ ነበር። መምህራኑ ተማሪዎቻቸው ያላቸውን የአማርኛ ቋንቋ ክፍተት ግምት ውስጥ አስገብተው እያንዳንዱ ፈተና አንድ ምንባብ ቢይዝ በቂ እንደሆነ በሰጡት አስተያየት መሰረት አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመለካት የታሰበው ፈተና ተስተካክሏል። በጥያቄዎቹ ይዘት ላይም ይከብዳሉ ብለው ያሰቧቸውን በመለየት የሰጡትን አስተያየቶች በመቀበል እና በማስተካከል ትክክለኛነትን ለማምጣት ጥረት ተደርጓል።

ሌላው በጥናቱ ሂደት የናሙና ጥናት (Pilot Study) በማካሄድ እና የመረጃ መሰብሰብያ መሳርያዎችን ትክክለኛነት በመፈተሽ ለደረጃ ማበልፀግያ ተቋቁሞ በማቅረብ በተገኘው ግብአት መሰረት የመረጃ መሰብሰብያ መሳርያዎችን የማሻሻል ስራ ተሰርቷል።

3.2.4.2. የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች አስተማማኝነት

በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ያለን አንድ ባህሪ ወይም ነገር በአንድ አይነት መለኪያ በተደጋጋሚ በመለካት የሚገኝ ተመሳሳይ ውጤት (የውጤት ወጥነት) የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያውን አስተማማኝነት (የልኬታ ስህተት የሌለው መሆኑን) ያመላክታል (ያለው 2006፡202፣ Muijs 2004፡71፣ Pallant 2001:85)። እንደ Muijs (2004፡73) አገላለፅ አንድን ነገር በመፈተሽ ሒደት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳርያዎች

አስተማማኝነት መደበኛ መስፈርት እንደሚያመላክተው የተሰላው አሀዝ ወደ 1 በተጠጋ ቁጥር አስተማማኝነቱ ከፍ እያለ የሚመጣ ሲሆን ወደ 0 በተጠጋ ቁጥር ደግሞ አስተማማኝነቱ እየቀነሰ ይመጣል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የመረጃ መሰብሰቢያ አስተማማኝነት ከ 0.7 በላይ ከሆነ የተቀረፀው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የጥናቱን አላማ ለማሳካት ምክንያታዊ አስተማማኝነት አለው ተብሎ ይወሰዳል፡፡

በምርምር ስራ አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመፈተሽ የተዘጋጀን ፈተና አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ከሚያስችሉ መንገዶች የፈተና ክብደት ቅለት ወይም የክብደት መጠን (Item Difficulty/Facility Index) እና የመለየት ብቃት (Item Discrimination) ማየት ወሳኝ ጉዳይ ነው (Muijs 2004፣ Pallant 2001)፡፡ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍም አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመለካት የቀረበውን ፈተና ክብደት ቅለት እና የመለየት ብቃት የናሙና ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት ለማየት ሞክሯል፡፡

ሀ.የፈተናዎቹ ክብደት ቅለት

በናሙና ጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ ታስበው የተዘጋጁትን ፈተናዎች ክብደት ቅለት ለመለካት የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በፈተናው ያመጡት ውጤት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይኸውም ተማሪዎቹ ያስመዘገቡት ውጤት ከትልቅ ወደ ትንሽ ቁጥር በመደርደር እና ለሶስት በመክፈል ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ ውጤት ያላቸው ተብለው ተለይተዋል፡፡ በመቀጠል መካከለኛ ውጤት ያላቸውን ቡድኖች በመተው እና ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ውጤት ያላቸውን በመውሰድ በመደበኛው ቀመር መሰረት ውጤታቸው ተሰልቷል፡፡ ጥናቱ የፈተናዎቹን ክብደት ቅለት ለመለካት የተጠቀመበት ቀመር የሚከተለው ገፅታ አለው፡፡

$$\text{ክብደት ቅለት} = \frac{\text{ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ውጤት ባስመዘገቡ ቡድኖች የተመለሱ ትክክለኛ መልሶች}}{\text{በሁለቱም ቡድኖች ያሉ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ቁጥር}}$$

Cohen et al. (2007:144)፣ Muijs (2004:71)

በቀረበው ቀመር መሰረት ተሰልቶ የተገኘው አሀዝ ከመደበኛ መስፈርት 0.3 - 0.7 ከሆነ (ከ0.3 በታች ከሆነ ከባድ ከ0.7 በላይ ከሆነ ቀላል) መረጃ ለመሰብሰብ የተቀረፀው ፈተና ክብደት ቅለት ምክንታዊ ነው ተብሎ ይታሰባል (Muijs 2004:71፣ ያለው 2006፡ 2002)።

ከላይ በቀረበው ቀመር መሰረት የናሙና ጥናቱ ቅድመ እና ድህረልምምድ አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመፈተሽ የቀረበው ፈተና የእያንዳንዱ ጥያቄ ክብደት ቅለት የተሰላ አሀዝ የሚያመለክተው 0.3 — 0.7 ወሰን ውስጥ በመሆኑ ክብደት ቅለቱ ምክንያታዊ አስተማማኝ ነው ማለት ይቻላል። በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመለካት የቀረበው ቅድመ እና ድህረልምምድ ፈተና ጥያቄ ቁጥር 9 እና 10 ከመደበኛ መስፈርቱ በታች መሆኑን ያሳያል። ይህ የሚያመለክተው ለዋናው ጥናት ጥያቄዎቹ መሻሻል እንዳለባቸው ነው። በናሙና ጥናቱ ግብአት መሰረት በሁለቱም ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመለካት የቀረበው ፈተና የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ መሰረት በማድረግ ተገቢ የይዘት ክብደት እንዲኖረው ጥረት ተደርጓል። በሙከራ ጥናቱ ቅድመልምምድ የማንበብ ብልሃት ግንዛቤን ለመፈተሽ የቀረበው ፈተና ክብደት ቅለት ሲታይ በአማርኛ ቋንቋ ጥያቄ ቁጥር 10፣11፣12፣14፣15 በሶማልኛ ደግሞ ጥያቄ ቁጥር 12፣14፣15 ከመደበኛ መስፈርቱ በታች መሆኑን ያሳያል። ይህ ፈተና በዋናው ጥናት ላይ ያልቀረበ በመሆኑ ማስተካከያ መስራት አላስፈለገም።

ከላይ በቀረበው ቀመር መሰረት በናሙና ጥናቱ ቅድመ እና ድህረልምምድ አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመፈተሽ የቀረበው ፈተና የእያንዳንዱ ጥያቄ ክብደት ቅለት የተሰላ አሀዝ የሚያመለክተው 0.3 — 0.7 ወሰን ውስጥ በመሆኑ ክብደት ቅለቱ ምክንያታዊ አስተማማኝ ነው ማለት ይቻላል።

ለ. መረጃ ለመሰብሰብ የቀረቡት ፈተናዎቹ የመለየት ብቃት

የፈተና ክብደት ቅለት ማብራርያ ውስጥ የተንፀባረቀው ሀሳብ እንደተጠበቀ ሆኖ የፈተናዎቹ የመለየት ብቃትን ለማረጋገጥ ጥናቱ የተጠቀመበት ቀመር የሚከተለው ገፅታ አለው (Muijs 2004)።



Cohen et al. (2007:144)፣ Muijs (2004:71)

በዚህ ቀመር መሰረት በናሙና ጥናቱ በአማርኛ ቋንቋ ቅድመ እና ድህረልምምድ አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመለካት የቀረበው ፈተና በክብደት ቅለት መደበኛ መስፈርት ሲታይ ጥሩ ቢሆንም የመለየት ብቃቱ ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል። በቅድመልምምድ አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመፈተሽ የቀረበው ፈተና ጥያቄ ቁጥር 1፣2፣3፣4፣5፣6፣7፣10 ድህረልምምድ ጥያቄ ቁጥር 2፣5፣7 ከመደበኛ መስፈርቱ 0.3-0.7 በታች (ከባድ) መሆኑን የተሰላው አሀዝ ያሳያል። በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመለካት የቀረበው ፈተና ክብደት ቅለት ከመደበኛ መስፈርቱ አንፃር ጥሩ እንደሆነ ከላይ የተገለፀ ሲሆን (በ ሀ. ክፍል) የመለየት ብቃት በቀረበው ቀመር መሰረት ቅድመልምምድ ጥያቄ ቁጥር 1፣2፣4፣10 ድህረልምምድ ጥያቄ ቁጥር 1፣2፣3፣4፣5፣6፣7 ከመደበኛ መስፈርቱ በታች መሆኑን ያሳያል። ከዚህ ግብአት በመነሳት ለዋናው ጥናት የቀረበው ፈተና ክብደት ቅለት እና የመለየት ብቃት የተሻለ እንዲሆን ጥረት ተደርጓል።

ሌላው አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመለየት የቀረበው ፈተና እና የማንበብ ብልሃት አጠቃቀምን ለመፈተሽ የተቀረፀው ሚዛናዊ የደረጃ ልኬት የፅሁፍ መጠይቅ አስተማማኝነትን ለማረጋገጥ በ SPSS Version 20 አገልግሎት ላይ ውሏል። በናሙና ጥናቱ አንብቦ መረዳትን ለመለካት የቀረበው ፈተና አስተማማኝነት በአማርኛ ቋንቋ .794 በሶማልኛ ደግሞ .696 Cronbach Alpha መሆኑን ያሳያል። ይህም በሶማልኛ ቋንቋ ወደ 0.7 የተጠጋ ቢሆንም ውስን ማስተካከያ የሚያስፈልግ እንደሆነ አመላክቷል። ሌላው የፅሁፍ መጠይቁ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ሰላሳ አራት ጥያቄዎች የያዘ ነው። በናሙና ጥናቱ የቀረቡት የፅሁፍ መጠይቆቹ በነጠላም ይሁን በድግግሞሽ ለትምህርት የቀረቡትን ሃያ አራት የማንበብ ብልሃት አይነቶች የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች እንዴት እንደተጠቀሙባቸው የሚፈትሹ ናቸው። የመጠይቁን

አስተማማኝነት ለማረጋገጥ በየቋንቋው የቀረቡትን መጠይቆች በጥቅል እና በአምስቱ ንኡሳን የማንበብ ብልሃት ጎራዎች (አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ፣ ትውስታ፣ ማካካስ፣ ማህበራዊ) በመከፋፈል ለማየት ተሞክሯል። በዚህም Cronbach Alpha መደበኛ መስፈርት ከ 0 - 1 ነው።

በመከራ ጥናቱ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀምን ለመፈተሽ የቀረበው ሚዛናዊ የደረጃ ልኬት የፅሁፍ መጠይቅ በአማርኛ በጥቅል (ሰላሳ አራት ጥያቄዎች) Cronbach Alpha .668 ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ የቀረበው በጥቅል (ሰላሳ አራት ጥያቄዎች) .734 ሆኖ ተመዝግቧል። በሁለቱም ቋንቋ የቀረበው የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ በ Cronbach Alpha መደበኛ መስፈርት 0.7 ሲታይ በሶማልኛ ቋንቋ የቀረበው ወደ 1 ይበልጥ የተጠጋ መሆኑን ያሳያል።

የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም አሳሽ የፅሁፍ መጠይቁ በአምስቱ ንኡሳን ጎራዎች ተከፋፍሎ ሲታይ በአማርኛ ቋንቋ አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት .774 (አስራ አምስት ጥያቄዎች) ልእለአእምሮታዊ .701 (ሶስት ጥያቄዎች)፣ ትውስታ .743 (ሶስት ጥያቄዎች) ማካካስ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃቶች .814 (ሁለት ጥያቄዎች) Cronbach Alpha አስተማማኝነት እንዳለው ያሳያል። በዚህ መጠይቅ ከአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት ዝርዝር ውስጥ ማስታወሻ መያዝ ተሻሽሎ Cronbach Alpha ወደ .690፣ ምልክት ማድረግ ተሻሽሎ በ Cronbach Alpha ወደ .702 አድጓል።

በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት .634 (አስራአምስት መጠይቆች)፣ ልእለአዕምሯዊ .679 (ሶስት ጥያቄዎች) ትውስታ .676 (ሶስት ጥያቄዎች)፣ ማካካስ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት .703 (ሁለት ጥያቄዎች) Cronbach Alpha ሆኖ ተመዝግቧል። በዚህ መጠይቅ ከአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት ዝርዝር ውስጥ መተንበይ እና የቀደመ እውቀትን መጠቀም ተሻሽሎ የተመዘገበው Cronbach Alpha ወደ .801 አድጓል፣ መገመት እና በአእምሮ ምስል መፍጠር ደግሞ በ Cronbach Alpha ወደ .702 አድጓል። ከላይ የተዘረዘረው የተሰላ አሀዝ በ Cronbach Alpha መደበኛ መስፈርት መሰረት ሲታይ በአማርኛም ሆነ በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀምን ለመፈተሽ የተቀረፀው ሚዛናዊ የደረጃ ልኬት የፅሁፍ መጠይቅ አስተማማኝነት ጥሩ ቢሆንም ለዋናው ጥናት

የበለጠ መሻሻል እንዳለበት ባመላከተው መሰረት ወደመደበኛ መስፈርቱ እንዲመጣ ጥረት ተደርጓል።

በናሙና ጥናቱ ተሞክሮ መሰረት ማሻሻያ የተደረገባቸው የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች በዋናው ጥናት ተግባራዊ ሆነዋል። በዋናው ጥናት አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመለካት የቀረበው ፈተና በ Cronbach Alpha አስተማማኝነት መለኪያ መደበኛ መስፈርት ሲታይ ቅድመልምምድ የቀረበው ፈተና .69 ሲሆን ድህረልምምድ የቀረበው ፈተና ደግሞ .76 መሆኑን ያመላክታል። ቅድመ እና ድህረልምምድ የተማሪዎችን የማንበብ ብልሃት ለመፈተሽ የቀረበው የፅሁፍ መጠይቅ በ Cronbach Alpha አስተማማኝነት መለኪያ መደበኛ መስፈርት ሲታይ በአማርኛ ቋንቋ የቀረበው .694 በሶማልኛ ቋንቋ የቀረበው .763 መሆኑን ያሳያል። አንብቦ መረዳትን ለመለካት የቀረቡት ፈተናዎች እና የማንበብ ብልሃትን ለመለካት የቀረበው የፅሁፍ መጠይቅ የ Cronbach Alpha መደበኛ መስፈርት 0.7 የተጠጋ እና ከፍ ያሉ በመሆናቸው ምክንያታዊ አስተማማኝነት አላቸው ማለት ይቻላል።

3.2.5 የፈተናዎች የውጤት ስርጭት ወጥነት (ጤናማነት)

በዚህ ጥናት አገልግሎት ላይ የዋሉት ስታትስቲካዊ የመፈተሻ መንገዶች (ቴስቶች) (Testes) አገልግሎት ላይ ከመዋላቸው በፊት በተለያዩ ፈተናዎች የተገኘው ውጤት የውጤት ስርጭት ወጥነት እና የአማካይ ውጤቶች የልይይት መጠን እኩሌታን በማረጋገጥ ፓራሜትራዊ ወይም ኢ-ፓራሜትራዊ የስታትስቲክስ የመፈተሻ መንገዶችን (ቴስቶችን) (Parametric and Non Parametric Test) (ነፃ እና ጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት፣ የልይይት ትንተና፣ ህብረድህረት ተዛምዶ መለኪያ ወዘተ) ለይቶ መጠቀም ተገቢ መሆኑ ታምኗል።

3.2.5.1 አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች ውጤት የውጤት ስርጭት ወጥነት

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ትኩረት ከሰጠባቸው ጉዳዮች አንዱ አንብቦ መረዳት ነው። በጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች ለትምህርት የታሰቡትን የማንበብ ብልሃቶች ከመማራቸው በፊት እና ብልሃቶችን ከተማሩ በኋላ አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው ምን ገፅታ እንዳለው

ተፈትሿል። ቅድመ እና ድህረልምምድ በተሰጡት ፈተናዎች የተገኘውን መረጃ በፓራሜትራዊ ወይም ኢ-ፓራሜትራዊ የስታትስቲክስ የመፈተሻ መንገዶች (ቴስት) ለመተንተን መሚላት ከሚኖርባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ የተገኘውን የውጤት ስርጭት ወጥነት መለየት ተቀዳሚ ተግባር ነው። በዚህ ጥናት ተተኳሪ ተማሪዎች በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ቅድመ እና ድህረልምምድ ያስመዘገቡት ውጤት ወጥ (ጤናማ) ስርጭት (Normal Distribution) ያለው መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የስርጭት ወጥነት ፍተሻ (Test of Normality) ተደርጓል።

በጥናቱ ቅድመልምምድ ሶስቱ ተተኳሪ ቡድኖች (መከራ ቡድን አንድ በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን የተከታተለ፣ መከራ ቡድን ሁለት የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን በሶማልኛ ቋንቋ የተከታተለ እና ጥብቅ ቡድን) ለየቡድኖቹ አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመፈተሽ ከቀረበው ፈተና የተገኘው ውጤት በኮልሞጎሮቭ - ስሚኖቭ ቴስት (Kolmogorov — Smirnov Test / K-S) የተደረገው ስሌት ያመላከተው በአማርኛ ቋንቋ መከራ ቡድን አንድ 0.134 ፣ መከራ ቡድን ሁለት .180 ፣ ጥብቅ ቡድን .174 የስመዘገቡ ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ ደግሞ መከራ ቡድን አንድ .274፣ መከራ ቡድን ሁለት .197 ፣ ጥብቅ ቡድን .193 መሆኑን ያመላክታል። ድህረልምምድ ያለው የውጤት ስርጭት ወጥነት ሲታይ በአማርኛ ቋንቋ መከራ ቡድን አንድ .233፣ መከራ ቡድን ሁለት .277 ፣ ጥብቅ ቡድን .204 ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ ደግሞ መከራ ቡድን አንድ .277፣ መከራ ቡድን ሁለት .231 እና ጥብቅ ቡድን .200 ጉልህነት ውጤቶች የተመዘገበ መሆኑን ፍተሻው ያመላክታል።

በጥናቱ መከራ ቡድን አንድ፣ መከራ ቡድን ሁለት እና ጥብቅ ቡድኖች ቅድመ እና ድህረልምምድ አንብቦመረዳትን ለመለካት የቀረበው ፈተና ውጤት በኮልሞጎሮቭ - ስሚኖቭ ቴስት ተፈትሾ የተገኘው የውጤት ስርጭት ወጥነት አመላካች አሃዝ ከ 0.05 በላይ (>0.05) በመሆኑ ወጥ የውጤት ስርጭት እንዳለ አመላክቷል። በውጤት ስርጭት ወጥነት መፈተሻ ስሌት አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች ውጤት ወጥ (ጤናማ) ስርጭት ማሳየቱ የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ፓራሜትራዊ የስታትስቲክስ መፈተሻ ቴስት (Parametric Test) ለመጠቀም መሚላት ከሚገባቸው ተጠባቂ ግምቶች (እሙኖች) (Assumptions) አንዱ መሚላቱን ያመላክታል።

ሌላው በምርምር ስራ ወቅት መረጃዎችን በፓራሜትራዊ የስታትስቲክስ ስልቶች ለመተንተን መሟላት ካለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ የአማካይ ውጤቶች የልይይት መጠን እኩሌታ ውጤቶችን መፈተሽ ነው። በዚህ ጥናት የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ ከመሰጠቱ በፊት እና ከተሰጠ በኋላ ለመከራ እና ጥብቅ ቡድኖች የተሰጠው አንብቦ የመረዳት ፈተና የአማካይ ውጤቶች የልይይት መጠን እኩልነት በሌቨን የልይይቶች ተመጣጣኝነት መፈተሻ ፈተና (Leven`s Test for Equality of Variance) ተፈትሿል። በዚህም የሌቨን የአማካይ ውጤቶች የልይይት መጠን እኩልነት እንዳመላከተው የመከራ እና የጥብቅ ቡድኖች በአማርኛ ቋንቋ ቅድመልምምድ .143 ድህረልምምድ .197 መሆኑን ያመላከተ ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ ደግሞ ቅድመልምምድ .198 ድህረልምምድ .200 መሆኑን የተሰላው አሃዝ ያሳያል። የሌቨን ፍተሻው ውጤት ከ 0.05 በላይ (>0.05) በመሆኑ በመከራ እና ጥብቅ ቡድኖች ውስጥ ተቀራራቢ የልይይት እኩሌታ እንደሚታይ አመላክቷል (አባሪ ሃያ አንድን ይመለከቷል)።

3.2.5.2 የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቆች የውጤት ስርጭት ወጥነት

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ቅድመ እና ድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት በተግባር የመጠቀም ብቃትን ለመለካት በየቋንቋው የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ ቀርቧል። የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቁ ለመከራ ቡድኖቹ ብቻ የቀረበ ነው። በጥናቱ የቀረበው የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ በናሙና ጥናቱ (Pilot Study) የተገኘውን ተሞክሮ እንደግብአት በመጠቀም ተሻሽሎ የቀረበ ነው። ይህ የፅሁፍ መጠይቅ ተጨማሪ የተገቢነት እና የአስተማማኝነት ፍተሻ ተካሂዶበታል። በዚህም መሰረት ተሻሽሎ የቀረበው ይህ የፅሁፍ መጠይቅ በክሮምባች አልፋ በአማርኛ ቋንቋ .794 በሳማልኛ ቋንቋ .714 ምክንያታዊ አስተማማኝነት እንዳለው ለማወቅ ተችሏል።

በጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች ቅድመ እና ድህረልምምድ በቀረበላቸው አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ ተሰልቶ ሲታይ የውጤት ስርጭት ወጥነት ያለው መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ፍተሻ ተካሂዷል። የውጤት ስርጭት ወጥነት መፈተሻ አንደኛው መንገድ የኮልሞጎሮቭ - ስሚኖቭ ቴስት ነው። በጥናቱ ለመከራ ቡድን አንድ እና ለመከራ ቡድን ሁለት (ለየቡብኖቹ) ቅድመልምምድ በፅሁፍ መጠይቁ የተገኘው የውጤት ስርጭት ወጥነት ለማረጋገጥ በኮልሞጎሮቭ - ስሚኖቭ የተደረገው ስሌት ያመላከተው በአማርኛ ቋንቋ መከራ ቡድን ሁለት ካስመዘገበው .079 በስተቀር ሁለቱም

የሙከራ ቡድኖች በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ .200 የውጤት ስርጭት ወጥነት እንዳላቸው የተሰላው አሀዝ አመላክቷል። የተሰላው አሀዝ ከ 0.05 በላይ (> 0.05) በላይ በመሆኑ በፅሁፍ መጠይቁ የተገኘው ውጤት ስርጭት ወጥ መሆኑን አመላክቷል (አባሪ ሃያ ስድስትን ይመለከቷል)። ከዚህ በተጨማሪ ለጠቅላላ ውጤቱ በተያይዝ አምድ ግራፍ በተደረገው ፍተሻ የውጤት ስርጭት ወጥነት እንዳለው ታይቷል። ከላይ የቀረበው የውጤት ወጥነት ስርጭት የሚጠበቀው መስፈርት ማሟላቱን ያመላከተ በመሆኑ በጥናቱ የተነሱትን ጥያቄዎች ለመመለስ ፓራሜትራዊ መፈተሻዎችን ለመጠቀም መሟላት ያለበትን አንዱን ተጠባቂ ግምት ወይም እሙን እንዳሟላ ያመላክታል።

በጥናቱ ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በቀረበው የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ አማካኝነት ከተተኳሪ ተማሪዎች የተገኘው የአማካይ ውጤት የልይይት መጠን እኩል ስለመሆኑ የሌቪን የልይይቶች ተመጣጣኝነት መፈተሻ መንገድ ተፈትሿል። በዚህም የተገኘው ውጤት ያመላከተው በሁለቱም ቡድኖች በጥቅል በአማርኛ ቋንቋ ቅድመልምምድ .751 ድህረልምምድ .606 ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ ደግሞ ቅድመልምምድ .580 ድህረልምምድ .642 መሆኑን ያሳያል። በሌቪን መፈተሻ መንገድ የተሰላው የአማካይ ውጤቶች የልይይት መጠን ከ0.05 በላይ (> 0.05) በመሆኑ በሙከራ ቡድኖቹ ተቀራራቢ የልይይት እኩሌታ እንደሚታይ አመላክቷል።

በአጠቃላይ ቅድመ እና ድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቁ የመረጃ ስርጭት ወጥነት እና የልይይት እኩሌታ ውጤቶች ከ 0.05 በላይ (> 0.05) ሆነው መመዝገባቸው በጥናቱ የቀረቡትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ በተለያ መንገድ የተገኘው መረጃ በፓራሜትራዊ የስታትስቲክስ ስልቶች መተንተን እንደሚችል ተረጋግጧል (አባሪ ሃያ ስድስትን ይመለከቷል)።

3.2.6 በጥናቱ ለትምህርት የቀረቡ የማንበብ ብልሃቶች አመራረጥ

ጥናቱ በዋናነት ትኩረት ያደረገው አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ፣ ትውስታ፣ ማካካስ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃቶች ላይ ነው። ከነዚህ ንኡሳን የማንበብ ብልሃቶች ውስጥ በማንበብ ሂደት የበለጠ ጠቃሚ ናቸው በሚል እና የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎችን የክፍል ደረጃ ባገናዘበ መልኩ አስራስድስት የማንበብ ብልሃቶች (መተንበይ፣ ደግሞ (ደጋግሞ)

ማንበብ፣ ዋናውን ሀሳብ በፍጥነት ማግኘት፣ መረጃን ፈልፍሎ ማውጣት፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ሀሳብን በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ፣ ማሸጋገር፣ አዳዲስ ቃላትን ለመረዳት አውዳዊ ፍቺ መጠቀም፣ የቀደመ እውቀትን መጠቀም፣ በአእምሮ ምስል መፍጠር፣ መገመት፣ ማቀድ፣ መቆጣጠር፣ ራስን መገምገም፣ መጠየቅ እና ከሌሎች ጋር መተባበር ለትምህርት ቀርበዋል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የማንበብ ብልሃቶች የተመረጡበት ምክንያት ለመጀመሪያ እና ሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ በጣም ጠቃሚ እና ታዋቂ በመሆናቸው፣ አቀናጅቶ ለማስተማር አመቺ በመሆናቸው፣ ከተሰጠው ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ምን ያህል በተግባር እንደተጠቀሙባቸው ለማወቅ የሚለኩ በመሆናቸው፣ ከአንድ ሁኔታ ወደሌላ አዲስ ሁኔታ ወይም ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ በማሸጋገር ለመጠቀም የሚያስችሉ በመሆናቸው፣ በምርምር የተደገፉ እና እጅግ ታዋቂ በመሆናቸው ነው። በዚህ ጥናት ከስሜት ጋር የሚያያዙ ብልሃቶች (Affective Strategies) ያልተካተቱበት ምክንያት ብልሃቶቹ አገልግሎታቸው በአብዛኛው ለተግባቦታዊ መስተጋብር በተለይ ለንግግር ክሂል የሚያገለግሉ በመሆናቸው ነው (Oxford 1990፣O`Malley and Chamot 1990)።

3.2.7 በጥናቱ የማስተማሪያ ፅሁፎች አዘገጃጀት

ሀ. የማንበብ ብልሃትን ለማስተማር የተዘጋጁት ፅሁፎች አዘገጃጀት

የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ለማስተማር አላማ በጥናቱ አቅራቢ የተዘጋጀው ፅሁፍ መሰረቱ በምእራፍ ሁለት ውስጥ የተንፀባረቀው ንድፈሀሳባዊ ማእቀፍ ነው። የማንበብ ብልሃትን ለማስተማር የተዘጋጀው ማስተማሪያ ፅሁፍ በአምስት ንኡሳን ብልሃቶች ውስጥ የሚካተቱትን አስራስድስት የማንበብ ብልሃቶች ለማስተማር አላማ የተዘጋጀ ነው።

የማንበብ ብልሃትን ለማስተማር የተዘጋጀው ፅሁፍ የማንበብ ብልሃትን ምንነት (ብያኔ)፣ ጠቀሜታ፣ አይነቶች እንዲሁም ተማሪዎች ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዴት እና መቼ መጠቀም እንዳለባቸው የሚያመላክቱ ጠቃሚ ቅደም ተከተሎችን አካቷል። ለምሳሌ ተማሪዎች የቀረበን ፅሁፍ ዋና ሀሳብ በፍጥነት ማግኘት

የተባለው የማንበብ ብልሃት ምንነት፣ ብልሃቱን እንዴት እና መቼ መጠቀም እንዳለባቸው በሚከተለው መንገድ ቀርቧል፡፡

ዋናውን ሀሳብ በፍጥነት ማግኘት፡- አንድን የቀረበ ፅሁፍ ዋና ሀሳብ በፍጥነት ማግኘት የማንበብ ብልሃት የሚባለው በገረፍታ እና በፍጥነት በማንበብ የፅሁፉን ዋና ሀሳብ መዞ ለማውጣት የሚያስችል ነው፡፡ ተማሪዎች በገረፍታ በሚያነቡበት ጊዜ ፅሁፉን በፍጥነት በማየት የተለየ (የተነጠለ) መረጃ ለማግኘት (ለምሳሌ እውነታዎች፣ ቁጥሮች፣ቁልፍ ቃላት እና ሀረጎችን መለየት) መጣር ነው፡፡ ይህንን ተግባር ለማከናወን ተማሪዎች በውህድአሀድ ውስጥ ባሉት በእያንዳንዱ ቃላት ላይ ያላቸውን ትኩረት በመቀነስ በውህአሀዱ ላይ አይናቸውን በፍጥነት እያንቀሳቀሱ እንዲያነቡ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች የሚፈልጉትን መረጃ በሚያገኙበት ወቅት ፍጥነታቸውን በመቀነስ ወይም በቆምታ አረፍተነገሩን በዝርዝር አንብበው የሚፈልጉትን መረጃ እንዲለዩ ማድረግ ነው፡፡ ተማሪዎች ይህንን የማንበብ ብልሃት የሚጠቀሙት በማንበብ ወቅት(While-Reading) ነው፡፡

የማንበብ ብልሃት ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ ለልምምድ ያገለገሉት ምንባቦች በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ከተዘጋጁት መማሪያ ማስተማሪያ መፅሀፎች ውስጥ ካሉ ምንባቦች የተመረጡ ናቸው፡፡ ለጥናቱ አላማ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ የተሰጠው ሁለተኛው መንፈቀ አመት (Second Semester) በመሆኑ ለማንበብ ተግባር ያገለገሉት ምንባቦችም ለሁለተኛው መንፈቀ አመት ታስበው የተዘጋጁቱ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በጥናቱ ከተለያዩ ምንጮች (ከመፅሀፍ፣ ከመፅሄት፣ ከጋዜጣ) የተገኙ ፅሁፎች ትምህርቱን ለማጠናከር አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡

በጥናቱ ቅድመ እና ድህረልምምድ በሁለቱም ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመለካት የተዘጋጁት ፈተናዎች፣ በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ ለመናገር ቃለ መጠይቅ ያገለገሉት ምንባቦች በመማሪያ ማስተማሪያ መፅሐፎቹ ውስጥ ካሉት ምንባቦች ጋር ተመሳሳይ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይኸውም በርዝመት (በ250-300ቃላት)፣ በዘውግ፣ በግልፅነት፣ በይዘት ክብደት፣ በቋንቋ አጠቃቀም ወዘተ ተመሳሳይ እንዲሆኑ እና ፅሁፎቹ ተራኪ፣ ገላጭ እና መረጃ ሰጪ እንዲሆኑ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ምንባቦቹ በዚህ መልክ የተዘጋጁበት ምክንያት በመማሪያ ማስተማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ከቀረቡት በተለየ መንገድ እንግዳ (አዲስ) የሆነ አቀራረብ እንዳይከሰት በማሰብ ነው፡፡

ዕሁፎቹን ከተለያዩ ምንጮች (ከመዕሀፍ፣ ከመዕሄት፣ ከጋዜጣ) በመውሰድ ለክፍል ደረጃው በተቀረፀው መርሀትምህርት እና በመማሪያ ማስተማሪያ መዕሀፎቹ ውስጥ በተቀመጠው አላማ መሰረት እንዲሁም Nuttall (1996) ባስቀመጡት መስፈርት መሰረት ለጥናቱ በሚያመች መንገድ የተዘጋጁ ናቸው። ምንባቦቹ ሲዘጋጁ በዋናነት የተማሪዎቹን የክፍል ደረጃ ግምት ለማስገባት ጥረት ተደርጓል። በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡትን ዕሁፎች የጥናቱ አቅራቢ ያዘጋጃቸው ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ የቀረቡትን በጥናቱ የተሳተፉት መምህርት አዘጋጅተውታል (ከአባሪ አራት እስከ አስራ ሰባት ያለውን ይመለከቱዋል)።

3.2.8 የማንበብ ብልሃት ትምህርት አሰጣጥ

አንድን የቀረበ ውህድአሀድ አንብቦ ለመረዳት ተማሪዎች ስለ ማንበብ ብልሃት ባላቸው እውቅት (ግንዛቤ) ልክ ሆንብለው ወይም ሳያስቡት ወይም ሁለቱንም አጣምረው በመጠቀም ተግባራዊ ሊያደርጉ ይችላሉ። ውጤታማ፣ ተገቢ እና ብቁ የማንበብ ብልሃቶችን መርጦ እና አቀናጅቶ በመጠቀም የቀረበውን ውህድአሀድ ለመረዳት ጥረት ማድረግ የተማሪዎች ድርሻ ነው። ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ሆንሳይሉ (ሳያስቡት) ወይም በተፈጥሮ ያገኙትን ብልሃት በግምት እና ኢላማ ቢስ በሆነ መልኩ ሊጠቀሙ ይችላሉ። ነገር ግን ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ምንነት እና አጠቃቀም በሚገባ ባወቁ (በተማሩ) ጊዜ ሳያስቡት ከመጠቀም ውጤታማ በሆነ መንገድ ሆን ብለው ወደመጠቀም ይሸጋገራሉ።

በዚህ ጥናታዊ ዕሁፍ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ ለመከራ ቡድኖች በሚሰጥበት ወቅት ተግባራዊ የሆነው የማስተማርያ ሞዴል መምህር በነፃ ማሰብ፣ አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ እና ትግግዝ ሞዴልን በማቀናጀት ነው።

በምእራፍ ሁለት እንደተገለፀው የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ ሲቀርብ ተግባራዊ የተደረገው ቅደም ተከተል በዋናነት አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ ሞዴል (CALLA) ያስቀመጠውን ቅደም ተከተል በመከተል ነው። ይኸውም **ዝግጅት፣ ሞዴል በመሆን አቅርቦት፣ ልምምድ፣ ራስን መገምገም ፣ማስፋፋት እና ምዘናን** ያካተተ ሲሆን ተማሪዎች በማንበብ ሂደት የተገነዘቡትን የሚገልፁበት (**ፅብረቃ**) እና **የሀሳብ መደጋገፍ (ትግግዝ)** ክንውኖችም በቅደምተከተሉ ተካተዋል። በጥናቱ የተጠቀሱት

ስድስቱ የትምህርት አቀራረብ ቅደምተከተሎች የሚከተሉትን ዝርዝር ነጥቦች (ክንውኖች) አካተዋል፡፡

- ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት ግንዛቤ ያላቸው መሆን አለመሆኑን ጥያቄ በመጠየቅ ማረጋገጥ እና ለትምህርት ማነሳሳት፣
- የማንበብ ብልሃት ምንነትን እና ጠቀሜታን ማስረዳት፣
- የማንበብ ብልሃት አይነቶችን በዝርዝር ማቅረብ፣
- በክፍል ውስጥ አነስተኛ ቡድኖች እያደራጁ ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ ማበረታታት፣
- መምህር ሞዴል በመሆን የማንበብ ብልሃቶችን በተግባር ማለማመድ እና በተግባር እንዲጠቀሙባቸው ማድረግ
- የማንበብ ብልሃቶችን አቀናጅተው እንዲጠቀሙ ማበረታታት፣
- በትግግዝ ድጋፍ የማንበብ ብልሃቶችን ተግባራዊ በማድረግ ደጋግመው እንዲለማመዱ ማድረግ፣
- የተለያዩ ፅሁፎችን በማቅረብ የማንበብ ብልሃቶችን ተግባራዊ አድርገው በተረዱት ዙርያ እንዲወያዩ እድል መስጠት፣
- የማንበብ ብልሃቶችን ወደአዲስ ተግባር (ሁኔታ) ወይም ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ ሽግግር እንዲያደርጉ ማስተማር
- የእገዛ ድጋፍን ቀስበቀስ መቀነስ እና ሀላፊነቱን ለተማሪዎች መስጠት
- የማንበብ ብልሃቶችን አቀናጅተው እና ደጋግመው በተገቢው መንገድ በመጠቀም አንብበው መረዳት አለመረዳታቸውን በመከታተል ራሳቸውን እንዲገመግሙ ማበረታታት
- በማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና አንብቦ መረዳት ውጤታማነታቸውን መፈተሽ፣
- በመጨረሻ የማንበብ ብልሃቶችን በራሳቸው መንገድ በመጠቀም ነፃ እና ራስመር አንባቢ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡

ከላይ በቀረበው ቅደም ተከተል መሰረት ትምህርቱ ለሙከራ ቡድን አንድ በአማርኛ ቋንቋ ለሙከራ ቡድን ሁለት ደግሞ በሶማልኛ ቋንቋ ቀርቧል፡፡ በአማርኛም ሆነ በሶማልኛ ቋንቋ ለትምህርት የቀረቡትን የማንበብ ብልሃቶች ለማስተማር በሚያመች መልኩ በመከፋፈል ምንነታቸውን፣ ጠቀሜታቸውን እና አገልግሎታቸውን በዝርዝር

በማስረዳት ተማሪዎች ውጤታማ በሆነ መልኩ በተግባር እንዲጠቀሙባቸው ለማድረግ ተሞክሯል።

ለጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች ትምህርቱ በሚከተለው መርሀግብር መሰረት ተሰጥቷል። በጥናቱ ሙከራ ቡድን አንድ፣ ሙከራ ቡድን ሁለት እና ጥብቅ ቡድን ተብለው በተመረጡት ክፍሎች መካከል በየቋንቋው አንብቦ የመረዳት ብቃት መበላለጥ መኖር አለመኖሩን ለማወቅ በመጀመሪያ ሳምንት የካቲት 6/2009 ዓ.ም ቅድመልምምድ አንብቦ የመረዳት ብቃት መለክያ ፈተና በሁለቱም ቋንቋ ተሰጥቷል። በሚቀጥለው የካቲት 10/2009 ዓ.ም በጥብቅ ቡድኖቹ መካከል የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ ቀርቧል። በተማሪዎቹ መካከል አንብቦ የመረዳት ውጤትም ሆነ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤ ልዩነት ባለመኖሩ ከቀጣይ ሳምንት ጀምሮ ትምርቱ መሰጠት ተጀምሯል።

ትምህርት የተጀመረበት **ሁለተኛው ሳምንት** ከየካቲት 13/2009 - የካቲት 17/2009 ዓ.ም ለሁለት ክፍለ ጊዜያት ተማሪዎች ስለማንበብ ብልሃት ምን እንደሚያውቁ በመጠየቅ እና ለትምህርቱ በማነሳሳት የማንበብ ብልሃት ምንነትን፣ አይነታቸውን እና ጠቀሜታቸውን በዝርዝር እንዲገነዘቡ ተደርጓል (አባሪ አስራሰባትን ይመለከቷል)። በመቀጠል **ሶስተኛው ሳምንት** የካቲት 20/2009 - የካቲት 24/2009 ዓ.ም ለሁለት ክፍለ ጊዜ መተንበይ እና ዋናውን ሀሳብ በፍጥነት ማግኘት የማንበብ ብልሃቶችን በማቅረብ በተግባር እንዲለማመዱባቸው ተደርጓል። **በአራተኛው ሳምንት** ከየካቲት 27/2009 - ግንቦት 27/2009 ዓ.ም ለሁለት ክፍለ ጊዜ ማቀድ እና መረጃን ፈልፍሎ ማውጣት የተባሉትን የማንበብ ብልሃቶች በዝርዝር በማቅረብ በተግባር እንዲጠቀሙባቸው ተደርጓል። **በአምስተኛው ሳምንት** መጋቢት 4/2009 - መጋቢት 8/2009 ዓ.ም ለሁለት ክፍለ ጊዜያት ማስታወሻ መያዝ እና ደግሞ (ደጋግሞ) ማንበብ የተባሉትን የማንበብ ብልሃቶች በዝርዝር በማቅረብ በተግባር እንዲለማመዱባቸው ተደርጓል። **በስድስተኛው ሳምንት** መጋቢት 11/2009 — መጋቢት 15/2009 ዓ.ም ለሁለት ክፍለ ጊዜ ጭምቀሀሳብ መፃፍ እና ጥያቄ መጠየቅ የተባሉት ብልሃቶችን ተማሪዎች በተግባር እንዲጠቀሙባቸው ጥረት ተደርጓል። **በሰባተኛው ሳምንት** መጋቢት 18/2009 - መጋቢት 22/2009 ዓ.ም ለሁለት ክፍለ ጊዜ የቀደመ እውቀትን መጠቀም እና ራስን እና አንብቦ መረዳትን መቆጣጠር የተባሉትን የማንበብ ብልሃቶች በዝርዝር በማቅረብ

ተማሪዎች በተግባር እንዲለማመዱባቸው ተደርጓል። **ስምንተኛ ሳምንት** መጋቢት 25/2009 — 29/2009 ዓ.ም ለሁለት ክፍለ ጊዜያት አውድ መጠቀም እና መገመት የተባሉት የማንበብ ብልሃቶች በዝርዝር ቀርበው ተማሪዎች በተግባር እንዲለማመዱባቸው ተደርጓል። **ዘጠነኛ ሳምንት** ሚያዝያ 2/2009 - ሚያዝያ 6/2009 ዓ.ም ራስን መገምገም እና ብልሃቶችን እያሸጋገሩ መጠቀም የተባሉ ብልሃቶች በዝርዝር ቀርበው ተማሪዎች በተግባር እንዲለማመዱባቸው ተደርጓል። **አስረኛ ሳምንት** ከሚያዝያ 9/2009 - ሚያዝያ 13/2009 ዓ.ም በአእምሮ ምስል መፍጠር እና ከሌሎች ጋር መተባበር የተባሉ ብልሃቶች በዝርዝር ቀርበው ተማሪዎች በተግባር እንዲለማመዱባቸው ተደርጓል። **አስራአንደኛ ሳምንት** ከሚያዝያ 16/2009- ሚያዝያ 20/2009 ዓ.ም አጠቃላይ የልምምድ ወቅት ሆኖ ተግባራዊ ተደርጓል። **አስራሁለተኛ ሳምንት** ከሚያዚያ 24- ሚያዝያ - 302009 ዓ.ም ድህረልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና፣ የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ እና በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ የመናገር ቃለ መጠይቅ ቀርቧል።

በጥናቱ የማንበብ ብልሃቶችን ለማስተማር እንዲያመች ለትምህርት የተመረጡት የማንበብ ብልሃቶች ተከፋፍለው የቀረቡ ቢሆንም ብልሃቶችን አቀናጅቶ ማስተማር እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ አንድን ብልሃት ለማስተማር በታቀደ የትምህርት መርሀግብር ሌለኛው ብልሃት መነሳቱ አልቀረም።

የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ በሚቀርብበት ጊዜ ተማሪዎች በአነስተኛ ቡድን እየተደራጁ ለማንበብ ተግባር የቀረቡ ምንባቦችን አንብበዋል፣ በሀሳቦቹ ዙርያ ተወያይተዋል፣ ያልገባቸውን በመጠየቅ ርስበርስ በትብብር ሀሳቡን ለመረዳት ጥረት አድርገዋል። በዚህ ወቅት መምህርት ገለፃ በመስጠት፣ ሞዴል በመሆን አጠር ያሉ ምንባቦችን በማንበብ (ምንባቦቹ ከመፅሀፍ፣ ከመፅሄት፣ከጋዜጣ ወዘተ የተገኙ ናቸው)፣ ቡድኖችን በማደራጀት እና በማንበብ ወቅት በክፍል ውስጥ እየተዘዋወሩ ችግሮችን ለመፍታት እና የመማር ማስተማር ሂደቱን ምቹ ለማድረግ ተግተዋል።

3.2.9 የጥናቱ አሰራር እና የመረጃ አሰባሰብ ቅደም ተከተል

ጥናታዊ ፅሁፍ አቅራቢው ስራውን ከመጀመሩ በፊት ስለምርምር ስራው በናሙናነት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ካሉ ርእሳነ መምህራን ጋር ሰፊ ውይይት በማድረግ

በመረጃ አሰባሰቡ ሂደት ተባባሪ እዲሆኑ ጥረት አድርጓል። በመቀጠል ምርምር አቅራቢው ከርእሳነ መምህራኑ ጋር በመሆን በምርምሩ የተሳተፉ ተማሪዎችን ስለምርምር ስራው ማስረዳት እና ተባባሪ እንዲሆኑ ማበረታታት፣ በምርምሩ የተሳተፉትን መምህርት ፈቃደኛ እንዲሆኑ ማድረግ እና የማንበብ ብልሃትን እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ስልጠና ሰጥቷል።

ጥናታዊ ፅሁፍ አቅራቢው በምርምሩ ለተሳተፉት መምህርት የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር ላይ የተመሰረተ የስልጠና ማንዋል በማዘጋጀት በታቀደ መርሀግብር ገለፃ እና ስልጠና ሰጥቷል (አባሪ ሶስትን ይመለከቱዋል)።

በመቀጠል በናሙናነት የተመረጡትን ክፍሎች በማዘጋጀት ለሙከራ ቡድኖቹ የማንበብ ብልሃት ትምህርት ከመስጠጥት አስቀድሞ የመጀመሪያ ክፍለ ፈተና (Session) በማዘጋጀት (ሁለት ክፍለጊዜ) በሙከራ እና ጥብቅ ቡድን ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ያላቸው አንብቦ የመረዳት ብቃት እኩል ደረጃ ላይ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቅድመልምምድ ፈተና እና የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ በየቋንቋው ቀርቧል። የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ ለአስራ ሁለት ሳምንት (16 ሰዓት / 960 ደቂቃ) ከተሰጠ በኋላም ድህረልምምድ ምዘናው በሁለቱም ቋንቋ ቀርቧል። ይህም የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ ከተሰጠ በኋላ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ከማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና አንብቦ መረዳት አኳያ ያላቸው ለውጥ ምን እንደሚመስል ለመረዳት ታስቦ የቀረበ ነው። በተጨማሪ በሙከራ ቡድን ውስጥ ካሉ ተማሪዎች የተወሰኑትን ፈቃደኛ የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት በቅድመ እና ድህረልምምድ ወቅት በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ የመናገር ቃለ መጠይቅ በተማሪዎች ፍላጎት በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ቀርቧል።

በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ መናገር ቃለ መጠይቅ ለሙከራ ቡድኖቹ በሚቀርብበት ጊዜ በመጀመሪያ በፅሁፍ የተዘጋጀ መመሪያ በመስጠት ተማሪዎቹ እንዲዘጋጁ ተደርጓል። በቃለመጠይቁ የቀረበው መመሪያ ያመላከተው ቃለመጠይቁ ለማንበብ ተግባር በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሰረተ እንደሆ፣ ፅሁፉን አንብበው መረዳት አለመረዳታቸውን መጠየቅ፣ ፅሁፉን ለማንበብ የተጠቀሙባቸውን የማንበብ ብልሃቶች እንዲገልፁ ማድረግ፣ በማንበብ ሂደት ፅሁፉን ለመረዳት ከተቸገሩ ችግራቸውን ለማስወገድ ምን እንዳደረጉ እንዲገልጡ የሚያስችል ነው (አባሪ ዘጠኝን

ይመለከታል)። በዚህ መረጃ የመሰብሰብ ሒደት ለተሳታፊዎች የዝግጅት፣ የትግበራ፣ የማሰብ እና ሀሳብን የማንፀባረቅ እንዲሁም የቃለመጠይቅ ክፍለ ጊዜ ተዘጋጅቷል። መጠይቁም በሁለት ጉዳዮች ላይ አተኩሯል። አንደኛው ትኩረት በቀረበው ፅሁፍ ይዘት ላይ ሲሆን ፅሁፉን ምን ያህል እንደተረዱት የሚያሳይ ነው። ሁለተኛው ውህድአሀዱን ለማንበብ የተጠቀሙበት የማንበብ ብልሃት ምን እንደሆነ መረጃ ማግኘት ነው።

በመቀጠል ለዚህ አላማ የተዘጋጀውን ምንባብ በማደል የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በየግላቸው እንዲያነቡ ተደርጓል። ለማንበብ ተግባር የተሰጠውን ውህድአሀድ በሚያነቡበት ወቅት የጥናቱ አቅራቢ እና ቃለመጠይቁን ያቀረቡት መምህርቷ ምልከታ አካሂደዋል። ይህም ተማሪዎች በነፃነት እንዲያነቡ ለማበረታታት እና በመመሪያው መሰረት ክንውኑን እንዲተገብሩ ለማድረግ በማሰብ ነው። መጠይቁ የቀረበው የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ምንባብ እንደጨረሱ አንድ በአንድ የማንበብ ሒደታቸውን እና እንዴት የማንበብ ብልሃቶችን እንደተጠቀሙ በመጠየቅ ነው። የተሳታፊዎች በፍጥነት መመለስ ዋና ጉዳይ አይደለም። ቃለመጠይቁ በመቅረፀ ድምፅ ተቀርፆ ወደፅሁፍ ከተገለበጠ (Transcribe) በኋላ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆነው መረጃ አገልግሎት ላይ ውሏል።

3.2.10 የመረጃ አተናተን

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ቅድመ እና ድህረልምምድ ፈተና በመስጠት የተገኘው አሀዛዊ መረጃ በ " SPSS Version 20" ተሰልቷል። የተሰላው አሀዛዊ መረጃ ትርጉም ሊሰጥ በሚችል መልኩ በገላጭ አቀራረብ ዘዴ በዝርዝር ተተንትኖ ቀርቧል። በጥናቱ በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ የመናገር ቃለመጠይቅ የተገኘውን መረጃ አሀዛዊ መልክ እንዲይዝ በማድረግ ትንታኔ ተሰጥቶበታል። በተለያየ መንገድ የተሰበሰበው መረጃ ለአተናተን እንዲያመች በጥናታዊ ፅሁፉ ውስጥ በተንፀባረቁት መሰረታዊ ጥያቄዎች መሰረት ትንተናው ቀርቧል። የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር

- የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እንዲጎለብት ምን ያህን እስችሏል?

- አንብቦ የመረዳት ውጤት እንዲጎለብት ምን ያህል አስተዋፆ አለው?
- የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር አዎንታዊ ዝምድና እንዲኖር ምን ያህል አስችሏል ?
- የማንበብ ብልሃትን ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ያለ ሽግግር እንዲጎለብት ምን ያህል አስተዋፆ አድርጓል?
- ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ያለ የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ውጤት እንዲጎለብት ምን ያህል አዎንታዊ ድርሻ አለው?

በአንድ የምርምር ስራ ውስጥ ነፃ እና ጥንድ ናሙና ቲ-ቴስትን (Independent and paired sample t-test) ለመጠቀም የሚያስፈልጉ ተጠባቂ ግምቶች (እሙኖች) (Assumption) አሉ። እነሱም ሁለት ተነፃፃሪ ቡድኖች መኖር፣ ከተነፃፃሪ ቡድኖች አንዱ ነፃ እና አንድ ጥገኛ ተላውጦዎች መኖር አለባቸው። በተጨማሪ ጥገኛ ተላውጦው የግድ ቀጣይ ልኬታ (Continuous/ Scale) መሆን አለበት (Muijs 2004,Pallant 2001) ። በመሆኑም በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ እነዚህ ተጠባቂ እሙኖች ተሟልተው የተገኙ በመሆናቸው የምርምሩን የመጀመሪያ ጥያቄ ለመመለስ ነፃ እና ጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ጥቅም ላይ ውሏል። በጥናቱ የተሳተፉት ሁለቱ የሙከራ ቡድኖች የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እውቀት ያላቸው መሆን አለመሆኑን ለመፈተሽ፣ በቡድኖቹ መካከል የአጠቃቀም ልዩነት (የአጠቃቀም እውቀት ልዩነት) ያለ መሆን አለመሆኑን ለመፈተሽ ነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ያገለገለ ሲሆን የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ ከተሰጠ በኋላ ያመጡት የባህሪ ለውጥ ምን እንደሚመስል ለማየት ጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት አገልግሎት ላይ ውሏል። በመቀጠልም ሁለቱ የሙከራ ቡድኖች ከልምምዱ በኋላ ያሳዩትን ለውጥ ለማነፃፀር ነፃ ናሙና ቲ-ቴስት አገልግሎት ላይ ውሏል።

በጥናቱ ሁለተኛ ጥያቄ መሰረት ጥብቅ ቡድኑ እና ሁለቱ የሙከራ ቡድኖች በየቋንቋው አንብቦ የመረዳት ብቃታቸውን ለመለካት ጥረት ተደርጓል። በሂደቱ መጀመሪያ እያንዳንዱ ቡድን ቅድመ እና ድህረልምምድ አንብቦ የመረዳት ብቃት ምን እንደሚመስል በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ታይቷል። በመቀጠል ሶስቱን ቡድኖች ለማነፃፀር የልይይት ትንተና (Analysis of Variance/ANOVA) አገልግሎት ላይ ውሏል። የልይይት ትንተና ለመጠቀም ተጠባቂ እሙኖቹ ከሁለት በላይ ተነፃፃሪ ቡድኖች መኖር፣ የቡድኖቹ ንፅፅር

እያንዳንዱን ቡድን በተናጠል (ለምሳሌ ሀ ቡድን፣ ለ ቡድን፣ ሐ ቡድን) ሊሆን ይችላል፤ ወይም ሁለት ቡድኖች ከአንድ ቡድን ጋር (ለምሳሌ ቡድን ሀ እና ለ ቡድንን ከ ሐ ቡድን ጋር ማነፃፀር) ። የቡድኖችን አማካይ ለማነፃፀር ጥገኛ ተላውጦው ቀጣይ (Continuous/ Scale) ወይም ደረጃዊ (Ordinal) ከብዙ ክፍልፋዮች ጋር (With many Categores) መሆን አለበት። በአንፃሩ ነፃ ተላውጦው ስያሜያዊ (Nominal) ወይም ደረጃዊ (Ordinal) ልኬታ ሊኖር ይገባል። ይህ ጥናትዊ ፅሁፍም ተጠባቂ እሙኖችን ያሟላ በመሆኑ የልይይት ትንተናን ተግባራዊ አድርጓል።

የጥናቱ ሶስተኛ ጥያቄ ያተኮረው በየቋንቋው የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና አንብቦ መረዳት ብቃት (ውጤት) ያላቸው ዝምድና ወይም የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም በአንብቦ መረዳት ላይ ያለው ተፅእኖ ምን እንደሚመስል መመርመር ነው። በጥናቱ ትኩረት የተሰጠባቸው የማንበብ ብልሃቶች ከሁለት በላይ በመሆናቸው የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም እና አንብቦ የመረዳት ብቃት (ውጤት) ያላቸውን ዝምድና ለማየት ህብረድህረት (Multiple Linear Regression) ጥቅም ላይ ውሏል። ትናቱ ህብረድህረትን ለመጠቀም መሟላት የሚገባቸውን ተጠባቂ ግምቶችን (እሙኖችን) ፈትሿል (ዝርዝሩን በአባሪ ሃያ ስድስት ይመለከቷል)።

የጥናቱ አራተኛ እና አምስተኛ ጥያቄዎች ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ምን ያህል ተተኳሪ ተማሪዎች በድግግሞሽ የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ እንደተጠቀሙ ማየት እና የማንበብ ብልሃቶችን ከአንዱ ቋንቋ ወደሌላው ቋንቋ እያሸጋገሩ በመጠቀማቸው አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው መጎልበት አለመጎልበቱን መፈተሽ ነው። ይህን ለማየት ጥናቱ ድግግሞሽ (Frecquency) እና መቶኛ ስሌትን ተግባር ላይ አውሏል። ከዚሁ በተጨማሪ በጥናቱ በነፃ ማሰብ እና ያሰቡትን ማንፀባረቅ ቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ ወደአሃዝ ስሌት ተቀይሮ ሰፊ ትንታኔ ተሰጥቶበታል። በዚህም በተማሪዎች አእምሮ ውስጥ የሚመላለሰውን ረቂቅ ሀሳብ ተጨባጭ እና እንዲለካ በማድረግ ለመቆጣጠር ተሞክሯል።

ምዕራፍ አራት

የናሙና ጥናት (Pilot Study)

ከላይ በቀረቡት ምእራፎች እንደተገለፀው ጥናታዊ ፅሁፉ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ውጤት መጎልበት እና ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ያለው አስተዋፆ ምን እንደሚመስል በጥልቀት መመርመር ላይ ያተኮረ ነው። ጥናቱ የተነሳበትን አላማ ለማሳካት እንዲያስችለው የናሙና ጥናት አካሒዷል። የናሙና ጥናቱ ዋና አላማ ለዋናው ጥናት የተቀረፁትን መሰረታዊ ጥቄዎች ለመመለስ የተሰናዱ የመረጃ መሰብሰብያ መሳርያዎች፣ የጥናቱ አሰራር ቅደም ተከተሎች፣ የመረጃ አተናተኖች በአጠቃላይ የጥናቱ ስነዘዴ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነ (በትክክል እንደተቀረፀ) በመፈተሽ የተገኘውን ውጤት ማንፀባረቅ እና ለዋናው ጥናት የተገኘውን ተሞክሮ ማመላከት ነው።

4.1 የናሙና ጥናቱ አካሄድ

በናሙና ጥናቱ ተግባራዊ የሆኑት የመረጃ መሰብሰብያ መሳርያዎች፣ የጥናቱ የመረጃ ምንጮች፣ የትምህርት አቀራረቦች፣ የመረጃ አተናተን ዘዴዎች፣ ወዘተ በምእራፍ ሶስት የተንፀባረቁቱ ናቸው። በናሙና ጥናቱ የተተገበሩ እና በዋናው ጥናት ለውጥ የተካሄደባቸው ጉዳዮች በተሞክሮነት የተወሰዱ በመሆናቸው ለውጡ በተሞክሮ ስር ተንፀባርቋል። በናሙና ጥናቱ መረጃ በመስጠት የተሳተፉ ተማሪዎች በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ ጅግጅጋ መሰናዶ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ጅግጅጋ ሼክ አብዱሰላም ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ የ 9ኛ ክፍል ሶማልኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች ናቸው (አባሪ ሁለትን ይመለከቱዋል)።

በናሙና ጥናቱ ትኩረት የተደረገባቸው የማንበብ ብልሃት አይነቶች 24 ሲሆኑ እነሱም ደጋግሞ ማንበብ፣ የቀደመ እውቀትን መጠቀም፣ ዋናውን ሀሳብ ፈጥኖ ማግኘት፣ መረጃን ፈልፍሎ በማውጣት ምክንያታዊ ድምዳሜ ላይ መድረስ፣ ሃብትን መጠቀም (ለምሳሌ መዝገብ ቃላት)፣ ምክንያት ላይ የተመሰረተ ድምዳሜ ላይ መድረስ፣ ገለፃን መተንተን፣ ንፅፅራዊ ወይም ተቃርኗዊ አተናተን መጠቀም፣ መተርጎም፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ፅሁፍን አሳጥሮ መፃፍ (ጭምቀ ሐሳብ መፃፍ)፣ ጠቃሚ ከሆነ ሐሳብ ስር

ምልክት ማድረግ፣ የቋንቋ ፍንጮችን መጠቀም፣ የፅሁፉን አጠቃላይ ሐሳብ መረዳት እና ሐሳብን ማያያዝ፣ ትኩረት መስጠት፣ ሐሳብን ማዋቀር፣ የማንበብ አላማና ግብን ማዋቀር፣ ማቀድ፣ መለማመድ፣ ራስን መቆጣጠር፣ ራስን መገምገም፣ ጥያቄ መጠየቅ፣ ቁልፍ ቃላትን መጠቀም፣ አዳዲስ ቃላትን በአውድ መረዳት፣ የፅሁፉ ሐሳብ በአእምሮ ውስጥ ምስል እንዲፈጥር ማድረግ ናቸው።

4.2 በናሙና ጥናቱ የተገኙ ተሞክሮዎች

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ የናሙና ጥናቱ የተካሄደበት ዋነኛ አላማ የጥናቱን አካሄድ ውጤታማነት ለማጤን፣ ለምርምር ስራው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተቀረፁት የመረጃ መሰብሰብያ መሳርያዎች ተገቢ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ፣ የመረጃ አተናተን ዘዴውን ተገቢነት ለመፈተሽ ወዘተ ነው። በዚህ መሰረት የናሙና ጥናቱ ከላይ በቀረበው መንገድ መከናወኑ ለዋናው ጥናት አስፈላጊ እና ጠቃሚ ግብአቶች እንዲገኙ አስችሏል። በናሙና ጥናቱ የተገኙ ተማክሮዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በናሙና ጥናቱ የመጀመሪያ መሰረታዊ ጥያቄ የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከቅድመልምምድ በተሻለ በድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት ግንዛቤን ያጎለብታል? የሚል ነው። የጥናቱ ሁለተኛ ጥያቄ የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከቅድመልምምድ በተሻለ በድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እንዲጎለብት ምን ያህል ያስችላል? የሚል ነው። የማንበብ ብልሃት ግንዛቤ ማለት የማንበብ ብልሃት ምንነትን ብቻ ሳይሆን የአጠቃቀም ግንዛቤን የሚመለከት በመሆኑ እነዚህን የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ወደአንድ ማጠቃለል ተገቢ መሆኑ ተሞክሮ ተገኝቷል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃትን በግልፅ በመማራቸው የማንበብ ብልሃት ግንዛቤያቸው መጎልበት አለመጎልበቱን ለመፈተሽ የምርጫ ጥያቄ ያካተተ ፈተና ቀርቧል። የማንበብ ብልሃት አጠቃቀማቸውን ለመረዳት ደግሞ የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ እና ቃለመጠይቅ አገልግሎት ላይ ውሏል። በጥናቱ ሂደት የማንበብ ብልሃት ግንዛቤን ለመፈተሽ የቀረበው ፈተና እና አጠቃቀምን ለማየት የቀረበው የፅሁፍ መጠይቅ የአቀራረብ ልዩነት ካልሆነ በስተቀር በይዘት ተመሳሳይ በመሆናቸው ለዋናው ጥናት ፈተናው መቅረት እንዳለበት ተሞክሮ ተገኝቷል።

በናሙና ጥናቱ ለትምህርት የቀረቡት የማንበብ ብልሃቶች ከአእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ፣ ትውስታ፣ ማካካስ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት ውስጥ የተመረጡ ሃያ አራት የማንበብ ብልሃቶች ናቸው። እነዚህ የማንበብ ብልሃቶች ከአንብቦ መረዳት ጋር በቀጥታ የሚያያዙ ቢሆንም የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት እና ብልሃቶቹን ለማስተማር የታሰበው ጊዜ ውስን በመሆኑ ሃያ አራቱን ለማስተማር ከመሞከር ይልቅ የተወሰኑትን ቀንሶ (ስምንቱን ቀንሶ) አስራስድስቱ ላይ ማተኮር ተገቢ መሆኑ ተሞክሮ ተገኝቷል።

በጥናቱ ትኩረት የተደረገበት አንዱ ጉዳይ የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ነው። በናሙና ጥናቱ ሂደት ለመፈተሽ የተሞከረው ከሶማልኛ ቋንቋ ወደአማርኛ ቋንቋ ያለን ሽግግሮሽ ነው። ተማሪዎች በማንበብ ሂደት የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን ከመጀመሪያ ቋንቋ ወደሁለተኛ ቋንቋ ወይም ከሁለተኛ ቋንቋ ወደመጀመሪያ ቋንቋ እያሸጋገሩ ሊጠቀሙ ይችላሉ። በዚህ መሰረት ጥናቱ ከሶማልኛ ወደአማርኛ ብቻ ሳይሆን ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ያለው የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ በየቋንቋው አንብቦ የመረዳት ውጤት እንዲጎለብት ያለውን አስተዋፆ መመልከት ተገቢ መሆኑ ተሞክሮ ተገኝቷል።

በጥናቱ የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽን ለመለየት እንዲያመች በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃቶችን ማስተማር ተገቢ ነው። በናሙና ጥናቱ በሶማልኛ ቋንቋ መማር ያለበት ሙከራ ቡድን አንድ በሶማልኛ ቋንቋ መምህር፣ በአማርኛ ቋንቋ መማር ያለበት ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ ቋንቋ መምህር እንዲማሩ ተደርጓል። በጥናቱ የማንበብ ብልሃትን ለማስተማር ሁለት መምህራን መሳተፋቸው ከቁጥጥር ውጪ የሆኑ ተላውጦዎች (የትምህርት ዝግጅት ልዩነት፣ የልምድ ልዩነት፣ የፆታ ልዩነት፣ የአቀራረብ ልዩነት ወዘተ) ሊከሰቱ እንደሚችሉ በመታመኑ ትምህርቱ በአንድ መምህር መሰጠት እንዳለበት ተሞክሮ ተገኝቷል።

በናሙና ጥናቱ አንብቦ መረዳትን ለመፈተሽ የቀረበው ፈተና አንድ ምንባብ እና አስር የምርጫ ጥያቄዎች ያካተተ ነው። የምዘና አስተማማኝነትን ለማሳደግ እንዲያስችል የጥያቄዎቹን ቁጥር መጨመር እንደሚያስፈልግ ተሞክሮ ተገኝቷል።

በጥናቱ ትኩረት የተሰጠባቸው የማንበብ ብልሃቶች በአምስት ንኡሳን ብልሃቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። እነዚህ ብልሃቶች ከሁለት በላይ በመሆናቸው በአንብቦ መረዳት ላይ

ያላቸውን አዎንታዊ ተፅእኖ ለመመልከት ከ Pearson ተዛምዶ ፍተሻ ይልቅ ህብረድህረት (Multiple Regression) መጠቀም አስፈላጊ እንደሆነ ተሞክሮ ተገንቷል።

በናሙና ጥናቱ የተተኳሪ ተማሪዎችን የማንበብ ብልሃት ለመፈተሽ በሁለቱም ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅፉፍ መጠይቅ ቀርቧል። መጠይቁ ሚዛናዊ የደረጃ ልኬት አቀራረብ የተዘጋጀ ሲሆን በእያንዳንዱ ቋንቋ 34 ጥያቄዎችን እንዲያካትት ተደርጓል። ሚዛናዊ የደረጃ ልኬት መጠይቁ ለትምህርት ከቀረቡት 24 ብልሃቶች ጋር ሲነፃፀር አንዳንድ ብልሃቶች ከአንድ በላይ በሆኑ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ይህ መረጃው የሚያንፀባርቀውን ውጤት ሊያዛባ ስለሚችል ለትምህርት የቀረቡትን ብልሃቶች እና የፅሁፍ መጠይቁን ቁጥር ማጣጣም ተገቢ መሆኑን ተሞክሮ ተገንቷል።

በናሙና ጥናቱ የተተኳሪ ተማሪዎችን የማንበብ ብልሃት ለመፈተሽ የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ ቀርቧል። መጠይቁ አምስት ደረጃዎች ያሉት ሚዛናዊ የደረጃ ልኬት አቀራረብን የተከተለ ነው። ይህ የፅሁፍ መጠይቅ የራሱ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች አሉት። በተለይ ደካማ ጎኑ ተማሪዎች አንብበው ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በግምት እና በግዴለሽነት ሊሞሉ ይችላሉ። በዋናው ጥናት ይህን ማስወገድ ባይቻልም ተማሪዎች አስበው መልስ እንዲሰጡ ለማድረግ በመጠይቁ አጭር ፅሁፍ በማካተት የቀረበውን ፅሁፍ ሲያነቡ ምን አይነት ብልሃት እንደተጠቀሙ ራሳቸው እንዲያመላክቱ ማድረግ ተገቢ መሆኑ ተሞክሮ ተገኝቷል።

ምእራፍ አምስት

ዋናው ጥናት (Main Study)

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ብቃትን (ውጤትን) ለማጎልበት እና ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ያለው አስተዋፆ ምን እንደሚመስል በጥልቀት መመርመር ነው። በጥናቱ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር ነፃ ተላውጦ ሲሆን አንብቦ መረዳት እና የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ጥገኛ ተላውጦዎች ናቸው። ይህ ምእራፍ ጥናቱ በሂደት ያከናወነውን የናሙና ጥናት ተሞክሮ እንደግብአት በመጠቀም በዋናው ጥናት የተንፀባረቁትን መሰረታዊ ጥያቄዎች እና መላምቶች በጥልቀት ፈትሾ የተገኘውን ውጤት እና አንድምታ በዝርዝር ያካተተበት ክፍል ነው። በዋናው ጥናት በተለያየ መንገድ የተሰበሰበው መረጃ በምእራፍ ሁለት ስር በተንፀባረቀው ንድፈሀሳባዊ እና ትውረታዊ ማእቀፍ መሰረት ትንታኔ ተሰጥቷል። በጥናቱ ትንታኔ ለማቅረብ እንዲያመች የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች የአቀራረብ ቅደም ተከተል መሪ አድርጎ ተጠቅሟል። በዚህ መሰረት ይህ ምራፍ በዋናነት ሁለት ጉዳዮችን አንፀባርቋል። እነሱም የጥናቱ መረጃ ትንተና (የተገኘ ውጤት) (Result) እና ትርጓሜው (የውጤት ማብራሪያ) (Discussion) ናቸው ።

5.1 የጥናቱ መረጃ ትንተና (የተገኘ ውጤት)

5.1.1 በፈተና እና በፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

የጥናቱ ጥያቄ ቁጥር አንድ፡- የማንበብ ብልሃቶችን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከቅድመልምምድ በጎላ መልኩ በድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም መጎልበት ላይ ምን ያህል አስተዋፆ አለው?

በዚህ ጥናት ትኩረት የተሰጠባቸው የማንበብ ብልሃቶች ርዕሱን እና ንኡሳን ርዕሶችን በማየት መተንበይ፣ ደግሞ (ደጋግሞ) ማንበብ፣ ዋናውን ሐሳብ በፍጥነት ማግኘት፣ መረጃዎችን ፈልፍሎ ማውጣት፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ሐሳብን በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ (ጭምቀ ሐሳብ)፣ ብልሃቶችን ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ ማሸጋገር፣ ፅሁፍን ለማንበብ ማቀድ፣ራስን እና አንብቦ መረዳትን መቆጣጠር፣ ራስን መገምገም፣ የፅሁፉ ሀሳብ በአእምሮ ምስል እንዲፈጥር አድርጎ መጠቀም፣ የቀደመ እውቀትን መጠቀም፣

የአዳዲስ ቃላትን እና ሀረጎችን ፍቺ መገመት፣ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመረዳት አውዳዊ ፍቺ መጠቀም፣ጥያቄ መጠየቅ እና ከሌሎች ጋር መተባበር ናቸው።

በጥናቱ በሙከራ ቡድኖች ውስጥ የተሳተፉ ተተኳሪ ተማሪዎች በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳታቸውን ለማጎልበት የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን ቅድመ እና ድህረልምምድ እንዴት እንደተጠቀሙ ማየት ተቀዳሚ ተግባር ነው። በጥናቱ የተተኳሪ ተማሪዎችን የማንበብ ብልሃት ለመፈተሽ የቀረበው አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ የመጀመሪያው ክፍል 32 ጥያቄዎችን ያካተተ ነው። ይህ ማለት አንድ ብልሃት በተለያየ አገላለፅ በሁለት ጥያቄዎች ተፈትሿል ማለት ነው። የጥያቄ አቀራረቡ ሚዛናዊ የደረጃ ልኬት ዘዴን የተከተለ ሲሆን የቀረቡትን ጥያቄዎች ለመመለስ አምስት አማራጮች (1.በጭራሽ አልጠቀምም፣ 2. አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ፣ 3. አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ (50%)፣ 4. አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ እና 5. ሁልጊዜ እጠቀማለሁ) ያካተተ ነው። በዚህ ጥናት 1 እና 2 የመረጡ ተማሪዎች በተጠየቀው የማንበብ ብልሃት ላይ ያላቸው እውቀት ዝቅተኛ፣ 3ትን የመረጡ ተማሪዎች መካከለኛ፣ 4 እና 5 የመረጡ ተማሪዎች ከፍተኛ የመተግበር ችሎታ አላቸው ተብሎ ተወስዷል። የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቁ የመጀመሪያ ክፍል በሚከተለው መንገድ ቀርቧል።

በመጀመሪያ ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ቅድመልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም የመተግበር ችሎታ ልዩነት (የችሎታ መበላለጥ) ያላቸው መሆን አለመሆኑ ታይቷል። (አህዛዊ መረጃው በነፃ ናሙና ቲ-ቴስት የተሰላ ነው)።

ሰንጠረዥ *ሶስት*:- ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ቅድመልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም

						Levene አቻዊ ልዩነት አመላካች ቴስት		የአማካይ እኩልነት መፈተሻ ቲ-ቴስት	
ተላውጦዎች		ሙከራ ቡድን	የተማሪ ቁጥር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	መደበኛ አማካይ ስህተት	የኤፍ ዋጋ	የቲ ዋጋ	የነፃነት ደረጃ	ጉልህነት (ሁለትዮሽ አመላካች
አማርኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት	ተጠባቂ የልይይት አቻዊነት Equal Variance assumed	አንድ ሁለት	73 69	3.21 3.27	.334 .451	.0391 .0543	.101	-.812	140	.418 .
ሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት	ተጠባቂ የልይይት አቻዊነት Equal Variance Assumede	አንድ ሁለት	73 69	3.27 3.36	.289 .275	.0338 .0331	.308	-1.875	140	.063

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ቅድመልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ተጠባቂ እና ኢ-ተጠባቂ የልይይት አቻዊነትን ያሳያል (ኢ-ተጠባቂ የልይይት አቻዊነት ለትንተናው አስፈላጊ ባለመሆኑ ከሰንጠረዥ ውጭ ሆንዋል) ። በነፃ ናሙና ቲ-ቴስት የተሰላው አሀዝ የሚያመላክተው በአማርኛ ቋንቋ ሙከራ ቡድን አንድ አማካይ 3.21 ሙከራ ቡድን ሁለት 3.27 ሲሆን የቲ-ዋጋ (t value) -.812 ሁለት አቅጣጫ ጉልህ ልዩነት አመልካች (sig/p 2 tailed) .418 ነው። በሶማልኛ ቋንቋ አማካይ ሙከራ ቡድን አንድ 3.27 ሙከራ ቡድን ሁለት 3.36 ሲሆን የቲ-ዋጋ -1.875 ጉልህ ልዩነት አመልካች .063 መሆኑን ያሳያል። በሁለቱም ቋንቋ ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤ ጉልህ ልዩነት አመላካች አሀዙ ከመደበኛ መስፈርት 0.05 በላይ (>0.05) መሆኑን ያሳያል። የተሰላው አሀዝ ያመላከተው ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ቅድመልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤ ልዩነት የሌላቸው መሆኑን ነው። ይህ በጥናቱ ከተሰጠው ትምህርት አስቀድሞ በሙከራ ቡድኖቹ መካከል የችሎታ መበላለጥ አለመኖሩን ያንፀባርቃል።

በጥናቱ የሙከራ ቡድኖቹ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ በመማራቸው ከቅድመልምምድ ጋር ሲነፃፀር ድህረልምምድ ያሳዩትን የባህሪ ለውጥ ማየት የጥናቱ ትኩረት በመሆኑ ዝርዝር ሀሳቡ በሚከተለው መንገድ ቀርቧል። በዚህ ክፍል ለትንተና እንዲያመች በመጀመሪያ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ለቀረበላቸው መጠይቅ የሰጡት ምላሽ ብልሃቶቹን በዝርዝር በማየት ቀርቧል።

የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቁ 32 ጥያቄዎችን የያዘ ቢሆንም የሚጠይቀው ተማሪዎች ለትምህርት የቀረቡትን 16 የማንበብ ብልሃቶች ምን ያህል ውጤታማ በሆነ መንገድ እንደተገበሯቸው የመፈተሽ አላማ ያለው ነው። በመጠይቁ አንድ ብልሃት በሁለት ጥያቄዎች ተፈትሿል (ለምሳሌ 1ኛ እና 17ኛ፣ 2ኛ እና 18ኛ፣ 3ኛ እና 19ኛ...)። በመሆኑም በመጠይቁ ከ1_16 ያሉትን እና ከ17_32 ያሉትን በመደመር (1ኛን ከ17ኛ፣ 2ኛን ከ18ኛ፣ 3ኛን እና ከ19ኛ...) በመደመር አማካይ ውጤቱን ለማስላት ተሞክሯል። ይህም ከ1_32 ጥያቄዎች ቢቀርቡ የሚፈጥረውን ድግግሞሽ ያስቀራል።

ከዚህ በታች የቀረበው ሰንጠረዥ ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤን ለመለየት የቀረበላቸው ዝርዝር ጥያቄ እና ተማሪዎቹ የሰጡትን ምላሽ አማካይ፣ መደበኛ ልይይት እና የተገኘን ውጤት የሚያሳይ ነው (በገላጭ አሃዛዊ ስሌት አማካይን መደበኛ ልይይትን እና የተገኘ ውጥት / የአማካይ ልዩነት/ በማነፃፀር የቀረበ)።

ሰንጠረዝ አራት፡- ሙከራ ቡድን አንድ ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት የመተግበር ልምድ በዝርዝር የሚያሳይ

		አማርኛ ቋንቋ					**ሶማልኛ ቋንቋ**				
		ቅድመልምምድ		**ድህረልምምድ**			**ቅድመ ልምምድ**		**ድህረልምምድ**		
ተ.ቁ.	የማንበብ ብልሃቶች	**አማካይ**	**መደበኛ ልይይት**	**አማካይ**	**መደበኛ ልይይት**	**የተገኘ ለውጥ**	**አማካይ**	**መደበኛ ልይይት**	**አማካይ**	**መደበኛ ልይይት**	**የተገኘ ለውጥ**
	አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት										
1	ርዕሱን በማየት የምንባቡን ሀሳብ መተንበይ	3.08	.91	4.06	.85	.99	3.44	.88	3.60	.84	..16
2	የምንባቡን ሀሳብ በፍጥነት ማግኘት	3.03	.99	3.81	.79	.78	3.33	.97	3.58	.81	.25
3	ከምንባቡ ውስጥ መረጃ ፈልፍሎ ማውጣት	3.35	.95	4.10	.74	.75	3.10	.98	3.77	.76	.66
4	ማስታወሻ መያዝ	3.21	1.01	4.03	.86	.82	3.36	1.01	3.70	.96	.34
5	ደጋግሞ ማንበብ	2.97	.88	3.99	.86	1.02	3.03	.89	3.77	.91	.74
6	የምንባቡን ሀሳብ በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ	3.44	.97	3.99	.73	.55	3.32	.94	3.89	.83	.57
7	አውዳዊ ፍቺ መጠቀም	3.36	.96	4.23	.69	.87	3.60	.86	3.85	.86	.25
8	የማንበብ ብልሃት ከሶማልኛ ወደአምርኛ / ከአማርኛ ወደሶማልኛ እያሸጋገሩ መጠቀም	3.03	.80	3.69	.69	.66	3.21	1.02	3.88	.92	.66
	ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት										
9	ምንባቡን ለማንበብ ማቀድ	3.25	1.24	3.64	.88	.38	3.22	0.91	3.54	.83	.32
10	በማንበብ ወቅት ራስን እና አንበቦ መረዳትን መቆጣጠር	3.34	.96	3.68	.92	.34	3.19	1.03	3.61	.99	.42
11	ምንባቡን በትክክል ማንበብን ለማረጋገጥ ራስን መገምገም	3.47	.97	4.08	.75	.60	3.21	1.00	3.71	.91	.50
	ማካካስ የማንበብ ብልሃት										
12	የቃላትን ፍቺ መገመት	3.20	1.02	3.40	.73	.20	3.30	1.12	3.76	.91	.46
	ትውስታ የማንበብ ብልሃት										
13	የቀደመ እውቀትን መጠቀም	3.14	1.06	3.65	.84	.51	3.25	1.07	3.61	.88	.36
14	የምንባቡ ሀሳብ በአእምሮ ውስጥ ምስል እንዲፈጥር አድርጎ መጠቀም	3.18	1.04	4.03	.69	.86	3.14	0.99	3.85	.94	.71
	ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት										
15	ጥያቄ መጠየቅ	3.32	.89	3.68	.82	.37	3.32	.84	3.79	.96	.47
16	ከተማሪዎች ጋር መተባበር	3.16	1.00	3.16	.86	.00	3.38	0.95	3.72	.85	.34

ሰንጠረዝ አምስት፡- *መ*ከራ ቡድን ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት የመተግበር ልምድ በዝርዝር የሚያሳይ

		አማርኛ ቋንቋ					ሶማልኛ ቋንቋ				
		ቅድመልምምድ		ድህረልምምድ			ቅድመ ልምምድ		ድህረልምምድ		
ተ.ቁ	የማንበብ ብልሃቶች	አማካይ	መደበኛ ልይይት	አማካይ	መደበኛ ልይይት	ለውጥ	አማካይ	መደበኛ ልይይት	አማካይ	መደበኛ ልይይት	ለውጥ
	አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት										
1	ርዕሱን በማየት የምንባቡን ሀሳብ መተንበይ	3.15	.98	3.62	.92	.46	3.28	.82	4.04	.78	.77
2	የምንባቡን ሀሳብ በፍጥነት ለማግኘት መጣር	3.30	.96	3.22	.84	-.07	3.45	.98	3.87	.86	.42
3	ከምንባቡ ውስጥ መረጃ ፈልፍሎ ለማውጣት መጣር	3.21	.96	3.42	.94	.21	3.63	.97	4.10	.82	.47
4	ማስታወሻ መያዝ	3.04	1.11	3.69	.92	.65	3.37	0.97	4.13	.69	.76
5	ደግሞ ማንበብ	3.26	.94	3.72	.86	.46	3.30	.90	4.18	.74	.88
6	የምንባቡን ሀሳብ በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ	3.71	5.84	3.63	.97	-.08	2.98	.94	4.00	.77	1.02
7	አውዳዊ ፍቺ መጠቀም	3.08	.86	3.54	.93	.46	3.30	.88	4.12	.75	.82
8	የማንበብ ብልሃት ከሶማልኛ ወደአምርኛ / ከአማርኛ ወደሶማልኛ እያሸጋገሩ መጠቀም	3.47	.95	3.88	.80	.41	3.42	.96	3.88	.90	.46
	ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት										
9	ምንባቡን ለማንበብ ማቀድ	4.08	5.69	3.57	.89	-.51	3.33	1.02	3.97	.79	.64
10	በማንበብ ወቅት ራስን እና አንበቦ መረዳትን መቆጣጠር	3.33	.86	3.58	.90	.25	3.43	.88	3.56	.87	.12
11	ምንባቡን በትክክል ማንበብን ለማረጋገጥ ራስን መገምገም	3.19	.90	3.62	.88	.43	3.32	.92	4.15	.67	.83
	ማካካስ የማንበብ ብልሃት										
12	የቃላትን ፍቺ መገመት	3.28	.90	3.73	.89	.46	3.20	0.92	3.46	.81	.26
	ትውስታ የማንበብ ብልሃት										
13	የቀደመ እውቀትን መጠቀም	3.14	.92	3.52	.95	.38	3.43	1.00	3.69	.92	.26
14	የምንባቡ ሀሳብ በአእምሮ ውስጥ ምስል እንዲፈጥር አድርጎ መጠቀም	3.33	1.04	3.54	.82	.20	3.28	0.92	4.04	.84	.76
	ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት										
15	ጥያቄ መጠየቅ	3.27	1.15	3.86	.76	.59	3.64	.91	3.93	.78	.30
16	ከተማሪዎች ጋር መተባበር	3.27	.98	3.58	.82	.31	3.47	0.95	3.83	.98	.36

ከላይ የቀረቡት ሁለት ሰንጠረገሮች በመከራ ቡድን አንድ እና በመከራ ቡድን ሁለት ውስጥ ያሉ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በእያንዳንዱ የማንበብ ብልሃት ላይ ያላቸውን የአጠቃቀም እውቀት ያንፀባርቃል፡፡ በመጀመሪያው ሰንጠረዥ እንደተመላከተው መከራ ቡድን አንድ በአማርኛ ቋንቋ ቅድመልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እውቀት ከፍተኛ አማካይ ውጤት ከአንድ እስከሶስት በቅደም ተከተል ሲታይ የምንባቡን ሀሳብ

በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ 3.4፣ አውዳዊ ፍቺ መጠቀም 3.36 ፣ ከምንባቡ ውስጥ መረጃ ፈልፍሎ በማውጣት ምክንያታዊ ድምዳሜ ላይ መድረስ 3.35 ሲሆን ድህረ ልምምድ አውዳዊ ፍቺ መጠቀም 4.23፣ ከምንባቡ ውስጥ መረጃ ፈልፍሎ ማውጣት 4.10፣ ምንባቡን በትክክል ማንበብን ለማረጋገጥ ራስን መገምገም 4.08 መሆኑን ያሳያል። የአማካይ ልዩነት (የተገኘ ለውጥ) ሲታይ ከፍተኛ ውጤት ከአንድ እስከሶስት የተመዘገበው ደግሞ (ደጋግሞ) ማንበብ 1.02፣ ርእሱን በማየት የምንባቡን ሀሳብ መተንበይ .99፣ አውዳዊ ፍቺ መጠቀም .87 ናቸው።

ሙከራ ቡድን አንድ በሶማልኛ ቋንቋ ቅድመልምምድ ከፍተኛ አማካይ ከአንድ እስከሶስት በቅደም ተከተል ሲታይ አውዳዊ ፍቺ መጠቀም 3.60፣ ርእሱን በማየት የምንባቡን ሀሳብ በተንበይ 3.44፣ ከተማሪዎች ጋር መተባበር 3.38 ሲሆን ድህረልምምድ የምንባቡን ሀሳብ በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ 3.89፣ የማንበብ ብልሃት ከሶማልኛ ወደአማርኛ / ከአማርኛ ወደሶማልኛ እያሻገሩ መጠቀም 3.88 ፣ አውዳዊ ፍቺ መጠቀም 3.85 እና የምንባቡ ሀሳብ በአእምሮ ምስል እንዲፈጥር አድርጎ መጠቀም 3.85 መሆኑን ያሳያል። የአማካይ ልዩነት (የተገኘ ውጤት) መሰረት በማድረግ ከአንድ እስከሶስት ሲታይ ደጋግም ማንበብ .74፣ የምንባቡ ሀሳብ በአእምሮ ውስጥ ምስል እንዲፈጥር አድርጎ መጠቀም .71፣ ከምንባቡ ውስጥ መረጃ ፈልፍሎ ማውጣት .66 እና የማንበብ ብልሃትን ከሶማልኛ ወደአማርኛ/ ከአማርኛ ወደሶማልኛ እያሻገሩ መጠቀም .66 መሆኑን ያሳያል።

በተመሳሳይ ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ ቋንቋ ቅድመልምምድ ከፍተኛ አማካይ ያስመዘገቡት ከአንድ እስከሶስት በቅደም ተከተል ሲታይ ምንባቡን ለማንበብ ማቀድ 4.08፣ የምንባቡን ሀሳብ በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ 3.71፣ የማንበብ ብልሃትን ከሶማልኛ ወደአማርኛ / ከአማርኛ ወደሶማልኛ እያሸጋገሩ መጠቀም 3.47 ሲሆን ድህረልምምድ የማንበብ ብልሃትን ከሶማልኛ ወደአማርኛ / ከአማርኛ ወደሶማልኛ እያሸጋገሩ መጠቀም 3.88፣ ጥያቄ መጠየቅ 3.86፣ ደግሞ ማንበብ 3.72 መሆኑን ያሳያል። የአማከይ ልዩነት (የተገኘ ውጤት) አንፃር ከፍተኛ ውጤት ከአንድ እስከሶስት በቅደም ተከተል ሲታይ ማስታወሻ መያዝ .65 ፣ ጥያቄ መጠየቅ .59፣ ምንባቡን ለማንበብ ማቀድ .51 መሆኑን ያሳያል።

መከራ ቡድን ሁለት በሶማልኛ ቋንቋ ቅድመልምምድ ዝርዝር የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እውቀት አማካይ ከአንድ እስከሶስት በቅደምተከተል ሲታይ ጥያቄ መጠየቅ 3.64 ፣ ከምንባቡ ውስጥ መረጃ ፈልፍሎ ማውጣት 3.63፣ ከተማሪዎች ጋር መተባበር 3.47 ሲሆን ድህረልምምድ ምንባቡን በትክክል ማንበብን ለማረጋገጥ ራስን መገምገም 4.5፣ ማስታወሻ መያዝ 4.13፣ አውዳዊ ፍቺ መጠቀም 4.12 መሆኑን ያሳያል። የአማካይ ልዩነት (የተገኘ ለውጥ) አንፃር ሲታይ ከፍተኛ ለውጥ ከአንድ እስከሶስት የምንባቡን ሀሳብ በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ 1.02፣ ደግሞ (ደጋግሞ) ማንበብ .88 ፣ አውዳዊ ፍቺ መጠቀም .82 መሆኑን ያሳያል።

በመከራ ቡድን አንድ እና በመከራ ቡድን ሁለት ውስጥ የተሳተፉ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች ለትምህርት የቀረቡትን ዝርዝር የማንበብ ብልሃቶች አጠቃቀም ሲጤን ከቅድመልምምድ በተሻለ ድህረልምምድ ከፍተኛ አማካይ ያስመዘገቡባቸው የማንበብ ብልሃቶች በአብዛኛው አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃቶች እንደሆኑ ያሳያል።

በመቀጠል የማንበብ ብልሃቶችን በየንኡሳን ምድባቸው (አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ፣ ትውስታ፣ ማካካስ፣ ማህበራዊ) በጥቅል በማቅረብ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ቀርቧል።

ከዚህ በታች የቀረበው ስንጠረዥም መከራ ቡድን አንድ እና መከራ ቡድን ሁለት በቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በየንኡሳን ክፍል የማንበብ ብልሃት አጠቃቀማቸው ምን እንደሚመስል ያሳያል (አሀዛዊ መረጃው በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት የተሰላ ነው)።

ሰንጠረዥ *ሰድሰት፡-* መከራ ቡድን አንድ እና መከራ ቡድን ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም

ተላውጦዎች	መከራ ቡድን	የተማሪ ቁጥር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	መደበኛ አማካይ ስህተት	የቲ ዋጋ	የነፃነት ደረጃ	ጉልህነት (ሁለትዮሽ አመልካች)
አማርኛ ቅድመ ልምምድ	አንድ	73	3.255	.354	.041	-13.312	72	.005
ድህረ ልምምድ			4.062	.405	.047			
	ሁለት	69	3.156	.340	.041	6.234	68	.010
			3.596	.471	.056			
ሶማልኛ ቅድመ ልምምድ	አንድ	73	3.275	.329	.038	-7.355	72	.000
ድህረ ልምምድ			3.774	.412	.048			
	ሁለት	69	3.307	.331	.039	-14.733	68	.000
			4.096	.339	.040			

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ቅድመልምምድ አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀማቸው መከራ ቡድን አንድ 3.255 መከራ ቡድን ሁለት 3.156 አማካይ ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ ደግሞ መከራ ቡድን አንድ 3.275 መከራ ቡድን ሁለት 3.307 መሆኑን ሳያል፡፡ ድህረ ልምምድም በአማርኛ ቋንቋ አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀማቸው ሲታይ መከራ ቡድን አንድ 4.062 መከራ ቡድን ሁለት 3.596 በሶማልኛ ቋንቋ መከራ ቡድን አንድ 3.774 መከራ ቡድን ሁለት 4.096 አማካይ አስመዝግበዋል፡፡ ቅድመ እና ድህረልምምድ አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም አማካይ ልዩነት በአማርኛ መካራ ቡድን አንድ -.807 መከራ ቡድን ሁለት .4402 ሲሆን በሶማልኛ መከራ ቡድን አንድ -.498 መከራ ቡድን ሁለት ደግሞ -.788 መሆኑን ያሳያል፡፡

ከላይ በሰንጠረጉቹ እንደተመላከተው የመከራ ቡድኖቹ ቅድመ እና ድህረልምምድ አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ልዩነት ጉልህ መሆን አለመሆኑ ሲታይ በአማርኛ ቋንቋ መከራ ቡድን አንድ የቲ ዋጋ -13.17 ሁለትዮሽ ጉልህ ልዩነት አሀዛዊ መረጃው .005 መከራ ቡድን ሁለት የቲ ዋጋ 6.234 ሁለትዮሽ ጉልህ ልዩነት አሀዛዊ

መረጃው .010 መሆኑን ያሳያል። በሶማልኛ ቋንቋ መካከራ ቡድን አንድ የቲ ዋጋ -7.355 መካከራ ቡድን ሁለት -14.733 ሲሆን የሁለቱም ቡድን ሁለትዮሽ ጉልህ ልዩነት አሀዛዊ መረጃው .000 እንደሆነ ያመላክታል። በአማርኛም ሆነ በሶማልኛ ቋንቋ የሁለቱም ቡድኖች ጉልህ ልዩነት አመላካች አሀዝ ከ0.05 በታች (<0.05) በመሆኑ መካከራ ቡድን አንድም ሆነ መካከራ ቡድን ሁለት በቅድመ እና ድህረልምምድ መካከል አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ጉልህ ልዩነት መኖሩን አመላክቷል። ጉልህ ልዩነት አመላካች አሀዙ እያንዳንዱ ቡድን ቅድመ እና ድህረልምምድ አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም በምን ያህል የጥንካሬ ደረጃ ልዩነት እንዳሳዩ ግን አያሳይም።

በቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛም ሆነ በሶማልኛ ቋንቋ አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ልዩነት በምን ያህል የልዩነት ጥንካሬ ደረጃ እንዳላቸው ለማረጋገጥ Cohen`s d የልዩነት ጥንካሬ ደረጃ (effect size) ስሌት ሲታይ በአማርኛ መካከራ ቡድን አንድ -2.126 መካከራ ቡድን ሁለት 1.085 በሶማልኛ መካከራ ቡድን አንድ -1.346 መካከራ ቡድን ሁለት -2.355 ተመዝግቧል። በቲ- ቴስት የተሰላ አሀዝ መደበኛ የጥንካሬ ደረጃ አመላካች (Cut of Point) ከ 0 — 0.20 ደካማ ወይም ዝቅተኛ (Weak)፣ ከ 0.21 — 0.50 መጠነኛ (Modest)፣ ከ 0.51 — 1.00 መካከለኛ (Moderate) እና ከ1.00 በላይ (>1.00) ከሆነ ጠንካራ (Strong) የልዩነት ጥንካሬ ደረጃ እንዳለ ያሳያል (Muijs 4004፡139)። በዚህ መሰረት ከላይ የቀረበው የተሰላ አሀዝ እንደሚያመላክተው መካከራ ቡድን አንድም ሆነ መካከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ቅድመ እና ድህረልምምድ አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም የልዩነት ጥንካሬ ደረጃ ከ 1.00 በላይ (>1.00) በመሆኑ ጠንካራ የልዩነት ጥንካሬ ደረጃ እንዳላቸው ያሳያል።

ሁለተኛው ጉዳይ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ነው። ከዚህ በታች የቀረበው ሰንጠረዥ ይህንኑ ያመላክታሉ።

ሰንጠረዥ *ሰባት፡-* መ*ከ*ራ ቡድን አንድ እና መ*ከ*ራ ቡድን ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም የሚያሳይ

ተላውጦዎች	መ*ከ*ራ ቡድን	የተማሪ ቁጥር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	መደበኛ አማካይ ስህተት	የቲ ዋጋ	የነፃነት ደረጃ	ጉልህነት (ሁለትዮሽ አመልካች)
አማርኛ ቅድመ ልምምድ ድህረ ልምምድ	አንድ	73	3.168 3.712	.689 .593	.080 .069	-5.165	72	.000
	ሁለት	69	3.253 3.401	.574 .588	.069 .070	-1.681	68	.097
ሶማልኛ ቅድመ ልምምድ ድህረ ልምምድ	አንድ	73	3.255 3.493	.667 .564	.078 .066	-2.140	72	.036
	ሁለት	69	3.437 3.705	.614 .476	.073 .057	2.622	68	.011

ልእለአእምሮታዊ የማንበብ የብልሃት አጠቃቀምን በተመለከተ ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚያንፀባርቀው በአማርኛ ቋንቋ ቅድመልምምድ መ*ከ*ራ ቡድን አንድ 3.168 መ*ከ*ራ ቡድን ሁለት 3.253 አማካይ ያስመዘገቡ ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ መ*ከ*ራ ቡድን አንድ 3.255 መ*ከ*ራ ቡድን ሁለት 3.437 አማካይ አስመዝግበዋል፡፡ ድህረልምምድ ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ መ*ከ*ራ ቡድን አንድ 3.712 መ*ከ*ራ ቡድን ሁለት ደግሞ 3.401 አማካይ ያስመዘገቡ ሲሆን በሶማልኛ መ*ከ*ራ ቡድን አንድ 3.493 መ*ከ*ራ ቡድን ሁለት 3.705 አማካይ አስመዝግበዋል፡፡ በመ*ከ*ራ ቡድን ውስጥ ያሉ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ቅድመ እና ድህረልምምድ ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም አማካይ ልዩነት በአማርኛ ቋንቋ መ*ከ*ራ ቡድን አንድ -.544 መ*ከ*ራ ቡድን ሁለት -.148 ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ መ*ከ*ራ ቡድን አንድ -.238 መ*ከ*ራ ቡድን ሁለት ደግሞ .268 ነው፡፡

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ እንደተመላከተው መ*ከ*ራ ቡድኖቹ ቅድመ እና ድህረልምምድ ያሳዩት ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ልዩነት ሲጤን በአማርኛ ቋንቋ

የቲ-ዋጋ ሙከራ ቡድን አንድ -5.165 ሙከራ ቡድን ሁለት -1.681 በሶማልኛ ቋንቋ ሙከራ ቡድን አንድ -2.140 ሙከራ ቡድን ሁለት 2.622 ሲሆን ሁለትዮሽ ጉልህ ልዩነት አሀዛዊ መረጃው ደግሞ በአማርኛ ሙከራ ቡድን አንድ .000 ሙከራ ቡድን ሁለት .097 በሶማልኛ ሙከራ ቡድን አንድ .036 ሙከራ ቡድን ሁለት .011 መሆኑን ያሳያል። በየቋንቋው የሁለቱም ቡድኖች ጉልህ ልዩነት ሲታይ በአማርኛ ቋንቋ ሙከራ ቡድን ሁለት ከ 0.05 በላይ (>0.05) በመሆኑ ቅድመ እና ድህረልምምድ ጉልህ ልዩነት እንደሌለው ያሳያል። በአማርኛ ሙከራ ቡድን አንድ እና በሶማልኛ ሁለቱም ቡድኖች ጉልህ ልዩነት አመላካቹ ከ 0.05 በታች (<0.05) በመሆኑ ቅድመ እና ድህረልምምድ ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ጉልህ ልዩነት እንዳላቸው አሳይቷል። ነገር ግን ይህ የተሰላ አሀዝ የልዩነት ጥንካሬ ደረጃን አያሳይም።

በቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ልዩነት በምን ያህል የልዩነት ጥንካሬ ደረጃ እንዳላቸው ለማረጋገጥ በልዩነት ጥንካሬ ደረጃ ስሌት ሲታይ በአማርኛ ቋንቋ ሙከራ ቡድን አንድ -.847 ሲሆን ሙከራ ቡድን ሁለት ጉልህ ልዩነት ባለማሳየቱ የልዩነት ጥንካሬ ደረጃውን መስራት አላስፈለገም። በሶማልኛ ሙከራ ቡድን አንድ -.385 ሙከራ ቡድን ሁለት ደግሞ .491 መሆኑን ያሳያል። ይህ የተሰላ አሀዝ ቅድመ እና ድህረልምምድ ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም በአማርኛ ቋንቋ ሙከራ ቡድን አንድ ከ 0.51—1.00 በመሆኑ መካከለኛ የልዩነት ጥንካሬ ደረጃ እንዳላቸው አሳይቷል። ይህ ሁኔታ በሶማልኛ ቋንቋ ሲታይ ሁለቱም የሙከራ ቡድኖች ከ 0.21—0.50 በመሆናቸው ቅድመ እና ድህረልምምድ ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ሲነፃፀር መጠነኛ የልዩነት ጥንካሬ ደረጃ እንዳሳዩ ግኙቱ አመላክቷል።

በዚህ ጥናት ሶስተኛው ጉዳይ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ትውስታ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ነው። ከታች የቀረበው ሰንጠረዥም ይህንኑ ያሳያሉ።

ሰንጠረዥ *ሰምንት፡-* *መ*ከራ ቡድን አንድ እና *መ*ከራ ቡድን ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ትውስታ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም የሚያሳይ

ተላውጦዎች	መከራ ቡድን	የተማሪ ቁጥር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	መደበኛ አማካይ ስህተት	የቲ ዋጋ	የነፃነት ደረጃ	ጉልህነት (ሁለትዮሽ አመልካች)
አማርኛ ቅድመ ልምምድ	አንድ	73	3.208 3.40	.909 .658	.106 .077	-1.437	72	.155
ድህረ ልምምድ	ሁለት	69	3.315 3.543	.748 .610	.090 .073	-1.886	68	.064
ሶማልኛ ቅድመ ልምምድ	አንድ	73	3.301 3.630	.719 .629	.084 .073	-3.077	72	.003
ድህረ ልምምድ	ሁለት	69	3.402 3.902	.739 .663	.088 .079	-4.502	68	.001

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እንዳመላክተው በአማርኛ ቋንቋ ትውስታ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ቅድመልምምድ *መ*ከራ ቡድን አንድ 3.208 *መ*ከራ ቡድን ሁለት 3.315 አማካይ ያስመዘጉ ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ *መ*ከራ ቡድን አንድ 3.301 *መ*ከራ ቡድን ሁለት 3.402 አስመዝግበዋል፡፡ ይህንኑ የማንበብ ብልሃት ድህረልምምድ በአማርኛ ቋንቋ *መ*ከራ ቡድን አንድ 3.40 *መ*ከራ ቡድን ሁለት 3.543 በሶማልኛ ቋንቋ *መ*ከራ ቡድን አንድ 3.630 *መ*ከራ ቡድን ሁለት 3.9702 አማካይ አስመዝግበዋል፡፡ *መ*ከራ ቡድኖቹ ያስመዘገቡት የአማካይ ልዩነት በአማርኛ *መ*ከራ ቡድን አንድ -.1927 *መ*ከራ ቡድን ሁለት .228 ሲሆን በሶማልኛ *መ*ከራ ቡድን አንድ -.329 *መ*ከራ ቡድን ሁለት .5 ነው፡፡

ሁለቱም የመከራ ቡድኖች በየቋንቋው ቅድመ እና ድህረልምምድ ትውስታ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀማቸው ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የተሰላው አሀዝ እንዳመላክተው በአማርኛ ቋንቋ *መ*ከራ ቡድን አንድ የቲ-ዋጋ -1.437 *መ*ከራ ቡድን ሁለት -1.886 በሶማልኛ ቋንቋ *መ*ከራ ቡድን አንድ -3.077 *መ*ከራ ቡድን ሁለት -

4.502 ነው። ሁለትዮሽ ጉልህ ልዩነት አሀዛዊ መረጃ (sig/p value) ሲታይ በአማርኛ ሙከራ ቡድን አንድ .155 ሙከራ ቡድን ሁለት .064 ሲሆን በሶማልኛ ሙከራ ቡድን አንድ .003 ሙከራ ቡድን ሁለት .001 መሆኑን ያመላክታል። በአማርኛ ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ጉልህ ልዩነት አመላካቹ ከ 0.05 በላይ (>0.05) በመሆኑ በቅድመ እና ድህረልምምድ ትውስታ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ጉልህ ልዩነት እንደሌለው ያሳያል። በሶማልኛ ቋንቋ ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት በየቋንቋው ጉልህ ልዩነት አመላካች አሀዝ ከ 0.05 በታች (<0.05) በመሆኑ በቅድመ እና ድህረልምምድ ትውስታ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ጉልህ ልዩነት ያለ መሆኑን አመላክቷል። ይህ የተሰላ አሀዝ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ምን ያህል የልዩነት ጥንካሬ ደረጃ እንዳለ አያሳይም።

በአማርኛ ቋንቋ ሙከራ ቡድን አንድም ሆነ ሙከራ ቡድን ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ ጉልህ ልዩነት ያልታየባቸው በመሆኑ የልዩነት ጥንካሬ ደረጃቸውን ማየት አላስፈለገም። በሶማልኛ ቋንቋ ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ ትውስታ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም የልዩነት ጥንካሬ ደረጃ ለማረጋገጥ በልዩነት የጥንካሬ ደረጃ ስሌት ሲታይ ሙከራ ቡድን አንድ -0.488 ሙከራ ቡድን ሁለት .713 ነው። ይህ የሚያሳየው በሶማልኛ ቋንቋ ሙከራ ቡድን አንድ ከ 0.21—0.50 ክልል ውስጥ በመሆኑ መጠነኛ የልዩነት ጥንካሬ ደረጃ ያለው ሲሆን ሙከራ ቡድን ሁለት ከ 0.51 — 1.00 ውስጥ በመሆኑ ቅድመ እና ድህረልምምድ መካከለኛ ልዩነት ጥንካሬ ደረጃ እንዳቸው አሳይቷል።

አራተኛው ትኩረት በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ማካካስ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ነው። ከዚህ በታች የቀረበው ሰንጠረዥ ይህንኑ ያመላክታል።

ሰንጠረዥ *ዘጠኝ*፦ መሐራ ቡድን አንድ እና መሐራ ቡድን ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ማካካስ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም

ተላውጦዎች	መሐራ ቡድን	የተማሪ ቁጥር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	መደበኛ አማካይ ስህተት	የቲ ዋጋ	የነፃነት ደረጃ	ጉልህነት (ሁለትዮሽ አመልካች)
አማርኛ ቅድመ ልምምድ	አንድ	73	3.198	1.01	.118	-1.321	72	.191
ድህረ ልምምድ			3.397	.726	.085			
	ሁለት	69	3.275	.897	.108	-3.499	68	.001
			3.731	.889	.107			
ሶማልኛ ቅድመ ልምምድ	አንድ	73	3.301	1.12	.131	-1.180	72	.242
ድህረ ልምምድ			3.50	.816	.095			
	ሁለት	69	3.202	.924	.111	-1.807	68	.075
			3.46	.810	.097			

በየቋንቋው ያለውን ማካካስ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም በተመለከተ ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እንዳመላከተው በአማርኛ ቋንቋ ቅድመልምምድ መሐራ ቡድን አንድ 3.198 መሐራ ቡድን ሁለት 3.275 በሶማልኛ መሐራ ቡድን አንድ 3.301 መሐራ ቡድን ሁለት 3.202 አማካይ ያስመዘገቡ ሲሆን ድህረ ልምምድም በአማርኛ ቋንቋ መሐራ ቡድን አንድ 3.397 መሐራ ቡድን ሁለት 3.731 በሶማልኛ ቋንቋ መሐራ ቡድን አንድ 3.50 መሐራ ቡድን ሁለት 3.463 አማካይ አስመዝግበዋል። በአማርኛ ቅድመ እና ድህረልምምድ አማካይ ልዩነት መሐራ ቡድን አንድ -.199 መሐራ ቡድን ሁለት .456 ሲሆን በሶማልኛ መሐራ ቡድን አንድ -.199 መሐራ ቡድን ሁለት -.258 እንደሆነ ያሳያል።

በየቋንቋው የሁለቱም ቡድኖች ቅድመ እና ድህረልምምድ ማካካስ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ጉልህ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የተሰላው አሀዝ እንዳመላከተው የቲ-ዋጋ በአማርኛ ቋንቋ መሐራ ቡድን አንድ -1.321 መሐራ ቡድን ሁለት -3.499 በሶማልኛ ቋንቋ መሐራ ቡድን አንድ -1.180 መሐራ ቡደን ሁለት -1.807 ነው። ሁለትዮሽ ጉልህ ልዩነት አሀዛዊ መረጃው (sig/p value) ሲታይ በአማርኛ ቋንቋ መሐራ

ቡድን አንድ .191 መካራ ቡድን ሁለት ደግሞ .001 ሲሆን በሶማልኛ መካራ ቡድን አንድ .242 መካራ ቡድን ሁለት .075 እንደሆነ ያሳያል። ማካካስ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ቅድመ እና ድህረልምምድ ጉልህ ልዩነት አመካላች አሀዝ በአማርኛ ቋንቋ መካራ ቡድን አንድ እና በሶማልኛ ቋንቋ ሁለቱም የመካራ ቡድኖች ከ0.05 በላይ (>0.05) በመሆናቸው በቅድመ እና ድህረልምድ አጠቃቀም መካከል ጉልህ ልዩነት የሌለ መሆኑን ያመላክታል። በአማርኛ ቋንቋ መካራ ቡድን ሁለት ጉልህ ልዩነት አመላካች ከ0.05 በታች (<0.05) በመሆኑ ቅድመ እና ድህረልምምድ አጠቃቀም ሲነፃፀር ጉልህ ልዩነት እንዳለ አሳይቷል።

ከላይ በቀረበው ትንተና አንደተገለፀው በአማርኛ ቋንቋ መካራ ቡድን አንድ እና በሶማልኛ ቋንቋ ሁለቱም የመካራ ቡድኖች ቅድመ እና ድህረልምምድ ማካካስ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ጉልህ ልዩነት ያላሳዩ በመሆናቸው የልዩነት ጥንካሬ ደረጃውን መስራት አላስፈለገም። በአማርኛ ቋንቋ መካራ ቡድን ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ ማካካስ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ጉልህ ልዩነት ያሳየ በመሆኑ የልዩነት ጥንካሬ ደረጃውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው። ይህን ለማረጋገጥ የልዩነት ጥንካሬ ደረጃ ማረጋገጫ ስሌት ሲታይ በአማርኛ መካራ ቡድን ሁለት .5109 መሆኑን ያመላክታል። በተሰላው አሀዝ መሰረት መካራ ቡድን ሁለት በአማርኛ ቋንቋ ማካካስ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ጉልህ ልዩነት ጥንካሬ ደረጃ ከ 0.51—1.00 በመሆኑ በቅድመ እና ድህረልምምድ መካከል ያለው ልዩነት መካከለኛ ጥንካሬ ደረጃ እንደሆነ አሳይቷል።

አምስተኛው ንዑስ የማንበብ ብልሃት ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት ነው። ከዚህ በታች የቀረበው ሰንጠረዥ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀምን ያሳያል።

ሰንጠረዥ *አስር፦* **መካራ ቡድን አንድ እና መካራ ቡድን ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም**

ተላውጦዎች	መካራ ቡድን	የተማሪ ቁጥር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	መደበኛ አማካይ ስህተት	የቲ ዋጋ	የነፃነት ደረጃ	ጉልህነት (ሁለትዮሽ አመልካች)
አማርኛ ቅድመ ልምምድ	አንድ	73	3.174	.560	.065	-5.549	72	.011
ድህረ ልምምድ	ሁለት	69	3.661	.645	.075			
			3.696	.684	.082	-4.710	68	.000
			3.869	.560	.067			
ሶማልኛ ቅድመ ልምምድ	አንድ	73	3.267	.668	..078	-4.352	72	.000
ድህረ ልምምድ	ሁለት	69	3.832	.773	.090			
			3.529	.666	.080	-3.768	68	.000
			3.909	.567	.068			

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ መሰረት በአማርኛ ቋንቋ ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ቅድመልምምድ መካራ ቡድን አንድ 3.174 መካራ ቡድን ሁለት 3.275 በሶማልኛ ቋንቋ መካራ ቡድን አንድ 3.267 መካራ ቡድን ሁለት 3.529 አማካይ አስመዝግበዋል። ድህረ ልምምድ በአማርኛ ቋንቋ መካራ ቡድን አንድ 3.661 መካራ ቡድን ሁለት 3.869 በሶማልኛ ቋንቋ መካራ ቡድን አንድ 3.832 መካራ ቡድን ሁለት 3.909 አማካይ አስመዝግበዋል። በየቋንቋው በሁለቱም ቡድኖች ቅድመ እና ድህረልምምድ ያለው አማካይ ልዩነት በአማርኛ መካራ ቡድን አንድ -.486 መካራ ቡድን ሁለት -0.173 ሲሆን በሶማልኛ መካራ ቡድን አንድ .565 መካራ ቡድን ሁለት -.380 ነው።

በየቋንቋው ሁለቱን የመካራ ቡድኖች ቅድመ እና ድህረልምድ ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩ ሲታይ በአማርኛ ቋንቋ የቲ-ዋጋ መካራ ቡድን አንድ -5.549 መካራ ቡድን ሁለት -4.710 በሶማልኛ ቋንቋ መካራ ቡድን አንድ -4.352 መካራ ቡደን ሁለት -3.768 ሲሆን ሁለትዮሽ ጉልህ ልዩነት አመላካቹ (sig/p value) በአማርኛ ቋንቋ መካራ ቡድን አንድ .011 መካራ ቡድን

ሁለት .000 ያስመዘገቡ ሲሆን በሶማልኛ ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት .000 አስመዝግበዋል። ይህ የተሰላ አሃዝ እንደሚያመላክተው በአማርኛም ሆነ በሶማልኛ ቋንቋ ሁለቱም የሙከራ ቡድኖች ጉልህነት አመላካች አሀዛዊ መረጃው ከ 0.05 በታች (<0.05) በመሆኑ በቅድመ እና ድህረልምምድ መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት መኖሩን አመላክቷል።

ከላይ ጉልህነትን ያንፀባረቀው ትንታኔ ጉልህነትን እንጂ የጉልህነትን ጥንካሬ ደረጃ አላመላከተም። ይህን ለማረጋገጥ የተሰላው አሀዝ በ Cohen`s d የልዩነት ጥንካሬ ደረጃ ማረጋገጫ ስሌት ሲታይ በአማርኛ ቋንቋ ሙከራ ቡድን አንድ -.808 ሙከራ ቡድን ሁለት -0.278 ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ ደግሞ ሙከራ ቡድን አንድ .784 ሙከራ ቡድን ሁለት -.616 መሆኑን ያመላክታል። ቅድመ እና ድህረልምምድ ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም የልዩነት ጥንካሬ ደረጃ በአማርኛ ሙከራ ቡድን ሁለት 0—0.20 ወሰን ውስጥ በመሆኑ ዝቅተኛ ሲሆን የተቀሩት በአማርኛ ሙከራ ቡድን አንድ እና በሶማልኛ ሁለቱም የሙከራ ቡድኖች ከ 0.51 —1.00 ባለው ወሰን ውስጥ በመሆናቸው መካከለኛ ጉልህ ልዩነት ጥንካሬ ደረጃ እንዳላቸው አመላክቷል።

ከላይ የቀረበው ትንታኔ እንዳመላከተው ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ቅድመልምምድ በሁለቱም ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤያቸው ልዩነት የሌለው (የችሎታ መበላለጥ የሌለ) መሆኑ ተረጋግጧል። ጥናቱ ትኩረት ያደረገባቸው የማንበብ ብልሃቶች (አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ፣ ትውስታ፣ ማካካስ እና ማህበርዊ የማንበብ ብልሃቶች) አጠቃቀም ቅድመልምምድ ከድህረልምምድ አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀር የተገኘው ውጤት ያመላከተው ሁለቱም የሙከራ ቡድኖች በተለይ አእምሮታዊ ፣ ልእለአእምሮታዊ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃቶችን ጉልህ በሆነ መልኩ ያጎለበቱ መሆናቸውን ነው። በተገኘው ውጤት መሰረት በአማርኛ ቋንቋ ሙከራ ቡድን ሁለት ልእለአእምሮታዊ፣ ሁለቱም የሙከራ ቡድኖች በአማርኛ ትውስታ፣ ሙከራ ቡድን አንድ በአማርኛ እና ሁለቱም የሙከራ ቡድኖች በሶማልኛ ቋንቋ ማካካስ የማንበብ ብልሃት ቅድመ እና ድህረልምምድ ያለው አጠቃቀም ሲነፃፀር ዝቅተኛ አፈፃፀም (ኢ-ጉልህ) እንዳላቸው ግኝቱ አመላክቷል።

የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በአምስቱ ንኡሳን የማንበብ ብልሃቶች ውስጥ የሚካተቱትን ሁሉንም የማንበብ ብልሃቶች ቅድመ እና ድህረልምምድ አጠቃቀም ምን እንደሚመስል የሚከተለው ሰንጠረዥ ያመላክታል (በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት የተሰራ)፡፡

ሰንጠረዥ *አሰራሰንድ፦* መከራ ቡድን አንድ እና መከራ ቡድን ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ሁሉንም የማንበብ ብልሃቶች አጠቃቀም የሚያሳይ

ተላውጦዎች	መከራ ቡድን	የተማሪ ቁጥር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	መደበኛ አማካይ ስህተት	የቲ ዋጋ	የነፃነት ደረጃ	ጉልህነት (ሁለትዮሽ አመልካች)
አማርኛ ቅድመ ልምምድ ድህረ ልምምድ	አንድ	73	3.219 3.822	.334 .365	.039 .042	-10.638	72	.000
	ሁለት	69	3.273 3.596	.451 .369	.054 .044	-4.398	68	.011
ሶማልኛ ቅድመ ልምምድ ድህረ ልምምድ	አንድ	73	3.275 3.709	.289 .346	.033 .040	-7.910	72	.000
	ሁለት	69	3.364 3.935	.275 .215	.033 .025	-14.714	68	.000

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ መከራ ቡድን አንድ እና መከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ሁሉንም የማንበብ ብልሃቶች አጠቃቀም ግንዛቤያቸው ሲታይ በሁሉቱም ቋንቋ ጉልህ ልዩነት አመላካች ከ0.05 በታች (<0.05) በመሆኑ ድህረልምምድ ጉልህ የሆነ የባህሪ ለውጥ ማምጣታቸውን ያመላክታል፡፡ ይህ ግኝት የሚያሳየው በመከራ ቡድኖች ውስጥ የተሳተፉ ተተኳሪ ተማሪዎች ድህረልምምድ በተወሰኑ ንኡሳን የማንበብ ብልሃቶች ኢ-ጉልህ አፈፃፀም የታየባቸው ቢሆንም በአማርኛም ሆነ በሶማልኛ ቋንቋ ከሁሉም የማንበብ ብልሃቶች አጠቃቀም እውቀት አንፃር ሲታይ ከፍተኛ ለውጥ ማስመዝገባቸውን ነው፡፡

ከላይ የቀረበው ትንተና መከራ ቡድን አንድ እና መከራ ቡድን ሁለት በተናጠል በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀማቸው ምን ገፅታ እንዳለው የሚያመላክት ነው፡፡ ከዚህ በታች የቀረበው አሃዛዊ መረጃ ሁለቱ የመከራ ቡድኖች

የማንበብ ብልሃት አጠቃቀማቸው ሲነፃፀር ምን ገፅታ እንዳለው የሚያንፀባርቅ ነው። ንፅፅሩ ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ውጤታቸው ላይ የተመሰረተ ነው። (ትንተናው በነፃ ናሙና ቲ-ቴስት የተሰራ ነው) ።

ሰንጠረዥ አስራሁለት፡- *መ*ከራ ቡድን አንድ እና *መ*ከራ ቡድን ሁለት ድህረልምምድ በአምርኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ንፅፅር

							የአማካይ እኩልነት መፈተሻ ቲ-ቴስት t-test for equality of means	
ተላውጦዎች		መ*ከ*ራ ቡድን	የተማሪ ቁጥር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	መደበኛ አማካይ ልይይት	የነፃነት ደረጃ	ጉልህነት (ሁለትዮሽ አመላካች
እእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት	ተጠባቂ የልይይት አቻዊነት Equal variance assumed	አንድ ሁለት	73 69	4.06 3.59	.405 .471	.047 .056	140	.000
ልዕለእእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት	ተጠባቂ የልይይት አቻዊነት	አንድ ሁለት	73 69	3.71 3.40	.593 .588	.069 .070	140	.002
ትውስታ የማንበብ ብልሃት	ተጠባቂ የልይይት አቻዊነት	አንድ ሁለት	73 69	3.40 3.54	.658 .610	.077 .073	140	.183
ማካካስ የማንበብ ብልሃት	ተጠባቂ የልይይት አቻዊነት	አንድ ሁለት	73 69	3.39 3.73	.726 .889	.085 .107	140	.015
ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት	ተጠባቂ የልይይት አቻዊነት	አንድ ሁለት	73 69	3.66 3.86	.645 .560	.075 .067	140	.042
ሁሉም የማንበብ ብልሃት	ተጠባቂ የልይይት አቻዊነት	አንድ ሁለት	73 69	3.82 3.59	.365 .369	.042 .044	140	.000

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ *መ*ከራ ቡድን አንድ እና *መ*ከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ ቋንቋ ድህረልምምድ አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ፣ ትውስታ፣ ማህበራዊ እና ሁሉም የማንበብ ብልሃቶች አጠቃቀም ተጠባቂ የልይይት አቻዊነትን የሚያሳይ ነው። ይኸውም ድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም አማካይ *መ*ከራ ቡድን አንድ አእምሮታዊ 4.06 ፣ ልእለአእምሮታዊ 3.71 ፣ ትውስታ 3.40 ፣ ማካካስ 3.39 ፣ ማህበራዊ 3.66 እና ሁሉም የማንበብ ብልሃት 3.82 ሲሆን *መ*ከራ ቡድን ሁለት አእምሮታዊ 3.59፣ ልእለአእምሮታዊ 3.40፣ ትውስታ 3.54፣ ማካካስ 3.73፣ ማህበራዊ 3.86 እና ሁሉም የማንበብ ብልሃት 3.59 *መ*ሆኑን ያሳያል። *መ*ከራ ቡድኖቹ ድህረልምምድ የማንበብ

ብልሃት አጠቃቀም ጉልህ ልዩነት አመላካች አሀዝ እንደሚያሳየው አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ፣ ማካካስ ፣ ማህበራዊ እና ሁሉም የማንበብ ብልሃት ከ 0.05 በታች (<0.05) በመሆናቸው መካራ ቡድኖቹ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀማቸው ጉልህ ልዩነት እንዳለ ያሳየ ሲሆን ትውስታ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከ 0.05 በላይ (>0.05) በመሆኑ መካራ ቡድኖቹ የብልሃቱ አጠቃቀም ጉልህ ልዩነት ያልታየባቸው መሆኑን አመላክቷል።

ሰንጠረዥ አስራሶስት ፦ መካራ ቡድን አንድ እና መካራ ቡድን ሁለት ድህረልምምድ በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀማቸው ንፅፅር

							የአማካይ እኩልነት መፈተሻ ቲ-ቴስት t-test for equality of means	
ተላውጦዎች		መካራ ቡድን	የተማሪ ቁጥር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	መደበኛ አማካይ ልይይት	የነፃነት ደረጃ	ጉልህነት (ሁለትዮሽ አመላካች
እእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት	ተጠባቂ የልይይት አቻዊነት Equal variance assumed	አንድ ሁለት	73 69	3.77 4.09	.412 .339	.048 .040	140	.000
ልዕለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት	ተጠባቂ የልይይት አቻዊነት	አንድ ሁለት	73 69	3.49 3.70	.564 .476	.066 .057	140	.017
ትውስታ የማንበብ ብልሃት	ተጠባቂ የልይይት አቻዊነት	አንድ ሁለት	73 69	3.63 3.90	.626 .663	.073 .079	140	.013
ማካካስ የማንበብ ብልሃት	ተጠባቂ የልይይት አቻዊነት	አንድ ሁለት	73 69	3.50 3.46	.816 .810	.095 .097	140	.791
ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት	ተጠባቂ የልይይት አቻዊነት	አንድ ሁለት	73 69	3.83 3.90	.773 .567	.090 .068	140	.501
ሁሉም የማንበብ ብልሃት	ተጠባቂ የልይይት አቻዊነት	አንድ ሁለት	73 69	3.70 3.93	.346 .215	.040 .068	140	.000

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዝ መካራ ቡድን አንድ እና መካራ ቡድን ሁለት በሶማልኛ ቋንቋ ድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ተጠባቂ እና ኢ-ተጠባቂ የልይይት አቻዊነት ሲታይ መካራ ቡድን አንድ አማካይ አእምሮታዊ 3.77፣ ልእለአእምሮታዊ 3.49 ፣ ትውስታ 3.63፣ ማካካስ 3.50፣ ማህበራዊ 3.83 እና ሁሉም የማንበብ ብልሃት 3.70 ሲሆን መካራ ቡድን ሁለት አእምሮታዊ 4.09፣ ልእለአእምሮታዊ 3.70፣ ትውስታ

3.90፣ ማካካስ 3.46፣ ማህበራዊ 390 እና ሁሉም የማንበብ ብልሃት 3.93 መሆኑን ያሳያል። መካራ ቡድኖቹ ድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ እና ትውስታ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ጉልህ ልዩነት አመላካች አሀዝ ከ 0.05 በታች (<0.05) በመሆኑ በመካራ ቡድኖቹ መካከል የአጠቃቀም ጉልህ ልዩነት እንዳለ አሳይቷል። የተቀሩት ማካካስ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃቶች አጠቃቀም ጉልህ ልዩነት አመላካች አሀዙ ከ 0.05 በላይ (>0.05) በመሆኑ የመካራ ቡድኖቹ የአጠቃቀም ጉልህ ልዩነት እንደሌላቸው አመላክቷል። በሶማልኛ ሁሉም የማንበብ ብልሃት አጠቃቀምም ከ 0.05 በታች (<0.05) በመሆኑ በቡድኖቹ መካከል ጉልህ የአጠቃቀም ልዩነት እንዳለ አመላክቷል።

ይህ የተገኘ ውጤት የሚያመላክተው መካራ ቡድን አንድ በአማርኛ መካራ ቡድን ሁለት ደግሞ በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ በመማራቸው ምክንያት የመካራ ቡድኖቹ ከቅድመልምምድ በጎላ መልኩ በድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እውቀታቸው የጎለበተ ቢሆንም ሁለቱ የመካራ ቡድኖች ሲነፃፀሩ የብልሃት አጠቃቀም የባህሪ ለውጣቸው ፍፁም ተመሳሳይ አለመሆኑን ነው።

ከላይ የቀረበው ትንተና የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ ክፍል አንድ ውስጥ በተካተተው ሚዛናዊ የደረጃ ልኬት የተገኘው መረጃ የተተነተነበት ክፍል ነው። በዚሁ መጠይቅ ክፍል ሁለት ተተኳሪ ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የቀረበውን አጭር ምንባብ አንብበው ለመረዳት የትኞቹን የማንበብ ብልሃቶች እንደተጠቀሙ የሚያሳይ ነው።

ከዚህ በታች የቀረበው ትንተና በመጠይቁ ክፍል ሁለት የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በየቋንቋው የቀረቡላቸውን አጭር ምንባብ አንብበው ለመረዳት የተጠቀሙባቸውን የማንበብ ብልሃቶች የሚያሳይ ነው። (መረጃው በድግግሞሽ እና መቶኛ የተሰላ ነው)።

በሰንጠረዡ ቁጥር 1. ርእሱን በማየት የምንባቡን ሀሳብ እተነብያለሁ 2 .ምንባቡን ለማንበብ አቅዳለሁ 3. የምንባቡን ሀሳብ በፍጥነት ለማግኘት እጥራለሁ 4 .ማስታወሻ እይዛለሁ 5. ደጋግሜ አነባለሁ 6. ጥያቄ እጠይቃለሁ 7. የቀደመ እውቀቴን እጠቀማለሁ 8. በማነብበት ወቅት አንብቦ መረዳትን እና ራሴን እቆጣጠራለሁ 9. አውዳዊ ፍቺ እጠቀማለሁ 10.የቃላትን ፍቺ እገምታለሁ 11. የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገርኩ እጠቀማለሁ 12.ከተማሪዎች ጋር እተባበራለሁ የሚለውን ይገልፃል።

ሰንጠረዥ አስራአራት፡- *መ*ከራ ቡድን አንድ እና መከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ ቋንቋ ቅድመ እና ድህረልምምድ የቀረበውን ምንባብ አንብበው ለመረዳት የተጠቀሙበትን የማንበብ ብልሃት የሚያሳይ

ተ.ቁ	አማርኛ								ሶማልኛ							
	መከራ ቡድን አንድ				መከራ ቡድን ሁለት				መከራ ቡድን አንድ				መከራ ቡድን ሁለት			
	ቅድመ ልምምድ		ድህረ ልምምድ		ቅድመ ልምምድ		ቅድመ ልምምድ		ቅድመ ልምምድ		ድህረ ልምምድ		ቅድመ ልምምድ		ድህረ ልምምድ	
	ድ	%	ድ	%	ድ	%	ድ	%	ድ	%	ድ	%	ድ	%	ድ	%
1	2	2.7	13	17.8	5	7.2	18	26	3	4.1	13	17.8	-		11	15.9
2	-		-		-		4	5.7	-	-	-	-	-		-	-
3	-		7	9.58	-		22	30.1	-		4	5.4	-		13	18.8
4	6	8.21	15	20.5	-		14	20.2	3	4.1	26	38.3	4	5.7	16	23.1
5	-		17	23.2	2	2.8	30	3.4	4	5.4	18	24.6	6	8.9	21	30.4
6	5	6.84	22	30.1	1	1.4	27	39.1	-		20	27.3	7	10	22	31.8
7	-		-		-		-		-						6	8.6
8	-		31	42.4	-		12	17.3	-						30	43.4
9	-		-		-		-		-						19	27.5
10	-		17	23.2	-		6	8.6	-		16	21.9				
11	-		14	19.1	-		9	13	-		18	24.6			11	
12	-		-		-		-		-		8	10.				

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በሁለቱም ቋንቋ ቅድመ እና ድህረልምምድ ለማንበብ ተግባር የቀረበላቸውን ምንባብ አንብበው ለመረዳት የማንበብ ብልሃቶችን በተለያየ የድግግሞሽ ደረጃ እንደተጠቀሙ ያንፀባርቃል፡፡ አሀዛዊ መረጃው እንደሚያመላክተው ተተኳሪ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ መከራ ቡድን አንድ ቅድመልምምድ ማስታወሻ መያዝ (8.21%)፣ ጥያቄ እጠይቃለሁ (6.84%)፣ ርእሱን በማየት የምንባቡን ሀሳብ እተነብያለሁ (2.7%) የተባሉ የማንበብ ብልቶችን የተጠቀሙ ሲሆን መከራ ቡድን ሁለት ርእሱን በማየት የምንባቡን ሀሳብ እተነብያለሁ (7.2%)፣ ደጋግሜ አነባለሁ (2.8%) እና ጥያቄ እጠይቃለሁ (1.4%) የተባሉ የማንበብ ብልሃቶችን ተጠቅመዋል፡፡ በሶማልኛ ቋንቋ ያለው ገፅታ ሲታይ መከራ ቡድን አንድ ደጋግሜ አነባለሁ (5.4%) ርእሱን በማየት የምንባቡን ሀሳብ እተነብያለሁ እና ማስታወሻ

እይዛለሁ (4.1%) የተባሉትን የማንበብ ብልሃቶች በድግግሞሽ የተጠቀሙ ሲሆን ሙከራ ቡድን ሁለት ጥያቄ እጠይቃለሁ (10%)፣ ደጋግሜ አነባለሁ (8.9%) እንዲሁም ማስታወሻ እይዛለሁ (5.7%) የተባሉ የማንበብ ብልሃት ተጠቅመዋል። አሃዛዊ መረጃው ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛም ሆነ መሶማልኛ ቋንቋ ቅድመልምምድ ጉልህ በሆነመልኩ በድግግሞሽ የማንበብ ብልሃቶችን አለመጠቀማቸውን ያሳያል።

ድህረልምምድ ለማንበብ ተግባር የቀረበውን ምንባብ አንብበው ለመረዳት የተጠቀሙበት የማንበብ ብልሃት ሲታይ በአምርኛ ቋንቋ ሙከራ ቡድን አንድ በማንበብ ወቅት ራሴን እቆጣጠራለሁ (42.4%)፣ ጥያቄ እጠይቃለሁ (30.1%)፣ ደግሜ (ደጋግሜ) አነባለሁ (23.2%) ሙከራ ቡድን ሁለት ደግሜ አነባለሁ (43.4%)፣ ጥያቄ እጠይቃለሁ (39.1%) እና የምንባቡን ሀሳብ በፍጥነት ለማግኘት እጥራለሁ (31.8%) የተባሉትን የማንበብ ብልሃቶች በድግግሞሽ የበለጠ እንደተጠቀሙባቸው ያመላክታል። በሶማልኛ ቋንቋም እንዲሁ ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ቅድመልምምድ ጉልህ በሆነ መልኩ በድግግሞሽ የተጠቀሙበት የማንበብ ብልሃት ባለመጠቀሱ የማንበብ ብልሃት ግንዛቤያቸው ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል። ነገር ግን በዚሁ ቋንቋ ድህረልምምድ ሙከራ ቡድን አንድ ማስታወሻ መያዝ (35.6%)፣ ጥያቄ መጠየቅ (27.3%)፣ የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገርኩ እጠቀማለሁ (24.6%) ሙከራ ቡድን ሁለት ደግሞ በማንበብ ወቅት ራሴን እና አንብቦ መረዳቴን እቆጣጠራለሁ (43.4%)፣ ጥያቄ እጠይቃለሁ (31.8%) እና ደጋግሜ አነባለሁ (30.4%) የተባሉ የማንበብ ብልሃቶችን በድግግሞሽ መጠቀማቸውን ያመላክታል። የተሰላው አሃዛዊ መረጃ እንደሚያሳየው የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች ከቅድመልምምድ በጎላ መልኩ ድህረልምምድ የማንበብ ብልሃቶችን እንደተጠቀሙ ያሳያል።

የጥናቱ ጥያቄ ቁጥር ሁለት፡- የማንበብ ብልሃቶችን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከቅድመልምምድ በተሻለ በድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃት እንዲጎለብት ምን ያህል አስተዋፆ አለው?

አንብቦ መረዳት የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ ነው። በጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ በመማራቸው በየቋንቋው አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው መጎልበት አለመጎልበቱ ተፈትሿል። በምእራፍ ሶስት እንደተገለፀው አንድ

ጥብቅ እና ሁለት የሙከራ ቡድኖች በጥናቱ ተሳትፈዋል። እነዚህ የሙከራ እና ጥብቅ ቡድኖች ቅድመ እና ድህረልምምድ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው ምን እንደሚመስል ከማየት አስቀድሞ ሶስቱ ቡድኖች ቅድመልምምድ ያላቸው አንብቦ የመረዳት የብቃት እኩል ደረጃ ላይ ያለ መሆን አለመሆኑን ማየቱ ተገቢ ነው። ይህን ለማጤን በጥናቱ የልይይት ትንተና (Analysis of Variance / ANOVA) አገልግሎት ላይ ውሏል።

በጥናቱ የልይይት ትንተና ውጤት በሶስቱ ቡድኖች መካከል ቅድመልምምድ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ጉልህነት አመልካች መስፈርት .178 ሲሆን በሶማልኛ ደግሞ .183 ነው። ይህ የተሰላ አሀዝ ከመደበኛ ጉልህነት አመልካች መስፈርት 0.05 (sig/p value) በላይ(<0.05) በመሆኑ ቅድመልምምድ በሶስቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ በሆነ መልኩ አንብቦ የመረዳት ብቃት ልዩነት አለመኖሩን ያመላክታል (ሙሉ መረጃው በሰንጠረዥ አስራስድስት ላይ ተመላክቷል) ።

በመቀጠል እያንዳንዱ ቡድን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃት ከቅድመልምምድ ውጤት ጋር ሲነፃፀር በድህረልምምድ ያሳየው የባህሪ ለውጥ ምን እንደሚመስል በተናጠል ታይቷል። ከዚህ በታች የቀረቡት ሰንጠረዦች በሙከራ ቡድኖች ውስጥ የተሳተፉ ተተኳሪ ተማሪዎች በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ በመማራቸው እና ሙከራ ቡድኑ በተለመደው መንገድ ትምህርቱን የተከታተለ በመሆኑ (የማንበብ ብልሃትን ሆን ብሎ በግልፅ ሳይማር) በሁለቱም ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው መጎልበት አለመጎልበቱን የሚያመላክቱ ናቸው (አሀዛዊ መረጃው በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት የተሰላ ነው)።

ሰንጠረዥ አስራአምስት፡- *መ*ከራ ቡድን አንድ፣ *መ*ከራ ቡድን ሁለት እና ጥብቅ ቡድን ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸውን የሚያሳይ

ተላውጦዎች	መከራ ቡድን	የተማሪ ቁጥር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	መደበኛ አማካይ ስህተት	የቲ ዋጋ	የነፃነት ደረጃ	ጉልህነት (ሁለትዮሽ አመልካች)
በአማርኛ አንብቦ መረዳት ቅድመ ልምምድ ድህረ ልምምድ	አንድ	73	5.01 9.37	1.712 1.368	.200 .160	-16.813	72	.000
	ሁለት	69	4.55 8.51	1.694 1.290	.204 .155	-17.111	68	.000
	ጥብቅ ቡድን	66	4.76 5.97	.824 1.607	.101 .198	-5.837	65	.000
በሶማልኛ አንብቦ መረዳት ቅድመ ልምምድ ድህረ ልምምድ	አንድ	73	6.37 9.70	2.247 1.468	. 287 .17	-9.507	70	. 000
	ሁለት	69	6.25 9.36	1.613 1.590	.194 .191	-11.625	68	. 000
	ጥብቅ ቡድን	66	6.98 7.83	1.827 2.692	.225 2.692	-2.613	65	.011

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚያንፀባርቀው በአማርኛ ቋንቋ ቅድመልምምድ አንብቦ የመረዳት ብቃት መከራ ቡድን አንድ 5.01 መከራ ቡድን ሁለት 4.55 ጥብቅ ቡድን 4.76 ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ መከራ ቡድን አንድ 6.37 መከራ ቡድን ሁለት 6.25 ጥብቅ ቡድን 6.98 አማካይ አስመዝግበዋል፡፡ በተመሳሳይ ድህረልምምድ መከራ ቡድን አንድ 937 መከራ ቡድን ሁለት 8.51 ጥብቅ ቡድን 5.97 አማካይ ያስመዘገቡ ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ ደግሞ መከራ ቡድን አንድ 9.70 መከራ ቡድን ሁለት 9.36 ጥብቅ ቡድን 7.83 አማካይ አስመዝግበዋል፡፡ በየቋንቋው ሁለቱ ቡድኖች ቅድመ እና ድህረ ልምምድ አንብቦ መረዳት ያላቸው አማካይ ልዩነት በአማርኛ ቋንቋ መከራ ቡድን አንድ -4.36 መከራ ቡድን ሁለት -3.96 ጥብቅ ቡድን -1.21 ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ የአማካይ ልዩነት መከራ ቡድን አንድ -3.33 መከራ ቡድን ሁለት -3.116 ጥብቅ ቡድን -.85 ነው፡፡

የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ቅድመ እና ድህረልምምድ ያላቸው አንብቦ የመረዳት ብቃት ልዩነት ጉልህ መሆን አለመሆኑ ሲታይ መከራ ቡድን አንድ የቲ-ዋጋ -16.813 ሁለትዮሽ ጉልህ ልዩነት አሀዛዊ ስሌት (sig/p value) .000 መከራ ቡድን ሁለት የቲ-ዋጋ -17.111 ሁለትዮሽ ጉልህ ልዩነት አሀዛዊ ስሌት .000 ጥብቅ ቡድን የቲ-ዋጋ -5.837 ሁለትዮሽ ጉልህ ልዩነት አሀዛዊ ስሌት .000 ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ ደግሞ መከራ ቡድን አንድ የቲ-ዋጋ -9.507 ሁለትዮሽ ጉልህ ልዩነት አሀዛዊ ስሌት .000 መከራ ቡድን ሁለት የቲ-ዋጋ -11.625 ሁለትዮሽ ጉልህ ልዩነት አሀዛዊ ስሌት .000 ጥብቅ ቡድን የቲ-ዋጋ -2.613 ሁለትዮሽ ጉልህ ልዩነት አሀዛዊ ስሌት .011 መሆኑን ያሳያል። በየቋንቋው ሁለትዮሽ ጉልህ ልዩነት አሀዛዊ መረጃው ከ0.05 በታች (<0.05) በመሆኑ በቅድመ እና ድህረልምምድ መካከል አሀዛዊ ጉልህ ልዩነት ያለ መሆኑን ያመላክታል።

በሰንጠረዡ የተንፀባረቀው አማካይ እና የአማካይ ልዩነት በየቋንቋው የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ቅድመ እና ድህረልምምድ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው በምን ያህል የጥንካሬ ደረጃ ልዩነት እንዳላቸው አያመላክትም። ይህን ለማረጋገጥ የተሰላ አሀዛዊ መረጃው በ Conen`s d የልዩነት ጥንካሬ ደረጃ ስሌት ሲጤን የሚያመላክተው በአማርኛ ቋንቋ መከራ ቡድን አንድ -2.83 መከራ ቡድን ሁለት -2.654 ጥብቅ ቡድን -0.995 ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ መከራ ቡድን አንድ -1.792 መከራ ቡድን ሁለት -1.942 ጥብቅ ቡድን 0.376 መሆኑን ያንፀባርቃል። ከዚህ በመነሳት በአማርኛ ቋንቋ የመከራ ቡድን አንድ እና ሁለት የተሰላው አሀዝ ከ1.00 በላይ (>1.00) የሚያመላክት በመሆኑ ጉልህ ልዩነት ደረጃው ጠንካራ (strong) ሲሆን ጥብቅ ቡድኑ ከ 0.51-1.00 ወሰን ውስጥ በመሆኑ ጉልህ ልዩነት ደረጃው መካከለኛ (moderate) ነው። በሶማልኛ ቋንቋም መከራ ቡድን አንድ እና ሁለት ቅድመ እና ድህረልምምድ አንብቦ የመረዳት ውጤት ሲነፃፀር የልዩነት ጥንካሬ ደረጃ መደበኛ ልኬት ከ1.00 በላይ (>1.00) በመሆኑ የጉልህ ልዩነት ጥንካሬ ደረጃው ጠንካራ (strong) ሲሆን ጥብቅ ቡድኑ ከ 0.21-0.50 ወሰን ውስጥ በመሆኑ ቅድመ እና ድህረልምምድ አንብቦ መረዳት መጠነኛ (modest) ጉልህ ልዩነት ጥንካሬ ደረጃ እንዳለው አመላክቷል።

ከላይ የቀረበው ትንተና ያንፀባረቀው መከራ ቡድን አንድ፣ መከራ ቡድን ሁለት እና ጥብቅ ቡድን በተናጠል በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ቅድመ እና ድህረልምምድ አንብቦ

የመረዳት ብቃታቸው ምን እንደሚመስል ነው፡፡ እነዚህ ሶስት የጥናቱ ተተኳሪ ቡድኖች በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው ሲነፃፀር ምን ገፅታ እንዳለው ማየት ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ በታች የቀረበው ሰንጠረዥ ይህንኑ ያመላክታል፡፡ አሀዛዊ መረጃው በልይይት ትንተና (ANOVA) የተሰላ ነው፡፡

ሰንጠረዥ አስራስድስት ፡- *መ*ከራ ቡድን አንድ፣ መከራ ቡድን ሁለት እና ጥብቅ ቡድን ቅድመ እና ድህረልምምድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸውን በንፅፅር የሚያሳይ

ተላውጦዎች		የካሬ ድምር	የነፃነት ደረጃ	የአማካይ ካሬ	የኤፍ ዋጋ	ጉልህነት
ቅድመ ልምምድ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ብቃት	በቡድኖች መካከል	7.647	2	3.823	1.741	.178
	በቡድኖች ውስጥ	450.180	205	2.196		
	አጠቃላይ	457.827	207			
ድህረ ልምምድ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ብቃት	በቡድኖች መካከል	302.618	2	151.309	74.592	.000
	በቡድኖች ውስጥ	415.839	205	2.028		
	አጠቃላይ	718.457	207			
ቅድመ ልምምድ በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ብቃት	በቡድኖች መካከል	18.553	2	9.277	2.520	.083
	በቡድኖች ውስጥ	747.374	203	3.682		
	አጠቃላይ	765.927	205			
ድህረ ልምምድ በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ብቃት	በቡድኖች መካከል	134.517	2	67.258	17.355	.000
	በቡድኖች ውስጥ	794.479	203	3.876		
	አጠቃላይ	928.995	207			

ከላይ በሰንጠረዡ እንደተንፀባረቀው በአማርኛ ቋንቋ ቅድመልምምድ አንብቦ መረዳት የሶስቱ ቡድኖች የኤፍ ዋጋ (F-Value) 1.741 እና ጉልህ ልዩነት አሀዛዊ መረጃው .178 መሆኑን ያመላክታል፡፡ ጉልህ ልዩነት አመላካች አሀዛዊ መረጃው ከ0.05 በላይ (>0.05) በመሆኑ በቡድኖቹ መካከል ቅድመልምምድ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃት ጉልህ የሆነ ልዩነት እንደሌላቸው ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ በሶማልኛ ቋንቋ ቅድመልምምድ ሶስቱ የጥናቱ ተሳታፊ ቡድኖች አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው በአንድዮሽ አቅጣጫ ልይይት ትንተና ሲታይ የኤፍ ዋጋ 2.520 እና ጉልህ ልዩነት አመላካች አሀዛዊ መረጃው .083 መሆኑን ያመላክታል፡፡ ጉልህ ልዩነት አመላካች አሀዛዊ መረጃው ከ0.05

በላይ (>0.05) በመሆኑ በሶማልኛ ቋንቋም በቡድኖቹ መካከል ቅድመልምምድ አንብቦ የመረዳት ብቃት ጉልህ የሆነ ልዩነት የለም።

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚያመለክተው በሙከራ ቡድን አንድ፣ ሙከራ ቡድን ሁለት እና በጥብቅ ቡድን መካከል ድህረልምምድ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ያላቸው አማካይ ልዩነት ሲነፃፀር የኤፍ ዋጋ 74.592 ሲሆን ጉልህ ልዩን አመላካች አሀዛዊ መረጃው .000 መሆኑን ያመላክታል። ጉልህ ልዩን አመላካች አሀዛዊ መረጃው ከ 0.05 በታች (<0.05) በመሆኑ በሶስቱ ቡድኖች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ጉልህ የሆነ ልዩነት መኖሩን ያመላክታል። በተመሳሳይ ሶስቱ ቡድኖች ድህረልምምድ በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ያላቸውን ብቃት ለመለየት በተካሄደው አንድዮሽ ልይይት ትንተና ስሌት ኤፍ ዋጋ 17.355 ሲሆን ጉልህ ልዩነት አመላካች አሀዛዊ መረጃው .000 መሆኑን ያመላክታል። ጉልህ ልዩነት የሚያሳየው አሀዛዊ መረጃ ከ0.05 በታች (<0.05) በመሆኑ በሶስቱ ቡድኖች መካከል በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ጉልህ ልዩነት እንዳለ ያሳያል።

ከላይ የተሰላው አሀዛዊ መረጃ እንደሚያንፀባርቀው በሶስቱ ቡድኖች መካከል በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ቅድመልምምድ አንብቦ የመረዳት ብቃት ልዩነት የሌለው በመሆኑ ዳህራይ ንፅፅር (Post hoc) መሰራት አላስፈለገም። ከላይ እንደተገለፀው በአማርኛም ሆነ በሶማልኛ ቋንቋ ድህረልምምድ አንብቦ መረዳት በቡድኖቹ መካከል ጉልህ ልዩነት እንዳለ ቢያመላክትም የትኛው ቡድን በተለየ ጉልህ ልዩነት እዳለው የማያሳይ በመሆኑ ዳህራይ ንፅፅር (Post hoc) መሰራት አስፈልጓል።

ከዚህ በታች የቀረበው ሰንጠረዥ ሙከራ ቡድን አንድ፣ ሙከራ ቡድን ሁለት እና ጥብቅ ቡድን ድህረልምምድ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ብቃታቸው ልዩነት ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ነው (ዳህራይ ንፅፅር / Post Hoc)

ሰንጠረዥ አስራሰባት፡- መከራ ቡድን አንድ፣መከራ ቡድን ሁለት እና ጥብቅ ቡድን ድህረልምምድ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃት ልዩነትን የሚያሳይ

ተላውጦዎች	(I) መከራ ቡድን አንድ መከራ ቡድን ሁለት ጥብቅ ቡድን	(J) መከራ ቡድን አንድ መከራ ቡድን ሁለት ጥብቅ ቡድን	የአማካይ ልዩነት (I- J)	መደበኛ አማካይ ስህተት	ጉልህነት
ድህረ ልምምድ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃት	መከራ ቡድን አንድ	መከራ ቡድን ሁለት	.180	.239	.452
		ጥብቅ ቡድን	2.674	.242	.000
	መከራ ቡድን ሁለት	መከራ ቡድን አንድ	-.180	.239	.452
		ጥብቅ ቡድን	2.494	.245	.000
	ጥብቅ ቡድን	መከራ ቡድን አንድ	-2.674	.242	.000
		መከራ ቡድን ሁለት	-2.494	.245	.000

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚያመላክተው ድህረልምምድ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት መከራ ቡድን አንድ እና መከራ ቡድን ሁለት ያላቸው አማካይ ልዩነት .180 **ሲሆን ጉልህ ልዩነት አመላካች አሀዛዊ መረጃው** .452 **መሆኑን ያመለክታል። አሀዛዊ መረጃው ከ**0.05 **በላይ (>**0.05**) በመሆኑ በመከራ ቡድን አንድ እና በመከራ ቡድን ሁለት መካከል ጉልህ ልዩነት እንደሌለ ያሳያል። ሌላው ቡድን አንድ ከጥብቅ ቡድኑ አማካይ ጋር ሲነፃፀር ያስመዘገቡት የአማካይ ልዩነት** 2.674 **ሲሆን ጉልህ ልዩነት አመላካች አሀዛዊ መረጃው** .000 **መሆኑን ያሳያል። ይህም አሀዛዊ የተሰላ መረጃ ከ**0.05 **በታች (<**0.05**) በመሆኑ በመከራ ቡድን አንድ እና ጥብቅ ቡድን መካከል ጉልህ ልዩነት እዳላቸው አመላክቷል። በተመሳሳይ ቡድን ሁለት ከጥብቅ ቡድን ጋር ሲነፃፀር ያላቸው የአማካይ ልዩነት** -.180 **ሲሆን ጉልህ ልዩነት አመላካች አሀዛዊ መረጃው** .452 **መሆኑን ያሳያል። ይህም ከ**0.05 **በላይ (>**0.05**) በመሆኑ በመከራ ቡድን ሁለት እና በጥብቅ ቡድን መካከል ጉልህ ልዩነት እንደሌለ አመላክቷል። ጥብቅ ቡድን ከመከራ ቡድን አንድ እና ከመከራ ቡድን ሁለት ጋር ያለው አንብቦ የመረዳት ሁኔታ ሲነፃፀር ጉልህ ልዩነት እንዳላቸው ከላይ ተንፀባርቋል። አሀዛዊ መረጃው የሚያመላክተው መከራ ቡድን አንድ (በአማርኛ ቋንቋ) እና መከራ ቡድን ሁለት ውስጥ ያሉ የጥናቱ ተሳታፊ**

ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን የተማሩ በመሆናቸው (ሙከራ ቡድን አንድ በአማርኛ ቋንቋ፣ ሙከራ ቡድን ሁለት በሶማልኛ ቋንቋ) ሁለቱ የሙከራ ቡድኖች ከጥብቅ ቡድኑ በተሻለ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው እንደጎለበተ ያሳያል፡፡ በተለይ ሙከራ ቡድን ሁለት ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን የተከታተሉት በሶማልኛ ቋንቋ ቢሆንም ከትምህርቱ ግብአት ያገኙ በመሆናቸው ከጥብቅ ቡድኑ በተሻለ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው መጎልበቱን መረጃው አመላክቷል፡፡

ሰንጠረዥ አስራስምንት፡- ሙከራ ቡድን አንድ፣ሙከራ ቡድን ሁለት እና ጥብቅ ቡድን ድህረልምምድ በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃት ልዩነትን የሚያሳይ

ተላውጦዎች	(I) ሙከራ ቡድን አንድ	(J) ሙከራ ቡድን አንድ	የአማካይ ልዩነት (I- J)	መደበኛ አማካይ ስህተት	ጉልህነት
	ሙከራ ቡድን ሁለት	ሙከራ ቡድን ሁለት			
	ጥብቅ ቡድን	ጥብቅ ቡድን			
ድህረ ልምምድ በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃት	ሙከራ ቡድን አንድ	ሙከራ ቡድን ሁለት	.336	.331	.310
		ጥብቅ ቡድን	1.865	.334	.000
	ሙከራ ቡድን ሁለት	ሙከራ ቡድን አንድ	-.336	.331	.310
		ጥብቅ ቡድን	1.529	.339	.000
	ጥብቅ ቡድን	ሙከራ ቡድን አንድ	-.865	.334	.000
		ሙከራ ቡድን ሁለት	-1.529	.339	.000

ሙከራ ቡድን አንድ፣ ሙከራ ቡድን ሁለት እና ጥብቅ ቡድን ድህረልምምድ በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው ሲነፃጠር ጉልህ ልዩነት እንዳሳዩ ከላይ በቀረበው የልይይት አሃዛዊ ስሌት ሰንጠረዡ ውስጥ (ሰንጠረዥ ሃያ አራት) ተመላክቷል፡፡ ነገር ግን በቡድኖቹ መካከል ያለው ልዩነት በዝርዝር አልተንፀባረቀም፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ ሃያ ስድስት ዳህራይ ንፅፅር ሶስቱ ቡድኖች በዝርዝር ተነፃፅረዋል፡፡ ይኸውም በቡድኖቹ መካከል ድህረልምድ በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃት ሲነፃፀር እንደሚያመላክተው ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ያላቸው አማካይ

ልዩነት .336 ሲሆን ጉልህ ልዩነት አመላካች አሀዛዊ መረጃው .310 ያሳያል። ይህ አሀዛዊ የተሰላ መረጃ ከ0.05 በላይ (>0.05) በመሆኑ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት የለም። ሙከራ ቡድን አንድ ከጥብቅ ቡድን ያላቸው አማካይ ልዩነት 1.865 ሲሆን ጉልህ ልዩነት አመላካች የተሰላ አሀዛዊ መረጃው .000 ያመላክታል። ይህም ከ0.05 በታች (<0.05) በመሆኑ በሁለቱ ቡድኖች መካል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያመላክታል። ሙከራ ቡድን ሁለት ከጥብቅ ቡድን ጋር ያላቸው አማካይ ልዩነት 1.529 ሲሆን ጉልህ ልዩነት አመላካች የተሰላ አሀዛዊ መረጃው .000 መሆኑን ያመላክታል። ጉልህ ልዩነት አመላካቹ ከ0.05 በታች (<0.05) በመሆኑም በሙከራ ቡድን ሁለት እና ጥብቅ ቡድን መካከል ጉልህ ልዩነት አለ።

ዳህራይ ንዕዕር የተሰላ አሀዝ እንዳመላከተው ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ድህረልምምድ በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው ከጥብቅ ቡድኑ በጎላ መልኩ መሻሻሉን ያመላክታል። ከዚህ በተጨማሪ ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ርስበርስ ሲነፃፀሩ በመካከላቸው ጉልህ ልዩነት እንደሌለ የተሰላው አሀዝ አመላክቷል። ይህ ግኝት በተለይ ሙከራ ቡድን አንድ ውስጥ ያሉ ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በአማርኛ ቋንቋ የተማሩ ቢሆንም ከትምህርቱ ግብአት ያገኙ በመሆናቸው በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው ከጥብቅ ቡድኑ በተሻለ መጎልበቱን ያመላክታል።

የጥናቱ ጥያቄ ቁጥር ሶስት፡- የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከቅድመልምምድ በተሻለ በድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ብቃት ጋር ምን ያህል አዎንታዊ ዝምድና ፈጥሯል?

በዚህ ጥናት በሙከራ ቡድን አንድ እና በሙከራ ቡድን ሁለት ውስጥ የተሳተፉ ተማሪዎች በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና አንብቦ የመረዳት ብቃት መካከል ምን አይነት ዝምድና እንዳለ ለመመርመር ተሞክሯል። በምእራፍ ሶስት እንደተገለፀው የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና አንብቦ የመረዳት ብቃት ዝምድናን ለመፈተሽ ጥናቱ ህብረድህረት ትንተናን (Multiple Linear Regression) ተጠቅሟል። ህብረድህረትን ተግባራዊ ለማድረግ የዝምድና ትንተና (Analysis of Correlation Coefficient) እጅግ አስፈላጊ ነው። በጥናቱ አንብቦ መረዳት ጥገኛ ተላውጦ (ውፃት) ሲሆን የማንበብ ብልሃቶች

(አእምሮታዊ፣ ልዕለአእምሮታዊ፣ ትውስታ፣ ማካካስ እና ማህበራዊ ብልሃቶች) ደግሞ ነፃ ተላምጦዎች ወይም አመላካች (Predictors) ናቸው።

በአንድ ጥገኛ ተላውጦ እና በአንድ ወይም ከዛበላይ ነፃ ተላውጦዎች መካከል ያለውን ዝምድና በማየት ሂደት (ነፃ ተላውጦዎች በጥገኛ ተላውጦው ላይ ያሳደሩት ተፅእኖ) አዎንታዊ፣ አሉታዊ ወይም ዜሮ ዝምድና (ምንም አይነት ዝምድና የሌለው) ሊከሰት ይችላል። በህብረድህረት የተሰላ አሀዝ ወደ 1 ሲጠጋ በተላውጦዎቹ መካከል (በተንባይ እና ተተንባይ) መካከል አዎንታዊ ዝምድና መኖሩን ወይም ተንባዩ በተተንባዩ ላይ ተፅእኖ እንዳለው ያሳያል። ውጤቱ ወደ -1 ሲጠጋ ዝምድናው አሉታዊ ይሆናል። የተሰላው አሀዝ ወደዜሮ በተጠጋ ጊዜ በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ምንም አይነት ዝምድና የለም ማለት ነው (Dorneyi 2007፣ Muijs 2004)።

ከዚህ በታች የቀረቡት ሰንጠረዦች ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር ያለውን ዝምድና የሚያመላክቱ ናቸው። ስሌቱ በተተኳሪ ተማሪዎች ድህረልምምድ የአንብቦ መረዳት ውጤት እና የምንበብ ብልሃት የመተግበር ችሎታ ውጤት ላይ የተመሰረተ ነው። (በህብረድህረት የተሰላ)።

ሰንጠረዥ አስራዘጠኝ፡- ሙከራ ቡድን አንድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር ያለውን ዝምድና የሚያሳይ

ተንባይ ተላውጦዎች ለተተንባይ ተላውጦው ያላቸው አስተዋፆ እና ጉልህነት

የሞዴሉ ጭምቀ ሀሳብ

	አማርኛ	ሶማልኛ			አማርኛ	ሶማልኛ
አር	.539	.684		አር ካሬ	.408	.342
የተስተካከለ አር ካሬ	.364	.290	ተገማች	መደበኛ ስህተት	1.15623	1.15623

በድህረት ትንተናው የገቡ ተላውጦዎች እና ጉልህነት (Cofficients)

ሞዴል	መደበኛ ያልሆነ የተሰላ አሀዝ (unstandared coefficient)		መደበኛ የተሰላ አሀዝ (stunderd coefficient)							
ተላውጦዎች	ቢ		መደበኛ ስህተት		ቤታ		የቲ ዋጋ		ጉልህነት (sig value)	
	አማርኛ	ሶማልኛ	አማርኛ	ሶማልኛ	አማርኛ	ሶማልኛ	አማርኛ	ሶማልኛ	አማርኛ	ሶማልኛ
ውስን(Constant)	8.78	8.56	.850	1.02			10.33	8.39	.000	.000
አእምሮታዊ	.275	.269	.115	.116	.227	.240	2.398	2.32	.019	.023
ልዕለአእምሮታዊ	.385	.384	..157	.137	.246	.295	2.454	2.79	.017	.007
ትውስታ	-.255	-.022	.110	.113	-.227	-.021	-2.32	-.191	.023	.849
ማካካስ	.093	.081	.136	.177	.067	.047	.684	.458	.496	.649
ማህበራዊ	-.377	-.481	.097	.118	-.376	-.438	-3.876	-4.06	.000	.000
ሁሉም የማንበብ ብልሃት										
ሁሉም የማንበብ ብልሃት	.440	.298	.181	.041	.277	.041	2.328	2.428	.018	.129

የሞዴሉ ጭምቀሀሳብ ሰንጠረዥ መከራ ቡድን አንድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር ያለውን ዝምድና ያመላከተው በአማርኛ አር ካሬ .408 (40%)፣ የተስተካከለ አር ካሬ .364 (36%)፣ ተገማች መደበኛ ስህተት 1.15623 ሲሆን በሶማልኛ የአር ካሬ .342 (34%)፣ የተስተካከለ አር ካሬ .290 (29%)፣ ተገማች መደበኛ ስህተት 1.18930 መሆኑን ያሳያል።

በህብረድህረት ጉልህነት ያመላከተው ሰንጠረዥ መከራ ቡድን አንድ በአማርኛ ቋንቋ አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ያመላክታል። ይኸውም በአማርኛ የቤታ ዋጋ.227፣ የቲ-ዋጋ 2.398፣ ጉልህነት .019 በሶማልኛ የቤታ ዋጋ .240፣ የቲ ዋጋ 2.322 ጉልህነት .023 መሆኑን ያሳያል። በአማርኛ ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት የቤታ ዋጋ .246፣ የቲ ዋጋ 2.454፣ ጉልህነት .017 ሲሆን በሶማልኛ የቤታ ዋጋ .295፣ የቲ ዋጋ 2.797፣ ጉልህነት .007 ነው። በአማርኛ ትውስታ የማንበብ ብልሃት የቤታ ዋጋ-.227፣ የቲ ዋጋ -2.325፣ ጉልህነት .023 ሲሆን በሶማልኛ የቤታ ዋጋ-.021፣ የቲ-ዋጋ -.191 ጉልህነት .849 ነው። በአማርኛ ማካካስ የማንበብ ብልሃት የቤታ ዋጋ .067፣ የቲ-ዋጋ .684፣ ጉልህነት .496 በሶማልኛ የቤታ ዋጋ .047፣የቲ-ዋጋ .684፣ ጉልህነት .649 መሆኑን ያሳያል። በአማርኛ ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት የቤታ ዋጋ -.376 የቲ-ዋጋ -3.876፣ ጉልህነት

.000 ሲሆን በሶማልኛ የቤታ ዋጋ -.438፣ የቲ-ዋጋ -4.06፣ ጉልህነት አመላካች አሀዙ .000 መሆኑን ያሳያል።

ከላይ የቀረበው የተሰላ አሀዝ እንዳመላከተው በአማርኛ ቋንቋ አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ፣ ትውስታ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃቶች ጉልህነት አመላካች ከ0.05 በታች (<0.05) በመሆናቸው የተጠቀሱት የማንበብ ብልሃቶች በጥናቱ ሙከራ ቡድን አንድ ተሳታፊ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ውጤት ላይ ጉልህ የሆነ አዎንታዊ ተፅእኖ መፍጠራቸውን ያመላክታል። የተሰላው አሀዝ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ማካካስ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም በአንብቦ የመረዳት ውጤት ላይ ጉልህ የሆነ ተፅእኖ (አስተዋፆ) እንደሌለው አመላክቷል። ከላይ በቀረበው የተሰላ አሀዝ መሰረት በሶማልኛ ቋንቋ አእምሮታዊ፣ ልፅለአእምሮታዊ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት ጉልህነት አመልካች ከ0.05 በታች (<0.05) በመሆኑ እነዚህ የማንበብ ብልሃቶች ለአንብቦ መረዳት ውጤት አዎንታዊ እና ጉልህ አስተዋፆ እንዳላቸው አመላክቷል። ከዚህ በተቃራኒው ትውስታ እና ማካካስ የማንበብ ብልሃት ጉልህነት አመልካች 0.05 በላይ (>0.05) በመሆኑ በብልሃቶቹ አጠቃቀም እና በአንብቦ መረዳት ውጤት መካከል ጉልህ የሆነ ዝምድና የሌለ መሆኑ አንብቦ የመረዳት ውጤት እንዲጎለብት ተፅእኖው (አስተዋፆው) ዝቅተኛ መሆኑን አመላክቷል።

በህብረድህረት አሃዛዊ ስሌት ሙከራ ቡድን አንድ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ሁሉም የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር ያለው ዝምድናን ያመላከተው ሰንጠረዥ እንደሚያሳየው በአማርኛ ቋንቋ የቤታ ዋጋ .277፣ የቲ ዋጋ 2.328 ሲሆን ጉልህነት አመላካች አሀዙ .018 መሆኑን ያሳያል። ይህ ሁኔታ በሶማልኛ ቋንቋ ሲታይ የቤታ ዋጋ .041፣ የቲ ዋጋ 2.428 ሲሆን ጉልህነት አመላካች አሀዙ .129 ነው። ይህ የተሰላ አሀዝ ሙከራ ቡድን አንድ በአማርኛ ቋንቋ ጉልህነት አመላካቹ ከ0.05 በታች (<0.05) በመሆኑ በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡት የማንበብ ብልሃቶች በጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች አንብቦ መረዳት ውጤት ላይ ጉልህ የሆነ አዎንታዊ ተፅእኖ መፍጠራቸውን ያመላክታል። ነገር ግን በሶማልኛ ቋንቋ ጉልህነት አመላካቹ ከ 0.05 በላይ (>0.05) በመሆኑ በሶማልኛ ቋንቋ ሁሉንም የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም በአንብቦ መረዳት ውጤት ላይ አዎንታዊ ተፅእኖ እንደሌለው ግኝቱ ያመላክታል።

ሰንጠረዥ ሃያ ፡- መከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር ያለውን ዝምድና የሚያሳይ

ተንባይ ተላውጦዎች ለተተንባይ ተላውጦው ያላቸው አስተዋፆ እና ጉልህነት

የሞዴሉ ጭምቀ ሀሳብ

	አማርኛ	ሶማልኛ		አማርኛ	ሶማልኛ
አር	.593	.684	አር ካሬ	.352	.468
የተስተካከለ አር ካሬ	.298	.426	ተገማች መደበኛ ስህተት	1.21415	.97797

በድህረት ትንተናው የገቡ ተላውጦዎች እና ጉልህነት(Cofficients)

ሞዴል	መደበኛ ያልሆነ የተሰላ አሀዝ				መደበኛ የተሰላ አሀዝ					
ተላውጦዎች	ቢ		መደበኛ ስህተት		ቤታ		የቲ ዋጋ		ጉልህነ ት(sig)	
	አማርኛ	ሶማልኛ	አማርኛ	ሶማልኛ	አማርኛ	ሶማልኛ	አማርኛ	ሶማልኛ	አማርኛ	ሶማልኛ
ውስን(Constant)	8.66	9.29	1.05	.804			8.22	9.07	.000	.000
አእምሮታዊ	.280	.197	.121	.111	.246	.171	2.32	1.77	.023	.001
ልዕለአእምሮታዊ	.048	.410	.184	.131	.027	.322	.258	3.13	.797	.003
ትውስታ	-.029	-.126	119	.092	-.028	-.136	-.246	-1.37	.806	.173
ማኻኻስ	.395	.164	141	.121	.303	.140	2.80	1.35	.007	.001
ማህበራዊ	-.497	-.458	.123	.106	-.447	-.428	4.02	4.34	.000	.000
ሁሉም የማንበብ ብልሃቶች										
ሁሉም ብልሃቶች	.226	-2.353	.398	.001	.099	-.243	.568	2.75	.272	.001

በሞዴሉ ጭምቀሀሳብ የተሰላው አሀዝ ያመላከተው መከራ ቡድን ሁለት የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር ያለው ዝምድና በአማርኛ አር ካሬ .352 (35%)፣ የተስተካከለ አር ካሬ .298 (34%)፣ ተገማች መደበኛ ስህተት 1.214 ሲሆን በሶማልኛ የአር ካሬ .468 (46%)፣ የተስተካከለ አር ካሬ .426 (42%)፣ ተገማች መደበኛ ስህተት .977 መሆኑን ነው።።

በህብረድህረት ጉልህነትን የሚያሳየው ሰንጠረዥ መከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ ቋንቋ አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ያሳያል።። ይኸውም በአማርኛ የቤታ ዋጋ .246 ፣የቲ ዋጋ 2.325፣ ጉልህነት .023 በሶማልኛ የቤታ ዋጋ .171፣ የቲ-ዋጋ 1.773 ጉልህነት .001 መሆኑን ያሳያል።።

በአማርኛ ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት የቤታ ዋጋ .027፣ የቲ ዋጋ .258፣ ጉልህነት .797 ሲሆን በሶማልኛ የቤታ ዋጋ .322፣ የቲ ዋጋ 3.130፣ ጉልህነት .003 ነው። በአማርኛ ትውስታ የማንበብ ብልሃት የቤታ ዋጋ-.028፣ የቲ ዋጋ -246፣ ጉልህነት .806 ሲሆን በሶማልኛ የቤታ ዋጋ-.136፣ የቲ ዋጋ -1.378 ጉልህነት .173 ነው። በአማርኛ ማካካስ የማንበብ ብልሃት የቤታ ዋጋ .303፣ የቲ ዋጋ 2.801፣ ጉልህነት .007 በሶማልኛ የቤታ ዋጋ .140፣ የቲ ዋጋ 1.353፣ ጉልህነት .181 መሆኑን ያሳያል። በአማርኛ ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት የቤታ ዋጋ -.447 የቲ ዋጋ -4.022፣ ጉልህነት .000 ሲሆን በሶማልኛ የቤታ ዋጋ -.426 ፣የቲ ዋጋ 4.345፣ ጉልህነት .000 መሆኑን ነው።

ከላይ የቀረበው የተሰላ አሀዝ እንዳመላከተው በአማርኛ ቋንቋ አእምሮታዊ፣ ትውስታ፣ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃቶች ጉልህነት አመላካች ከ0.05 በታች(<0.05) በመሆናቸው የተጠቀሱት የማንበብ ብልሃቶች በጥናቱ ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ውጤት ላይ ጉልህ የሆነ አዎንታዊ ተፅእኖ መፍጠሩን ያመላክታል። የተሰላው አሀዝ እንዳመላከተው ልዕለአእምሮታዊ እና ትውስታ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም በአንብቦ የመረዳት ውጤት ላይ ጉልህ የሆነ ተፅእኖ (አስተዋፆ) እንደሌለው ነው። በሶማልኛ ቋንቋም አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት ጉልህነት አመልካች ከ0.05 በታች (<0.05) በመሆኑ እነዚህ የማንበብ ብልሃቶች ለአንብቦ መረዳት ውጤት አዎንታዊ እና ጉልህ አስተዋፆ እንዳላቸው አመላክቷል። ከዚህ በተቃራኒው ትውስታ እና ማካካስ የማንበብ ብልሃቶች ጉልህነት አመልካች 0.05 በላይ (>0.05) በመሆኑ በብልሃቶቹ አጠቃቀም እና በአንብቦ መረዳት ውጤት መካከል ጉልህ የሆነ ዝምድና የሌለ በመሆኑ የብልሃቶቹ አጠቃቀም አንብቦ የመረዳት ውጤት እንዲጎለብት ተፅእኖ (አስተዋፆ) እንደሌው አመላክቷል።

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እንዳመላከተው ሙከራ ቡድን ሁለት ሁሉንም የማንበብ ብልሃቶች አጠቃቀም ለአንብቦ መረዳት ውጤት መሻሻል ያለው አስተዋፆ (ዝምድና) ሲታይ በአማርኛ የቲ ዋጋ .56፣ የቤታ ዋጋ .099 ጉልህነት .272 በሶማልኛ ቋንቋ ደግሞ የቲ ዋጋ 2.75፣ የቤታ ዋጋ -.243 ጉልህነት .001 መሆኑን ያሳያል። በተሰላው አሀዝ መሰረት ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ ቋንቋ ጉልህነት አመልካቹ ከ 0.05 በላይ (>0.05) መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን በሶማልኛ ከ 0.05 በታች (<0.05) መሆኑን ያሳል።

የተሰላው አሀዝ እንደሚያመላክተው መከራ ቡድን ሁለት ሁሉንም የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ለአንብቦ መረዳት ውጤት መጎልበት አዎንታዊ ጉልህ አስተዋፆ እንደሌለው ያመላክታል። ነገር ግን በሶማልኛ ቋንቋ ሁሉንም የማንበብ ብልሃቶች አጠቃቀም ለአንብቦ መረዳት ውጤት መሻሻል አዎንታዊ ጉልህ አስተዋፆ ማድረጉን ግኝቱ አመላክቷል።

የጥናቱ ጥያቄ ቁጥር አራት፡- የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከሶማልኛ ወደ አማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ያለን የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ እንዲጎለብት ምን ያህል አስተዋፆ አለው?

ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ሒደት ከአንድ ተግባር (ሁኔታ) ወደሌላ ተግባር ወይም ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ የማንበብ ብልሃቶችን ሽግግር ያደርጋሉ (Talibi 2012፣ Zhang 2012)። በዚህ ጥናት የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃቶችን በማሸጋገር አንብቦ መረዳታቸውን ማጎልበት አለማጎልበታቸውን ለማየት ተሞክሯል።

በጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ከአማርኛ ወደሶማልኛ እና ከሶማልኛ ወደአማርኛ ቋንቋ እያሸጋገሩ መጠቀማቸውን ለማየት የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ እና በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ የመናገር ቃለመጠይቅ አገልግሎት ላይ ውሏል።

በጥናቱ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በቀረበው የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ ውስጥ ከቀረቡት 32 ጥያቄዎች ሁለቱ የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽን የሚመለከቱ ናቸው። የጥያቄዎቹ አላማ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በማንበብ ሂደት የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን ከአንዱ ቋንቋ ወደሌላው እያሸጋገሩ መጠቀማቸውን መፈተሽ ነው። የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ እያሸጋገሩ የመጠቀማቸው ብቃት ቅድመልምምድ እና ድህረልምምድ ሲነፃፀር ምን ገፅታ እንዳለው የሚከተለው ሰንጠረዥ ያመላክታል።

ሰንጠረዥ ሃያ አንድ፡- **መከራ ቡድን አንድ እና መከራ ቡድን ሁለት የማንበብ ብልሃቶችን ከአማርኛ ወደሶማልኛ እና ከሶማልኛ ወደአማርኛ ቋንቋ እያሸጋገሩ የመጠቀም ሁኔታቸውን የሚያሳይ**

ተ.ቁ	ተላውጦ	መከራ ቡድን አንድ				መከራ ቡድን ሁለት			
		ቅድመልምምድ		ድህረልምምድ		ቅድመልምምድ		ድህረልምምድ	
		አማካይ	መደበኛ ልይይት	አማካይ	መደበኛ ልይይት	አማካይ	መደበኛ ልይይት	አማካይ	መደበኛ ልይይት
1	የማንበብ ብልሃትን ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ እያሻገርኩ እጠቀማለሁ	3.21	1.4715	3.91	1.192	3.33	1.347	3.54	1.197
2	የማንበብ ብልሃትን ከሶማልኛ ወደአማርኛ ቋንቋ እያሻገርኩ እጠቀመለሁ	3.56	1.24	3.76	1.28	3.18	1.494	3.94	1.1045

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እንዳመላከተው የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በማንበብ ሂደት የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ መጠቀማቸውን ነው፡፡ ግኙቱ እንዳሳየው መከራ ቡድን አንድ ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ እያሸጋገርኩ እጠቀማለሁ በማለት የሰጡት ምላሽ ቅድመልምምድ አማካይ 3.21 ድህረልምምድ 3.91 የተገኘ ለውጥ -0.7 ሲሆን መከራ ቡድኑ ከሶማልኛ ወደአማርኛ እያሸጋገርኩ እጠቀማለሁ በማለት የሰጠው ምላሽ ቅድመልምምድ 3.56 ድህረልምምድ 3.76 የተገኘ ለውጥ -0.2 ነው፡፡ መከራ ቡድን ሁለት በበኩሉ ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ እያሸጋገርኩ እጠቀማለሁ በማለት የሰጠው ምላሽ ቅድመልምምድ አማካይ 3.33 ድህረልምምድ 3.54 የተገኘ ለውጥ -0.21 ሲሆን ከሶማልኛ ወደአማርኛ እያሸጋገርኩ እጠቀማለሁ በማለት የሰጠው ምላሽ ደግሞ ቅድመልምምድ 3.18 ድህረልምምድ 3.94 የተገኘ ለውጥ -0.76 መሆኑን ያሳያል፡፡ የተሰላው አሀዝ እንደሚያመላክተው መከራ ቡድን ሁለት ውስጥ ያሉ ተማሪዎች መከራ ቡድን አንድ ውስጥ ካሉት በጎላ መልኩ ከሶማልኛ ወደአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ መጠቀማቸውን ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ መከራ ቡድን አንድ ከመከራ ቡድን ሁለት በጎላ መልኩ የማንበብ ብልሃቶችን ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ እያሸጋገሩ እንደሚጠቀሙ ግኙቱ አመላክቷል፡፡

5.1.2 በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ጊዜ አስታውሶ መናገር ቃለመጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ የመናገር ቃለመጠይቅ በተገኘ መረጃ የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽን ለማየት ተሞክሯል። ቃለመጠይቁ ሁለት ተግባራትን (ክፍሎችን) አካቷል። የቃለመጠይቁ የመጀመሪያ ክፍል በጥናቱ ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ውስጥ የተሳተፉ ተማሪዎች (ከየሙከራ ቡድኑ ስድስት ስድስት ተማሪዎች) ለማንበብ ተግባር በየቋንቋው የቀረበውን ምንባብ አንብቦ ለመረዳት ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ እያሸጋገሩ የተጠቀሙበትን የማንበብ ብልሃት እንዲገልፁ የተደረገበት ክፍል ነው። የቃለመጠይቁ ሁለተኛ ክፍል ቃለመጠይቅ ለሚደረግላቸው ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት ዝርዝር በመስጠት ለማንበብ ተግባር የቀረበውን ፅሁፍ አንብቦ ለመረዳት የትኞቹን ብልሃቶች እንደተጠቀሙ የሚያመላክቱበት ነው። በቃለመጠይቁ ከሙከራ ቡድን አንድ የተመረጡቱ (በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን የተከታተሉት) በሶማልኛ ቋንቋ የተዘጋጀውን ምንባብ ያነበቡ ሲሆን ከሙከራ ቡድን ሁለት የተመረጡት (በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት የተማሩት) ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ አንብበዋል። በመጠይቁ የመጀመሪያ ክፍል የቀረቡት ጥያቄዎች እና ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ተማሪዎች የተሰጡ ምላሾች በሚከተለው መንገድ ቀርቧል። ቃለመጠይቁ በተማሪዎች ፍላጎት በሶማልኛ ቋንቋ የቀረበ ነው።

1. **ለማንበብ ተግባር የቀረበውን ምንባብ አንብበህ ተረዳህ? ግለፅ።**

በቃለመጠይቁ የቀረበው ይህ የመጀመሪያ ጥያቄ ተተኳሪ ተማሪዎች የቀረበውን ምንባብ አንብበው መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የቀረበ ነው። አላማውም ተማሪዎች ምንባቡን በንቃት ማንበባቸውን ማረጋገጥ ነው (ድግግሞሽ እና በመቶኛ የተሰላ)።

ሰንጠረዥ ሃያ ሁለት፡- በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ የመናገር ቃለመጠይቅ ሙከራ ቡድን አንድ በሶማልኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ አንብበው የሰጡት ምላሽ

ተ.ቁ	ሙከራ ቡድን አንድ					
	ቅድመልምምድ	መላሾች		ድህረልምምድ	መላሾች	
		ድ	%		ድ	%
1	ፅሁፉን አንብቤዋለሁ ። የምንባቡ ሀሳብ ውስብስብ በመሆኑ በተወሰነ ደረጃ ለመረዳት ተቸግሬለሁ። አንዳንድ ቃላት ትርጉማቸው አልገባኝም።	3	50	የቀረበውን ምንባብ አንብቤዋለሁ። ለመረዳት አልተቸገርኩም። የተወሰነ ሀሳብ አልገባኝም። ፅሁፉን ለመረዳት ግን ጥረት አድርጌያለሁ።	5	83.33
2	የፅሁፉ ሀሳብ ይከብዳል	3	50	ፅሁፉ ምንም አልገባኝም	1	16.66

ሰንጠረዥ ሃያ ሶስት ፡- በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ የመናገር ቃለመጠይቅ ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ አንብበው የሰጡት ምላሽ

ተ.ቁ	መከራ ቡድን ሁለት					
	ቅድመልምምድ	መላሾች		ድህረልምምድ	መላሾች	
		ድ	%		ድ	%
1	የቀረበውን ምንባብ አንብቤዋለሁ ። አብዛኛው የፅሁፉ ሀሳብ ግልፅ አይደለም። ፅሁፉን ለማንበብ ግን ሙከራ አድርጌያለሁ	3	50	የቀረበውን ምንባብ አንብቤዋለሁ። በተወሰነ መልኩ ፅሁፉን ለመረዳት ተቸግሬያለሁ። የፅሁፉ ሀሳብ፣ ቋንቋው፣ የማላውቃቸው ቃላት በመኖራቸው የፅሁፉን ሙሉ ሀሳብ ለመረዳት ከብዶኛል።	4	66.66
2	ፅሁፉ ምንም አልገባኝም	3	50	የፅሁፉ ሀሳብ ይከብዳል	2	33.33

ከላይ የቀረቡት ሰንጠረገሮች እንዳመላከቱት በሁለቱም የመከራ ቡድኖች ውስጥ ለቃለመጠይቅ የቀረቡት ተማሪዎች በየቋንቋው የቀረበላቸውን ምንባብ አንብበዋል። በሰንጠረገሮቹ እንደተንፀባረቀው በመቶኛ ሲታይ ቅድመልምምድ ሁለቱም የመከራ ቡድኖች ለማንበብ ተግባር የቀረበውን ምንባብ አንብበው ለመረዳት 50% ያህሉ ለመረዳት ቢቸገሩም የተቀሩት 50% የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ምንባቡን አንብበው ለመረዳት ጥረት እንዳደረጉ አመላክተዋል። ቃለመጠይቅ የቀረበላቸው ተማሪዎች ከቅድመልምምድ በተሻለ ድህረልምምድ የቀረበውን ምንባብ አንብበው በመረዳት ለውጥ እንዳሳዩ የተሰላው አሀዝ ያመላክታል። በመቶኛ የተሰላው አሀዝ እንደሚያመላክተው

መከራ ቡድን አንድ 5(83.33%) መከራ ቡድን ሁለት 4(66.66) የቀረበውን ፅሁፍ አንብበው ለመረዳት ጥረት አድርገዋል፡፡ ይህ አሃዝ የሚያመላክተው በአማርኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ ካነበቡት ተማሪዎች ይልቅ በሶማልኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ ያነበቡት ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምንባብ በተሻለ አንብበው እንደተረዱ ነው፡፡

2. **የቀረበውን ምንባብ አንብበህ ለመረዳት ተቸግርክ? ለምን? ያጋጠመህን ችግር ለማስወገድስ ምን አደረክ? ግለፅ ::**

በቃለመጠይቁ የመጀመሪያ ጥያቄ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የቀረበውን ምንባብ አንብበው ለመረዳት ጥረት ማድረጋቸውን ገልፀዋል፡፡ ተማሪዎቹ የቀረበውን ምንባብ አንብበው በመረዳት ሂደት ያጋጠማቸው ችግር ካለ እንዲደልፁ በማሰብ ሁለተኛው ጥያቄ ቀርቧል፡፡ የሚከተሉት ሰንጠረረገሮች ይህንኑ ያመላክታሉ (በድግግሞሽ እና በመቶኛ የተሰላ)፡

ሰንጠረዥ ሃያ አራት፡- መከራ ቡድን አንድ በሶማልኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ አንብበው በመረዳት ሂደት ያጋጠማቸውን ችግር ለማስወገድ ያደረጉትን ጥረት የሚሳይ

ተ.ቁ	መከራ ቡድን አንድ					
	ቅድመልምምድ	መላሾች		ድህረልምምድ	መላሾች	
		ድ	%		ድ	%
1	የቀረበውን ፅሁፍ አንብቤ ለመረዳት ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ ያልገባኝን ለመረዳት ደግሜ አነበብኩ፡፡	6	100	የቀረበውን ምንባብ አንብቤ ለመረዳት አልተቸገርኩም፡፡ አንዳንድ ቦታ ያለው ሀሳብ አልገባኝም፡፡ ይህን ችግር ለማስወገድ በጥንቃቄ አነበብኩ፣ ያልገባኝን ቦታ ደግሜ አነበብኩ፣ ቃላትን በአውዳቸው ለመረዳት ጥረት አደረኩ	5	83.33
2	----------			ስለርእሱ የማውቀው ነገር ባለመኖሩ ሀሳቡን ለመረዳት ተቸግሬያለሁ፡፡ ይህን ችግር ለማስወገብ የተወሰነውን ክፍል ደግሜ አነበብኩ	1	16.66

ሰንጠረዥ ሃያ አምስት፡- *መ*ከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ አንብበው በመረዳት ሂደት ያጋጠማቸውን ችግር ለማስወገድ ያደረጉትን ጥረት የሚሳይ

ተ.ቁ	መከራ ቡድን ሁለት					
	ቅድመልምምድ	መላሾች		ድህረልምምድ	መላሾች	
		ድ	%		ድ	%
1	የፅሁፉ ሀሳብ ከብዶኛል፡፡ ይህን ችግር ለማስወገድ ደጋግሜ አነበብኩ	3	50	በአማርኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ አንብቤ ለመረዳት ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ በምንባቡ ውስጥ ብዙ አዳዲስ ቃላት በመኖራቸው ፅሁፉን በቀላሉ ለመረዳት ተቸግሬያለሁ፡፡ ዋናው ችግሬ አማርኛ ቋንቋ በደንብ አለመቻሌ ነው፡፡ ይህን ችግር ለማስወገድ ፅሁፉን ደግሜ አነበብኩ፣ የቃላትን ፍቺ ገመትኩ፣ ከርእሱ በመነሳት ሀሳቡን መተንበይ በቀረበው ፅሁፍ ዙርያ ከዚህ በፊት የማውቀውን ለማስታወስ ሞከርኩ	5	83.33
2	ፅሁፉን ለመረዳት ተቸግሬያለሁ	3	50	ፅሁፉ ምንም አልገባኝም	1	16.66

ከላይ በቀረቡት ሰንጠረገሮች መከራ ቡድን አንድ እና መከራ ቡድን ሁለት ውስጥ የተሳተፉ ተማሪዎች ቅድመልምምድ የቀረበውን ፅሁፍ አንብበው ለመረዳት እንደተቸገሩ፣ ችግራቸውን ለማስወገድ ደጋግመው እንዳነበቡ አመላክተዋል፡፡ ይህም የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ቅድመልምምድ ብዛት ያላቸው የማንበብ ብልሃቶችን እንደማያውቁ ከጠቀሱት የማንበብ ብልሃት አይነት መረዳት ይቻላል፡፡

በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ድህረልምምድ መከራ ቡድን አንድ ውስጥ የተሳተፉ ተተኳሪ ተማሪዎች ለሁለተኛው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ እንደሚያመላክተው በሶማልኛ ቋንቋ የቀረበው ምንባብ አንዳንድ ቦታ ከበድ ያለ ሀሳብ ቢኖረውም ምንባቡን አንብበው ለመረዳት አለመቸገራቸውን የገለፁ ሲሆን ይህንን ችግራቸውን ለማስወገድ በጥንቃቄ ማንበብ (ራስን እና አንብቦ መረዳትን መቆጣጠር)፣ ደግሞ ማንበብ፣ ቃላትን በአውድ መጠቀም የማንበብ ብልሃቶችን መጠቀማቸውን ገልፀዋል፡፡ በመከራ ቡድን ሁለት ቃለመጠይቅ ላይ የተሳተፉ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ለማንበብ ተግባር የቀረበውን ውህድአሀድ አንብበው ለመረዳት ጥረት አድርገዋል፡፡ ከመከራ ቡድን ሁለት በቃለመጠይቅ የተሳተፉ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በሚገባ የመጠቀም ችግር ያለባቸው በመሆኑ ምንባቡን አንብበው ለመረዳት ውስን ችግር እንደገጠማቸው ገልፀዋል፡፡ ይህንን

ችግር ለማስወገድ ፅሁፉን ደግሞ ማንበብ፣ የቃላትን ፍቺ መገመት፣ ከርእሱ በመነሳት ሀሳቡን መተንበይ እና የቀደመ እውቀት መጠቀም የተባሉትን የማንበብ ብልሃቶች መጠቀማቸውን ገልፀዋል።

የቃለመጠይቁ ምላሽ የሚያመላክተው ሁለቱም የሙከራ ቡድኖች ቅድመልምምድ የቀረበውን ፅሁፍ አንብበው ለመረዳት ቢችገሩም የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤያቸው ዝቅተኛ በመሆኑ ብልሃቶችን አቀናጅተው እንዳልተጠቀሙ ያሳያል። ድህረልምምድ በሁለቱም ሙከራ ቡድኖች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት ባልተማሩበት ቋንቋ የቀረበላቸውን ፅሁፍ አንብበው ለመረዳት ጥረት ባደረጉበት እና የተወሰነ ቦታ ለመረዳት ችግር በገጠማቸው ጊዜ የተማሩዋቸውን ብልሃቶች እያስታወሱ መጠቀማቸውን ያሳያል። ይህም ተማሪዎቹ ተጠቀምን ብለው የገለፁዋቸው ብልሃቶች ውስን ቢሆኑም አንብቦ የመረዳት ችግራቸውን ለማስወገድ የማንበብ ብልሃቶችን መጠቀማቸውን (እያሸጋገሩ) ያሳያል።

3. **በአማርኛ ቋንቋ ስታነብ ሶማልኛ ቋንቋ ይጠቅመኛል ብለህ ታስባለህ / በሶማልኛ ቋንቋ ስታነብ አማርኛ ቋንቋ ይጠቅመኛል ብለህ ታስባለህ ? ለምን?**

የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በአማርኛ ወይም በሶማልኛ ቋንቋ ለማንበብ ተግባር የተለያዩ ፅሁፎች ቀርቦላቸው በሚያነቡበት ወቅት የማንበብ ብልሃቶችን ከአንዱ ቋንቋ ወደሌላው ቋንቋ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ የመጠቀም ግንዛቤያቸውን ለመፈተሽ ታስቦ የቀረበ ጥያቄ ነው። በዚህ ጥያቄ መሰረት ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ተሰባስቦ ሲታይ የሚከተለው ገፅታ አለው።

ሰንጠረዥ ሃያ ስድስት፡- መካራ ቡድን አንድ የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ የመጠቀም ግንዛቤያቸውን የሚያሳይ

ተ.ቁ	መካራ ቡድን አንድ					
	ቅድመልምምድ	መላሾች		ድህረልምምድ	መላሾች	
		ድ	%		ድ	%
1	ሶማልኛ ቋንቋ የመጀመሪያ ቋንቋዬ በመሆኑ ሳነብ ብዙ አልቸገርም፡፡ በሶማልኛ ቋንቋ ሳነብ አማርኛ ቋንቋ ይጠቅማል ብዬ አስቤ አላውቅም፡፡	6	100	በሶማልኛ ሳነብ አማርኛ ይጠቅማል ለማለት እቸገራለሁ፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ሳነብ ግን ሶማልኛ ሊጠቅም እንደሚችል ከትምህርቱ ተረድቻለሁ፡፡ በሶማልኛ የማውቀውን እያስታወስኩ እጠቀማለሁ፣ እተረጉማለሁ ወዘተ፡፡	5	83.33
-----	----------	--		በአንድ ቋንቋ በማንበብ ወቅት ሌላ ቋንቋ ይጠቅማል ለማለት ይከብዳል፡፡	1	16.66

ሰንጠረዥ ሃያ ሰባት፡- መካራ ቡድን ሁለት የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ የመጠቀም ግንዛቤያቸውን የሚያሳይ

ተ.ቁ	መካራ ቡድን ሁለት					
	ቅድመልምምድ	መላሾች		ድህረልምምድ	መላሾች	
		ድ	%		ድ	%
1	፡ ሶማልኛ እና አማርኛ ቋንቋ የተለያዩ በመሆናቸው በአንዱ ሲነበብ ሌላው አይጠቅምም፡፡	5	83.33	አዎ፣ በሶማልኛ ወይም በአማርኛ ቋንቋ የቀረበውን ፅሁፍ አንብቦ ለመረዳት በሶማልኛ ቋንቋ የተማርናቸው ብልሃቶች ይጠቅማሉ፡፡ የአንዱ ቋንቋ ልምድ ለሌላው ይጠቅማል፡፡	5	83.33
2	ሞክሬ ባላውቅም በአንድ ቋንቋ የተገኘ ልምድ ለሌላ ሊጠቅም ይችላል፡፡	1	16.66	በትክክል ይጠቅማል ለማለት አልችልም	1	16.66

በሰንጠረዥ ሰላሳ አራት እና በሰንጠረዥ ሰላሳ አምስት የተንፀባረቀው የተማሪዎች ምላሽ እንደሚያመላክተው ተማሪዎች ቅድመልምምድ በአማርኛ ቋንቋ ሲነበብ የሶማልኛ ቋንቋ ልምድ ወይም በተቃራኒው በሶማልኛ ሲነበብ የአማርኛ ቋንቋ ልምድ ይጠቅማል የሚል እምነት እንደሌላቸው ያሳያል፡፡ ይህም ተማሪዎች ቅድመልምምድ ብልሃቶችን ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ እያሸጋገሩ የመጠቀም ግንዛቤ እንደሌላቸው ያሳያል፡፡

በመከራ ቡድን አንድ እና በመከራ ቡድን ሁለት ለቃለመጠይቁ የተሳተፉ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች ድህረልምምድ ከቅድመልምምድ በተሻለ የአንደኛው ቋንቋ ልምድ ለሌላኛው የሚጠቅም መሆኑን አንፀባርቀዋል። በተለይ ሶማልኛ ቋንቋ የመጀመሪያ ቋንቋቸው እንደመሆኑ በአማርኛ ቋንቋ በማንበብ ወቅት የበለጠ ጠቀሜታ እንዳለው በሰጡት መልስ አንፀባርቀዋል። ለዚህም የሰጡት ምክንያት በአማርኛ ቋንቋ ሲያነቡ የሶማልኛ ቋንቋ የቀደመ እውቀታቸውን መጠቀም፣ ያልገባቸውን ሀሳብ መተርጎም የሚችሉ መሆኑን ነው። በሶማልኛ ቋንቋ ሲያነቡም አማርኛ ቋንቋ እንደጠቀማቸው አንፀባርቀዋል።

4. ለማንበብ ተግባር የቀረበውን ምንባብ አንብቦ ለመረዳት ከሶማልኛ ወደአማርኛ / ከአማርኛ ወደሶማልኛ የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገርክ ተጠቀምክ?

በጥናቱ መከራ ቡድን አንድ በአማርኛ መከራ ቡድን ሁለት ደግሞ በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን ተከታትለዋል። በዚህ መሰረት በየመከራ ቡድኑ ውስጥ የተሳተፉት ተተኳሪ ተማሪዎች የቃለመጠይቁ አራተኛ ጥያቄ የቀረበላቸው ትምህርቱ ከተሰጠበት ቋንቋ ጋር ተያዞ ነው። ማለትም በአማርኛ ቋንቋ የተማረው መከራ ቡድን አንድ ለማንበብ ተግባር የቀረበውን ምንባብ አንብበህ ለመረዳት ከአማርኛ ወደሶማልኛ የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገርክ ተጠቀምክ? የሚል ነው። መከራ ቡድን ሁለት ደግሞ ለማንበብ ተግባር የቀረበውን ምንባብ አንብበህ ለመረዳት ከሶማልኛ ወደአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገርክ/ሽ ተጠቀምክ? የሚል ነው። ይህ ጥያቄ አዎ እና አይ የሚል ምላሽ የሚያሰጥ (Dichotomy) ቢሆንም ተማሪዎቹ ምክንያታቸውን እንዲገልፁ ተደርጓል። ጥያቄው ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምንባብ በማንበብ ሂደት የተጠቀሙባቸውን የማንበብ ብልሃቶች ለማስታወስ እና ለማነቃቃት ታስቦ የቀረበ ነው።

የቃለመጠይቁ አራተኛ ጥያቄ ቅድመልምምድ ለጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ቀርቦላቸው የሰጡት ምላሽ ስለማንበብ ብልሃት ብዙ የሚያውቁት እንደሌለ እና ብልሃቶችንም እያሸጋገሩ እንዳልተጠቀሙ ገልፀዋል። ድህረልምምድ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የተሰጠው ምላሽ በመከራ ቡድን አንድ ቃለመጠየቁ ከቀረበላቸው 6 ተማሪዎች 3ቱ በሶማልኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ አንብቦ ለመረዳት የማንበብ ብልሃቶችን ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ እያሸጋገርኩ እጠቀማለሁ ያሉ ሲሆን የተቀሩት 3ቱ የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ እንደማይጠቀሙ ገልፀዋል። የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገርኩ

እጠቀማለሁ ያሉት ተማሪዎች ያቀረቡት ምክንያት በአማርኛ ቋንቋ የተማሩዋቸው የማንበብ ብልሃቶች በጣም ጠቃሚ መሆናቸውን በመረዳታቸው በሶማልኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ አንብበው ለመረዳት ተግባራዊ እንዳደረጉዋቸው አስረድተዋል። አልጠቀምም ያሉቱ ተማሪዎች ያቀረቡት ምክንያት በሶማልኛ ቋንቋ የቀረቡ ምንባቦችን አንብበው ለመረዳት የማይቸገሩ በመሆናቸው፣አማርኛ ቋንቋን በሚገባ የመጠቀም ችግር ስላለባቸው ብልሃቶችን እያሸጋገሩ መጠቀም አለመጠቀማቸውን እንደማያውቁ ገልፀዋል።

በመከራ ቡድን ሁለት ለቃለመጠይቁ ከቀረቡት 6 ተተኪ ተማሪዎች 4ቱ በአማርኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ አንድ አንብቦ ለመረዳት የማንበብ ብልሃቶችን ከሶማልኛ ወደአማርኛ ቋንቋ እያሸጋገሩ ለመጠቀም መከራ እንዳደረጉ የገለፁ ሲሆን 2ቱ ተማሪዎች ይህን እንዳላደረጉ ገልፀዋል። በመከራ ቡድን ሁለት ውስጥ የተሳተፉት 4ቱ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ከሶማልኛ ወደአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ የሚጠቀሙበት ምክንያት በአማርኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ አንብቦ ለመረዳት በመፈለጋቸው እንደሆነ ገልፀዋል። በመከራ ቡድን ሁለት ውስጥ ብልሃቶችን እያሸጋገርኩ አልጠቀምም ያሉት 2 ተማሪዎች ያቀረቡት ምክንያት በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ፅሁፎችን አንብቦ ለመረዳት በመቸገራቸው እና የአማርኛ ፅሁፍ ከሶማልኛ የተለየ በመሆኑ እንደሆነ ገልፀዋል። የተሰጠው ምላሽ በመቶኛ ቢሰላ ከመከራ ቡድን አንድ ይልቅ መከራ ቡድን ሁለት ያሉ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት ሽግግር አድርገዋል። ወይም በሌላ አገላለፅ ተተኪ ተማሪዎች ከአማርኛ ወደሶማልኛ ካደረጉት ይልቅ ከሶማልኛ ወደአማርኛ ቋንቋ ያደረጉት በመቶኛ ሲሰላ የበለጡ ናቸው። ለዚህ ልዩነት ተጠቃሽ የሆነው ዋነኛ ምክንያት ተተኪ ተማሪዎች ውስን የአማርኛ ቋንቋ ችግር ያለባቸው መሆኑ ተንፀባርቋል።

5. የቀረበውን ፅሁፍ አንብቦ ለመረዳት ምን ምን የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገርክ ተጠቀምክ?

ከላይ በጥያቄ ቁጥር 4 እንደተገለፀው ከሁለቱም የመከራ ቡድን በቃለመጠይቅ የተሳተፉ ተማሪዎች ቅድመልምምድ የማንበብ ብልሃቶችን ከአንዱ ቋንቋ ወደሌላው እያሸጋገሩ እንዳልተጠቀሙ ገልፀዋል። ድህረልምምድ በሁለቱም የመከራ ቡድን ውስጥ ያሉ ተተኪ ተማሪዎች መጠናቸው የተለያየ ይሁን እንጂ የማንበብ ብልሃቶችን ከአንዱ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ እያሸጋገሩ እንደተጠቀሙ አስረድተዋል። በመሆኑም ተተኪ

ተማሪዎች ድህረልምምድ የቀረበውን ፅሁፍ አንብቦ ለመረዳት ምን ምን የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ እንደተጠቀሙ ማየቱ ተገቢ ነው። በዚህ መሰረት ከላይ ለቀረበው ጥያቄ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ቀርቧል(ድግግሞሽ እና በመቶኛ የተሰላ)።

ሰንጠረዥ ሃያ ስምንት፡- *ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ድህረልምምድ ለማንበብ ተግባር የቀረቡ ምንባቦችን አንብቦ ለመረዳት ከአንዱ ቋንቋ ወደሌላው ቋንቋ እያሸጋገሩ የተጠቀሙባቸውን የማንበብ ብልሃቶችን የሚያሳይ*

ተ.ቁ	የማንበብ ብልሃቶች	ሙከራ ቡድን አንድ ከአማርኛ ወደሶማልኛ እያሸጋገሩ የተጠቀሙባቸው የማንበብ ብልሃቶች ዝርዝር		ሙከራ ቡድን ሁለት ከሶማልኛ ወደአማርኛ እያሸጋገሩ የተጠቀሙባቸው የማንበብ ብልሃቶች ዝርዝር	
		የተማሪ ቁጥር	መቶኛ(%)	የተማሪ ቁጥር	መቶኛ(%)
1	ርዕሱን በማየት የምንባቡን ሀሳብ እተነብያለሁ	3	50	4	66.6
2	ምንባቡን ለማንበብ አቅዳለሁ	-	-	4	66.6
3	የምንባቡን ሀሳብ በፍጥነት ለማግኘት እጥራለሁ	-	-	3	50
4	ማስታወሻ እይዛለሁ	2	33.3	3	33.3
5	ደጋግሜ አነባለሁ	3	50	4	66.6
6	ጥያቄ እጠይቃለሁ	2	33.3	4	66.6
7	የቀደመ እውቀቴን እጠቀማለሁ	2	33.3	3	50
8	በማንበብ ወቅት ራስን እቆጣጠራለሁ	3	50	-	-
9	አውዳዊ ፍቺ እጠቀማለሁ	1	16.6	4	66.6
10	የቃላትን ፍቺ እገምታለሁ	1	16.6	-	-
11	የማንበብ ብልሃት ከሶማልኛ ወደአምርኛ /ከአማርኛ ወደሶማልኛ እያሸጋገርኩ እጠቀማለሁ	3	50	4	66.6
12	ከሌሎች ጋር መተባበር	**3**	**33.3**	4	66.6

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚያመላክተው ሙከራ ቡድን አንድ ርዕሱን በማየት የምንባቡን ሀሳብ እተነብያለሁ፣ ደግሜ አነባለሁ፣ በማንበብ ወቅት ራሴን እና አንብቦ መረዳቴን እቆጣጠራለሁ፣ የማንበብ ብልሃቶችን ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ እያሸጋገርኩ እጠቀማለሁ፣ ከሌሎች ጋር እተባበራለሁ ያሉ ተማሪዎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ናቸው። ሙከራ ቡድን ሁለት ደግሞ ርዕሱን በማየት የምንባቡን ሀሳብ እተነብያለሁ፣ ምንባቡን ለማንበብ አቅዳለሁ፣ ደግሜ አነባለሁ፣ ጥያቄ እጠይቃለሁ፣ የማንበብ

ብልሃቶችን ከሶማልኛ ወደአማርኛ ቋንቋ እያሸጋገርኩ እጠቀማለሁ፣ ከሌሎች ጋር እተባበራለሁ ያሉቱ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ናቸው።

ሰንጠረዡ እንደሚያመላክተው ምንባቡን ለማንበብ አቅዳለሁ፣ የምንባቡን ሀሳብ በፍጥነት ለማግኘት እጥራለሁ እና የምንባቡ ሀሳብ በአእምሮዬ ውስጥ ምስል እንዲፈጥር አደርጋለሁ የሚሉት የማንበብ ብልሃቶች በሙከራ ቡድን ሁለት ቢጠቀሱም በሙከራ ቡድን አንድ ተተኳሪ ተማሪዎች አልተጠቀሱም። በማንበብ ወቅት ራሴን እቆጣጠራሉ፣ የቃላትን ፍቺ እገምታለሁ የተባሉት ብልሃቶች ደግሞ በሙከራ ቡድን አንድ ቢጠቀሱም ሙከራ ቡድን ሁለት ያልጠቀሷቸው ናቸው። በዚህ የጥያቄ ክፍል ሁለቱም የሙከራ ቡድኖች ያልጠቀሷቸው የማንበብ ብልሃቶች መረጃን ፈልፍሎ በማውጣት ምክንያታዊ ድምዳሜ ላይ መድረስ፣ ጭምቀ ሀሳብ መፃፍ፣ ራስን መገምገም እና የምንባቡ ሀሳብ በአእምሮዬ ምስል እንዲፈጥር አድርጌ እጠቀማለሁ የተባሉት ናቸው።

6. በአማርኛ/በሶማልኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ አንብቦ ለመረዳት የበለጠ ጠቅሞኛል የምትለውን የማንበብ ብልሃት ግለፅ/ጭ

የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ቅድመልምምድ ለአምስተኛው ጥያቄ የተሰጡት ምላሽ የለም። ከላይ በቀረበው ጥያቄ መሰረት ድህረልምምድ ሙከራ ቡድን አንድ ውስጥ ያሉ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በሶማልኛ ቋንቋ ሲያነቡ ይበልጥ ጠቅሞናል በማለት የገለፁት ዋናውን ሀሳብ በፍጥነት ለማግኘት መጣር፣ ደጋግሞ ማንበብ፣ መቆጣጠር እና ጥያቄ መጠየቅ ናቸው። በሙከራ ቡድን ሁለት ውስጥ የተሳተፉ ተማሪዎች በበኩላቸው በአማርኛ ቋንቋ ሲያነቡ የበለጠ ጠቅሞኛል በማለት የገለፁዋቸው የማንበብ ብልሃቶች መተንበይ፣ በጥንቃቄ ማንበብ፣ ጥያቄ መጠየቅ፣ መተርጎም፣ መገመት እና ደጋግሞ ማንበብ እና የቀደመ እውቀትን መጠቀም ናቸው። በሁለቱም ሙከራ ቡድን የተሳተፉ ተማሪዎች የቀረበን ምንባብ አንብቦ ለመረዳት የበለጠ ጠቅሞናል በማለት የጠቀሱዋቸው ብልሃቶች 83.3% ተመሳሳይነት አላቸው። ይህ የሚያሳየው ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በመማራቸው ድህረልምምድ ለማንበብ ተግባር የቀረቡ ምንባቦችን አንብበው ለመረዳት ተማሪዎች ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ እያሸጋገሩ (ብልሃትን ከተማሩበት ቋንቋ ብልሃትን ወደአልተማሩበት ቋንቋ) መጠቀማቸውን ነው።

ጥናቱ በቃለመጠይቅ ክፍል ሁለት ቃለመጠይቅ አቅራቢው በዝርዝር ለተተኳሪ ተማሪዎች ካቀረባቸው የማንበብ ብልሃቶች ውስጥ የትኞቹን የማንበብ ብልሃቶች እንደተጠቀሙ ለማንፀባረቅ የሚከተለውን ጥያቄ ተጠቅሟል፡፡

በአማርኛ / በሶማልኛ ቋንቋ የቀረበውን ፅሁፍ አንብቦ ለመረዳት ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ውስጥ የትኛውን ተጠቀምክ/ሽ?

ይህ ጥያቄ ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራቡድን ሁለት ውስጥ ያሉ ተተኳሪ ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የቀረቡትን ፅሁፍ አንብቦ ለመረዳት የተጠቀሙበትን የማንበብ ብልሃት ለመፈተሽ የቀረበ ነው፡፡ ጥያቄው በተጨማሪ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ መጠቀማቸውን ለማየትም አስችሏል፡፡ በዚህ መሰረት ተተኳሪ ተማሪዎች ድህረልምድ የሰጡት ምላሽ በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል (ድግግሞሽ እና በመቶኛ የተሰራ) (አባሪ ስምንትን ይመለከቱዋል)፡፡

ሰንጠረዥ ሃያ ዘጠኝ፡- ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ድግግሞሽን የሚያሳይ

ተ.ቁ	የማንበብ ብልሃቶች	**ሙከራ ቡድን አንድ** በሶማልኛ ቋንቋ የቀረበላቸውን ምንባብ አንብቦ ለመረዳት የተጠቀሙባቸው የማንበብ ብልሃቶች ድግግሞሽ እና መቶኛ ስሌት		**ሙከራ ቡድን ሁለት** በአማርኛ ቋንቋ የቀረበላቸውን ምንባብ አንብቦ ለመረዳት የተጠቀሙባቸው የማንበብ ብልሃቶች ድግግሞሽ እና መቶኛ ስሌት	
		ድግግሞሽ	መቶኛ(%)	ድግግሞሽ	መቶኛ(%)
	አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት				
1	ርዕሱን በማየት የምንባቡን ሀሳብ መተንበይ	5	83.3	5	83.3
2	የምንባቡን ሀሳብ በፍጥነት ለማግኘት መጣር	4	66.6	3	50
3	ከምንባቡ ውስጥ መረጃ ፈልፍሎ ለማውጣት መጣር	2	33.3	1	16.6
4	ማስታወሻ መያዝ	4	66.6	2	33.3
5	ደጋግሞ ማንበብ	4	66.6	6	100
6	የምንባቡን ሀሳብ በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ	-	-	2	33.3
7	አውዳዊ ፍቺ መጠቀም	4	66.6	4	66.6
8	የማንበብ ብልሃት ከሶማልኛ ወደአምርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ እያሸጋገሩ መጠቀም	3	50	5	83.3

	ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት				
9	ምንባቡን ለማንበብ ማቀድ	2	33.3	5	83.3
10	በማንበብ ወቅት ራስን መቆጣጠር	5	83.3	5	83.3
11	ምንባቡን በትክክል ማንበብን ለማረጋገጥ ራስን መገምገም	5	83.3	5	83.3
	ማካካስ የማንበብ ብልሃት				
12	የቃላትን ፍቺ መገመት	3	50	4	66.6
	ትውስታ የማንበብ ብልሃት				
13	የቀደመ እውቀትን መጠቀም	3	50	3	50
14	የምንባቡ ሀሳብ በአእምሮ ውስጥ ምስል እንዲፈጥር አድርጎ መጠቀም	**2**	33.3	-	-
	ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት				
15	ጥያቄ መጠየቅ	6	100	5	83.3
16	ከተማሪዎች ጋር መተባበር	3	50	3	50

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እንደያመላክተው ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የቀረበውን ምንባብ አንብቦ ለመረዳት የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን መጠቀማቸውን ያሳያል። በሰንጠረዡ እንደተንፀባረቀው ሙከራ ቡድን አንድ በተለይ ጥያቄ መጠየቅ፣ ርእሱን በማየት የምንባቡን ሀሳብ መተንበይ፣ በማንበብ ወቅት ራስን መቆጣጠር እና ምንባቡን በትክክል ማንበብን ለማረጋገጥ ራስን መገምገም ብልሃቶችን አብዛኞቹ ተማሪዎች እንደተጠቀሙ ያንፀባርቃል። ሙከራ ቡድን ሁለት ደግሞ በማንበብ ሂደት ግልፅ ያልሆነውን የምንባብ ክፍል (ሙሉውን ወይም የተወሰነውን ክፍል) ደጋግሞ ማንበብ፣ ርእሱን በማየት የምንባቡን ሀሳብ መተንበይ፣ ምንባቡን ለማንበብ ማቀድ፣ ጥያቄ መጠየቅ፣ በማንበብ ወቅት ራስን መቆጣጠር፣ ምንባቡን በትክክል ማንበብን ለማረጋገጥ ራስን መገምገም እና የማንበብ ብልሃቶችን ማሻሻገር የተባሉትን ብልሃቶች አብዛኞቹ ተማሪዎች መጠቀማቸውን ያንፀባርቃል።

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ሀሳብ ሁለቱም የሙከራ ቡድኖች አእምሮታዊ እና ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃቶች ላይ የበለጠውን ትኩረት ማድረጋቸውን እንዲሁም በሙከራ ቡድን አንድ ውስጥ ካሉ ተተኪሪ ተማሪዎች በበለጠ በሙከራ ቡድን ሁለት ውስጥ ያሉ ተተኪሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን እያሻሻገሩ የተጠቀሙ (ከሶማልኛ ወደአማርኛ) መሆናቸውን ነው።

የጥናቱ ጥያቄ ቁጥር አምስት፡- ከሶማልኛ ወደ አማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ያለ የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃት (ውጤት) እንዲጎለብት ምን ያህል አዎንታዊ ድርሻ አለው?

በዋናው ጥናት ጥያቄ ቁጥር አራት ግኝት እንዳመላከተው የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ከመጀመሪያ ወደሁለተኛ ወይም ከሁለተኛ ወደመጀመሪያ ቋንቋ የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ እንደሚጠቀሙ አመላክቷል፡፡ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ የመጠቀም ብቃታቸው በጨመረ መጠን አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው መጎልበት አለመጎልበቱ የዚህ ጥናት ሌላኛው ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡

የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ከአንዱ ቋንቋ መደሌላው ቋንቋ እያሸጋገሩ በመጠቀማቸው አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው መጨመር አለመጨመሩን ለማየት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ውጤት ማየት ተገቢ ነው፡፡

ከዚህ በታች የቀረበው ሰንጠረዥ ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ በመማራቸው በሶማልኛ እና በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳታቸው መጎልበት አለመጎልበቱን የሚያሳይ ነው(በጥንድ ናሙና ቲ- ቴስት የተሰላ)

ሰንጠረዥ ሰላሳ ፡- ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳታቸው መጎልበት አለመጎልበቱን የሚያሳይ

ተላውጦዎች	ቡድን	የተማሪ ቁጥር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	መደበኛ አማካይ ስህተት	የቲ ዋጋ	የነፃነት ደረጃ	ጉልህነት (ሁለትዮሽ አመልካች)
በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ቅድመ ልምምድ	ሙከራ ቡድን አንድ	73	5.01 8.64	1.712 1.368	.200 .160	-16.813	72	.000
ድህረ ልምምድ	ሙከራ ቡድን ሁለት	69	4.55 8.51	1.694 1.290	.204 .155	-17.111	68	.000
በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ቅድመ ልምምድ	ሙከራ ቡድን አንድ	73	6.55 9.70	2.247 1.468	287 .17	-9.507	70	000
ድህረ ልምምድ	ሙከራ ቡድን ሁለት	69	6.25 9.36	1.613 1.590	. .194 .191	-11.625	68	. 000

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ውስጥ የተሳተፉ ተተኳሪ ተማሪዎች በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው መጎልበት አለመጎልበቱን የሚያሳይ ነው። በሰንጠረዡ የተሰላው አሃዝ እንደሚያሳየው ቅድመልምምድ አንብቦ የመረዳት ብቃት ሙከራ ቡድን አንድ 5.01 ሙከራ ቡድን ሁለት 4.55 ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ ሙከራ ቡድን አንድ 6.55 ሙከራ ቡድን ሁለት 6.25 አማካይ ሆኖ ተመዝግቧል። በተመሳሳይ ድህረልምምድ ሙከራ ቡድን አንድ 8.64 ሙከራ ቡድን ሁለት 8.51 ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ ደግሞ ሙከራ ቡድን አንድ 9.70 ሙከራ ቡድን ሁለት 9.36 መሆኑንም ያሳያል። በየቋንቋው ሁለቱ ቡድኖች ቅድመ እና ድህረልምምድ አንብቦ መረዳት ያላቸው አማካይ ልዩነት በአማርኛ ቋንቋ ሙከራ ቡድን አንድ -3.630 ሙከራ ቡድን ሁለት -3.957 ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ የአማካይ ልዩነት ሙከራ ቡድን አንድ -3.155 ሙከራ ቡድን ሁለት -3.116 ነው።

ከላይ በሰንጠረዡ እንደተመላከተው በሙከራ ቡድን አንድ እና በሙከራ ቡድን ሁለት ውስጥ የተሳተፉ ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የቀረቡ ፅሁፎችን አንብበው መረዳታቸው ከቅድም ልምምድ ጋር ሲነፃፀር ጉልህ በሆነ መልኩ ለውጥ ማሳየታቸውን የተሰላው አሀዝ ያመላክታል። በሙከራ ቡድኖቹ ውስጥ የተሳተፉት ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የቀረቡላቸው ፅሁፎች የማንበብ ብልሃቶችን በተማሩባቸው ቋንቋዎች ባይሆንም (የማንበብ ብልሃቶችን ምን ያህል እያሻጋገሩ እንደተጠቀሙ ለማየት በማሰብ) በየተማሩባቸው ቋንቋ ያገኙትን የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እውቀት በመጠቀም አንብበው ለመረዳት ጥረት ማድረጋቸውን ግኝቱ ያመላክታል። ይህ የሚያሳየው ተማሪዎቹ የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን የመጠቀም ብቃታቸው በመጨመሩ እና ብልሃቶችን ከአንዱ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ እያሻጋገሩ በመጠቀማቸው አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው (ውጤታቸው) ጉልህ በሆነ መልኩ መጎልበቱን ነው።

5.2 የውጤት ማብራርያ (ትርጓሜ)

በዚህ የጥናቱ ክፍል የዋናው ጥናት መረጀ ውጤት ባመላከተው ግኝት መሰረት የውጤት ማብራሪያ የተሰጠ ሲሆን በዚህም የቀረበው መላምት አማራጭ ወይም ውድቅ መሆኑ የተንፀባረቀበት ነው።

የጥናቱ የመጀመሪያ ጥያቄ የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከቅድመልምምመድ በጎላ መልኩ በድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት እንዲጎለብት ምን ያህል አስችሏል? የሚል ነው። በዋናው ጥናት የውጤት ትንተና (የተገኘ ውጤት) በተንፀባረቀበት ክፍል አሀዛዊ መረጃው እንዳመላከተው ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ከቅድመልምምድ ውጤታቸው ጋር ሲነፃፀር ድህረልምምድ የማንበብ ብልሃቶችን መቼ፣ የት እና እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ከመገንዘብ በላይ ለማንበብ ተግባር የቀረቡ ፅሁፎችን አንብቦ ለመረዳት ብልሃቶችን በተግባር የመጠቀም ብቃታቸው ጉልህ የሆነ ለውጥ ማምጣቱ ተንፀባርቋል። በዚህም በጥናቱ የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እንዲጎለብት አስተዋፆ አለው? ብሎ የተነሳው መሰረታዊ ጥያቄ በግኝቱ መሰረት አዎንታዊ ምላሽ አግኝቷል።

በተለይ በጥናቱ የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ ሚዛናዊ የደረጃ ልኬት የተገኘው የተሰላ አሀዛዊ መረጃ (በሰንጠረዥ ስድስት፣ ሰባት፣ ስምንት፣ ዘጠኝ እና አስር) እንዳመላከተው ሙከራ ቡድን አንድ በአማርኛ አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት፣ በሶማልኛ ደግሞ አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ፣ ትውስታ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ አእምሮታዊ፣ ማካካስ፣ ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት በሶማልኛ አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ፣ ትውስታ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት ከቅድመልምምድ በጎላ መልኩ ድህረልምምድ ለውጥ አስመዝግበዋል። ሁለቱ የሙከራ ቡድኖች በተመሳሳይ ያጎለበቷቸው የማንበብ ብልሃቶች አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃቶች ናቸው። እነዚህ ብልሃቶች በአብዛኛው የማይታዩ (Non Observable) በመሆናቸው ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ በመማራቸው የበለጠውን አእምሮታዊ ባህሪ ማጎልበታቸውን ያሳያል። በጥናቱ ሰንጠረዥ አስራስድስት እና አስራሰባት እንደታየው ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት በሁለቱም ቋንቋ ትውስታ እና ማካካስ የማንበብ ብልሃት ድህረልምምድ ውጤታቸው በተወሰነ መልኩ ኢ-ጉልህ እንደሆነ አመላክቷል።

በጥናቱ የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ ክፍል አንድ ግኝት መሰረት (ሰንጠረዥ አራት እና አምስት) ተተኳሪ ተማሪዎች በሁለቱም ቋንቋ ድህረልምምድ

ጉልህ ለውጥ ካመጡበት አእምሮታዊ ብልሃት ውስጥ መረጃ ፈልፍሎ ማውጣት፣ ከልእለአእምሮታዊ ፅሁፍን ለማንበብ ማቀድ እንዲሁም ከማካካስ የማንበብ ብልሃት የቃላትን ፍቺ መገመት፣ ከትውስታ የፅሁፉ ሀሳብ በአእምሮ ምስል እንዲፈጥር አድርጎ መጠቀም ላይ ድህረልምምድ ዝቅተኛ አፈፃፀም ታይቶባቸዋል። በተመሳሳይ በሁለቱም ቋንቋ ድህረልምምድ ዝቅተኛ አፈፃፀም ከታየባቸው ከትውስታ የቀደመ እውቀትን መጠቀም ላይ ጠንካራ ለውጥ አሳይተዋል።

በጥናቱ የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ ክፍል ሁለት ለማንበብ ተግባር የቀረበን አጭር ፅሁፍ አንብቦ ለመረዳት ሙከራ ቡድኖች የተጠቀሙባቸውን የማንበብ ብልሃቶች እንዲገልፁ የተደረገበት ክንውን ውጤት እንዳንፀባረቀው (ሰንጠረዥ አስራአራት) ሙከራ ቡድን አንድ በአማርኛ ቋንቋ በተለይ ራስን እና አንብቦ መረዳትን መቆጣጠር፣ ጥያቄ መጠየቅ እና ማፍለቅ፣ ደጋግሞ ማንበብ እና አውድ መጠቀም ብልሃቶችን በድግግሞሽ ጉልህ በሆነ መልኩ መጠቀማቸው ተንፀባርቋል። ሙከራ ቡድን ሁለት ደግሞ ጥያቄ መጠየቅ፣ ደጋግሞ ማንበብ እና የምንባቡን ሀሳብ በፍጥነት ማግኘት የማንበብ ብልሃቶችን እንዲሁ በድግግሞሽ ጉልህ በሆነ መልኩ እንደተጠቀሙ ያሳያል። በሶማልኛ ቋንቋም ሙከራ ቡድን አንድ በተለይ ማስታወሻ መያዝ፣ ጥያቄ መጠየቅ እና የማንበብ ብልሃቶችን ማሻሻገር የተባሉ ብልሃቶችን ጉልህ በሆነ መልኩ በድግግሞሽ መጠቀማቸውን ያመላክታል። በተመሳሳይ ሙከራ ቡድን ሁለት ራስን እና አንብቦ መረዳትን መቆጣጠር፣ ጥያቄ መጠየቅ እና ደጋግሞ ማንበብ የማንበብ ብልሃቶችን ጉልህ በሆነ መንገድ መጠቀሙን ግኙቱ ያመላክታል። ይህ የሚያሳየው የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በተወሰኑ ብልሃቶች ላይ ዝቅተኛ አፈፃፀም ቢታይባቸውም በአብዛኛው ውጤታማ በሆነ መንገድ በራሳቸው ብልሃቶችን መርጠው መጠቀም መቻላቸውን ነው።

በጥናቱ ግኝት መሰረት የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች *መተንበይ፣ ዋናውን ሀሳብ በፍጥነት ማግኘት፣ *ማስታወሻ መያዝ፣ *ደግሞ ማንበብ፣ *አውድ መጠቀም፣ ጭምቀሀሳብ መፃፍ፣ *ብልሃቶችን እያሸጋገሩ መጠቀም፣ *የቀደመ እውቀትን መጠቀም፣ *ራስን እና አንብቦ መረዳትን መቆጣጠር፣ ራስን መገምገም፣ *ጥያቄ መጠየቅ፣ *ከሌሎች ጋር መተባበር የተባሉትን የማንበብ ብልሃቶች ከቅድመልምምድ በተሻለ ድህረልምምድ በጎላ መልኩ እድገት ማሳየታቸው ግኙቱ አመላክቷል። ከነዚህ ውስጥ

ልዩ ምልክት (asterisk) የተደረገባቸው ደግሞ ተተኳሪ ተማሪዎች ከፍተኛ ለውጥ ያሳዩባቸው ብልሃቶች ናቸው። ተተኳሪ ተማሪዎች የተወሰኑ ብልሃቶች በተለይ ምንባቡን ለማንበብ ማቀድ የቃላትን ፍቺ መገመት፣ ከምንባቡ ውስጥ መረጃ ፈልፍሎ ማውጣት፣ የፅሁፉ ሀሳብ በአእምሮ ምስል እንዲፈጥር አድርጎ መጠቀም ላይ አነስተኛ አፈፃፀም ተስተውሎባቸዋል።

ሌላው በሰንጠረዥ አስራሁለት እና አስራሶስት አንድ እንደተንፀባረቀው ሁለቱ የሙከራ ቡድኖች በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀማቸው ሲነፃፀር በተወሰኑ ብልሃቶች አጠቃቀም ጉልህ ልዩነት መኖሩ ታይቷል። ይህ የሚያስረዳው ሁለቱም የሙከራ ቡድኖች የማንበብ ብልሃቶችን በአማርኛ እና መሶማልኛ ቋንቋ በመማራቸው በየራሳቸው መንገድ ብልሃቶችን የመጠቀም አእምሮታዊ ብቃታቸው መጎልበቱን ያሳያል። የማንበብ ብልሃትን የማስተማር ዘዴ ጠንካራ መሆን አለመሆን፣ ተማሪዎች ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ የመጠቀም የአለመጠቀም ልዩነት እንጂ የማንበብ ብልሃትን የማስተማርያ ቋንቋ መለያየት የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ብቃት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ አያመጣም የሚል አንድምታ አለው።

የማንበብ ብልሃት የተለየን ግብ ለማሳካት ሆንተብሎ የሚተገበር ወይም አእምሮታዊ ክፍተት ባጋጠመ ጊዜ ክፍተቱን ለመሙላት በጠንካራ አንባቢዎች ሆንተብሎ የሚተገበር እቅድ ተኮር የመረዳት መንገድ ነው (Carrell 2006፣ Mokhtari and Richard 2002)። ለማንበብ ተግባር የቀረበን ፅሁፍ አንብቦ ለመረዳት የማንበብ ብልሃቶችን አቀናጅቶ መጠቀም ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ግኝት ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት ውስጥ የተሳተፉ ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ ከተሰጠ በኋላ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን በተለይ አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃቶችን ጉልህ እና ጠንካራ በሆነ መልኩ መጠቀም እንደቻሉ አመላክቷል። አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃቶች ከእያንዳንዱ የማንበብ ተግባር ጋር በቀጥታ የሚገናኙ፣ ውስብስብ የማንበብ ተግባር ባጋጠመ ጊዜ ችግሩን ለማስወገድ እና መረዳትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ፣ አቀናጅተው ለመጠቀም፣ ከአንድ አዲስ ሁኔታ ወደሌላ አዲስ ሁኔታ ወይም ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ ብልሃትን እያስፋፉ እና እያሸጋገሩ ለመጠቀም አቅም የሚፈጥሩ፣ የመረዳት እውቀትን እና መረዳትን

የመቆጣጠር እውቀትን ያካተቱ እንዲሁም ተማሪዎች በጥንድ እና በቡድን በመሆን በመወያየት ፣ በመከራከር ወዘተ ሀሳባቸውን በነፃነት በመግለፅ በንቃት እንዲሳተፉ የሚያስችሉ ናቸው (McNamara 2007፣ Lee 2007፣ Carrell 2006)።

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ግኝት ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን መቼ፣ የት እና እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው የተገነዘቡ በመሆናቸው ነፃ እና ራስመር ተማሪዎች በመሆን ከመምህራቸው ጥገኝነት ተላቀው በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ ራሳቸውን ችለው ብልሃቶችን በራሳቸው መንገድ መጠቀም እንደሚችሉ ያመላከተ ነው። ይህም Zhang (2012)፣ Ling (2011)፣ Talibi (2012)፣ Bimmel et al. (2001)፣ Cohen (1998)፣ Chamot and O`Malley (1990)፣ Oxford (1990) ጥናቶችን በሚደግፍ መልኩ በጥናቱ የተንፀባረቀው አልቦ መላምት ውድቅ ሆኖ "የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከቅድመልምምድ በተሻለ መልኩ በድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እንዲጎለብት አስተዋፆ አለው" የሚለው አማራጭ መላምት ተቀባይነትን አግኝቷል።

የጥናቱ ሁለተኛ ጥያቄ የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከቅድመልምምድ በጎላ መልኩ በድህረልምምድ አንብቦ የመረዳት ብቃት (ውጤት) እንዲጎለብት ምን ያህል አስተዋፆ አለው? የሚል ነው። አንብቦ መረዳት ውስብስብ አእምሯዊ ተግባር ነው። ተማሪዎች ይህን አእምሯዊ ሂደት ለመቆጣጠር፣ በውህድ አህድ ውስጥ ያለውን መረጃ ለመተርጎም፣ የማንበብ ብልሃቶችን ቢጠቀሙ ውጤታማ ይሆናሉ (Afflerbach et al. 2008)። የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አብይ ትኩረትም ተማሪዎች የማንበብ ብልሃትን በግልፅ በመማራቸው አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው መጎልበት አለመጎልበቱን መመርመር ነው። ጥናቱ በውጤት ትንተና ክፍል ባቀረበው መረጃ ላይ ተመስርቶ በሰጠው ትንተና መሰረት ለምርምሩ ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ አግኝቷል። ይህም Zhang (2008)፣ Rubin et al. (2007)፣ Greenfell and Macaro (2007)፣ Cohen (1998)፣ Chamot and O'Malley (1994)፣ Anderson (1991)፣ Oxford (1990)፣ O'Malley and Chamot (1990) ባቀረቡት ጥናት የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው እንዲጎለብት አስተዋፆ አለው ከሚለው ሐሳብ ጋር የሚስማማ ነው።

በጥናቱ ሂደት መከራ ቡድን አንድ፣ መከራ ቡድን ሁለት እና ጥብቅ ቡድኑ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ቅድመልምምድ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው ተፈትሾ እኩል ደረጃ ላይ መሆናቸው ተረጋግጧል (ሰንጠረዥ አስራስድስት)። ጥናቱ በመቀጠል እያንዳንዱን ቡድን በተናጠል የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ ከመሰጠቱ በፊት እና ከትምህርቱ በኋላ አንብቦ የመረዳት ውጤት ምን እንደሚመስል ፈትሿል (ሰንጠረዥ ሃያ ሶስት)። በዚህ መሰረት ሁለቱ የመከራ ቡድኖች እና ጥብቅ ቡድኑ በአማርኛም ሆነ በሶማልኛ ቋንቋ ከቅድመልምምድ በተሻለ ድህረልምምድ አንብቦ የመረዳት ውጤት ጉልህ በሆነ መልኩ ለውጥ (እድገት) ማሳየታቸው የጥናቱ ግኝት አመላክቷል። ይህ በዝርዝር ሲታይ በአማርኛ ቋንቋ መከራ ቡድን አንድ እና መከራ ቡድን ሁለት ጠንካራ፣ ጥብቅ ቡድኑ መካከለኛ የጉልህነት ጥንካሬ ደረጃ ያሳዩ ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ ደግሞ መከራ ቡድን አንድ እና መከራ ቡድን ሁለት ጠንካራ ጥብቅ ቡድኑ መጠነኛ የጉልህነት ጥንካሬ ደረጃ እንዳላቸው የተገኘው ውጤት ያንፀባርቃል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው መከራ ቡድን አንድ እና ሁለት ድህረልምምድ አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው ከፍ ባለ ደረጃ መጎልበቱን ነው። ጥብቅ ቡድኑም ቢሆን የተማረ በመሆኑ (በተለመደው መንገድ ቢሆንም) ከቅድመልምምድ በተሻለ ድህረልምምድ አንብቦ የመረዳት ውጤቱ ተሻሽሏል።

በዚህ ጥናት አንደኛው ቁልፍ ጉዳይ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር ተተኪ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው እንዲሻሻል አስተዋፆ ማድረግ አለማድረጉን መመርመር ነው። በጥናቱ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን የተከታተሉት ሁለቱ የመከራ ቡድኖች እና ሆንተብሎ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ ያልተሰጠው ጥብቅ ቡድን መካከል አንብቦ የመረዳት ውጤት መሻሻል አለመሻሻሉ ታይቷል። በዚህም ሶስቱ ቡድኖች ሲነፃፀሩ ድህረልምምድ በአማርኛም ሆነ በሶማልኛ ቋንቋ መከራ ቡድኖቹ ጉልህ በሆነ መልኩ ውጤታቸው መጎልበቱን ግኙቱ አመላክቷል (ሰንጠረዥ አስራስድስት)።

በተለይ በሰንጠረዥ አስራሰባት እና አስራስምንት የተንፀባረቀው ግኝት እንዳመላከተው በአማርኛም ሆነ በሶማልኛ ቋንቋ መከራ ቡድን አንድ እና መከራ ቡድን ሁለት ከጥብቅ ቡድኑ በተሻለ መልኩ አንብቦ መረዳታቸው መጎልበቱን ያሳያል። መከራ ቡድኖቹ ርስበርስ ሲነፃፀሩ ጉልህ ልዩነት አላሳዩም። ይህ የሆነበት ምክንያት መከራ ቡድን አንድ በአማርኛ መከራ ቡድን ሁለት ደግሞ በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን የተከታተሉ ቢሆንም የማንበብ ብልሃት ባልተማሩበት ቋንቋ የቀረበላቸውን

ፅሁፍ አንብበው ለመረዳት ችለዋል። ይህም ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት በተማሩበት ቋንቋ የቀረበላቸውን ፅሁፍ አንብበው ከመረዳታቸው በተጨማሪ የሙከራ ቡድኖቹ የማንበብ ብልሃቶችን ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ እያሸጋገሩ በመጠቀማቸው በሁለቱም ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው ጨምሯል። ይህም ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ከአንዱ ቋንቋ ወደሌላው ቋንቋ እያሸጋገሩ በመጠቀማቸው አንብቦ መረዳታቸው እንደጎለበተ ያሳያል። ከዚህ በተጨማሪ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ሶማልኛ ቋንቋ እናት ቋንቋቸው በመሆኑ ከአማርኛ ቋንቋ በተሻለ በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው መጎልበቱ ታይቷል። በአጠቃላይ ግኙቱ የሚያሳየው ሙከራ ቡድኖቹ የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ በመማራቸው አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው ጨምሯል። ይህም Zhang (2012)፣ Talibi (2012)፣ Bimmel et al. (2001)፣ Pressley (2000)፣ King (1994)፣ Olsen and Gee (1991) ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ከተጠቀሙ በሚታይ መልኩ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው ይጨምራል ብለው ካስቀመጡት ሀሳብ ጋር የሚስማማ ነው።

በምዕራፍ ሁለት ትውረታዊ ክፍል እንደተገለፀው Kellerman (1991) የተባሉት ፀሐፊ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር (በተለይ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች) አስፈላጊ አይደለም የሚል አቋም አራምደዋል። ፀሀፊው ያቀረቡት ምክንያት ተማሪዎች አስቀድመው የማንበብ ብልሃቶችን በመጀመሪያ ቋንቋ ያጎለበቱ (ሊያጎለብቱ የሚችሉ) እና ወደሁለተኛ ቋንቋ የሚያሸጋግሩ በመሆናቸው ብልሃቶችን ማስተማሩ አያስፈልግም የሚል ነው። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በግኙቱ መሰረት በተለይ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር አያስፈልግም የሚለውን ሐሳብ አልተቀበለውም (ውድቅ አድርጎታል)። ይልቁኑም የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ በመማራቸው ጉልህ በሆነ መልኩ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው መጎልበቱን ጥናቱ አመላክቷል። በመሆኑም በጥናቱ የተንፀባረቀው አልቦ መላምት ውድቅ ሆኖ "የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ተማሪዎች በራሳቸው መንገድ የማንበብ ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ በመጠቀም አንብቦ መረዳታቸው እንዲጎለብት አስተዋፆ አለው" የሚለው አማራጭ መላምት ተቀባይነትን አግኝቷል።

የጥናቱ ሶስተኛ ጥያቄ የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከቅድመልምምድ በተሻለ በድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ የመረዳት ብቃት ጋር አዎንታዊ ዝምድና እንዲኖር ምን ያህል አስችሏል? የሚል ነው። በዚህ ጥናት የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር ያለው ዝምድና ምን ገፅታ እንዳለው መመርመር ትኩረት የተሰጠው ሌለኛው ጉዳይ ነው። በዋናው ጥናት ለትምህርት የቀረቡት የማንበብ ብልሃቶች በአምስቱ ንኡሳን ብልሃት አይነቶች ውስጥ የሚካተቱ እና ከማንበብ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው አስራስድስት ብልሃቶች ናቸው። እነዚህ የማንበብ ብልሃቶች ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር ያላቸውን ዝምድና ወይም እነዚህ ብልሃቶች በአንብቦ መረዳት ውጤት ላይ አዎንታዊ ተፅእኖ ያላቸው መሆን አለመሆኑን ለመፈተሽ ህብረድህረት አሃዛዊ ስሌት አገልግሎት ላይ ውሏል።

በጥናቱ የውጤት ትንተና መሰረት የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና አንብቦ መረዳት አዎንታዊ ዝምድና እንዳላቸው አመላክቷል። በዚህም የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከቅድመልምምድ በተሻለ በድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና አንብቦ የመረዳት ብቃት እንዲጎለብት አስተዋፆ አለው? በሚል የቀረበው መሰረታዊ ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ አግኝቷል። ይህም Oyetunji (2013) ፣ Zhang (2012)፣ Ling (2011)፣ Pressley (2000)፣ King(1994)፣ O`Malley and Chamot (1990)፣ Oxford (1990) ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በሚገባ በተገነዘቡ እና በዛ ያሉ ብልሃቶችን በተደጋጋሚ እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው አውቀው በተግባር የመጠቀም ብቃታቸው በጨመረ መጠን አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው ይጨምራል ከሚለው ሀሳብ ጋር የሚስማማ ነው። እንደፀሀፊዎቹ ገለፃ ይህ እውን የሚሆነው የማንበብ ብልሃትን በግልፅ በማስማር ነው።

በጥናቱ የተገኘ ውጤት በተብራራበት ክፍል ሰንጠረዥ አስራዘጠኝ እና ሃያ አምስቱ ንኡሳን የማንበብ ብልሃቶች ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር ያላቸው ዝምድና ሙከራ ቡድን አንድ በአማርኛ ማካካስ በሶማልኛ ትውስታ እና ማካካስ ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ ልእለአእምሮታዊ እና ማካካስ በሶማልኛ ትውስታ የማንበብ ብልሃቶች ከአንብቦ መረዳት ጋር ኢ-ጉልህ ዝምድና ያላቸው ሲሆን የተቀሩት የማንበብ ብልሃቶች ጠንካራ አዎንታዊ ዝምድና እንዳላቸው አመላክቷል። ይህ ሁኔታ ከሁሉም የማንበብ ብልሃት

አጠቃቀም አንፃር ሲታይ በሰንጠረዥ አስራዘጠኝ ሙከራ ቡድን አንድ በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር አዎንታዊ ዝምድና እንዳለው ያመላከተ ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ ኢ-ጉልህ ግንኙነት እንዳለ ግኝቱ አመላክቷል። በሰንጠረዥ ሃያ የታየው ሙከራ ቡድን ሁለት በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ጋር ያለው ተዛምዶ ኢ-ጉልህ ሲሆን በሶማልኛ ቋንቋ ጠንካራ እና አዎንታዊ ጉልህ ዝምድና ያለው መሆኑን ነው። የማንበብ ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር አዎንታዊ ጉልህ ዝምድና አለው ማለት የብልሃቶች አጠቃቀም እውቀት በመጨመሩ ምክንያት በአንብቦ መረዳት ውጤት ላይ አዎንታዊ ተፅእኖ መፍጠር ችሏል ማለት ነው። ይህ የሚያሳየው በሙከራ ቡድን አንድ እና በሙከራ ቡድን ሁለት ውስጥ ያሉ ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በተማሩበት ቋንቋ የብልሃት አጠቃቀም እውቀታቸው የበለጠ መጎልበቱን ነው።

በጥናቱ ግኝት መሰረት በሙከራ ቡድን አንድ እና በሙከራ ቡድን ሁለት ውስጥ የተሳተፉ ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ በመማራቸው በአመዛኙ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀማቸው እና አንብቦ የመረዳት ብቃት (ውጤት) አዎንታዊ ዝምድና ያለው በመሆኑ በጥናቱ የተንፀባረቀው አልቦ መላምት ውድቅ ሆኖ “የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከቅድመልምምድ በተሻለ በድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ የመረዳት ውጤት ጋር አዎንታዊ ዝምድና አለው” የሚለው አማራጭ መላምት ተቀባይነትን አግኝቷል።

የጥናቱ አራተኛ ጥያቄ የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከአማርኛ ወደሶማልኛ እና ከሶማልኛ ወደአማርኛ ላለ የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ምን ያህል አስተዋፆ አለው? የሚል ነው። በዚህ ጥናት የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ያለ የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ እንዲጎለብት አስተዋፆ ያለው መሆን አለመሆኑን ለማየት ተሞክሯል። የጥናቱ ግኝት እንዳመላከተው የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ እያሸጋገሩ መጠቀማቸውን አመላክቷል። ይህም Talebi (2014: 2013: 2012)፣ Zhang (2012)፣ Yamashita (2012)፣ Liu (2001)፣ Bimmel et al. (2001)፣ ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የቀረበን ፅሁፍ አንብበው ለመረዳት ወይም በማንበብ

ሒደት የገጠማቸውን ችግር ለማስወገድ የማንበብ ብልሃቶችን ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ ወይም ከአንድ ተግባር (ሁኔታ) ወደሌላ ተግባር ሽግግር በማድረግ ይጠቀማሉ ብለው ካስቀመጡት ሀሳብ ጋር የሚስማማ ነው።

በዋናው ጥናት የመከራ ቡድኖችን የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤ ለመፈተሽ የቀረበው የማንበብ ብልሃት አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ ግኝት እንዳመላከተው (ሰንጠረዥ አራት እና አምስት) መከራ ቡድን አንድ እና መከራ ቡድን ሁለት ከቅድመልምምድ በጎላ መልኩ በድህረልምምድ የማንበብ ብልሃቶችን ከአንዱ ቋንቋ ወደሌላው ቋንቋ እያሸጋገሩ መጠቀማቸውን አመላክቷል። በጥናቱ በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ መናገር ቃለመጠይቅ ግኝት እንዳመላከተውም (ቃለመጠይቅ ጥያቄ ቁጥር 1-6) መከራ ቡድን አንድ ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ ከተጠቀሙት ይልቅ መከራ ቡድን ሁለት የማንበብ ብልሃቶችን ከሶማልኛ ወደአማርኛ ቋንቋ በጎላ መልኩ እያሸጋገሩ መጠቀማቸው ተንፀባርቋል። ይህ የሆነበት ምክንያት ተማሪዎች ውስን የአማርኛ ቋንቋ ችግር ያለባቸው በመሆኑ ብልሃቶችን ከአማርኛ ወደእናት ቋንቋቸው ሶማልኛ እያሸጋገሩ ከመጠቀም ይልቅ ከሶማልኛ ወደአማርኛ እያሸጋገሩ መጠቀም እንደሚቀናቸው ያመላክታል። ይህ ግኝት በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት ውስጥ የቋንቋ ጀማሪ ደረጃ መላምት (ሞዴል) (Linguistic Threshold Hypotheses) ትውረታዊ ሀሳብ በተንፀባረቀበት ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችንም ሆነ ክሂላቸውን ከመጀመሪያ ቋንቋ ወደሁለተኛ ቋንቋ ወይም ከሁለተኛ ቋንቋ ወደመጀመሪያ ቋንቋ እያሸጋገሩ ለመጠቀም የሁለተኛ ቋንቋ ብቃት (Second Language Proficiency) ወሳኝ ነው በማለት ያንፀባረቀውን ሀሳብ ያጠናክራል። በተጨማሪ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ፅሁፎችን አንብበው ለመረዳት ሶማልኛ ቋንቋ በጣም እንደሚረዳቸውም አስረድተዋል። ይህም ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ሒደት የመጀመሪያ ቋንቋቸውን እንደ ሀብት ወይም ብልሃት ይጠቀሙበታል (Cohen 2005፣ Grabe 1991) ከሚለው ሐሳብ ጋር ይስማማል።

በጥናቱ ግኝት መሰረት የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በድህረልምምድ ጉልህ በሆነ መንገድ በተለይ አእምሮታዊ እና ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃቶችን ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ እያሸጋገሩ የመጠቀም ብቃታቸው

እንደጎለበተ ያመላክታል። የማንበብ ብልሃትን ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ እያሸጋገሩ ለመጠቀም የመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ እና የሁለተኛ ቋንቋ የቋንቋ እውቀት ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው (Pressley et al.1998. Alderson 1984)። የማንበብ ብልሃትን ከመጠቀም አንፃር ደግሞ የልእለአእምሮታዊ ብልሃት እውቀት መሳኝ ነው። ይህም Zhang (2010፣ 2012)፣ Pressley et al. (1989) ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በንቃት ወደአዲስ የመማር ሁኔታ ለማሸጋገር የሚችሉት የማንበብ ብልሃት ግንዛቤ በተለይ የልእለአምሮታዊ ብልሃት ግንዛቤ እና የመጠቀም ብቃት ሲኖራቸው ነው ይላሉ። ልእለአእምሮታዊ እውቀት ሁለት መሰረታዊ እውቀቶችን አቅፎ የያዘ ነው። ይኸውም የመገንዘብ እውቀት እና መገንዘብን የመቆጣጠር እውቀት ናቸው። የመገንዘብ እውቀት የብልሃቶችን ምንነት መቼ፣ የት እና እንዴት መጠቀም እንደሚገባቸው የሚያስገነዝብ ሲሆን መገንዘብን የመቆጣጠር እውቀት ደግሞ ማቀድን፣ ራስን እና አንብቦ መረዳትን መቆጣጠርን እና የመገምገም እውቀት የያዘ ነው (O'malley and Chamot 1990)። በመሆኑም በጥናቱ ግኝት መሰረት ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ በመማራቸው እና ልእለአእምሮታዊ ብቃታቸውን በማጎልበታቸው የማንበብ ብልሃቶችን ከአንዱ ቋንቋ ወደሌላው ቋንቋ እያሸጋገሩ ለመጠቀም ችለዋል።

ይህ የጥናቱ ግኝት Zhang (2010፣ 2012)፣ Talebi (2013)፣ Bimmel et al. (2001) የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር ተማሪዎች ብልሃቶችን ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ ወይም ከአንድ ሁኔታ ወደሌላ አዲስ ሁኔታ እያሸጋገሩ ለመጠቀም ከፍተኛ አስተዋፆ አለው ከሚለው ሐሳብ ጋር ይስማማል። ከዚህ በተጨማሪ Oxford (1990)፣ O'Malley and Chamot (1990)፣ Carrell et al. (1989) በሁለተኛ ቋንቋ ውጤታማ አንብቦ መረዳት እንዲኖር የማንበብ ብልሃቶችን አቀናጅቶ ማስተማር እና ተማሪዎች ብልሃቶችን ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ እያሸጋገሩ እንዲጠቀሙ አቅም መፍጠር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው የሚለውን ሐሳብ ይደግፋል። የማንበብ ብልሃቶችን አቀናጅቶ ማስተማር በጥናቱ የተተገበረ ቁልፍ ጉዳይ ነው። በዚህ መሰረት በጥናቱ የተንፀባረቀው አልቦ መላምት ውድቅ ሆኖ "የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማሳተማር የማንበብ ብልሃት ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ያለን ሽግግር ለማጎልበት አስተዋፆ አለው " የሚለው አማራጭ መላምት ተቀባይነትን አግኝቷል።

የጥናቱ አምስተኛ ጥያቄ ከሶማልኛ ወደ አማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ያለ የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃት (ውጤት) መጎልበት ምን ያህል አስተዋፆ አለው? የሚል ነው። ከላይ በጥያቄ ቁጥር አራት በቀረበው ትንታኔ መሰረት የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ በድህረልምምድ በተደጋጋሚ እያሸጋገሩ መጠቀማቸውን አመላክቷል። ይህም Zhang (2008፣ 2012)፣ Cohen (2005)፣ Bimmel et al. (2001)፣ Pressley et al. (1998)፣ Grabe (1991) የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ከመጀመሪያ ወደሁለተኛ ወይም ከሁለተኛ ወደመጀመሪያ ቋንቋ እሸጋገሩ እንዲጠቀሙ ለማድረግ ያስችላል ከሚለው ሀሳብ ጋር ይስማማል።

በዚህ ጥናት የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ እያሸጋገሩ በመጠቀማቸው በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ከጥብቅ ቡድኑ በተሻለ መልኩ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው (ውጤታቸው) እንደጨመረ ግኝቱ ያመላክታል። የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ብቃት (ውጤት) ማደግ አንዱ ግብአት ተማሪዎቹ የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን በማቀናጀት ከአንዱ ቋንቋ ወደሌላው እያሸጋገሩ በመጠቀማቸው ነው። ይህም Zhang (2008፣ 2012)፣ Cohen (2005)፣ Bimmel et al.(2001)፣ Pressley et al. (1998) ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ከአንድ ሁኔታ ወደሌላ አዲስ ሁኔታ ወይም ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ እያሸጋገሩ በመጠቀማቸው የማንበብ ብልሃቶችን ለማጎልበት ያስችላል የሚለውን ሀሳብ ያጠናክራል።

በጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን በተለይ አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃቶችን ከሌሎቹ ብልሃቶች በተሻለ መልኩ ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ እያሸጋገሩ መጠቀማቸው በጥናቱ ግኝት ተንፀባርቋል። ለዚህ ተጠቃሽ የሆነው ምክንያት ተተኳሪ ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የቀረቡ ፅሁፎችን አንብቦ ለመረዳት በተለይ አእምሮታዊ እና ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃቶች ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው በመሆኑ ነው ። የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ድህረልምምድ በተለይ ልእለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃቶች ላይ ያላቸው ግንዛቤ ከፍ በማለቱ የማንበብ ብልሃቶችን ከአንዱ ቋንቋ

ወደሌላው እያሸጋገሩ ለመጠቀም አስችሏቸዋል። ተማሪዎች በማንበብ ሂደት የመረዳት እውቀታቸው (Knowledge of Cognition) እና መረዳታቸውን የመቆጣጠር ችሎታቸው (እውቀታቸው) (Regulation of Cognition / Knowledge of Regulation) መጨመር የማንበብ ብልሃትን እያሸጋገሩ ለመጠቀምም ሆነ ለማንበብ ተግባር የቀረበን ዕሁፍ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመረዳት ያስችላቸዋል። ይህም የልእለአእምሮታዊ ብልሃት አጠቃቀም ተክህኖ ነው (Zhang 2012፣ Phakiti 2006፣ Oxford 1990፣ O`Mally & Chamot 1990)።

በጥናቱ ግኝት መሰረት የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ ማስተማር ተማሪዎች ብልሃቶችን ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ እያሸጋገሩ በመጠቀም አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው እንዲጎለብት አስችሏል። በመሆኑም በጥናቱ የተንፀባረቀው አልቦ መላምት ውድቅ ሆኖ "ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ያለ የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ብቃት (ውጤት) እንዲጎለብት አስተዋፆ አለው" የሚለው አማራጭ ለማምት ተቀባይነትን አግኝቷል።

በአጠቃላይ የዚህ ጥናታዊ ዕሁፍ ግኝት እንዳንፀባረቀው በቀጥተኛ እና ኢ-ቀጥተኛ የማንበብ ብልሃት አይነቶች ውስጥ የሚካተቱ ንኡሳን የማንበብ ብልሃቶች (በተለይ በዚህ ጥናታዊ ዕሁፍ ውስጥ ትኩረት የተደረገባቸው) ተተኳሪ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ብቃታቸው እንዲጎለብት ከፍተኛ አስተዋፆ እንዳላቸው አመላክቷል። የማንበብ ብልሃት ተማሪዎች በማንበብ ሂደት የገጠማቸውን ችግር በመቅረፍ አንብቦ የመረዳት ብቃታቸውን ለማጎልበት የሚጠቀሙበት ሁነኛ መንገድ በመሆኑ ተተኳሪ ተማሪዎች ከቅድመልምምድ በተሻለ ድህረልምምድ ጉልህ በሆነ የአጠቃቀም ደረጃ (የብልሃት አይነቶችን አጠቃቀም ሁኔታዎች በተወሰነ መልኩ ልዩነት ቢኖርም) በመጠቀማቸው አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው ጎልብቷል። ይህ ግኝት በሁለቱም ተተኳሪ ቋንቋዎች አንብቦ መረዳት ላይ የተስተዋለ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ እያሸጋገሩ በመጠቀማቸው በሶማልኛ ቋንቋም ሆነ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው እንዲሻሻል ከፍተኛ አስተዋፆ አድርጓል።

ምእራፍ ስድስት

ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳብ

6.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር (Explicit Reading Strategy Instruction) አንብቦ የመረዳት ውጤትን ለማጎልበት እና ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ያለው አስተዋፆ ምን እንደሚመስል መመርመርን አላማ አድርጓል። ጥናቱ በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ ጅግጅጋ ሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት እና ጅግጅጋ ሼክ አብዱሰላም ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክህፍ ሶማልኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎችን ተተኳሪ አድርጎ የተነሳ ነበር። ጥናታዊ ፅሁፉ በጥናቱ ሒደት መከራ ቡድን አንድ፣ መከራ ቡድን ሁለት እና ጥብቅ ቡድን በማዘጋጀት እና ለመከራ ቡድኖቹ የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ግልፅ በሆነ የአቀራረብ ዘዴ በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ 40 ደቂቃ ርዝማኔ ያለው የማንበብ ብልሃት ትምህርት ለአስራ ሁለት ሳምንት (ለ 16 ሰዓት/ 960 ደቂቃ) በማስተማር እና ከጥብቅ ቡድን ጋር በማነፃፀር ከቅድመልምምድ በጎላ መልኩ ድህረልምምድ የባህሪ ለውጥ ማምጣት አለማምጣታቸውን በጥልቀት መርምሯል። ጥናቱ በምርምሩ ሂደት ያነሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በግልፅ ማስተማር

- ከቅድመ ልምምድ በጎላ መልኩ በድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እንዲጎለብት ምን ያህል አስችሏል?
- ከቅድመ ልምምድ በተሻለ በድህረልምምድ አንብቦ የመረዳት ውጤት እንዲጎለብት ምን ያህል አስተዋፆ አለው?
- የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር ምን ያህል አዎንታዊ ዝምድና እንዲኖር አስችሏል ?

- ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ያለ የማንበብ ብልሃት ሽግግር እንዲጎለብት ምን ያህል አስተዋፆ አድርጓል?

- ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ያለ የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ውጤት እንዲጎለብት ምን ያህል አዎንታዊ ድርሻ አለው? የሚሉ ናቸው።

በጥናታዊ ፅሁፉ ውስጥ የተነሱትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ በተለያየ መንገድ የተሰበሰበውን መረጃ በማስላት እና በመተንተን የተመዘገበው ግኝት ያመላከተው ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ በመማራቸው የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እውቀታቸው እንዲጎለብት፣ ብልሃቶችን በራሳቸው መንገድ በመጠቀም አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው ከፍ እንዲል የረዳቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ብልሃቶችን ከአንድ ሁኔታ ወደሌላ አዲስ ሁኔታ ወይም ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ በማሸጋገር በማንበብ ሂደት የገጠመን ችግር ማቃለል መቻላቸውን በዚህም ሳቢያ አንብቦ የመረዳት ውጤታቸው መጎልበቱን ነው።

በጥናቱ ሙከራ ቡድን አንድ እና ሙከራ ቡድን ሁለት በተለይ ከአእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ፣ ትውስታ፣ ማካካስ እና ማህበራዊ የማንበብ ብልሃቶች ውስጥ አንብቦ መረዳትን ለማጎልበት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸውን ብልሃቶች (መተንበይ፣ ዋናውን ሀሳብ በፍጥነት ማግኘት፣ መረጃን ፈልፍሎ ማውጣት፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ደግሞ (ደጋግሞ) ማንበብ፣ ሀሳብን በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ፣ አዳዲስ ቃላትን ለመረዳት አውዳዊ ፍቺ መመጠቀም፣ ከሶማልኛ ወደአማርኛ/ ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ማሸጋገር፣ የቀደመ እውቀትን መጠቀም፣ በአእምሮ ምስል መፍጠር፣ ዘዴ በተሞላበት መንገድ መገመት፣ ፅሁፍን ለማንበብ ማቀድ፣ ራስን እና አንብቦ መረዳትን መቆጣጠር፣ ራስን መገምገም፣ ጥያቄ መጠየቅ፣ ከሌሎች ጋር መተባበር) በግልፅ በመማራቸው ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም፣ አንብቦ የመረዳት ብቃት እና ብልሃትን እያሸጋገሩ በመጠቀም አንብቦ መረዳታቸው ከቅድመልምምድ ይልቅ በድህረልምምድ ጉልህ የሆነ ለውጥ አሳይቷል። ከማንበብ ብልሃት አጠቃቀም አንፃር የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች አእምሮታዊ፣ ልእለአእምሮታዊ እና ማህበራዊ ብልሃቶች ላይ የበለጠ ትኩረት ማድረጋቸው ታይቷል። የልእለአእምሮታዊ ብልሃት አጠቃቀም እውቀት

መጎልበት ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲጠቀሙ ከማስቻሉም በተጨማሪ ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ትልቅ ሚና አለው።

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ በመማራቸው ከቅድመልምምድ በጎላ መልኩ ድህረልምምድ የብልሃት አጠቃቀም እውቀታቸው ጨምሯል። በዚህም የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ርዕስን እና ንኡሳን ርዕሶችን በማየት መተንበይ፣ የምንባቡን ሀሳብ በፍጥነት ማግኘት፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ደጋግሞ ማንበብ፣ አውዳዊ ፍቺ መጠቀም፣ የማንበብ ብልሃት ከሶማልኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደሶማልኛ እያሸጋገሩ መጠቀም፣ በማንበብ ወቅት ራስን መቆጣጠር፣ የቀደመ እውቀት መጠቀም፣ ጭምቀሀሳብ መፃፍ፣ ጥያቄ መጠየቅ እና ከተማሪዎች ጋር መተባበር የተባሉ የማንበብ ብልሃቶች ላይ የበለጠ ትኩረት እንዳደረጉ መረዳት ተችሏል። ተተኳሪ ተማሪዎች በተወሰኑ ብልሃቶች ላይ ማለትም ምንባቡን ለማንበብ ማቀድ፣ የቃላትን ፍቺ መገመት፣ ከምንባቡ ውስጥ መረጃ ፈልፍሎ ማውጣት፣ የፅሁፍን ሀሳብ በአእምሮ ምስል እንዲፈጥር አድርጎ መጠቀም ላይ ዝቅተኛ አፈፃፀም ታይቶባቸዋል። ለዚህ የቀረበው ተጠቃሽ ምክንያት አብዛኞቹ የተጠቀሱት ብልሃቶች ውስብስብ አእምሯዊ ሂደት የሚታይባቸው በመሆኑ ነው።

በጥናቱ የተንፀባረቀው መሰረታዊ የምርምር ግኝት የማንበብ ብልሃትን በማስተማር የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም፣ አንብቦ መረዳት እና ሽግግር እንዲሁም በሽግግር ምክንያት አንብቦ መረዳት መካከል ግንኙነት እንዳለ አመላክቷል።

6.2 የመፍትሄ ሀሳብ

የማንበብ ክሂል በቋንቋ ትምህርት ክፍል የሚሰጥ ተግባርን በሚገባ ለመረዳት እና ለማከናወን፣ አካዳሚያዊ ግብን ለማሳካት እና ጠንካራ የህይወት ዘመን ተማሪ ለመሆን የሚያግዝ ክሂል ነው። የማንበብ ክሂል መሰረታዊ የሚባሉትን ክፍሎች ማለትም ፊደልን እና ቃላትን መለየት የሀሳብ ፍሰትን ጠብቆ ማንበብ፣ ቅላፄ እና አንብቦ መረዳትን አካቶ የያዘ ነው። ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የቀረበላቸውን ፅሁፎችንም ሆነ ሌሎች ተጨማሪ አጋዝ ፅሁፎችን በሚገባ አንብበው መረዳት እንዲችሉ የተለያዩ ብልሃቶችን ማስተማር ያስፈልጋል። ከዚህ አንፃር ጥናቱ በግኝቱ መሰረት ያንፀባረቀውን

የመፍትሄ ሀሳቦች ወይም አስተምህሮታዊ አንድምታዎች (Pedagogical Implication) እና ወደፊት ሊሰሩ የሚገባቸውን የምርምር አቅጣጫዎች አመላክቷል።

የመጀመሪያው ሀሳብ የማንበብ ክሂልን የማስተማር የመጨረሻ ግብ ተማሪዎች የማንበብ አላማ እና ግብ ያላቸው፣ በራሳቸው የሚተማመኑ እና ከፍ ያለ አንብቦ የመረዳት ብቃት የተጎናፀፉ፣ የተረዱትን ማንፀባረቅ የሚችሉ ማድረግ ነው። በመሆኑም ማንበብን በጥንቃቄ እና በትጋት በማስተማር ተማሪዎች ውጤታማ አንባቢዎች እንዲሆኑ መስራት እንደሚገባ አሳይቷል።

ሌላው በማንበብ ሂደት ከፍተኛ መካከለኛ እና ዝቅተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የቀረቡ ፅሁፎችን አንብበው ለመረዳት እና በማንበብ ሒደት የገጠሙ ችግሮችን ለማቃለል የማንበብ ብልሃት ጉልህ ጠቀሜታ ያለው እንደሆነ ግኙቱ አመላክቷል። የማንበብ ብልሃት ተማሪዎች ራስ መር አንባቢዎች እንዲሆኑ፣ ለትምህርት መነሳሳት ያላቸው፣ ነፃ እና የማር ብቃት እምነታቸው ከፍ ያለ እንዲሆኑ የሚያስችል ነው። በመሆኑ ተማሪዎች ለማንበብ ብልሃት ትኩረት በመስጠት የማንበብ ክሂላቸውን ራሳቸው እንዲያጎለብቱ እድል መስጠት እንደሚያስፈልግ ግኙቱ አሳይቷል።

የማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽን በግልፅ ማስተማር ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በተማሬበት ቋንቋ እንዲጠቀሙ ብቻ ሳይሆን ከአንድ አዲስ ሁኔታ ወደሌላ አዲስ ሁኔታ ወይም ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ ጠቃሚ በሆነ መልኩ እያሸጋገሩ በመጠቀም በማንበብ ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ችግር መፍታት እንዲችሉ የሚያደርግ በመሆኑ በዚህ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንደሚገባ ጥናቱ አመላክቷል።

Cohen et al. (1998) እንደሚመክሩት መምህራን ጠንካራ በሆነ የማስተማር መንገድ የማንበብ ብልሃትን ሲያስተምሩ እና የተማሪዎችን አቅም ሲገነቡ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት አቅማቸው እንዲጎለብት እና ራስመር ተማሪዎች እንዲሆኑ ያስችላል። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍም የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና አንብቦ የመረዳት ብቃት ላይ አዎንታዊ አስተዋፆ እንዳለው ያመላከተ በመሆኑ መምህራን ይህን የማንበብ ብልሃት የማስተማሪያ ዘዴ (የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር) አጠናክረው ተግባራዊ በማድረግ ተማሪዎች ጉልህ በሆነ መንገድ የማንበብ ክሂላቸውን ማጎልበት እንደሚገባቸው አመላክቷል።

ለጥናቱ መረጃ በማሰባሰብ ወቅት መምህራን የማንበብ ብልሃት የማስተማር ዘዴ እና ምዘናን በተመለከተ አስቀድመው ስልጠና ወስደው የማያውቁ በመሆናቸው የማንበብ ብልሃትን ሆን ብለው በግልፅ እና በዝርዝር አስተምረው እንደማያውቁ አመላክተዋል። በመሆኑም ቅድመስራ እና በስራ ወቅት የማንበብ ብልሃትን እንዴት ማስተማር እና መመዘን እንዳለባቸው ጠንካራ ስልጠና በመስጠት መምህራንን ማጠናከር አስፈላጊ መሆኑን አመላክቷል።

ሌላው የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ በሚሰጥበት ወቅት ተማሪዎች ላይ የታየው የደስተኝነት ስሜት፣ መነቃቃት፣ ለመማር መፈለግ እና ለማንበብ ተግባር የቀረበን ፅሁፍ አንብቦ ለመረዳት የታየ ጥረት ትምህርቱ አንዳች ነገር እንደፈጠረ አመላክቷል። በመሆኑም የማንበብ ብልሃት የቋንቋ ትምህርት አካል ሆኖ በስርአተ ትምህርት እና በመማሪያ ማስተማሪያ መፅሀፍ ውስጥ በማካተት በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት በሀገራችን ኢትዮጵያ በየትኛውም አካባቢ ያሉ ተማሪዎች በማንበብ ሂደት የማንበብ ብልሃቶችን ሆን ብለው በመጠቀም በራሳቸው መንገድ የማንበብ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ለማድረግ እድል መስጠት እንደሚያስፈልግ አመላክቷል።

በመጨረሻ በየትኛውም የትምህርት መስክ ለትምህርት የሚቀርበውን ጉዳይ የማስተማሪያ መንገድ ተማሪዎች ትምህርቱን በሚገባ እንዲገነዘቡ ወይም የታሰበው ሳይሳካ እንዲቀር ሊያደርግ ይችላል። በመሆኑም በቋንቋ ትምህርት ክፍል የተለያዩ ክሂሎችን እና ብልሃቶችን ለማስተማር ተገቢ የትምህርት አቀራረብ መምረጥ የቀረበው ትምህርት ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል መሆኑን አመላክቷል።

ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ መነሻ ሀሳብ በመውሰድ ወደፊት ቢሰሩ መልካም ነው ብሎ ያሰባቸውን የምርምር አቅጣጫዎች ከዚህ በታች አቅርቧል።

- በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ የተገኘው ውጤት የበለጠ እንዲዳብር የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን ረዘም ላለ ጊዜ በመስጠት ጥናት ቢደረግ (Longitudinal Research)፣
- የማንበብ ብልሃቶችን አቀናጅቶ ማስተማር በጣም ጠቃሚ እንደሆነ በጥናቱ የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት ውስጥ ተንፀባርቋል። በመሆኑም ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ አስራስድስት ንኡሳን የማንበብ ብልሃቶችን ለትምህርትነት አቅርቧል በተማሪዎች

የብልሃት አጠቃቀም እና አንብቦ መረዳት ላይ አመርቂ ውጤት እንደታየ ግኙቱ አመላክቷል። ወደፊት ማንበብን ለማስተማር ይጠቅማሉ ተብለው የሚጠቀሱትን የማንበብ ብልሃቶች በማካተት ቁጥራቸውን ጨምሮ በማስተማር ጥናት ቢደረግ፣

- ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የማንበብ ብልሃቶችን ከአንብቦ መረዳት ጋር አያዞ በጥልቀት መርምሯል። ሌሎች ወገኖች ብልሃቶች በሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ላይ ያላቸውን ተተግባሪነት እና አስተዋፆ በተመለከተ ጥናት ቢያካሂዱ፣
- ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የማንበብ ብልሃቶችን በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ በማስተማር የተገኘውን ውጤት መርምሮ ዝርዝር ግኙቶችን አንፀባርቋል። ከቋንቋ ቤተሰብ አንፃር አማርኛ ሴሜቲክ ሶማልኛ ቋንቋ ደግሞ ኩሺቲክ በመሆናቸው በስርአተ ፅህፈት፣ በቋንቋ መዋቅር ወዘተ የተለያዩ ናቸው። ወደፊት ተመሳሳይ ቋንቋዎችን በመውሰድ እና ብልሃቶችን በማስተማር ያለው ገፅታ ቢመረመር፣
- በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ግኝት መሰረት የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በሚገባ የመጠቀም ችግር ተስተውሎባቸዋል። ሌሎች ወገኖች ሁለት ወይም ከዛ በላይ ቋንቋዎችን በሚገባ የሚጠቀሙ ተማሪዎችን (ተመጣጣኝ የሁለት ቋንቋዎች እውቀት ያላቸውን ተማሪዎች) የማንበብ ብልሃት ሽግግር እና አንብቦ መረዳት ምን ገፅታ እንዳለው ቢያጠኑ፣
- ሽግግርን በተመለከተ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ኢ-ቋንቋ ጉዳዮች ተብለው ከሚጠቀሱት ውስጥ የማንበብ ብልሃት ላይ ትኩረት አድርጓል። ሌሎች ወገኖች ቋንቋ ነክ ጉዳዮች ላይ በመመስረት (ድምፅ፣ ምእላድ፣ ቃል ፣ትርጉም፣ አገባብ፣ ዲስኮርስ ...) ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ ያለው ሽግግር ዝርዝር ገፅታ ምን እንደሚመስል ጥናት ቢያደርጉ፣
- የማንበብ ብልሃት በሌሎች የሀገሪቱ ቋንቋዎች እና በሌሎች የትምህርት መስኮች (በማህበራዊ ሳይንስ፣ በተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት መስክ ለምሳሌ ሂሳብ፣ ፊዚክስ ወዘተ) ላይ ያለው ተተግባሪነት እና አስተዋፆ ቢጠና፣
- በመጨረሻም በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ ያልተሸፈነን ጉድይ ወይም ያለን ክፍተት በማጤን ሌሎች ወገኖች ጥናት ቢያደርጉ ይጠቅማል።

ዋቢ ፅሁፎች

መኮንን ናና፡፡ (2000)፡፡ “በኦሮምኛ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ግምገማ ” አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምርት መርሀ ግብር ለኤም ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት(ያልታተመ)፡፡

ሜዲካል ሳይንሳዊ መፅሄት (አማርኛ እትም፡፡ በሳምንት ቅዳሜ አንድ ጊዜ የሚታተም)፡፡ (2002)፡፡ (ሐምሌ 2002)፡፡ አዲስ አበባ፡፡ በሜደ.አይ.አ.ሲ. የሕክምና መረጃዎች አሳታሚ ኃ.የተ.የግ.ማ. ስር እየታተመ የሚወጣ፡ ሚሊኒየም ማተምያ ቤት የሚታተም፡፡

ሪፖርተር ጋዜጣ (አማርኛ እትም፣ በሳምንት ሁለት ቀን የሚታተም)፡፡ (2007)፡፡ (ሰኔ 10/2007)፡፡ አዲስ አበባ፡፡ በሚዲያ እና ኮሚኒኬሽን ሴንተር (ኤም.ሲ.ሲ.) ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

ሺፈራው በቀለ፡፡ (2004)፡፡ ባህል እና ልማት በኢትዮጵያ፡፡ አዲስ አበባ ፡፡ በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ፅሁፎች፡፡ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ፡፡

ተክላይ ትእዛዙ፡፡ (2000)፡፡ “በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ8ኛ እና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ንባብ ጊዜ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና የመምህራን ግንዛቤ ተጣጥሞሽ ፍተሻ ” አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምርት መርሀ ግብር ለኤም ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት(ያልታተመ)፡፡

አለማየሁ አበበ፡፡ (ተርጓሚ) (2003)፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ከመጀመሪያው እስከ አሁን ዘመን (ፀሀፊዎች- አንድርዜይ ባርተኒስኪ እና ዮሳና ማንቴል-ኒችስ) አዲስ አበባ ZA ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡

አማርኛ የተማሪ መፅሀፍ 9ኛ ክፍል፡፡(2005)፡፡ አማርኛ፡፡ የተማሪ መፅሀፍ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሚክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር፡፡

አዲስ አድማስ ጋዜጣ፡፡(አማርኛ እትም፣ ዘወትር ቅዳሜ የሚታተም ሳምንታዊ ጋዜጣ)፡፡(2006)፡፡ (ጥር 17/2006)፡፡አዲስ አበባ፡፡ አድማስ አድቨርታይዚንግ ኃ.የተ.የግ.ማ ብርሃንና ሰላም ማተምያ ድርጅት እየታተመ የሚወጣ፡፡

አዲስ ዘመን ጋዜጣ፡፡ (2003)፡፡ (አማርኛ እትም፣ በየእለቱ እየታተመ የሚወጣ)፡፡ (ሚያዝያ 28/2003) የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፡፡ አዲስ አበባ፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡

አዲስ ዘመን ጋዜጣ፡፡ (1994)፡፡ (አማርኛ እትም፣ በየእለቱ እየታተመ የሚወጣ)፡፡ ሐምሌ 24/1994 ዓ.ም፡፡የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡

እንዳለጌታ ከበደ፡፡ (1996)፡፡ ከጥቁር ሰማይ ስር፡፡ (አጫጭር ልቦለዶች እና ትረካዎች)፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተምያ ቤት ታተመ፡፡

እንግዳ ዘውዴ፡፡ (1992)፡፡ “የቶፕ ዳውን (Top-down) የንባብ ማስተማርያ ሞዴል በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ተተግባሪነትና ውጤታማነት”አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምርት መርሀ ግብር ለኤም ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት(ያልታተመ)፡፡

የኔሰው ደሴ፡፡ (1990) ፡፡ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ መካክስ የንባብ ክሂል ማስተማርያ ሞዴልን በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋፆ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምርት መርሀ ግብር ለኤም ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት(ያልታተመ)፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት፡፡ (1987)፡፡ አዲስ አበባ፡፡ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ፡፡

ያለው እንዳወቅ፡፡ (2006)፡፡ የምርምር መሰረታዊ መርሆዎች እና አተገባበር፡፡ አዲስ አበባ፡፡ አልፋ አታሚዎች፡፡

ገቢዎች ኤጀንሲ፡፡ (1996)፡፡ ግብር፡፡ ለግብር ከፋዮች ህብረተሰብ የተዘጋጀ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና መረጃ ሰጪ ፅሁፍ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በገቢዎች ኤጀንሲ የተዘጋጀ፡፡

ጌትነት ማሞ፡፡ (1998)፡፡ “በጋሞኛ ቋንቋ አፍፈት የሆኑ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መዋቅር እውቀት እና የአማርኛ ውህድ አሀዶችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ” አዲስ

አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምርት መርሀ ግብር ለኤም ኤ ዲግሪ በከፊል ማሚያነት የቀረበ ጥናት(ያልታተመ)።

ግሩም ጥበቡ። (2000)። “የታች ላይ (Bottom-up) የንባብ ማስተማርያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂልን ለማዳበር ያለው ውጤታማነት እና ተተግባሪነት አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ተማሪዎች ላይ የተካሄደ” አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምርት መርሀ ግብር ለኤም ኤ ዲግሪ በከፊል ማሚያነት የቀረበ ጥናት(ያልታተመ)።

ዘሪሁን አስፋው። (1992)። የስነጽሁፍ መስረታውያን። አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ቤት ታተመ።

ዘውዱ መብሬ። (1998)። “በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ አሀዶችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ” አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምርት መርሀ ግብር ለኤም ኤ ዲግሪ በከፊል ማሚያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

Abebe Damtew. (2011). “Teaching Reading Skills in English as a Foreign Language Through Interactive Class Room: Teacher Versus Plasma Teaching” College of Humanities, Language, Communication and Journalize Studies A.A.U (Unpublished Dissertation).

AF SOOMAALI. (2003). AF SOOMAALI. BUUGGA ARDAYGA: FASALKA 9aad: Waxxaa Soo Saaray Xafiska Waxbarashada DDS. Geeddi Socodaka Horumarinta Manhajka, C/baadhista & Qiimeynta.

Afflerbach, P., Pearson, P. D., and Paris, S. G. (2003). Clarifying Differnces Between Reading Skills and Reading Sategies. Journal of International Reading Association ISSN. 0034-0561, DOI:10: 1598/ RT. 61-5.1.

Akamatisu, N(2003). The effects of frst lanauge orthographic features on second language reading in text.Journal of language learning vol. 53 N5 pp. 207-230.

Alderson,J.C. (2005). Diagnosing forign language proficiency: The interface between learning and assessment. New York: The Tower Building.

Alderson, J.C. (1984). Reading in a Foreign Language.A Reading or a Language Problem?In Alderson, J. C., and Urquart, A. H. (Eds.).Reading in a Foreign Language London; Longman Publishers/pp.1-24.

Ali- Hassan, H.(2005). Instructional Design Model and Theories: Information Processing Theory .Retrivede on 27 Julay 2016 from https://elearningindustry.com/information-processing-theory.

Anastasion, D. and Griva, E. (2009).Awareness of Reading Strategy Use and Reading Comprehension Among Poor and Good Readers. (Online) Available In http: // ilkogreim –online.org.tr.

Anderson,N.J. (2005). L2 Learning Strategies. In E.Hinkel (Ed.),Hadbook of research in second language teaching and learning . Mahwah, NJ.Lawrence Erlbaum Associates.

Anderson, N. (1991). Individual Differences in Strategy use in Second Language Reading and Testing. The Modern Language Journal Vol. 7,5N,2 pp 46 -72.

Anderson, N.J. (1999). Exploring Second Language Reading.Issues and Strategies. Boston: Heinle and Heinle Publishers

Anderson, R. C., and Pearson, P. D. (1984).A Schema –Theoretic View of Basic Processes in Reading Comprehension.In P. D. Pearson (Ed.). Handbook of Reading Research New York: Longman. Vol. 1, pp 225-291.

Ballow, A. K. (2012). Using Explicit Strategy Instruction to Improve Reading Comprehansion.Submitted in Partial Fulfillment of the Requirments for the Degree of M. S. Literacy Education Ralph C. Wilson, Jr. Schhool of Education.Fisher Digital Publications.

Bandura,A. (1989). Social Cognitive Theory.In R. Vasta (Ed.), Annals of Child Development.Vol. 6.Six Theories of Child Development. Greenwich, CT: JAI Press.

Belilew Molla. (2015). The Relationship between Reading Strategy use and Reading Comprenension among Ethiopian EFL Learners International Journal on Studies in English Languge and Literature (IJSELL) ISSN 4347-3126 Vol. 3. No. 9, pp 34-41.

Bernhardt ,E. (1991). Reading Development in a Second Language: Theortical, Empirical and Classroom Perspectives.Norwood ,NJ: Ablex.

Bernhardt, E. B. and Kamil, M. L. (1995). "Interpreting Relationships Between L1 and L2 Reading: Consolidating the Linguistic Threshold and The Linguistic Interdependence Hypotheses." Applied Linguistic 16,pp 115-34.

Bimmel, P. E., Bergh, H.V., and Oostdam, R.J. (2001).Effects of Strategy Training on Reading Comprehension in First and Foreign Language.European Journal of Psychology of Education. Vol. XVI N 4, pp 509-529.

Bimmel, P.E (1999). Training and transfer of reading strategies instruction in the first language and transfer to a foreign language- An intervention study with students in secondary education Hertogenbosch: Malmberg 1999.

Block, C. C., and Pressley, M. (2002). Comprehension Instruction Research – Based Best Practices (Eds.) New York: Guilford Press.

Block, E. (1986). The Comprehension Strategies of Second Language Readers. TESOL, Journal of Education Vol. 20(3) PP. 463-494.

Bossers, B. (1991). Reading in two language : a study of reading comprehension in Dutch as a second language and in Turkish as a first language. Rotterdam, the Netherlonds Drukkeri, Van Driel.

Brown, H.D. (2001). Teaching by Principles an Interactive Approach to Language Pedagogy (2nd Ed.). White Plains, NY: Addison Wesley Longman.

Brown, H.D. (1994). Principles and Practices of Language Learning and Teaching . Englewood cliffs, NJ: Prentice Hall .

Byrd, E.H., Carter, E.C. and Waddoups, S. D. (2001).Taking Control of Your Collage Reading and Learning Orlando, EL. Harcourt College Publishers.

Cain, K. and Oakhill,J.V.(2006). Assessment matters:Issues in the measurement of reading comprehension . British Journal of Education Psychology vol. 76(4) pp 697-708.

Carrell, P. L. (1998). Can Reading Strategies be Successfully Taught? Retrieved on 18-July – 2014, from http://longue;hyperhuba.acjp.galt/pub/tlt/98mar/Carrall.htm/.

Carrell, P. L. (1998). Can Reading Strategies be Successfully Taught? Retrieved on 21- May 2015, from http://Alt-publications-org/old-tit-files198/ mar carrell /htm.

Carrell, P. L. (2006). Can Reading Strategies be Successfully Taught? The Language Teacher Journal JALT N22/pp 2-8.

Carrell, P. L., Gajduseve, L. and Wise, T. (1998).Metacognition and EFL/ESL.Reading Instructional Science. Vol. 26 , pp 97-112.

Celce – Murcia, M. (1991).Teaching English as a Second or Foreign Language.(2nd Ed.) Los Angeles, Univesity of California.

Chamot, A. U. (2005). Language Learning Strategy Instruction. Current Issues and Research Annual Review of Applied Linguistics 25,pp 112 -130.

Chamot, A. U. and Kupper, L. (1989).Learning Strategies in Foreign Language Instruction. Foreign Language Annals, N 22, pp 13-24.

Chamot, A.U., & O'Malley, J.M. (1994). The CALLA Handbook: Implementing the Cognitive Academic Language Learning Approach. New York: Longman.

Clear, J. (2010). Mental Models: How to Train your Brain to Think in new ways. Retrive Jun 20/ 2016, From https://jamesclear. Com/Feynman-mental models.

Cohen, A. D (1991).Strategies in Second Language Learning Insight from Research. In Philips ,K.A.(Ed) pp 107-119.

Cohen, A. D. (1996). Second Language Learning and use Strategies Clarifing the Issues Center for Advanced Research on Language Acquisition University of Minnesota, Minneapolis.

Cohen, A. D. (1999). Strategies in Learning and using a Second Language. New York. Addison Wesley Longman.

Cohen, A. D, Wearer, S. F., & Li, T. (1998) . The impact of strategic based instruction on speaking a foreign language. In A. Cohen (Ed.). Strategies in learning and using a second language . London: Longman .pp107-56.

Cohen, A.D (1998). Strategies in Learning and Using a Second Language.London : Longman.

Cohen, A. D., and Chi, J. C. (2005). Language Strategy use Survey. Retrieved atMarch 13, 2016 from http://www.carla. umn. edu /about/profiles/cohen-papers/Lg-strat-Srvy.htm/.

Cohen,L.,Manion,L.,and Morrison,K. (2007). Research Methods in Education . USA and Canada: Routledge, New York, NY 10016.

Cook, V. (2004). Bilingual Cognition and Language Teaching ,Draft of Paper for Talk in Taiwan. Retrieved at May 13/2015, from http://www..Net/ world.com/ Vivian.c/ writing/ paper/ Bil cog Teaching.htm 10/1/2013.

Cook,V.(2003).Changing The First Language In The L2.Retrieved at May 13/2015, from http:// www.Net/ Word .Com/Vivian C/ Writing /paper/Fxintro.Htm.

Cubukcu, F. (2007).An Investigation of Reading Strategies Employed by Trainee Teachers. GEMA online Journal of Languate Studies, Vol. 7(2) pp 95 -110.

Cummins, J. (1979). Linguistic Interdependence and the Development of Bilingual Children. Review of Educational Research: Vol. 49, PP. 222-251.

Cummins, J. (1981). The Role of Primary Language Development in Promoting Educational Success for Language Minority Students.In California State Department of Education (Ed), Schooling and Language Minority Students.A Theoretical framework. Los Angeles. Evaluation, Dissemination and Assessment Center California State University.

Cummins,J.(1991).Interdependence of First and Second Language Proficiency in Bilingual Children. In E. Bialystok (Ed), Language Processing in Bilingual Children New York, NY: Cambridge University Press: Pp 70-89.

Cummins, J. (2005). Teaching for Cross – Language Transfer in Dual Language Education: Possibilities and Pitfalls. TESOL Symposium on Dual Language Education: Teaching and Learning Two Languages in the EFL Setting. Turkey. Istanbul – Bogazici University.

Cummins, J., Swain, M., Nakajima, k., Handscombe, J., Green, D., and Tran, C. (1984). Linguistic interdependence among Japanese and Vietnamese immigrant. In C. Revera (Ed). Communicative Competence Approaches to Language Proficiency Assessment: Research and Application. Clevedom. Avon, VK: Multilingual matters LTD.

Dataworks Educational Research (2011).Explicit Direct Instruction.Retrieved October 22, 2012 from http://www/datawords-ed.com/research/edi.

Dawit Tibebu. (2014). The Effect of Explicit Reading Strategy Instruction on Reading Comprehnesion of Upper Primary Grade Students, International Journal of Education. ISSN 1948 – 5476 Vol. 6. No 3.pp 81-100.

Derry, S.J.(1996). Cognitive Schema Theory in the Constructivist Debate. Educational Psychologist., Lawrence Erlbaum Associates, Inc. 31(314), pp 163-174

Dhambaal (2006). Dhambaal (Somali Language News Paper) Cadadka 3, aad Tirsigii 68, Ee Bisha. Megabitt 10/2005 – da.

Dole, J.A. Brown, K.J., and Trathen, W. (1996).The effects of strategy instruction on the comprehension performance of at-risk students.Reading Research Querterly 31/1 pp. 62-88.

Dornyei, Z. (2007). Research Methods in Applied Linguistics.Quantitative, Qualitative and Mixed Methodologies. New York, Oxford: Oxford University Press.

Duffy, G. G. (2002). The Case for Direct Explanation of Strategies. In C. C. Block and M. Pressley (Eds.) Comprehension Instruction: Research – Based Best Practices. New York: Guilford Press pp 28-41.

Economic and Social Research Council (E. S. R. C). (2000). Reading Comprehension Nature, Assessment and Teaching.

Ehrman, M., and Oxford, R. (1989).Effects of Sex Differences, Career Choice, and Psychological Type on Adult Language Learning Strategies. The Modern Language Journal, 73/1, pp 1-13.

Ehrman, M., and Oxford, R. (1990).Adult Language Learning Styles and Strategies in an Intensive Training Setting. The Modern Language Journal, 7413, pp 311-327.

Ellis, R. (1994). Understanding Second Language Acquisition. Oxford: Oxford University Press.

Ertmer, P. A. and Newby, T. J. (2013). Behaviorism, Cognitivism, Constructivism: Comparing Critical Features from an Instructional Design Perspective. International Society for Performance Improvement, published online in Wiley online Library 26(2) PP. 43-71.

Evangelisto, T. (2002).Constructivist Approches to Theaching and Learning. California. Educational Administration and Secondary Education. The College of New Jersey (Ewing ,NJ, USA).

Flavell, J. H. (1992). Metacognitive and Cognitive Monitoring.A New Area of Cognitive Development Inquiry. In to E. Nelson (Ed.), Metacognitive: Core Reading: Boston Alyn and Bacon.

Flavell, J.H (1976). Metcognitive aspects of problem solving. In L.B. Resnick (Ed.), The nature of intelligence. Hillsdale, NJ: Erlbaum. Pp 231-235.

Gessesse Tadesse. (1992). The Effect of a Process Approach Teaching Reading on First Year Students at Kotebe College of Teacher Education. College of Humanities, Language, Communication and Journalize Studies A.A.U (Unpublished Dissertation).

Goodman, K.S (1984) Reading: A Psycholinguistic Guessing Game in Ruddell, H,S.R.B.(Ed.).Theoretical Models and Processes of Reading ,Newark, Del: International Reading Association:Pp259-272.

Grabe, W. (1991).Current Development in Second Language Reading Research .TESOL Quarterly, Vol 23/3 pp 357-405.

Grabe, W. (2009). Reading in a second Language: Moving from theory to practice. New York, NY Cambridge University press.

Grabe, W. (2012).Key Issues in L2 Reading Development. CELC Symposium: Northern Arizona University.

Grabe, W. and Stoller, F. L. (2002).Teaching and Researching Reading. London: Pearson Education.

Green, J. M., and Oxford, R. (1995). A Closer Look at Learning Strategies, L2Proficiency and Gender, TESOL Quarterly, 2912, pp 261-297.

Grenfell, M. and Razi, O. (2012).The Impact of Linguistic Knowledge on Learner Strategy Development.Dublin School of Education.

Griffiths, C. (2004). Language learning strategies. Theory and Research. New Zealand, AIs St Helens, Auckland, New Zealand, School of Foundations Studies. pp 1-25.

Griffiths, C., and Parr, J. M.(2000). Language Learning Strategies, Nationality, Independence and Proficiency, Independence, 28, pp 7-10.

Haas, C., and Flower, L. (2006).Rhetorical Reading Strategies and the Construction of Meaning.JSTOR- Vol. 39 No 2, 167 -183.

Harris, T, and Hodges, R. (1995). The literacy dictionary: The vocabulary of reading and writing. Newark, DE: International reading association.

Herber, H.L. (1970).Teaching reading in content areas. Englewood Cliffs, N.J: prentice hall.

Hittleman, D.R. (1998). Developmental Reading, k-8.Teaching from a whole Language Perspective. (3rd Ed.), Columbus, Ohio: Merrill, a Bell and Howell.

Hollingsworth, J. and Ybarra, S. (2009). Explicit Direct Instruction. The Power of the Wellcrafted, Well- taught Lesson. Fowler, California; Data Works Educational Research.

Hudson,T. (2007). Teaching Second Language Reading . New Yourk Ny: Oxford University Press.

Huitt, W. G. (2003). The Information Processing Approach to Cognition .Retrieved on August 24 2015, from http://ch.ron.valdosta,edu/ whuitt/col/ cogsys/ info.proc.htm.

Hulstun, J.H., and Matter, J.F. (1991). Reading In Two Language. The Netherlands, Haveka B.V. Alblasserdam

Jiang, X. (2011).The Role of First Language Literacy and Second Language Proficiency in Second Language Reading Comprehension.The Reality Matrix. Vol 11/2 April 2011.

Karimi, K. (2008) Reading Strategies, What are They? University of Tehran.

Kasimi, Y. (2012). Cognitive and Metacognitive Strategies Employed by Iranian and Turkish EFL Readers. International Association of Research in Foreign Language Education and Applied Linguistics: ELT Research Journal 1(3). Pp 159-174.

Keer, H. V., and Verheaghe, J. P. (2005). Effects of Explicit Reading Strategy Instruction and Peer Tutoring on Second and Fifth Graders' Reading Comprehension and Self-

Efficacy Perceptions, The Journal of Expermantal Education, 73: 4, 291-329, DOI: 10: 3200/JEXE. 73. 4. pp291 – 329.

Kellerman, E. (1991). Compensatory Strategies in Second Language Research: A Critique, a revision and some non- implications for the classroom .In R.Phillipson, E.Kellerman,L.Selinkers M. Sharwood – Smith, and M. Swain (Eds.). Foreign and Second Language Pedagogy Research.Clevedon. UK: Multilingual Matters.

Khalifa, H. and Weir, C. J. (2009).Examining Reaching Cambridge University Press, Cambridge.Studies in Language Testing , Examining Reading: Research and Pratice in Assessing Second Language Reading . Cambridge: Cambridge University Press.

Khaokaew, B. (2013). An Investigation of Explicit Strategy Instraction on EL Reading of Undergraduate English Majors in Thailand University of Bedfordshire. (Unpublished Dissertation)

Khezrlou, S. (2012). The Relationship Between Cognitive and Metacognitive Strategies, Age, and Level of Education. The Readin Martix.Vol. 12 N 1, pp 50 -61.

King, K. (2008). Reading strategies, retrived at May 17 2016, from http: //www.Isv. Edu/kingkath/Readstvt.Htm/.

Kong, A. (2006). Connections Between L1 and L2 Reading: Reading Strategies used by Four Chinese Adult Readers. The Reading Matrix.Vol. 6 No. 2, pp 19 -42.

Krashen, S. (2013). Should We Teach Strategies? Electronic Journal of Foreign Language Teaching.National University of Singapore Vol. 10 No. 1, pp 35 -39.

Kyemes,A.(2005).Teaching Online Comprehension Strategies Using Think Aloud. Journal of Adolescent and Adult Literacy. March 2005:Vol488,Pp 494 – 500.

Larsen – Freeman, D. (1986). Techniques and Principles in Language Teaching New York: Oxford, Oxford University Press.

Lau, K. (2003). Reading Strategy Use and Motivation Among Chinese Good and Poor Readers in Hong Kong. Journal of Research in Reading. ISSN 014-1-0423 Vol.26 NO 2 177-190.

Lee, J. W. and Schallert. D. L. (1997). The Relative Contribution of L2 Language Proficiency and L1 Reading Ability to L2 Reading Performance.A Test of Threshold hypothesis in an EFL Context TESOL.Quarterly. 31, PP 713-739.

Lee, K. R. (2007). Stratgey Awarenss Raising for Success, Reading Strategy Instruction in the EFL Context. Maryland :University of Maryland,College Park (Unpublished Dissertation)

Lencion, G. M. (2013). The Effects of Explicit Reading Strategy Instruction and Cooperative Learning on Reading Comprehension in Fourth Grade Students. San Francisco :University of San Francisco. USF Scholarship Repository. (Unpublished Disseration)

Ling, S. (2011). Investigation Chinese English Majors Use of Reading Strategies. A Study on the Relationship Between Reading Strategies and Reading Acheivements. Sweden, Tutor: Carita Lundmark. Kvistianstad University. EN 2460 Level 1V English, School of Teaching Education.

Liu, S, (2001). Studies on Transfer in Second Language Acquisition. China, Guangxi Normal University; Ginlin,541004. Journal of Language Learning Vol.21/3 pp 1-29.

Masoud, G. A. (2011). The Transferability of Reading Strategies between L1 (Arabic) and L2 (English). Libya: Durham University, School of Education (Unpublished Dissertation).

Mayer. R. E. (1996). Learning Strategies for Making Sense out of Expository Text.The SOI Model for Guiding Three Cognitive Processes in Knowledge Consruction.Educational Psychologist Review, 8.pp 357- 371.

McDonough, J. and Shaw, C. (1993).Materials and Methods in ELT: A Teachers Guide. Applied Language Studies, Edited by D. Crystal and K. Johnson Oxford UK and Cambridge USA: Blackwell.

McNamara, D. (2004). The Importance of Teaching Reading Strategies Perspective on Language and Literacy. The International Dyslexia Association pp 34-38.

McNamara, D. S. (2007). Reading Comprehension Strategies: Theories, Interventions, and Technologies, Mahwan, New Jersey: Lawrence Erlbaum Associates, Inc., Publishers.

Medina, S. L. (2011). Effects of Strategy Instruction in an EFL.Reading Comphrension Course.A Case Study. Bogota: Colombia: Journal of Language Learning Skill: Vol. 14. No 1 ISSN 1657 -0790: pp 79-89.

Mehrpour, S., Sadighi, F., and Bagheri, Z. (2011).Teaching Reading Comprehension Strategicies to Iranian EFL- Per- University Students. The Journal of Teaching Language Skill(JTLS) Previously Journal of Social Sciences, and Humanties 4 (1) pp 107 -139.

Midnimo. (2008) Midnimo (Somali Language News Paper) Xarunta Dhexe ee X. D. SH. S. I. Hidaar 30/Cadadka 08/03.

Mikulecky, L., Albers, P., and Peers, M. (1994). Literacy Transfer (1994).Philadelphia, National Center on Adult Literacy. University of Pennsylvania: R117 Q003, PA 19-104-3111.

Mokhtari, K. and Sheory, R. (2002). Measuring ESL Student Awareness of Reading Strategies Journal of Devlopmental Education,Vol. 1/25 pp 1-10.

Mokhtari, k. and Reichard, C.A. (2002).Assessing Students' Metcognitive Awareness of Reading Strategies. Journal of Educational Psychology: American Psychological Association Inc. 022-0603:DOI:10:1037/0022-0663.94.2.249 Vol 94 no 2 249-259.

Mooney, C. G. (2000). Theory of Childhood: An Introduction to Dewey, Montessori, Erikson, Piaget and Vygostky. St. Paul, MN Redleaf Press.

Muijs, D. (2004). Doing Quantiative Research in Education. London: SAGE Publication Ltd.

Nation,K. (2006).Assessing children's reading comprehension .In M.J. Snowling and J.Stackhouse(Eds.), Dyslexia,Speech and Landuage: A Practitioner's Handbook. Whurr.

Nation, K. (2005). Children's Reading Comprehension Difficulties in Snowline, M. J and Hulme, X. (Eds.). The Science of Reading, Oxford, Blax well Publishing Ltd, pp 248-266.

National Reading Panel. (2000).Teaching Children to Read: An Evidence Based Assessment of Scientific Research Literature on Reading and Its Implications For Reading Instruction. Jessup. MD: National Institute for Literacy.

Ness, M. (2011).Explicit Reading Comprehension Instruction in Elementary Classrooms.Teacher use of Reading Comprehension Strategyies. Journal of Research in Childhood Education, 25, pp 98-117. ISSN 0256-8543: Doi:10.1080/ 02568543 .2010531076.

Nuttal, C. (1982).Teaching Reading Skills in a Foreign Language Practical Language Teaching. London – Edinburgh.

O`Malley,J.M., Chamot, A.U., Stewner -Manganaves, G, Russo, R.P. And Kopper, L .(1985). Learning Strategy Applications with Students of English as a Scond Language. TESOL Quarterly:Vol 19 (3),Pp 557 – 584.

O'Malley, J. M., and Chamot, A. U. (1990).Learning Strategies in Second Language Acquisition. Cambridge: Cambridge University Press.

Omaggio, A. (1993). Teaching Language In Context, Boston: Heinle and Heinle Publishers.

Oxford, R. L. (1990). Language Learning Strategies. What Every Teacher should know. New York: New bury House.

Oxford, R. L., and Ehrman, M. E..(1995). Adults' Language Learning in an Intensive Foreign Language Program in the United States. System, 23,pp 359 -386.

Oxford, R., and Nyikos, M. (1989).Variables Affecting Choice of Language Learning Strategies by University Students. The Modern Language Journal, 7331 pp 291-300.

Oyetunji, C. (2013). Does Reading Strategy Instruction Improve Students' Comprenension? Journal of Languge Learning (Perlinguam) 29(2)33-55. http//dx.doi.org/ 10.5785/29-pp 2-144.

Pallant,J.(2001). SPSS SURVIAL MANUAL, A step by step guide to data analisis using SPSS for windows (version 10 and 11); Maidenhead Philadelphia : Open University Press.

Pang, J.(2008). Research on Good and Poor Reader Characteristics: Implications for L_2 Reading Research in China. Reading in a Foreign Language: JSSN 1539-0578. Vol. 20. N. 1 1-18. (http:// nfirc.hawaii.edu/rfl.)

Paris, S.G., Wasik, B.A, and Turner, J.C (1991).The development of strategic readers.In R. Barr, M. Kamil, P. Monsenthal, and D. Pearson (Eds).Handbook of Reading Research. New York: Longman Vol. 2 pp609-640.

Pavlenko, A, and Jarvis, S.(2001). Conceptual transfer: New perspective on the study of cross.- linguistic influence. In E. Nemeth (ed). Cognition in language use: selected papers from the 7th international pragmatics conference, Vol.1 pp 288-301. Antwerp, NL: International pragmatics Association.

Pearson, P. D. (2016). Explicit Comprehension Instrution.A Review of Research and a New Conceptalization of Instruction.The Elementary School Journal.University of Chicago Press Vol. 88 No 2. pp 151-165.

Perr, J.F. (2005). Research in Applied Linguistics.Becoming a Discerning Consumer. New Jersey: Lawrence Erlbaum Associates, Inc.

Phakiti, A. (2006). Theoretical and Pedagogieal Issues in ESL/EFL. Teaching of Strategic Reading. TESOL, N 1, pp 19-50.

Pressely, M. (2000). What should comprehension instruction be the comprehension of? In M.L kamil, P.B. Mosenthal, P.D Pearson, and R. Barr. (Eds.), Handbook of reading research Mahwah, NJ; Erlbaum Vol. 3 pp 545-561.

Pressley, M. (2002). Metacognitive and Self Regulated Comprehension in Farstrup A.E. and Samules, S. J. (Eds.) what Research has to say about Reading Instruction (3rd Ed) Network, DE: International Reading Association. PP 243 -260.

Pressley, M. and Afflerbach, P. (1995).Verbal Protocols of Reading the Nature of Constructively Responsive Reading. Hillsdale, NJ: Lawrence Erlbaum Associates.

Pressley, M., Wharton-McDonald, R., Mistretta-Hampton, J.M., and Echevarria, M. (1998).The nature of literacy instruction in ten grade 4/5 class rooms in up state New York Scientific studies of reading 2, pp 159-194.

Reading Stydy Group (RAND). (2002). Reading for understanding toward an Rand D program reaching comprehension. Santamonica, CA:RAND.

Richards, J.C. (2006). Communicative Language Teaching Today. New York: Cambridge University Press.

Richards, J., Platt, J.& Weber, H. (1990). Dictionary of Applied Linguistics. London: Longman.

Richards, J.C. and Rodgers, T. S. (1986).Approaches and Methods in Language Teaching. USA. Cambridge University Press.

Ringbom,H.(1192). On L1 transfer in L2 comprehension and L2 production. Journal of Language Learning vol. 42/1 pp 85-112

Romance, N.R., and Vital, M.R. (2009). Transfer Effects of a Reading Comprension Strtagey on Achievement and Teacher Judgments Across Grades 3-7. Education Science through Grant R 305 G 04089/ pp 1-6

Rowell, C. G., and Palmer, B. C. (2007).Cognitive and Constructivist Strategies for Teaching about Language and for Providing Reading and Writing Instruction. Forum on Pubic Policy pp 1-30.

Rubin, J. (1975). What the "Good Language Learner" can teach us. TESOL Quarterly 9/2 pp 41-51.

Rubin, J. (1996). Using Multimedia for Learner Strategy Instruction. In R. L. Oxford (ed.), Language Learning Stategies Arourd the World: Cross – Cultural Perspectives. Honolulu, HI: University of Hawaii Press. pp 151-156.

Rubin, J., and Thompson, I. (1994).How to be More Successful Language Learner. Boston: Heinle and Heinle.

Rubin, J., Chamot, A. V., Harris, V., Anderson, N. J. (2007). Intervening in the use of Strategies.In A. D. Cohen and E. Macaro (Eds.).Language Learner Strategies Thirty Years of Research and Practice. Oxford. Oxford University Press. pp 141 – 146.

Rumelhart, D. E. (1994).Toward an Interactive Model of Reading.In R.B. Ruddell, M. R. Ruddell, and H. Singer (Eds.).Theoretcial Models and Processes of Reading. Newark, DE: International Reading Association (4^{th}ed) pp 864 – 894.

Schramm, K. (2006). Cognitive and MetaCognitive Aspecs of the L2 Reading Pocess.Retraived at March 18/2016, from http://www.baby/osia.ch -pp 25-30.

Seid Mohammed. (2012). "Effects of Cooperative learning on Reading Comprehension Achievement in EFL and Social Skill of Grade 10 Students AAU" (Unpublished Dissertation).

Slavin. R. E. (1997). Educational Psychology: Theory and Practice (5^{th}ed) Needham Heights, MA: Allyn and Bacon.

Snow, C. E. (2002). Reading for Understanding: Torard a Research and Development Program in Reading Comprehension Santa Monica, CA: RAND.

Solomon Hailu. (2000). A Study of Reading Strategy of First Year Students at Addis a University College in Ethiopia.College of Humanities, Language, Communication and Journalizem (Unpublished PhD Dissertation).

Stanovich, K.E. (1980). Toward an Interactive – Compensatory Model of Individual Diffrnces in the Development of Reading Fluency. Reading Research Quarterly, 16,pp 32-71.

Stenagel, L. O. (2005). The Effects of Reading and Reading Strategy Training on Lower Proficincy Level Second Language Learning (Doctorial Dissertations).Brigham Young Univsity BYV Scholars Arclive.

Stern, H. H. (1975). What Can We Learn from the Good Language Learner? Canadian Modern Language Review 31/ 3o, pp 4-18.

Stern, H.H. (1992). Issues and Options in Language Teaching, Oxford: Oxford University Press.

Tacey, D. H., and Morrow, L.M. (2006).Lenses on Reading.An Introduction to Theories and Models. Eew York. Ny 10012. The Guilford Press, Inc.

Talebi, S. H. (2007). Strategic Reading in L1 and L2: One System or Two Systems? Language in India, Vol. 7/11 pp 1 -15.

Talebi, S. H. (2012). Reading in L_2 (English) and L_1 (Persian): An Investigation into Reveres Transfer of Reading Strategies. Iran, University of Mazandavan.URL: http://dx.doi.org/105539/ elt V5n3, pp 217-229.

Talebi, S. H. (2013). Cross – Linguistic Transfer (from L1to L2, L2 to L1, and L2 to L3 of Reading Srategies in a Multicompetent mind. Journal of Language Teaching and Research Vol 4 No 2.Doi 10.4304/jltr. 4.2. pp 432-436.

Talebi, S. H. (2014). Cross- Linguistic Transfer among Iranian Learners of English As a foreign Language. Issues in Educational Research, Vol 24(2), pp 212-227.

Talebi, S. H. (2015). Where Should Reading Strategies Be Taught First. In Persian (L1), English (L2), or Arabic (L3)?Journal of Creative Practices in Language Learning and Teaching (CPLT). Vol 3 No 2, pp 33-45.

Tarone, E. (1980). Communication Strategies, foreigner talk, and repair in interlanguage, language learning , 30/2/ pp 417-429.

Taye Regassa. (1999). "The Effect of Academic Background on Reading Comprehension. The Case of First Year Students at the College of Social Science" A.A.U. College of Humanities, Language, Communication and Journalize Studies A.A.U (Unpublished Dissertation).

Tesfu Gebre. (2015). "The Effect of Strategy Instruction on Grade Eleven Students Reading Compression Performance: The Case of Kulla Preparatory School in Arsi Zone, Oromia Region." (Haramay University Unpublished MA Thesis).

Urquhart, S. and Weir, C. (1998). Reading in a Second Language: Process, Product and Practice. London: Longman.

Vygotsky, L.s.(1978). Mind in Society: The development of higher psychological processes. Cambridge, Cambridge , MA:MIT Press.

Wang, M.T. (2009). Effects of Metacognitive Reading Strategy Instruction on EFL High School Students Reading Comprehension Reading Strategies Awareness, and Reading Motivation. Florida: University of Florida.

Webster`s Third New World International Dictionary. (1989).New Haver : The Merrianm Webster .Inc.

Weir, C.J (1990). Communication Language Testing .London: Prentice Hall International Ltd.

Wenden, A.L (1991). Learning strategies for learner autonomy UK: prentice Hall.

Wikipedia, the Free Encyclopedia.(2012). C onstructivism (philosophy of education). Retrived at Jun 23 2017, from mhtml:file://F:/Constructivism %20(philosophy %20of%20education)%20-%20Wikipedia.

Williams, J.P. (2002). Reading comprehension strategies and teacher education. In A.F. Farstrup and S.T. Samuels, What research has to say about reading instruction (3rd Ed). Newark: International Reading Association pp. 239-257.

Willing , K. (1989). Teaching how to learn: learning strategies in ESL. Sydney: National centre for English Language Teaching and Research.

Willing, K. (1998). Learning styles in adult migrant education. Sydney: National Centre for English Language Teaching and Research.

Wollfolk, A. E. (1998). Educational Psychology (7thed.). Boston: Allyn and Bacon.

Yamashita, J. (1999). Transfer of L1 Reading Ability to L2 Reading: An Elaboration of the Linguistic Threshold.

Yamashita, J. (2012). Influence of L1 Reading on L2 Reading: Different Perspectives from the Process and Product of Reading.pp 271-283.

Yang, N.D (1995).An interviewing study of college students. English learning strategy use, studies in English language and literature vol. 4 pp. 1-11.

Yorio, C. (1971).Some Sources of Reading Problems in Foreign Language Learners, Language Learning.

Yoshida, M. (2008). Think – Aloud Protocol and type of Reading Task: The Issue of Reacting in L2 Reading Research. Selected Proceeding of the 2007 Second Language Research Forum melissa, B. (Ed.). Somerville, Macascadilla Proceeding Project PP. 199 – 201.

Zainal, Z. (2011). Critical Review of Reading Models and Theories in First and Second Language Journal Kemanusiaan – pp 104-124.

Zare, P., and Othman, M. (2013). The Relationship Between Reading Comprenension and Reading Strategy use Among Malaysian ESL Learners. International Journal of Humanities and Social Science Vol.3 N 13, pp 187 – 193.

Zhang, L. J. (2008). Consractivist pedagogy in strategic reading instruction, exploring path ways to leasner development in the English as a second language (ESL) classroom. Science + Business media, B.V. 36: 89-116.doi:10.1007/s/251 – 007 -90256.

Zhang, L.J. (2012). Effects of explicit instruction in cognitive and metacognitive reading strategies on Iranian EFL students reading performance and strategy transfer. Science + Business media B.V. 40: 1063 – 1081, doi 10. 1007/s/1251-011-9202-5.

አባሪዎች (Appendix)

አባሪ አንድ

ለትምህርት የቀረቡት የማንበብ ብልሃት ዝርዝር(በአማርኛ ፣በሶማልኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ)

ተ.ቁ	የማንበብ ብልሃት ዝርዝር		
	አማርኛ	Somaliga	English
1	መተንበይ	Sadaalin	Prediction
2	ማቀድ	Qorsheyn	Planning
3	ዋናውን ሀሳብ በፍጥነት ማግኘት	Si dag daga u helay fikrada	Getting the Idea Quickly
4	መረጃዎችን ፈልፍሎ ማውጣት	Raadinta Xagta dhabta ah	Inference
5	ማስታወሻ መያዝ	Qaadashada xusuusnanata	Note Taking
6	ደጋግም ማንበብ	Akuriska ku celinta	Repeating
7	ሀሳብን በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ	Koobida fikrada	Summarizing
8	መጠየቅ	Weydiinta ju aalaha	Asking Question
9	የቀደመ እውቀትን መጠቀም	Is tic maal ka maskaxda aad waxkubaratey	Using Background Knowledge
10	ራስን እና አንብቦ መረዳትን መቆጣጠር	Ismaamulida	Monitoring
11	አውዳዊነት	Erayada jum lada dhan	Context
12	ዘዴ በተሞላበት መንገድ መገመት	Qiyaasid	Guessing Intelligently
13	ራስን መገምገም	Isqiimeyn	Self-Evaluation
14	የማንበብ ብልሃቶችን ከሶማልኛ ወደ አማርኛ /ከአማርኛ ወደሶማልኛ ቋንቋ ማሸጋገር	Gudbin	Transferring
15	ከሌሎች ጋር መተባበር	Is bar bar dhigid kuwa kale	Cooperate with others
16	በአእምሮ ውስጥ ምስል መፍጠር	Sawir ku abuurida maskaxda dhexdeeda	Imaging/Visualize

አባሪ ሁለት

በናሙና ጥናቱ የተሳተፉ ተተኳሪ ተማሪዎች እና መምህራንን ዳራዊ መረጃ የሚያሳይ

ሀ. በመከራ ጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎች ዳራዊ መረጃን የሚገልፅ

ተ.ቁ	የተተኳሪትምህርት ቤቶችስም	የተጠኚ ተማሪዎች ብዛት			የተመጡ ክፍሎች	የምርምሩ ቡድኖች	የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ የተሰጠበት ቋንቋ
		ፆታ	በቁጥር	%			
1	ጅግጅጋ ሼክ አብዱ ሰላም ሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ት/ቤት	ወንድ	23	46	9ኛ G	9ኛG መከራ ቡድን አንድ	ሶማልኛ
		ሴት	27	54			
		ድምር	50	100			
2	ጅግጅጋሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ት/ቤት	ወንድ	22	48.8	9ኛ D	9ኛ D መከራ ቡድን ሁለት	አማርኛ
		ሴት	23	51.1			
		ድምር	45	100			
		ወንድ	25	59.5	9ኛ H	9ኛ H ጥብቅ ቡድን ሶስት	ለጥብቅ ቡድን የማንበብ ብልሃት ትምህርት አልተሰጠም
		ሴት	17	40.5			
		ድምር	42	100			
ጠቅላላ ድምር		ወንድ	70	51.1			
		ሴት	67	48.9			
		ድምር	**137**	**100**			

ለ. በናሙና ጥናቱ የተሳተፉ መምህራን ዳራዊ መረጃ የሚገልፅ

ተ.ቁ	መምህራን የተወሰዱበት ትምህርት ቤት	የመምህራን ብዛት			የትምህርት ዝግጅት እና የሚያስተምሩት የትምህርት አይነት	በሙከራ ጥናቱ የተሳተፉት	ያስተማሩበት ክፍል	ያስተማሩበት ጊዜ
		ፆታ	በቁጥር	%				
1	ጅግጅጋ ሼክ አብዱ ሰላም ሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ት/ቤት	ወንድ	1	100	ዲፕሎማ ሶማልኛ ቋንቋ ማስተማር የመጀመሪያ ዲግሪ እንግሊዝኛ ቋንቋ ማስተማር	-የማንበብ ብልሃትን በሶማልኛቋንቋ ለሙከራ ቡድን በግልጽ ማስተማር -ጥብቅ ቡድኑን በተለምዷዊ መንገድ ማስተማር	-G ሙከራዊ ቡድን -Hጥብቅ ቡድን	ለሙከራ ቡድን ለአስራ ሁለት ሳምንት በሳምንት ሁለት ጊዜ የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 40 ደቂቃ (በጠቅላላ ለ16 ሰአት)
		ሴት	-	-				
		ድምር	1	100				
2	ጅግጅጋሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ት/ቤት	ወንድ	1	100	የመጀመሪያ ዲግሪ አማርኛ ቋንቋ ማስተማር	የማንበብ ብልሃትን በአማርኛ ቋንቋ ለሙከራ ቡድን በግልጽ ማስተማር -ጥብቅ ቡድኑን በተለምዷዊ መንገድ ማስተማር	-Dሙከራዊ ቡድን -H ጥብቅ ቡድን	ለሙከራ ቡድን ለአስራ ሁለት ሳምንት በሳምንት ሁለት ጊዜ የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 40 ደቂቃ (በጠቅላላ ለ16 ሰአት)
		ሴት	-	-				
		ድምር	1	100				
	ጠቅላላ ድምር	ወንድ	2	100				
		ሴት	-	-				
		ድምር	2	100				

አባሪ ሶስት

በማንበብ ብልሃት ዙርያ ለመምህር (ለመምህራን) የተሰጠ ስልጠና መመሪያ

ክፍል አንድ

መግቢያ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነት እና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን በማስተማር ለተባለው የትምህርት መርሀ ግብር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ምርምራዊ ፅሁፍ ለማዘጋጀት ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ የሚሰራው ምርምር ርዕስ "የማንበብ ብልሃትን በግልፅማስተማር አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለማጎልበት እና ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ያለው አስተዋፆ" የሚል ሲሆን በሶማሌ ክልል በጅግጅጋ ከተማ 9ኛ ክፍል ሶማልኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎችን ተተኳሪ አድርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ጥናቱ ያተኮረበትን የማንበብ ብልሃት በተመለከተ ለጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች (ሙከራ ቡድኖች) በአማርኛ እና በሶማልኛ ቋንቋ ለማስተማር እንዲያስችል በምርምር አቅራቢው ስልጠና ወስዶ የተዘጋጀ የቋንቋ መምህር በማስፈለጉ ነው ፡፡

ጥናቱ የተነሳበትን አላማ ለማሳካት የተከተለው የምርምር ንድፍ ቅድመ እና ድህረ ልምምድ ፈተና በመስጠት በተገኘው አሀዛዊ መረጃ ላይ ተመስርቶ ሰፊ ትንታኔ የሚያቀርብ ከፊል ፍትነታዊ (Quasi Experiment) የምርምር ንድፍ ነው፡፡ መረጃ ለማሰባሰብ እንዲያስችል በጥናቱ የሚሳተፉ ሁለት የሙከራ እና አንድ ጥብቅ ቡድኖች ይዘጋጃሉ፡፡ በጥናቱ ለሙከራ ቡድን አንድ በአማርኛ ለሙከራ ቡድን ሁለት ደግሞ በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃትን የተመለከተ ለአስራሁለት ሳምንት(16 ሰዓት/960 ደቂቃ) ትምህርት ይሰጣል፡፡ ጥብቅ ቡድኑ የማንበብ ብልሃትን የተመለከተ ፍንጭ እንዳያገኝ ቀድሞ በነበረው የትምህርት አሰጣጥ ይቀጥላል፡፡

በትምህርቱሂደት ጥብቅ ቡድኑ ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀው መማሪያ ማስተማሪያ መፅሀፍ ቀደም ሲል በመጀመሪያ ሰሚስተር እንደተማሩት የሚቀጥል ሲሆን በሶማልኛ እና በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት የሚማሩት ሙከራዊ ቡድኖች ለደረጃው የተዘጋጀውን መማሪያ ማስተማሪያ መፅሀፍ መሰረት በማድረግ የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ እንዲማሩ ይደረጋል፡፡

የሚሰጠው ትምህርት ተግባር ተኮር እንዲሆን ለማድረግ መምህር በነፃ ማሰብ (እየተገበሩ ማሰብ ወይም ሞዴል መሆን) (Teacher think aloud)፣ አእምሯዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ(Cognitive academic language learning approach/CAALA) እና ትግግዝ (Scaffolding) ሞዴሎችን በማቀናጀት ተግባራዊ ይሆናል። በተለይ የጥናቱ ምሰሶ የሆነው አእምሯዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን ለማቅረብ የሚያስችል ቅደም ተከተል ያካተተ በመሆኑ እጅግ ጠቃሚ ነው። በዚህ መሰረት ትምህርቱ የዝግጅት፣ሞዴል በመሆን የአቅርቦት፣የልምምድ፣ ራስን የመገምገም(ተማሪዎች)፣ የማንበብ ብልሃቶችን ከአንድ አዲስሁኔታ ወደሌላ አዲስ ሁኔታ ወይም ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ የማስፋፋት እና የምዘና ተግባራትን ያካተተ የአቀራረብ ቅደም ተከተል አለው።

የስልጠና መመሪያው ያካተታቸው ጉዳዮች

ይህ ለመምህር የተዘጋጀው የስልጠና መመሪያ ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ከተለያዩ ማብራሪያዎች ጋር ያካተተ ነው። የስልጠና መመሪያው የመጀመሪያ ክፍል መግቢያ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የሚካተተው የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን ለሚሰጠው መምህር የተፃፈ ደብዳቤ ፣ትምህርቱን ለመከራ ቡድኖች የመስጠት ስምምነት ቅፅ፣ ስልጠናው ምን ምን ነገሮችን ማካተት እንዳለበት የሚያመላክት አጠቃላይ እይታን የሚያንፀባርቅ ሀሳብ እና ለሰልጣኝ መምህሩ ስልጠናው የሚሰጥበት የጊዜ ቀመር ነው።

ሁለተኛው ክፍል የማንበብ ብልሃት ምንነትን፣ጠቀሜታን እና አይነቶችን የተመለከተ ትውረታዊ ሀሳቦችን ያካተተ ነው። የዚህ ክፍል ጠቀሜታው ስልጠናውን የሚከታተለው መምህር በማንበብ ብልሃት ምንነት እና ባህርያት ዙርያ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ ነው። ይህም መምህሩ ከስልጠናው በኋላ የሚያስተምራቸው የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን ተግባራዊ በማድረግ ፅሁፎችን አንብበው ለመረዳት ጥረት ከማድረጋቸው በፊት ስለማንበብ ብልሃት ምንነት እውቀት እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችል አቅም ይፈጥራል።

ሶስተኛው ክፍል የማንበብ ብልሃቶችን ለማስተማር የሚያስችል የትግበራ ቅደም ተከተልን የሚያመላክት ነው። ይኸውም ለመከራ ቡድኖቹ ትምህርቱ ሲቀርብ ምን ገፅታ እንዳለው ለእርስዎ ለመምህር ግንዛቤ ለማስጨበጥ ያለመ ነው።

1.1 በምርምር አቅራቢው ስልጠና ከተከታተለ በኋላ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን ለተማሪዎች ለሚያስተምረው መምህር የተፃፈ ደብዳቤ

ውድ መምህር

በመጀመሪያ ደረጃ በዚህ የምርምር ስራ ውስጥ ለመሳተፍ ጊዜዎትን እና አካዳሚያዊ እውቀትዎትን በመስጠት የሚያደርጉት ሙያዊ ድጋፍ የምርምር ስራው የተነሳበትን አላማ ለማሳካት ትልቅ ድጋፍ የሚሰጥ በመሆኑ የመርምር ፅሁፍ አቅራቢው ከልብ የመነጨ ምስጋና ያቀርባል።

ይህ የምርምር ስራ ዋነኛ ትኩረቱ የማንበብ ብልሃቶችን በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ብቃትን(ውጤትን) ለማሳልበት እና ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ያለው አስተዋፆ ምን እንደሚመስል በጥልቀት መመርመር ነው። የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን ተማሪዎች በሚገባ እንዲከታተሉ እና ተገቢ በሆነ መንገድ የማንበብ ብልሃቶችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ የእርስዎ ድርሻ ከፍተኛ ነው።

የምርምር ስራው ከፊል ፍትነታዊ በመሆኑ በምርምር ስራው ሁለት የሙከራ ቡድኖች እና አንድ ጥብቅ ቡድን ይኖራሉ። ከሁለቱ ሙከራዊ ቡድኖች ለአንደኛው (9ኛ ሀ) በአማርኛ ለሁለተኛው ሙከራዊ ቡድን ደግሞ (9ኛለ) በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት ትምህርት ለአስራሁለት ተከታታይ ሳምንት (16 ሰዓት) የማንበብ ብልሃት ትምህርት ይሰጣል (ከአስራሁለቱ ሳምንታት ውስጥ የመጀመሪያው እና የመጨረሻው ሳምንቶች ቅድመ እና ድህረልምምድ ፈተና ለመስጠት ያገለግላሉ)። በዚህ መሰረት ይህ የስልጠና መመሪያ ለእርስዎ እንዲደርስ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

ይህ የስልጠና መመሪያ የተለያዩ ምሁራን (Talibi 2012፣2013፣ McNamara 2007 ፣ Tracey and Morrow 2006፣Griffiths 2004፣ Dole et al. 1996፣Oxford 1990፣ O`Malley and Chamot 1990) ካስቀመጡት ንድፈሀሳብ እና ከጥናቱ ትውረታዊ ክፍል መነሻነት የተዘጋጀ ነው።

አመሰግናለሁ !

1.2 የትምህርት (የስልጠና) ስምምነት ቅፅ

ይህ ቅፅ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ ለሙከራ ቡድኖች ከመሰጠቱ አስቀድሞ በምርምር አቅራቢው እና ስልጠና በሚሰጠው መምህር መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው። ስምምነቱ የሚያተኩረው በምርምር ስራው መረጃ በመስጠት ለሚሳተፉ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን የሚያስተምረው መምህር ትምህርቱን ከመስጠቱ አስቀድሞ ስልጠና መውሰድን እና ከስልጠናው በኋላ ተማሪዎችን በስልጠናው መሰረት ማስተማርን የሚመለከት ነው።

የምርምር አቅራቢው ሙሉ ስም እና አድራሻ

ስም _____

አድረሻ _____ ስ.ቁ _____

E-mail _____

የሰልጥኖ አሰልጣኙ መምህር ሙሉ ስም እና አድራሻ

ስም _____

አድረሻ _____ ስ.ቁ _____

ለሰልጥኖ አሰልጣኙ መምህር ስልጠናው የሚሰጠው ከ _____ እስከ _____

በምርምሩ ለሚሳተፉ ተማሪዎች ትምህርቱ የሚሰጠው ከ _____እስከ_____

እኔ መምህር _____በማንበብ ብልሃት ዙርያ በምርምር አቅራቢው የሚሰጠኝን ስልጠና በሚገባ ተከታትዬ ሀሳቡን ከተገነዘብኩ በኋላ በስልጠናው ባገኘሁት እና ከተለያዩ ፅሁፎች በማንበብ ባገኘሁት እውቀት መሰረት በታቀደው ጊዜ በምርምር ስራው ለሚሳተፉ ተማሪዎች ለአስራሁለት ሳምንት(16 ሰአት)ትምህርት ለመስጠት ተስማምቻለሁ።ለተማሪዎች የሚቀርበው የማንበብ ብልሃት ትምህርት በታቀደው መሰረት ቅደም ተከተል ጠብቄ ለማቅረብ ፈቃደኛ መሆኔን መግለፅ እወዳለሁ። ስራውንም ጀምሬ አላቋርጥም።

የምርምር አቅራቢው ሙሉ ስም እና ፊርማ _____ ቀን _____

የመምህር ሙሉ ስም እና ፊርማ _____ ቀን _____

1.3 የስልጠና መመሪያው አጠቃላይ እይታ

የዚህ ምርምራዊ ፅሁፍ አላማ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ብቃትን (ውጤትን) ለማጎልበት እና ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ያለው አስተዋፆ ምን እንደሚመስል በጥልቀት መመርመር ነው። በመሆኑም ጥናቱ የተማሪዎችን የማንበብ ሂደት እና ውጤታቸው ላይ ያተኩራል። ይህን አላማ ለማሳካት ለሙከራ ቡድኖቹ የማንበብ ብልሃት ትምህርት የሚሰጠው መምህር የማንበብ ብልሃት ምንነትን እና ባህርያትን እንዲሁም ትምህርቱ የሚሰጥበትን አቀራረብ በሚገባ ማወቅ አለበት።

ይህ የስልጠና መመሪያ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን የሚሰጠው መምህር ከላይ የተጠቀሰውን ፅንሰ ሀሳብ በሚገባ እንዲገነዘብ በማሰብ የተዘጋጀ ነው። የስልጠና መመሪያው የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ለማስተማር የሚያስችል በመሆኑ ተማሪዎች የሚያመጡትን አንብቦ የመረዳት ብቃት እድገት ለማየት አመቺ ነው። የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ በሚገባ ከተሰጠ በተማሪዎች ላይ የሚታየውን ለውጥ ለመመርመር ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል። እዚህ ግብ ላይ ለመድረስ ለተማሪዎች የሚቀርበው ትምህርት መምህር በነፃ ማሰብ (እየተገበሩ ማሰብ/ ሞዴል መሆን)፣ አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ አቀራረብ እና ትግግዝ ሞዴሎችን በማቀናጀት እና ቅደም ተከተልን መከተል እጅግ አስፈላጊ ነው።

ክፍል ሁለት

የማንበብ ብልሃት ላይ ትኩረት ያደረገው ስልጠና ተማሪዎችን ለሚያስተምረው መምህር በሚሰጥበት ወቅት ትኩረት የሚሰጥባቸው ይዘቶች የእርስዎን መደበኛ የስራ ሰአት በማይነካ መልኩ ተዘጋጅቶ ቀርቧል። በዚህ ክፍል የማንበብ ብልት ስልጠናው ለእርስዎ ለመምህር በሚሰጥበት ወቅት ትኩረት የሚሰጥባቸው ጉዳዮችን በዝርዝር ያካተተ ነው። መምህር ስልጠናውን በትኩረት መከታተልዎ ከስልጠናው በኋላ ትምህርቱን ለተማሪዎች ለማስተላለፍ ትልቅ አቅም ይሆኖዎታል።

2.1 ለመምህር ስልጠናው የሚሰጥበት ጊዜ እና የትምህርት አካል

የማንበብ ብልሃት ትምርቱ ላይ ትኩረት ያደረገው ስልጠና ለእርስዎ ለመምህር በሚሰጥበት ጊዜ የእርስዎ የመምህር የነቃ ተሳትፎ እና ክትትል ወሳኝ ነው። በስልጠናው የሚቀርቡትን ሀሳቦች ለማዳበር የተለያዩ ድረ-ገፆችን በማየት ፣ጥናታዊ ፅሁፍ አቅራቢው ከተለያየ ድረ-ገፅ እና መፅሀፎች ያገኛቸውን ፅሁፎች በደረቅ ቅጂ አባዝቶ ያዘጋጃቸውን እና በስልጠና መመርያ ውስጥ የተካተቱትን ሀሳቦች በማንበብ ማዳበር ይገባል።

በስልጠናው ትኩረት የተደረገባቸው ጉዳዮች

ተ.ቁ	የትምህርት አካል	ጊዜ
1	የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር እና ተለምዷዊ ማስተማር	አንድ ሰዓት
2	የማንበብ ብልሃት ምንነት፣ ዋና ዋና የሚባሉት የማንበብ ብልሃት አይነቶች	አንድ ሰዓት
3	የተለያዩ ፅሁፎችን አንብቦ ለመረዳት የማንበብ ብልሃቶችን ተግባራዊ ማድረግ ያለው ጠቀሜታ	አንድ ሰዓት
4	የማንበብ ብልሃቶችን በመማር ማስተማር ወቅት የመምህር እና የተማሪዎች ሚና	አንድ ሰዓት
5	የማንበብ ብልሃቶችን የማስተማርያ ሞዴሎች	አንድ ሰዓት
6	የማንበብ ብሃቶችን የአቀራረብ ቅደም ተከተል	አንድ ሰዓት

2.2 በሰንጠረዡ የቀረበው ሀሳብ በዝርዝር

2.2.1 የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር እና ተለምዷዊ ማስተማር

አላማ፡- የዚህ ትምህርት ክፍል አላማ የማንበብ ብልሃትን ስራዬ ብሎ በግልፅ ማስተማር እና የማንበብ ብልሃቶችን ሆን ሳይሉ (ሳያስቡ) ተለምዷዊ በሆነ መንገድ ማስተማር መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሙከራ እና ጥብቅ ቡድን የሚባሉት ፅንሰሀሳባዊ ቃሎች ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

ሀ. ሙከራ እና ጥብቅ ቡድን የሚባሉት ፅንሰሀሳባዊ ቃሎች የሚያንፀባርቁት ሀሳብ

ጥብቅ ቡድን የሚባለው የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ ሆን ተብሎ የማይሰጥበት(የማንበብ ብልሃትን በተመለከተ ፍንጭ እንዳያገኝ በማድረገድ) ቀደም ሲል በነበረው የትምህርት አቀራረብ የሚቀጥል ለምርምሩ ስራ ሲባል ለንፅፅር የሚዘጋጅ ክፍል ነው፡፡ ጥብቅ ቡድን ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ሌላ ክፍል የተለየ ትምህርት እየተሰጠ እኛ ለምን አንማርም የሚል ስሜት እንዳይፈጠርባቸው (የሚሰጠውን አዲስ ትምህርት እኛስ ለምን አንማርም የሚል) ታሪክችን በመንገር እና ሙያዊ ችሎታን(ብቃትን) በመጠቀም ተማሪዎችን መያዝ ይገባል፡፡ ክፍሉ ጥብቅ የተባለበት ምክንያት ለሙከራ ቡድኖቹ የሚሰጠው የማንበብ ብልሃት

ትምህርት ሊሰጥ ከታሰበው ውጪ ወደሌሎች ክፍሎች ክንውኑ እንዳይዛመት በጥንቃቄ ትምህርቱ በተለመደው መንገድ የሚቀርብ በመሆኑ ነው።

የሙከራ ቡድን የሚባለው የምርምር ስራው ሊፈትሽ የተነሳበትን ጉዳይ ለማረጋገጥ በታቀደ መልኩ ለተወሰነ ጊዜ በምርምሩ ለሚሳተፉ ተማሪዎች የተዘጋጀውን ትምህርት በመስጠት በስተመጨረሻ ትምህርቱን ካልወሰደው ጥብቅ ቡድን ጋር በማነፃፀር በቀረበው ትምህርት ምክንያት ያመጡትን የባህሪ ለውጥ ለመፈተሽ የሚያስችል ነው። ክፍሉ ሙከራዊ የተባለበት ምክንያት የታሰበውን ትምህርት በመስጠት(በመሞከር) በተማሪዎች ላይ የተከሰተውን ለውጥ ለማየት የሚያስችል በመሆኑ ነው።

ለ. የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር (መማር)

የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር ማለት ለተማሪዎች የትምህርቱ አላማ የሚነገርበት ፣ ተማሪዎች የተለያዩ ፅሁፎችን አንብበው ለመረዳት እንዲችሉ የማንበብ ብልሃቶችን በስማቸው እየጠሩ ምንነትን በተመለከተ ብያኔ የሚሰጥበት፣የማንበብ ብልሃት ጠቀሜታ በዝርዝር የሚቀርብበት፣የተለያዩ የማንበብ ብልሃት አይነቶችን እንዴት፣ መቼ፣ የት፣ ለምን መጠቀም እንዳለባቸው ማስተማር ነው። ትምህርቱ በተግባር የተደገፈ መሆን አለበት። በዚህ መንገድ የሚቀርበው ትምህርት የማንበብ ብልሃቶችን በዝርዝር ከማቅረቡ ጋር በተያያዘ ተማሪዎች የሚያውቋቸውን ብልሃቶች የሚያቀርቡበት፣ በተግባር የሚለማመዱበት፣ ራሳቸውን የሚገመግሙበት እና ለሌላ አዲስ ተግባር የማንበብ ብልሃት እውቀታቸውን የሚያስተላልፉበትን ተግባራት ያካተተ ነው። በመሆኑም ትምህቱ በተግባር የተደገፈ ቀጥተኛ እና ከትምህርቱ ይዘት ጋር የተጣመረ (Explicit / Direct and Integrated) ነው።

ሐ. ተለምዷዊ ማስተማር (መማር)

ተለምዷዊ ማስተማር (መማር) ለምርምሩ ስራ ሲባል በተዘጋጀው ክፍል ውስጥ ሆን ተብሎ የሚሰጠው የማንበብ ብልሃት ትምህርት አይነት ሆን ተብሎ በግልፅ የማይሰጥበት ነው። ትምህርት አሰጣጡ ተለምዷዊ የተባለበት ምክንያት የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ ሆን ተብሎ በታቀደ እና ቅድመ ዝግጅት እና ቅደምተከተል ባለው መልኩ ስለማይቀርብ ነው። (በዚህ የትምህርት አቀራረብ ሳይታሰብ የተወሰኑ የማንበብ ብልሃት አይነቶችን ተማሪዎች እንዲጠቀሙ ሊያደርግ ይችላል) በዚህ መንገብ የሚማሩ ተማሪዎችም ሳያስቡት የተወሰኑ የማንበብ ብልሃቶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ። ብልሃቶቹን ለምን እንደተጠቀሙ ሲጠየቁ ግን በዝርዝር ያልተማሩ በመሆናቸው መልስ ለመስጠት ይቸገራሉ።

2.2.2 የማንበብ ብልሃት ምንነት እና በጥናቱ ትኩረት የተሰጠባቸው የማንበብ ብልሃቶች

አላማ፡- የዚህ ትምህርት ክፍል አላማ እርስዎ መምህር የማንበብ ብልሃት ላይ ትኩረት ያደረገውን ትምህርት ለተማሪዎች ከመስጠትዎ በፊት በፅንሰሀሳቡ ላይ ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖርዎት የማንበብ ብልሃት ምንነት እና ዋና ዋና የሚባሉት የማንበብ ብልሃት አይነቶች ምን ገፅታ እንዳላቸው በዝርዝር ማቅረብ ነው፡፡ መምህር በዚህም ጥሩ ግንዛቤ እንደሚያገኙ ይታሰባል፡፡

ሀ. የማንበብ ብልሃት ምንነት

የማንበብ ብልሃት ፅንሰሀሳብ ከቋንቋ መማር ብልሃት ጋር ቀጥተኛ ትስስር አለው፡፡ ቋንቋ የመማር ብልሃት ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ በመማር ሂደት የተገኘን ፣ የተጠራቀመን ፣ የታወሰ መረጃን ተግባራዊ ለማድረግ በተደጋጋሚ የሚጠቀሙበት ማንኛውም አዕምሯዊ ተልኮ፣ ቅደም ተከተል ወይም እቅድ ነው፡፡ የቋንቋ መማር ብልሃት ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት የሚታይባቸው ባህሪ ወይም አስተሳሰብ ሲሆን የመማር ሂደቱን የበለጠ ውጤታማ፣ ግለመር ለማድረግ እና የቋንቋ ትምህርታቸውን ለማጎልበት በተማሪዎች ሆን ተብሎ የሚለመድ ባህሪ፣ድርጊት(ተግባር) ነው (Oxford 1990፣ O`Malley & Chamot 1990)፡፡

የማንበብ ብልሃት ተማሪዎች የቀረበውን ፅሁፍ አንብበው ለመረዳት ሆን ብለው የሚተገብሩት ስልታዊ እቅድ ፣ዘዴ፣ የአዕምሮ ተልኳዊ አሰራር ወይም ቅደም ተከተል ነው፡፡ የማንበብ ብልሃት አንድን ፅሁፍ በማንበብ ሂደት ተማሪዎች ውህድ አሀዳዊ ፍንጮችን ለማግኘት ያነበቡት እንዴት ስሜት ሰጪ እንደሚሆን ለማድረግ ፣ያነበቡት ባልገባቸው ጊዜ ወይም በማንበብ ሂደት ችግር በገጠማቸው ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለባቸው አቅጣጫ የሚያሳይ (ችግር ለመፍታት የሚያስችል)ሁነኛ መንገድ (መሳርያ) ነው (McNamara 2007፣ Block 1986)፡፡

ለ. የማንበብ ብልሃት አይነቶች

የማንበብ ብልሃት አይነቶች በቀጥታ ከቋንቋ መማር ብልሃት አይነቶች እንደሚቀዳ በዚህ ዙርያ የሚፅፉ እና ምርምር የሚያደርጉ ወገኖች ይገልፃሉ(Zhang 2012፣ Phakiti 2006፣ O`Malley and Chamot 1990፣ Oxford 1990)፡፡ እነዚህ የተጠቀሱት እና ሌሎች ፀሀፊዎች የማንበብ ብልሃት አይነቶችን በተለያየ መንገድ ቢከፍሉትም የ Oxfored (1990) አከፋፈል የዚህ የጥናታዊ ፅሁፍ አቅራቢ በጥናቱ የተጠቀመበት እና የማንበብ ብልሃት

አይነቶችን ለማሳየት አመቺ በመሆኑ የስልጠና መመሪያውም ይህንኑ ተከትሎ የቀረበ ነው።።

እንደ Oxfored (1990) አገላለፅ የማንበብ ብልሃት በዋናነት ቀጥተኛ እና ኢ-ቀጥተኛ ተብሎ በሁለት ይከፈላል። ቀጥተኛ የማንበብ ብልሃት የሚያተኩረው በቀጥታ በመማር እና ታላሚውን ቋንቋ በማፍለቅ ላይ ነው። ሁሉም ቀጥተኛ የመማር ብልሃቶች የሚፈልጉት የቋንቋውን አእምሯዊ የማብላላት ሂደት ነው። ኢ-ቀጥተኛ የማንበብ ብልሃት በስሩ ያሉ ንዑሳን ብልሃቶችን ተግባራዊ በማድረግ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ቋንቋ መማርን የሚደግፍ ነው።።

ቀጥተኛ የማንበብ ብልሃት በስሩ አእምሮታዊ፣ ማካካስ እና ትውስታ ብልሃቶችን ያካትታል። ኢ-ቀጥተኛ የማንበብ ብልሃት ስር ደግሞ እና ስሜታዊ ብልሃቶችን ያካተተ ነው። በነዚህ ንኡሳን የብልሃት አይነቶች ስር በርካታ ብልሃቶች አሉ። እነዚህን ብልሃቶች አቀናጅቶ ማስተማር የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አላማ በመሆኑ ከየንኡሳን ብልሃቶች የተውጣጡ አስራስድስት የማንበብ ብልሃቶች (መተንበይ፣ደግሞ ማንበብ፣ዋናውን ሀሳብ በፍጥነት ማግኘት፣መረጃን ፈልፍሎ ማውጣት፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ዋናውን ሀሳብ በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ፣የማንበብ ብልሃትን ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ ማሸጋገር፣ አውድን መጠቀም፣ ማቀድ፣ መቆጣጠር፣ራስን መገምገም፣ መገመት፣ የቀደመ እውቀትን መጠቀም፣ መጠየቅ፣ ከሌሎች ጋር መተባበር እና በአእምሮ ምስል መፍጠር) ላይ ያተኩራል።

አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት(Cognitive Reading Strategy) ከተለየ የመማር ተግባር ጋር የሚያያዝ ተማሪዎች በማንበብ ወቅት ውስብስብ የሆኑ ተግባራትን ለማከናወን እንዲችሉ የሚያግዝ ሆን ተብሎ የሚተገበር እና አንባቢዎች የተለየ የማንበብ ግባቸውን ለማሳካት የሚያገለግል በማንበብ ተግባር ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ብቻ ሳይሆን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት የሚረዳ አእምሯዊ ሂደት ነው። በሌላ አገላለፅ አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት ለተለየ የመማር ተግባር የሚያገለግል በማንበብ ሂደት የሚያጋጥምን ችግር ለማስወገድ የአእምሮ ተልኳዊ አሰራር ወይም ቅደም ተከተልን ጨምሮ ቀጥተኛ ትንተና፣ሽግግር እና ማዋሃድን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ነው(O`Malley & Chamot 1990:99)::

አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት በስሩ በርካታ ንዑሳን ብልሃቶችን ያካትታል። እነዚህ ብልሃቶች ከማንበብ፣ገለፃን ከማብላላት (ከመተንተን) እስከ ሀሳብን በራስ መንገድ አሳጥሮ

መፃፍ ድረስ መጠነ ሰፊ ናቸው። ዋና ዋና የሚባሉት አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አይነቶች እና በጥናቱ ትኩረት የተደረገባቸው መተንበይ፣ ደግሞ ማንበብ፣ ዋናውን ሀሳብ በፍጥነት ማግኘት፣ መረጃን ፈልፍሎ ማውጣት፣ ማስታወሻ መያዝ፣ሀሳብን በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ፣ማሸጋገር ፣ አዳዲስ ቃላትን ለመረዳት አውዳዊ ፍቺ መጠቀም ናቸው።

ማብራርያ

መተንበይ (Pridicting):- አንድ የቀረበን ፅሁፍ በማንበብ ሂደት ርዕሱን እና ንዑሳን ርዕሶችን እንዲሁም የእንዳንዱን አንቀፅ የመጀመሪያ አረፍተነገር በማንበብ እና ከቀደመ እውቀት ጋር በማገናኘት ፅሁፉ የያዘውን ሀሳብ አስቀድሞ በመተንበይ ለመረዳት የሚያስችል ነው። ይህ ብልሃት ለማንበብ ተግባር የቀረበን ፅሁፍ ከማንበብ አስቀድሞ ወይም በማንበብ ሂደት የሚተገበር ሲሆን ተማሪዎች አስቀድመው በመነቃቃት (የቀደመ እውቀታቸውን በመቀስቀስ) ፅሁፉን በሚገባ እንዲረዱ የሚያነሳሳ ነው።

ለምሳሌ፡- ለማንበብ ተግባር የቀረበው ርዕስ “የተፈጥር ሀብትን ጥበቃ” የሚል ቢሆን የተፈጥሮ ሀብት ምንድን ነው?በተፈጥሮ ሀብት ውስጥ የሚካተቱት ምን ምን ናቸው? የተፈጥሮ ሀብትን እንዴት መጠበቅ ይቻላል? የሚሉ ሀሳቦችን አስቀድመው በማሰላሰል እና ከቡድን አጋሮቻቸው ጋር በመወያየት የፅሁፉን ሀሳብ መተንበይ እንዲችሉ ማበረታታት ተገቢ ነው። በመማሪያ ማስተማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ቅድመ ንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ተብለው የሚቀርቡ ጥያቄዎች ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የቀረበውን ፅሁፍ መተንበይ እንዲችሉ የሚያነሳሱ በመሆናቸው እነሱንም መጠቀም ተገቢ ነው ።

ደግሞ(ደጋግሞ)ማንበብ (Repeating)፡- ይህ የማንበብ ተግባር በማንበብ ወቅት አገልግሎት ላይ የሚውል ነው። ተማሪዎች የተሰጠን የማንበብ ተግባር መሰረት በማድረግ በሚያነቡት ወቅት ፅሁፍ ውስጥ ያልገባቸው የቋንቋ ሀሳብ (Chanks of Language) ሲገጥማቸው ወደኋላ በመመለስ ቃላትን፣ሀረጎችን ወይም አንቀፆችን መልሶ ማንበብ ነው። ደግሞ የማንበብ ብልሃት የቀረበውን ምንባብ ከፊል አካሉን ወይም በሙሉ ከአንድ ጊዜ በላይ እንደገና በማንበብ ፅሁፉን ለመረዳት የሚያስችል ተግባር ነው። ተማሪዎች ይህን የማንበብ ብልሃት በብዛት መጠቀም ያለባቸው በምንባቡ ውስጥ ያለውን ጠቃሚ ሀሳብ የበለጠ ለመረዳት እና ያነበቡትን እንዳይዘነጉ ለማድረግ ነው።

ዋናውን ሀሳብ ፈጥኖ ማግኘት (Getting the Idea Quickly)፡-አንድንየቀረበ ፅሁፍ ዋና ሀሳብ በፍጥነት ማግኘት የማንበብ ብልሃት የሚባለው የቀረበውን ፅሁፍ ዋና ሃሳብ በፍጥነት ለማግኘት ከሚደረግ የገረፍታ ንባብ (Skimming) እና ከምንባቡ ውስጥ

የተለየ(የተነጠለ) ዝርዝር ሀሳብ ለማግኘት ከሚደረግ የምልከታ ንባብ (Scanning) ጋር የሚያያዝ ነው። ተማሪዎች በገረፍታ በሚያነቡበት ጊዜ ፅሁፉን በፍትነት በማየት የተለየ (የተነጠለ) መረጃ ለማግኘት (ለምሳሌ እውነታዎች፣ ቁጥሮች፣ ቁልፍ ቃላት እና ሀረጎችን መለየት) መጣር ነው። ይህንን ተግባር ለማከናወን ተማሪዎች በውህድአሀድ ውስጥ ባሉት በእያንዳንዱ ቃላት ላይ ያላቸውን ትኩረት በመቀነስ በውህአሀዱ ላይ አይናቸውን በፍጥነት እያንቀሳቀሱ እንዲያነቡ ማበረታታት ያስፈልጋል። ተማሪዎች የሚፈልጉትን መረጃ በሚያገኙበት ወቅት ፍጥነታቸውን በመቀነስ ወይም በቆምታ አረፍተነገሩን በዝርዝር አንብበው የሚፈልጉትን መረጃ እንዲለዩ ማድረግ ነው።

ዋናውን ሀሳብ በፍጥነት ለማግኘት ሁለት ዘዴዎች አሉ። እነሱም የገረፍታ ንባብ- በገረፍታ ንባብ ዋናውን ሀሳብ ለማግኘት ጥረት ማድረግ እና የአሰሳ ንባብ - ከፅሁፉ ውስጥ የተነጠለ ዝርዝር ሀሳብ (specific details) ለማግኘት የሚያገለግል ነው። በዚህ ወቅት ማስታወሻ መያዝ ጠቃሚ ነው።

ለጀማሪ አንባቢዎች ቅድመጥልቅ አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች (preview questions) ተማሪዎች በቀላሉ ገረፍታ እና አሰሳ ንባብ እንዲከናውኑ ይረዳቸዋል። ቅድመጥልቅ ጥያቄዎች ፍንጭ ሰጪ እና ቀላል መሆን አለባቸው። በተለይ እውነት ሀሰት ፣ አዎ/አይ አማራጭ ጥያቄዎች ጠቃሚ ናቸው። ላቅ ላሉ አንባቢዎች ቅድመጥልቅ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ የተወሰነ ፍንጭ በመስጠት ገረፍታ እና አሰሳ ንባብ እንዲያደርጉ ማበረታታት ያስፈልጋል።

ለምሳሌ- በቀረበው ምንባብ ውስጥ የተጠቀሱት ሶስት ጠቃሚ ነጥቦች ምን ምን ናቸው?

(በምንባቡ ውስጥ ሶስት ጠቃሚ ነጥቦች መኖራቸውን ፍንጭ መስጠት)

የገረፍታ እና የአሰሳ ንባብ ጥቅም እንዳለው ሁሉ ተማሪዎች ፅሁፉን በሚገባ ሳያነቡ እና ሳይረዱ መልስ ወደመስጠት (ጥቂት ጉዳዮችን ወደመፈለግ) አዝማሚያ ሊወስድ ስለሚችል ሙሉውን ፅሁፍ በሚገባ ማንበብን እና መረዳትን ማለማመድ ያስፈልጋል።ተማሪዎች ይህንን የማንበብ ብልሃት የሚጠቀሙት በማንበብ ወቅት እና ድህረ ማንበብ ነው።

መረጃን ፈልፍሎ በማውጣት ምክንያት ላይ የተመሰረተ ድምዳሜ ላይ መድረስ (Inference):- በቀረበ አንድ ፅሁፍ ውስጥ ዋና ሀሳብ እና ዝርዝር ሀሳቦች ይኖራሉ። ከዚህ በተጨማሪ እነዚህን ጠቃሚ ሀሳቦች ለማስረዳት እና አጉልቶ ለማሳየት የሚያስችሉ ማብራርያዎችም ይገኛሉ። ተማሪዎች አንድን የቀረበ ፅሁፍ በሚያነቡበት ወቅት ጠቃሚ

መረጃዎችን (ለምሳሌ አንደኛ ፣ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ወዘተ ተብለው ተዘረዘሩ) ፈልፍለው እንዲያወጡ ማድረግ የሚያስችል ብልሃት ነው። መረጃን ፈልፍሎ ማውጣት በቀረበው መረጃ የአዳዲስ ጉዳዮችን ትርጉም መገመት፣ ውዕአትን መተንበይ ወይም የጎደለ(ያልተሟላ)መረጃን ማሟላትም ነው። ብልሃቱ ለማንበብ ተግባር የቀረበን ፅሁፍ በማንበብ ሂደት የሚከናወን ነው። ይህ የማንበብ ብልሃት ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የቀረበን ፅሁፍ በሚያነቡበት ወቅት አንዳች ማስረጃ ወይም ምክንያት ላይ ተመስርተው ድምዳሜ ላይ የሚደርሱበት እና አንድምታን (implication) ፈልፍለው የሚያገኙበት ነው።

ለምሳሌ፦ አጭር ምንባብ ርዕስ ፦ የኢትዮጵያ ሚና

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጠንሳሽ የኢትዮጵያ መንግስት ነው። ይህ ድርጅት የአፍሪካ መንግስታት መሪዎች በተሳተፉበት ጉባኤ በ1963 ዓም አዲስ አበባ ላይ ተመሰረተ። ለነፃነትዋ መከበር ስትታገል በከፈለችው ታላቅ መስዋእትነት ምክንያት በአፍሪካ ከፍ ያለ ተደማጭነት ስላላት ኢትዮጵያ ወሳኝ ፖለቲካዊ ሚና እንደምትጫወት ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ከሰሜን አፍሪካ የአረብ አገሮችም ሆነ ከሰሀራ በታች የአፍሪካ አገሮች ጋር የተለየ ጥብቅ ትስስር የሌላት በጣም የተለየች ግን አፍሪካዊት አገር ስለሆነች በአፍሪካ አገሮች መካከል በሚነሱ ውዝግቦች ላይ ጠቃሚ አስታራቂ እንድትሆን አስችሏታል።

አለማየሁ አበበ፦ የኢትዮጵያ ታሪክ ከመጀመርያው እስከ አሁኑ ዘመን (2003፡580)

በዚህ ምንባብ ውስጥ ለአፍሪካ አንድነት መመስረት ትልቁን ሚና የተጫወተው ማነው ? ምክንያቱስ ? ተብሎ ቢጠየቅ ምላሽ የሚሆነው ምክንያት ላይ የተመሰረተ መልስ ነው። ይህም መረጃን ፈልፍሎ በማውጣት ድምዳሜ ላይ መድረስ ነው።

ማስታወሻ መያዝ (Note Taking)፦ በማንበብ ጊዜ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ሀሳቦችን ለማስታወስ እንዲያስችል ቃላትን እና ፅንሰሀሳቦችን በራስ መንገድ አሳጥሮ ማስታወሻ መያዝ ነው። አፃፃፉ በምህፃረ ቃል ማሳጠር፣በግራፍ መልክ ወይም በቁጥር መልክ ማድረግ ሊሆን ይችላል። ማስታወሻ መያዝ ተማሪዎቹ በመማር ማስተማር ሂደቱ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋል። ብልሃቱ በማንበብ ጊዜ የሚከናወን ሲሆን ተማሪዎቹ ጠቃሚ ፅንሰ ሀሳቦችን ለማዋቀር፣ መረጃዎችን ለማስታወስ እና መልሶ ለመጠቀም እንዲሁም የጥናት (የመማር) ሀሳብ እንዲያፈልቁ ይረዳቸዋል።

ተማሪዎች በተለያየ መንገድ ማስታወሻ ሊይዙ ይችላሉ (ይገባል)፡፡ ቀላሉ እና በጣም የተለመደው ማስታወሻ አያያዝ መስመራዊ ማስታወሻ አያያዝ መስመራዊ ማስታወሻ (raw note) ነው፡፡ መስመራዊ ማስታወሻ በጣም ያልተደራጀ እና ዋናውን ሀሳብ ያለቀቀ ነው፡፡ ተማሪዎች በዚህ መንገድ ማስታወሻ በሚይዙበት ወቅት ያነበቡት እንዳይረሳቸው ወደምንባቡ ወድያው መለስ እያሉ በመፃፍ ማስታወሻቸውን ስልታዊ በሆነ መንገድ ያደራጃሉ፡፡ ተማሪዎች በዚህ መንገድ ማስታወሻ ሲይዙ ጠቃሚ ነጥቦችን በመዘርዘር (ገበያ እቃ በመግዛት ወቅት አንዳች ነገር እንዳይረሳ እንደተፃፈ ዝርዝር (Shopping list) ዘርዝረው ይፅፋሉ፡፡

ሌላው መስመራዊ አፃፃፍን በመተው በአማርኛ የ “ፐ” ቅርፅ ማስታወሻ ሊይዙ ይችላሉ፡፡ ይህ ዘዴ ተማሪዎች ያነበቡት ሀሳብ እንዳይረሳ አደራጅቶ ለማስቀመጥ፣ ፅሁፉን በቀላሉ ለመረዳት፣ ያነበቡትን እና የቀደመ እውቀታቸውን ለማስተሳሰር ይረዳቸዋል፡፡

ለምሳሌ፡- “በቴክኖሎጂ ዘመን የሞባይል ጥቅም እና ጉዳት” የሚል ፅሁፍ ቢቀርብ በ “ፐ” ቅርፅ ማስታወሻ መያዝ ይችላሉ፡፡

በቴክኖሎጂ ዘመን የሞባይል ጥቅም እና ጉዳት

ጥቅም	ጉዳት
- ከሰወች ጋር በቀላሉ- በድምፅ መገናኘት - የፅሁፍ መልእክት መለዋወጥ - ድረ ገፆችን ማንበብ -የተለያዩ ጨዋታዎችን በመጫወት ራስን ማዝናናት	- በሀሰተኛ መረጃ መደናገር - የተለያየሁ ጨዋታዎችን እና ድረገፆችን በማንበብ በሱስ መጠመድ -ጊዜን ማባከን

ሌላው ትርጉም አመቻች ካርታ (semantic mapping) ማዘጋጀት ነው (ይህ የማስታወሻ አያያዝ ሌላው የብልሃት አይነት ነው፡፡ ማስታወሻ አያያዙ የቀረበው ፅሁፍ ይዘት እና ይዘቶቹ ያላቸውን ግንኙነት ሊያመላክት በሚችል መልኩ ትርጉም አመልካች ካርታ እንዲያዘጋጁ ማድረግ ነው፡፡

ቁልፍ ፅንሰሀሳቦችን (በቃላት ደረጃ) ተመሳሳይ ሀሳብ ካላቸው ጋር በመስመር በማያያዝ ማስቀመጥ ነው፡፡ ይህ ብልሃት ሀሳቦች እንዴት ርስበርሳቸው እንደሚተሳሰሩ ምስላዊ በሆነ መንገድ በማስቀመጥ ለመረዳት ያስችላል፡፡ ብልሃቱ ቃላትን ማቧደን ምስል መፍጠር ማዛመድ (ማስፋፋት) ጋር ይያያዛል፡፡

ለምሳሌ



ሌላው መደበኛ ቢጋር (outline) በማዘጋጀት ማስታወሻ መያዝ ነው። የቢጋር ማስታወሻ በቁጥር ወይም በፊደል ሊሆን ይችላል። ሁሉም ተማሪዎች የግድ በአንድ አይነት መንገድ ማስታወሻ እንዲይዙ ለማድረግ ሳይሆን የማስታወሻ አያያዝ መንገዶችን ከተረዱ በተመቻቸው መንገድ ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ ነው።

ሀሳብን በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ/ጭምቀ ሀሳብ (Summarizing)፡- በማንበብ ጊዜ የተገኘውን አዲስ መረጃ አዕምሯዊ ፣ቃላዊ ወይም ፅሁፋዊ በሆነ መንገድ አሳጥሮ ማቅረብ የሚያስችል ጠቃሚ ቴክኒክ ነው። ሀሳብን በራስመንገድ አሳጥሮ መፃፍ ምንባቡን በጥንቃቄ በማንበብ ሀሳብ ሳይዛነፍ በራስ ቋንቋ አጠር አድርጎ መፃፍ ነው። ጭምቀ ሀሳብ በፅሁፍ ውስጥ ያለውን ሀሳብ ለመያዝ እና የበለጠ ለመረዳት የሚያስችል ከመሆኑም በተጨማሪ የቀረበውን ፅሁፍ ለመተንተን እና ለመሄስ(ሂስ ለማድረግ) ያስችላል። ጭምቀ ሀሳብ ለመፃፍ ከፍ ያለ የመረዳት፣ የቋንቋ አጠቃቀም እና የማደራጀት ችሎታን የሚጠይቅ ቢሆንም ቀስ በቀስ ተማሪዎችን ማለማመድ ያስፈልጋል። ጭምቀ ሀሳብ ለመፃፍ በማንበብ ጊዜ ማስታወሻ መያዝ በጣም ጠቃሚመነው። ይህ ብልሃት ድህረምንባብ አገልግሎት ላይ የሚውል ነው።

ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የቀረበንፅ ፅሁፍ አንብበው በመረዳት ዋናውን ሀሳብ በራሳቸው መንደግ አሳጥረው ጭምቀሀሳብ በሚፅፉበት ጊዜ ማከናወን ያለባቸው ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

- የቀረበውን ፅሁፍ ዋና ሀሳብ መለየት፣
- በፅሁፉ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ሀሳቦች ማገናኘት እና በማስታወሻ ላይ መፃፍ፣
- በፅሁፉ ውስጥ ዋናውን ሀሳብ ለማብራራት የገቡትን የማያስፈልጉ መረጃዎች መተው
- ፅሁፉን ደጋግሞ በማንበብ ያነበቡትን ማስታወስ
- በራሳቸው መንገድ የሚፅፉት ሀሳብ ከዋናው ፅሁፍ የተለየ እንዳይሆን መጠንቀቅ
- የምንባቡን ሀሳብ በራሳቸው ቋንቋ መፃፍ
- በራሳቸው መንገድ አሳጥረው የፃፉት እና የቀረበው ፅሁፍ ሀሳብ ተመሳሳይ መሆኑን ማረጋገጥ ናቸው፡፡

ማሸጋገር(Transfering):- ተማሪዎች በሚማሩበት ቋንቋ አዲስ እውቀት ለማግኘት የቀደመ እውቀታችሁን መጠቀም ወይም በሌላ አገላለፅ በመጀመሪያ ወይም በሁለተኛ ቋንቋ የቀረበው ምንባብ ውስጥ ያለውን ሀሳብ ለመረዳት የማንበብ ብልሃቶችን ከመጀመሪያ ቋንቋ ወደሁለተኛ ቋንቋ ወይም በተቃራኒው ማሸጋገር ነው፡፡ ይህ የማንበብ ብልሃት በተለይ በሁለተኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ ለመረዳት አስቸጋሪ ሁኔታ ሲያጋጥም በመጀመሪያ ቋንቋ የተማሩትን አምጥቶ በመጠቀም የገጠመን ችግር ለማስወገድ ጥረት ማድረግ ነው፡፡ ብልሃቱ በማንበብ ወቅት ተግባራዊ የሚሆን ሲሆን በተለይ ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በእናት ቋንቋቸው የተማሩትን እያመጡ ለመጠቀም የሚያስችል በመሆኑ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

አውድ መጠቀም (Context)፡- የቀረበን ምንባብ አንብቦ ለመረዳት በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ቃላት ሁሉ ማወቅ ሊከብድ ይችላል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በማንበብ ሂደት በምንባቡ ውስጥ አዳዲስ ቃላት ሲያጋጥማቸው መዘገበ ቃላት ከመጠቀም ይልቅ ቃላቱ በሀረግ ወይም በአረፍተ ነገር ውስጥ ያላቸውን ሀሳብ ለመረዳት አውድን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ አውድን ተጠቅሞ ለአዳዲስ ቃላት ወይም ሀረጎች ፍቺ ለመስጠት ፅሁፉን ደጋግሞ ማንበብ ማንበብ ያስፈልጋል፡፡ በመቀጠል አዲስ የተባለው ቃል ወይም ሀረግ ብቻውን እና በአረፍተነገር ውስጥ የሚሰጠውን ፍቺ ለመለየት ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ለምሳሌ ከዚህ በታች በቀረበው አጭር ምንባብ ውስጥ የተሰመረባቸው አዳዲስ ቃላት አውድ በመጠቀም ፍቻቸውን መፈለግ ይቻላል፡፡

ትራጀዲ ተውኔት

የትራጀዲ ታሪክ አሳሳቢ በሆኑ እና ማህበረሰቡ ትልቅ ግምት በሚሰጣቸው ጉዳዮች ላይ ይመሰረታል። በታሪክ ውስጥ የሚፈፀሙ አበይት ድርጊቶች ማህበረሰቡን የሚነኩ እና ዘላቂነት ያላቸው ናቸው። በሰዎች ዘንድ ሊደርሱ የሚችሉ ከፍተኛ ቦታ እና ላቅ ያለ ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው። አሳሳቢነታቸው ከፍ ያለ በመሆኑ እና የሁሉም ሰዎች ጉዳይ ስለሚሆኑ በሰዎች ስሜትም ላይ የሚያስከትሉት ተፅእኖ ከባድ እና አስጨናቂ ይሆናል። የሰው ስሜት ጨቋነው በፍርሃት እና በሰቀቀን እንዲዋጥ ያደርጋሉ። የተረጋጋን ህይወት የሚያናጉ ሰላማዊውን እንቅስቃሴ በሽብር የሚሞሉ ናቸው። እንዲህ በመሆናቸው በተመልካቹ ላይ የሚፈጥሩት ድባብ የፍርፋት፣ የሰቀቀን እና የጭንቀት ነው። ትራጀዲ በዋናነት በግለሰቡ እና የእሱን ውድቀት በሚያመጡ ሀይሎች መካከል የሚደረግ ግጭት ነው። ገፀባህርያት ከማይችሉት ሀይል እና ሁኔታ ጋር ይጋጫሉ። ጦርነት የሚገጥሙትም ከነሱ ከጠነከረ እና ከላቀ ሀይል ጋር በመሆኑ ይህ በራሱ አስጨናቂ ነው የሚሆነው። እንዲህ ያለ ሁኔታ ውስጥ ባሉ ገፀባህርያት ላይ የሚደርሰው መፍጨርጨር እና መሰቃየት ተመልካቹን ያሸብራል። በገፀባህሪው ይደርሳል ብሎ የሚገምተው አስከፊ ነገር ይበልጥ ይሰቀጥጠዋል። በዚህም በሽብር እና በጭንቀት ይዋጣል።
ዘሪሁን አስፋው -የስነፅሁፍ መሰረታውያን (1992፡277)

ሌላው በቀጥተኛ የማንበብ ብልሃት ስር የሚካተተው ማካካስ የማንበብ ብልሃት (Compensation Reading Strategy) ነው። ማካካስ የማንበብ ብልሃት በታላሚው ቋንቋ የሰዋስው እና የቃላት እውቀት ማነስን የማስተካከል እቅድን ለማሳካት የሚያገለግል ብልሃት ነው። እንደ Oxford (1990፡90) ገለፃ ማካካስ የማንበብ ብልሃት ተማሪዎች የገጠማቸውን የእውቀት ማነስ ለማስተካከል የሚያስችል በተለይ ለጀማሪ እና መካከለኛ ደረጃ ቋንቋ ተማሪዎች እጅግ ጠቃሚ ነው። ብልሃቱ ቋንቋን በሚገባ ለሚጠቀሙበት ወገኖችም ያገለግላል። በተለይ አንዳንድ ጊዜ ያልገባቸው ገለፃ ሲገጥማቸው ለመረዳት ያስችላል። በዚህ ብልሃት ስር የሚካተተው እና ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ትኩረት የሚያደርግበት መገመትን ነው።

ማብራርያ

መገመት **(Guessing Intelligently)፡-** ተማሪዎች በማንበብ ወቅት የሚያነቡትን ፅሁፍ አጠቃላይ ትርጉም ለመረዳት እያንዳንዱን ቃል ማወቅ አስቸጋሪ ነው። በመሆኑም አንብቦ ለመረዳት ሁሉንም ጉዳይ በዝርዝር ልረዳ ብለው ሳይታገሉ ዘዴ የታከለበት ግምት መጠቀም አለባቸው። ብልሃቱ በማንበብ ሂደት ግልፅ ያልሆኑ ቃላትን፣ ሀረጎችን እና

አረፍተነገሮችን ለመረዳት ያስችላል። ተማሪዎች በሁለት መንገድ መገመት ይጠበቅባቸዋል።

ሀ. የቋንቋ ፍንጭ ላይ የተመሰረተ ግመታ(Using Lingustic Clues)- በቅርብ ጊዜ በታላሚው ቋንቋ ያገኙት እውቀት፣ የተማሪዎች የራሳቸው ቋንቋ ወይም ሌላ ቋንቋ ፍንጭ ላይ መሰረት ያደረገ ግመታን ተግባራዊ ለማድረግ ሊያገለግል ይችላል። ተማሪዎች በሚያነቡበት ወቅት በምንባቡ ውስጥ ግልፅ ያልሆኑ ቃላት ቅድመ እና ድህረግንድ ቅጥያዎችን፣ የቃላት አደራደርን ማየት ግመታ ለማድረግ ጠቃሚ የቋንቋ ፍንጮች ናቸው።

ለምሳሌ- የተፈጥሮ ሀብት በየጊዜው እየተመናመነ ከመጣ በአካባቢው ያለውን ስነምህዳር ሊያጣ ይችላል። ህንን አረፍተነገር ያነበበ አንድ ተማሪ በአረፍተነገር ውስጥ እየተመናመነ የሚለው ቃል ባገባው አንደኛ በአገባቡ ሊገምት ይችላል። ሌላው "እየተ" የሚለውን ቅድመ ግንድ ቅጥያ ቢወጣ መናመነ ወይም መነመነ የሚል ቃል ያገኛል። ይህን ቃል ለመገመት አይቸገርም።

ለ. ሌሎች ፍንጮች (ኢ-ቋንቋ ፍንጭ) (Using Other Clues) - ሌሎች ፍንጮች ወይም ቁልፍ ቃላትን መጠቀም ከቋንቋ እውቀት በተጨማሪ ከቋንቋ ጋር ያልተገናኙ ጉዳዮችን በማስተዋል መገመት ይቻላል። ለምሳሌየሰዎች የማዕረግ ወይም ቅፅል ስሞች ለአንባቢዎች ግመታ ፍንጭ ይሰጣሉ። ለምሳሌ- ውድ እህቴ፣ የተከበርክ ባለቤቴ፣የቀድሞ ወዳጄ፣ የትምህርት እና የስራ ማእረግ ዶክተር፣ፕሮፌሰር፣ዋና ሀላፊ፣ክቡር ፕሬዘዳንት፣ሚኒስቴር ዴኤታ ወዘተ። ሌላው የቀደመ እውቀትን መጠቀም ነው (የቋንቋ እውቀት፣ በጉዳዩ ዙርያ ያለ እውቀት፣ ወቅታዊ አለምአቀፍ እውቀት፣ የባህል እውቀት እና አጠቃላይ የቀደመ እውቀት) ።

በቀጥተኛ የማንበብ ብልሃት ስር ሶስተኛው ትኩረት የተሰጠው የማንበብ ብልሃት ትውስታ የማንበብ ብልሃት(Memory Reading Strategy) ነው። ትውስታ የማንበብ ብልሃት አንዳንድ ጊዜ ለትውስታ የሚረዳ (Mnemonics) ተብሎ ይጠራል። በትውስታ ብልሃት አጠቃቀም መረጃን ማጠራቀም እና ያጠራቀሙትን (ያስቀመጡትን) መረጃ እንደገና መጠቀም ወሳኝ ጉዳይ ነው። የብልሃቱ ዋነኛ ጉዳይ ተማሪዎች እውቀታቸውን ለማዳበር ያነበቡትን ጠቃሚ ሀሳብ ለአጭር እና ለረጅም ጊዜ ማስቀመጥ እና አስታውሶ እንደገና መጠቀም ነው። በዚህ የማንበብ ብልሃት ስር የሚካተቱት በአእምሮ ምስል መፍጠር እና የቀደመ እውቀትን መጠቀም (ሀሳብን ማያያዝ ወይም ማስፋፋት) የማንበብ ብልሃቶች በጥናቱ ትኩረት የተሰጠባቸው ናቸው።

ማብራርያ

1. **የቀደመ እውቀትን መጠቀም** (Using Background Knowladge)፡- ይህ የማንበብ ብልሃት ስለአለም እና ስለሚነበበው ፅሁፍ ይዘት ያለ እውቀትን በአግባቡ መጠቀምን የሚመለከት ነው፡፡ በውህድ አሃድ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ቃላት መለየት አንብቦ መረዳትን አያረጋግጥም፡፡ በመሆኑም አንባቢዎች ትርጉምን ለማዋቀር የውህድ አሃዱን መረጃ አስቀድመው ከሚያውቁት ጋር ማገናኘት አለባቸው፡፡ ይህንን ብልሃት ምሁራን ማስፋፋት ወይም ማብራራት በማለት ይገልፁታል፡፡ በተለይ አጠቃላይ የቀደመ እውቀት (የታላሚው ቋንቋ ባህል፣ለማንበብ የቀረበው ፅሁፍ ርዕሰ ጉዳይ፣ ለአለም ያለ እውቀት እና የወቅታዊ ጉዳይ እውቀት፣ ስነጥበብ ፣ ፖለቲካ፣ ስነፅሁፍ) ተማሪዎች በማንበብ ሂደት ለመገመት እና ውህድ አሃዱን ለመረዳት ያስችላቸዋል፡፡ ጥናቶችም የቀደመ እውቀት በተደጋጋሚ መጠቀም ውህድ አሃድን ለመረዳት በጣም ጠቃሚ እንደሆነ ያመላክታሉ፡፡ ይህ ብልሃት የማንበብ ክንውኑ ተጀምሮ እስኪያልቅ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

2. **በአእምሮ ውስጥ ምስል መፍጠር**(Using Imagery/Visualize)

   በአእምሮ ውስጥ ምስል መፍጠር የማንበብ ብልሃት የቀረበን ምንባብ መሰረት በማድረግ መረጃ በአእምሮ ውስጥ ትርጉም ያለው ይዘታዊ ምስል እንዲከሰት ለማድረግ የሚስችል ነው፡፡ በአእምሮ ውስጥ የሚከሰተው ምስል የቃላትን ወይም የገለፃን ቅደም ተከተል ለመለየት የሚያገለግል ነው፡፡ ይህ ብልሃት በአእምሮ ውስጥ ሁነቶችን ወይም ነገሮችን ከሀሳባዊ ምስል ጋር በማያያዝ ውስብስብ ቃላትን ለማስታወስ ይረዳል፡፡ ለምሳሌ፡- ማብሰል፣ ማፅዳት፣ ማጠብ፣ መቁረጥ፣ መግዛት፣ ወዘተ ቃላት ሁነቶች በአእምሮ ውስጥ ምስል እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ አካባቢን የሚገልፁ ለምሳሌ ተራራው በአደይ አበባ ተንቆጥቁጧል፡፡ ክረምት በመሆኑ አካባቢው ጨቅይቷል፡፡ ድርጊቶች ለምሳሌ ሰላማዊት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ ሳሎን ቤት መመገብያ ወንበር ላይ ተቀምጣ ጠረቤዛው ላይ ትልቅ መፅሀፍ ዘርግታ ታነባለች፡፡

   የፅሁፍን ሀሳብ በአእምሮ ምስል እንዲሀጥር ማድረግ ቃላትን ጨምሮ የፅሁፍን ሀሳብ ለማስታወስ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ለምሳሌ ቃላቱ ረቂቅ ቢሆኑ - ብርሃን፣ፍቅር፣ተስፋ ግኡዝ ነገርን የሚያመላክቱ ቢሆኑ ለምሳሌ - ቤት፣ ዛፍ፣ መጠንን የሚያመላክቱ ረጅም፣ አጭር፣ ሰፊ ጠባብ መስተዋድዶች ለምሳሌ- ከላይ በውስጥ፣ከ...መካከል፣ በታች፣ በስር ቃላትን አእምሯዊ ምስል በመፍጠር እንዳረሱ ማድረግ ነው፡፡ ሌላው

ምንባቡን በሚገባ በማንበብ እና አወቃቀሩን በመረዳት ሀሳብ እንዴት ተደራግቶ እንደተቀመጠ በአእምሮ ምስል በመፍጠር የምንባቡን ጠቃሚ ሀሳብ ለማስታወስ ያገለግላል። ብልሃቱ በማንበብ ሂደት የሚተገበር ነው።

በኢ-ቀጥተኛ የማንበብ ብልሃት ስር የሚካተተው ልእለአዕምሮታዊ የማንበብ ብልሃት (Metacognitive Reading Strategy) ስለማሰብ ማሰብ ነው። ብልሃቱ የመረዳትን እውቀት (Knowledge of Cognition) እና መረዳትን የመቆጣጠርን እውቀት (Regulation of Cognition/ Knowledge of Regulation) አካቶ የያዘ ነው። ብልሃቱ በማንበብ ሂደት ማንበብን ለማቀድ፣ ራስን እና መረዳትን መቆጣጠር እንዲሁም የማንበብ ሂደቱ በሚከናወንበት ጊዜ እና ካበቃ በኋላ ራስን መገምገም ያስችላል። በሌላ አገላለፅ ልእለአዕምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አእምሮታዊ ሂደትን የመቆጣጠር ልምድ ሲሆን አንባቢው የሚጠቀምበትን አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት በማገዝ የማንበብ ግብን ለማሳካት የሚያስችል ነው። ልእለአዕምሮታዊ የማንበብ ብልሃት አንባቢዎች ምን አይነት የማንበብ ብልሃቶችን መጠቀም እና እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ለመቆጣጠር የሚያግዝ ብቻ ሳይሆን ብልሃቶችን ለምን፣ መቼ እና የት መጠቀም እንዳለባቸው እንዲሁም እንዴት ራሳቸውን መመዘን እንዳለባቸው የሚገነዘቡበት ነው። በልእለአዕምሮታዊ የማንበብ ብልሃት ስር የሚካተቱት ንዑሳን የማንበብ ብልሃቶች የማንበብ አላማ እና ግብ ማስቀመጥ (ማቀድ)፣ መቆጣጠር እና የማንበብ ሂደቱን መገምገም ናቸው።

ማብራርያ

1. **ማቀድ(Planning) ፦** ይህ የማንበብ ብልሃት አንድን ፅሁፍ ለማንበብ አስቀድሞ በምን መልኩ መነበብ እንዳለበት ማብሰልሰልን እና በማንበብ ጊዜ አንብቦ መረዳትን ተግባራዊ ለማድረግ እንዴት መነበብ እንዳለበት ማቀድን ያመላክታል። በዚህም ትኩረት የሚሰጠው ተግባር፦

   ሀ. በከፍተኛ ሁኔታ ማደራጀት - የማንበብ ተግባሩን አላማ መወሰን እና እንዴት መጨረስ እንደሚገባ ማቀድ፣

   ለ. ትኩረትን ቀጥተኛ ማድረግ - የማይጠቅም መረጃን በመተው እና ወደሚነበበው ዋና ጉዳይ ትኩረት በማድረግ አጠቃላይ ግንዛቤ ለማግኘት መጣር ፣

   ሐ. ትኩረትን መምረጥ - ከአንብቦ መረዳቱ ተግባር ጋር በማገናኘት ወደተነጠለ ዝርዝር ጉዳይ ማተኮር

መ. ራስን መምራት - በተሰጠው የማንበብ ተግባር መሰረት አስፈላጊ ሁኔታዎችን በመረዳት ለማንበብ እና የራስን መነሳሳት መምራት እና የማንበብ ፍጥነትን ማስተካከል ናቸው።

2. **መቆጣጠር** (Monitoring) ፡- ይህ የማንበብ ብልሃት የማንበብ ሂደትን እና መረዳትን መቆጣጠር የሚያስችል ነው። በስሩ ያሉት ተግባራት፡-

   ሀ. አንብቦ መረዳትን መቆጣጠር - የሚነበበውን ፅሁፍ ለመገንዘብ መረዳትን መቆጣጠር እና ማጣራት ወይም መረዳትን ማረጋገጥ

   ለ. ተግባርን መቆጣጠር - ተግባርን ለማጠናቀቅ ራስን መቆጣጠር

3. **ራስን መገምገም**(Self-Evaluation)፡- በማንበብ ሂደት አንባቢው የቀረበው ፅሁፍ ገብቶት እንደሆነ እና እንዳልሆነ፣ አንብቦ ለመረዳት ምን ችግር እንዳጋጠመው ወዘተ የሚገመግምበት ነው። በዚህም ስር ያሉት ተግባራት ፡-

   ሀ. ብቃትን (ክወናን) መገምገም - በተሰጠው የማንበብ ተግባር መሰረት ምን ያህሉን በማንበብ መረዳት ቻልኩ ብሎ ራስን መገምገም

   ለ. ያጋጠመን ችግር መገምገም- በተሰጠው የማንበብ ተግባር መሰረት በማንበብ ሂደት የአጋጠመኝ ችግር ምንድነው በማለት ራስን መገምገም ነው።

ተማሪዎች ልእለአዕምሮታዊ የማንበብ ብልሃት በመጠቀም ወቅት ተግባራዊ ሊያደርጓቸው የሚገቡ ክንውኖች

ማቀድ፡-

- ፅሁፉን በአጠቃላይ ከማንበብ በፊት የሚነበበውን ለማወቅ ፅሁፉን በአጠቃላይ መመልከት (ለምሳሌ፡- አስፈላጊ የሆኑ ርዕሶች፣ ንኡሳን ርዕሶች፣ የምህራፍ ቢጋሮች፣ ጭምቀ ሀሳቦች ወዘተ ....
- የፅሁፉን ርዝመት እና አወቃቀር ማጤን
- የተሰመረባቸው፣ ቀልመው ወይም ደምቀው የተፃፉ፣ ጋደድ ብለው የተፃፉትን ማስተዋል፣ ከማንበብ በፊት የማንበብ አላማን በአዕምሮ ማስቀመጥ፣
- የፀሀፊውን መልዕክት መገመት
- እራስን መጠየቅ ፣
- የሚነበበውን በሚገባ ለመረዳት ስለርዕሱ ምን አውቃለሁ ብሎ ማሰብ፣
- በጥልቀት የሚነበበውን እና የሚተወውን በመለየት መወሰን፣
- በሚነበብበት ጊዜ ማስታወሻ መያዝ ፣ ምልክት ማድረግ፣ ማንበብን ገታ (ቆም) አድርጎ ማሰላሰል፣

መቆጣጠር፡-

- የፅሁፉ ርዕስ እና ይዘት ከማንበብ አላማችን ጋር የሚዛመድ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- ማስታወሻ መያዝ (ምሳሌዎች ፣ ሀሳቦች ፣ ተያያዥ ጉዳዮች) ፣
- በየተወሰነ ቦታ ማንበብን ገታ (ቆም) በማድረግ ስለሚነበበው ጉዳይ ማሰላሰል፣

- በፅሁፍ ውስጥ አስፈላጊ የሆነን ጉዳይ ለማስታወስ ጠቃሚ በሆነ ሀሳብ ላይ ምልክት ማድረግ ፣ ማስመር፣ ማክበብ ወዘተ...፣
- የበለጠ ለመረዳት አውዳዊ ፍንጮችን መጠቀም፣
- በፅሁፍ ውስጥ ያለውን ሀሳብ በትክክል መገመታችንን ማረጋገጥ፣
- ከምንባቡ ውስጥ አዲስ መረጃ አገኘሁ ወይ ብሎ ራስን መጠየቅ፣
- ከምንባቡ ውስጥ ፍፁም የማይታወቁ ቃላት ካሉ መዝለል ፣ አንዳንዶቹን መዝግቦ መያዝ እና ማረጋገጥ (በዚህ ምክንያት ማንበብን ማቋረጥ አያስፈልግም)፣
- ግልጽ ያልሆነን ሀሳብ ተመልሶ ማንበብ፣

ማጠቃለያ፡-

- ተጨማሪ ጥያቄዎችን፣ የችግሮች መፍትሄዎችን እና ተግባራትን ማሰብከ፣
- ማስታወሻን መልሶ ማየት፣ የተዘነጋ ሀሳብ ካለ ማካተት፣ መፃፍ፣
- ምንባቡን በሚገባ ለመረዳት ደግሞ ማንበብ፣ የፀሀፊውን ሀሳብ በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ፣
- ከማንበብ አላማ በመነሳት ምን ተማርኩ ብሎ ራስን መጠየቅ (በምንባቡ መሰረት የተሰጡ ተግባራትን ማከናወን፣ የቤትና የክፍል ስራ መስራት፡፡

ሌላው በኢ-ቀጥተኛ የማንበብ ብልሃት ስር የሚካተተው ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት(Social Reading Strategy) ትኩረት የተሰጠበት ብልሃት ነው፡፡ የቋንቋን መሰረታዊ ክሂሎችን ለምሳሌ ማንበብን በመማርሂደት የሰዎችን ተግባቦታዊ ተሳትፎ (Involvement) ይፈልጋል፡፡ ተግባቦትም በሰዎች መካከል የሚፈጠር መስተጋብር ነው፡፡ ቋንቋን በመማር(በማንበብ) ሂደት የሰዎች ተሳትፎ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ተገቢ ማህበራዊ ብልሃት መጠቀም ያስፈልጋል (Oxford 1990)፡፡ በማህበራዊ ብልሃት ስር የሚካተቱት ንኡሳን ብልሃቶች ጥያቄ መጠየቅ ፣ ከሌሎች ጋር መተባበር እና ሌሎችን ማዳመጥ ናቸው፡፡ በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ እና ከሌሎች ጋር መተባበር ትኩረት የተሰጠባቸው የማንበብ ብልሃቶች ናቸው፡፡

ማብራርያ

1.ጥያቄ መጠየቅ (Asking Question)፡- ጥያቄ መጠየቅ ዋነኛው ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት አካል ነው፡፡ ጥያቄ መጠየቅ ተማሪዎች ትክክለኛ ትርጉም ለማግኘት እና ለመገንዘብ የሚረዳቸው ነው፡፡ ተማሪዎች ከመምህራቸው፣ ከአቻዎቻቸው ጋር እርስ በርስ በመነጋገር በታላሚው ቋንቋ ሰፋ ያለ ግብአት በማግኘት የመማር ፍላጎታቸው እና ተነሳስቷቸው እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ በዚህ ብልሃት ሌላን ሰው መጠየቅ (ለምሳሌ መምህርን ወይም በታላሚው ቋንቋ አፉን የፈታ ወይም የበለጠ ብቃት ያላቸው ተማሪዎችን (ጓደኛን) መጠየቅ እና ራስን መጠየቅ ነው፡፡ በተለይ ራስን መጠየቅ ተማሪዎች

ፅሁፉን አንብበው ካጠናቀቁ በኋላ ያነበብኩት ምን ያህል ገብቶኛል እያሉ ራሳቸውን የሚጠይቁበት ነው። ተማሪዎች ራሳቸውን ሲጠይቁ ይማራሉ። ብልሃቱ በማንበብ ሂደት እና ድህረማንበብ የሚከናወን ነው። በዚህ ሂደት ተማሪዎች ለማብራራት (ለማጣራት) ፣ ለማረጋገጥ እና ለማረም ይጠይቃሉ።

ሀ. ለማብራራት (ለማጣራት) ወይም ለማረጋገጥ መጠየቅ(Asking for clarification or verification)፡- ተናጋሪው ሪፖርት እንዲያደርግ፣ ሀሳብን አሳጥሮ እንዲያቀርብ፣ ረጋ እንዲል ወይም ምሳሌ እንዲሰጥ፣ እያንዳንዱ ንግግር ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ወይም ህጎች ከእያንዳንዱ ጉዳይ ጋር የሚገጥሙ መሆኑን ፣የሆነ ሀሳብ ትክክል መሆኑን እና ምጋቤ ምላሽ ለማግኘት ሀሳብን አሳጥሮ ማቅረብ ወይም መድገም ያለበት ነው።

ለ. ለማረም መጠየቅ(Asking correction)፡- በአብዛኛው በንግግር ልውውጥየሚያገለግል ሲሆን በንግግር ጊዜ ያለን ሀሳብ ለማረም መጠየቅ ነው። አንድን ነገር ለማረም መጠየቅ በተለይ ክፍል ውስጥ በጣም ጠቃሚ የሆነ ብልሃት ነው። በክፍል ውስጥ ያለ መማር ማስተማር በአብዛኛው ግልፅ እርማት (Overt Correction) የሚፈልግ በመሆኑ ለማረም መጠየቅ ጠቃሚ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ብልሃቱ ራስንም የመጠየቅ ሂደት ያስተናግዳል። ይህም አንባቢው የሚያነበው እያንዳንዱ የፅሁፍ አካል የገባው መሆን አለመሆኑን ከራሱ ጋር እየተነጋገረ ይጠይቃል።

2. **ከሌሎች ጋር መተባበር** (Cooperating with others)

ይህ የማንበብ ብልሃት ከሌሎች አቻዎች (ከአንድ ወይም ከብዙዎች)ጋር መስተጋብር በመፍጠር የቋንቋ ችሎታን እና የማንበብ ችሎታን ለማዳበር የሚያስችል ነው። ይህ ብልሃት ከቋንቋ መማር ብልሃት ጋር መሰረታዊ ግንኙነት ያለው ሲሆን ተማሪዎች የቋንቋ ብቃታቸውን ለማጎልበት ብቻ ሳይሆን በራስ መተማመንን እና ማህበራዊ ተቀባይነትን እንዲያጎለብቱ ይረዳል።

ሀ.ከጥንድ አቻ ጋር መተባበር፡- በክፍል ውስጥ በተደጋጋሚ የሚከናወን ሆኖ ተማሪዎች ከአቻዎቻቸው ጋር በመተባበር ተወዳዳሪነታቸውን እና ተፎካካሪነታቸውን እንዲያጎለብቱ ያደርጋል።

ለ.ብቃት ካላቸው ጋር መተባበር፡- ብዙ ጊዜ በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ ተተኳሪው ቋንቋ የመጀመሪያ ቋንቋቸው ከሆኑ ወይም በችሎታቸው ከእነሱ ላቅ ካሉ አቻ ተማሪዎች ጋር በመተባበር መወያየት ፣ መከራከር እና ባነበቡት ሀሳብ ዙርያ ልምድ መጋራትን ለማከናወን ይጠቅማል።

2.3 የተለያዩ ፅሁፎችን አንብቦ ለመረዳት የማንበብ ብልሃቶችን ተግባራዊ ማድረግ ያለው ጠቀሜታ

ተማሪዎች የተለያየ የመማር ስልት ያላቸው በመሆኑ በዛ ያሉ የማንበብ ብልሃቶችን ከትምህርቱ ይዘት ጋር በማቀናጀት ማስተማር ተማሪዎቹ በራሳቸው መንገድ አንብበው የሚረዱ እና ራስመር እንዲሆኑ ከማስቻሉም በላይ ብልሃቶችን እየመረጡ በመጠቀም አንብቦ የመረዳት ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ እገዛ ያደርጋል፡፡ በግልፅ የተማሩትንም የማንበብ ብልሃቶች ተለዋዋጭ በሆነ አውድ ውስጥ ራሳቸውን እያስተካከሉ ጠንካራ እና ዘላቂ አንባቢዎች እንዲሆኑ ይረዳል፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን አቀናጅተው ሲጠቀሙ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እውቀታቸው ከመጎልበቱ በላይ አንብቦ መረዳታቸውን እናራሳቸውን መቆጣጠር የሚችሉ ንቁ አንባቢዎች እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፡፡ ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በሚገባ ተግባራዊ የሚያደርጉ ጠንካራ አንባቢዎች ከሆኑ ራሳቸውን የቻሉ አንባቢዎች እንዲሆኑ፣ ነፃ እና ለትምህርት ሃላፊነት የሚወስዱ፣ በራሳቸው መንገድ የማንበብ ብልሃቶችን መጠቀም የሚችሉ እና የሚያነቡትን የሚገነዘቡ (የሚረዱ) በመሆናቸው ሁልጊዜ ለመማር የተነሳሱ ንቁ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ ብልሃት ተኮር ማስተማር የመጨረሻ ግቡ ተማሪዎች ውጤታማ የማንበብ ብልሃቶችን በራሳቸው መንገድ በመምረጥ አንብቦ ለመረዳት ጥረት የሚያደርጉ ነፃ እና ራስ መር አንባቢዎች እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

ክፍል ሶስት

የማንበብ ብልሃትን የማስተማሪያ ሞዴል እና አቀራረብ

3.1 የማንበብ ብልሃትን የማስተማርያ ሞዴል

የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ ለሙከራ ቡድኖቹ በሚሰጥበት ወቅት ተግባራዊ የሚሆነው የማስተማርያ ሞዴል መምህር በነፃ ማሰብ(እየተገበሩ ማሳብ ወይም ሞዴል መሆን) ፣ አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ እና ትግግዝ ሞዴሎችን በማቀናጀት ነው፡፡

ሀ. መምህር በነፃ ማሰብ (እየተገበሩ ማሰብ) ሞዴል(Teacher think aloud model)

መምህር በነፃ ማሰብ (እየተገበሩ ማሰብ) ብልሃቶችን የማስተማር ሞዴል መምህር ሞዴል በመሆን ተማሪዎች እንዴት የማንበብ ብልሃቶችን አቀናጅተው መጠቀም እንዳለባቸው ለማስተማር የሚያስችል ነው፡፡ በዚህ ሞዴል መምህር ፅሁፎችን ማንበብ፣ ብልሃቶችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ምሳሌ እያሳዩ ማስተማር እንዲችሉ ያስችላል፡፡ በሞዴሉ

ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በመጠቀም የተረዱትን ማንፀባረቅ እንዲችሉ እድል ለመስጠት የተመቸ ነው።

በዚህ ሞዴል ተማሪዎች በማንበብ ሂደት የውህድአሀዱን ትርጉም መገንዘብ ሲያቅታቸው ምን እንደሚያደርጉ እና ምን እንደሚያስቡ ችግሮችንስ ለማስወገድ ምን እርምጃ እንደወሰዱ ወዘተ መግለፅን ለማለማመድ ያስችላል። ይህ ዘዴ የአንባቢዎችን የማንበብ ሂደት በተመለከተ አጠቃላይ ሰፊ ምስል መስጠት የሚያስችል በመሆኑ የማንበብ ብልሃትን በመጠቀም ጊዜ ያለውን ሂደት ለመረዳት በሰፊው የሚያገለግል ፣ በማንበብ ተግባር የማይታይን ሂደት ለመሰብሰብ ወይም ድብቅ በሆነው አዕምሮ ውስጥ ያለውን ሂደት ለማግኘት ልክ እንደመስኮት የሚያገለግል በመሆኑ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። በመሆኑም የማንበብ ብልሃት ትምህርቱ ለሙከራ ቡድኖች በሚሰጥበት ወቅት እርስዎ መምህር ሞዴል በመሆን ለማስተማርያነት ከተመረጡት ምንባቦች የተወሰኑትን ለተማሪዎች በማንበብ እና የማንበብ ብልሃቶችን በመጠቀም ተማሪዎች እንዴት አንብበው መረዳት እንዳለባቸው የሚያለማምዱበት መንገድ እየተገበሩ ማሰብ ሞዴል ነው።

ለምሳሌ እርስዎ መምህር መረዳትን ለመቆጣጠር ሞዴል በመሆን ድምፅን ከፍ አድርገው ካነበቡላቸው በኋላ “ይህን አንቀፅ ተረድቸዋለሁ ስለዚህ መቀጠል እችላለሁ” ወይም “አንቀፁ ስላልገባኝ እንደገና አነበዋለሁ” እያሉ ይነግሩዋቸዋል። በዚህ መሰረት ተማሪዎችም በሚያነቡበት ወቅት “ስለርዕሱ የማውቀው ነገር አለ?” “የምንባቡ ዋና ሀሳብ ምንድን ነው?” “ያነበብኩትን ሀሳብ በራሴ መንገድ አሳጥሬ መፃፍ እችላለሁ?” እያሉ በመጠየቅ ወደተግባር እንዲሸጋገሩ የሚያለማምዱበት ሞዴል ነው።

ለ.አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ (Cognitive Academic Language learning Approch):- አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር ሞዴል አእምሮታዊ ትውረት ላይ መሰረት በማድረግ የተፈጠረ ነው። የሞዴሉ ዋነኛ አላማ ተማሪዎች በመማር ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ በማድረግ ይዘትን ማስተማር፣ አካዳሚያዊ ቋንቋን ማጎልበት እና ብልሃትን ማስተማር ናቸው። ሞዴሉ የሚከተለው መርህ መጀመሪያ ማስተማር፣ ጥያቄ መጠየቅ፣ ተማሪዎችን ማቀናጀት (በቡድን ማደራጀት)፣ ለመሳተፍ ፍቃደኛ ያልሆኑ ተማሪዎችን መለየት፣ እንዲሳተፉ እድል በመስጠት ምላሻቸውን ማዳመጥ እና ተገቢ ምጋቤ ምላሽ መስጠት ነው።

አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ መሰረታዊ የሚባሉ የትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተሎች አሉት። እነሱም ዝግጅት፣ አቅርቦት፣ልምምድ፣መገምገም፣ማስፋፋት እና

ምዘና ናቸው(መምህር ዝርዝሩን በዚሁ ፅሁፍ የማንበብ ብልሃት አቀራረብ ቅደም ተከተል የሚለውን ርእስ ይመልከቱ)፡፡

ሐ. ትግግዝ ሞዴል(Scaffolding)

ተማሪዎች የመማርም ሆነ የማንበብ ልምዳቸው እንዲጎለብት እና ራሳቸውን የቻሉ ውጤታማ አንባቢ እንዲሆኑ የመምህር ድጋፍ ወሳኝነት አለው፡፡ ይህም ሂደት መደጋገፍ (Scaffolding)ይባላል፡፡ እርስዎ መምህር ተማሪዎችን መርዳት ወይም መደገፍዎ የሚገለፀው ከተማሪዎች ጋር በመነጋገር ፣በመጠያየቅ እና ድምፅ አልባ በሆነ እንቅስቃሴ ተማሪዎችን በማበረታታት ተማሪዎች የተሰጣቸውን ተግባራት በብቃት እንዲተገብሩ ማድረግ ሲችሉ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች ርስበርስ እንዲረዳዱ በተለይ ጠንካራ ተማሪዎችን ደከም ካሉ ተማሪዎች ጋር በማጎዳኘት እንዲደጋገፉ ማድረግ ያለበት አቀራረብ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው ጠንካራ አንባቢ እንዲሆኑ የእርስዎ የመምህር ድጋፍ ቀስ በቀስ እየቀነሰ በመሄድ ሙሉ በሙሉ ሀላፊነትን ለተማሪዎች መስጠት ደረጃ የሚያደርስ መሆን አለበት፡፡

በዚህ ሂደት ሁለት ማእከላዊ ጉዳዮች ትኩረት ያገኛሉ፡፡ ይኸውም የእቀዳ እና የትግበራ ምእራፎች ናቸው (የማንበብ ብልሃትቶችን የአቀራረብ ቅደም ተከተል ይመልከቱ)፡፡ በእቀዳ ምዕራፍ እርስዎ መምህር ትኩረት የሚያደርጉት ተማሪዎችን ማለትም ፍላጎታቸው፣ ትኩረታቸው፣ መሻታቸው፣ ጥንካሬያቸው፣ ድክመታቸው፣ የቀደመ እውቀታቸው ወዘተ ነው፡፡ የመማሪያ ማስተማሪያ መፅሀፍትን በተመለከተ የምንባቦችን ርዕሶች እና ጭብጣቸው፣ ተነባቢነታቸው ወዘተ ፣የማንበብ አላማን በተመለከተ ተማሪዎች የቀረበውን ውህድ አሃድ ለምን አላማ ነው የሚያነቡት የሚሉትን ግምት ያስገባሉ፡፡ በትግበራ ምእራፍ የማንበብ ብልሃትን በቅድመ ማንበብ ፣በማንበብ እና በድህረ ማንበብ ጊዜ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ግምት ውስጥ መግባት እና ተግባራዊ ማድረግ ላይ ያተኩራል፡፡

እንደ Talibi (2004) አገላለፅ ሶስት አይነት ትግግዝ አለ፡፡ የኸውም የመምህር እና አቻ ትግግዝ፣ የውህድ አሀድ ትግግዝ እና የተግባር ትግግዝ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የመምህር እና አቻ ትግግዝን ተግባራዊ ለማድረግ እበራ የማንበብ ብልሃት ትግበራ (Collaborative)፣ ትክ (ሚና ለዋጭ) ማስተማር (Reseprocal Teaching) እና ትብብራዊ ማስተማር (Cooperative Learning) ተግባራዊ ለማድረግ የሚጋብዝ ነው፡፡ ሂደቱ ተማሪዎችን በአነስተኛ ቡድኖች በመከፋፈል እና በግል በተደጋጋሚ ልምምድ እንዲያደርጉ እድል የሚሰጥ በመሆኑ ተማሪ ተኮር የትምህርት አቀራረብን ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል፡፡

ሁለተኛው ውህድ አሃድ ትግግዝ ነው። ይህም የውህድ አሀድ ምክንያታዊ የመነበብ ክብደት፣ የማንበብ ብልሃትን የመጠቀም ትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት፣የክትትል ሁኔታ፣ የተማሪዎች ግራ መጋባት፣ የሚነበበው ፅሁፍ ጭብት እና ድጋፍ ሰጪ ዝርዝር ጉዳዮች እና ለግመታ የሚያመቹ የተለያዩ ፍንጭ ሰጪ አንቀፆች እና ስዕሎች እንዳሉት ግምት ማስገባት ነው።

ሶስተኛው የትግግዝ አይነት የተግባር ትግግዝ ነው። ይህም ተማሪዎች የተሰጣቸውን የማንበብ ተግባር በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያግዛቸው የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን ሽግግር ያደርጋሉ። የተግባር መመሳሰል ሽግግርን ይፈጥራል። ከአንድ ተግባር ወደ ሌላ ተግባር ሽግግር የመከሰት ሁኔታ እንዲጨምር የሚሰጠው አዲስ ተግባር ቀደም ሲል ከተሰጠው ተግባር ጋር መመሳሰል ሲኖር ነው። በዚህም ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው እየተገነዘቡ ይመጣሉ። ተማሪዎችም የቀረበው ውህድአሀድ እና የተሰጠው የማንበብ ተግባር በሚጠይቀው መሰረት የማንበብ ብልሃቶችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ እርስዎ መምህር ያበረታቷቸዋል።

3.2 የማንበብ ብልሃቶችን የአቀራረብ ቅደም ተከተል

በዚህ ጥናት የማንበብ ብልሃቶችን ለማስተማር ሶስት ሞዴሎችን በማቀናጀት የሚቀርብ መሆኑ ከላይ ተገልጿል። የማንበብ ብልሃት ትምህርት የሚጀምረው የማንበብ ብልሃት ምን እንደሆነ እና አይነቱ ምን ምን በመባል እንደሚታወቅ ግንዛቤ በማስጨበጥ ይሆናል። በዛውም ተማሪዎች በማንበብ ሂደት የትኞቹን የማንበብ ብልሃቶች ተጠቅመው እንደሚያውቁ በመጠየቅ የትምህርት ፍላጎታቸውን ማነሳሳት ያስፈልጋል። ትምህርቱ ትኩረት የሰጠበት የማንበብ ብልሃት ምንነቱን ተማሪዎች ከተገነዘቡ በኋላ በተግባር የተደገፈ ልምምድ እና ትግበራ ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው። ትምህርቱ በሚቀርብበት ጊዜ አሳታፊ እና ተማሪዎችን የጉዳዩ ባለቤት ያደረገ መሆን አለበት ። በዚህ ተግባር የእርስዎ የመምህር ሀላፊነት እና ብቃት ወሳኝ ነው።

የተማሪዎችን የማንበብ ብልሃት መገንዘብ ለማነሳሳት በማለም ትምህርቱ ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎችን በማቅረብ ይጀምራል። ይኸውም

1. የማንበብ ብልሃት የሚለውን ፅንሰ ሀሳባዊ ቃል ከዚህ ቀደም ሰምታችሁ (ተምራችሁ፣አንብባችሁ) ታውቃላችሁ ?
2. ስለማንበብ ብልሃት ሰምታችሁ (ተምራችሁ) የምታውቁ ከሆነ በማንበብ ሂደት የትኛውን የማንበብ ብልሃት ተጠቅማችሁ ታውቃላችሁ ?

3. የበለጠ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማንበብ የማንበብ ብልሃትን በተመለከተ መማር ትፈልጋላችሁ ? የሚሉ ናቸው

እነዚህ ግንዛቤን የማነሳሳት ጥያቄዎች ተማሪዎች ስለራሳቸው የማንበብ ብልሃት እንዲያስቡ ይረዳቸዋል። በዚህ መሰረት የተጀመረው ትምህርት በመቀጠል ተማሪዎች ብልሃቶች ላይ መሰረት ያደረገ ውይይት እንዲያደርጉ በማበረታታት በማንበብ ተግባር በየአነስተኛ ቡድን ተከፋፍለው በቅድመ ማንበብ ፣በማንበብ ጊዜ እና በድህረ ማንበብ በተግባር እንዲለማመዱ ማድረግ ተከታይ ተግባር ነው።

ከዚህ ተቀዳሚ መስተጋብራዊ የውይይት ተግባር ቀጥሎ ሁሉም ተሳታፊዎች የማንበብ ብልሃቶችን እንዲለዩ ክፍሉ በትንንሽ ቡድኖች ተከፍሎ በብልሃቶቹ ዙርያ ውይይት እንዲያደርጉ ይደረጋል። ውይይቱም የማንበብ ብልሃት ምን እንደሆነ (ብያኔ)፣ የማንበብ ብልሃቶችን ለመጠቀም ምን አይነት ሁኔታዎች አመቺ እንደሆኑ፣ የማንበብ ብልሃቶች ለምን እንደሚጠቅሙ እና የማንበብ ብልሃቶችን ተጠቅሞ ማንበብ እንዴት የአንብቦ መረዳት ችሎታን እንደሚያዳብር ይወያያሉ።

ቅድመማንበብ፡- ቅድመማንበብ ተማሪዎች የቀረበውን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት ርእሱን እና ንኡሳን ርእሶችን በማየት የሚተነብዩበት፣ ቅድመማንበብ የመወያያ ጥያቄዎች ቀርበው ከሆነ የቀደመ እውቀታቸውን በማነቃቃት በጥያቄዎቹ ዙርይ ከአቻዎቻቸው ጋር የሚወያዩበት ነው። በዚህ ወቅት ተማሪዎች ማድረግ የሚጠበቅባቸው አላማን መወሰን፣ ምንባቡን ማንበብ፣ የቀደመ እውቀታቸውን ማነቃቃት እና መተንበይ

የማንበብ ጊዜ ፡-ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የቀረበውን ምንባብ አንብበው ለመረዳት ጥረት የሚያደርጉበት ወሳኝ ምእራፍ ነው። በዚህ ወቅት ደግሞ (ደጋግሞ) ማንበብ የምንባቡን ሀሳብ በሚገባ መረዳት፣ መተንበይ እና ትንበያው ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ፣ አልገባ ያለን ሀሳብ መዝለል፣ በጥልቀት ማንበብ ፣ወደኋላ ተመልሶ ማንበብ፣ የቀደመ እውቀትን ከምንባቡ ሀሳብ ጋር ማጣመር(ማስተሳሰር)፣ግልፅ እና ድብቅ መረጃዎችን ለማግኘት መጣር፣ ማስታወሻ እየያዙ ማንበብ እና ቆም ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል።

ድህረማንበብ፡- ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የቀረበን ፅሁፍ አንብበው ከጨረሱ በኋላ ያነበቡትን ፅሁፍ ሀሳብ መረዳት አለመረዳታቸውን የሚያረጋግጡበት ነው። በዚህ ወቅት ተማሪዎች ማድረግ የሚጠበቅባቸው ሀሳቦችን ማስታወስ እና ጭምቀሀሳብ መፃፍ፣ አቀናብሮ መፃፍ (use a graphic orginizer)፣ ደግሞ ማንበብ፣ ትንታኔ

መስጠት እና አንዳች ድምዳሜ ላይ ለመድረስ፣ መወያየት እና ማላሽ መስጠት ወዘተ ናቸው።

በዚህ ትምህርት አቀራረብ ሂደት እርስዎ ምህር ሞዴል በመሆን ብልሃቶችን ያቀርባሉ ። በዚህም ተማሪዎች የራሳቸውን የማንበብ ብልሃት ግንዛቤ እንዲያስቡ እገዛ ያደርጋል። የእርስዎ የመምህር እርዳታ እና መተጋገዝ ቀስ በቀስ እየቀነሰ በዛ ያሉ ሙከራዎችን ተማሪዎቹ ራሳቸው በመተግበር የማንበብ ብልሃቶችን በመለማመድ ነፃ ሆነው በራሳቸው መንገድ እንዲተገብሩ ይደረጋል።

ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በሚገባ መጠቀማቸውን ለመገንዘብ ራሳቸውን ይገመግማሉ። ሌሎች ፅሁፎችን ሲያነቡም የማንበብ ብልሃቶችን በማሸጋገር ይጠቀማሉ። ተማሪዎች የቀረበላቸውን ፅሁፍ በሚያነቡበት ሂደት የእርስዎ የመምህር ድጋፍ ቀስ በቀስ እየቀነሰ ተማሪዎች በእርግጠኝነት ትኩረት የተሰጠባቸውን ብልሃቶች በራሳቸው መንገድ በተደጋጋሚ በመለማመድ እና በመጠቀም በነፃነት የማንበብ ብቃትን ማጎልበት ወይም ራስ መር በሆነ መንገድ ማንበብ የማንበብ ብልሃት ተኮር ትምህርት የመጨረሻ ግብ ነው ።

ውጤታማ በሆነ መንገድ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ለማስተማር በክፍል ውስጥ ተግባራዊ መደረግ ያለባቸው ቅደም ተከተሎች ዝግጅት፣ ሞዴል በመሆን አቅርቦት፣ ልምምድ (በተግቦር መሞከር)፣ ተማሪዎች ራሳቸውን እንዲገመግሙ ማድረግ፣ ማስፋፋት ወይም ከአንድ ሁኔታ ወደሌላ ሁኔታ ማሸጋገር እና ግምገማ ናቸው (Zhang 2012:1070):: እነዚህ ሂደቶች በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በሚሆኑበት ጊዜ ትኩረት የሚሹ ክንውኖች የሚከተሉት ናቸው (Medina 2011፣ Zhang 2012፣ Bimmle et al. 2001፣ Carrell 2006)።

- የማንበብ ብልሃት ምንነትን እና አይነታቸውን ግልፅ በሆነ አቀራረብ ማስረዳት፣
- የተለያዩ ፅሁፎችን በማንበብ ሂደት የማንበብ ብልሃቶችን መጠቀም ምን ያህል ጠቀሜታ እንዳለው ማስረዳት፣
- ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን እንዴት በተግባር መጠቀም እንደሚችሉ መምህር ሞዴል በመሆን (እየተገበሩ) ማሳየት፣
- ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን መቼ እና የት መጠቀም እንዳለባቸው ማሳየት፣ መምራት፣ ማገዝ፣
- ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን በትክክል መጠቀም አለመጠቀማቸውን መከታተል፣ ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም አለመጠቀማቸውን ለማረጋገጥ ራሳቸውን እንዲገመግሙ ማበረታታት፣

- ተማሪዎች በተማሩት መሰረት የማንበብ ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም አለመጠቀማቸውን መመዘን ናቸው፡፡

ይህ የትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተል ከአእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ (Cognitive Academic Language Learning Approch/CALLA) አንፃር ሲታይተደራጅቶ ተቀምጧል፡፡ አቀራረቡ የጎለበተው በአእምሯዊ(ግንዛቤያዊ) ትውረት ላይ ተመስርቶ ነው Chamot (2005)፣ O'Malley and Chamot (1990)፡፡ ይህ አእምሮታዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ ሞዴል ስድስት ቅደም ተከተል ያለው ሲሆን በሚከተለው መንገድ ይተገበራል፡፡

ከታች በሰንጠረዥ የተቀመጠውን ቅደም ተከተላዊ የማንበብ ብልሃት ትምህርት አቀራረብ ትግበራ መነሻ ሲሆን ቅደም ተከተሉ የግድ በቀረበው መንገብ ብቻ ላይሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም እርስዎ መምህር እና ተማሪዎችዎ በሚመቻችሁ መንገድ አስተካክላችሁ ወይም እንዳለ መጠቀም ትችላላችሁ፡፡

ተ.ቁ	ቅደም ተከተል	ተግባራት
1	ዝግጅት	ተማሪዎች አሁን ያላቸው የተለያየ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤን መለየት ልየታው ፡- - የማንበብ ብልሃቶች ላይ የተመሰረተ ጥያቄ በማቅረብ ለትምህርት ማነሳሳት ለምሳሌ:- የማንበብ ብልሃት ምንድን ነው? ብሎ መጠየቅ - በአነስተኛ ቡድን ሆነው ያለፈን ነገር የማስታወስ ተግባር እንዲያከናውኑ ማደረግ(ከዚህ በፊት እንዴት እንደሚያነቡ ፣ምን አይነት ብልሃት ይጠቀሙ እንደነበር ወዘተ እንዲወያዩ ማድረግ) - እየተናገሩ በማሰብ ሞዴል ተማሪዎች አነስተኛ ቡድኖች መስርተው ያሰቡትን እንዲያንፀባርቁ ማድረግ - እየተናገሩ በማሰብ ውይይቱ እንዲቀጥል ማድረግ
2	አቅርቦት	የተማሪዎችን የማንበብ ብልሃት እውቀት ማጎልበት ትግበራው፡- - የማንበብ ብልሃትን ለመጠቀም ምክንያታዊ እንዲሆኑ ማስረዳት - ብልሃቶችን በየስማቸው መጥራትና(ብያኔ መስጠት) ማስረዳት - የማንበብ ብልሃቶች አይነታቸውን እና ጠቀሜታቸውን ማስረዳት - ብልሃቶችን ለማስተማር ሞዴል መሆን
3	ልምምድ	ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶችን የመጠቀም ክህሎታቸውን ማጎልበት ትግበራው፡- - ትብብራዊ የመማር ተግባራትን ተግባራዊ ማድረግ - ችግሮችን ለመፍታት በነፃ ማሰብ (እየተናገሩ ማሰብ) - የአቻ መማርን መተግበር - የቡድን ውይይት - ራሳቸውን ችለው ብልሃቶችን እንዲጠቀሙ ማበረታታት
4	ግምገማ	ከልምምድ በኋላ ተማሪዎች የራሳቸውን የማንበብ ብልሃት የሚገመግሙበትን ልምድ እንዲያዳብሩ ማድረግ ትግበራው፡-

		- ከተሰጠው ተግባር በኋላ የተጠቀሙበትን ብልሃቶች እንዲፅፉ ማድረግ - በተጠቀሙበት ብልሃቶች ዙርያ በቡድን እንዲጠያየቁ እና እንዲወያዩ ማድረግ - በብልሃት አጠቃቀም ዙርያ ከመምህር ጋር የተደረገውን ውይይት በማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ
5	ማስፋፋት	ተማሪዎች ብልሃቶችን ከመጀመርያ ቋንቋ ወደሁለተኛ ቋንቋ ወይም በተቃራኒው (ከአንድ ተግባር ወደሌላ ተግባር) እያሸጋገሩ እንዲጠቀሙ ማድረግ ትግበራው፡- - የልዕለአዕምሮታዊ ብልሃት አጠቃቀም እውቀታቸው እንዲጨምር ማበረታታት - የቀደመ እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ ማድረግ - በተማሪዎች ባህላዊ ዳራ ላይ መሰረት በማድረግ የማንበብ ብልሃት ትግበራ ያለበት ተደጋጋሚ የክፍል እና የቤት ስራ መስጠት - ጠቃሚ(የተሻሉ) ብልሃቶችን እንዲጠቀሙ ማበረታታት - ብልሃቶችን አቀናጅተው እንዲጠቀሙ ማድረግ
	ምዘና	የተማሪዎችን የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም እና አጠቃቀማቸው በአንብቦ መረዳታቸው ላይ የፈጠረውን ውጤት መገምገም

O'Malley and Chamot (1990፡158)

እንደ O'Malley and Chamot (1994b:66) አቀራረብ የማንበብ ብልሃትን በማስተማር ወቅት የመምህሩ እና የተማሪው ሚና የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ምስል አንድ፡-አእምሮታዊአካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ ሞዴል



O'Mallye and Chamot (1994b:66)

መመህር እየተገበሩ ማሰብ፣ አእምሯዊ አካዳሚያዊ ቋንቋ መማር አቀራረብ እና ትግግዘ ሞዴልን በማቀናጀት የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን በግልፅ ለማስተማር የሚያስችል የትምህርት አቀራረብ ያስፈልጋል። ይህንን ለማከናወን የሚከተለው የትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተል በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ ተግባራዊ የሚሆን ነው፡ የትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተሉ በአንድ ክፍለ ጊዜ የሚከናወን ሳይሆን እንደትምህርቱ ይዘት በሚቀረፅ የእለት ትምህርት እቅድ መሰረት የሚተገበር ነው። የትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተሉን እርስዎ መምህር እና ተማሪዎችዎ አሻሽለው ወይም እንዳለ ልትጠቀሙበት የሚያስችል ነው።

የትምህርት አቀራረቡ መነሻ እና መድረሻ ግቡ የሚከተለውን ይመስላል፡-

ክፍል አራት

የተማሪዎችን አዲስ ስሜት ማረጋጋት (Managing Resistance)

ተማሪዎች በተለያየ ምክንያት የማንበብ ብሃትን መማር ጥቅም የለውም ብለው ሊያስቡ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ተማሪዎች በዛ ያሉ የማንበብ ብልሃቶችን መማር አይጠቅምም ብለው ሊያስቡ ይችላሉ፣ሌሎች ደግሞ ብልሃቶችን አቀናጅቶ መማር አያስፈልግም የሚል ሀሳብ ሊኖራቸው ይችላል ፣ የማንበብ ብልሃቶችን ለረጅም ጊዜ መማር አይገባም ወይም በአጠቃላይ የማንበብ ብልሃትን መማር አያስፈልግም የሚሉ ተማሪዎች ሊገጥሙ ይችላሉ፡፡

የማንበብ ብልሃት የተለያዩ ፅሁፎችን አንብቦ ለመረዳት ወሳኝ መሆኑን የተለያዩ ምሳሌዎች በማቅረብ እና ራስን ሞዴል በማድረግ በሚገባ ማስተማር ተማሪዎች ፅንሰ ሀሳቡን በቀላሉ እንዲረዱ ለማድረግ ያስችላል፡፡ እርስዎ መምህር ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ በምርምር አቅራቢው የሚሰጥዎትን ስልጠና በሚገባ መከታተል እና በማንበብ ብልሃት ዙርያ በተለያዩ ምሁራን የተፃፉ ፅሁፎችን ማንበብ ይጠበቅብዎታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የማንበብ ብልሃትን በተመለከተ ለተማሪዎች በዝርዝር ከማቅረቡ በፊት ተማሪዎች የማንበብ ብልሃት ምን ጥቅም እንዳለው እንዲገነዘቡ ጊዜ ሰጥቶ ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡ በዚህም የእርስዎ የመምህር እውቀት በተማሪዎች ዘንድ ሊፈጠር የሚችለውን መደናገር በቀላሉ ሊያስቀረው የሚችል በመሆኑ ድርሻዎ ከፍተኛ ነው፡፡

ማሳሰብያ፡- የማንበብ ብልሃት ስልጠናው ለእርስዎ ለመምህር ተሰጥቶ እንዳበቃ ወዲያውኑ ለተማሪዎች ትምህርቱ መቅረብ ይጀምራል፡፡ በዚህ ወቅት የምርምር አቅራቢው ትምህርቱ በሚሰጥበት ክፍል ውስጥ በመገኘት የክትትል ቼክ ሊስት በመታገዝ ምልከታ (Observation) በማካሄድ የትምህርት አቀራረቡ በተገቢው መንገድ የሚቀርብ መሆኑን ሊከታተል ይችላል፡፡ ከምልከታው በኋላም ከእርስዎ ከመምህር ጋር በትምህርት አሰጣጡ ዙርያ ውይይት በማድረግ የትምህርት አቀራረቡ የበለጠ እንዲጎለብት ጥረት ይደለጋል፡፡

አባሪ አራት

በምርምር ስራው የማንበብ ብልሃት ትምህርት ለሚከታተሉ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የተዘጋጀ የትምህርት (የስልጠና) ቅፅ

ተማሪዎች! ይህ የትምህርት (የስልጠና) ቅፅ የተዘጋጀበት ምክንያት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፤የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፤ተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን በማስተማር በተባለው የትምህርት መርሀ ግብር የዶክትሬት ፍልስፍና (PhD) የምርምር ፅሁፍ ለማዘጋጀት ታስቦ የቀረበ ነው። የምርምሩ ርዕስም “የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ብቃትን (ውጤትን) ለማጎልበት እና ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ያለው አስተዋፆ” የሚል ነው። ጥናቱ ጅግጅጋ ከተማ 9ኛ ክፍል ሶማልኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች ተተኳሪአድርጓል። በዚህ የምርምር ስራ በፈቃደኝነት ተሳታፊ የሆናችሁ እናንተ የጥንቱ ተሳታፊ ተማሪዎችየተለያዩ ፅሁፎችን በተሻለ ብቃት አንብባችሁ ለመረዳት እንድትችሉ የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን እንድትማሩ ይደረጋል። በዚህ የትምህርት ሂደት የማንበብ ብልሃት ምንነትን ፣አይነትን፣ ጠቀሜታን በሚገባ ተገንዝባችሁ የማንበብ ብልሃቶችን መቼ፣የት እና እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባችሁ በመማር ብልሃቶችን በተግባር እንድትጠቀሙባቸው ትበረታታላችሁ።

ቋንቋን በመማር ሂደት አንብቦ መረዳት ወሳኝ ጉዳይ ነው። እናንተ ተማሪዎች ማንኛውንም ፅሁፍ በምታነቡበት ወቅት የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን አቀናጅታችሁ በመጠቀም የቀረበውን ፅሁፍ አንብባችሁ ለመረዳት መሞከር አለባችሁ። የማንበብ ብልሃት የሚለው ሙያዊ ቃል የሚገልፀው ተማሪዎች አንድን የቀረበ ፅሁፍ አንብባችሁ ለመረዳት ተግባራዊ የምታደርጉት እቅድ፣ቴክኒክ ወይም ቅደም ተከተል ሲሆን የሚነበበው ፅሁፍ ባልገባችሁ ጊዜ ያልገባችሁን ሀሳብ (በቃል፣በሀረግ፣በአረፍተነገር ወይም በአንቀፅ ደረጃ) ለመረዳት እንዳትችሉ እንቅፋት የሆነባችሁን ችግር በማስወገድ የምታነቡት ስሜት እንዲሰጣችሁ የምታደርጉበት አእምሯዊ ሂደት ነው።

የማንበብ ብልሃትን መማር አንድ ሰው ቤት ለመስራት ሲያስብ ቤቱን ለመስራት የሚያስፈልጉ ተገቢ(ትክክለኛ)መሳርያዎችን መምረጥ እና ቤቱ እንዴት እንደሚሰራ እቅድ እንደመንደፍ አይነት በጣም ጠቃሚ ነው። ቤት የራሱ የሆነ መሰረት ግድግዳ እና ጣራ እንዳለው ሁሉ የቀረበ አንድ ፅሁፍም የራሱ ቅርፅ፣ ይዘት እና እነዚህን ጠቃሚ ጉዳዮች

ለማዋቀር የሚያስችሉ ቃላት፣ ሀረጎች፣አረፍተ ነገሮች እና አንቀፆች አሉት። ቤት በመስራት ሂደት ቤቱን ለመስራት የሚገለግሉ ግብአቶች በመሰብሰብ በታቀደው መሰረት ቅድምያ፣ቀጣይ ወዘተ ምን መደረግ እንዳለበት እያሰቡ መስራት ጥሩ ቤት መገንባት እንደሚያስችል ሁሉ የቀረበን ፅሁፍ በማንበብ ሂደት ቅድምያ ምን ማድረግ እንደሚያስፈልግ በቀጣይነትስ መከናወን የሚገባው ምን እንደሆነ ጠልቆ በማሰብ እና በመቆጣጠር የማንበብ ተግባሩን ማከናወን ያስፈልጋል። እንዲህ ባለ መንገድ የማንበብ ብልሃቶችን ተግባራዊ በማድረግ ማንበብ የቀረበን ፅሁፍ በቀላሉ አንብቦ ለመረዳት ያስችላል።

አንድን ፅሁፍ በምታነቡበት ወቅት ራሳችሁን መጠየቅ ያለባችሁ መሰረታሚ ጥያቄዎች አሉ። እነሱም

- የቀረበውን ፅሁፍ እንዴት ማንበብ አለብኝ ?
- የቀረበውን ፅሁፍ አንብቤ ለመረዳት ምን አይነት ብልሃት መጠቀም አለብኝ ?
- የተጠቀምኩባቸው ብልሃቶች የቀረበውን ፅሁፍ አንብቤ ለመረዳት ጠቅመውኛል ወይ?
- የቀረበውን ፅሁፍ አንብቤ ተረድቻለሁ ወይ ?
- የቀረበውን ፅሁፍ አንብቤ ለመረዳት ምን ያላደረኩት ነገር አለ? የሚሉ ናቸው።

የማንበብ ብልሃት ጠቀሜታ

የማንበብ ብልሃት የቀረበን አንድ ፅሁፍ በማንበብ ሂደት በፅሁፍ (text) ውስጥ አጠቃላይ እውቀት እና የተለየ ጥልቅ ወይም ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ዋናውን ሀሳብ (ጭብጥ) ለይቶ ለማውጣት፣ ለመማር፣ ለማስታወስ፣ ደስታን ለመፍጠር፣ ጭምቀሀሳብ ለመፃፍ እና ምርምር ለመስራት ያገለግላል (Cubukcu 2007፡ McNamare 2007)።

የማንበብ ብልሃት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች እንዳሉት የተለያዩ ምሁራን ዘርዝረው አስቀምጠዋል። ምሁራኑ በዋናነት የጠቀሱዋቸው ጠቀሜታዎች ተማሪዎች የበለጠ ራሳቸውን የቻሉ (ራስ መር)አንባቢዎች እንዲሆኑ፣ ነፃ እና ለትምህርት ኃላፊነት የሚወስዱ ጠንካራ አንባቢዎች እንዲሆኑ፣ የማንበብ ብልሃቶችን በሚገባ በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ፣ የሚያነቡትን የሚገነዘቡ (የሚረዱ) በመሆናቸው ሁል ጊዜ ለመማር የተነሳሱ ንቁ እንዲሆኑ፣ የትምህርት መነሳሳት ያላቸው ተማሪዎች እንዲሆኑ ያደርጋል። ተማሪዎች በንቃት የመማር ማስተማር ሒደቱን የሚከታተሉ በመሆናቸው ተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን ተግባራዊ ለማድረግ አመቺ

ሁኔታን ይፈጥራል። የተለያዩ የምርምር ስራዎች እንደሚያመላክቱት ተማሪዎች ተገቢውን የማንበብ ብልሃት ትምህርት በሚገባ ሲያገኙ እና እነዚህን የማንበብ ብልሃቶች በአግባቡ ሲጠቀሙ የመረዳት ብቃታቸው ብቻ ሳይሆን የሚጨምረው ብዙ ቃላትን የማወቅ እና የመጠቀም፣ በቃላት ውስጥ ያሉትን ምልክቶች የመተርጎም፣ በማበብ ሒደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል አቅም ይፈጥራሉ።

የማንበብ ብልሃት አይነቶች

ለትምህርት የቀረቡ የማንበብ ብልሃት አይነቶች

1. *መተንበይ*(Prediction)፡-አንድ የቀረበን ፅሁፍ በማንበብ ሂደት ርዕሱን እና ንዑሳን ርዕሶችን በማንበብ የእንዳንዱን አንቀፅ የመጀመሪያ አረፍተ ነገር በማንበብ ፅሁፉ የያዘውን ሀሳብ ለመረዳት መተንበይ ነው። ይህ ብልሃት ጠልቆ ማሰብን ይፈልጋል። ለማንበብ የቀረበው ፅሁፍ በመማሪያ ማስተማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ከሆነ ቅድመ ማንበብ የውይይት ጥያቄዎችን በማጤን እና በጋራ በመወያየት ምንባቡ የያዘው ሀሳብ ምን እንደሆነ መተንበይ ያስፈልጋል። የቀረበው ምንባብ ከተለያዩ ፅሁፎች የተወሰደ ከሆነ ደግሞ ርዕሱን በማየት እና ጥያቄዎችን በማንሳት መተንበይ ተገቢ ነው።

ለምሳሌ፡- የሚከተለውን አጭር ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት ርእሱን በመመልከት ተንብዩ። በመቀጠልም ፅሁፉን በማንበብ የተነበያችሁት እና ፅሁፉ የያዘው ሀሳብ መገናኘታቸውን አስተውሉ

የፖም ጥቅም

አትክልት እና ፍራፍሬ አዘውትሮ መመገብ ከፍተኛ የጤና ጥቅም እንዳለው ተመራማሪዎች ይናገራሉ፤ይመክራሉ። ከፍራፍሬ አይነት አንዱ የሆነው ፖም የተለያዩ ጥቅሞች አሉት። ዋና ዋና የሚባሉት ጠቀሜታዎች የሚከተሉት ናቸው። ፖም አልዛሂመርን ይዋጋል። ይህ በእድሜ የገፉ ሰዎች በህይወታቸው ሙሉ የሚያውቁትን ነገር እንዲረሱ የሚያደርግ የአንጎል በሽታ ነው። በሽታው የያዛቸው ሰዎች ከጥቂት ደቂቃ በፊት ያደረጉትን ነገር እንዲሁም እናታቸውን ጭምር ሊረሱ ይችላሉ።

ፖም የአንጎል ሴሎች እንዳያረጁ የሚያደርግ ከርስቲን (quercetin) የተባለ ኃይለኛ ፀረ-ኦክሲደንት (ኦክሲጅን ከሌላ ንጥረ ነገር ሲዋሃድ የሚፈጠር ቅሪት ወይም ዝቃጭ)ኬሚካል አለው። ይህ ኬሚካል በአይጦች ላይ ተሞክሮ ጥሩ ውጤት ስላስገኘ ሳይንቲስቶች ለሰው ልጅም ሳይጠቅም አይቀርም የሚል እምነት አላቸው። ሌላው ጥቅም የደንዳኔ ካንሰርን

ይከላከላል፡፡ በቅርቡ በጀርመን የተደረገ አንድ ጥናት ተፈጥሯዊው የፖም አሰር(Fliber) በደንዳኔ ውስጥ ሲብላላ ወይም ፈርመንት ሲደረግ የካንሰር ሴሎች እንዳይፈጠሩ የሚያደርጉ ኬሚካሎች እንደሚፈጥሩ አመልክቷል፡፡ ሌሎች ጥናቶች ደግሞ በፖም ውስጥ የሚገኘው ፕሮካያሚዲያንስ (Procayamidins) የተባለ ፀረ-ኦክሲደንት የካንሰር ሴሎችን የሚገድሉ በርከት ያሉ ሴሎች እንዲነቃቁ እንደሚደርግ አረጋግጠዋል፡፡

ፖም የደም ስኳር እንዳይዋዥቅም ያደርጋል፡፡ ፖም በሚሚ አሰር የተሞላ በመሆኑ የምግብ ስልቀጣና ጉሉኮስ ከደም ጋር የሚቀላቀልበትን ፍጥነት ያዘገያል፡፡ አንድ የተመራማሪዎች ቡድን በቀን ቢያንስ አንድ ፖም የሚበሉ ሴቶች ከማይበሉት ጋር ሲነፃፀር በስኳር ህመም የመያዝ ስጋታቸው 28 በመቶ መቀነሱን ደርሶበታል፡፡ ፖም የድድን ጤና ከፍ ያደርጋል፡፡ ፍሬው ተፈጥሯዊ የድድ ማፅጃ መሆኑ ከታወቀ ብዙ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ፖም መብላት ድድ ማፅዳት ባይሆንም ፖም ገምጦ ማኘክ ድድ እንዲነቃቃ ያደርጋል፡፡ ጣፋጭነቱ ደግሞ የምራቅ ምርት እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ ይህ ሁኔታም በአፍ ውስጥ የሚኖሩትን ባክቴሪያዎች መጠን ዝቅ በማድረግ የጥርስ መበስበስ እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡ ፖም ሌሎችም በርካታ ጠቀሜታዎች ያሉት በመሆኑ አዘውትሮ መመገብ እንደሚያስፈልግ ይመከራል፡፡

ምንጭ፡- አዲስ አድማስ ጥር 17/2006 ተሻሽሎ የተወሰደ

2. **ደግሞ (ደጋግሞ) ማንበብ(Repetition)**፡-አንድን የተሰጠ ፅሁፍ በምታነቡበት ጊዜ ያልገባችሁ ሀሳብ ካለ ወደኋላ በመመለስ የተወሰነውን የምንባብ ክፍል ለምሳሌ ቃላትን ሀረጎችን አንቀፆችን ወይም ፅሁፉን በሙሉ ማንበብ ነው፡፡

3.**ዋናውን ሀሳብ ፈጥኖ ማግኘት**(Getting the idea quickly) ፡-በቀረበ አንድ ፅሁፍ ውስጥ ያለውን ዋና ሀሳብ ፈጥኖ ለማግኘት ፈጠን ብሎ ላይ ላዩን ከሚነበብ የአሰሳ ንባብ(Skimming)እና ከምንባቡ ውስጥ የተለየ(የተነጠለ)ሀሳብ ለማግኘት ከሚደረግ የምልከታ ንባብ (Scanning) ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ በዚህ ወቅት ከምንባቡ ጋር የቀረቡ ጥያቄዎች ካሉ ጥያቄዎችን አስቀድሞ መመልከት(Preview)ይጠቅማል፡፡ ስለካንሰር በሽታ የሚያብራራ አንድ ምንባብ ቢቀርብ ምንባቡን ተከትሎ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማቅረብ ዋናውን ሀሳብ ፈጥናችሁ እንድታገኙ ማበረታታት ይቻላል፡፡

ለምሳሌ ሀ፡- በዚህ ምንባብ ውስጥ የተጠቀሱት ሶስት መሰረታዊ ነጥቦች ምን ምን ናቸው?

(ለአሰሳ ንባብ የሚቀርቡ ጥያቄዎች)

ምሳሌ ለ1፡-በምንባቡ ውስጥ የጡት ካንሰር በሽታ ምልክቶች ተብለው የተጠቀሱት ምን ምን ናቸው?(ለምልከታ ንባብ የሚቀርቡ ጥያቄዎች)

ምሳሌ ለ2፡-የጡት ካንሰር በሽታን ለመከላከል ምን መደረግ አለበት?(ለምልከታ ንባብ የሚቀርቡ ጥያቄዎች)

4. ***መረጃን ፈልፍሎ በማውጣት ምክንያት ላይ የተመሰረተ ድምዳሜ ላይ መድረስ*** (Inference):- በቀረበ አንድ ፅሁፍ ውስጥ ዋና ሀሳብ እና ዝርዝር ሀሳቦች ይኖራሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እነዚህን ጠቃሚ ሀሳቦች ለማስረዳት እና አጉልቶ ለማሳየት የሚያስችሉ ማብራርያዎችም ይገኛሉ፡፡ እናንተ ተማሪዎች አንድን የቀረበ ፅሁፍ በምታነቡበት ወቅት ጠቃሚ መረጃዎችን (ለምሳሌ አንደኛ፣ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ወዘተ ተብለው ተዘረዘሩ) ፈልፍላችሁ እንድታወጡ የሚጠቅም ብልሃት ነው፡፡ መረጃን ፈልፍሎ ማውጣት በቀረበ መረጃ የአዳዲስ ጉዳዮችን ትርጉም መገመት፣ ውፅአትን(output) መተንበይ ወይም የጎደለ(ያልተሟላ)መረጃን ማሟላትም ነው፡፡

ከላይ በቀረበው ማብራርያ መሰረት የሚከተለው ምንባብ የያዘውን ዋና ሀሳብ ፈጥናችሁ በማውጣት በሀሳቡ ዙርያ ከመምህራችሁ እና ከተማሪዎች ጋር ተወያዩ፡፡

መልእክትን በኮሜዲ

ኮሚዲ ተመልካችን የማያስጨንቅ ብሩህ ድባብ የሰፈነበት ፈገግ እያሰኘ ወይም በሳቅ እያንከተከተ ቁም ነገርን የሚያስጨብጥ የተውኔት አይነት ነው፡፡ እንደትራጀዲ ተውኔት ነፍስን አስጨንቆ ስሜትን በፍርሀት አሸብሮ ስጋት ላይ አይጥልም፡፡ መፍትሄያቸው በቅርቡ በማይታወቁ አሳሳቢ ጉዳዮች ላይ ስለሚያተኩር አስጨናቂነትና አሰቃቂነት አይኖረውም፡፡ ገጸባህሪያትም ከማይችሉት ሀይል ጋር በጠበቀና በከረረ ሁኔታ ውስጥ ገብተው መከራቸውን አያዩም፡፡

የኮሜዲ ተውኔት ዋነኛ ትኩረት በአንድ በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ በሚገኝ ማህበረሰብ ባህል፣ ወግ እና ልማድ እንዲሁም እሴቶች ላይ ነው፡፡ እነዚህ ደግሞ ብዙ ጊዜ ቋሚነት የሌላቸው ለተወሰነ ጊዜ አገልግለው የማህበረሰቡን እድገት እየተከተሉ የሚሻገሩና የሚለወጡ በመሆናቸው ኮሜዲ ከትራጀዲ ጋር ሲነጻጸር ዘላቂነቱ ወይም ዘመንን ዘሎ ተሰሚነቱ ዝቅ ያለ ነው፡፡ ነባሩ በአዲሱ የሚተካ በመሆኑ እና የአንዱ ማህበረሰብ ባህል ከሌላው የሚለይ በመሆኑ ተውኔቱን ዘመን አዘልሎ የወትሮውን አይነት ተቀባይነት ማግኘት ያዳግታል፡፡ ተአማኒነቱም የጎላ አይሆንም፡፡ ከዚህም የተነሳ እያንዳንዱ ዘመን የራሱ ኮሜዲ ይኖረዋል

ማለት ይቻላል፡፡ “ባንድ ትውልድ ያሉ ስነምግባሮች በሁለተኛው ሊሻሻሉ በሶስተኛው ደግሞ ሊረሱ ይችላሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ኮሜዲ በጣም ተለዋዋጭ የተውኔት አይነት ነው፡፡”

የዚህ ተውኔት ትልም አብዛኛውን ጊዜ እንደትራጀዲ የጠበቀ አይሆንም፡፡ በድርጊቶች የጠበቀ መከታተል ላይ ሳይሆን ድንገት በሚታዩ የገጸባህርያት አንድነት መምጣት እና በተግባሮቻቸው ላይ ያተኩራል፡፡ ገጸባህርያቱም ቀርጠው የተነሱበትን አላማ እንደትራጀዲ ገጸባህርያት እስከመጨረሻው እግብ ለማድረስ አይጨነቁም፡፡ ሲያሳስባቸው የቆየን ጉዳይ ወደኋላ እንደዋዛ ይተውታል፡፡

በኮሜዲ ተውኔት የሚገኙት ገጸባህርያት በትራጀዲ እንደሚገኙት በደረጃቸውም ሆነ በአስተሳሰባቸው የላቁ የረቀቁ አይደሉም፡፡ ከቀረው የማህበረሰቡ ክፍል ተነጥለው ከፍ ባለ ደረጃ ላይ የተቀመጡ ሀያል እና አዋቂ ገጸባህርያት የሚባሉ አይደሉም፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ እለት በእለት የሚታዩ ዘወትራዊ ሰዎች ናቸው፡፡ አቀንቃኝ ገጸባህሪውም በጀግንነቱ ወይም በአሸናፊነቱ የሚደነቅ በተሸናፊነቱ የሚታዘንለት፣ ምን ያጋጥመው ይሆን እያለ ተመልካቹ የሚጨነቅለት የሚጠበብለት ስሜቱ በሽብር እስኪዋጥ ድረስ የሚራራለት ሆኖ አይሳልም፡፡

በቋንቋ ረገድ ኮሜዲ እንደትራጀዲ የታመቀና የናረ ቋንቋ የለውም፡፡ ግልጽ እና ሁኔታውን በቀላሉ ለአንባቢ አብራርቶ የማሳየት አቅም ባለው ቋንቋ ነው እሚጻፈው፡፡ የቋንቋውም ግልጽነትና ቀላልነት በቀላሉ ሳቅን ለማጫር ያስችለዋል፡፡ በቋንቋ ርቀት ምክንያት ተመልካቹ ፊቱን አጨፍግጎ ገጸባህሪው ምን ማለቱ ይሆን እያለ በብሩህ ስሜት የሚጠባበቅበት አይደለም፡፡ አናዳጅና አስቆጪ ሁኔታዎች እንኳን ቢሆኑ ክብደት ባለውና አጥንት ድረስ ዘልቆ በሚሰማ ንግግር ንረው አይቀርቡም፡፡ የኮሜዲ ቋንቋ ግልጽና ቀላል ነው ሲባል ግን ፍጹም ተራ ነው ማለት አለመሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡ የገላጭነት ሀይል ባላቸው ብሩህና ምርጥ በሆኑ ቃላት መጻፍ አለበት፡፡

ምንጭ፡- ዘሪሁን አስፋው፣ የስነፅሁፍ መሰረታውያን፣(1996፡287)

5.**ማስታወሻ መያዝ**(Taking note) ፡-በማንበብ ሂደት በጣም ጠቃሚ የሆነ የማንበብ ብልሃት ነው፡፡ አንድ ፅሁፍ በሚነበብበት ወቅት በጣም ጠቃሚ የሆኑ ሀሳቦችን ለማስታወስ እንዲያስችል ቃላትን፣ሀረጎችን እና ፅንሰ ሀሳቦችን በራስ መንገድ አሳጥሮ ማስታወሻ መያዝ ነው፡፡ ይኸውም በሚነበበው ፅሁፍ ውስጥ ያለውን ቁልፍ መረጃ ለመያዝ በቃላት ደረጃ እቃ ለመግዛት ዝርዝር ማዘጋጀት በሚመስል መንገድ መፃፍ፣

በግራፍ መልክ የተነበበውን ሀሳብ ለማስታወስ በሚያስችል መልኩ ግራፍ ማዘጋጀት እንዲሁም በአማርኛ ፊደል "ፐ"በሚመስል ቅርፅ ማስታወሻ ሊያዝ ይችላል

ለምሳሌ፡-የቡና ተክል እና ክብካቤው

-አስፈላጊ ነገሮች	-መወገድ ያለባቸውነገሮች
-ችግኝ	-አረም
-የተዘጋጀ መሬት	-ተባይ
-ውሃ	-የሰው እና የእንስሳት
- ማዳበሪያ	አላስፈላጊ ንክኪ
-የዘወትር ክትትል	

6. ዋናውን ሀሳብ በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ(ጭምቀ ሀሳብ)(Summarizing)፡-አንድን ፅሁፍ በማንበብየተገኘውን አዳዲስ መረጃ አእምሯዊ፣ቃላዊ ወይም ፅሁፋዊ በሆነ መንገድ አሳጥሮ ማቅረብ የሚያስችል ጠቃሚ ብልሃት ነው፡፡ ጭምቀ ሀሳብ ማስታወሻ ከመያዝ የበለጠ ጠቃሚ ቢሆንም ለመፃፍ ከባድ ሊሆን ይችላል፡፡ ጭምቀ ሀሳብ ሲፃፍ ዋናውን ፅሁፍ በማንበብ ፅሁፉ የያዘውን ዋና ዋና መረጃ በራስ አገላለፅ አሳጥሮ መፃፍ ነው፡፡

ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር የቀረበንፅ ፅሁፍ አንብባችሁ በመረዳት ዋናውን ሀሳብ በራሳቸው መንደግ አሳጥራችሁ ጭምቀሀሳብ በምትፅፉበት ጊዜ ማከናወን ያለባችሁ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

- የቀረበውን ፅሁፍ ዋና ሀሳብ መለየት፣
- በፅሁፉ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ሀሳቦች ማገናኘት እና በማስታወሻ ላይ መፃፍ፣
- በፅሁፉ ውስጥ ዋናውን ሀሳብ ለማብራራት የገቡትን የማያስፈልጉ መረጃዎች መተው
- ፅሁፉን ደጋግሞ በማንበብ ያነበባችሁትን ማስታወስ
- በራሳችሁ መንገድ የምትፅፉት ሀሳብ ከዋናው ፅሁፍ የተለየ እንዳይሆን መጠንቀቅ
- የምንባቡን ሀሳብ በራሳችሁ ቋንቋ መፃፍ
- በራሳችሁ መንገድ አሳጥራችሁ የፃፋችሁት እና የቀረበው ፅሁፍ ሀሳብ ተመሳሳይ መሆኑን ማረጋገጥ ናቸው፡፡

7.አውዳዊነት(Context)፡- የቀረበውን ምንባብ አንብቦ ለመረዳት በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ቃላት ሁሉ ማወቅ ሊከብድ ይችላል፡፡ በመሆኑም በምንባቡ ውስጥ አዳዲስ ቃላት ሲያጋጥም መዝገበ ቃላት ከመጠቀም አስቀድሞ ቃላቱ በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ሀሳብ ለመረዳት አውድን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

ምሳሌ ሀ ፡- ወጣቶች የነገ ሀገር ተረካቢ ዜጎች መሆናቸውን በመመልከት ዛሬ ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ እድል መስጠት ያስፈልጋል፡፡

በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ **ማስተዋል** ማለት ነው፡፡

ምሳሌ ለ ፡- አዘውትሮ ስፖርት መስራት አካልን ከመገንባት በላይ ጤናማ ህብረተሰብን የማፍራት ትልቅ ድርሻ አለው፡፡

በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ**ማጎልበት ወይም ማዳበር** ማለት ነው፡፡

8.**ማሸጋገር**(Transferring)፡-በምትማሩበት ቋንቋ አዲስ እውቀት ለማግኘት የቀደመ እውቀታችሁን መጠቀም ወይም በሌላ አገላለፅ በሁለተኛ ቋንቋ የቀረበው ምንባብ ውስጥ ያለውን ሀሳብ ለመረዳት የማንበብ ብልሃቶችን ከመጀመሪያ ቋንቋ ወደ ሁለተኛ ቋንቋ ማሸጋገር ነው፡፡ ይህ የማንበብ ብልሃት በሁለተኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ ለመረዳት አስቸጋሪ ሁኔታ ሲያጋጥም በመጀመሪያ ቋንቋ የተማራችሁትን አምጥቶ በመጠቀም የገጠመን ችግር ለማስወገድ ጥረት ማድረግ ነው፡፡

9.**የቀደመ እውቀትን መጠቀም**(Using background knowledge)፡-ይህ የማንበብ ብልሃት ስለአለም እና ስለሚነበበው ፅሁፍ ይዘት ያለ እውቀትን በአግባቡ መጠቀምን የሚያመላክት ነው፡፡ በውህድ አሀድ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ቃላት መለየት አንብቦ መረዳትን አያረጋግጥም ፡፡ በመሆኑም አንባቢዎች ትርጉምን ለማዋቀር የውህድ አሀዱን መረጃ አስቀድሞ ከሚያውቁት ጋር ማገናኘት አለባቸሁ፡፡ የሚከተለውን ፅሁፍ በምሳሌነት ተጠቀሙ፡፡

ምሳሌ፡-ለአንድ ሀገርእድገት እና ብልፅግና ዲሞክራሲያዊ ስርአት ወሳኝ ነው፡፡ያለ ዲሞክራሲ ልማትንም ሆነ ብልፅግናን ማምጣት አይቻልም፡፡

ይህን አረፍተ ነገር ስታነቡ በተለያየ መንገድ ስለዴሞክራሲ ያገኛችሁትን እውቀት በማስታወስ በመጀመሪያ ዴሞክራሲ ምንድነው ብላችሁ ፅንሰ ሀሳቡን ለመረዳት ሞክራችሁ ከሆነ በትክክል የቀደመ እውቀታችሁን ተጠቀማችሁ ማለት ነው፡፡

10. ***መገመት*** (Guessing Intelligently)፡- ተማሪዎች የምታነቡትን ፅሁፍ አጠቃላይ ትርጉም ለመረዳት እያንዳንዱን ቃል ማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡ በመሆኑም አንብቦ ለመረዳት ሁሉንም ጉዳይ በዝርዝር ልረዳ በማለት ሳታተገሉ ብልሃት የታከለበት ግምት መጠቀም አለባችሁ፡፡ መገመትን ሁልጊዜ ለመጠቀም መሞከር(የምንባቡን ሀሳብ ከዳር እስከዳር) ለስህተት ይዳርጋል፡፡ በማንበብ ሂደት መገመት የሚገባችሁ የማታውቋቸውን አዳዲስቃላት፣በሀረግ በአረፍተነገር፣በአንቀፅ ውስጥ ያሉ አዳዲስ ሀሳቦች ወዘተ ነው፡፡ ተማሪዎች በሁለት መንገድ መገመት ትችላላችሁ፡- እነሱም

ሀ. **የቋንቋ ፍንጭ ላይ የተመሰረተ ግመታ**(Using Lingustic Clus) - በቅርብ ጊዜ በታላሚው ቋንቋ ያገኛችሁት እውቀት፣የተማሪዎች የራሳችሁ ቋንቋ ወይም ሌላ ቋንቋ (የምትማሩት ቋንቋ)ፍንጭ ላይ መሰረት ያደረገ ግመታን ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል። ቅድመ ግንድ ፣ድህረ ግንድ ቅጥያ፣ የቃላት አደራደር ግመታ ለማድረግ ጠቃሚ የቋንቋ ፍንጮች ናቸው።

ለ. **ሌሎች ፍንጮች (ኢ-ቋንቋ ፍንጭ)** (Using Other Cluse) - ከቋንቋ እውቀት በተጨማሪ ከሌላ ምንጭ የሚገኝ ግመታ አለ።(ለምሳሌ በማህበራዊ ግንኙነት የአድራሻ ቅርፅ) ሌሎች ደግሞ ከቋንቋ ጋር ያልተገናኙ ይሆናሉ። የአድራሻ ቅርፅ ለምሳሌ ማዕረግ ወይም ቅፅል ስሞች ለአንባቢዎች ግመታ ፍኝጭ ይሰጣሉ። ሌላው እውቀት ነው (በጉዳዩ ዙርያ ያለ እውቀት እና አጠቃላይ የቀደመ እውቀት) በቅርብ ጊዜ የተነበበው ትርጉም ምን እንደሆነ በተደጋጋሚ መረጃ ለመስጠት ያስችላል።

ከላይ የቀረቡትን ብልሃቶች (ማስታወሻ መያዝ፣ ዋናውን ሀሳብ በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ፣ አውዳዊነት፣ ብልሃቶችን እያሸጋገሩ መጠቀም) ተግባራዊ ለማድረግ ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ ደጋግሞ በማንበብ ተለማመዱ።

አባይ እና የህዳሴ ግድብ

የጥንታዊ አለም ስልጣኔ ታሪክ እና የአብዛኛዎቹ ህዝቦች እድገት ያቆጠቆጠው እና የስልጣኔ አሻራቸው ያረፈው በወንዞች ዳርቻ ነው። ቻይናውያን በየሐፊሻራ (ቢጫ ወንዝ)፣ ኢራቅ እና ኢራን በኤፍራጣስ እና በጤግሮስ ወንዝ፣ ግብፃውያን እና ኑቢያውያን በአባይ ወንዝ እና ሌሎችም በአካባቢያቸው የሚገኙ ወንዞችን ለግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ በሚጠቅም መንገድ አደራጅተው የበርካታ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ማእከል አድርገው ተጠቅመውባቸዋል። እንዲሁም የህልውናቸው መሰረት እና የእለታዊ ህይወታቸው አንቀሳቃሽ ሞተር በማድረግ ተገልግለውባቸዋል።

ሀገራችን ኢትዮጵያም የአፍሪካ የውሃ ማማ የሚል ስያሜ ማግኘት ያስቻላት ከፍተኛ የውሀ ሀብት ባለቤት በመሆንዋ ነው። ኢትዮጵያ ብዛት ያላቸው ወንዞች መፍለቅያ፣ የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች መገኛ ውብ ሀገር ናት። ከነዚህ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች በአለም ትልቅ እና ረጅም ከሚባሉት ወንዞች አባይ አንዱ እና ተቀዳሚው ነው።

የአባይ ወንዝ ከሰከላ ተነስቶ ሜዲትራንያን ሀይቅ እስኪገባ ብዙ አገሮች ያቋርጣል። አባይ በአለም አቀፍ ደረጃ በሁለት ስም ይታወቃል። ይኸውም ነጭ አባይ እና ጥቁር አባይ

ወይም ራሱ አባይ ተብሎ ይጠራል። የነጭ አባይ ምንጭ የቪክቶርያ ሀይቅ ከኡጋንዳ ሲሆን የጥቁር አባይ ምንጭ የጣና ሀይቅ ከሆነው ከኢትዮጵያ ነው። ጥቁር አባይ ወይም ትልቁ አባይ የሚያቋርጣቸው አገሮች መነሻው ከኢትዮጵያ ሆኖ ዛየር፣ ኬንያ፣ ታንዛንያ፣ ሩዋንዳ፣ ቡሩንዲ ናቸው። አባይ ነጭ አባይ ተብሎ የሚያቋርጣቸው አገሮች ኡጋንዳ፣ ሱዳን እና ግብፅ ናቸው። በአጠቃላይ አባይ ዘጠኝ አገሮችን ያቋርጣል። እነሱም ሱዳን (ደቡብ ሱዳንን ይጨምራል)፣ ቡሩንዲ፣ ሩዋንዳ፣ ዲሞክራቲክ ኮንጎ፣ ታንዜንያ፣ ኬንያ፣ ኢትዮጵያ፣ ኡጋንዳ እና ግብፅ ናቸው። የተለያዩ የመረጃ ምንጮች እንደሚያመላክቱት የአባይ ርዝመት 6695 ኪሜ ወይም 418 ማይልስ ነው። የውሃ መጠኑም በቀን ስሌት ሲሰላ በግምት 300 ሚሊዮን ኪውቢክ ሜትር ሊሆን እንደሚችል ይነገራል።

አባይ ለኢትዮጵያውያን ተስፋ ነው። ድህነትን ማስወገጃ የነገ መፃኢ እድላቸውን የሚወስኑበት በደማቸው ውስጥ ሰርፆ የገባ የማንነት መገለጫ ነው። አባይ ኢትዮጵያ ወደፊት ለመራመድ እንቅፋት የሆነባትን ድህነት ለመቅረፍ ተስፋ የጣለችበት የሀይል አቅርቦት መገኛ ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያውያን የአንድነታችን ማሳያ፣ የእኛነታችን መገለጫ፣ ከድህነት የመውጫችን መንገድ፣ የህልውናችን ማረጋገጫ ቁልፍ መሳርያ የሆነውን የህዳሴ ግድብ በወንዙ ላይ እየገነባን ያለነው።

የህዳሴው ግድብ ከአዲስ አበባ በደብረማርቆስ በኩል 750 ኪሎ ሜትር ከሱዳን ደገግሞ 40 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በቤኒሻንጉል ክልላዊ መንግስት በጉባ ወረዳ “ቡምባዲ” በምትባለው አካባቢ የሚገነባው ግድብ ሲጠናቀቅ የሀገሪቱን የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት በሶስት እጥፍ በማሳደግ 6450 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም አለው። ይህ ግድብ በሁለት ተራሮች መካከል የሚገነባ ነው። በተራሮቹ መካከል ያለው ርዝመት 1.8 ኪሎ ሜትር ይደርሳል።በነዚህ ተራሮች መካከል ለዘመናት ሲፈስ የኖረው የአባይ ወንዝ የሚገደበው በነዚህ ተራሮች መካከል ነው።

የግድቡ ከፍታ ከመሬት ወደላይ 145 ሜትር ነው። የግድቡ የጎን ስፋትም ከታች 120 ሜትር ይሆንና የመጨረሻው ጫፍ ላይ አምስት መኪና ማስተላለፍ የሚችል ሆኖ ይገነባል። በ 1.8 ኪሜ ርዝመት እና በ 145 ሜትር ከፍታ የሚገነባው የአባይ ወንዝ ከግድቡ ወደኋላ 63 ቢሊዮን ሜትር ኪዩቢክ ውሃ ያለው (280 ኪሎ ሜትር ርዝመት) ሰው ሰራሽ ሀይቅ ይፈጥራል። ይህም 5 ሺህ 250 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም ይፈጥራል። የህዳሴው ግድብ በጎን እና በጎን ያጠራቀመውን ውሀ እንዳያፈስ ከዋናው

ግድብ ሌላ በ5 ኪሎ ሜትር ርዝመት45 ሜትር ከፍታ ያለው እና 5 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው በድንጋይ የተሞላ ግድብ ይገነባል፡፡ የግድቡ ውሃ እንዳይፈስ አቅፎ የሚይዝ ነው፡፡ ይህ ግድብ በሙያው አጠራር “ሳድል ዳም” ይባላል፡፡

በግድቡ አማካኝነት የሚያዘው የአባይ ውሃ ወደኋላ ተመልሶ እንደሚተኛ እና እንደሚጠራቀም ይጠበቃል፡፡ በዚህ ወቅት የግድቡ ውሃ ከፍተኛ መጠን ላይ ሲደርስ በጠቅላላው 1 ሺህ 680 ስኩዌር ኪሜ ቦታ እንደሚሸፍን እና ግድቡ ወደኋላ ተመልስ ወደሸለቆ ውስጥ እንደሚገባ ይጠበቃል፡፡ ግድቡ ሲጠናቀቅ የኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጨት ብቻ ሳይሆን የአካባቢውን ስነምህዳር ማሻሻል፣ በሚፈጠረው ሰው ሰራሽ ሀይቅ አማካኝነት ከፍተኛ የአሳ ሀብት ልማትን ማጎልበት፣ የጀልባ ትራንስፖርት፣ የቱሪስም የሀብት ምንጭ ወዘተ በመሆን ያገለግላል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል

ምንጭ፡- አዲስ ዘመን ጋዜጣ ፣ሚያዝያ 28/2003 ዓም(ለአቀራረብ እንዲያመች ተሻሽሎ የተወሰደ)

11. **ማቀድ**(Planning) ፡-ይህ የማንበብ ብልሃት አንድን ፅሁፍ ለማንበብ አስቀድሞ በምን መልኩ መነበብ እንዳለበት ማብሰልሰልን እና በማንበብ ጊዜ አንብቦ መረዳትን ተግባራዊ ለማድረግ እንዴት መነበብ እንዳለበት ማቀድን ያመላክታል፡፡ በዚህም ትኩረት የሚሰጠው ተግባር፡-

ሀ .**በከፍተኛ ሁኔታ ማደራጀት** - የማንበብ ተግባሩን አላማ መወሰን እና እንዴት መጨረስ እንደሚገባ ማቀድ

ለ. **ትኩረትን ቀጥተኛ ማድረግ**- የማይጠቅም መረጃን በመተው እና ወደሚነበበው ዋና ጉዳይ ትኩረት በማድረግ አጠቃላይ ግንዛቤ ለማግኘት መጣር

ሐ. **ትኩረትን መምረጥ**- ከአንብቦ መረዳቱ ተግባር ጋር በማገናኘት ወደተነጠለ ዝርዝር ጉዳይ ማተኮር

መ. **ራስን መምራት** - በተሰጠው የማንበብ ተግባር መሰረት አስፈላጊ ሁኔታዎችን በመረዳት ለማንበብ እና የራስን መነሳሳት መምራት እና የማንበብ ፍጥነትን ማስተካከል ናቸው፡፡

12.**መቆጣጠር** (Monitoring) ፡- ይህ የማንበብ ብልሃት የማንበብ ሂደትን እና መረዳትን መቆጣጠር የሚያስችል ነው፡፡ በስሩ ያሉት ተግባራት፡-

ሀ. አንብቦ መረዳትን መቆጣጠር- የሚነበበውን ፅሁፍ ለመገንዘብ መረዳትን መቆጣጠር እና ማጣራት ወይም መረዳትን ማረጋገጥ

ለ. ተግባርን መቆጣጠር - ተግባርን ለማጠናቀቅ ራስን መቆጣጠር

13.**ራስን መገምገም**(Self-Evaluation)፡- በማንበብ ሂደት ተማሪዎች የቀረበው ፅሁፍ ገብቷቸው እንደሆነ እና እንዳልሆነ ፣አንብቦ ለመረዳት ምን ችግር እንዳጋጠማቸው ወዘተ የምትገመግሙበት ነው፡፡ በዚህም ስር ያሉት ተግባራት ፡-

ሀ. ብቃትን (ክወናን) መገምገም - በተሰጠው የማንበብ ተግባር መሰረት ምን ያህሉን በማንበብ መረዳት ቻልኩ ብሎ ራስን መገምገም

ለ. ያጋጠመን ችግር መገምገም- በተሰጠው የማንበብ ተግባር መሰረት በማንበብ ሂደት የአጋጠመኝ ችግር ምንድነው በማለት ራስን መገምገም ነው፡፡

ተማሪዎች ልእለአዕምሮታዊ የማንበብ ብልሃት በምትጠቀሙበት ወቅት ከዚህ በታች የቀረቡትን ተግባራት ማከናወን እንደሚገባ አስተውሉ፡፡

ማቀድ፡-

- ፅሁፉን በአጠቃላይ ከማንበብ በፊት የሚነበበውን ለማወቅ ፅሁፉን በአጠቃላይ መመልከት (ለምሳሌ፡- አስፈላጊ የሆኑ ርዕሶች፣ ንኡሳን ርዕሶች፣ የምህራፍ ቢጋሮች፣ ጭምቀ ሀሳቦች ወዘተ ....
- የፅሁፉን ርዝመት እና አወቃቀር ማጤን
- የተሰመረባቸው፣ ቀልመው ወይም ደምቀው የተፃፉ፣ ጋደድ ብለው የተፃፉትን ማስተዋል፣ ከማንበብ በፊት የማንበብ አላማን በአዕምሮ ማስቀመጥ፣
- የፀሀፊውን መልዕክት መገመት
- እራስን መጠየቅ ፣
- የሚነበበውን በሚገባ ለመረዳት ስለርዕሱ ምን አውቃለሁ ብሎ ማሰብ፣
- በጥልቀት የሚነበበውን እና የሚተወውን በመለየት መወሰን፣
- በሚነበብበት ጊዜ ማስታወሻ መያዝ ፣ ምልክት ማድረግ፣ ማንበብን ገታ (ቆም) አድርጎ ማሰላሰል፣

መቆጣጠር፡-

- የፅሁፉ ርዕስ እና ይዘት ከማንበብ አላማችን ጋር የሚዛመድ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- ማስታወሻ መያዝ (ምሳሌዎች ፣ ሀሳቦች ፣ ተያያዥ ጉዳዮች) ፣
- በየተወሰነ ቦታ ማንበብን ገታ (ቆም) በማድረግ ስለሚነበበው ጉዳይ ማሰላሰል፣
- በፅሁፍ ውስጥ አስፈላጊ የሆነን ጉዳይ ለማስታወስ ጠቃሚ በሆነ ሀሳብ ላይ ምልክት ማድረግ ፣ ማስመር፣ ማክበብ ወዘተ...፣
- የበለጠ ለመረዳት አውዳዊ ፍንጮችን መጠቀም፣
- በፅሁፍ ውስጥ ያለውን ሀሳብ በትክክል መገመታችንን ማረጋገጥ፣

- ከምንባቡ ውስጥ አዲስ መረጃ አገኘሁ ወይ ብሎ ራስን መጠየቅ፣
- ከምንባቡ ውስጥ ፍፁም የማይታወቁ ቃላት ካሉ መዝለል ፣ አንዳንዶቹን መዝግቦ መያዝ እና ማረጋገጥ (በዚህ ምክንያት ማንበብን ማቋረጥ አያስፈልግም)፣
- ግልጽ ያልሆነን ሀሳብ ተመልሶ ማንበብ፣

ማጠቃለያ፡-

- ተጨማሪ ጥያቄዎችን፣ የችግሮች መፍትሄዎችን እና ተግባራትን ማሰብከ፣
- ማስታወሻን መልሶ ማየት፣ የተዘነጋ ሀሳብ ካለ ማካተት፣ መፃፍ፣
- ምንባቡን በሚገባ ለመረዳት ደግሞ ማንበብ፣ የፀሀፊውን ሀሳብ በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ፣
- ከማንበብ አላማ በመነሳት ምን ተማርኩ ብሎ ራስን መጠየቅ (በምንባቡ መሰረት የተሰጡ ተግባራትን ማከናወን፣ የቤትና የክፍል ስራ መስራት።

14.ጥያቄ መጠየቅ (Asking Question)፡- ጥያቄ መጠየቅ ተማሪዎች ትክክለኛ ትርጉም ለማግኘት እና ለመገንዘብ የሚረዳችሁ ነው። ተማሪዎች ከመምህራሁ፣ ከአቻዎቻችሁ ጋር ርስበርስ በመነጋገር በታላሚው ቋንቋ ሰፋ ያለ ግብአት በማግኘት የመማር ፍላጎታችሁን እና ተነሳስቷችሁ እንዲጨምር ያደርጋል። በዚህ ብልሃት ሌላን ሰው መጠየቅለምሳሌ መምህርን ወይም በታላሚው ቋንቋ አፉን የፈታ ወይም የበለጠ ብቃት ያላቸው ተማሪዎችን (ጓደኛን) መጠየቅ ነው። በዚህም ለማብራራት(ለማጣራት)፣ለማረጋገጥ እና ለማረም መጠየቅ አለ።

ሀ. ለማብራራት (ለማጣራት) ወይም ለማረጋገጥ መጠየቅ፡- ተናጋሪው ሪፖርት እንዲያደርግ፣ሀሳብን አሳጥሮ እንዲያቀርብ ፣ረጋ እንዲል ወይም ምሳሌ እንዲሰጥ፣ እያንዳንዱ ንግግር ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ወይም ህጎች ከእያንዳንዱ ጉዳይ ጋር የሚገጥሙ መሆኑን፣ የሆነ ሀሳብ ትክክል መሆኑን እና ምጋቤ ምላሽ ለማግኘት ሀሳብን አሳጥሮ ማቅረብ ወይም መድገም ያለበት ነው።

ለ. ለማረም መጠየቅ፡- በአብዛኛው በንግግር ልውውጥ የሚያገለግል ሲሆን በንግግር ጊዜ ያለን ሀሳብ ለማረም መጠየቅ ነው። አንድን ነገር ለማረም መጠየቅ በተለይ ክፍል ውስጥ በጣም ጠቃሚ የሆነ ብልሃት ነው። በክፍል ውስጥ ያለ መማር ማስተማር በአብዛኛው ግልፅ እርማት (Overt Correction) የሚፈልግ በመሆኑ ጠቃሚ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ብልሃቱ ራስንም የመጠየቅ ሂደት ያስተናግዳል። ይህም ተማሪዎች የሚያነበው እያንዳንዱ የፅሁፍ አካል የገባችሁ መሆን አለመሆኑን ከራሳችሁ ጋር እየተነጋገራችሁ እና እየጠየቃችሁ መልስ ለማግኘት ጥረት የምታደርጉበት ነው።

ከላይ የቀረቡትን ብልሃቶች (የቀደመ እውቀትን መጠቀም፣ መገመት፣ ማቀድ፣ መቆጣጠር፣ ራስን መገምገም፣ ጥያቄ መጠየቅ) መሰረት በማድረግ በሚከተለው ምንባብ ውስጥ ያለውን ዋና ሀሳብ እና ዝርዝር ሀሳቦች በማውጣት ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ። በውይይቱ የደረሳችሁበትን ሀሳብም ለመምህራችሁ አብራሩ።

ቋንቋ አጠቃቀም

በቋንቋዎች መካከል የቋንቋ አካላትን (ድምፅ፣ቃላት፣ ሐረጋት፣ ምእላዶች፣ ወዘተ.) ሆነ፣ የቋንቋ ባህርያትን (የአገላለጽና የመዋቅር መልኮችን) መዋዋስ የነበረ፣ ዛሬም ያለ፣ ወደፊትም የሚቀጥል ጉዳይ ነው። መዋዋስን የገታ የአንድም ህብረተሰብ ታሪክ እስከ ዛሬ ድረስ አልተመዘገበም። ለምሳሌ ዛሬ በአማርኛ ውስጥ የምንጠቀምባቸው አንዳንድ ቃላት ቁርጥ አማርኛ ይምሰሉን አንጂ፣ በተውሶ የተወሰዱ ናቸው። ፊርማ፣ መኪና ፣ ስኳር፣ ኪሎ፣ መዲና ለዚህ እንደማስረጃ ሊጠቀሱ ይችላሉ። እርግጥ እነዚህንና መሰል ቃላትን ከተዋስን በኋላ፣ ለአጠቃቀም እንዲመቹን በማሰብ “አማርኛ” ባህርያትን ሰጥተናቸዋል። ለምሳሌ “ፊርማ= ፈረመ”፤ “ዳንስ = ደነሰ”... እያልን በአማርኛ ርባታ ስልት መሰረት እንገለገልባቸዋለን።

በቋንቋዎች መካከል መዋዋስ አይቀሬ ነገር ቢሆንም፣ አንዳዴ መረን የለቀቀ ሁኔታ መታየቱ ተደጋፊነትም፣ ዘላቂነትም የለውም። የማይዘልቅበት ምክንያ ግልጋሎቱ ወቅታዊ ሆኖ ስለሚቀር ነው። ማንኛውም ማህበረሰብ፣ የየእለት ገጠመኙንና ስሜቱን የሚገልጽባቸው ቃላትና የአገላለጽ መንገዶች ይኖሩታል። እነዚያን መንገዶች የሚጋፉበት ባእድ ቀመስ የቋንቋ ባህርያት ሲመጡ ወዲያው ለመቀበል ይቸግራል። እንዲያውም ከጥራዝ ነጠቆቹ ጋር እስከ መጋጨት ይደርሳል። እነዚያን አዳዲስ የቋንቋ ጠባያት ተቀብሎ ሳያጸድቃቸው ሲቀር ስር ሳይዙ ይደርቃሉ።

የባእድ ቃላትና አገላለጾች ሳያስፈልጉ (ሳይቸግር) ወደ አንድ ነባር ቋንቋ በብዛት ሲሰርጉ መመልከት መረን ለቀቅነትን ይጠቁማል። መረን ለቀቅነቱ በሁለት አቅጣጫ ሊታይ ይችላል። አንድም ቃላቱም ሆነ አገላለፆቹ ሳያስፈልጉ (የሚያመጡት አዲስ ጽንሰ ሀሳብ ሳይኖር) ስለመጡ ሂደቱ ተገቢነት የለውም። እንደገናም መጥተውም አይቆዩም። ማህበረሰቡ የውሰት ቃላቱ የሚገልጹትን ሀሳብና ስሜት የሚገለጽበት የራሱ ቃላትና የአገላለጽ መንገዶች ስላሉት፣ ተቀብሎ በተግባር አያውላቸውምና አመጣጣቸው የዘላቂነት አይደለም። ከላይ ያየናቸው (መኪና፣ ስኳር) እና ዛሬም እየተዋስናቸው ያሉት (ቪዲዮ፣ ኮምፒውተር፣ካሴት) ቃላት፣ አገልግሎታቸው ከፍ ያለ ነውና (አዲስ ነገር በማምጣታቸው)

የቋንቋችንን ወዘና እየለበሱ ይኖራሉ። እንደ ዳዲ፣ ማዘር፣ አይ ላቭ ዩ፣ ወንበር ውሰድ ያሉት ግን የነበሩትን ቃላት አሸንፈው ለመውጣት ኃይል አያገኙም(አላገኙም)።

ብሉምፊልድ የተባለው ምሁር እንደሚለው፣ የቋንቋ ውሰት፣ ስነልሳናዊ ብቻም ሳይሆን፣ ባህላዊ ተላልፎንም ይጨምራል። የቃላትን ውሰት የሚያስከትሉ ጉዳዮች ከባህል ጋርም ይያያዛል ማለት ነው። ቃላትንም ሆነ የአገላለፅ መንገዶችን የሚዋስ ማህበረሰብ፣ የሚዋስበትን ባለቋንቋ የሚገነዘበው ከራሱ ላቅ አድርጎ ነው። ለምሳሌእኛከእንግሊዝኛ ቃላትን በብዛት የምንዋስ ከሆነ፣ እንግሊዝኛ ተናጋሪዎችን ከእኛ የላቁ ህዝቦች እንደሆኑ አድርገን እናስባለን ማለት ነው። በዚህ የተነሳ ተገቢ ከሆነ ሰብአዊ ምርታዊ ግንኙነትም አልፈን፣ የአለባበስ፣ የአኗኗር፣ የጋብቻ፣ የባህርይ፣ ወዘተ ቅጅዎችን ሁሉ ከቋንቋው ጋር ማምጣት እንመኛለን። ይህ ደግሞ የራስን ማንነት ዝቅ ያደርጋል።

በሌዊስ አባባል መሰረት፣ የዘመናችን ማህበረሰብ ለምእራባውያን ስሜትና ፍላጎት ተሸንፏል። ይህን ያመጣው የቴክኖሎጂ አብዮት ነው። ከሕትመት ውጤቶች በተጨማሪ፣ ኤሌክትሮኒክስ ነክ መገናኛዎችም አለምን ከጠርዝ እስከ ጠርዝ ተቆጣጥረውታል። እያንዳንዱ የነዚህ ግንኙነቶች ተጋሪ (ተቋዳሽ) ለምእራባውያኑ ባህል ተጋላጭ ሆኗል ማለት ነው። አብላጫው የባህሉ መምጫ ዘዴም ቋንቋዊ ተግባቦት መሆኑ እየታመነ ነው። ሀቁ በእያንዳንዳችን ዘለለታዊ ገጠመኝ ውስጥ ቁልጭ ብሎ እየታየ ነው። በተለይ በቀላሉ በትምህቱ እልፍ ያልነው የማህበረሰብ አባላትና ከተሜው፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋችን ስንናገር መላውን እንግሊዝኛ በርዘን ነው። ይህ ሁኔታ፣ የባዕዳን ቋንቋ ማወቅ ላቅ ያለ ግምት ያሰጣል የሚለውን ማጠቃለያ እንድንሰጥ ያደርገናል። ስነልቦናዊ ቀውስ ከምንለካው እሳቤ አኩዋያም ይታያል።

ባጭሩ መረን ለቀቅ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ከማህበረሰባዊ ገፅታው አንጻር ሲታይ፣ አሉታዊ መልኩ ጎልቶ ይታያል ማለት ይቻላል።

ምንጭ፡- የሻው ተሰማ፣ ልሳነ ብዕር ከመልሳነ ሰብእ(1996)

15.**ከሌሎች ጋር መተባበር** (Cooperating with others)

ይህ የማንበብ ብልሃት ከሌሎች አቻዎች (ከአንድ ወይም ከብዙዎች)ጋር መስተጋብር በመፍጠር የቋንቋ ችሎታን እና የማንበብ ችሎታን ለማዳበር የሚያስችል ነው። ይህ ብልሃት ከቋንቋ መማር ብልሃት ጋር መሰረታዊ ግንኙነት ያለው ሲሆን ተማሪዎች የቋንቋ ብቃታቸውን ለማጎልበት ብቻ ሳይሆን በራስ መተማመንን እና ማህበራዊ ተቀባይነትን እንዲያጎለብቱ ይረዳል።

ሀ.ከጥንድ አቻ ጋር መተባበር፡- በክፍል ውስጥ በተደጋጋሚ የሚከናወን ሆኖ ተማሪዎች ከአቻዎቻቸው ጋር በመተባበር ተወዳዳሪነታቸውን እና ተፎካካሪነታቸውን እንዲያጎለብቱ ያደርጋል፡፡

ለ.ብቃት ካላቸው ጋር መተባበር፡- ብዙ ጊዜ በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ ተተኳሪው ቋንቋ የመጀመሪያ ቋንቋቸው ከሆኑ ወይም በችሎታቸው ከእነሱ ላቅ ካሉ አቻ ተማሪዎች ጋር በመተባበር መወያየት ፣ መከራከር እና ባነበቡት ሀሳብ ዙርያ ልምድ መጋራትን ለማከናወን ይጠቅማል፡፡

16. በአእምሮ ውስጥ ምስል መፍጠር(Using Imagery/Visualize)

በአእምሮ ውስጥ ምስል መፍጠር የማንበብ ብልሃት የቀረበን ምንባብ መሰረት በማድረግ መረጃ በአእምሮ ውስጥ ትርጉም ያለው ይዘታዊ ምስል እንዲከሰት ለማድረግ የሚስችል ነው፡፡ በአእምሮ ውስጥ የሚከሰተው ምስል የቃላትን ወይም የገለፃን ቅደም ተከተል ለመለየት የሚያገለግል ነው፡፡ ይህ ብልሃት በአእምሮ ውስጥ ሁነቶችን ወይም ነገሮችን ከሀሳባዊ ምስል ጋር በማያያዝ ውስብስብ ቃላትን ለማስታወስ ይረዳል፡፡ ለምሳሌ፡- ማብሰል፣ ማፅዳት፣ ማጠብ፣ መቁረጥ፣ መግዛት፣ ወዘተ ቃላት ሁነቶች በአእምሮ ውስጥ ምስል እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ አካባቢን የሚገልፀው ለምሳሌ ተራራው በአደይ አበባ ተንቆጥቁጧል፡፡ ክረምት በመሆኑ አካባቢው ጨቅይቷል፡፡ ድርጊቶች ለምሳሌ ሰላማዊት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ ሳሎን ቤት መመገብያ ወንበር ላይ ተቀምጣ ጠረቤዛው ላይ ትልቅ መፅሀፍ ዘርግታ ታነባለች፡፡

የፅሁፍን ሀሳብ በአእምሮ ምስል እንዲሀጥር ማድረግ ቃላትን ጨምሮ የፅሁፍን ሀሳብ ለማስታወስ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ለምሳሌ ቃላቱ ረቂቅ ቢሆኑ - ብርሃን፣ፍቅር፣ተስፋ ግኡዝ ነገርን የሚያመላክቱ ቢሆኑ ለምሳሌ - ቤት፣ ዛፍ፣ መጠንን የሚያመላክቱ ረጅም፣ አጭር፣ ሰፊ ጠባብ መስተዋድዶች ለምሳሌ- ከላይ በውስጥ፣ከ...መካከል፣ በታች፣ በስር ቃላትን አእምሯዊ ምስል በመፍጠር እንዳረሱ ማድረግ ነው፡፡ ሌላው ምንባቡን በሚገባ በማንበብ እና አወቃቀሩን በመረዳት ሀሳብ እንዴት ተደራግቶ እንደተቀመጠ በአእምሮ ምስል በመፍጠር የምንባቡን ጠቃሚ ሀሳብ ለማስታወስ ያገለግላል፡፡ ብልሃቱ በማንበብ ሂደት የሚተገበር ነው፡፡

ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ በትኩረት በማንበብ ከላይ የቀረቡትን ብልሃቶች (በአእምሮ ምስል መፍጠር እና ከሌሎች ጋር መተባበር) ተለማመዱ፡፡

ሲጨልም

ወደ ሰባዎቹ የሚጠጉ የሚመስሉ አንድ አረጋዊ “ልጄ” አሉት አስተናጋጁን፡፡ “የወሰድኩትን መድኃኒት ይገፍብህ መጣሁ፣ እባክህን የሰጠኸኝን ወስደህ…”

አላስጨረሳቸውም፡፡ ግርግዳው ላይ ወደተለጠፈው ጽሑፍ አመለከታቸው፡፡ የተሸጠ መድኃኒት አይመለስም አረጋዊው በለሰለሱ ቃላት መማጸን ያዙ፡፡

“ሰውዬ ዞር በል! ስራ ልስራበት! ለእንቶ ፈንቶ ጉዳይ የማባክነው ጊዜ የለኝም…” አለ ቁጣው እየተወለደ፡፡

“ዛሬ በዚህ ሰውዬ እንድጨቀጨቅ ተፈርዶብኛል ልበል?”

“እባክህን ልጄ አሳፋሪ ነገር ደርሶብኝ ነው ዘመድና ዕድር የለለኝ በመሆኑ እንጂ…” አሉ ትሁት በሆነች ፈገግታ ሊያባብሉት እየሞከሩ፡፡

“ቅናሽ ዋጋ ብትከፍለኝም…”

“ይሄ ሰውዬ ነካ ያረገዋል ልበል?” አለና ሌሎች መድኃኒት ገዥዎችን ያስተናግድ ገባ፡፡

“ከያዙ አይለቁ”

“ድህነት ቢፈትነኝ ነው ልጄ” አሉ ያደፈና የነተበ ነጠላቸውን እያሳዩት፡፡ ነጠላው ከሰውነታቸው በከፋ ሁኔታ ያረጀውን ኮታቸውን ደብቆላቸዋል፡፡

“አቅሜ የደከመ ባይሆን ኖሮ …” ጫማ ካገኘ የከረመ እግራቸውን እያዩ፡፡ አንዲት ተስተናጋጅ “አልመልስም ካለ አልመልስም ነው፡፡ ለምንድን ነው የሚነዘንዙት?” አለች በሚነጫነጭ ድምጽ “ይሄኮ ፋርማሲ እንጂ አዛውንቶች የሚጦሩበት የድኩማን መርጃ ድርጅት አይደለም”

አነጋገሯን ያልወደደው የሚመስል ሌላኛው ጎልማሳ ደግሞ “መድኃኒቱን ሙሉ በሙሉ የገዙት ከዚሁ መደብር ነው?” የሚል ጥያቄ አመጣ፡፡

“አዎ ዶክተሩ ጽፎ በሰጠኝ መሠረት”

“ምን ያሕል ፈጅበዎት?”

“ሰባ ሁለት ብር ከሰማኒያ አምስት ሳንቲም፡፡ መድኃኒቱን ወስደው እንኳን ግማሹን እንኳን ቢሰጡኝ ምን አለበት?” አሉ በሃዘኔታ፤

“የሁለታችንንም የጋብቻ ቀለበት አስይገፍ ነው ከማምነው ሰው የተበደርኩት”

“መድኃኒቱን ለምን መመለስ ፈለጉ?” ዘንቢል ያንጠለጠሉ ያንዲት ምስኪን እናት ጥያቄ፡፡

በዚህ ጊዜ አስተናጋጁ ጣልቃ ገባ፡፡ “ባህላዊ ህክምና ብትከታተል ኪስ እንደማታራቁት ገብቷቸው ይሆናላ! ወይ ፀበል ሊያስጠምቋት! ወይ…”

“አይ ልጄ! ጉዳዩን ብታውቀው ኖሮ ያፌዝክብት ምላስህን ታፍርበት ነበር…” አሉ እንባ እየተናነቃቸው፡፡

“መድኃኒቱን ምን ላድርገው? ልዋጠው ወይስ ሽንት ቤት ልጨምረው?”

“ለባለቤቱ ነው የምገዛላት ብለው አልነበር? በጠና ታማብኛለች የእድሜዬ ጀምበር እየጠለቀ ባለበት ሰዓት ለእህል ያላነሱና ለትምህርት ያልደረሱ ሶስት ልጆች በትናብኝ እንዳትሄድ ፀልይልኝ ብለውኝ አልነበር?”

“ማለቱንስ ብዬህ ነበር ልጄ!... ብዬ ነበር”

“እና ሩብ ሰዓት እንኳን ሳይቆዩ ሃሳብዎን አሰርዞ የገዙትን መድኃኒት የሚያስመልስ ምን ተአምር ተፈጠረ?! ቅድም የማይመለከተኝን ነገር ሲዘላብዱልኝ ነበር እኮ” አረጋዊው አንገታቸውን ደፉ። “እኮ ምን ቢፈጠር ነው...?”

“ቤት ሳልደርስ ነው አንተ ዘንድ የመጣሁት”

“ለምን?” የሌሎች ጥያቄ።

“ሰፈርተኞቼ ደጄ ላይ ሲጫጫሁ አየሁ። ባለቤቴን በህይወቷ ልደርስላት አልቻልኩም!” አሉ አረጋዊው ድምጻቸው እየሻከረ። እንባቸው እየወረደ። በመድኃኒት ሻጩ ፊት ላይ ፀፀት ድንጋጤ እየታየ ድፍን መቶ ብር አውጥቶ በሻካራ እጃቸው ላይ አኖረው። ሌሎቹም ኪሶቻቸውን ይፈታትሹ ጀመር።

“ይባርካችሁ ልጆቼ! ከፈን መግዣ ስላልነበረኝ እንጂ... ”እንባ ተናነቃቸው።

መንሰቅሰቃቸውን እየቀጠሉ ወጡ።

ፀጥታ።

ምንጭ፡- እንዳለጌታ ከበደ፣ ከጥቁር ሰማይ ስር፣(1996፡43)

አባሪ አምስት

ቅድመልምምድ አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመለካት የተዘጋጀ ፈተና

ቀን _____

ይህፈተና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን በማስተማር ለተባለው የትምህርት መርሀግብር ለዶክትሬት ፍልስፍና (PhD) የምርምር ፅሁፍ ለማዘጋጀት ታስቦ የቀረበ ነው።

የዚህ ፈተና ዋና አላማም አንተ/አንቺ መረጃ ሰጪ ተማሪ በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ፅሁፎችን አንብቦ የመረዳ ብቃትህ/ሽ ምን እደሚመስል ለመረዳት ነው። የሚሰበሰበው መረጃ ከምርምሩ አላማ ውጪ ለምንም ሌላ ተግባር አይውልም። (ስም መፃፍ አያስፈልግም)

1. የትምህርት ቤት ስም _____ ክፍል _____
2. በክፍል ውስጥ አንተን/አንቺን የሚወክለው ቁጥር _____

አቅጣጫ፡- ውድ መረጃ ሰጪ ተማሪ ከዚህ በታች አንድ ምንባብ ቀርቧል። ከምንባቡ ጋር ተያይዞ አስራ አምስት ጥያቄዎች አሉ። ለእያንዳንዱ ጥያቄ አራት አራት ምርጫዎች ተዘጋጅተዋል። ምንባቡን በጥንቃቄ ካነበብክ/ሽ በኋላ ትክክለኛ የምትለውን/የምትይውን መልስ ፊደል ላይ በማክበብ መልስህን/ሽን አስቀምጥ/ጪ። በጥንቃቄ ማንበብ እና ተገቢ መልስ መስጠት ለሚሰራው ጥናታዊ ፅሁፍ ጠቃሚ መሆኑን አስተውል/አስተውይ።

ምንባብ

ቅርስና የቅርስ አይነቶች

ቅርስ በውስጡ ካካተው ከፍተኛ እሴት አኳያ በተለያዩ አለም አቀፋዊ እና አገር አቀፋዊ መስፈርቶች፣ማለትም ከእድሜው፣ ከውበቱ፣ ከጠቀሜታው፣ ከብርቅዬነቱ... ወዘተ አኳያ በተለያዩ መመዘኛዎች የተመረጠ የተፈጥሮ ስጦታ እና ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የሰው ልጆች የፈጠራ ውጤት ወይም ሁለቱንም በጣምራ (የተፈጥሮ እና ባህላዊ ቅርስን ያያዘ) ያካተተ ነው። ቅርስ ተፈጥሮ የለገሰንን እና የሰው ልጅ በኖረበት ዘመን ያከማቻቸውን የፈጠራ ውጤቶች ሁሉ የሚያካትት በመሆኑ ቁጥሩ እና አይነቱ እጅግ ብዙ ነው። ቅርስን በአራት አይነት ከፍሎ ማየት ይቻላል።

1. ባህላዊ እና ተፈጥሯዊ ቅርስ

ቅርስ ሲባል አብዛኞቻችን የምናስበው ከባህል ጋር በተገናዘበ መልኩ ብቻ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ቅርስ የተመረጡ የተፈጥሮ ስጦታዎችንና የሰው ልጅን የፈጠራ ውጤቶችን ወይም የሁለቱንም ጥምረት የሚያካትት ነው። ከዚህ አንጻር ባህላዊና ተፈጥሯዊ ቅርስ በመባል በሁለት ይከፈላል።

የባህል ቅርስ የተመረጡ የሰው ልጅ የፈጠራ ውጤቶን ማለትም ሀውልቶችን፣ ህንፃዎችን፣ ዋሻዎችን፣ በድንጋይ እና በብራና... ወዘተ. በመሳሰሉት ላይ የተጻፉ ወይም የተቀረጹ ጽሁፎችን፣ ቅርጻ ቅርጾችን፣ አልባሳቶችን፣ እምነቶችን፣ ወጎችን፣ ስርአቶችን... ወዘተ ሁሉ ያካትታል። የተፈጥሮ ቅርስ ደግሞ በላቀ ጠቀሜታቸው የተመረጡ ማራኪ እና ውብ የሆኑ ደኖችን፣ ሐይቆችን፣ ዋሻዎችን፣ ብሔራዊ ፓርኮችን፣ የእንስሳት መጠለያዎችን፣

በአጠቃላይ ህይወት ያላቸውን እና የሌላቸውን ፍጡሮች እና እነርሱም የሚገኙባቸውን ቦታዎች ሁሉ ያካትታል።

2. የአለም ቅርስ እና ብሔራዊ ቅርስ

ቅርስ ካለው ጠቀሜታ አንጻር የአለም ቅርስ እና ብሔራዊ ቅርስ በሚል በሁለት ይከፈላል። አንድ ቅርስ (የባህል፣ የተፈጥሮ እና ሁለቱንም በጣምራ ያካተተ ቅርስ) የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት ባወጣው መመዘኛ መሰረት በውስጡ የላቀ አለም አቀፍ እሴት ካለው፣ የአለም ህዝቦች ሊያደንቁት፣ ሊማሩበት እና ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ከሆነ በአለም ቅርስነት ተመዝግቦ የአለም ቅርስ በመባል ይታወቃል። ብሔራዊ ቅርስን በተመለከተ ደግሞ እያንዳንዱ መንግስት ባወጣው መመዘኛ መሰረት ማንኛውም ብሔራዊ እሴት ያለው ቅርስ (የባህል፣ የተፈጥሮ እና ሁለቱንም በጣምራ ያከተተ ቅርስ) ህዝቦች ሊያደንቁት፣ ሊማሩበት እና ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ከሆነ በብሔራዊ ቅርስነት ተመዝግቦ ብሔራዊ ቅርስ በመባል ይታወቃል።

በዩኔስኮ የውሳኔ ሰነድ መሰረት የአለም የባህል ቅርስ የሚባሉት ሐውልቶች፣ ሕንጻዎች፣ ከታሪክ፣ ከስነ ጥበብ እና ከሳይንስ አንጻር የላቀ አለም አቀፍ እሴት ያላቸው ቦታዎች፣ የተፈጥሮ እና የሰው ስራዎችን በአንድ ላይ ያጣመሩ የቁፋሮ ቦታዎችንም ያካትታል።

3. ተንቀሳቃሽ እና የማይነቀሳቀስ ቅርስ

ከአይነቱ ከተፈጥሮው እና ከመጠኑ አንጻር ቅርስ ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ተብሎ በሁለት ይከፈላል። ተንቀሳቃሽ የሚባለው በቀላሉ ከቦታ ወደቦታ ሊንቀሳቀስ ወይም ሊወሰድ የሚችል የቅርስ አይነት ነው። ለምሳሌ በቅርስነት የተመዘገቡ በብራና ላይ የተጻፉ ጽሁፎች፣ አልባሳት በተለያለዩ ቁሳቁሶች (ከእንጨት፣ ከብረት፣ከሸክላ ከድንጋይ ከወርቅ... ወዘተ) የተሰሩ እቃዎች እናቅርፃቅርፆች መጠናቸው አነስተኛየሆነ በቁፋሮ የተገኙ ጥናታዊ የመገልገያ እቃዎች... ወዘተ በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ ሊንቀሳቀሱ ወይም ሊወሰዱ ስለሚችሉ ተንቀሳቃሽ ቅርስ በመባል ይታወቃሉ።

የማይንቀሳይስ የሚባለው በቀላሉ ካለበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሊንቀሳቀስ ወይም ሊወሰድ የማይችል የቅርስ አይነት ነው። ለምሳሌ የላሊበላ ውቀር አብያተ ክርስትያናት፣ ታሪካዊ የሐረር ከተማ ጆጎል ግንብ፣ የአል-ነጃሺ መስጊድ፣ የሰሜን ብሔራዊ ፓርክ... ወዘተ ይጠቀሳሉ። በአለም ቅርስነትም የተመዘገቡ ናቸው። አፈጣጠራቸው ከግዘፈታቸው እና ከሚገኙባቸው ቦታዎች አኳያ በቀላሉ ለማንቀሳቀስ አይቻልም።

4. ተጨባጭ እና ተጨባጭ ያሆነ ቅርስ

ልናየው፣ ልንዳስሰው፣ ልናሽተው... ወዘተ በአጠቃላይ በሁሉም ስሜት ህዋሳቶቻችን ልንገነዘበው የምንችለው ተንቀሳቃሽም ሆነ የማይነቀሳቀስ ቅርስ ተጨባጭ ቅርስ በመባል ይታወቃል። ለምሳሌ ሀውልቶች፣ ህንጻዎች ዋሻዎች፣ መጻህፍት፣ የተለያዩ ቅርሳ ቅርሶች፣ አልባሳት... ወዘተ ተጨባጭ ቅርስ በመባል ይታወቃሉ።

ልናየው፣ ልንዳስሰው፣ ልናሽተው... ወዘተ የማንችለው ነገር ግን የውስጥ ስሜታችንን የሚያረካ ቅርስ ተጨባጭ ያልሆነ ቅርስ በመባል ይታወቃል። ወጎች፣ ተረቶች፣ ስርአቶች፣ ማራኪ እይታዎች፣ባህላዊ እና ሃማኖታዊ ስርአቶች ወዘተ ቁሶች አይደሉም። በውስጣቸው ግን መንፈሳችንን የሚያነሳሱ፣ የአእምሮ እርካታንም የሚሰጡን በርካታ እሴቶች አሏቸው። የሰው ልጅ በተፈጥሮው ማወቅን መመራመርን፣ መፍጠርን፣ መደሰትን... ወዘተ፣ ሁሉ ይፈልጋ። ፍላቶጎች ሁሉ ግን በቁሳዊ ፍላጎቶች ብቻ ሊረኩ ከቶውንም አይቻላቸውም። ተጨባጭ ከሆኑት ወይም ከቁሳዊ ፍላጎቶቹ በተጨማሪ ተጨባጭ ወይም ቁሳዊ ያልሆኑ

ፍላጎቶችም አሉት፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ቁሳዊ ያልሆኑና መንፈሳችንን በማነሳሳት የአእምሮ እርካታን የሚሰጡን ነገሮች በቅርስነት ሲመዘገቡ ተጨባጭ ያልሆነ ቅርስ በመባል ይታወቃሉ፡፡

በአጠቃላይ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ቅርሶች የሰውን ልጅ አኗኗር፣ ፖለቲካዊ ፣ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ፣ የህይወት ፍልስፍና ወግ እና ስርአትን የሚያንፀባርቁ የዘመን አሻራዎች ናቸው፡፡

ምንጭ፡- ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፣ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (2004)

ተሸስሎ የተወሰደ

1. በምንባቡ መሰረት ቅርስ ማለትን የማይገልጸው የቱ ነው?
   ሀ. በእድሜ አንጋፋ የሆነ ማንኛውም ቁስ ቅርስ ነው፡፡
   ለ. የተፈጥሮ ስጦታ እና ጠቃሚ ባህላዊ እሴቶች ቅርስ ይባላሉ፡፡
   ሐ. ቅርስ ከእድሜው፣ ከውበቱ፣ ከጠቀሜታው፣ ከብርቅየነቱ አንጻር ሊታይ ይችላል፡፡
   መ. የሰው ልጅ የፈጠራ ውጤት ቅርስ ሊባል ይችላል፡፡
2. ብርቅ የሚለው ቃል ትርጉም _____ ነው፡፡
   ሀ. አዲስ ሐ. ነባር
   ለ. አስገራሚ መ. ትንሽ
3. ተጨባጭ እና ተጨባጭ ያልሆነ ቅርስ ማለትን የሚያዛባው ሐሳብ የቱ ነው?
   ሀ.ተጨባጭ እና ተጨባጭ ያሆነ ቅርስ ተንቃሳቃሽ እና የማይንቀሳቀስ ቅርስ ሊሆን ይችላል፡፡
   ለ. በአይን የማይታይ አእምሯዊ የሆነ ሐሳብ ተጨባጭ እና ተጨባጭ ያሆነ ቅርስ ተብሎ ይከፈላል ፡፡
   ሐ.ተጨባጭ እና ተጨባጭ ያልሆነ ቅርስ በአብዛኛው በአለም አቀፍ ቅርስነት ሲመዘገብ የሀገር ገፅታንለማንፀባረቅ ይረዳል፡፡
   መ. ባህላዊ እና ተፈጠሯዊ ቅርስ ህይወት ያላቸውን እና የሌላቸውን ፍጡሮች ያካትታል፡፡
4. በቁፋሮ የሚገኙ ጥንታዊ የመገልገያ እቃዎች _____ ናቸው፡፡
   ሀ. ተጨባጭ ያልሆኑቅርሶች ሐ. ተጨባጭ ቅርሶች
   ለ. ተፈጥሯዊ እና ተጨባጭ ቅርሶች መ. የማይንቀሳቀሱ ቅርሶች
5. የአለም ቅርስ የሚባሉት ምን መስፈርት ያሟሉናቸው፡፡
   ሀ. አብረቅራቂ እና ትልቅ ከሆኑ
   ለ. በቁፋሮ ከተገኙ
   ሐ. በቆዳ ላይ እና በድንጋይ ላይ ከተጻፉ
   መ. በውስጣቸው ከፍተኛ እሴት ካላቸው፡፡
6. በምንባቡ መሰረት ብራና_____ ነው፡፡
   ሀ. ከፍተኛ ገንዘብ ሐ. ከቆዳ የተሰራ መጻፍያ
   ለ. ጠንካራ ብረት መ. ደማቅ በርሃን
7. ፀሐፊው ማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ምድን ነው?
   ሀ. ቅርሶች የሐገርና የአለም ሐብት መሆናቸውን
   ለ. የሐገራችን ቅርስ እየተመዘበረ መሆኑ
   ሐ. ቅርሶች አይነታቸው ብዙ በመሆኑ መለየት አስቸጋሪ መሆኑን
   መ. ቅርሶች ዋጋቸው ውድ መሆኑን

8.ተፈጥሯዊ ቅርስ ከተዘረዘሩት ከየትኛው ጋር ይመሳሰላል?

ሀ. ከሚንቀሳቀስ እና ከማይንቀሳቀስ ቅርስ ጋር
ለ. ከተጨባጭ እና የማይጨበጥ ቅርስ ጋር
ሐ. ከአለም ቅርስ እና ብሔራዊ ቅርስ ጋር
መ. ሁሉም መልስ ነው

9. በምንባቡ መሰረት እሴት የሚለው ቃል ፍቺ _____ ነው።

ሀ. ዋጋ ሐ.ቀረጥ
ለ.ውበት መ.መጠን

10.በምንባቡ አውድ ማድነቅ የሚለውን ቃል ሊተካ የሚችለው የቱ ነው?
ሀ.ማክበር ሐ.ማምጣት
ለ.ማጥፋት መ.ማውራት

11.ተጨባጭ ያልሆነ ቅርስ ውስጥ የሚካተተው የቱ ነው?
ሀ. ብሔራዊ ፓርኮች ሐ. ሐውልቶች እና ቅርፃቅርፅች
ለ. የተለያዩ እምነታዊ ስርአቶች መ. አልባሳት

12.ጠቀሜታ ላይ የተመሰረተ የቅርስ አከፋፈል_____ ይባላል።
ሀ. ባህላዊ እና ተፈጥሯዊ ቅርስ
ለ. የአለም ቅርስ እና ብሔራዊ ቅርስ
ሐ. ተንቀሳቃሽ እና የማይንቀሳቀስ ቅርስ
መ. ተጨባጭ እና ተጨባጭ ያልሆነ ቅርስ

13.በምንባቡ መሰረት አሻራ የሚለው ቃል ፍቺ _____ ነው።
ሀ.ምልክት ሐ. እንከን
ለ.ጠባሳ መ. እንቅፋት

14.የሰው ልጅ ቅርስ አልባ ቢሆን ምን ጉዳት አለው?
ሀ. የየትኛው ሀገር ዜጋ መሆኑን መለየት አይቻልም ነበር
ለ. እርስ በእርስ በግጭት ይጠፋ ነበር
ሐ. በአንድ ዘመን የነበረን አስተሳሰብ ፣ወግ እና ስርአት መገንዘብ ይቸግር ነበር
መ.የተፈጥሮ አደጋዎች ይበዙ ነበር

15.ቅርስ ተፈጥሮ የለገሰንን እና የሰው ልጅ በኖረበት ዘመን ያከማቻቸውን <u>የፈጠራ ውጤቶች</u> ሁሉ የሚያካትት በመሆኑ ቁጥሩ እና አይነቱ እጅግ ብዙ ነው። በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ከአማራጮቹ የማይገልፀው የቱን ነው?
ሀ. መስጊዶችን እና ቤተክርስትያኖችን ሐ.ወንዞችን እና ፏፏቴዎችን
ለ.ሀውልቶችን እና ቅርፃ ቅርፆችን መ.ቤተመንግስቶችን

አባሪ ስድስት

ድህረልምምድ አንብቦ የመረዳት ብቃትን ለመለካት የቀረበ ፈተና

ቀን _____

ይህ ፈተና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን በማስተማር ለተባለው የትምህርት መርሀ ግብር ለዶክትሬት ፍልስፍና (PhD) የምርምር ፅሁፍ ለማዘጋጀት ታስቦ የቀረበ ነው።

የዚህ ፈተና ዋና አላማም አንተ/አንቺ መረጃ ሰጪ ተማሪ በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ፅሁፎችን አንብቦ የመረዳ ብቃትህ/ሽ ምን እደሚመስል ለመረዳት ነው። የሚሰበሰበው መረጃ ከምርምሩ አላማ ውጪ ለምንም ሌላ ተግባር አይውልም። (ስም መፃፍ አያስፈልግም)

1. የትምህርት ቤት ስም _____ ክፍል _____
2. በክፍል ውስጥ አንተን/አንቺን የሚወክለው ቁጥር _____

አቅጣጫ፡- ውድ መረጃ ሰጪ ተማሪ ከዚህ በታች አንድ ምንባብ ቀርቧል። ከምንባቡ ጋር ተያይዞ አስራ አምስት ጥያቄዎች አሉ። ለእያንዳንዱ ጥያቄ አራት አራት ምርጫዎች ተዘጋጅተዋል። ምንባቡን በጥንቃቄ ካነበብክ/ሽ በኋላ ትክክለኛ የምትለውን/የምትይውን መልስ ፊደል ላይ በማክበብ መልስህን/ሽን አስቀምጥ/ጪ። በጥንቃቄ ማንበብ እና ተገቢ መልስ መስጠት ለሚሰራው ጥናታዊ ፅሁፍ ጠቃሚ መሆኑን አስተውል/አስተውይ።

ምንባብ

ጆሮና መስማት

የመስማት ችሎታ እንደ ትልቅ ሐብት ሊቆጠር የሚገባ ውድ ስጦታ ነው። ብዙዎቻችን ግን ይህንን ልብ አንልም። ትልቅ ሐብትነቱን የምንረዳው በህመም ወይም በሌላ ድንገተኛ ክስተት መስማት ሳንችል ስንቀር(ስንታወክ)አልያም እድሜያችን እየገፋ እና የመስማት ችሎቻችንም እየተዳከመ ሲሄድ ነው።

ድንገተኛ ለሆነ ከፍተኛ ድምጽ መጋለጥ በውስጠኛው የጆሮ ክፍል በሚገኙ ብዙ አቅም የሌላቸው ሕዋሳት ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል። ይሁን እንጂ እንደ ፍንዳታ ያለ ከፍተኛ ድምጽ ሲሰማ በተቻለፍጥነት አፋችንን ብንከፍት ይህን ጉዳት ማስቀረት እንችላለን። ምክንያቱም የፍንዳታው ድምጽ በጆሮ ብቻ የሚገባ ከሆነ የድምጽ ግፊት በዚያው በጆሮ ውስጥ ያሉትን ስስ ስሮች ሊበጣጥሳቸው ይችላል። አፋችንን ከከፈትን ግን ድምጹ በሁለቱም በኩል በአፍንጫም በጆሮም የመግባት እድል ያገኛና በመስሚያ አካላት ላይ ሚዛናዊ የድምጽ ግፊት ያርፋል። ይህም ጉዳት አያስከትልም።

በሌላ በኩል አብዛኛውን ጊዜ አንድ ሰው የመስማት ችሎታውን የሚያጣው ጫጫታ በሚበዛባቸው የስራ ቦታዎችና ከፍተኛ ድምፅ ባለባቸው ስፍራዎች ብዙ ጊዜ ሲገኝ እንደሆነ በጥናት ተደርሶበታል። ከፍተኛ የሚባለው ድምጽ ምን አይነት ነው? የሚለው ጥያቄ በውስጣችን ሊፈጠር ይችላል። ድምጽ በሶስት መንገዶች ማለትም በጊዜ፣ በድግግሞሽ እና በኃይል ይመደባል። ጊዜ የሚያመለክተው ድምጹ የሚሰማበትን የጊዜ ርዝመት ነው። የአንድ ድምጽ ድግግሞሽ መጠን ወይም ቃና በሰከንድ ይህን ያል ድግግሞሽ ወይም

ኽርዝነው ተብሎ ይገለጻል። ልንሰማው የምንችለው ልከኛ ድምጽ በሰከንድ ከ 20 እስከ 20 ሺህ የሚበልጥ ድግግሞሽ ሊኖረው ይገባል።

የአንድ ድምጽ ኃይል ወይም ጥንካሬ የሚለካው ደግሞ “ዴሲቤል” በሚል አሃድ ነው። ተራ የሆነ ጭውውት በአማካይ 60 ዴሲቤል የሚያህል ጥንካሬ ይኖረዋል። ከ85 ነጥብ ዴሲቤል ለሚበልጥ የድምጽ መጠን ለረዥም ጊዜ የተጋለጠ ሰው ውሎ አድሮ የመስማት ችሎታውን የማጣት አጋጣሚው ከፍተኛ እንደሚሆን የጆሮ ሐኪሞች ይናገራሉ። ድምጽ በጣም ጮክ ባለ መጠን በጆሮ ላይ የሚያደርሰው ጉዳት የከፋ ይሆናል። “በኒውስዊክ” መጽሄት ላይ የቀረበ አንድ ሪፖርት “ጆሮ አንድ በኤሌክትሪክ የሚሰራ መሰርሰሪያ የሚያሰማውን ድምጽ (100 ዴሲቤል) ለሁለት ሰዓት ያህል መቋቋም ይችላል። በቪዲዮ ማጫወቻ ቦታዎች የሚሰማውን ሁከት ግን (110 ዴሲ ቤል) ከ30 ደቂቃ በላይ መቋቋም አይችልም። የድምጽ መጠን በ10 ዴሲቤል ሲጨምር ጆሮን የመጉዳት ኃይሉ በ10 እጥፍ ይጨምራል” ሲል ገልጻል።

አንድ ድምጽ 120 ዴሲቤል ገደማ ሲደርስ ጆሮ እንደሚያሳምም ሙከራዎች አረጋግጠዋል። አንዳንድ የቤት ውስጥ የሙዚቃ መሳሪዎች ከ140 ዴሲቤል የሚበልጥ ድምጽ ማውጣት ይችላሉ። የተለያዩ ድምጾች የተለያዩ የዴሲቤል መጠን ይኖራቸዋል። ለምሳሌ መተንፈስ 10፣ ማንሾካሾክ 20፣ ጭውውት 60፣ የስራ መግቢና መውጪያ ሰዓት ግርግር 70፣ የመኪናዎች እንቅስቃሴ 80፣ በኤሌክትሪክ የሚሰራ መጋዝ 110፣ አውሮፕላን ሲያርፍ 120፣ የጠብ መንጃ ተኩስ 140 ዴሲቤል ይኖራቸዋል።

ለመሆኑ ድመጽ የምንሰማው እንዴት ነው? ከውጪ አይናችን ኃላ የሚገኘው የጆሮ ክፍል የሚያገለግለው የድምጽ ሞገዶችን ሰብስቦ ወደ ውስጠኛው የጆሮ ክፍል ለማስገባት ነው። ከዚያም የድምጽ ሞገድ ወደ ጆሮ ታምቡር ይደርሳል። የድምጽ ሞገድ የጆሮው ታምቡር እንዲርገበገብ ያደርግና የጆሮ ታምቡሩ በተራው በመካከለኛው ጆሮ ውስጥ የሚገኙት ሶስት አጥንቶች እንዲርገበገቡ ያደርግና የጆሮ ታምቡሩ በተራው በመካከለኛው ጆሮ የሚገኙት አጥንቶች እንዲርገበገቡ ያደርጋል። ቀጥሎ እርግብግቢቱ ፈሳሽ ወደ ተሞላውና በአጥንት ወደ ተከበበው የውስጠኛ ጆሮ ይገባል። ከዚያም የድምጹ አርግብግቢት የቀንድ አውጣ ቅርጽ ባለውና ኮክሊያ በተሰኘው የውስጠኛው ጆሮ ክፍል በሚገኘው ፈሳሽ በኩል ያልፋል። በኮክሊያ ውስጥ ፀጉር መሰል ሕዋሳት ይገኛሉ። በኮክሊያ ውስጥ የሚገኘው ፈሳሽ ፀጉር መሰል ሕዋሳት የላይኛው ክፍላቸውን በማንቀሳቀስ የነርቭ መልእክት እንዲተላለፍ ያደርጋሉ። እነዚህ መልዕክቶች ወደ አንጎል ይተላለፉና ድምፅ ሆነው ይሰማሉ።

ለመስሚያ የሚያገለግለው የአንጎል ክፍል ደግሞ አንጎል ለየትኛው ድምጽ ትኩረት መስጠትና የትኛውን ደግሞ ችላ ብሎ ማለፍ እንደሚኖርበት እንዲለይ ያስችላቸዋል። ለምሳሌ አንዲት እናት ስራ እየሰራች ህፃን ልጅዋ ሲጫወት የሚያሰማውን ድምጽ ሆን ብላ አታዳምጠውም። ደንግጦ በሚጮህበት ጊዜ ግን ወዲያው ብድግ ትላለች። የዚህ ምክንያቱ አንጎሏ ድምጽን የመለየት ስራ ስለሚያካሂድ ነው። በሁለት ጆሯችን የምናዳምጥ መሆናችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚመጡ ድምፆችን ለመስማት ያስችለዋል። ይሁን እንጂ ንግግርየታከለበት ድምጽ ከሆነ አንጎል ሊረዳ የሚችለው በአንድ ጊዜ አንድ መልእክት ብቻ ነው። ሌሎችን ድምጾች ይሰማቸዋል እንጂ አይረዳቸውም። ለማንኛውም በጣም ጮክ ያለ ድምጽ መስማት የጆሮ የመስማት አቅም እየቀነሰ እንደሚመጣ መረዳቱ ጠቃሚ ነው። ከ90 ዴሲቤል በላይ መጠን ላለመጋለጥ መጣርም ይገባል።

ምንጭ፡-አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ሐምሌ 24/1994ዓ.ም.

1. የመስማት ችሎታ እንደ ትልቅ ሀብት ሊቆጠር የሚገባ ውድ ስጦታ ነው። ብዙዎችን ግን ይህንን ልብ አንልም። በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ሐረግ ትርጉም_ ነው?
   ሀ. አናገኘውም ሐ. አናስበውም
   ለ. አንመኘውም መ. አንጠብቀውም
2. በምንባቡ መሰረት ድንገተኛ ለሆነ ከፍተኛ ድምጽ ስንጋለጥ ማድረግ ያለብን_____ ነው።
   ሀ. ጆሯችንን መድፈን ሐ. ድምጽ በሌለበት አካባቢ መኖር
   ለ. አፋችንን መክፈት መ. መሸሽ
3. የድምፅ መለኪያ _____ ነው።
   ሀ. ሕዋስ ሐ. ኸርዝ
   ለ. ዴሲቤል መ. ኮክሊያ
4. በምባቡ መሰረት ድምጽ እንዲሰማ ከሚያስፈልገን ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?
   ሀ. ዴሲቤል ሐ. የድምጽ ሞገድ
   ለ. የጆሮ የውጨኛው ክፍል መ. የጆሮ ታምቡር እርግብግቢት
5. የምባቡ መልእክት _____ ነው
   ሀ. ድምፅ በተለያየ መንገድ ይመደባል ሐ. መጠነኛ ድምጽ ለጤናማ ጆሮ
   ለ. ድምጽ እንዴት ይሰማል መ. እናቶች ለህጻናት ትኩረት ይስጡ
6. በጣም ጮክ ያለ ድምጽ መስማት የጆሮን የመስማት አቅም እየቀነሰው እንደሚመጣ መረዳቱ ጠቃሚ ነው። በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ትርጉም ____ ነው።
   ሀ. ፀጥ ለ. ከፍ ሐ. ፈጠነ መ. ዝግ
7. የ 6 ኛው አንቀጽ ትኩረት ምንድን ነው?
   ሀ. ድምጽ እንዴት እንደሚፈጠር ሐ. ድምጽን እንዴት እንደምንሰማ
   ለ. ድምጽ ለጆሮ እንዴት ጠንካራ እንደሆነ መ. የጆሮ አፈጣጠር ምን እንደሚመስል
8. ይህ ምንባብ ርዕሱ ይቀየር ቢባል ሊስማማው የሚችለው የቱ ነው?
   ሀ. የጆሮን ጤንነት መጠበቅ ሐ. ከፍተኛ ድምጽ
   ለ. መስማት ጠቃሚ ነው መ. መስማትን መለማመድ
9. ሆን ብላ ሲል _____ ማለቱ ነው።
   ሀ. ተቆጥታ ሐ. አስባ
   ለ. በተንኮል መ. ደንግጣ
10. በምንባቡ መሰረት ከሚከተሉት አንዱ ስህተት ነው
   ሀ. ድንገተኛ ድምጽ በጆሮ ብቻ የሚገባ ከሆነ የድምጹ ግፊት በጆሮ ውስጥ ያሉትን ስራ ስሮች ይበጣጥሳል።
   ለ. ልንሰማው የምንችለው ወይም የሚገባው ልክኛ ድምጽ ከ20 እስከ 20 ሺህ የሚበልጥ ርግብግቦሽ ሊኖረው ይገባል።
   ሐ. ለከፍተኛ የድምጽ ዲሲቤል የተጋለጠ ሰው የመስማት ችሎታውእየጠነከረ ይመጣል
   መ. የድምጽ መጠን በ10 ዴሲቤል ሲጨምር ጆሮን የመጉዳት ኃይሉ 10 እጥፍ ይጨምራል።
11. በአንቀፅ አራት እና አምስት ከተዘረዘሩት የድምፅ መከሰቻዎች ለጆሮ ተስማሚ ሊሆን የሚችለው የድምፅ መጠን የቱ ነው?
   ሀ.60 ዴሲ ቤል ለ.85 ዴሲ ቤል ሐ.100 ዴሲ ቤል መ.120 ዴሲ ቤል
12. በምንባቡ መሰረት ኸርዝ ምንድን ነው?
   ሀ.መስማትን የሚያውክ ጫጫታ ሐ.የጆሮ ህመም
   ለ.የድምፅ መለክያ መ.የድምፅ ድግግሞሽ
13.በምንባቡ እንደተገለፀው ህዋስ _____ነው።

ሀ.ስሜት ሐ.ሰውነት የተገነባበት ደቂቀ አካል
ለ.በሽታ አምጪ ተህዋስ መ. የጆሮ የውጨኛው ክፍል

14.ሰዎች የመስማትን ጥቅም የበለጠ ከሚረዱበት መንገድ ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?

ሀ. መስማት ሲሰለቻቸው
ለ. በህመም ምክንያት መስማት ሲቸገሩ
ሐ. በእድሜ መግፋት ምክንያት መስማት ሳይችሉ ሲቀሩ
መ.ድንገተኛ በሆነ ክስተት ሲታወኩ

15.በምንባቡ መሰረት ማንሾካሾክ የሚለው ቃል ፍቺ _____ ነው

ሀ.ማንኳኳት ሐ.መጋጨት
ለ.ቀስ ብሎ ማውራት መ.መጣራት

አባሪ ሰባት

ቅድመ እና ድህረልምምድ የማንበብ ብልሃት ግንዛቤ ለመፈተሽ የቀረበ ፈተና በናሙና ጥናቱ ተግባራዊ የተደረገ (ለሙከራ ቡድን)

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ አንተ/አንቺ መረጃ ሰጪ ተማሪ በማንበብ ብልሃት ዙርያ ያለህን/ ያለሽን ግንዛቤ ለመፈተሽ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

ቀን _____

(ማስታወሻ- ይህ መጠይቅ ለአቀራረብ አመቺ እንዲሆን በማሰብ ተባዕታይ ያታን መጠቀም አስፈልጓል።)

አቅጣጫ፡- ውድ መረጃ ሰጪ ተማሪ ከዚህ በታች አስራ አምስት ጥያቄዎች ቀርበዋል። እያንዳንዱ ጥያቄ አራት አራት ምርጫዎች አሉት። አንተ መረጃ ሰጪ ተማሪ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል ነው ብለህ የምታምንበትንመልስ በምርጫው ፊደል ላይ በማክበብ አመልክት። ለአንድ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ አንድ ብቻ ነው።

1.አንድን የቀረበ ፅሁፍ ለማንበብ ስትዘጋጅ ከሚከተሉት የትኛውን ትተገብራለህ?

ሀ.የማንበብ አላማን ማስቀመጥ ሐ. ራስን መጠየቅ

ለ.ሀሳቡን በራስ መንገድ መፃፍመ.በዋናው ሀሳብ ስር ማስመር ወይም ምልክት ማድረግ

2. የቀረበ ፅሑፍ ይዘትን ለመረዳት ርዕሱን እና ንኡሳን ርእሶችን በማስተዋል በቅድመ ንባብ ጊዜ ምን ታደርጋለህ?
   ሀ. ማስታወሻ እይዛለሁ ሐ. ጥያቄ እጠይቃለሁ
   ለ. እተነብያለሁ (predicting) መ. በዋና ዋና ሐሳቦች ስር አሰምራለሁ
3. ለማንበብ ተግባር የቀረበውን ፅሁፍ በምታነብበት ወቅት ዋናውን ሐሳብ በፍጥነት ለይቶ ለማውጣት ከምታደርጋቸው ተግባራት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?
   ሀ. ማስታወሻ መያዝ
   ለ. በፍጥነት የዳሰሳ ንባብ እና በፍጥነት አገላብጦ መመልከት ንባብ ማድረግ
   ሐ. ድምፅን ከፍ አድርጎ ማንበብ
   መ.የምንባቡን ሐሳብ በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ
4. የቀረበን ፅሁፍ በቀላሉ ለመረዳት እና በፅሁፍ ውስጥ ያሉትን ቁልፍ ቁልፍ ጉዳዮች ምንባቡን ከአነበብክ በኋላ ለማስታወስ በመንባቡ ወቅት ምን ታደርጋለህ?
   ሀ. የምንባቡን ሐሳብ እተረጉማለሁ
   ለ. ደጋግሜ አነባለሁ
   ሐ. በዋና ዋና ሐሳቦች ስር ምልክት እጠቀማለሁ
   መ. በሀ፣ለ፣ሐ የተጠቀሱትን አደርጋለሁ
5. በምታነብበት ጊዜ የቀረበውን ፅሁፍ አስቀድመህ ከምታውቀው ሐሳብ ጋር ለማስተሳሰር ምን ታደርጋለህ?
   ሀ. በምንባቡ ውስጥ ያለውን ገለፃ በማጤን እተነትናለሁ

ለ. በምንባቡ ውስጥ ያለውን ሀሳብ ሁሉ ለመረዳት እገምታለሁ
ሐ. ምንባቡን እንዳለ በራስ ቋንቋ እተረጉማለሁ
መ. ምንባቡ ስለያዘው ሐሳብ አስቀድሜ የማውቀውን ለማስታወስ እሞክራለሁ

6. በቀረበ አንድ ዕሁፍ በተለይ በሶስተኛው አንቀጽ የተካተተውን ሐሳብ ፈጥነህ መረዳት ከተቸገርክ ምን ታደርጋለህ?
ሀ. እገምታለሁ ሐ. አንቀጹን ደጋግሜ አነባለሁ
ለ. ራሴን እጠይቃለሁ መ. ማስታወሻ እይዛለሁ

7. በምንባቡ ውስጥ ዋናውን ሐሳብ የተሸከሙ ቁልፍ ቃላትን በቀላሉ ለመረዳት ከሚከተሉት የትኛው ዝቅተኛ አገልግሎት አለው ትላለህ?
ሀ. የቃላቱን ትርጉም በአውድ መተርጎም
ለ. መዝገበ ቃላት ካለ መጠቀም
ሐ. ለመረዳት የሚያስቸግሩ ቃላትን መተው
መ. ቃላቱን በራስ ቋንቋ መተርጎም

8. በቀረበ ምንባብ ውስጥ ዋናውን ሐሳብ ነጥሎ ለማውጣት እንዲያስችል ከሚከተሉት የትኛውን ትተገብራለህ?
ሀ. እተረጉማለሁ ሐ. ዋናውን ሐሳብ ፈልፍዬ ለማውጣት እጥራለሁ
ለ. የማንበብ ብሃቶችን ሸግግር አደርጋለሁ መ. ማስታወሻ እይዛለሁ

9. በአንድ ቋንቋ (ለምሳሌ በአማርኛ)አንድ ምንባብ ቀርቦ በምንባቡ ውስጥ ያለውን ሐሳብ የበለጠ ለመረዳት ምን ታደርጋለህ?
ሀ. ወደ ሶማልኛ ቋንቋ ለመተርጎም እሞክራለሁ
ለ. ራሴን ለምን እንዳልገባኝ እጠይቃለሁ
ሐ. ማስተወሻ እይዛለሁ
መ. እገምታለሁ

10. አንድ የቀረበን ምንባብ ካነበብክ በኋላ የምንባቡን አጠቃላይ ሐሳብ የበለጠ ለመረዳት ምን ታደርጋለህ
ሀ. እተረጉማለሁ
ለ. የምንባቡን አጠቃላይ ሐሳብ በራሴ መንገድ አሳጥሬ አዕፋለሁ
ሐ. የቀደመ እውቀቴን እጠቀማለሁ
መ. መዝገበ ቃላት እጠቀማለሁ

11. የማንበብ ተግባር በክፍል ውስጥ የሚካሄድ እንደመሆኑ የቀረበውን ዕሁፍ አንብበህ እንደጨረስክ አንተ የተረዳኸውን የበለጠ ለማጎልበት እና ያልገባህን ለማጥራት ምን ታደርጋለህ?
ሀ. አሰተማሪዬን እጠይቀለሁ ሐ. በክፍል ውስጥ ካሉ ጓደኞቼ ጋር አወያያለሁ
ለ. ግምት ላይ አተኩራለሁ መ. ሀ እና ሐ ተግባራዊ አደርጋለሁ

12. ምንባቡን አንብበህ ከጨረስክ በኋላ ያነበብከውን ምንባብ በትክክል መረዳትህን ለማረጋገጥ ምን ታደርጋለህ?
ሀ. የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት ምንባቡ የገባኝ መሆኑን ራሴን እገመግማለሁ
ለ. ምንባቡን በጠቅላላ ወደራሴ ቋንቀ እተረጉማለሁ

ሐ. እተነብያለሁ

መ. በዋና ዋና ሐሳቦች ስር አሰምራለሁ ወይም ምልክት አደርጋለሁ

13.ፅሁፍን በማንበብ ሒደት ከሚከተሉት ትክክል ነው ብለህ የምታስበው የቱን ነው?

ሀ.የምንባቡን አጠቃላይ ሐሳብ በአእምሮዬ ውስጥ ምስል እንደፈጥር በማድረግ ለመረዳት መሞከር

ለ. ርዕሱን በመመልከት የምንባቡ ይዘት ከባድ ነው ብለህ ካሰብክ ምንባቡን መተው

ሐ.በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ቃላት ለመረዳት እና ለመተርጎም ጥረት ማድረግ

መ. ሁሉንም ሐሳብ ለማግኘት ግምት ላይ ማተኮር

14.ከሚከተሉት አንዱ በማንበብ ጊዜ (while reading) የሚከናወን ነው

ሀ. መረዳትን እና ራስን መቆጣጠር

ለ. ደጋግሞ መለማመድ

ሐ. የቀረበውን ምንባብ በትክክል ስለመረዳቱ ራሴን መገምገም

መ. ራስን መጠየቅ

15.የቀረበን ፅሁፍ ለመረዳት ከሚከተሉት አንድ ትክክል አይደለም?

ሀ. በፅሁፍ ውስጥ ያለውን ዋና ሐሳብ በመገመት መረዳት

ለ. በአማርኛ ቋንቋ የቀረበን ፅሁፍ ለመረዳት በሶማልኛ ቋንቋ ያለን የማንበብ ብልሃት ወደ አማርኛ ቋንቋ ማሸጋገር

ሐ. በምንባቡ ውስጥ ያለን ሐሳብ ለመረዳት ጥያቄዎች አዘጋጅቶ ራስን መጠየቅ እና መልስ ማፈላለግ

መ. በፅሁፍ ውስጥ የቀረበን ትንታኔ እያነፃፀሩ ለመረዳት መሞከር

አባሪ ስምንት
ቅድመ እና ድህረልምምድ የማንበብ ብልሃትአሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ (ለሙከራ ቡድን)

ቀን _____

ይህ ፈተና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን በማስተማር ለተባለው የትምህርት መርሀ ግብር ለዶክትሬት ፍልስፍና (PhD) የምርምር ፅሁፍ ለማዘጋጀት ታስቦ የቀረበ ነው።

የዚህ የጽሁፍ መጠይቅ አላማ አንተ/አንቺ መረጃ ሰጪ ተማሪ በአማርኛ ቋንቋ የቀረበን ጽሁፍ በምታነብበት/ቢበት ጊዜ የምትጠቀምበት/ሚበት የማንበብ ብልሃት ምን እንደሚመስል መረጃ ለማግኘት ነው። የሚሰበሰበው መረጃ ከምርምሩ አላማ ውጪ ለምንም ሌላ ተግባር አይውልም። (ስም መፃፍ አያስፈልግም)

የትምህርት ቤት ስም _____ ክፍል _____

በክፍል ውስጥ አንተን/አንቺን የሚወክለው የክፍል ቁጥር _____

ክፍል አንድ

አቅጣጫ፡-ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ውስጥ የቀረቡትን ዝርዝር ሐሳቦች በጥሞና አንብብ/አንብቢ።ከተዘረዘሩት በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ፅሁፎችን በማንበብ ወቅት የምትጠቀምበት/ሚበት ከሆነ በምን ያህል መጠን እንደምትጠቀምበት/ሚበት 1፣2፣ 3፣ 4፣ 5 ተብለው ከተቀመጡት አማራጮች አንዱን መርጠህ/ሽ በማክበብ አስረዳ/ጂ።ቁጥሮቹ የየራሳቸው ትርጉም አላቸው። መረጃውን በጥንቃቄ መስጠት ተገቢ ነው። ለአንድ መጠይቅ የምትሰጠው/ጪው መልስ አንድ ብቻ ነው። ማንኛውም ጥያቄ ካለህ/ሽ መጠይቁን የሚያስሞላውን መምህር ማናገር ትችላለህ/ትችያለሽ። ከ1-5 ያሉት ቁጥሮች ያላቸው ትርጉም የሚከተለው ነው።

1 በጭራሽ አልጠቀምም፣
2 አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ፣
3 አንድ አንድ ጊዜ እጠቀማለሁ (50% ያህል)፣
4 አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፣
5 ሁልጊዜ እጠቀማለሁ

ማሳሰቢያ፡- በዚህ መጠይቅ ትክክለኛ ወይም ስህተት የሆነ መልስ ስለሌለ የአንተን/የአንቺን ሐሳብ ብቻ አመልክት/ቺ።

ተ.ቁ	የማንበብ ብልሃትን የሚያመላክት ዝርዝር	የአጠቃቀም ሁኔታ				
1	የቀረበው ምንባብ ስለምን ጉዳይ እንደሚዘረዝር ርዕሱን እና ንዑሳን ርዕሶችንእንዲሁም የአንቀፅ መጀመሪያ አረፍተ ነገሮችን በማንበብየምንባቡን ሀሳብ እተነብያለሁ።	1	2	3	4	5
2	ምንባቡን ለማንበብ የተወሰነ ጊዜ እመድባለሁ፣ ለማንበብ ስዘጋጅ የማንበብ ግቤን አስቀምጣለሁ (ምን አጠቃላይ እና ዝርዝር መረጃ ማግኘት እንዳለብኝ አስባለሁ)።	1	2	3	4	5
3	ከቀረበ አንድ ፅሁፍ ውስጥ ዋናውን ሐሳብ ለማግኘት ምንባቡን መጀመሪያ በፍጥነት ካየሁ በኋላ ዝርዝር ሐሳብ ለማግኘት አነባለሁ።	1	2	3	4	5

4	የቀረበ አንድ ፅሁፍ በማነብበት ወቅት በምንባቡ ውስጥ ያለውን ዝርዝር እና ጠቃሚ መረጃ ፈልፍዬ (ፈልጌ) ለማግኘት ጥረት አደግጋለሁ።	1	2	3	4	5
5	ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን በማስታወሻ እይዛለሁ (ለምሳሌ ጠቃሚ ቃላት፣ ግልጽ ያልሆኑ (አዳዲስ) ቃላት፣ዋና ሐሳብ፣ዝርዝር ሀሳብ ወዘተ)።	1	2	3	4	5
6	የመረዳት ችግር ከገጠመኝ ወደኋላ መለስ ብዬ ያልገባኝን አረፍተ ነገር፣አንቀፅ ወይም ሙሉውን ምንባብ አነባለሁ።	1	2	3	4	5
7	ባነበብኩት መሰረት በአእምሮዬ ውስጥ ያለውን ሐሳብ በራሴ መንገድ አሳጥሬ እፅፋለሁ። በራሴ መንገድ አሳጥሬ የፃፍኩት ጭምቀ ሀሳብ ከምንባቡ መልእክት ጋር መዛመዱንም አረጋግጣለሁ።	1	2	3	4	5
8	በማነብበት ወቅት ምንባቡ እንደገባኝ እና እንዳልገባኝ ጥያቄ እጠይቃለሁ(ለምሳሌ፦ የምንባቡ ዋና ሀሳብ ምንድን ነው? ምን ምን ዝርዝር ሀሳቦች ቀርበዋል? የማነበው እና የማውቀው ምን ያህል ይዛመዳል? የአረፍተ ነገር አወቃቀቀር፣ የሰዋስው ህግ፣ ቃላት ወዘተ ገብቶኛል ወይ ?) በተጨማሪ ምንባቡ እንዲገባኝ ጓደኞቼን እና መምህሬን እጠይቃለሁ።	1	2	3	4	5
9	የቀረበ አንድ ምንባብ በማነብበት ወቅት የምንባቡ ሀሳብ የበለጠ እንዲገባኝ የምንባቡን ሀሳብ ከቀደመ እውቀቴ ጋር ለማገናኘት ጥረት አደርጋለሁ።	1	2	3	4	5
10	በማነብበት ወቀት ሌላ ነገር ማሰብ አቆማለሁ፣ የምንባቡን ዝርዝር ሐሳብ በምን ያህል ደረጃ እንደተረዳሁ እፈትሻለሁ፤ በዚህ መሰረት የተነሳሁበትንየማንበብ ግብ ካላሳካሁ የአነባበብ ስልቴን እቀይራለሁ።	1	2	3	4	5
11	በምንባቡ ውስጥ ያሉትን አዳዲስ ቃላት ፍቺ ለመረዳት ቃላቱ በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ ፍቺ ለመረዳት እጥራለሁ።	1	2	3	4	5
12	በማነበው ፅሁፍ ውስጥ የማላውቀው ሀሳብ በቃል (በቃላት) ወይም በሀረግ ደረጃከገጠመኝ የማውቀውን መሰረት በማድረግ (የቃል ክፍል፣ ቅጥያ) የቃሉን (ቃላቱን) ፍቺ ለማግኘት እገምታለሁ።	1	2	3	4	5
13	አስቀድሜ የገመትኩት ትክክል መሆኑን አረጋግጣለሁ።ፀሐፊው ሊያስተላልፍ የፈለገው ሀሳብ ላይ ትኩረት በማድረግ የማይዛመድን ሀሳብ ከአእምሮዬ ማስወገዴን አረጋግጣለሁ፣በተሰጠው የማንበብ ተግባር መሰረት የማንበብ ብልሃቴ በትክክል ተግባራዊ ማድረጌን አጣራለሁ፣ምንባቡን አንብቤ እንደጨረስኩ ጠቅለል አድጌ በራሴ መንገድ የፃፍኩትን እና ምንባቡን በማንበብ ያገኘሁት ሐሳብ መዛመዱን አረጋግጣለሁ፣ በአጠቃላይ የማንበብ አላማዬ መሳካቱን አረጋግጣለሁ።	1	2	3	4	5
14	በሶማልኛ ቋንቋ የምጠቀምበትን የማንበብ ብልሃት በአማርኛ ቋንቋ ሳነብ ለመጠቀም እጥራለሁ፤በአማርኛ ቋንቋ የምጠቀምበትን የማንበብ ብልሃት በሶማልኛ ቋንቋ ሳነብ እጠቀማለሁ።	1	2	3	4	5
15	አንድን የቀረበ ፅሁፍ በማነብበት ጊዜ የምንባቡን ሀሳብ የበለጠ ለመረዳት በክፍል ውስጥ ካሉ ሌሎች ተማሪዎች ጋር ተባብሬ እወያያለሁ፣ሀሳቤን እገልፃለሁ፣ያልገባኝን እጠይቃለሁ	1	2	3	4	5
16	የፅሁፉን አጠቃላይ ገፅታ ለመረዳት የፅሁፉን ይዘት እና ቅርፅ በአእምሮዬ ምስል እንዲፈጥር አደርጋለሁ	1	2	3	4	5
17	በማነብበት ጊዜ ፀሀፊው ምን ለማለት እንደፈለገ እና ቀጣዩ ሀሳብ ደግሞ ምን እንደሆነ እተነብያለሁ	1	2	3	4	5
18	ለንባብ በቀረበ ፅሁፍ ውስጥ በጥልቀት የማነበውን እና ብዙ ትኩረት	1	2	3	4	5

	የማልሰጥበትን ሀሳብ በመለየት አነባለሁ					
19	ዋናውን እና ዝርዝር ሀሳቦችን ለማግኘት በሚያስችል መለረኩ የማንበብ ፍትነቴን አስተካክላለሁ	1	2	3	4	5
20	የማነበው ፅሁፍ እንዲገባኝ እና ጠቃሚ መረጃዎችን ከምንባቡ ውስጥ ፈልፍዬ ለማውጣት በተመጠነ ፍጥነት እና በጥንቃቄ አነባለሁ	1	2	3	4	5
21	በማነብበት ወቅት አዳዲስ መረጃዎችን ለማስታወስ እንዲያስችለኝ ዋና ዋና ጉዳዮችን በማስታወሻ እይዛለሁ	1	2	3	4	5
22	ያነበብኩት ሲከብደኝ እና በሀሳቦች መካከል ያለውን ዝምድና ለማጤን ያነበብኩትን ተመልሼ አነባለሁ	1	2	3	4	5
23	የቀረበውን ፅሁፍ ካነበብኩ በኋላ በምንባቡ ውስጥ ያለውን ጠቃሚ ሀሳብ በሚያንፀባርቅ መልኩ ፅሁፉን አሳጥሬ ጭምቀ ሀሳብ እፅፋለሁ	1	2	3	4	5
24	ከምንባቡ ጋር ተያይዘው የቀረቡ ጥያቄዎች ካሉ በምንባቡ መሰረት ጥያቄዎችን መመለስ መቻሌን ለማረጋገጥ ራሴን እጠይቃለሁ	1	2	3	4	5
25	በማነብበት ወቅት ፅሁፉን ለመረዳት እንድችል ከቀረበው ምንባብ ጋር በተያያዘ ምን እንደማውቅ አስባለሁ	1	2	3	4	5
26	በማነብበት ወቅት በየተወሰነ ቦታ እየቆምኩ የማነበው ምን እንደሆነ አስባለሁ፡፡ በዚህም የማንበብ አላማዬ መሳካቱን እቆጣጠራለሁ	1	2	3	4	5
27	አዳዲስ ቃላትን በተናጠል (ለየብቻ)ሳልመለከት በአውዳቸው ያላቸውን ፍች ለማግኘት አነባለሁ	1	2	3	4	5
28	የማላውቃቸው አዳዲስ ቃላት ወይም ሀረጎች ካሉ ፍቻቸውን እገምታለሁ፡፡ ግምቴም ትክክል መሆኑን አረጋግጣለሁ	1	2	3	4	5
29	የምንባቡን ዝርዝር ሀሳብ በምን ያህል ደረጃ እንደተረዳሁ እፈትሻለሁ፡፡ በዚህም መሰረት የተነሳሁበትን ግብ ካላሳካሁ የአነባበብ ስልቴን እቀይራለሁ	1	2	3	4	5
30	የማንበብ ብልሃቶቼን ከአንድ አዲስ ሁኔታ ወደሌላ አዲስ ሁኔታ ወይም ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ እያሸጋገርኩ እጠቀማለሁ(ከአማርኛ ወደሶማልኛ/ ከሶማልኛ ወደአማርኛ)	1	2	3	4	5
31	ያነበብኩትን ፅሁፍ መረዳቴን ለማረጋገጥ ከሌሎች ጋር እወያያለሁ	1	2	3	4	5
32	የማነበውን ለማስታወስ እንድችል በፅሁፉ ውስጥ ያሉት ክስተቶች በአእምሮዬ ውስጥ ምስል እንዲፈጥሩ ለማድረግ እጥራለሁ	1	2	3	4	5

Mokhtari and Sheory (2002)፣ Mokhtari and Reichard (2002)

ክፍል ሁለት

ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ አንብቦ ለመረዳት ምን ምን የማንበብ ብልሃቶችን ተጠቀምክ/ሽ ግለፅ/ግለጭ

ኢትዮጵያዊው ጤፍ

በዚህ ዘመን በአለም አቀፍ ደረጃ “ታላቅ እህል”(ሱፐር ግሬይን) በመባል እውቅናን እያገኘ ያለው ሰብል ኢትዮጵያዊው ጤፍ እንደሆ ቢቢሲ፣ አልጀዚራ፣ሲኤንኤንን ጨምሮ ሌሎች ታዋቂ አለም አቀፍ የብዙሃን መገናኛዎች እየዘገቡ ነው። ጤፍን አስመልክቶ “ኢዝ ጤፍ ዘ ኒው ሱፐር ፉድ” በሚል እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር በ2006 ዓ.ም ዋሽንግተን ፖስት ያወጣው ዘገባ እንዳመለከተው ጤፍ በየትኛውም የአየር ንብረት የሚበቅል ተመራጭ እህል እንደሆነ ገልፀዋል። ጤፍ ኢትዮጵያ ውስጥ ከተለመደው እንጀራ በተጨማሪ በዳቦ ፣በፓንኬክ እንዲሁም በብስኩቶች መልክ ሊበላ እንደሚችል ይገለፃል። ጥናቶች እንዳመላከቱት ጤፍ ከሌሎች እህሎች በተለየ መልኩ 50 በመቶ ብልጫ ፕሮቲን ፣አምስት እጥፍ ፋይበር (አሰር) እንዲሁም ከሩዝ የበለጠ ካልሺም እንደያዘም ታውቋል። ከምግብ ጋር የተያያዘው ”ፉድስ ፎር ቤተር ሄልዝ” የተባለው ድረገፅ እንዳስረዳው ጤፍ በካልሺም፣በማንጋኔዝ እንዲሁም በአይረን የበለፀገ እንደሆነ ዘግበዋል። ድረገፁ እንዳስረዳው ከሌሎች እህሎች በተለየ (ባልተለመደ) መልኩ ጤፍ ቫይታሚን ሲ የተባለውን ጠቃሚ ንጥረ ነገር ይዟል። የተለያዩ የምርምር ስራዎች እንዳመላከቱትም ጤፍ ከፍተኛ የሆነ ካርቦሃይድሬት ቢይዝም ግሊስማክ የሚባለው እና በደም ውስጥ ያለው የስኳር መጠን የሚመለክተው ንጥረ ነገር ዝቅተኛ እንደሆነ ታውቋል። ኢትዮጵያ ይህንን የልብ ህመምን የሚቀንሰው፣ ከኮሌስትሮል እንዲሁም ከአላስፈላጊ ውፍረት (ኦብሴስ) እና የስኳር ህመም የሚከላከለውን ምርጥ ሰብል የባለቤትነት መብት በማስከበር ለአለም ገበያ ልታቀርበው እንደሚገባ ብዙዎች ያስረዳሉ።

ምንጭ፡- ሪፖርተር ጋዜጣ ፣ ሰኔ 10 /2007 ዓ.ም

አባሪ ዘጠኝ

ቅድመ እናድህረልምምድ በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶመናገር ቃለመጠይቅ (ለሙከራ ቡድን)

ቃለ መጠይቅ፡- (በቃለመጠይቅ ወቅት ቃለመጠይቅ አቅራቢው የሚያቀርባቸው መጠይቆች)

(ማሳሰብያ፡- ቃለመጠይቁ በሚቀርብበት ጊዜ እነደተጠያቂዎቹ ፆታ አቀራረቡ ሊቀያየር ይችላል)

በናሙና ጥናቱ የቀረቡ

ተግባር አንድ፡- ቃለ መጠይቅ (በቃለ መጠይቅ ወቅት ቃለ መጠይቅ አቅራቢው የሚያቀርባቸው መጠይቆች)

ሀ. ከይዘት አንጻር የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ፅሁፉ ስለምን ያወራል?
2. ፀሐፊው ለአንባብያን ማስተላለፍ የፈለገው ምንድን ነው (የጸሐፊው ፍላጎት)?
3. ፅሁፉን ስታነብ መረዳት ተቸግረሃል? ለምን?
4. የቀረበው ፅሁፍ ለመረዳት ከባድ ነው ? ለምን?

ለ. ከብልሃት አጠቃቀም አንጻር የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ርዕሱን እንብበኸዋል? ርዕሱን ስታነብ በአእምሮህ ውስጥ ምን ተከሰተ? በምታነበው/ቢውፅሁፍ ወስጥ ያነሳሀው/ሽው ጥያቄ አለ?ወይምጽሁፉ ምን እንደሚያካትት ገመትክ/ሽ?
2. ምንም ሳታቋርጥ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው አነበብክ? አንቀጾችን ስታነብ በአንቀጽ መሐል ወይም አንቀጹን እንደጨረስክ ማንበብህን አቋረጥክ? የት አቋረጥክ? መቼ አቋረጥክ? ለምን አቋረጥክ? ካቋረጥክ በኋላ ምን አደረክ?
3. በማንበብ ሂደት መደናገር ያጋጠመህ የት ነው? መደናገርህ በተለየ ሁኔታ ምን ፈጠረብህ? በተደናገርክ ጊዜ ምን አደረክ? (በማንበብ ወቅት ወደ ኃላ ተመልሰህ አነበብክ? መቼ እና ለምን? ያነበብከውን ጽሁፍ አስቀድመህ ከምታውቀው (ከቀደመ ልምድና እውቀት ጋር) አገናዘብክ?
4. የማታውቃቸው ወይም እርግጠኛ ያልሆንክባቸው ቃላት በጽሁፉ ውስጥ አሉ? የተወሰኑት የትኞቹ እንደሆኑ መጥቀስ ትችላለህ?

5. ፀሀፊው በጽሁፉ ውስጥ ማስተላለፍ የፈለገውን ሐሳብ በራስህ መንገድ አሳጥረህ መጻፍ ትችላለህ? ይህን የምታደርገው መቼ ነው?
6. የአማርኛ እና የሱማልኛ ጽሁፎችን የምታነበው በተመሳሳይ ወይስ በተለያየ መንገድ ነው ? እንዴት? ምሳሌ መስጠት ትችላለህ?
7. በአጠቃላይ በአማርኛ ቋንቋ ስታነብ የገጠመህ ትልቅ ችግር ምንድን ነው? ይህ የሆነው ለምን ይመስልሃል? ችግሩንስ ለማቃለል ምን ዘዴ ተጠቀምክ (ምን አደረክ)።
8. በአንተ አመለካከት ጸሀፊው ያስተላለፈውን መልእክት በሚገባ ተረድቻለሁ ትላለህ? የፀሐፊውን መልእክት ለመረዳት ምን አደረክ?
9. በአጠቃላይ ስለ ማንበብ ልምድህ እና የማንበብ ብልሃት አጠቃቀምህ የሚሰማህእና የምትነግረኝ ሐሳብ አለ?

በዋናው ጥናት ተሻሽለው የቀረቡ

1. ለማንበብ ተግባር የቀረበውን ምንባብ አንብበህ ተረዳህ ?ግለፅ።
2. የቀረበውን ምንባብ አንብበህ ለመረዳት ተቸገርክ ለምን?
   ያጋጠመህን ችግር ለማስወገድ ምን አደረክ? ግለፅ።
3. በአማርኛ ቋንቋ ስታነብ ሶማልኛ ቋንቋ ይጠቅመኛል ብለህ ታስባለህ/ በሶማልኛ ቋንቋ ስታነብ አማርኛ ቋንቋ ይጠቅመኛል ብለህ ታስባለህ? ለምን?
4. ለማንበብ ተግባር የቀረበውን ምንባብ አንብቦ ለመረዳት ከሶማልኛ ወደአማርኛ / ከአማርኛወደሶማልኛ የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገርክ ተጠቀምክ?
5. የቀረበውን ፅሁፍ አንብቦ ለመረዳት ምን ምን የማንበብ ብልሃቶችን እያሸጋገርክ ተጠቀምክ?
6. በበአማርኛ/ ሶማልኛ ቋንቋ የቀረበውን ምንባብ አንብቦ ለመረዳት የበለጠ ጠቅሞኛል የምትለውን የማንበብ ብልሃት ግለፅ።

በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሶ መናገር ቃለመጠይቅ (ለሙከራ ቡድን)(ከቃለመጠይቁ አስቀድሞ ለመረጃ ሰጪ ተማሪዎች የሚታደል)

ቀን_____

የዚህ መጠይቅ አላማ አንተ ተማሪ ወገኔ በአማርኛ ቋንቋ በምታነብበት ወቅት የምትጠቀምበትን የማንበብ ብልሃት ምን እንደሚመስል መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡

ተግባር አንድ

አቅጣጫ፡- የተሰጠህን ምንባብ በሚገባ አንብብ፡፡ ምንባቡን በምታነብበት ወቅት የሚከተሉትን ተግባራት አከናውን፡-

- ምንባቡን ሁል ጊዜ እንደምታነበው/ቢውፍውም በነፃነት አንብብ፡፡ ከፈለክድምፅህን በተወሰነ መጠን ከፍ አድርገህ ማንበብ ትችላለህ፡፡
- ማንበብህን/ሽን ትቀጥላለህ፡፡
- በምታነብበት ወቅት ማንበብህን ካቋረጥክ ለምን እንዳቋረጥክበመጠይቁ ወቅት ትናገራለህ፡፡

  ለምሳሌ፡- እዚህ ሐሰብ አካባብ ለምን አቆምኩ? አልገባኝም ማለት ነው? እንደገና ተመልሼ አነባለሁ ወዘተ ትላለህ፡፡ይህም ለምን እንዳቆምክ እና የተጠቀምክበትን ዘዴ ለማየት ያግዛል፡፡
- በምታነብበት ጊዜ ማስታወሻ እየያዝክ ብታነብ በመጠይቁ ወቅት ጠቃሚሀሳቦችን እያስታወስክ ለመናገር አትቸገርም፡፡
- በእያንዳንዱ አንቀፅ ያለውን ሐሳብ ለመረዳት የቻልክበትንመንገድ ድምፅህንከፍአድርገህ ትገልፃለህ፡፡ በዚህ ወቅት የተጠቀምክበትን የማንበብ ብልሃት ትናገራለህ፡፡ ብልሃት ካልተጠቀምክ/ሽም ይህንኑ አስረዳ፡፡
- የምትሰጠው መረጃ እጅግ ጠቃሚ ስለሆነ ክንውኑን በጥንቃቄ ተግብር፡፡

ተግባር ሁለት

አቅጣጫ፡- የቀረበውን ፅሁፍ ለማንበብ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት የትኞቹን ተጠቀምክ/ሽ ? (ተጠያቂው ተማሪ የጠቀሰውን ብልሃት ተጠቅሚያለሁ ካለ መጠይቅ አቅራቢው ይህን ምልክት [✓] ያደርጋል፡፡ ተጠያቂው ተማሪ አልተጠቀምኩም ካለ ደግሞ [x] ይህን ምልክት አልተጠቀምኩም ማለትን ያንፀባርቃል፡፡ ጥያቄዎቹ በቃል የሚቀርቡ ናቸው፡፡

ዝርዝር

1. በማንበብ መተንበይ [ ]
2. .ማቀድ [ ]
3. ዋናውን ሀሳብ በፍጥነት ማግኘት [ ]
4. መረጃ ፈልፍሎ ማውጣት [ ]
5. ማስታወሻ መያዝ [ ]
6. ደግሞ(ደጋግሞ)ማንበብ [ ]
7. ዋናውን ሀሳብ በራስ መንገድ አሳጥሮ መፃፍ [ ]
8. ጥያቄ መጠየቅ [ ]
9. የቀደመ እውቀትን መጠቀም [ ]
10. ራስን እና አንብቦ መረዳትን መቆጣጠር [ ]
11. አውድ መጠቀም
12. መገመት [ ]
13. ራስን መገምገም [ ]
14. ማሸጋገር [ ]
15. ከሌሎች ጋር መተባበር [ ]
16. በአእምሮ ምስል መፍጠር [ ]

አባሪ አስር

ቅድመ እና ድህረልምምድ በነፃ ማሰብ ያሰቡትን ማንፀባረቅ እና ያለፈን ነገር አስታውሰ መናገር ቃለመጠይቅ የተዘጋጀ ምንባብ (በሶማልኛ ቋንቋ የማንበብ ብልሃት ትምህርቱን ለተከታተሉ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች /ሙከራ ቡድን ሁለት የቀረበ)

ግብር

በሀገራችን ብዙውን ጊዜ ግብርን እንደ ዕዳ የመመልከት አዝማሚያ በስፋት ሲንፀባረቅ ይታያል። በእርግጥ መንግሥታዊ ገቢን የማመንጨት ሕጋዊ ስልጣን ለረዥም ዘመናት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ምክንያት ግብርን መክፈል ከውዴታ አስተዋጽኦነቱ ይልቅ የግዴታ ይዘቱ አመዝኖ እንዲታይ እንዳደረገው እሙን ነው። ይሁንና የዘመናዊ አስተዳደር ዴሞክራሲያዊ አሠራር በተሟላ መልኩ ከተከሰተበት ዘመን ወዲህ ግን ይኸው ሥልጣኔ ኤኮኖሚን ለማረጋጋት፣ የተፋጠነ የኢኮኖሚ እድገትን ለማስገኘት፣ እንዲሁም የዜጎች የኑሮ ሁኔታ ትርጉም ባለው መልኩ ለማሻሻል እንደ ዓይነተኛ መሳሪያ ሆኖ ሊያገልገል የሚችል መንግስታዊ ሥልጣን መሆኑን በተጨባጭ ለማስመስከር በመብቃቱ በአሁኑ ወቅት በበርካታ ሀገራት ዜጎች ዘንድ ግብርን መክፈል እንደ ዋነኛ የዜግነት መብት ማረጋገጫ እየተወሰደ ይገኛል። በዚህም የተነሳ በልማት በገፉ ሀገሮች ግብርን በወቅቱ እያሳወቁ አለመክፈል በተሰማሩበት የሥራ ዘርፍ በሕግ መጠየቅ እንደተጠበቀ ሆኖ መልካም ስምን ጨርሶ እስከማሳጣት የሚያደርስ አስነዋሪ ድርጊት ተደርጎ እየተወሰደ ነው። በተቃራኒው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገራችን የሚነበበው አዝማሚያ ግን ከዚሁ ዘመናዊ አመለካከት በተፃራሪ የቆመ ነው። በመሆም የግብርን ግዴታ አለመወጣት የማንነትንና የዜግነት መለያን ጨርሶ እንደሚያሳጣ አሉታዊ ሥነ ምግባር ከመታየት ይልቅ የጀግና ስም የሚያጎናጽፍ ዓይነት ሆኖ እሚታይበት ደረጃ ላይ ደርሷል። እርግጥ ነው ይህ አመለካከት ቀደም ሲል በሀገራችን ሲነገር ከቆየው "ከሞት እና ከመንግስት ግብር የሚያመልጥ የለም" አባባል አኳያ ሲነጻጸር አዝማሚው የቅርብ ጊዜ ክስተት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

ስለሆነም ይህ ለረዥም ዘመናት ተይዞ የዘለቀው ግዙፍ የተከበረ ማህበራዊ እሴት ከመቼውም በበለጠ ሁኔታ አብቦ እና ጠንክሮ የሚቀጥልበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል። በተለይም የዛሬው ትውልድ በቴክኖሎጂም፣ በትምህርትም ሆነ በስልጣኔ ከቀደምቱ በእጅጉ የላቀ ደረጃ ላይ ስለሚገኝ ይህን ባህል በይበልጥ በማዳበር ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲደርግ ይበቃል።

እንደሚታወቀው የተያያዝነው ክፍለ ዘመን ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር እድገትና የሕብረተሰብ ፍላጎት እመርታ የተመዘገበበት ዘመን ነው። መንግስት ደግሞ እነኝህን ክስተቶች ግምት ውስጥ የሚያስገባ የልማት ስልት እየነደፈ በኢኮኖሚ የጠነከረች ሀገር የመፍጠር ኃላፊነት እና ግዴታ ተጥሎበታል። ይህን ከባድ ኃላፊነትና ግዴታ በብቃት እንዲወጣ እስከተፈለገ ድረስ ደግሞ የሚኖረው አማራጭ አስተማማኝ የገቢ ምንጭ እንዲኖረው የሚስችለውን ሕጋዊ ሥልጣን በሚገባ አመላክቶ መስጠት ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ከተገኙት እና አስተማማኝነታቸውና ቀጣይነታቸው ከተረጋገጠላቸው መንግስታዊ የገቢ ምንጮች መካከል ግብር፣ ታክስ፣ የአገልግሎትና የመጠቀሚያ ክፍያዎች ዓይነተኞቹ ናቸው። እነኝህ ገቢዎች በበኩላቸው ከሕዝብ ተሰብስበው ተመልሰው ለሀገርና ለሕዝብ ጥቅም የሚውሉ በመሆቸው ማንኛውም ዜጋ የእርሱነቱ ዓይተኛ መለክያዎች መሆናቸው በውል ተገንዝቦ አዎንታዊ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል። በእርግጥ በየትም ማህበረሰብ ሊከሰት እንደሚችለው ያልተጠበቀ የሥነ-ምግባር ዝቅጠት ሲያጋጥም ግብርን በወቅቱ ወይም ተገቢውን የግብር መጠን ላለመክፈል የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀምና አጭበርብሮ ማለፍ እንደ ብልህነት መስሎ የሚታያቸው ወገኖች እንደማይጠፉ በግልጽ የሚታወቅ ሀቅ ነው። ይህ ማለት ግን ግብርን ያለመክፈል ግዴታ ያለመወጣት አዝማሚያ ከማጭበርበር ፍላጎት ጋር ሙሉ በሙሉ የተቆራኘ የመላ ዜጎች ወይም የሕብረተሰብ ባህርይ ነው ማለት አይቻልም። እንዲያውም በአንዳንድ መልኩ አዝማሚያው ግብርን ካለመክፈል ፍላጎት ጋር ከማያያዝ ይልቅ ሕጉን ካለማወቅ የመነጨ ሊሆን እንደሚችል መገመቱ የተሻለ ነው። ሕጉን አለማወቅ በራሱ ከተጠያቂነት የማያድን ሕጋዊ መርህ መሆኑ ቢታወቅም ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ሲገመገም ግን በርካታዎቹ ደንበኞች የግብርን ግዴታ በወቅቱ የማይወጡት ግብርን በሚመለከት የወጡ ሕጎችን ጠንቅቀው ባለማወቃቸው እንደሆነ ይታመናል። ይህን ክፍተት ደግሞ በራሳቸው ይወጡት ተብለው መታለፍ የሚኖርበት አይደለም። በርግጥ የሕጉን ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ ሲባል ብቻ ሕብረተሰብን በቅጣት መልክ ለማስተማር መጣሩ የተወሰነ ውጤት ሊያስከትል ይችል ይሆናል። ውጤቱ ግን በመንግስትና በዜጎች መካከል መተማመንን ከመፍጠር እና የልማት ሽርክናቸውን ይበልጥ ከማጠናከር ይልቅ መራራቅን እና አለመተማመንን ሊያስከትል ይችላል። በመሆኑም ተመራጩ አቀራረብ በዚህ መደብ የሚፈረጁትን ብዙሃን ግብር ከፋዮች ወደ ግብሩ መረብ ለማምጣት በቀጣይነት ለማስተማር እና ለማሳወቅ መጣር ነው። ሕብረተሰቡም በበኩሉ በየጊዜው በመገናኛ ብዙሃን እና በሌሎች መንገዶች የሚተላለፉ የግብር መልእክቶችን ትኩረት በመስጠት የመከታተል ባህል ሊያዳብር ይገባል።

ምንጭ፡-በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፤ ገቢዎች ኤጀንሲ 1996ዓ.ም

አባሪ አስራ አንድ

የማንበብ ብልሃት ለሚያስተምር መምህር በሶማልኛ ቋንቋ የተዘጋጀ የስልጠና መመርያ

Tababar Ku Saabsan Awooda Akhrinta Ee Baraha (barayaasha) Loosoojeedinayo

Qaybta 1aad (koobad)

Hordhac

Darasadan jamacada Adis Ababa hiwmanitu qaybta luuqada waryell iyo kuliyada fookloor luuqada amhariga iyo qaybita faklarka luuqadaha itoobiya barista luuqadaha doktaratka diyaarinta darasadan ayay ku saabsan tahay ciwaanka daraa sadan.Awooda akhrinta ee cad (Explicity) awood barida fahanka iyo akhrinta deeganka soomalida ee magalada Jigjiga fasalka 9aad ardayda afka hooyo ayu ku saabsanyanay .

Ujeedada awooda akhrinta oo uga talagalay darasada hore iyo luqabsashada danbe oo ah mid itixaamed (quasi experment).

Soo uririnta tijaaboyinka silo qayib qaato laboo kooxad tijaabeyn iyo koox fircoon iyaladiyaarin midi waa kooxda afsoomaliga talia badna af Amharic aya awood da akhrinta labiyo toban todoobta (sideed sac) cashirka la bixindoona.

Teermki hore dabaca ay ku qaateen luuqada soomaliga iyo amhariga sidaas ayaloogu wadi doona luuqad kasta kala gooni inay kooxdu u awoodan akhrinta.

Cashirkalabixinayo in uu ahaado mid wax soo saar leh waa in baruhu sicad u fikiro (islamarka uu hadtayo fikiro).

(teacher think aloud) garasiada barasho cashir luuqad soo jeedin (cognitive acadamic language learning approach/ caala)iyo iscaawin (scaffelding) iskudibur ka nooyana hawl galin.

Arimaha uu tababarku raacayo tababarkan baraha ku saabsan sadex qoodabood oo waa wieyn oo faa'faahin leh ayu wataa qaybta hore waa hordhac waan waana mid kahadlaysa waraaq loo qoray baraha kooxaha tijabinta iyo wakhtiga uu baruhu taharka bixinayo.

Qaybta Labaad 2aad Awooda akhrintax faoodaada iyo argtida ayu ku saleeyan yahay baraha tababarkan qaadanaya aya fahmi dabee cadaha awooda akharinta tanina waxa ardayda u dhibyareeyn marka uu baruhu tababarkan kadib hawlgalin ku saabsan awooda adurinka in ay ardaydu ka soobaxaan oo ay dadaalan akhrinta qooralada fahan siin soona.

Qaybta Sadeexad 3aadQaybtani waa habka barista khibrada akhriska dadagal ka ayay dusmo u tahay taanina kooxada tijajabad marka cashirka loo bandhigo aya baraha tusmo u tahay.

1.1. Warqad loo qoray kadib soojeedito darasadan marka oo ka qaybqaatay tababarka baraha ardayda baraya awooda akhriska.
Mudane Bare.

Markeen horeysa waxa loo mahad naqaya baraha sharaftaleh ee wakhtigisa iyo aqoontisa ka qayib galiyay hawshan tababarku madama uu door weynka qatay.

Ujeedo darsadan waxay tahay khibrada akhriska iyo fahanka in ay ardaydu si tahadir leh ka qaybiqaatan oo ay hawshan akhrirta baruhu masuleyad weey in uu saaxan yahay waan uu ogaado.

Madaama uu tababaarkani yahay qaybiti hameed hawsha laba koox oo tijaba ah iyo koox kale oo firfircon ayu yeelan kara.

Labada koox ee tijabooyin ku midi waa (9aad B) khibrada akhrintaa kooxda labaadna (9aad T) labiyo tobeen todoobad oo isku xigta (sideed sacdood) aya lasin (labiyo toban kun todoobaadka hore loo isticmali doona itixamo baraha ayna loo diyariyay.

Horumarkan tababarka aqoonyamin kala duwan (tailbi 2012-2013 mcnamara 2007 traceyand morrow 2006 tankersley 2005 naue hard 2005 oxford 1990 omalley and chamot 1990 waxay soo bardigan tixracooda mahaasad.

1.2 Foormka Heghiiska

